# መራራ እውነት

## በኢትዮጵያ ታሪክ



ታየ ቦጋለ አረጋ (ኢ.ሕ.መ ደሱ ኦዳ)

t.me/OLDBOOKSPDF

Biruktawit Getachew
from Getachew Abate

# መራራ እውነት

(በኢትዮጵያ ታሪክ)

ታየ ቦጋለ አረጋ

(ኢልመ ደሱ ኦዳ)

ዐዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

t.me/OLDBOOKSPDF

# ማውጫ

ይዘቶች ገፅ

ማውጫ.................................3
መራራ እውነት.................................6
መቅድም...............
0
ምስጋና.................................24
መግቢያ.................
.....26
ምዕራፍ ንድ.................................34
የኢትዮ ታሪክ አጻጻፍ ጥናት (Historiography).........34
ታሪ ንድነው?.................................35
የኢ ያ ታሪክ ምንጮች (ማስረጃዎች እና መረጃዎች) ......66
ያ ዘመናዊ ታሪክ አጻጻፍ አጀማመር ......119
ያ ታሪክ ጸሐፍት ተቃርኖ ......123
ሰት.................................156
ሪካችን ሰበዞች.................................156
ታሪክ ......157
......160

t.me/OLDBOOKSPDF

ሆሄያት / ፊደላት እና አኃዞች ........ 161
የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ........ 165
ዋቂፈና፣ ክርስትና እና እስልምና ........ 169
የገዳ ሥርዓት (የዴሞክራሲ ውኃ ልክ) ........ 191
ካሌንደር / የዘመን መቁጠሪያ ........ 208
የዘመናዊ ታሪካችን ፈርጦች ........ 212
ምዕራፍ ሦስት........ 277
'ዘመን ዕልመት (1991 - 2018)........ 277
ምዕራፍ ዐራት........ 318
መራራ እውነትን ፍለጋ. :........ 318
ታሪካችን የተናጠል የየአንዳንዱ ጎሳ፣ የየብሔረሰቡ ወይስ የጋራ? ........ 326
ኃይል ሲጠቀም የኖረው ማነው? ........ 330
የስንት ዘመን ታሪክ? ........ 338
የኦሮሞ መነሻ (ምንጭ) ከየት ነበር? ........ 342
የሸዋ ፖለቲካ፣ ዐዲስ አበባ እና የታሪክ ውዝግብ ........ 356
ከፋው ገፃችን ........ 359
የዐዲስ አበባ ጉዳይ እንዴት ይታያል? ........ 361
የዐማራው ገበር መደብ ትርክት ........ 365
የኤርትራ እና የአሰብ ወደብ ጉዳይ ........ 373
ሕገ መንግሥት/ 'ሕገ አራዊት':- ........ 386
ማጠቃለያ........ 397
መውጫ........ 402
ዋቢ መጻሕፍት (References)........ 405



t.me/OLDBOOKSPDF

'በጢያራ አዳፍኔ እና ሙትረየስ በሚካሄድ ዐውደ ውጊያ ውስጥ

ጩቤ ይዘህ አትሰለፍ'

ለዛሬውም ሆነ ለሚመጡ የኢትዮጵያ ትውልዶች

የታሪክ ዐይን ጥላ መፍትሔ ሥራይ እንዳኖር የፈቀደልኝ ፈጣሪ ይመስገን።



t.me/OLDBOOKSPDF

# መራራ እውነት

## እውነት ትመርራለችን?

በመጽሐፉ አዘገጃጀት ውስጥ ከተለመዱ የአጻጻፍ ዘይቤዎች ወጣ ያሉ አገላለፆች በአመክንዮ ላይ ተመሥርተን ተጠቅመናል። ከእነዚህም መሀከል የሚጠቀሱት፡- በመቅድሙ፣ መግቢያው እና ከመቅድሙ በፊት የርዕሱ ማብራሪያ በዚህ ገፅ መከተሉ፤ ቃላት ለሥነ ጽሑፋዊ ውበት ትኩረት ሠጥተን የምዕራፍ አንድ መነሻ ላይ ጠጠር ባሉ ቋንቋ ማቅረባችን፤ ታሪክን ሊሎቹን ይዘቶች እንባቢው እንዲገነዘባቸው በቀላል (History) እና የታሪክ አፃፃፍ ጥናት (Historiography) አጣምረን ማቅረባችን፤ በኢትዮጵያ ታሪክ አፃፃፍ ውስጥ የተስተዋሉ ህፀፆችን ማመላከት ብቻ ሳይሆን መፍትሔያቸውን ጎን ለጎን እያሳየን መሄዳችን፤ አሰልቺ በሆነ ግትር አቀራረብ ታከቶ አንባቢው ከጉዞው እንዳይናጠብ ለማራኪነቱ ሲባል ከተለመዱት የታሪክ አፃፃፍ ዝንባሌዎች ጠርዎሰን መውጣታችን፤ አብዛኛውን ተደራሲ ባገናዘበ መልክ የማስታወሻ (Notes) እና ገፅ የሚሻሙ የግርጌ ማስታወሻዎችን አስቀርተን የበዛ ግልዕነት ለመፍጠር ምንጮቹን አስፈላጊ በሆኑ ሥፍራዎች ሁሉ ለፀሐፊዎቹ የትምህርት ማዕረግ ሳይቀር ትኩረት ሰጥተን መፃፋችን (የፀሐፊዎቹን የመጨረሻ የትምህርት እርከን ያላወቅን ሆኖ ሲገኝ በማለፋችን ይቅርታ እንጠይቃለን)፤ ታሪኮቹ በሚገባ የሚታወቁና ከበይነመረቦች ጭምር በቀላሉ የሚገኙ መሆናቸውን ስናምን ምንጭ ሳንጠቅስ አብራርተን (ጠለቅ ብለው መረዳት ለሚሹ በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆኑ በሚያስችል አግባብ መረጃዎቹን በእንግሊዝኛ ጭምር ማስቀመጣችን ናቸው።)

እውነት፡- መዓዛዋ የሚያውድ፣ ጣዕሟ እንደ ወይን ጭማቂ ፍስሐ የሚያቀዳጅ፣ ለነሲና የማትቆረቁር ምቹ ትራስ ናት። በሲራ ፖለቲከኞች ሸንጎ ሰይፏን ከሰገባዋ መዝዛ ስትከሰት፡- የተንኮልን ምሽግ የምትንድ፤ የቅጥፈትን ካባ የምትገላልጥ፤ በሸፍጥ የተተበተበ ድርን የምትበጣጥስ፤ በአሸዋ መሠረት ላይ የተገነባውን መሠረ ፖለቲካ የምትደረምስ፤ የፖለቲካ ቡከኖችን ዕርቃን አስቀርታ ምታርበደብድ፤ በተንኮላቸው ፍርሀት ቆፈን የሚንዘፈዘፉ 'ካድሬዎችን' የምታበረክርክ፤ ለሆድ አደሮችና በቀቀኖች የምትጎረብጥ፤ የታሪክ መጋኛ ላጠናፈራቸው የቡዳ መድህኒት፤ ለቁሳሮች፣ አልፍኝ



t.me/OLDBOOKSPDF

እስክልካዮቻቸው፣ አጋፋሪ፣ አበጋዝ፣ ምስለኔ፣ ተጠሪ፣ ጭቃ ሹም፣ እረ. ቀላጢ እና ሺህ ምንተሺህ ነጭ ለባሽ ጋሻ ጃግሬዎቻቸውና ኮልኮሌ ጀሌዎቻቸው የማትመች፤ ... ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች ቢሰለፉ፣ ባዙቃና ነፋሪዮች የነጎድጓድ ያህል ቢያስገመግሙ፤ አውዳሚ መሣሪያዎች በአፈሙዛቸው አረሮቻቸውን ቢቀስቱ፤ ላንቃቸው እንደ አዞ አፍ ቢከፈት፣ ምድር በከፋት ቀውጢ ብትሆን፤ መረመሩ በደም ቢጎርፍ ... በፍፃሜው ጦርነት ሀቅ ከሰገባዋ ሰይፏን መዝዛ ብቅ ስትል፦ መልአከ ሞት ይንበረከካል፤ ኩሸቶች በፍርሀትና ረአድ እግራቸው ቁጠማ ዐይናቸው ጨለማ ይሆናል። ሀቅ በእንግሩ በፍፁም የራስ መተማመን መንፈስ የዘመናት ትውስቷንና ትዝብቷን አጠራቅማ ፈርዖኖችን ሰገነቱ ጫፍ ላይ ቆማ ቁልቁል ትገረምማቸዋለች።

እምባገነኖች የተራራ ያህል ቅጥፈትን የቁልል ደመና ያህል አግዝፈው ቢከምሩ፤ በጠሸት ላይ እብለትን እንደ ዝተት ቢያነጥፉ፤ የቁሳሮች ጡንቻ ፈርጥሞ ቢደድር፤ ሊጋባዎቻቸው የአቦ ሸማኔ ያህል ፈረሶቻቸውን ቢሰግሩ፤ አጃቢዎቻቸው እንደ እራስ ነብር በሚንተለተሉና ደም በሚተፉ ዐይኖቻቸው እየተወራጩ ቢቅበዘበዙ፤ ጠያራዎቻቸው ሰማያትን እንደ ንሥር በአክናፎቻቸው እያሰነጠቁ ቢቀዝፉ፤ ለዐይን እንደ መብረቅ አጥበርብረው በአስደንጋጭ ነጎድጓድ ታጅበው ቢያስገመግሙ፤ ጣዕረ ሞት ጥርሱን እያፋጨ አለቅጥ ቢያንገራግጭ፤ ጎልያድ ጥሩር ለብሶ፣ በጋሻው ሊመከት፣ በጎራዴው ቀልቶ በደም አበላ ሊያጠምቅ እየፎገላ እንደ ገመሬ ዝንጀሮ ጎፈሩን ነስንሶ ቢንጎማለል... እውነት በዳዊት ትንሽ ምጡቅ አእምሮ ውስጥ ጎልቶ መሣፍርት አውታሮች በእልፍ አእላፍ ወትእልፊተ አእላፋት ደቂቅ ህዋሶች ባስተሳሰረ ህሊና የጎልያድ መተለቅ ሳያገብራት ይልቁኑ ግዝፈቱ ለወንጭፏ ጠጠር የዒላማ አመቺነት ያለው መልካም አጋጣሚ ላይ ታነጣጥራለች። ዒላማዋ ለስኬት እንደሚበቃ ስታምን ከትንሽ ተራራ ልብ ውስጥ ደቃቅ ጠጠር ተስፈንጥራ በጉግ ማንጉግ የራስ ቅሉ ትቀበቀባለች። ቁንጠጦው ላይ ቆሞ በአሸናፊነት ትዕቢት ተወጥሮ ሲጀነን አውገርምዥርማና አፍገምግማ ትገረስሰዋለች። ዙሪያቸውን የከበቧቸው 'የአህያ ባሎች' ላያስጥሏቸው፣ 'የፍየል ጭራዎች' ገመናቸውን ላይሸፍኑላቸው እርቃን ስለሚቀሩ ባፍጢማቸው ይወድቃሉ።

ቦረና ሲተርት፦

'ቅጥፈት ምሽት ላይ አለቅጥ ወፍራ ሲነጋ እጅግ የምትመነምን ሲሆን፤ እውነት አመሻሽ ላይ ብትከሳም ንጋት ላይ ወዟ ጢም ብሎ ታወደውዳለች' ሲል በዘመናት የተባ የአስተዋይነት ፍተሻው ተመርኩዞ የሐቅን አሸናፊነት ያስረግጥልናል።

እውነት ከአፈጣጠሯ አኳያ ጣፋጭ እንጂ መራር አይደለችም። እንደ ማር ወለላ ብትጥም እንጂ እንደ ሀሞት አፍን በምሬት አትሞላም። እንደ መተሬ አታንገሽግሽም። እንደ እንቶቶ ለኋለኛው የምላስ ክፍል የመንገግዘዝ ባሕርይ የላትም። በተቃራኒው የአውር ድንብራቸውን የቅጥፈት ምናባዊ ዓለም ፈጥረው በራሳቸው የክህደት ዛቢያ ለሚሾሩ ከንቱዎች ምሬቷ ከሬት ልግ በላይ አይሎ ሲቋቋሚት ይሰናቸዋል።

የጥበብ ኮሶ፦ ግጥም አድርገው ያለማቅማማት ለሚጨልጧት ከተጣባቸው ተውሳክ ፍቱን መድሀኒት ሆና ታሽራቸዋለች። በከፊል ለሚቀምሷት በግማሽ ልብ ትኩስ ወይም በሩድነትን በመወሰን መሀከል በመዋለላቸው ሳቢያ እንደአዳም ዕፀ - በለስ ከጉሮሯቸው ባለመውረድ ተሰንቅራ 'በልተፋህ ነው' ስሜት ታጥወለውላቸዋለች። ተጉመጥምጠው ለሚተፏት ደግሞ አብዝተው በገፏት ልክ የርግማን መአት ከፊትለፊታቸው ትደቅናለች። እጣ ፈንታቸውም እንደ ፀጉራም ውሻ እሱ ሲባሉ በአመንንም ተቀጥተው፤ ነቀዝ እንደበላው ሰብል ቀልለው፤ ምስጥ እንዳነከተው ዛፍ ተቦርቡረው፤ ስብዕናቸው ተሸርሽሮ ደቅቀው፤ ውጪያቸው የቱንም ያህል ያማረ ቢመስል ውስጣቸው የሸረሪት ድር ያህል እስቀይሞ፤ ማር የሊሰበት ቀፏቸው በገጋ ተሞልቶ፤ እንደ ባቢሎን ግንብ ያቆሙት የከፋት መንጠራራት ባለመደግመጥ ተገትቶ፤ ግዙፍ የመሠለ ውጥናቸው ቀንጭሮ፤ ከነከፋታቸው በአጓጉል አወዳደቅ ተንኳኩተውና ተንኮታኩተው፤ ግብአተ መሬታቸው ወደ ጥልቁ እንጦርጦስ፤ እመቀ አመቃት ይወርዳል።

አምባገነኖች ካለፈው አይማሩም። የኢራቁ ሳዳም ሁሴን ከተሸጎጠበት ጥግ እንደ ውሻ ከብሩ ረከሶ፤ ተጎትቶ፤ በአደባባይ ተሰቅሎ ምላሱ ሲጎለጎል፤ ዐላይም፤ አልሰማም፤ አልማርም ያለው የሊቢያው መአመር ቃዳፊ በተራው በራሱ ወታደር ቱቦ ውስጥ ተገድሎ እስከሬኑ እንደ አልባሌ ሲጎተት የግብፅ ሙርሲ ካላገጠ፤ የሱዳኑ አልበሺር ወድቆ ሲታይ ካሽሟጠጠ፤ ባለሳምንቱም 'ንፍር ውሀ አንገቱ ድረስ እስምጦትም ጭምር 'የአበራሽን ጠባሳ ዕያየ በእሳት ከተጫወተ'፤ 'ንጉሥ በሠራዊቱ ብዛት አይድንም' ዘንግቶ ምሽግ መቆፈር፤ የሽቦ አጥር መደርደር፤ ጠባቂውን ማጠናከርን ከመረጠ፤ እንደ ኢያሪኮ ግንብ አንድ ቀን በህዝብ ብሶት የውስጥ ጩኸት ይፈርሳል። 'መንግሥት የሾላ ፍሬ አይደለም' አይነት ትዕቢት ውሎ አድሮ የፀፀትን ዋጋ ያስከፍላል።

እንደ እሳት እራት ስሜቱን ያቀዘቀዘ መስሎት ከእጥፊው ጋር ሲራኮብ ተጠብሶ ያከትማል። በሰራ ፖለቲካ ከዘቀጠ ከድጡ ወደ ማጡ ወርዶ ጥልቅ አረንቋ ውስጥ ይቀበራል። ብልህ መሪ የሠለጠነው ዓለም እንደምን ከዚህ አዙሪት እንደተላቀቀ ይመረምራል። ሰጥቶ የመቀበል የአርታ - ልርታ (Win - Win) ወርቃማ መንገድ እጅ



t.me/OLDBOOKSPDF

ለአጅ ተያይዞ በጋራ መመንደግ መሆኑን ያስተምሩናል። የአፍሪካ የጎንዮሽ እርግጫ ፖለቲካ አሸናፊ አልባ ሆኖ ምድራቱን አኬልዳማ እንዳደረጋት ተገንዝቦ ሁሌጊዜም የተሻለውን ይመርጣል።

በመራራ እውነት የጨዋታ ህግ ጡብጡብ ላልቶ የሚተገበር ቁልፍ የቃል ቅኔ አለ። አንድም የምሬቱ መጠን እያ የማይገኙለትን የሆነ ምሬት እንቅፋ በድፍረት ጨልጦ ከተጣባው ኮሶ 'የመሻር'፤ አንድም የእንድምታውን የመድሀኒት ብልታ ግፍቶ ውሻትን ወንዞ በሾተላይ ጨንግፎ 'የመሻር'። ጊዜ በንዑሳን ደቃቆች የተከፋፈለ፤ ከዐይን ጥቅሻ ፈጥኖ በብርሃን ፍጥነት የሚወነጨፍ፤ ያለፈው ላይመለስ፣ የደረሰው ላይቆም፣ የሚከተለው ላይገታ፣ እንደ ጅረት እየተከታተለ የሚያምዘገዝግ 'አባክህ አንድ ጊዜ' ብለን የማናስቆመው ንብሬ ነው። በዚህ ግስጋሴ ሁለት ምህረት የለሽ አማራጮች ከፊትለፊታችን ተደቅነዋል። አንድም ፈረሳችን ላይ በፍጥነት በመፈናጠጥ ሽምጥ በመጋለብ ስግረን ከወቅት መሰናንት፣ አንድም ከተራራው ጫፍ እየተንከባለለ የሚያምዘገዝገውን ቋጥኝ ለማምለጥ በወጉ ሳይሰናዱ ጉዞን ቀንሶ ተንቀርፍፎ በማይገታው ናዳ መጨፍለቅ።

የጊዜ ምስጢር የገባቸው 'In the game of life there is no timeout, the clock is always ticking' ይላሉ። ጊዜ በገንዘብ የሚሸመት ወርቅ ሳይሆን ካለፈ የማይገኝ ህይወት ነውና ዋጋውን በአግባቡ ተምኖ 'ላምጪው እንዲከፈል ህግ ያስገድዳል' እንዲል በብልህነት ልንጠቀምበት ይገባል። ለመሆኑ 'Payable to the bearer on demand' በኢትዮጵያ የወረቀት ገንዘብ 'ኖት' የሠፈረው መሪ ቃል 'አዳም ሆይ በወዝህ ጥረህ ግረህ ብላ' ከሚለው የምርቃት እርግማን ጋር መዛመዱን ስንቶቻችን አስተውለናል? አገልግሎት ሰጪው መልስ የመስጠት ግዴታ እንደተጣለበትስ? ለተፈጠርንበት ዓላማ ለመኖር ዕውቀትን ከጥበብ አሰናስለን፣ የወገንን ሀብት ሳንሰርቅ በላባችን ብቻ መብላት እንዳለብን የቱን ያህል ተገንዝበናል? የሀገር ሀቅ መዝረፍ ትርፉ ስኳር ግፊት ስጋት ቀውስ ዞበጥያ መውረድ ወዘተርፈ ነው። 'የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው'ና ለእውነት እንኑር!

ቃየ ቦጋለ አረጋ፣ ኢልሞ ደሱ አዳ



t.me/OLDBOOKSPDF

# መቅድም

ኢትዮጵያ፡- በዘመናት የዘር ሐረግ አወራረስና የትውልድ ቅደም ተከተል መሠረት፡- ውላጅ፣ ፍናጅ፣ ቅናጅ፣ አመለጥ፣ እሰለጥ፣ ማን ቢቱ፣ደረበ ቢቱ፣ ደረሰ ቢቱ፣ ድሮ-ቢቱ፣ ሸማት፣ ምንዝላት፣ እንዝላት፣ እንጅላት፣ ቅማንት፣ ቅምቅም አያት፣ ቅም አያት፣ ቅድመ አያት፣ አያት፣ አባት፣ ልጅ፣ የልጅ ልጅ... በቅብብሎሽ ሲወርድ ሲወራረድ (ሲዋረድ አይባልም፤ ምክንያቱም ወላጆቻችን ጮማ ቆርጠው፣ ሙዳ ስጋ ጎርሰው በማር ብርዝና በገብስ ጭማቂ ያወራርዱታል እንጂ አያዋርዱትምና። ደግሞም ታሪክ ይወራረዳል እንጂ አይዋረድም።) ሲያልፍ ሲተላለፍ እየተወራረሰ ከቀደመው ትውልድ ቀጣዩ እየተረከባት የተላለፈች የእንፀባራቂ ገድሎች ባለቤት የሆነች ሀገር ናት። ይህ ሲባል በታሪካዊ መገፋፋት ውስጥ የሁሉም አያቶች በተለያዩ ጊዜያት የተፈፀሙ በደሎች አካል መሆናቸው መዘንጋት የለበትም። ቁምነገሩ የግፊያውን ምክንያት በዘመን መነፅር በልኩ መዝኖ ለመማሪያነት እንዲያገለግል መጠቀሙና በየዘመናችን እንዳይደገም ማድረጉ ነው።

ኢትዮጵያ፡- የእኛነታችን መገለጫ፣ የስመ ጥር ተጋድሎዎች እምብርት፣ የሰው ልጅ መገኛ መሠረተ-ግንድ 'ምድረ-ቀደምት'፣ የዘመናት ሥልጣኔ ማማ፣ የጥቁር፣ ጠይም፣ የቀይ ዳማ፣ ቀይ (አበባ ቀለማት ውብት ህብር) ኩሻዊ፣ ሴማዊ፣ ኦሞቲክ፣ ቻራ-ናይል እና ኮማን መሠናኛ ምድር፤ የድንግል ተፈጥሮ ማህፀን፣ በማህበራዊ ህይወት በዓለም አደባባይ ከፍ ብሎ ሊነገርለት የሚገባ ትስስር ማህደር፣ የተባ እልፍ ባህሎች መሠናሠያ ቃኜ፣ እምነቶችን በፍቅር ተቀብላ አስተናግዳ፤ አማኞች ተከባብረው አንዱ የሌላኛውን አምልኮ ቤተ እምነት የሚያንፅባት አፀ-ብ ድንቅ ምድር፤ የብዝሀ ህይወት



t.me/OLDBOOKSPDF

አምባ፣ የመላው ዓለም ነፃነት ወዳድ ህዝቦች የትግል ተምሳሌት፣ ለጥቁር ህዝቦች ድል ፋና ወጊ አርአያ፣ የአፍሪካውያን መጠለያ ዋርካ፣ ቁመተ ረጅም ዝግባ፣ የኀልዮ መሣፍርት ቅርሶች ባለቤት፣ 'የ13 ወራት የፀሐይ ብርሀን ፀጋ' / '13 Months of Sunshine' መታያ፣ ከዓለም ቀደምት ሥልጣኔዎች ተርታ የተሰለፈች ብትሆንም አምቅና አጀብ የሚያሰኝ ታሪኳ የልእልና ሥፍራውን ጠብቆ በወጉ አልተሰነደም።

በየሰንዱቁ ተሰድረው የምናገኛቸው ጦማሮች ውስጣዊ ይዘታቸው ሲፈተሽ ሚዛን የሚያነሳው ከፍላቸው የተገፋበት ዓላማም ሆነ ያነጣጠሩበት ዒላማ (አንዳንዶቹ የየዘመናቸው አስተሳሰብ ውጤት መሆናቸው እንደተጠበቀና እንደተከበረ ሆኖ) ከውጤት አኳያ ሲሠፈሩ የሚከተሉት ህፀፆች አሊያም ፍላጎቶች ይስተዋሉባቸዋል። አንዳንዶቹ የነገሥታትን ክብር ማግዘፍ እንደ ግዴታ የተጣለባቸው፣ ሌሎቹ የእምነትን ዶግማና ቀኖና ለማፅናት ቀለም ተበጥብጦ ብራና ተፍቆ ለሀይማኖት ክብር የተደጎሱ፣ የተወሰኑት የፖለቲካዊ ሥርአቶችን ነዕሮተ-ዓለም አምልተውና አስፍተው ህዝብን ለመግዛት ጡንቻና ክንድ የነበሩ፣ ከቅርቦቹ መሀከል የአንድን ዘውግ አሊያም ቡድን የበላይነትና ፍላጎት ለማሳካት የተቀመሩና የተቆመሩ፣ ከውስጥ እስከ ውጭ ያሉ ጠላቶችን ፍላጎት ለማጅብና ለማርካት የተዘጋጁ፣ በዘመናት ታሪክ ፍቅር በተማረኩ ሰዎች የተፃፉ፣ ጥቂቶቹ የሙያውን ስነምግባር ተከትለው የተዘጋጁ ናቸው።

ከዚህ አኳያ አብዛኞቹ ዘውጎች የታሪክን ትምህርት ዓላማ ተልእኮ እና ግቦች እንዲሁም ጠቀሜታ ያላገናዘቡ እንደሆኑና የተጠመሩትም የታሪክን ትምህርት ታሳቢ አድርገው እንዳልሆነ መረዳት ፊትለፊት ያለ ግልብ ሰም እንጂ ከህብረ አምሳል ቅኔ ወርቅን የመፈለግ ያህል የሚከብድ አይደለም። በአንፃራዊ ዐተያይ የታሪክ ምሁራን ያቆዩልን መዛግብት ጭምር የውስጥ ገፆቻቸውን አገላብጠን ስናስስ ስቅል የሚያስንነብሰው ታሪክን ከፖለቲካ አሳከሮ ማሳበድ ነው። የታሪኩ አካታችነት ውስን መሆንም ጥያቄ የሚያስነሳ አለመሆኑ እሱ አይባልም።

በታሪካችን ዙሪያ ከ1970ዎቹ ጀምረው የተዘጋጁ ሰነዶች በሴራ ፖለቲካ እግር ተወርች ተቀፍድደዋል። ከታሪክ አልፋና ዖሜጋ ርቀው፣ ከመዳረሻ ግቡ በአያሌው አፈንግጠዋል። ትውልዱን በጥላቻ ጋሪ አፈናጥጠው ለመስገር በከፋት መርዝ ተለውሰዋል። የታሪክ ጠቀሜታ ስለራቃቸው ለሀገር ችግር መፍትሔ ከመሆን ይልቅ 'በአንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ' ተደራቢ ደዌዎች ሆነዋል። ተፅዕኖ ፈጣሪ ሆነው ልቀው የወጡት ግለሰቦች በታቀደ በተጠናና በተደራጀ ቡድን የሚደገፉና የሚመሩ መሆናቸው ደግሞ ትውልዱን የጥላቻ አዙሪት ውስጥ ዘፍቆታል።



t.me/OLDBOOKSPDF

የታሪክ ዐፅ ነጥሮ ወጥቶ በተሣለለት 'የማይታይ ጭራቅ'፤ ፊሰም የሚያገባውን አጠገቡ ሆኖ ኑሮውን ለማሸነፍ የሚውተረተረውን ወንድሙን በሌለ የበቀል ዐይን ይመለከተዋል። በትውልድ ተሸጋግሮ ያልመጣ በምናብ የተሳለለትን አመክንዮ አልባ 'ጥቁር ደም' ፍለጋ ይተጋል። ለምን የሌላ ብሔረሰብ አባል የሆነ ወንድሙን እንደሚጠላው ቢጠየቅ በርግጠኝነት ምላሽ የለውም። 'ጥላ' ተባለ ጠላ። 'የታሪክ ዕውቀቱ፡ ምኒልክ ጡት ቆረጡ' ብሎ ይጀምርና ሲጨርስም 'ምኒልክ ጡት ቆረጡ' ብሎ ይደመድማል። በሚገባ ታቅዶ፤ ተቀምሞ፤ ተበጥብጦ፤ ተበርዞ፤ ተቀንጥሶ፤ ተደልዞ፤ ተለንቅጦ፤ ተበላልቶ የተቀመመው መርዝ ያጣመመው፤ አቅጣጫ አልባ ግዙፍ ቁመና በዘመናት ውብ ኑባሬያችን ፊት እንደ ጅብራ ተገተረ። እንደ ጋሬጣ ተሰነቀረ። የአበው ወኢመውን የእምነት፣ የመንፈስ እና የስጋ ትስስር፤ የገመና ምስጢር፤ የአብሮነት ህብር፤ የመተሳሰብ ፍቅር ሽምጥጥ አድርጎ ከዶ፤ በፈጠራ ድርሳን የትውልዱን ህይወት እንደ ጨንጊት ጨምድዶ ተበተበው።

በየዘመናቸው መቼት፣ በጊዜው ዳራ መነፅር፤ በቦታ ልኬት ሥፍር ቢመዘኑ ክብር የሚገባቸው ወርቃማ የታሪክ ዕንቁ ሰነዶች እንደዋዛ በአሪያዎች ፊት ተጣሉ። የወጭ ፀሐፍት ከምር አፈር ዝቀው ግራም ወርቅ ማውጣትን ተክነው ተጠብበውበታል። የኛዎቹ የተገላቢጦሽ ከመፍትሔው ላይ ችግር ፍለጋ የሚንቀገፈገፉ መሆናቸው ገሀድ ወጥቷል። ከአፍሪካ ቀርቶ ከሌላው ዓለም ልህቀት የተጎናፀፉ የታሪክ አሻራ ሰበዞቻችንን አጉልተን አምልተንና አስፍተን በማሣየት ትውልዱ ከጥንካሬው እንዲማርና እንዲጎለብት፤ አፍ ከልብ አሰናኝተን፤ የአባቶቹን የተጋድሎ ፅናት እንደ ጃፓኖች 'ሳሙራይ' ባህል ለቴክኖሎጂ አልኸኝነት እንዲጠቀምበት ልናተጋው ሲገባ፤ በተቃራኒው ከዕጹ አሻራ የታሪክ ገፆቻችንን ከየመሀከሉ ገንጥለንና ቀድደን አውጥተን የጠቆረና የወየበ ሰንደዶ እየመዘዝን እንደምን ለጥላቻ ማዋል እንደምንችል በተንኮል ተካንንና ለእልቂት ጥናትና ምርምር ማድረግን ተያያዝነው። 'ወሬ ከፈታው ጦር የፈታው' እንዲሉ የታሪክ ጅምላ ጨራሽ መሣሪያ ማምረትን መተዳደሪያ አደረግነው።

በአጉል አባዜ ታሪክን ከማዛባትና መፍጠር ሴራ የተነሳ ዕጹ የታሪካችንን ገፆች የፖለቲካ ደባ አነወራቸው። በየዘመናቸው ሰነዶችን በዕሑፍ ከማኖር እኳያ በአወቀታቸው የተሻሉ ልሂቃን ያቆዩልንን መዛግብት እያሳደድንና እየለቀምን በእሳት እንዲጋዩ ፈረድንባቸው። ድንቅ ጠማሮቻችን ጥላቻ እንዳንገለጣቸው ሰውሮብን በየቤተመጻሕፍቱ፣ ቤተመዛግብቱ፣ ሙዚየሙ እና መደርደሪያዎች የዘመን ትዝብት ትቢያ ሸፈናቸው። አብዝተን ልናተርፍባቸው የሚገባ ድርሳናት ጥቀርሻ ጠገቡ። የሸረሪት ድር ተበተባቸው። እንደ እሮጌ ቁና ሲያውም ሳንገለገልባቸው በየሥርቻው

ተማሱ። ጨረቃ እየወጣባቸው ለየነጋዴው ተሸጠው የሻይ ቅጠል መጠቅለያ ሆኑ። የታሪካችንን ወርቃማ ገፆች የያዙ ጥራዞች በዘመቻ መልክ ደብዛቸው እንዲጠፋ ተደረገ።

በተሰጣቸው ምትክ የፈጠራ ድርሳናት ከፍተኛ መጥዕል ንዋይ ፈሰሰባቸው፤ ሀገር ለማዳን ይውል የነበረ ጊዜ ባከነ፤ ሀብት መከነ፤ እውቀት ለከፋት ውሎ፤ ሀገር ቆራርጦ ለመተራመት በመንጠራራት አባዜ የሚከተሉት ሁነቶች ግዘፉ። ከሶማሊ ምድር ሊሂቃን የአክራሪ ምኞት እስከ አዋሽ ጫፍ ቢሸፍቱ ድረስ ተንጠራራ። የኦሮሞ ሰንፈኛ የምንብ ተስፋፊዎች የመሬት መሥመት ከንቱ ፍላጎት እስከ ደቡብ ጎንደር አኖኒ ሀይቅ ድረስ ተዘረጋ። የአማራ አክራሪ ተስፈኞች የርስት መመለሻ እንቅስቃሴ ጉጉት 'ፈጣሪ ጉልበት ቢሰጠን እና በለስ ቢቀናን ሞቃዲሾ (መቅደስ) ድረስ የኛ ነው' በሚል ያልተገራ ስሜት አድማስን ተሻግሮ በምኞት ፈረስ ናወዘ። የአማራም ሆነ የኦሮሞ አዎምብርት አልባዎች የኛ 'ከኛ' ፋክክር ጎረቤት ሀገር ድረስ ኬንያ (ኬኛ/ Kenya) የአያቶቻችን ይዞታዎች ነበሩ አሉ።

ህዝባቸው በየተማሩበት መስክ ኑሮዬን ይለውጡልኛል የሚል ተስፋን ሰንቆ ቢያስተምራቸውም፦ የህግ ምሁሩ የተሻለ የፍትህና የዴሞክራሲ ሥርአት ዘርግቶ ሰላም እንዲሰፍን በመጣር ፈንታ ወንድም ከወንድሙ የሚጠፋፋበትን ፀረ-ሰላም ሽመል መቁረጡ የእርካታው ጥግ ሆነ። የማህበራዊ ሳይንስ ፈላስፋው አብሮ የኖረውን ወገን በማናቆር የማህበራዊ ምስቅልቅል አጋፋሪ ሆነ። ሀኪሙ የሚፈሰውን የወገን ደም በህክምና ጥበብ ከማስቆም ይልቅ ማህበረሰብን ከማህበረሰብ አናክሶ ደም ማፋሰስ መረጠ። የፀጥታ ሀይሉ ከሽፍታ እየተመሣጠረ ምስኪን ወገኑ ላይ ይተኩሳል። ሲቪና ፖሊስ በየመሽታ ቤቱ ይቀጣጠራሉ። የትራፊክ ፖሊስ ተደራድሮ ይጠበድላል። መምህሩ ውጤት ይሸጣል።

ሰውነት ረከሰ። ማንነት ጎሰቆለ። ወላጆቻችን ያቆዩን የመከባበር የፍቅር የአንድነት የአብሮነት እሴት 'እኛ ቋሚዎች በምንመሠክረው የቅርብ ጊዜ እውነት' ድሮ ሆኖብን እየተሸረሸረ መልካሙ የታሪክ አዝመራ መሀከል አረማሞ ተተከለ። ተስፋ ሰጪው ቡቃያ በእህል በሽታ ዋግ ተመታ። ኩርንችት ለመለመ። አረማሞው ተስፋፋ። አረሙ ከሰብሉ ፋፍቶ ዘር ቀጨጨ። የሰይጣን ማሽላው ዘለግ ብሎ ታሪክ ድንክ ሆነ። ከፋት ተዘርቶ መልካምነት አይዘመርምና የእውነት ገበያ ከአዘቦት ቀን በታች ቀዘቀዘ። የቅጥፈት ሸመታ ከገበያ ቀን በእል ልቆ የአውዳመት ገበያ ያህል ደራ። በዘር ፖለቲካ ሦስት ትውልድ በአንድ ዘመን ከረጢት መከነ።



t.me/OLDBOOKSPDF

የነቀርሳው ሰንኮፍ እንደዋዛ አልተነቀለምና እንደዘበት የሚነቀል አይደለም። ለኀሣ ፖለቲካ አስቻይ ሁኔታ ተፈጥሮለት ያልተገራ ነፃነትና ምኅ፣ አየር መደላድል ሆኖት እየፋፋና እየተንሠራፋ የፈጠራ ትርክት አምቦጭ የታሪክን ሐይቅ የሚያደርቅበት ምቹ አጋጣሚ ተፈጠረ። ለግማሽና ሩብ ክፍለ ዘመን (1970 - 2018) የተደረተው የፖለቲካ ቡትቶ፣ የምኞት እንቶፈንቶ፣ የጮላቻ ዝግንትል፣ የከንቱነት ወለፈንዲ፣ የብኩንነት ገዊ፣ የማይም አልቦ ድፍረት ፤ የተደረተ መደዳ እሳቤ ገነነ። በትክክለኛ የታሪክ አረዳድ ከንድ ካልተደቆሰ፤ በሀሳብ ጥይት ካልተበረቀሰ፤ በታሪክና ፖለቲካ መሀከል የተፈጠረው ጋብቻ ሰማንያው ካልተቀደደ - ኢትዮጵያ ታላቋ ባለታሪክ የዘመናት ነፃነት ሀገር በቅርቡ ነፃ ከወጡ የአፍሪካ ሀገሮች ግርጌ እንደምትሆን ሳይታለም የተፈታ ነው። የታሪክ ደንቃራው ጦስ አንድ ሥፍራ ላይ ተወርውሮ መጣል አለበት። ጊዜውም በቀጥታ ዛሬ ነው። 'አስቀድሞ ማመስገን ኋላ ለማማት ያስቸግራል' ብሂል ቢሆንም ሀገር ለማዳን ኋላም ቢሆን ለማማት በጎ ስናይ አመስግነን ስህተትን መረጥን። የኋላውን ጠባይ በመፍራት መልካሙን ካላወደስን በጎነትን እንቀብራለን።

'የአዲሱ ለውጥ' ያልተገደበ ቅጥ ያጣ ነፃነት፤ ለፖለቲካ ፍጆታ የተቀነቀነው የኀሣ መዝሙር እንዳሻው እንዲሠግር ምቹ ሁኔታ ፈጠረለት። ወያኔ ጥቅሟን ልታስጠብቅበት በኃይል እምቃ የያዘችውን የረጋ ኩሬ ከርፋት በዘዴ ከማስተንፈስ ይልቅ በአኩይ ልሂቃን በጥባጮች ፊታውራሪነት ተንቦራጨቁበትና እንኳን ሊጠጣ ቀርቶ የአልቅት የወባ የተውሳክ መራቢያ ሆነና የህዝብን ጤና ነሣ።

መሣ ለመሣ የታሪክ ምሁራን በዘመናት የተባ የምርምር ሥራቸውና እንቱ በተሰኘ እውቀት - ሽበት ሺውበት ሆኖላቸው ከጥልቅ የድርሳናት ፍተሻቸው፦ ከእውቀት ውቅያኖስ ጨልፈው እንዳያጠጡን፤ የጥበብ ማእድ ገበታ ዘርግተው እንዳይመግቡን፤ እየተንዶለዶለ ከሚወርደው የጥበብ ወንዝ ቀድተው ጥማችንን ሊያረኩ - ከታሪክ ምንጭ ረጭተው እንዳያረሰርሱን፤ ከሚያስጎመዠው የታሪክ ዘለላ እሸት አዝመራ ፍሬ በሌማት ሞልተው እንዳያቀርቡልን እንቅፋት በዛባቸው፡፡

ቀናዎቹ ተግዳሮቶቻቸው፦ የዘውግ ፖለቲካ የፈጠረው መፈራራትና መጠራጠር የጨለምተኝነት ዳራ እነገሠ። የየወቅቱ ሹማምንት የታሪክ ትምህርት ከፍልን በዐይነ ቁራኛ መከታተል፣ ፖለቲካዊ ጉሽማና ታሪክን ለመንበራቸው ፍላጎትና ለሥልጣን ጠኔያቸው ማስታገሻ ለመገልገል ያላቸው የበዛ መሻት እሚከላ አበቀለ። የታሪክ ምሁራኑ የሚያምኑበትን ላለመግፍና 'በደመና ስለመብረቅ ላለማውራት'፣ ከበዛ የኩብር መጨነቅ በመነጨ የትችት ፍርሀት/ ሽሽት ጉብስ ጉብሱን ካልሆነ እወዛጋቢውን በአይነኬ ሐሳብ ሸሹት። ምሁራኑም ከግራና ከቀኝ ከፊትና ከኋላ ሰቅዞ በያዛቸው

ተግራሪ ፍላጎቶች ተቀስፈው ተይዘው ላለመነካካት በመናበብና በመግማል 'አቧራ በናው ይስከን' - በትምህርት ከፍሉ ቋንቋ (Let the dust settles) የሚታወቅ ስሜት መሸበብን መረጡ። (በርግጥ በዚህ ረገድ የታሪክ ምሁራኑ በጥበብ የደርግንና የወያኔን ዘመን ማለፍ መቻላቸው ይደነቃል።

የማንሪያ ካምፑን መከራም የቀመሡ አልታጡም።) መሠል ተጨማሪ እንቅፋቶች ተዳልበው ታሪክ የሀገሬ ገበሬ 'ፈርመህ ልቀቅ' የተሰኘ ስያሜ በሰጠው አረም ተዋጠ። የጨለምተኝነት ድባቡን ጠርምሶ (Breakthrough) አንዳች አዲስ አመለካከት (Paradigm Shift) የታሪክ ባለሙያዎች ማህበር መሥርቶ የታሪክ ዝንፈትን መከላከል አልተቻለም። እንዲያውም ማህበሩን ለማቋቋም አስቸጋሪ ስለሚሆንባቸው እሳቤዎች ትንተና መሥጠት ተመራጭ ዘይቤ ሆኖ ተወሰደ። በድምሩ የኢትዮጵያ የታሪክ ፀሐይ ደምቆ እንዳያበራ የፖለቲካ ቋሚ ግርዶሽ ሸፈነው።

በታሪክ እንከኖች የተበረገደውን ገዋ በመጠቀም የብሔረሰብ፣ የዘውግ፣ የጎሣ እና የማለያየት ፖለቲከኞች በጥላቻ የታጀለ ለከት የለሽ ስንከሳራቸውን ማገረፍ ጀመሩ። አዶልፍ ሂትለር 'ከዋሸህ አይቀር አሣሣች ትልቅ ውሸት ዋሽ' ብሂል ለናዚዎች እንዳልጠቀመ እያወቁም ለእኩይ ዓላማቸው ልቦለድ ደረሡ። ታሪክን በተገቢው አኳኋን በማስረጃና በተመሣከረ መረጃ አስደግፈው፣ የአጠናን ስልቱን ተከትለው በተጠየቃዊ አግባብ መፃፍ (Writing of History) ተተውና በዘፈቀደ ሀገርን እንደ ቅርጫ ሥጋ መሸንሸን በሚያስችል፤ ለትውልድ ሃላፊነት በማይሰማው መንገድ የውሸት ትርክትን መፍጠር (Invention of History) ገንግኖ ወጣ። የሠለጠነው ዓለም እንኳን ጥላቻን በጦማር መልክ ሰንዶ ሊያወጣ እውነት እንኳ ከበዛ ጎጂ ጎን አለው በማለት ለእያንዳንዱ ድርጊት ትውልድን ታሳቢ ያደርጋል። (As frankness strengthen friendship, extreme frankness kills it.) እንዲባል።

ዘውጌዎቹ፡- ቡትቶ የጥላቻ ድርሰታቸው ተቀባይነት እንዲያገኝ ጥቂት ጥፋትን የዝሆን ያህል በማጋነን፤ የበዛ የታሪክ መልካምነትን በመሸፈን፤ የፖለቲካ ግልሙትናቸው የፀነሰውን የጥላቻ ሾተላይ ያለአንዳች ርህራሄ በትውልዱ ዛሬና ነገ ላይ ጨነገፉ። በተረጋጋ በሰከነ በበሰለ የዘመን ዕይታ ሲመዘን በደማቅ አለላ ከተሰናኘውና በጥበብ መሠረት፣ በጠንካራ ምሰሶ፣ በድንቅ ማዕዘናት፣ በእፁብ ወጪና ወራጅ፣ በድንቅ ከፈፍ፣ በማይዝል ብርቱ ከንድ፣ በባለሙያ የተሰናኘውን ውብ ሰበዞች የሞሉበት ጎጆ ባላየ እና ባልሰማ አልፈው፤ ከታሪክ ስህተት ስንጥር ነቅሰው፣ የወየበ የጠየመ የጠቆረ የተበላሸ የመሰሏቸውን ነጠላ ሰበዞች በመምዘዝ እና የዳያኖሰር ያህል በማግዘፍ የጥላቻ ቀንድ አብቅለው፣ የከፋት ጭራ ቀጥለው፣ እበላ ባይ ወና



t.me/OLDBOOKSPDF

አሳቢዎቻቸው በፈጠረው የከርስ ስሜት በማዘሬ አካላቸው ልክ ቦርጭ ከምረው፤ በታሪክ ጉዞ ጥፋት ቢጭረው፣ በብርዕ ፍላፃ አቁስለው፣ ቁስሉ እንዳይሽር አመርቅዘው፤ ጠግግ እንዳይል በደም ባደፈና በጨቀየ እጃቸው እየነካኩ ታሪክን አረከሱት።

ስለ ጊዛው የግብፅ ፒራሚድ ኩፉ ወይም ቺዎፕስ፣ ከጨረቃ ሆኖ ላይ 'ስለሚታየው የቻይና ግንብ፣ ስለፈረንሳዩ ኢፈል ታወር፣ ስለሱሜርያውያንና ፎኒሺያውያን የአፃፃፍ ዘዴ፣ ስለራሳችን ዓባይ የግብፅ ሥልጣኔ አልፍ ስንከሳር እየተገፊ፤ የሀገራችን ኢትዮጵያ ታሪክ እንዳይበቅ ዘመን የወለዳቸው አውታሮች በሙሉ የወል ታሪካችንን ለማጠልሸት ተረባረቡ። የብዙኃን መገናኛ፣ የህትመት ውጤቶች፣ የኤሌክትሮኒክስ ዘዴዎች፣ ማህበራዊ ሚዲያ፡- 'ዩቲዩብ ፌስቡክ ኢንስታግራም ትዊተር ቫይበር ...ሁሉም አይነት ድረገፆችና በይነመረቦች የጠላት ታሪክ ይመስል በማራገብ በቀላሉ በማይድን የታሪክ ደዌ የሀገርን ከራሞት አነወሩ።

ትውልድ ገዳዩ የትምህርት ፖሊሲና ጠልቆ እንዳይመለከት ሆኖ የተቀረፀው መንጋ በምክንያት ሳይሆን በስሜት እንዲነዳ አድርገው ሥሩት። እንዳሻቸው 'ቹ' ለማለትና ለመሥገር አመቻቸው። 'ዝለል' ሲሉት እስከየት? በማለት እስከመሰበር የሚዘልል እንጂ 'ለምን?' ብሎ የማይጠይቅ ትውልድ ፈጠሩ። ተው ይህ አካሄዳችሁ አይበጅም የሚል መካሪና ዘካሪ ጠፋ። ደፍሮ ብቅ ካለም የማፍን ጽዋ ይጎነጭና ለሌሎችም ጥምር ማስፈራሪያ ሆኖ ልሳኑ ይዘጋል፡፡

ትክክለኛ የታሪክ አረዳድ አዕምሮን አዳዲስ ሀሳቦችን ለመቀበል ክፍት ማድረግን ይጠይቃል። ታሪክ በመሠለኝና በደሣለኝ በዘፈቀደ የሚጠና እና የሚነበብ የትምህርት ዘርፍ አይደለም። ማስረጃና መረጃዎች ተሰባስበው፤ የምንጮቹ ተአማኒነት በጥንቃቄ ተመሳክሮና ተመርምሮ፤ ራስን ታሪኩ በተፈፀመበት ዘመን ሊኖር በሚችል የግንዛቤ ደረጃ አርቆ በማሰብ መለካት - በጥንት በመሀከለኛው በዘመናዊና የቅርብ ጊዜያችን የአኗኗር ዘይቤ፤ የሥልጣኔ ደረጃ በዚያ ሩቅ ዘመን በነበሩ ሰዎች ጫማ ውስጥ ገብቶ ማሰብ ይጠይቃል። ተራ ገፊ የተመረዘ ስሜት አዝሎ ታሪክን የመረዳት ብቃት ከቶውኑ አይታሰብም። ከምንግዜ መንፈስ ተፋትቶ በጥበብ እና ሳይንሳዊ የአጠናን ስልት እያንዳንዱን የታሪክ አንጓ መመርመር ያሻል።

የፈጠራ ልቦለድ ትርክቶችን አሽቀንጥሮ በመጣል ኢትዮጵያ ከዓለም የተለየች ደሴት ባለመሆኗ ሀገሮች እንዴት ባሉ ስርአቶች ውስጥ እንዳለፉ፣ በገዢዎችና በተገዢዎች መሀከል ሰፍኖ የቆየው ማህበራዊ ግንኙነት የነበረውን መልክ፣ የተፈፀሙ የታሪክ ግድፈቶችንና ጥንካሬዎችን በርብሮ በጥሞና ማጤን፣ ታሪካችንን ከየዘመኑ የዓለምና



t.me/OLDBOOKSPDF

የአፍሪካ ሀገሮች ገቢሮች ጋር ማወዳደርና ለምን? እንዴት? መቼ? የት? በምን? ስንገነዘብ በርግጠኝነት በወንድማማቾች መሀከል ጠብ ለማብቀል ዐረ-ኢትዮጵያ አመለካከት በምን ሥውር እጅ እንደሚዘወር መረዳት የሚያስችል አቅም እንፈጥራለን።

'ፔትሮ ዶላር' የሚያሾራቸውን ሀይሎች መነሻ፤ የጠላቶቻችን ሥውር ግዙፍ እጅ፤ ካፒታሊስቶች ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ በሀገራቸው ፈፅሞ ሊያዩት የማይሹትን የዘውግ አደረጃጀትን ለምን በሌሎች ሀገሮች ሲሆን በፖሊሲ ደረጃ ቀርፀው እንደሚተገብሩ፤ የኛ ልሂቃን መናጆዎች ከአፈንጋጭ የሚያገኙት ጥቅም ፤ለምን ከሀገር ውስጥ ምሁራን ይልቅ በውጭ ሀገር የሚኖሩ የተማሩ ማይማን ዋነኛ ተዋናይ እንደሚሆኑ ሞጋች ትውልድ ተፈጥሮ መገንዘብ ሲችል ያኔ ይረግማቸዋል፤ አምርሮ እንደሚጠየፋቸው ሀቁን መረዳት እስኪቻል የመፅሐፉ አዘጋጅ ያለ አንዳች ተጨባጭ ምክንያት በየዩኒቨርሲቲዎች በተነገራቸው የፈጠራ ታሪክ ተመሥርተው ተማሪዎች እርስ በርስ ሲጎዳዱ ሲያስተውል ለመምከርና ለመገሠፅ በማል የፌስቡክ ገፁ ያኖረውን 'ስታተስ እነሆ እንደሚከተለው አቅርቢል፡-

*በየትኛውም ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ የተመደባችሁ የኢትዮጵያ ልጆች፡- አጠገባችሁ ያለው ወንድማችሁ የእናታችሁ ልጅ እንደናንተው ከምስኪን ቤተሰብ የተገኘ ነው። ነገ ያልፍልኛል ብሎ ተስፋ የሰነቀ። ጭራሮ ለቅሞ፣ ጠላ ሸጦ፣ ግፋ ቢል በገሊት ችርቻሮ ወይም በመንግሥት ስራ ከእጅ ወደአፍ ኑሮ የምትኖር የእንተንው እናት የምትመስል እደይ /ሀቶ/ ሀርሜ እለቿው። እንዳንተው አባት በእርሻ በመለስተኛ ንግድ በመንግሥት ስራ የሚባትል አባት፤ እንዳንተው የሚያዝንለት ወገን አለውና ዛሬ ለሰው ልጅ መሰመር በማይገባው ከልሊ ገባ ብለህ አታጥቃው። ያ በመበላላት የኖረ የጃጀ ትውልድ ውስኪውን እያንቃረረ፤ ልጆቹን በምእራቡ ዓለም እንቀባሮ እያስተማረ ወይም በግል ዩኒቨርሲቲዎች እያመናሸ አንተን ያናከሳልና ዘመኑን ዋጅተህ አትስማው።*

*አመነኝ አንድ ሆነህ ከቆምህ ከፊትህ ብሩህ ተስፋ አለ። ተመርቀህ፣ ወልደህ ከብደህ ... የዓለማችን ትልቁ ሰው መሆን። አመነኝ በዩኒቨርሲቲ እመዕ ደም ገብረህ፣ ወንድምህን ገድለህ ... ትምህርቱ ይቀጥላል እንጂ አይቆምም። በፀፀት እለንጋ እየተገረፍህ እድሜህን በእስር ትማቅቃለህ። አሊያም ራስህ ሰለባ ትሆናለህ። ባይሆንስ ምንም ውስጥ ከሌለበት ወንድምህ ተባልተህ ትርፉ ምንድነው? የሚያናከሷችሁን የዘመን መጋኛዎች ፈፅሞ አትስሟቸው። የዋነኞቹ ሌቦቹ ልጆች በምእራቡ ዓለም በቅንጡ ተቋማት እሉላችሁ። የደሀዎች ልጆች*

በምን ምክንያት ደም ትቃባላችሁ? የአንዳችሁ እናት ወይም በዓለም ቁጥር አንድ ወዳጃችሁ ተመርቃችሁ ትመጣላችሁ ብለው ሲያስቡ ለምን አስከሬናችሁን ይቀበላሉ? ለምን? ለምን? ለምን? በጥቅሉ እናንተ የአንዲት ኢትዮጵያ ልጆች፣ ቤተሰብ ናችሁና (ወንድማማቾችና እህትማማቶች ናችሁና) እጅ ለእጅ ተያይዛችሁ የማይደገመውን ጣፋጭ የካምፓስ 'ላይፍ' በፍቅር አጣጥሙት።

Taye Bogale Arega (Ilma Dasu Odaa)

አባት እናቶቻችን በየዘመናቸው አስተሳሰብ ልክ በየቆሙበት ምድር ላይ ዳናቸውን አሳርፈው፣ አሻራቸውን ከዘመናቸው ልቀው አኑረው፤ በአብሮነት ተወዳዳሪ የሌለው የፈሪሀ ፈጣሪ ባለቤት ታላቅ ህዝብ ከትልቅ ሀገር ጋር ገነቡ። ዕንቁውን ማየት ተሰኖን እንጂ እጅግ የደመቀ ታሪክ ባለቤት የሆነች ሀገር ኢትዮጵያን የቻሉትን መሠረት አውጥተው፤ የበለጠ አስውበን እናበጃት ዘንድ አስረክበውናል። መሪዎቿን ለነፍሳቸው ዕረፍት - 'ላዕሉ ሰላም' ብለን ባለሙት ልናወድስ፣ ባጠፉት ልንወቅስ ከመነሳታችን በፊት ዛሬ ባለንበት ዘመን በሥራቸው መልካም ከዋኞች 'አበጀህ የኛ ጀግና' ተብሎ የሚሞካሽ፣ ኒሻን የሚታሰርለት፣ የክብር አቀባበል የሚደረግለት ወገን እንደሌለ ሁሉ - ባጠፉት የሚወቀስ የሚወገዝ የሚኮነን የሚረገም የሚሳደድ ሊኖር ከቶውኑ አይገባም።

ደፈር ብሎ እኩያኑን - ለመሆኑ ትላንትን እያነሳህ እብዝተህ የምትወቅሰው፣ የመሪዎችን ስራ የምታማርረው፣ እየደጋገምህ የአቅም ማምከኛ ስልጠና የምትሰጥባቸው ምን ፈልገህ ነው? ብለን ብንጠይቅ፤ ዛሬ በትላንት፡ ጥፋት ከሳሽ፣ተከሳሽ፣ ፈራጅ፣ ዳኛ፣ ዓቃቤ ህግ፣ ምስክር፣ የደረጃ ምስክር፣ ካሽ፣ ተካሽ እለ ወይ? ተብሎ ቢሞገት የእኩያኑ ምላሽ - 'ታሪኩ እንዳይደገም ለመዘከር ነው' ከመሆን የዘለለ አይደለም። እድሜ ልክ 24/7 ዝክር ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም።

ዓላማው ግልፅና አፍጥጦ ያገጠጠ ነው። ኢትዮጵያን ማፍረስ፣ ከብሯን ማርከስ፣ ቢቻል 'የትግራይ ሪፐብሊክ፣ የአምኃራ አባት ሀገር፣ የሲዳማ ግዛት፣ የኦጋዴን ምድር፣ የኩሽ መንግሥት' ... መፍጠር፤ ያን ጊዜ እንደነርሱ መሻት ቢሆን ኢትዮጵያ በመፈከር አትቆምምና ተረት ትሆናለች። በእርግጥ ኢትዮጵያ ሊያፈርሷት የወጠኑትን እያፈረሰች ትላንትን ተሻግራለች፤ ዛሬን እየተንገዳገደች ቆማለች፤ የቱንም ያህል ብትወዘወዝ በዘመናት የፍቅር ቃልኪዳኗ ዋጋ ያስከፍል ይሆናል እንጂ ፀንታ ትቀጥላለች።



t.me/OLDBOOKSPDF

ዓለም የኢትዮጵያን ያህል ታሪክ አጥጠበት - የሚዕፈው ብዙ ታሪክ፣ የሚያኖረው ቅርስ፣ የሚያስተላልፈው ገቢር አንሶት - ንዋየ ቅድሳት እና ቅርሶቻችንን ሲዘርፍ፣ የአዲቱዎድሮስን የፀጉር ሹሩባ ሳይቀር ሳጥኑ ለትዕይንት ሲያቀርብ፣ ከአባት እናቶቹ የወረሰውን ጭላጭ ጀግንነትም ቢሆን አግዞፎ ወጣቱን ለማንሳሳት ይጠቀማል። በትላንቱ እየተቆጨ የጎደለውን ሊሞላ ለቁሳዊና መንፈሳዊ ሀብት ለውጥ በእውቀት ላይ ተደማሪ ጥበብ እያከለ የአጠቃላይ ፍጥረተ ዓለምን (Cosmos) ምስጢር ለመበርበር ሲመነደግ፣ የከርሠ ምድርን እምብርት የውቅያኖስ ወለልን ጥልቀት ሲበረብር፣ ሌላ ፕላኔት ሲያስስ ጨረቃ ላይ አዝመራ ሲተክል፣ የሌሊትን አስፈሪ ጨለማ ግርማ በሰው ሰራሽ ብርሀን ለውጦ ሲታትር እኛ የተገነባውን እያፈረስን፣ የቆመውን እየናድን፣ ዘወትር ከአልቦ ስንጀምር ፍርቱናችን ባለህበት እርገጥ ሆነ። በከፋም ደረጃ ከድጡ ወደ ማጡ፣ ወደ እንጦርጦስ ወደ ጥልቁ በፍጥነት መዝቀጥን መረጥን።

በአሜሪካ የነጭ ዘረኞች 'ኩ ክሉክስ ክላን' የጥቁሮችን እኩልነት ላለመቀበል ሲላላጥ ኃያሏ ሀገር ልክ አስገብታ ደፈቀቻቸው። በቅርቡ የ'ባስከ' ነጮች ዘረኛ ንቅናቄ በማህበራዊ ሚዲያ ሲቀነቀን (2019) ኮስተር ወዳለ እርምጃ ገባች። እንደ ጋና እና ታንዛኒያ ያሉ ሀገሮች የብሔረሰብ ፖለቲካ አደረጃጀት ፈፅሞ እንዳይኖሩ ተግባራዊ እርምጃ ጀመሩ። ኬንያ በህገ መንግሥቷ ጥምር የብሔረሰብ አደረጃጀት አግዳለች። ሩዋንዳ ስለ ብሔረሰብ ልዩነት መናገር ዘብጥያ እንዲወርድ ህግ ደንግጋለች። ኢትዮጵያ በስመ ነፃነት ልጓም ያልተበጀለት ብሔረሰቦችን የሚያጥላላ፣ አብሮነትን የሚያከፋፋ፣ አንድነትን የሚያሻክር፣ ጥላቻን በአደባባይ መስበክን በለሆሳስ አልፋ ዛሬ (2019) የጥላቻ ንግግርን የሚከለክል ህግ የማፅደቅ ጅምሯ መልካም ቢሆንም የአኖሌ የጨለንቆ እና ወንድም ወንድሙን የገደለባቸው የሚኙቹ ሐውልቶች አቁማ መሳለቋን ስንመዝን ህጉ ለላንቲካ የወጣ ነው የምንለው እርምጃው መልካም በመሆኑ አያበረታታን ከውጢት አንገር ግን የምንኮንነው 'መላ ሰውነት ቆሽሾ ሳለ ከእንገት በላይ 'ሻወር' እንደመውሰድ በመሆኑ ነው።'

ሀቅ ሀቁን እንነጋገር ካልን በግልፅና በተዘዋዋሪ ሀገር መበተን 'ውጉዝ ከመ አርዮስ' - 'አዑገዘቢላሂ መነ ሼይጣን ረጂም' ተብሎ በእምነት ተቋማት እንደገባች ውሻ ሊያስነውር ሲገባ፣ የተገላቢጦሽ ውርደት ተሸክሞ በአደባባይ መፎከር የተለመደ አባዜ ሆነ። አሁን ባለው የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ዳራ ሰውነት ዜግነት አመክንዮ አንድነት ህብረት ፍቅር መተሳሰብ መከባበር እና መሠል የመልካም ስብዕና መገለጫዎችን የሚያስተምር፦ 'የድሮ ሥርአት ናፋቂ፣ የአቢሲኒያ የበላይነት

እስቀጣይ፤ የነፍጠኛ ውላጅ' እየተባለ (የሚሸማቀቅ የለም እንጂ) ለማራከስ ተሞከረ። ግቡ እጅግ በጣም ግልፅ ነው። 'ኦሮሞ ፈርስት'፣ 'አማራ ፈርስት'፣ 'ትግራይ ፈርስት'፣ 'ሲዳማ ፈርስት' ... ብዙ የ'ፈርስት' እንቅስቃሴዎች ፈጥሮ ኢትዮጵያ እንደ ትርፍ የሁለተኛ እና ሦስተኛ ደረጃ እንድትይዝ በማድረግ የተነሱበትን ሀገር የማፍረሱን ዲላማ የመምታት ርጉም ሸር አካል ነው። 'መሪ ህዝብን ሲፈራ ዴሞክራሲ መኖሩን፤ በተቃራኒው ህዝብ መሪውን ከፈራ ዲሞክራሲ መሞቱን እናውቃለን:: ወጥቶ ለመግባት ወገን ወገኑን ሰው ሲላውን የጎረቤቱን ሰው ከፈራ ግን ምን ማለት ይሆን?

የኢትዮጵያ ታሪክ መበላሸት ምክንያት የጥፋቱ ተልእኮ ተቀባዮች 'እንደ ብርሌ እና ሰካራም ሠፈ ሆድና ረጂም አንገት እንጂ ንፁህ ህሊናን ያልታደሉ' ሆነው ለግላዊ ፈንጠዝያ ሀገርን በደም እንባ የሚሸፍኑ መሆናቸው ነው። የሺህዎች ዘመናት ታሪካችንን በ3ሺህ መቀሸብ፣ በመቶ ዓመት መቆንፀል፤ ትልቅ ሀገርና ገናና ታሪክን የክብር ካባዋን አስወልቆ ጥብቆ ማልበስ፤ መንናፀፊያ ቀሚሷን ገፍፎ ቁምጣ ማጥለቅ፤ የወርቅ ጫማዎቿን በሀሳባቸው ልክ አውርዶ ሸበጥ ማጫማት ሀገርንም ሆነ ትውልድን አይጠቅምም።

አበው ወእመው በእርታ ልርታ፣ አንተ ትብስ አንቺ ትብሽ ስሜት በአለት አምድ ላይ ያቆሙት ታሪክ በአቅም ግንባታ ተብዬ ሰነድ ልቦለድ ጥላሸት ተቀባ። የትውልዱ እምቅ አቅም ስለ ግብርና መዘመን፣ የትምህርት ጥራት፣ የሥራ ፈጠራ፣ የምርምር ጠቀሜታ፣ የንግድ አዋጪነት፣ የስነልቡና ግንባታ፣ የሀገር ገፅታ ቅብ፤ የቱሪዝም ልማት፣ የደን እንክብካቤ፣ የስነተዋልዶ ጤና ክብካቤ፣ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት፣ የታሪክ ጠቀሜታ፣ የከርሠ ምድር ምርምር፣ የብሔረሰቦች ወግ ባህል ልምድና ትውፊት ሳይሆን መሽ ጠባ አጤ ምኒልክ መቃብር ፈንቅለው ተነስተው ያስተዳድሯቸው ይመስል የሥልጠና መነሻና ማማሟሻ ሆኑ። ሥልጠናዎቹ በምን ደረጃ ሰይጣናዊ እንደሆኑ የሚያስገነዝበው (1991 - 2018) ዕያዩና እየሰሙ ፊት ለፊታቸው የተፈፀመውን ሲጀሮ የሚቀፍ ግፍ፣ ዐይንን በዕንባ የሸፈነ ሰቆቃ አሪታ ዋይታ ጩኸት ባላየ እና ባልሰማ አልፈው በሚያሳቅቅ መልክ ከዛሬ 130 ዓመታት በፊት በዋናነት አኖሌ እና (ጨለንቆን በብድር) 'ተፈፀመ' የተባለ የበሬ ወለደ ቅጥፈት ፀንሰው፤ ጉዳት ሲያደርሱ እና ለጥፋት ተዘጋጅተው በመስተዋሉ ነው።

የሚያሳፍረው 'የአቅም ማምከኛ ሰነዶቹ' የዳግማዊ ምኒልክን እንዳችም ጥንካሬ ለማውሣት ካለመድፈራቸው እና የአፄ ዮሐንስ አራተኛን የግፍ ግፍ ለማንሣት ካለመሞከራቸውም በላይ፤ የገንዘቡ ምንጭ ኩበት ጠፍጥፋ ከምትተዳደር ምስኪን እናት መቀነት ተፈትቶ፤ ላቡን አንጠፍጥፎ ወዙን ጨምቆ ከሚታትር ላብአደር



t.me/OLDBOOKSPDF

ተቀምጦ፤ ከጎስቋላ ገበሬ አርብቶአደር አርሶአደር እና የቆዳቸው ቁርበት ከአጥንታቸው ከተጣበቀ የከተማ ምንዱባን ተቀምጦ፤ ሌት ተቀን ለፍቶ ካገኘው ነጋዴ ላይ ከተጣለው ፍትሀዊነቱ ከሚያጠራጥረው ግብር ተሰብስቦ መሆኑ የህመሙን ጥዝጣዜ ውስጥ ድረስ ዘልቆ እንዲሰማ ያደርጋል። ከሀገር በተዘረፈ አንጡራ መዋዕለ ንዋይ ለአከሊዳማ የተጠነሰሰው ብቅል፤ ከመርገ| ጌሾ እና ቂጣ ጋር ተብሳልቶ ምርጊቱ ሲከፈት የፈነዳው ጠላ የማመዛዘኛ ናላን የሚያዞር፤ የማስተዋል አእምሮን የሚያስት፤ ወገንን ከወገን አፈናክቶ ደም የሚያፋስስ፤ ከአንድ እናት ከሁለት አባት የተወለዱ ወንድማማቾችን ጭምር (ከተለያየ አባት አብራክ ስለተከፈሉ) በአባት ዘውግ ለያይቶ ዐይንና ናጫ የሚያደርግ ነቀርሳ ሆነ።

በዘመናት አብሮነት ከተፈጠረ ወዳጅነት ከሁለት ብሔረሰቦች የተገኙ ባልና ሚስት (ሁሉም ወገን መሆኑ ጥርጣሬ የማይኖረው ሆኖ 'የአንደኛው የተባለው' የጦር አበጋዝ ቡድን የሌላኛውን ሲያጠቃ የስሜት መለዋወጥ፤ የቃላት መሠናዘር)፤ በመሀከላቸው ንፋስ በገባ ቁጥር የተገኙበትን ብሔረሰብ የእሳቱ ማቀጣጠያ ነዳጅ በማድረግ ትዳር እየፈረሰ፤ የልጆች መበተን፤ በየመሥሪያ ቤቱ በብሔረሰብ ላይ ያነጣጠረ ግላዊ ጥቃት የመድረሱን ያህል የራሱን የስነምግባር ግድፈት 'በአካባቢዬ ምክንያት ተጠቃሁ' ሰንካላ ሰበብ መደበቂያ ለማድረግ ረዳ። ብሔረሰቦች የከፉ ሰብአዊ መብቶችን ለፈፀሙ የመደበቂያ ዋሻ ሆኑ። የፍትህ ሥርአቱ የሚተገበረው እንዛራዊ ጉልበት ያነሰው ላይ ሆነና 'ከክልላችሁ እገሌ ወንጀል በመሥራቱ እንፈልገዋለን' ሲባል 'የእናንተንም አብራችሁ እሠሩ እንጂ የኛን ብቻማ አሳልፈን አንሰጥም' ድረስ የመዝቀጥ ስሜት ገነነ። ፖለቲካ ከህግ ጋር ተዛነቀ። አንዳንዴ ታሪክ ራሱን ይደግማልና ጉዟችን ወደ ዘመነ መሣፍንት ይመስላል።

ቋንቋ መግባቢያና እርስበርስ መገናኛ መሆኑ ቀርቶ ፖለቲካዊ ትርጉም ተላበሰና ከቅኝ ግዛት በቅርቡ ነፃ የሆኑ የአፍሪካ ሀገሮች ጭምር ያላደረጉትን፤ ምናልባት ተሰምቶ በማይታወቅ መልክ አንዳንድ እኩይ ልሂቃን 'ትላንት ለመፈታታቸው የታገለና የሞተ ወገናቸውን ለማስጠቃት በቀጥታና ተዘዋዋሪ 'ቋንቋውን አትናገሩ' አይነት የበሸቀጠ ዲስኩር ያለኃፍረት በአደባባይ ጭምር መለፈፍ ጀመሩ። የበለጠ የሚያሳዝነው ፈፃሚዎቹ አድማጌ ልምድ ሙያና የፖለቲካ እውቀት አላቸው ተብለው የሚገመቱ የፖለቲካ ልሂቃን መሆናቸው ነው። በወገን መሀከል ግብይት እንዳይካሄድ ጭምር የመሞከሩ መዳረሻ፤ ያለጥርጥር ህዝብ የመለያየት ፕሮገራው ራሱን ፊትለፊት የመግለጡ ማሳያ ነው። እያያዛችንም ሲቃኝ ከደበተን ዱካክ ለመንቃት አሁንም ዝግጁ የሆንን አይመስልም። ከወቀሳችን መሣ ለመሣ በተፈጠረው እንፃራዊ ምቹ ድባብ በመጠቀም ከ2018 ወዲህ ለትውልድ መድህንና ተስፋ የሆኑ ምሁራን ወደ መድረኩ



t.me/OLDBOOKSPDF

ብቅ ብቅ ማለታቸው በሀገራችን ጨርሰን ሙሉ ተስፋ እንዳንቆርጥ ምርኩዝ ሆኖናል።

ከ1970ዎቹ ጀምሮ በተለይ በግራ ዘመም፣ የዘውግ እና ፅንፈኛ ፖለቲከኞች እየተቀነባበሩ የተደጎሱ መርገዘ ስንክሳሮች ከየትኛቱም መዛግብት ይልቅ ድጋፍ ተደርጎላቸው፣ የገነኑ የገነነ የተደረተ አውራ ልበለዶች ሆነው ታዩ። በተፈጠረላቸው ምቹ ሁኔታ ሳቢያ ከምንም በላይ ተነባቢና ለዕይታ ተደራሽ በመሆናቸው፣ ሀገር ሊያጠፉ በታቀደው ልክ ሚሊዮኖችን ከአንዱ ከልል ወደ ሌላው የማፈናቀል ሥራ በተዘዋዋሪ በአቅድ ተተግብሮ በወገን መሀከል መጠራጠርና ተወልዶ ባደገበት ቀዬ እያለ የባይተዋርነትና የስጋት ስሜት ተፈጠረበት።

ኢትዮጵያ በታሪኳ ብቻ ሳይሆን ዓለምም ይህ ታሪክ በተጻፈበት ዘመን በመጠኑ ያላየው የሀገር ውስጥ መፈናቀል የተስተዋለው በዚሁ የዘውግ ፖለቲካና አገርን የማፈራረስ ተልእኮ ውጤት ነው፡፡ መንግሥትም ተፈናቃዮችን ወደነበሩበት የመመለስ ሳይሆን ተሰደው በመጡበት አካባቢ የማቆየትና ወደ ቀድሞ የትመጣቸው የማስፈር ተግባር ሲታይ ችግሩ ምን ያህል ስር የሰደደ መሆኑን በግልጽ ያሳያል፡፡ በአንድ ቀዬ አብሮ አጠገብ ለአጠገብ የሚኖረውን ወገን መለያየት የግዙፉን ሴራ አጀንዳ ለማስፈፀም መንገድ ጠራጊ ሆኖ ታይቷል። የተፈናቀሉ ዜጎችን በተላመዱትና በተወለዱበት ባድማ ከመመለስ ይልቅ የውላጅ ፍናጅ ... የትመጣቸው እየተፈለገ ሀገርን በጎሳ ለመሸንሸን ለተያዘው የረጅም ጊዜ እቅድ አስቻይ ሁኔታ ተፈጠረለት።

የዓለማችን ተሞክሮ እንደሚያሳየን በገዛ ሀገራቸው ውስጥ የተፈናቀሉ ዜጎች ይቅርና ወደ አጎራባች ሀገሮች የተሰደዱ ሰዎች ጭምር ሰላም ሲሠፍን ወደየቀደመ ቀዬና አኗኗራቸው ይመለሳሉ። ከዚህ በተቃራኒው አስረግጠን ልንገልፅ እንደሞከርነው 'የቅድመ አያቶች ቀዬ እየተፈለገ በየክልላችሁ ሥፈሩ' የሚባለው ብሂል መዳረሻው ምንድነው? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ይመስለናል። ኦሮሞውን ወደ 'ኦሮሚያ'፣ አማራውን ወደ 'አማራ'፣ ሶማሊውን ወደ 'ሶማሊ' ... የራሱ ከሚለው ከተማና መሬት ነቅለው የደም ውርስ ፍለጋ በማስፈር የሚተባበሩ ሁሉ ታሪክ ይቅር የማይላቸው የሴራው አካል ከመሆን አያመልጡም። ይህ ድርጊታቸውም በየክልሉ ያሉ ፅንፈኞችን 'በርትታችሁ አፈናቅሉ' አይነት ተዘዋዋሪ ማበረታቻ ስለመሆኑ ለማወቅ ምርምር አይጠይቅም።

ታሪክ ከ1991 - 2018 በሸምባሽ፣ ታሪክ ጠል የደደቢት /ህወሓት/ ትህነግ ጉጀሌዎች መዳፍ ሥር መውደቁ በኢትዮጵያ 'ታላቁን የታሪክ ጨለማ ዘመን' ፈጠረ።



t.me/OLDBOOKSPDF

'ሀገር አርጅቶ ጃርት አፈራ'። ውጤቱ ባስከተለው ጨለምተኝነት እውነት አንገቷን ስትደፋ፤ ቅጥፈት ቅንድቧን ተላጭታ አደባባይ ስትውል፤ ኅጠኛ በኩራት ቀና ብሎ እየተጀነነ ሲራመድ በአርምሞ ማለፍ ይከብዳል። ሰውነት ኢትዮጵያዊነት ታሪክ ዜግነት አመከንዮ ይሻለናል የሚለውና የሀገር ፍቅር ስሜት ያነደደው ወገን አንገቱን ደፍቶ ሲሸማቀቅ ዕያዩ በለሆሳስ መሸበብ ይከብዳል። በመሆኑም የመፅሐፉ አዘጋጅ በማህበራዊ ሚዲያ ባለው ጠንካራ ቆይታ የታዘበውን፤ በአጭር የፖለቲካ ተሳትፎ የተመለከተውን እና ከከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ እስከ ዩኒቨርሲቲዎች ከሦስት ዐሥርት ዓመታት በላይ ሲያስተምር የታዘበውን፤ እንደ ታታሪ መምህርነቱ በንባብ ያበለፀገውን፣ በመፃሕፍት ውስጥ ራሱን የሚደብቅ (Bookworm) እንደመሆኑም የዘገነውን ትንሽ ዕውቀት፤ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ውሰታ ባለእዳ በመሆኑ በዋናነት መፍትሔውን ለማመላከት 'ምሁራን ገዐም ሲሉ መምህራን ይናገራሉ' በሚል የግል መፈከሩ ባለሁለት ስለት ሰይፋን ከሰገባው መዝዞ፤ የተዛነፈውን የታሪክ እብደት ለመፈወስ 'የያዘውን የወረወረ ፈሪ አይባልም' ተቀባይነት ያለው አባባል ነውና 'በረዶ ሰባሪ' ይሆን ዘንድ እነሆ የዘመናት ፅንሡን፦

**'መራራ እውነት በኢትዮጵያ ታሪክ'**

በተሰኘው በዚህ የበኩር ልጁ ፍቅርን በምጥ ተገላገለ።

ሌሎች መንትያ ፅንሶቹ 'የቦረና እና የጉጂ ኦሮሞ' እና 'መፅሐፈ ነገሥት' እኔ እቀድም እኔ ልወለድ ሽሚያ ይዘው ተገባድደዋል። ጤና ይስጠን እንጂ ብዙ ሰንቀናል፤ መሻታችን ዳርቻ የለውም። ወደ ባህረ ሀሳቡ ከመጥለማችን በፊት ለእኛነታችን መሠረት የሆኑ አካላትን ባናመሰግን የሀሊናችን ባለእዳ እንሆናለንና ቃላት ሊገልጿቸው አቅም ባይኖራቸውም ሊላ አማራጭ የለንም።



t.me/OLDBOOKSPDF

## ምስጋና

በነጋሌ ቦረና ከተማ ጥንታዊ (ጥንቱ) በመባል ይታወቅ የነበረው 'ኦዳ ጋርደን' ውስጥ ከአንጋፋችን መገርሣ እስከ ሙጣጩ ከድር ቀርዖ 'ለፈጠረን' (የ98 ዓመታት ጉዞውን በስኬት ያጠናቀቀው የጦር ሠራዊት አባል) አባቴ ቦጋለ አረጋ እና የፅናት፣ የትዕግሥት፣ የምክር ተምሳሌት የሁላችንም እናት ለሆነቺው መልኳ ለሆንኩት ደሴ አዳ (76 ዓመታት የክብር ጉዞ)፤ አባ ከአብራከህ ክፍለኸኝ፤ እማ ከማህፀንሽ ያኑርልኝ። ሁልጊዜም አብቅለሺኛልና ሁለታችሁንም ፈጣሪ ነፍሳችሁን በአፀደ ገነት ያኑርልኝ። ሁልጊዜም በልባችንና በእኛ ህያው ናችሁ።

ወንድሜ አበባው ከፊት ለፊቴ እየቀደምህ እትብታችን የተቀበረባትንና ያደግንባትን ቦታ- ያሁኑ 'ኦዳ ጋርደንን' የበለጠ አስውበህ፣ በስኬት ላይ ድል እየተቀዳጀህ፣ ተስፋ ሳትቆርጥ በመውደቅ ውስጥ መነሣትን በአርአያነት አስተምረኸኛል፡፡ መፅሐፌን ያለመታከት በአርትዖት ውበት አላብሰኸዋልና አመሰግናለሁ። እህቴ ሙሉ ለውለታሽ ቃል የለኝም የእናቴ ምትክ ነሽ። ወንድሜ መገርሣ በመዲናችን እንድኖር ምክንያቴ ሳጠፋ ምትገስፀኝ አንጋፋችን ነህና ክበርልኝ።

ከተፈጥሮ ሳይንስ የትምህርት ዘርፍ ወደ ታሪክ የትምህርት ክፍል እንዳዘነብል ምክንያት ለሆንከኝ (ለማውቅህ ለማታውቀኝ) የሐዋሳ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የታሪክ መምህር ዓባያ ባይሳ፤ ለኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የታሪክ መምህራን በሙሉ (ልዩ ምስጋና ለተባባሪ ፕሮፌሰር ምናለ አዱኛ)፤ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ መምህራን በሙሉ (ልዩ ምስጋና ለፕሮፌሰር ተሰማ ተዓ፣ ለተባባሪ ፕሮፌሰር ተካልኝ ወልደማርያም እና ለረዳት ፕሮፌሰር አበባው አያሌው) ለመላው የኢትዮጵያ መምህራን።



t.me/OLDBOOKSPDF

በፍቅር ምድር ነጌሌ ቦረና (ከሀርቀሎ እስከ ድቤ አዳማ፤ ከ14ኛ 21ኛ ሻለቃ እስከ 43ኛ ፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ ብርጌድ፤ ለገጉላ ትብቻ እና ቀርሳመሌ፣ ቢታታ፣ ገናሌ) ለተሰናኛችሁ የትንሿ ኢትዮጵያ' ወገኖቹ በሙሉ። (ልዩ ምስጋና ለቦረና እና ጉጂ ማህበረሰብ አባላት።) ለነጌሌ ደ/መ/ቅ/ኪ/ቤ/ከ ካህናት በሙሉ (ልዩ ምስጋና ለመምሬ ታደሰ በቃሉ)

ለሠለስቱ አንስት፦ አብሮ አደጌ (የልጅነት ፍቅሬ ሚስት፣ እናት አጅግ አካሌ እና ደስታዬ በእናንተ ሙሉ ለሚሆነው ልጆቼ ብርሀን እና ሎኮ ሥጦታዎቼ ናችሁ። ትንሿ ጎጆዬ ያለእናንተ ዳፈና ናትና በፍቅር ወዳችኋለሁ። ያለ እናንተ ትእግስትና ድጋፍ ይህን የዘመናት ምጢን መገላገል እንደምን ይቻለኝ ነበር?

በዘመናት ለሀገር በሁሉም መስከ መስዋዕትነት ለከፈላችሁ ሁሉ (በተለይ ለጦር ሠራዊት አባላት።) ለመላው ኢትዮጵያዊ ወገኔ ያለእናንተ ምንም ነኝና እዳችሁ አለብኝ። ለሰው ልጅ ሥልጣኔ ፈር ለቀደዳችሁ በሙሉ ልዩ አክብሮት አለኝ፤ መዕሐፉስ ያለ እናንተ መች ይታሰባል?!

ሥርቶኝ ሥራዬን ላስጀመረኝ እና እስከ መጨረሻውም ለሚጠብቀኝ ለእግዚአብሔር፤ ሰው አይከፍለውምና ወደር ለማይገኝለት ችሮታው በአባባ በረከ መለያ 'ለእግዜር እግዜር ይስጠው።'

ታየ ቦጋለ አረጋ፣ ኢልመ ደሱ አዳ

ዘነጌሌ ቦረና (2011/2019)



t.me/OLDBOOKSPDF

## መግቢያ

"የታሪክ ትምህርት ጥናት ለታመመ ጭንቅላት ፍቱን መድኃኒት ነው"

ፕሮፌሰር ሲቪ.

ኢትዮጵያ፡- በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ በአፍሪካ ካርታ ላይ በሚታየው ቀንድ መሰል ቅርፅ የአፍሪካ ቀንድ (Horn of Africa) እየተባለ በሚጠራው የምስራቃዊ አፍሪካ ክፍል ውስጥ የምትገኝ ታሪካዊ እና በዓለማቀፍ ደረጃ ስመ ጥር ሀገር ነች። በውሀ ሀብቷ መጠን የተነሳ 'የውሀ ማማ' (Water tower) የተሰኘ የማእረግ ስም ብትታደልም ከጠረፍ ውሀማ አካላት ርቃ የባህር በር እና ወደብ አልባ ምድር ሆናለች። ደረቅ ወደብ ሠርታ የውሀ ወደብ ፍለጋ ለህልውናዋ የምትባትል ሀገር መሆኗ በምክንያት ያስቆጫል። በየብስ ጎረቤቷ ከሆኑ ሀገሮች ማለትም ኤርትራ ኬንያ ሶማሊያ (ሶማሊያ/ ሶማሊላንድ/ ፑንትላንድ/ ጁባላንድ ... አፍሪካ ምኗ ያስተማምናል? ብዙ 'ላንዶች') ሱዳን (በቅርቡ የተገነጠለቺውና የምትታመሰው ደቡብ ሱዳን)፣ በቋፍ ላይ ያለቺው ሱዳን እና ጂቡቲ በተለያዩ አቅጣጫዎች ያዋስኗታል።

ከ100ሚሊየን የሚበልጥ ህዝብ እና በቋንቋ ከሰማንያ በላይ ማህበረሰብ አቅፋ የያዘች ሲሆን ህዝቧ ከአራቱ አፍሪካዊ ልዕለ-ቋንቋዎች (Language Super Families / Protolanguages) መሀከል ሁለቱን ማለትም አፍሮ-እስያዊና ናይሎ - ሰሀራዊ



t.me/OLDBOOKSPDF

ልዕለ ቋንቋዎች ይናገራሉ። የኢትዮጵያ ህዝብ የተለያዩ ቋንቋዎች የሚናገር ቢሆንም በታሪክ በስነልቡና እምነት የቆዳ ቀለም ከሠርገኛ ጤፍ በላቀ ሁኔታ ለመለየት የሚያስቸግር ከአንድ እናት የበቀለ በርካታ መንትያ ነው። በብሔረሰብ የተለያየው በሀይማኖት ይገናኛል። በጋብቻ ይሰናኛል። ሀገር ሲጠብቅ አንድ ይሆናል። በንግድ ይተሳሰራል። በከፋ ደጉ በተለያዩ ፍፃሜዎች ይተባበራል። የኢትዮጵያ ልጆች የትኛውም አይነት የአመለካከት የእምነት የቋንቋ ልዩነት ይኑራቸው ሀገራቸውን በፍፁም ልበ ሙሉነት እና ኩራት 'ኢትዮጵያ እናታችን' በማለት ይጠሯታል።

ጥቂት ከሀገራቸው ጎሳቸውን የሚያስቀድሙ እነ 'ፈርስት' መገኘታቸውንም ሳንዘነጋ። ምንም እንኳ ጥቂቶች ቢሆኑም ባዶ በርሜል ጩኸት ስለሚያበዛ የኢትዮጵያን መሠረታዊ ህዝብ 'የልቡና ውቅር' ጠልቀው ላልተረዱ ግለሰቦችና ቡድኖች አስፈሪ መስለው ይታያሉ። ባህርያቸውን በማስረጃ ለማሳየት ጭር ያለች ዶሮ አንድ እንቁላል ጥላ በማስካካት ሀገር እንደምታምሰው ሁሉ ጠብመንጃ፣ ዱላ፣ ሜንጫ፣ ገጀራ እና ባልጩት ድንጋይ ተሸክመው በአንድ አካባቢ በቁጥር አንሶ የተገኘ ወገናቸው ላይ እጃቸውን ሲያነሱ እና የሚፈፅሙት ጭካኔ ሲታይ ለስጋ ያስፈራሉ፣ ለነፍስ ተገዳይ ህያው ሆኖ ገዳይ የሰማዩ እንዳለ ሆኖ በምድርም በቁም ቢሞትም። አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ ኮሽታ ሳታሰማ አብዝታ ወተት በምትሰጥ ላም ይመሰላል። በሌላ አገላለፅ በተለምዶ 'ባጃጅ' (ባለ ሦስት እግር ተሽከርካሪ) በተፃፉ ጥቅሶች ይኸርጎረጎራል። እንደ 'ሐመር' እና 'ኢንፊኒቲ' አይነት ዘመናዊ አውቶሞቢሎች አሠራራቸው በራሱ ውበት ስለሆነ እንደ ፈረስ ጋሪ ማስታወቂያ አይለጣጥፉም።

ይሁንና በአናሳ አስተሳሰባቸውና የሚከተላቸው መንጋ በአእምሮው እንዳያስብ ስለጋረዱት እነ 'ጎጤ' ውለው ሲያድሩ በሀገር ደረጃ የሚደቅኑት አደጋ ቀላል አይደለምና በአመለካከት መግራት በመንግሥት በኩል ቁርጠኝነቱ ካለ አደብ ማስገዛት ይቻላል። ምንም ይሁን ምን ለሽፍቶችና ቅጥረኞች የሚደነግጡ ቢኖሩ የኢትዮጵያን ህዝብ ማህበራዊ መሠረት የማይገነዘቡ ናቸው። በተደጋጋሚ እንደምንጠቅሰው ዘውጌዎቹ ቁጥራቸው እዚህ ግባ የሚባል አይነት ባይሆንም ሊፈጥሩ የሚችሉት አደጋና እየደቀኑ ያለው ስጋት የሚናቅ አይደለም። ስምሪቱ ከኢትዮጵያ ውጭ አድርጎ ስምሪት በሚሰጠው ዓለማቀፋዊ ኃይል የሚሽከረከሩ ቡድኖች ከኋላቸው ሉላዊ ገፊ ኃይል አላቸውና 'ይህቺ ባቄላ ካደረች አትቆረጠምም' ታሳቢ ማድረግ የግድ አስፈላጊ ነው። በመሆኑም በበቂ ስጋት ላይ በተንተራሰ የትንተ አግባብ ሀገርንና ወገንን ከዓለማቀፋዊ ደባ ለማዳን እጅለእጅ ተያይዘን በአንድነ መቆም ይጠይብቀናል። እንደ አበያ እና ፊጋ በሬ አጠገባችን ያለውን ነገ በከፋ በ



t.me/OLDBOOKSPDF

የሚደርስልንን እና ሀገር ብትወረር የምንተገንበትን ወገን ለማግኘት ከማሰብ ፈቀቅ ያለ የዕይታ አድማስን ማስፋት ይጠይቃል።

ትንሽ አለፍ ብለን ዙሪያ ገባችንን እንቃኝ። ደቡብ ሱዳን ያለማቋረጥ እየታመሰች ነው። የኤርትራ ጉርብትና ባልተቋጨ ጥያቄዎች ሳቢያ በፈገግታ የተጀመረ ቢመስልም የአጋምና ቀጋ ሁኔታ ውስጥ ነው። ሶማሊያ ቀስ በቀስ ወደ ደከም መንግሥት (Failed State) በመቀየሯ ለየትኛውም በሀይማኖት ሽፋን ለሚንቀሳቀስ ፅንፈኛ ቡድን መፈልፈያ ኩሬ ሆናለች። በሀገሪቱ ጥርኝ ብርኝ እያሉ የሚንቀሳቀሱ ፅንፈኛ ቡድኖች አል ሸባብ፣ አል ኢትሀድ እና ሌሎች ሁኔታውን ተከትለው ሊፈጠሩ የሚችሉ ቡድኖች 'ከዓለማቀፍ የሽብርተኝነት ትስስር መረብ' ጋር ተሳስረው ድጋፍ ለማግኘት አመቺ እድል አላቸው። ሱዳን በጎንደር ድንበር አካባቢ የምታሳየው የድንበር ለም መሬት ፍላጎትና በወያኔ ህወሓት የተደረገው ምሥጢራዊ ስምምነት የማይቀነው አደጋ ቀላል አይደለም። የጅቡቲ ወደብ ጉልበት ያላቸው ባእዳን መፈንጫ ሆኗል። ኬንያ በኢትዮጵያ ደረጃ ወጣ ገባ የሚል ሰላም ያላት ሀገር ናት። የግብፅ ዐይኖች ከኢትዮጵያ ላይ ለአፍታ ይነሳሉ ብሎ ለማሰብ የዋህነት ያልሆነ የበዛ ቂልነት ይጠይቃል።

ጎረቤቶቻችንን ከላይ በስጋት ሳይሆን በሥጋትነት ብንመለከታቸውም አለመጠርጠርም ዋጋ ያስከፍላልና በያዝናት ሀገር ልክ ጥንቃቄን ታዛ አድርገን እንዝለን። ዙሪያው ውሎ አድሮ የሚቀጣጠል የተዳፈነ ፍም መሆኑ የማይጠበቅ አይደለም። የሚቀጣጠለው ሰደድ እሳት ለከፋ ጉዳት ሳይዳርገን የአንድነት እሳት ማጥፊያ መላበስ ሁለተኛ አማራጭ አይደለም። ስለሆነም አእምሯችንን ሠፋ አድርገን ሉላዊነት እስከሚፈጥረው አደጋ ማማተር ይገባናል። ሆኖም የፍቅራችን ምክንያት ከሁኔታዎች ሁሉ በላይ የሆነው የኢትዮጵያዊነት ትርጉም ነው።

ወደ ሀገራችን ታሪክ ስንመለስ የአርኪዎሎጂ ጥናትና ምርምር ውጤቶችም ሆኑ በታሪክ ትምህርት መስክ የተደረጉ ፍተሻዎች እንደሚያመላክቱት ኢትዮጵያ በቅድመ ታሪክም ይሁን የታሪክ ዘመን ረጅም እድሜ ያስቆጠረች ሀገር መሆኗ የማይታበል እውነት ነው። ይሁንና ከታሪኳ ርዝመት አንፃር የዘመናት ጉዞዋ ሆነ ተብሎ ከ'ትኩስ ድንች' በሚመነጩ ተልዕኮዎች ወይም እድሜውን በመቀሸብ ከማሳጠር ጀምሮ በተለያዩ ዘንጎች ዙሪያ የማያባሩ እሰጥ አገባዎች ቀጥለዋል። በእያሌ ሁነቶችም አፈፃፀም ተንተርሶ በሚነሳው ንትርክ በታሪክ ምሁራን ዘንድ የወል ታሪካችንን ለመሰነድ የሚያስችል ወጥ እና የጋራ የሆነ ስምምነት ላይ አልተደረሰም። በሳንካው ምክንያት በሥርአተ ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱ የሌሎች የትምህርት አይነቶች የመማሪያ መፃሕፍት (1991 - 2018) በየወቅቱ ሲከለሱ፤ የታሪክ መፃሕፍት ግን በየደረጃው ማሻሻያ ሳይደረግባቸው በነበሩበት እንዲቀጥሉ መንስዔ ሆነዋል። ድባቡ



t.me/OLDBOOKSPDF

በፈጠረው ሙግት ላለመዘፈቅ እና ታሪክ ላይ የታየው የመንግሥት ጥላቻ ተከማምረው ዜጎች ለታሪክ ትምህርት ያላቸው ፍላጎት ቀዝቅዞ ተስተውሏል። በደምሳሳው ለወል አገልግሎት የሚውሉ የታሪክ ትምህርት መማሕፍትን ለማሠናዳት የተደረጉ ሙከራዎችም ፍሬ አላፈሩም።

ኢትዮጵያ በውጭ ግንኙነት የዘመናት ታሪክ ያስቆጠረች፤ የራሷ ሆሄያት፤ የገዳ ዴሞክራሲያዊ ሥርአት፤ የተለያዩ የዘመን መቁጠሪያ ዘዴዎች፤ ሀገር በቀልና ድንበር ተሻጋሪ እምነቶች፤ ኪነህንፃ፤ እደ ጥበብ፤ ስነፅሑፍ፤ ሥልጣኔ፤ ፍልስፍና፤ ቱባ ባህሎች፤ ምጣኔ ሀብታዊ ማህበራዊ ፖለቲካዊና ፊርጀ ብዙ መስተጋብሮች፤ ሁለንተናዊ ዓለምን አጀብ ያሰኙ ድንቅ አሻራዎች የተንናፀፈች ሀገር ብትሆንም ታሪኳ በጥቂቱ እንኳ በደርዝ አልተሰናዳም። በተለያዩ ዘውጎች ተመርኩዘው የተፃፉ የታሪክ ሰነዶችም ቢሆኑ በአወዛጋቢ ምልከታዎች የተሞሉ ናቸው። ባልተገባ የታሪክ አፃፃፍ ምክንያት ታሪኮቿ የወል ተቀባይነት እና ስምምነት በማጣታቸው ጥቂት የታሪክ ዝንባሌ ካላቸው ወገኖች በስተቀር ተነባቢ እና ተደራሽ አይደሉም።

በታሪኩ ዙሪያ ስምምነት መጥፋቱ፤ ለፖለቲካ ትርፍ ማጋበሻ መዋሉ፤ መነሻውም ሀገርን ማተራመሥ መሆኑ ተዳልበው ለምናየው ማህበረሰባዊ መከፋፋት (Social Bitterness) እና ምስቅልቅል የታሪክ የተዛቡ ትርክቶች የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳሉ። የውጡቱ አስከፊነት ታላቅ ማሣያ ኢትዮጵያን ለማፍረስ አለያም ከፋፍሎ ለመግዛት ያቀደው አካል በቀጥታ የትኩረቱ ማዕከል ያደረገው ከሀገሪቱ ሕዝብ ወደ 2/3ኛ የሚጠጉ የኦሮሞና የአማራን ማህበረሰብ በፍፁም አብረው መኖር እንዳይችሉ ለማድረግ (የአማራ እና የኦሮሞ ማህበረሰብ በደም እና በመንፈስ የተዋሀዱ እንደመሆናቸው እስከፍፃሜው መለየት ባይቻልም) በተከታታይ አበከሮ በመሠራቱ የኢትዮጵያውያንን አንድነት ለማጠናከር በሚሠራው ልክ የሁለቱን ወገኖች ትስስር ለማጥበቅ አበከሮ መረባረብ ይጠይቃል። ይህ ሃላፊነት በዋነኝነት በሁለቱ ክልሎች አመራሮች አስቻይ ሁኔታ ቢፈጠርለት ሀገር በአያሌው ታተርፋለች። በህወሓት፤ አነግና በአማራ እያቆጠቆጡ ባሉ ተገቢ ያልሆኑ ስሜቶች በየጊዜው እየሻከረ የታየውን ግንኙነት ለማደስለ ያላሰለሰ የአንድነት ትግል ያስፈልጋል።

(2016 - 2019) የተጀመረው የሁለቱ ክልሎች መሪዎች ቀና ግንኙነት (ቁርጠኝነታቸው ላይ ባለን ጥርጣሬ ምክንያት ገደብ ጥለን) የሁለቱም ህዝቦች መሪዎች ነሸጥ ሲያደርጋቸው 'ለማለያየት የሚሠራ አካል የመኖሩን' ሀቅ በአደባባይ ሲያፈርጡት መስማታችን ችግሩን መለየት የመፍትሔው ጅማሬ በመሆኑ አመስግነን፤ በሁለቱም ውስጥ በገፊ ሁኔታዎች ከምርቱ ጋር የበቀለውን እንክርዳድ እየለየን፤ ከላይ



t.me/OLDBOOKSPDF

በስሱ ለማንሳት እንደሞከርነው በጥልቀት ማስተዋል የሚጠይቀው ዓብይ ጉዳይ ሀገር የማፍረስ አጀንዳው ማከፋፈያ ማዕከል ከኢትዮጵያ ውጪ፤ ለግል ጥቅማቸው በችርቻሮ ተቀብለው የሚያስራጩት ደግሞ ውጭና በሀገር ውስጥ የሚኖሩ የተማሩ ማይማን መሆናቸውን ተገንዝበን ልዩ ትኩረት ልናደርግ የሀገር ጉዳይ ያገብረናል። ደባውን ሳይረዱ የተጃመሉ የተማሩ መንጋዎች በመተላለቃቸው እና በስሜት የሚነዳ ጀሌ ፈጥረው በመቆየታቸው እነዚህን የዋህ የሆኑና በስሜት ፈረስ የሚጋልቧቸውን ወገኖች የማዳን ተልእኮው እረፍት አልባ እንድንሆን ያስገድዳል። በርግጥ ከህሊና ሆድ እንዲቀድም የስነምግባር ደረጃ እንዲወድቅ በመሥራት፣ ረብጣ ዶላር በተሸጎጠለት ቁጥር ወገኑን አሳልፎ የሚሰጠው እንደሙበዛት፣ የጉዳቱን መጠን ተገንዝቦ ሆድ ህሊና ላይ እንዳይከመር ጠንክሮ መሥራት የማይታለፍ ይሆናል።

የታሪክ ሰበዞችን ከዚህ ንድፈ ሀሳባዊና ገቢራዊ ንጣፍ በመነሣት ጠማሩ አከራካሪ ባለመረዳት የዘመሙ በመምዘዝ የተጣመሙ፣ ያጋደሉ፣ የተዛቡ እና እውነታውን ዓመታት በከፋት በጥላቻ ዝንፈቶችን ለማቃናት ይጣጣራል። ፍልሚያው ለሃምሳ ቅጥፈት ያደነደነው በመሣሪያ እና በእቅድ ጥልቅ ጉድጓድ ቆፍሮ ተንጠራርቶ ከቆመ፤ በደረጃው ልክ የጠነከረ በህቡዕ አደረጃጀቶች ከደደረ ጎራ ጋር በመሆኑ አፀፋው ያለኃፍረት እንደ ገመሬ መሆን ይገባዋል። የጥላቻ ደጃገዛማቾቹ ሀገር ለማተራመሥ ኢትዮጵያዊነትን የያዘ የሀቅ ዝንጀሮ በየራሳቸው መንጋ ተከብበው ካልተሸማቀቁ፤ የሀገር ጀግኖችን ወኔ ሰንቆ ብእር የማይደፈሩ ብጉንጆችን ለማፍረጥ ላያሸልብ በውብ ታሪካችን ገላ ላይ ሳያመነታ ቆሟል። በመሆኑም የመዕለፋ አዘጋጅ ለማዕዳት ይንደረደራል።
የተለደፈውን ጭቅቅት በእንዶድ ሙልጭ አድርጎ

'የጥሮፓጋንዳ' (የቃላት በከፍተኛ መዋእለ ንዋይ እና በርግጥም ጠመዝማዛ ጉዘው ትንቅንቅ ውስጥ ማለፍን ጦርነት) ከሚታገዘ አጋንንታዊ ቡድን ጋር በሚደረግ ጠንቅቆ ይገነዘባል። የሚጠይቅ በመሆኑ መሰናከሉን መሻገር አልጋ በአልጋ እንዳልሆነ ይችላል። ሁሉም የዘመቻው ሴራ ከስብእና መንካት እስከ መስዋዕትነት ሊያስከፍል ከሀገርና ከወገን አይወዳደርምና 'ቆርቻ ቡዳ'ው እንደየአስፈላጊነቱ ባልተለመደ ሁናቴ ጠጣር አገላለፆችንና ያልተለመዱ ቃላትን ይጠቀማል። በታሪክ ሽብልቅ ቅጥፈትን ለመፈረካከስም ጀግኖ በአጥቂ መንፈስ ይታገላል።

የዛሬው ትውልድ ከተጋተውና የነገው ትውልድ ከተደገሰለት መርዝ የተበከለው በማርከሻ፤ የታቀደለት በ'ከትባት' መዳን አለበት። ውጥኑን ከዳር ለማድረስ መራራ እውነት በኢትዮጵያ ታሪክ የተሰኘ 'መፍትሔ ሥራይ' ተቀምሞ ተዘጋጅቶለታል። መድህኒቱን ጨርሶ የወሰደ ይፈወሳልና ለታሪክ ህሙማን እና ታሪክን ለሚያፈቅሩ ላምትወዷቸው ወገኖች ሁሉ ይህንን ጠጣር እና ማራኪ የታሪክ እንክብል በስጦታ



t.me/OLDBOOKSPDF

መልክ ጭምር ለወገን ማድረስ በርካታ ህይወት መታደግ ነው። ለምትሳሱለት ወገን ከዚህ የበለጠ ሥጦታ እንደሌለ ስንነግራችሁ በትህትናና በድፍረት ነው። የጊዜው ሁለንተናዊ ድባብ በጥልቀት ማሰብና ወደሌሎች በመዘርጋት ለወገን መድረስን አብዝቶ ይጠይቃል። ኃላፊነትን መወጣት ደግሞ ከህሊናም ከታሪክ ተጠያቂነትም ያድናል።

በታሪክና የፖለቲካ ፍላጎት በተሟገናቸው ሰነዶች ውስጥ በጉልህ እንደሚታየው የኢትዮጵያን ታሪክ በማነወር መስከ የ'ህዝባዊ ወያነ ሐርነት ትግራይ' (ህወሓት) እና የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) ልሂቃንን ያህል የከፋ ሚና የሚይዝ አለ ብለን አንወስድም። የሃፏቸው ዘውጎች ዓብይ ማእከል የሚያጠነጥነው 'የኦሮሞ በደል' የሚሉትን ማሣየት፣ መነሻ ትኩረቱ አፄ ምኒልክ ላይ አጠንጥኖ፣ መድረሻ ግቡ በኦሮሞና አማራ መሀከል ታላቅ ግጭት መፍጠርን ታሳቢ ያደርጋል። የግጭቱ (የጥሮገሮው)ጊዜአዊ ስኬቱ ከፋፍሎ መግዛት ሲሆን የመጨረሻና አደገኛ ዒላማ ያነጣጠረው ኢትዮጵያን ማፍረስ ላይ ነውና አጀንዳው ዓለማቀፍ ታላላቅ 'ስፖንሰሮች' እንደሚያገኝ ሳይታለም የተፈታ ነው።የሁለቱም ዘውገኛ ወገኖች የትርከት መነሻ፣ የትግራዩ አፄ ዮሐንስ ዘመን ማብቂያ (1889) እና የአፄ ምኒልክ ዘመን መጀመሪያ (1889) አንድ ዘመን ሆኖ ሳለ የአፄ ዮሐንስ አራተኛን የበዛ በደል ማንሳት አይፈልጉም። ጉዳዩ የአፄ ዮሐንስ ታሪክ የመሸፈን አለመሸፈኑ ሳይሆን ነጋ ጠባ አዬዬው (የሚያላዝኑትም ጭምር) በአፄ ምኒልክ ዙሪያ የመሆኑን እንቆቅልሽ መፍቻ ውሉን ያልተገነዘበው ወገን የጉዳቱ ሰለባ ከመሆኑ ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው።

የአኩይ ፖለቲከኞቹ መዳረሻዎች የኢትዮጵያን የዘመናት ታሪክ በ100 ዓመት ቀንበሎ የመላውን ጥቁር ኑባሬ መደምሰስ፣ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር አንድ ሆና እንዳትራመድ ማሽመድመድ እና የአፍሪካን ህብረት እስከማተራመስ ይዘረጋል። ከሕዝብ ብዛታቸውና ከሚኖሩቸው ተጽእኖ አንጻር የሴራው ትኩረት አምብርት ኦሮሞና አማራ ላይ እንደመሆኑ የመፅሐፉ አዘጋጅም የኢትዮጵያን ታሪክ ህመም ለመፈወስ በኦሮሞ አካባቢ ለሚነሱ የቀጭት ስሜቶች ተገቢ ትኩረት አድርጓል። በአማራው ላይ የተፈጸሙ መገፋቶችንም ዳስሷል:: የታሪክ እብደቱን ለማከም፣ የተተረተረውን ለመስፋት ጠንከር ያሉ ወስፌዎች፣ ጠጠር ካሉ አገላለፆች ጋር በገፆቹ ውስጥ እንግዳ አይሆኑም።

በፈጠራ ትርከቱ 'ተበደልሁ' ያለው ወገን የራሱ የቀድሞ እና የአሁን ጦር አበጋዞች ምን ያህል ግፍ እንደፈፀሙ ማስገንዘቡ ቆም ብሎ እንዲያስብ በማስቻል ረገድ አዎንታዊ ድርሻ ይኖረዋልና በፅሑፉ ውስጥ ተካትቷል። ሀቁ ሲገለጥ የሁሉም ወገን



t.me/OLDBOOKSPDF

አያቶች ያሰለዩነት በማያሻማ መልከ በጥንካሬውም ሆነ በድከመት የታሪኩ ዋነኛ ተዋናዮች ነበሩ። በዘመናት ለነበሩ ኀልቆ መሣፍርት የጥቡብ ውጤቶችና ድንቅ አሻራዎች 'አበጀህ የኛ ጀግና' ተብሎ የሚሞካሽና ሜዳሊያ የሚዘጋጅለት፤ ልዩ ገፀ በረከት የሚበረከትለት ወገን እንደሌለ ሁሉ! በታሪክ 'ደረሰ ለሚባለው ጥፋት ተጠያቂ የሚሆን አንድም ወገን ዛሬ የለም። የሚወቀሱ ቢኖሩም በዘመን ውስጥ ያለፉ፤ በህይወት ያሉ የአፄ ኃይለሥላሴ ዘመን ጥቂቶች፤ በዘመኑ ደርግ እና ዘመነ ወያኔ ጥፋት ፈፃሚው፣ የተጠየቁ፣ በመጠየቅ ላይ ያሉ እና የሚጠየቁ መሆናቸው አያከራከርም።

እውነታው ከዚህ ውጭ እንዳልሆነ እየታወቀ በባዶ ሜዳ ከማይመለከተው መጋጨት፤ ከትላንት ተበድሮ ዛሬን ለማበላሸት መከፋፋት ታሪክ ይቅር የማይለው ጅልነት ነው። ወደዚህ ምድር ሲመጣ ግለሰብም ሆነ ቡድን ሌላውን በሐር ጠልቶ በራሱ ምርጫ ከእናቱ ማህፀን፦

'ማል አባሺ' 'ወዲ ሰበይቲ' 'ዘራፍ'... በማለት በፉከራ ወጥቶ አልተከሰተም። ለአንተ፤ ለአንቺ፣ ለእኔ፣ ለእኛ፣ ለእሱ፣ ለእነርሱ፣ ለእነዚያ የዖታ ሁኔታ፣ የቆዳ ቀለም፤ የብሔረሰብ መገኛ፣ በሀገርና በመሣሠሉት አህዶች የመጀመሪያ ምርጫ እኛ ከቶውኑ ድርሻ አልነበረንም። በሂደት ሰው በምርጫው ፆታውን የቆዳ ቀለሙን ብሔረሰቡን ሀገሩን ሊቀይር ቢችልም 99.9 እጅ ለዛሬ መለያዎቻችን የኛ ድርሻ ምንም ነው። ሳንወለድ እነዚህን የመወሰን ምርጫ ቢሰጠን ኖሮ የሠለጠነ ሀገር፣ ሰላም የሰፈነበት ምድር፣ በሀብት የተንቆጠቆጠ አባት፣ በፍላጎታችን የምንመርጠው ፆታ እና ተከለ ሰውነት የዛሬው ባልሆነ ነበር። በዚህም ምክንያት በየት መጣችን ለመጋጨት የሚሆን አመክንዮ መነሻው ምንድነው? የሚለውን ቁልፍ ነጥብ መመርመር ያስፈልጋል።

በመቅድሙ እና በመግቢያው ውስጥ የተነካኩ ሐተታዎች መነሻ እና መድረሻ፤ አልፋ እና ዖሜጋ ለዓላማው ስኬት ታልሞ መፅሐፉ በአራት ምዕራፎችና በአጭር ማጠቃለያ ተቀንብቧል።

የመጀመሪያው ምዕራፍ፦ በኢትዮጵያ ታሪክ ምዝገባ ወቅት የታለፈባቸውን ሂደቶች በመተንተን በታሪክ አመዘጋገብ ዙሪያ ለሚነሱ ሙግቶች ምላሽ እየሰጠ ለመሄድ ይሞከራል።

ቀጣዩ ምዕራፍ፦ በወል ታሪካችን ውስጥ ልንኮራባቸው የሚገቡ ሰበዞችን ከብፌው መሀከል መርጦ ያሳያል። ሌሎች ሀገሮች ታሪክ ፈጥረው ሲኮሩ ኢትዮጵያ



t.me/OLDBOOKSPDF

የሠራቺውን ታሪክ ስታደበዝዝ ዝምታው ሀገርን ይጎዳልና። ከምዕራፉ ግብ አንፃር ለታሪክ ድክመቶች አልፎ አልፎ ካልሆነ ቁብ አይሰጥም።

ሦስተኛው ምዕራፍ፡- የኢትዮጵያን የፖለቲካ ታሪክ 'ታላቅ የጨለማ ዘመን' በስፋት ይዳስሳል። የመጨረሻው ምዕራፍ፡- አወዛጋቢና አሻሚ የታሪክ ገፆችን በየጊዜው በሚነሱ ጥያቄዎች ላይ ተመርኩዞ ጥበብና ሳይንስን በማሠናኘት ምላሽ ይሰጣል።

ማጠቃለያው፡- በአራቱ ምዕራፎች ላይ ተመስርቶ ታሪካችን እንዴት ይዘጋጅ? ጉድለቱን በምን አግባብ እናሟላ? በሚሉ አንኳር ነጥቦች በማጠንጠን ወደ አጭር መፍትሔ ያስጉዘናል። ምክንያቱም በሚነሱ ነጥቦች ዙሪያ በፅሑፉ ውስጥ ከጅምሩ እስከ ፍፃሜው በያንዳንዱ ትንተና መፍትሔዎች ተመላከተዋልና።

ማንበብ ከመጀመራችሁ በፊት፡- የእናንተ ያልነበሩ ሰዎች የጠቀጠቁባችሁንና ያጨቁባችሁን ሀሳቦች አውጥታችሁ በቀናነት በንፁህ ህሊና ነጥቦቹን በጥምና በመመርመር ወደ እውነታው ለመድረስ ጣሩ። በፍለጋችሁ በፅሑፉ ውስጥ የተጣመመውን አቃንታችሁ፣ የተወላገደውን አስተካክላችሁ፣ የተዛነፈውን አርማችሁ እና በጎደለ ሞልታችሁ ታነበቡ ዘንድ በላቀ ትህትና ተጋብዛችኋል።

'ቀና መሆን ወጪ ከሌለው ሰው ለምን ከፉ ይሆናል?'

ታየ ቦጋለ አረጋ

ኢልመ ደሱ ኡዳ



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አንድ

## የኢትዮጵያ ታሪክ አጻጻፍ ጥናት (Historiography)

የኢትዮጵያ ታሪክ አፃፃፍ ጥናት በሀገራችን የታሪክና የፖለቲካ አውድ አለቅጥ አሻሚ አከራካሪ አጨቃጫቂ እና የንትርክ ምንጭ ሆኖ ቀጥሏል። ውዝግቡን በሰለጠነ አመክንዮ ሀሳቦችን አፋጭቶና ከማስረጃና መረጃዎች ጋር አመሳከሮ አልባት ለማስቀመጥ በምሁራት ዘንድ ዳተኝነት ይታያል። ዝምታውን ለመስበር ባለመቻሉ ታሪክ በቆመበት አምድ መሠረት የመፍትሔ ቁልፍ መሆን አልቻለም። ከመተከሉ በተፃራሪ የጥላቻ ምንጭ፣ የግጭቶች መነሻ፣ የመከፋፋት ማህደር፣ በልዩነት የሚሰነጠቅ አከርማ ወደ መሆን ደረጃ አሽቆልቁሏል። ውጤቱም ኢትዮጵያን 'አኬልዳማ' የደም መሬት አያደረጋት ተስተውሏል። በመደበኛም ሆነ በኢመደበኛ መድረክ በታሪክ ዙሪያ የሚደረጉ ውይይቶች እና ጭውውቶች የሚቋጩት ባለመግባባት ነው። የልዩነቶቹ ድንበር የሚፈጠረው በሀሳብ ልዕልና ላይ ሳይመረኮዝ በብሔረሰባዊ መልክ ስለሆነ አሳሳቢነቱን በበለጠ አደገኛ ያደርገዋል። የመንጋ ፍላጎት ምክንያትን ሲደፍቅ ሰውነት ስፍራ ያጣል።

በመሆኑም ይህ ምዕራፍ የታሪክ ምንጮችን ምንነት፣ በአዘገጃጀት ታሪክ አፃፃፍ ሂደት የታለፈባቸውን ደረጃዎች፣ የተለያዩ ዘውጎች ፀሐፊዎች ልዩነትና የመነሻቸውን



t.me/OLDBOOKSPDF

ምክንያት፣ የታሪክ ግብአቶች ሆነው የሚያገለግሉ ምንጮችን፣ የታሪክ ምሁራንን ምልከታ እና መሠል ዘንጎችን እያወሳ ጉድለቱንም ሆነ ጥንካሬውን በጥንቃቄ ለማሳየት ይንደረደራል። በመሆኑም በንባባችን ወቅት የታሪክን ጉድለትም ሆነ ጥንካሬ ለመፈተሽ ጥልቅ ምልከታ ያሻል። ወደ ይዘቱ ከማለፋችን በፊት በዘውጌ ልሂቃን መሪነት፦ 'ታሪክ ወደ ሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ባጠቃላይና ወደ አማራ ብሔረሰብ ታሪክ በተለይ ያደላል'፣ 'ታሪካችን የብሔረሰቦች መጨቋቆን ታሪክ ነው'፣ 'ታሪካችን የጦርነት ታሪክ ነው'፣ 'ታሪክ የሞቱ እና የማጭት ምንጭ በመሆኑ ቢቀርስ?'፣ 'ታሪካችን ምሉዕ አይደለም'፣ 'ታሪካችን የተዛባ በመሆኑ የኢትዮጵያ ታሪክ ነው ለማለት ይከብዳል' የሚሉና ሌሎች መሠል ቅሬታዎች ይንፀባረቃሉ። ንትርኮቹ ውሀ የማይቋጥሩ ናቸው ወይስ ተአማኒነት አላቸው? በጥልቀት መፈተሽ ያስፈልጋል።

## ታሪክ ምንድነው?

የሰው ልጅ በእያንዳንዱ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ እና የእምነት አውዶች ዙሪያ ያደረጋቸው መስተጋብሮች እጅግ በጣም በርካታ እና ውስብስብ በመሆናቸው ተቆጥረውም ሆነ ተዘርዝረው የሚያልቁ አይደሉም። አንዳች ሳያስቀሩ በሙሉ መመዝገብ ልቅም አድርጎ የሰው ልጅ ያለፈባቸውን ውጣ ውረዶች አይቻልም። ጉልቆ መሣፍርት የሌላቸውን የታሪክ አውዶች ይቅርና ዋና ዋና ታሪካዊ ፍፃሜዎችን የሰው ልጅ ከትቦና ደጉሶ አላኖራቸውም። አብዛኛው የዓለማችን ክፍል ለረጂም ዘመን የፅሑፍ ክህሎትን ባለማዳበሩ፣ በቀደመው የታሪክ ወቅት ታሪክን ሰንዶ የማኖር ፍላጎት እምብዛም ስለነበር እና በመሰል ምክንያቶች የዓለም ማህበረሰብ ታሪክ አብዛኛው ክፍል አልተጠመረም።

እስካሁን የተደረጉ ጥናቶች ውጤቶች ላይ ተንተርሰው ከተገኙ መረጃዎች ስንነሳ ታሪክን ለመጀመሪያ ጊዜ የዛሬ 3,000 ዓመት መመዝገብ የጀመሩት ቻይናዎች ናቸው። ለጥቆ የምዕራቡን ዓለም ታሪክ በመፃፍ የመጀመሪያ የሆነውንና ምዕራባውያን "የታሪክ አባት" በማለት በሰየሙት ሄሮዶቱስ እና ተከትለው በመጣው ቱሲዲደስ አማካይነት በተሻለ አኳኋን የመሰነድ ቡቃያ ጀምረዋል። በዓለም ታሪክ በዘመናዊ እና በሳይንሳዊ ዘዴ ታሪክን ተንትኖ የመፃፍ ልምድ ዘለግ ያለ እድሜ ያላስቆጠረ ሲሆን፣ በኢትዮጵያ ደረጃም በሀገር ውስጥ ታሪክን በጥልቀት ማጥናት የተጀመረበት ጊዜ



t.me/OLDBOOKSPDF

ከ1960ዎቹ "የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም /Institute of Ethiopian Studies" ከመመሥረቱ ጋር ተያይዞ እውን እንደሆነ መረዳት ይጠቅማል።

ታሪክ ምንድነው? የሚለውን ፅንሠ ሀሳብ ለመበየን ምሁራን የተለያዩ ትርጓሜዎች ይሰጣሉ። ይዘቶቹ ሲጨመቁ:- ታሪክ:- የሰው ልጅ ባሳለፋቸው ረጂም ዘመናት ውስጥ በተወሰነ ጊዜ (ዘመን)፣ ቦታ፣ የአኗኗር ዘይቤ የተፈፀሙ ክንውኖች በምን አኳኋን፣ እንዴት ባለ አውድ፣ ለምን ዓላማ፣ በእነማን አስተባባሪነትና ተባባሪነት እንደተፈፀሙ፤ ቢቻል ታሪካዊ ማስረጃዎችን በማጣቀስ፤ ባይቻል የተሰበሰቡ መረጃዎችን በማገላበጥ እና በሚጠናው ድርጊት አቅጣጫ ከተገኙ ሌሎች ሰነዶች አኳያ በማመሳከር ወደ እውነታው ለመድረስ የሚጥር ነው።።

እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገሮች ደግሞ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተወራረሱ የተላለፉ የቃል መረጃዎችን (ትውፊቶችን) ጭምር በድምሩ (Sources) በመመርመር፤ በጊዜ ቅደም ተከተል ከራሞት (Chronology) አማካይነት በአድማኢ አንጋፋ ከሆነው ወደ ቅርብ ጊዜ በመሰደር፤ በታሪክ ትምህርት ጥበብና የአጠናን ሳይንሳዊ ዘዴ ላይ ተመሥርቶ አሳማኝ በሆነ መንገድ በተቻለ አቅም ከአድልዎ እና ወገንተኝነት፣ የፖለቲካ ፍላጎት፣ የቡድን ስሜት፤ ጥቅምና ሽፍጥ በፀዳ ሁኔታ ሚዛናዊነትን ገንዘብ የጋራ፤ ዓላማ ላይ በመመሥረት (Objectivity) እና ተጨባጭ አድርጎ፤ በትምህርቱ ዓላማ ላይ በመመሥረት ተደራሲውን /አንባቢውን ታሳቢ አድርጎ ጠቀሜታዎች ላይ አማትሮ፤ በመጨረሻም ተደራሲውን /አንባቢውን ታሳቢ አድርጎ ውበት ባለው ቀለል ያለ ቋንቋ (Presenting facts on paper) የሚቀርብ ፊርጂ ብዙ የሰው ልጅ ትላንትና (Past) ላይ የተመሠረተ የትምህርት ዘርፍ ወይም የጥናት መንገድ ነው።

ታሪክ:- በዘመናት ኑባሬ ውስጥ የሰው ልጅ በማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ምጣኔሀብታዊ፣ ፖለቲካዊ ፍልስፍና እና መሠል ሁነቶች በተለያዩ ሠፋፊ አህዶችና ዳራዎች ያደረጋቸው ፊርጂ ብዙ መስተጋብሮች እንዲሁም በየጊዜው አፈር ላይ ያሳረፋቸው አሻራዎች (ኪነጥበብ፣ ኪነህንፃ፣ ስነጥበብ፣ እደጥበብ፣ ሙዚቃ፣ ጥበብ፣ ፍቅር፣ አብሮነት፣ መዋሀድ፣ መገፋፋት፣ መዋዋጥ ወዘተርፈ ከአነስተኛ የሰው ልጅ አኗኗር ዘይቤ ፍራፍሬ ለቀማና አደን (የሰብአ ትካት ደረጃ) ተነስቶ ሥልጣኔ እስከ ደረሰበት፤ በየቅፅበቱ የሚፈለሰፍ አጀብ ያሰኘ የዘመናዊው ዓለም ውስብስብ ሙያዊነት፣ ምጥቀትና ርቀት፤ ባለፈው ዘመን ላይ ተመርኩዞ የሚጠና ሳይንስም ጥበብም ነው። የጥናቱ ዋነኛ ትኩረት ዛሬን ማሳመር፤ ዕይታው ትላንት ላይ ያነጣጠረ ነው።



t.me/OLDBOOKSPDF

## የታሪክ ትምህርት ዓላማ

በታሪክ ትምህርት ጥናት ውስጥ ታሳቢ የሚደረጉ ሦስት ዋነኛ አምዶች አሉ። እነዚህ ዋልታዎች በትላንት፣ ዛሬ እና ነገ መሀከል አይነተኛ ጥምረት ፈጥረው የማህበረሰብን ጉዞ ለማቀላጠፍ ወሳኝ ድርሻ ይይዛሉ። በታሪክ ትምህርት ጥናት መሠረት በማህበረሰብ እድሜ ጠገብ ጉዞ የተከናወኑ ድርጊቶችን በመመዝገብ የተባ ፍተሻ አድርገው የበሰሉ ጠማሮች ካቀረቡልን የምሁራን የጥናትና ምርምር ሥራዎች በመነሳት ታሪክ የሚከተሉት መሠረታዊ መዳረሻዎች አሉት።

ያለፈውን ለማጥናት፡- ሰው ትላንቱን ካላወቀ ነገ ወደየት እንደሚሄድ በቅጡ አይረዳም። ትላንትን ካልተገነዘበ ከእርሱ ቀድመው የነበሩ መሪዎችና ማህበረሰቦች የፈጠሯቸውን ስህተቶችን በመድገም ይኳትናል። ጉዞው እንደ ዓሊ እርምጃ ቀርፋፋ ይሆናል። የተገነባውን ከማፍረስ አዙሪት ተላቅቆ፤ በቆየው መሠረት ላይ እየካበ ካልቀጠለ ዘወትር ጀማሪ ይሆናል። እድሜ ልኩን ሲወጥን ወደፊት መራመድ ሲገባው ከኋላ ስለሚጀምር እንቅስቃሴው አዝጋሚ ሆኖ በአብዛኛው ሂደት ባለበት ይረግጣል። የታሪክ ጥናት ካለፉ የሰው ልጅ ድርጊቶች መሀከል ጥንካሬዎችን በመመዝገብ የበለጠ ለማጎልበት፤ መልካም ግንኙነቶችን ለማሻሻል፣ በጎ እሴቶችን ወርሶ ለማስተላለፍ፤ ጥበቦችን ቀስሞ ለመጠቀም፤ ከድሎች ጀግንነትን ተረክቦ ወኔን ለመሰነቅ፤ በታሪክ ውስጥ የዘመናት ማንነቱን ለመፈለግ ይረዳዋል።

ያለፈውን በማጥናት ፍተሻ ውስጥ ደካማ ጎኖች የማይጠበቁ አይደሉም። መነሳትና መውደቅ፣ ጥንካሬና ድክመት፣ ርህራሄና ጭካኔ፣ ለጋስነትና ንፉግነት፣ ጨለማና ብርሀን፣ ማሸነፍና መረታት፣ ሰሜን ዋልታና ደቡባዊ ዋልታ በተለያዩ አቅጣጫዎች በተፃራሪነት የቆሙ፤ ተቃርኖዎቹ የእድገትና የመኖር ፍርቱናዎች ናቸው። 'ዓለም የተቃራኒዎች ውጤት' ጥምር እንደመሆኗ መልካሙን ይዘን፣ መጥፎውን እየከላን እንጓዛለን። ትላንትናን በጥሞና መመርመር ስህተቶችን ላለመድገም በአያሌው ያግዛል። በምንም መንገድ ትላንትን የምናጠናው ጥላቻን ለመቀስቀስ፣ ግጭቶችን ለማራገብ፣ ቁስሎችን ለመነካካትና እንዳይድኑ ለማመርቀዝ አይደለም። ታሪክን ለጥፋት ለልዩነት እና ለመከፋፈያ የሚጠቀሙበት የፖለቲካ ቁማርተኞች እና የህዝብ ጠላቶች ብቻ ናቸው። በየትኛውም የሰለጠነ ዓለምና የዘመናዊነት አሳቢ ታሪክ ለግጭት በሚያገለግል አግባብ አይታኝም። የኢትዮጵያ የፖለቲካ ዐሐፊዎች መሠረታዊ ድክመት ለፖለቲካ ትርፍና ጊዜያዊ ፍላጎት የትናንትናን መልካም ጎን

በማግዘፍ ትውልድን ከማዳን ይልቅ ቀዳዳዎቹን የበለጠ ሸንቁሮ በማስፋት ለሀገርና ወገን ጉዳት ሃላፊነት በጎደለው ሁናቴ አጣምመው ለጥፋት ማዋላቸው ነው።

ዛሬ የታሪክ ትምህርት ዓላማ ሁሉንም አጠንክሮ የቆመበት አምድ በመሆኑ ለድርድር አይቀርብም። በትላንት መስታወትነት ዛሬን በጥሩ መሠረት ላይ ማነፅ የታሪክ ትምህርት እምብርት ነው። የታሪክ ጥናት ትላንትን የሚመረምረው ዛሬን ለማስዋብ፣ ለማሣመር፣ ለማሻሻል እና ከትላንት ከፍ ባለ የፍቅርና የተግባር ልዕልና ለመኖር ነው። ትላንት የሚመረመረው ለዛሬ የማይቆረቁር መደላድል ለማመቻቸትና የተሠሥሩ ገመድ የሚጠብቀው የችግሮቻችንን እንቆቅልሽ ለመፍታት በሚያስችለን አኳኋን ነው። ስለሆነም ዛሬ በጠንካራ አለት ላይ መታነፅ ይገባዋል። ውጤቱ ዛሬን ማበላሸት የሆነ፣ የምንኖርበትን ምዕራፍ ለማመሰቃቀል የሚከወን ተግባር ሁሉ ታሪካዊ መሠጠት ሳይሆን ፖለቲካዊ ግልሙትና ተደርጎ ይወሰዳል። ከዚህ አኳያ በታሪክ ስም የሚደረጉ ሽፍጦችን ለማስወገድ የመረረና የከረረ የሀሳብ ትግል ሊደረግ ይገባል። ዛሬ የትላንት ውጤት እንደመሆኑ ከህፀፆቹ መማር ከቻልን፣ መልካም ገፅታዎቹን ለማደርጀት ከታደልን፣ ፀጋውን ማጣጣም የምንችልበት አመቺ የመጫወቻ ሜዳ ይፈጥርልናል።

በዚህ ምድር ላይ የምንኖርበት የማይደገም እድል አንድ ጊዜ ብቻ ነው። ይህንን አጭር ዘመን በአማዛኙ ከ20 ዓመት እድሜ እስከ 60 ዓመት የ40 ዓመታት ውጤታማነት ብለን ልንወስደው እንችላለን። የተረፈው ሲታኝ ጅማሬው (ከ0 እስከ 20 ዓመታት እድሜያችን) ከአካባቢያችን ጋር የመላመድና የመለማመድ፣ ከታላላቆቻችን የመማር፣ ዝንባሌያችንን የመፈለግ፣ የሕይወት ራዕይን የመሰነቅ፣ በድምሩ አጠቃላይ የዝግጅት ምዕራፍ ነው። ፍፃሜው (ከ60 እስከ ህይወታችን ማብቂያ ) በአመዛኙ የተካበ ልምዳችንን፣ ተሞክሯችንን፣ ርጋታና ጥበባችንን ይዘነው እንዳንቀብር ከልጅ ልጆቻችን እና ልጆቻችን ጋር መልካም ወግ እያወጋን፣ ለመንግሥት አቅጣጫ እየጠቆምን፣ የመፍትሔ እንጂ የችግር አካል ሳንሆን፣ ማህበራዊ ትስስርን ለማደርጀት የምንሠራበት ቢሆን አብዝቶ ይመከራል።

በሀገራችን የሚታየው ድባብ ግን ከዚህ በተቃራኒው እየሆነ ነው። ጉድጓዳቸው የተማሰ ልጣቸው የተራሰ አዛውንት የራሳቸውን ዘመን በመናከስ አሳልፈው የወጣቶችን ዛሬና ነገ፣ የመጪውን ትውልድ አኗኗር ሊያበላሹ በስተርጅና ሲውተረተሩ ማየት ያሳፍራል። በ1970ዎቹ አጋማሽ ሰደድ፣ ኢህአፓ፣ መኢሶን፣ ኢዲዩ፣ ማገብት /ህወሓት ደም ሲያንገራቀኝሩ የኖሩ አዛውንቶች ዛሬም በጥፋት መንገዳቸው መቀጠላቸው ቁጭት ይፈጥራል። በአንፃሩ በጅምላ ላለመኮነን ከዛው



t.me/OLDBOOKSPDF

ትውልድ የተገኙ ትላንትም ዛሬም ለወገን መድህኒት ለመሆን የሚተጉት በከበሬታ ወንበር ሊቀመጡ ይገባል። ይህ ድጋሚ የማይገኝ የእድሜ ፀጋ ለራሳችንም ሆነ ለሌሎች ልንኖርበት የሚቻረን እንደመሆኑ የኑሮን ትርጉም ተረድተን ፀጋውን ለማጣጣም ራሳችንን እድለኛ ለማድረግ ሰው ለመሆን መትጋት ይገባል። በደመ ነፍስ መንቀሳቀስ ሰው የተፈጠረበት ዓላማ አይደለም። ዛሬ በትላንት አልፎ ወደ ነገ የመሸጋገሪያ ድልድይ ነው። የመተሣሠሪያውን ህብር ያፀኑ ሀገሮች ከፍታ ማማ ላይ ቆመው ነገን አሻግረው ሲያማትሩ፤ በትላንት ቆዝመው ዛሬን ያበላሹ ሀገሮች ደግሞ ለከፋ ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ውድመት፤ ለማይተካ ሰብአዊ ሀብት ኪሣራ እና ለዓለም ጭምር የአዘቦት ተረክ ሆኗል። ዘርፈ ብዙ ምስቅልቅሎች ተዳርገዋል። ጥላቻን ዘርተው ሰቆቃና ሞትን ማጨዳቸው

ነገ ያልኖርንበት፣ የኛ ሊሆንም ላይሆንም የሚችል፤ ላፈራነው ትውልድ እና ለሚቀጥለው ተረካቢ አሻግረን በርቀት የምናማትርበት የጊዜ አንድ ገፅታ ነው። ነገን ከወዲሁ የማያመላክት ድንግዝግዝ የታሪክ ጉዞ ጎዶሎ ነው። ትላንትና እና ዛሬ በመናበብ ከተሰናሰሉ ያለጥርጥር መጪው ጊዜ ደማቅ ብርሀንን እና ብሩህ ተስፋን አዝሎ ይመጣል። የሰው ልጅ ዘር የመተካት ዋነኛ ፍላጎት ትውልዱን ለማስቀጠል ያለው የበዛ መሻት ነው። በመሆኑም ለልጆቹ የማወርሰው ሀገር ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ካልሰጠ ጉዞው ሰዋዊ ሳይሆን ደመ ነፍሳዊ ነው። ደመ ነፍስ ለእንስሳት የተተወ ነው። ሰብአዊነት የሰው ልጅ ዋነኛ ማንነት ነው። ነገን በይሆናል ድንግዝግዝ ሳንሸብበው በተሻለ እርግጠኝነት እንድናሸጋግረው ዛሬን የሙጥኝ ብሎ መጣጣር የሰውነት የውዴታ ግዴታ ነው። አንድ ፀሐፊ የሚከተሉትን ስንኞች አሰፈረ፡-

"ትላንትና አትበል፥ ያለፈ ነውና

ነገም ደግሞ አትበል፥ ያንተ አይደለምና

ዛሬን ግን ሥራበት፥ ተሰጥቶሀልና"

ጸሐፊው መሻቱ ስለትናንትና እናስብ አለማለቱ መሆኑ ቅቡል ነው። ማስተላለፍ የፈለገው መልእክት ትላንት አልፏልና ባልኖሩበት ዘመን እየተባሉ የሚኖሩበትን ማበላሸት መረገም ነው ለማለት ፈልጎ ይመስላል። ቀጥሎም ከብዙ የሚከታተሉ ነገሮች በአንዱ ታልፍና ቀጣዩን ነገ ዐታየውም እያለ የዛሬን አስፈላጊነት እያፀና ነው። ትጋፈጠው ዘንድ የተሰጠህ ዛሬ ነውና ዛሬን አሳምር እያለ የቆሙባትን ቀን አስፈላጊነት እያስረገጠ ነው። ሲደመደም ታሪክ ጠቀሜታው ዛሬን በተዋበ ዓለም ውስጥ ለመኖር ነውና በፍፁም በፀጋው በተጨመረልን ቀን እንደራደር። በታሪክ ትምህርት ዓላማ



t.me/OLDBOOKSPDF

ውስጥ እንደ ሠንሰለት በተያያዙት ሦስት እንኳር ይዘቶች ትላንት ዛሬና ነገ መሀከል ያሉትን ነጥቦች ማያያዝ የመኖር ቁልፍ ቅኔ ነው።

በታሪክ ትምህርት ዓላማ ላይ ተመሥርተን ዛሬን ለማደርጀት በየትኛውም የውይይት ወቅት በታሪክ ዓላማ ዙሪያ በተገቢው መንገድ ግንዛቤ መጨበጥ እጅግ በርካታ እርምጃዎች ወደፊት ይወስደናል። በታሪክ ትምህርት እሴቶች መገባባት ያለውን የላቀ ፋይዳ ከግምት አስገብቶ ፍሊጋችን እንደሚከተለው ቀርቧል። ሀገሮች የታሪክን በጎ ገፅታ አጉልተው፣ አግዝፈው፣ አግዝፈው፣ አግልተው በድራማ ቲያትር፣ ፊልም፣ የካርቱን ምስል፣ ዐውደ ርእይ/ ኤግዚቢሽን፣ የፓናል ውይይቶች፣ ሐውልቶች እና እአምሮ ምስል፣ ዐውደ ርእይ/ ኤግዚቢሽን፣ የፓናል ውይይቶች፣ ሐውልቶች እና አእምሮ ውስጥ ሰርፀው ለረጂም ጊዜ በሚቆዩ ዘይቤዎች ያቀርባሉ። ጠቀሜታው ትውልዱ ልእለ ሰብእ ከሚላቸው ተምሳሌቶቹ ወኔ ሰንቆ፣ ዛሬን በአሸናፊነት ስነልቡና እንዲጀግን አብዝተው ለማስቻል ነው።

የኢትዮጵያ የታሪክ አካሄድ በተቃራኒው ከ1970ዎቹ ጀምሮ ለትውልዱ ስብራት፣ የስነልቡና ድቀት፣ ፍርሀት፣ ወኔው የላሸቀ ትውልድ ለመፍጠር፣ በምሬት የታጀለ ህሊና የያዘ ወጣት ለማፍራት የታለመ እንደመሆኑ፤ ግድ የለሽ የሆነ ትውልድ በብዛት በመፍጠር ረገድ ተስተካካይ የለውም ብንል ግነት አይደለም። የታሪክ ግድፈቶች በተቻለ አቅም ሳይዘለሉ በዘመን መነፅር ተቃኝተው በስሱ መቅረባቸው (ከግድፈት መማር) አስፈላጊ መሆኑ አሌ አይባልም። በታሪክ ውስጥ የተፈጠሩ ችግሮችን ስሜት እና ትላንትን እንከን አልባ እንዳይነሱ አጉል የመከላከል (Patronage) በመሆኑ አያስተምርም። ስህተቶችን አድርጎ ማቅረብም በስህተት የተሞላ አካሄድ ከሌላው ሊማር እድል በማያገኝበት እንኳን ትላንትና ባልሰለጠነው ዓለም እንኳ ከሌላው ሊማር እድል በማያገኝበት ወቅት ቀርቶ ዛሬም አማላይ ተሞክሮዎች በበርካታ ሀገሮች ሞልተውልን ልምድ ቀስመን መሻሻል አልቻልንም። ትላንትን እየወቀስን እኛ ዛሬ በአራ. ታሪክ እንኳን ተሰምተው የማይታወቁ ጀሮን ጭው የሚያደርጉ ዘግናኝ ድርጊቶች ከመፈፀም አለመታቀባችን በግላጭ ዕየታየ ነው።

የትላንቱ ትውልድ ሕፃናት ልጃገረዶችን ጠልፎ ግዳይ እንደጣለ 'ሆ እያሆሆ ማታ ነው ድሌ' በማለት ከባላጋራዎቹ ተናጥቆ እንዲት ጨቅላ 'መማረኩ' እንደ ጀግንነት ተቆጥሮ ጥይት ይንጣጣለት፣ በሆታ ይዘፈንለት፣ ለወግ ለማዕረግ ሽማግሌ ተልኮ እንደ መከበሪያ ይቆጠርለት ነበር። በቅርቡ ሴት ልጅን መማረዝ የሥ-ነምግባር መለኪያ ተደርጎ ሲወሰድ እናውቃለን። ዛሬ ሁለቱም ድርጊቶች በማኅበረ-ሰቡ የተወገዙ ነውሮች፤ በሕግ የሚያስጠይቁ ወንጀሎች ስለመሆናቸው በሕግ ተደንግጓል። ከልምዶቹ በጊዜ ሂደት መወገዝ ተነሥተው የወጡ ሕጎች ለቀጣዩ ትውልድ መልካም



t.me/OLDBOOKSPDF

አስተማሪዎች ናቸው። ለምሳሌ:- ሠለጠነ በሚባለው ዓለም ፊት ለፊት በሕግ ጭምር ታግዞ በእኛ ሀገር ውስጥ ውስጡን ከተፈጥሮ ጭምር የሚጋጩ የግብረ-ሰዶማዊነት ድርጊቶች እንደ ሰደድ እሳት እየሰፉ ነው።

ውሎ አድሮ የሚመጣው ትውልድ ከተፈጥሮ በተቃራኒ የሚያደርገው ሩካቤ ዘር ሲያሳጣው፣ ትውልድ ማስቀጠል ሲሳነው ወይም በአንዳች ህሊናዊና ተፈጥሯዊ ምክንያት ድርጊቶቹን ኮንኖ ሕጋዊ ከልከላ ሊጥልባቸው ይችላል። የአንድ ዘመን ነውር በሌላ ዘመን ክብር፤ የአንድ ወቅት ጀግንነት በሌላው ዘመን ውርደት እየሆነ ታሪክ ቀጥሏል። ከዚህ አንፃር ታሪካዊ ክስተቶችን በየዘመኑ አስተሳሰብ ደረጃ መገዳኖ፣ ተፈፅመው ቢሆን እንኳ ታሪክ ተበድረው ለሚሰቃዩ መፍትሔ ይሆን ዘንድ በይቅርታ መከደን አስቸጋሪ አይደለም። ችግሩ በመከፋፈል የሚያተርፉ የፖለቲካ ቁማርተኞች በደል በሕልባት እንዲዘጋ አለመፈለጋቸው ነው። ሙሾ አውጪ ሁልጊዜ ሞት ቢኖር፤ ዱላ ሻጭ ዘወትር ጥምቀት ቢኖር አትራፊ እንደሚሆኑ ሁሉ ዘውጌዎች የሰዎች ዋይታ ሰቆቃ እሪታ ሰደት መፈናቀል ስቃይ ለእነርሱ የኑሯቸው መሠረት ነው።

ሰው እንደ ዕቃ ይሸጥና ይለወጥበት ከነበረበት የባሪያ አሳዳሪ ማህበረሰብ ጀምሮ የእያንዳንዱን ሰው ሙብት ለማስጠበቅ እስከተወሰዱ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች የዘለቁ እርምጃዎችን ሂደት በመመርመር ካለፈው መማር ቀጣዩ ጊዜ የሰው ልጅ ያለእንከን ነፃነቱ ይጠበቅ ዘንድ ትግል እንዲደረግበት የማንቂያ ደወል ነው። በዓለማችን ተሞክሮ በትላንት ታሪክ በደለኛ የሚሆኑት በዘመኑ የነበሩ የድርጊቱ ተዋናዮች ናቸው። በቀጥታ ከበደል ፈፃሚዎቹ የተወለዱ ልጆቻቸው ጭምር በወላጆቻቸው ጥፋት ተጠያቂ አይደሉም። የናዚ ወንጀለኞች ልጆች ዛሬ በጀርመን ውስጥ ተዘልለው እየኖሩ ነው። በወላጆቻቸው ድርጊት በማፈር በህሊናቸው ይፀፀቱ ካልሆነ በስተቀር የተጠያቂነት ገደብ አይጣልባቸውም።

ሩዋንዳ በ1994 በተደረገው የዘር ጭፍጨፋ ምክንያት የከፈሉትን ዋጋ በቁጭት ከመግለፅ በስተቀር ተዋናዮች ሆነው በዘመናችን ቆመው ያልተጠየቁ እያሌ ናቸው። በየዓመቱ ሁሉም ሩዋንዳዊ በፀፀት እለቱን እያወሳ በታሪካዊ እብደቱ እብዝቶ ያዝናል። የአፍሪካ መሪዎችም አልቂት ያረገዘ ደመና በህገራቸው ሰማይ ሥር አርግዞ 'ወግ አይቀርምና' ጉንጉን አበባ ለማስቀመጥ በየዓመቱ ወደ ሩዋንዳ ያቀናሉ። ሩዋንዳ ከቁስሏ ተምራ ስለብሔረሰብ ትንፍሽ ማለት እንዳይቻል የሚያደርግ ህግ አውጥታ ተግብራለች።

አፍሪካ በራሱ ደርሶበት እስኪጠበስ ለብሔረሰብ 'ደርቢ' እያሟሟቀ ነው። ደቡብ አፍሪካ (1948-90) የሠፈነውን የአፓርታይድ ሥርአት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ



t.me/OLDBOOKSPDF

ዘግታ ነጭና ጥቁር ያውም ከነበደላቸው በአርቅ በፍቅር ድህረ 1990 የጥላቻን ጉድጓድ ደፍነዋል። የኢትዮጵያ አኩይ ልሂቃን በተቃራኒው እነሱም ሆነ የተደጡ ትውልዶች የኖሩበትን የፍቅር ዘመን ገፍተው፤ ያልኖሩበትን ትላንትና ከምናብ ዓለም ተውሰው ሲናከሱ መመልከት ያሳቅቃል። እንኳን መቶ ዓመታት ላለፈው ድርጊት ይቅርና አሁን ባለንበት ዘመንም ዘግናኝ ወንጀል የፈጸሙ ባለስልጣኖች በድርጊታቸው የሚጠየቁት ግለሰቦቹ እንጂ ልጆቻቸው፤ የጎሳቸው አባላት ወይም እነሱ የተገኙበት ብሄረሰብ አባላት ሊሆኑ አይችሉም፡፡

ሲጠቃለል ከታሪክ ትምህርት ዓላማ የማይቀዳ፣ ዛሬን በመልካም ምሠሦ የማያፀና፣ የመከፋፈል የጥላቻ የልዩነት የበደል የሴራ የደባ የተንኮል የሽፍጥ የቁርሾ የቂም በቀል ፅሑፍ በሙሉ ፖለቲካዊ ሸፍጥ እንጂ ታሪክ አይደለም። የከፋ የፖለቲካ ግልሙትና መሆኑን ለማወቅ ግን ፍልስፍና ሳይጠይቅ ይደረስበታል። ለሀገር እድገት የማይጠቅም፤ የትውልድን አእምሮ ጉልበት ገንዘብና ወርቃማ ጊዜ የሚያባክን፤ የሀገር እድገት፣ ሰላም እና ብልፅግና ፀር፤ ንፁሐን ወገኖችን በደም አበላ ለማጥመቅ ተጠንስሰ ጠላትነትና የከፋ የበታችነት ደዌ የወለደው፤ ከሙያዊነት ያፈነገጠ የዘመን መጋኛ የፖለቲካ ደባ ነው። መነሻው ለግል ጥቅም፣ ርካሽ ዝና፣ የጥቂቶችን ፍላጎት ለማሟላት የተበጠበጠ ገዳይ መርዝ ነው። ፅሑፎችን ደግሞ የቡዳ መድሀኒት 'ቅርቻ ቡዳ'። ሰቀጣዮቹ ከፍሎች የተቀመጡ ትንተናዎችን በአፅንዖት ለማየት አብረን እንዝለቅ።

## የዓለም ተሞክሮዎችና ተግዳሮቶች

የሰው ልጅ የተሻለውን ፍለጋ የሚያደርገው ጉዞ አያቋርጥም። ከተሻሉት ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር ትምህርት መቅሰም፤ ከግድፈቱ ነቅሶ በመማር ከጥፋት መዳን ይቻላል። በመሆኑም ታሪክን በዓላማው መሠረት የተጠቀሙበት ያገኙትን በረከት፤ ከታሪክ ጥልፍልፍ መታረም ያልቻሉ ደግሞ የፀፀትን ዋጋ እየከፈሉ መሆኑን ለማሳየት የተወሰኑ አብነቶችና መገለጫዎች ተመርጠዋል።

ለህያዋን ፍጥረታት ህመሞች የተሻሉ መላዎችን ለመዘየድ ጠቢባን ያለማቋረጥ ምርምሮችን ያደርጋሉ። መፍትሔ ይሆናሉ ያሏቸውን መድሀኒቶች ለሰው ልጅ ካላቸው ክብር የተነሳ በቀጥታ ንዑዱ ሰው ላይ አይሞከሩም። አይጥ ጥንቸልና ሌሎች ምሣል እንስሳትን የሙከራቸው መፈተኛ በማድረግ ፍቱንነታቸው እስኪረጋገጥ ተደጋጋሚ ጥረት ያደርጋሉ። ሰዎች ላይ የሚሞከሩ ፈዋሾች ሊያስከትሏቸው የሚችሏቸው የጎንዮሽ ጉዳት በየጊዜው እየተመዘነ ማሻሻያ ይደረግበታል። ዘመን



t.me/OLDBOOKSPDF

እየሥለጠነ ሲመጣ እንኳን የከበሩን ሰዎች ይቅርና የእንስሳት መብት ተሟጋቾች ቁጥር ስንኳ በየጊዜው እየተበራከተ ሄዷል።

በ2019 በምዕራባውያን የተዘጋጀው የወባ ህመም ከትባት ባደጉ ሀገሮች ዜጎች ላይ ሳይሆን በደቡብ አፍሪካዊቷ ሀገር ናሚቢያ ላይ ሊተገበር መሆኑን ስንሰማ አብዛኞቻችን አማራጭ የለንም። የወባ ህመም ያደጉ ሀገሮችም የሚጋሩት ችግር ሆኖ ሳለ አፍሪካ ላይ መሞከሩ ሲታይ ከመፍጠር ወደ ኋላ ቀርቶ ተቀባይ የመሆንን ህመም ከብደት እንመዝንበታለን። የማህበረሰብ ችግሮች በባህርያቸው ውስብስብ እና የረቀቁ በመሆናቸው የመፍቻ ብልሀቶቹም የዚያንው ያህል ጥልቀት ያለው ፍቱን የሚሹ ናቸው። ኢትዮጵያ ሀገራችን የረጅም ጊዜ የመንግሥት ምሥረታ፣ የገዳ ሥርአት ልምምድ፣ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ እና የአብሮነት እሴቶች ያላት ቢሆንም፣ እንዳለመታደል ሆኖ (1991-2018) ከዓለም ተሞክሮዎች በአይጥ በጥንቸል በጦጣ ዝርያዎች በላቦራቶሪ የሚሞከር ያይደለ የዘመነ ተሞክሮ የተረጋጋ መንግሥት ካላቸው ሀገሮች መውሰድና መጠቀም ሲቻል ሆነ ተብሎ ከፋፍሎ የመግዛት (Divide and Rule) የቅኝ ግዛት አይነት አገዛዝ ሥርአት በመመሥረቱ ዛሬ ለተፈጠረው ሀገራዊ ቀውስ መንስዔ ሆኗል።

ኢትዮጵያም በመንታ መንገድ አጣብቂኝ ቋፍ ላይ ቆማለች። ይህ ወቅት ከምንም ጊዜ በላይ ሰከን ብሎ ነገሮችን በርጋታ ማየትን ይጠይቃል። በስሜት ፈረስ ከመሥገር ወጥቶ አካሄዳችን የት እንደሚያደርሰን በጥሞና ማየት ያሻል። ስለሆነም ሀገራችን ካላት 100ሚሊየን በላይ ህዝብ ስነልቡና እና የዘመናት ልምዱ ጋር የትኛውን መንገድ መከተል ይሻላል? የሚለው ሀሳብ በብዙዎቻችን ህሊና የሚመላለስ በመሆኑ ለአስተማሪነት የሚከተሉት ተመርጠዋል።

### አሜሪካ

ባለንበት የሉላዊነት (ግሎባላይዜሽን) ዘመን ከልዕለ ኃያላን አንዷና ቁንጮ ለመሆን ያስቻላት ዘዴ ምሁራን እንደሚሉት፦ 'አሜሪካ ጉንፋን ሲይዛት ዓለም የሚያስነጥሰው' /'When America coughs, the rest of the world sneezes' የተባለው መላውን ዓለም በብዝሀነት ማካተቻ (Diversity Visa/ DV) አጣጥማ መመንደግ የቻለችበት ብልሀት፤ ዋሺንግተን ዲሲ ብቻ መቶሺህ ገደማ ኢትዮጵያውያን የመኖራቸው፣ ሚኒሶታ በአሥርሺህዎች ኢትዮጵያውያን



t.me/OLDBOOKSPDF

የከተሙበት፤ ሜሪላንድ በተመሣሣይ በአስር ሺህዎች ኢትዮጵያውያን የሚኖሩበት ምሥጢር፤ ዓለም ወቅያኖሶችን አቋርጦ ወደዚያች 'አዲስ ዓለም' የሚተምበት ሳቢ ምክንያት፤ ቅኔው የታመቀው በተወሰኑ እሳቤዎች በመሆኑ ነው።

አሜሪካ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ እና ለወታደራዊ ዝግጁ ከምትሰጠው ሥፍራ ባልተናነሰ ለታሪክ (ዜግነት) ትምህርት ቁልፍ ቦታ ትሰጣለች። በትምህርቱ ሥርአት ውስጥ ታሪክ እስከ ዩኒቨርሲቲ ድረስ በሁሉም የትምህርት እርከን የላቀ አፅንዖት ተችሮት በትውልዱ ህሊና ውስጥ እንዲሰርፅ በትጋትና በተከታታይ ይሠራል። ይህ ልምድ በኢትዮጵያም እስከ ዘመነ ደርግ የቀጠለ ሲሆን በሁሉም የትምህርት ዘውጎች ዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች ውስጥ 'የኢትዮጵያ ታሪክ ቅኝት' እንደ አንድ ኮርስ ይሠጥ ነበር።

በታሪክ ጠኋ የህወሓት አገዛዝ ለመጀመሪያ ጊዜ ልምዱ እንዲቀር ሆኗል። ምንም እንኳ "የስነዜጋ እና የስነምግባር ትምህርት" ቢዘረጋም በውስጡ ስነምግባርን ያላከተተ፤ በኢፌዴሪ ህገመንግሥት ላይ የበዛ ትኩረት የሚያደርግ ሆኖ ሳለ ይህም ፍሬ እንዳያፈራ ተማሪዎች የሚማሩት የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ እንዲሁም ሌሎች መብቶችን መሬት ላይ በተግባር የማያዩቸው በመሆኑ ሳቢያ ትምህርቱ ዋጋ አልባ ከመሆን አላመለጠም። በመሆኑም በደርግ ሥርአትና በአጼ ኃይለሥላሴ ከዚያም ቀድሞ የነበረው ያ የአድዋ ትውልድ ፍቅር ደበዘዘ። ያለጥርጥር በሀገር ፍቅር ጥልቅ ስሜትም ሆነ ስነምግባር ከወያኔ ትውልድ ጋር ሲነፃፀር (ለማወዳደር በሚያስቸግር አኳኋን) የቀደመው በአያሌው የመጠቀ እንደሆነ የሚመሰከሩ ሚሊየን ህያዋን አሉ። የተተከለው መርዝ በየሥፍራው በኢትዮጵያ ታሪክ ተሰምተው በማይታወቁ አረመኔያዊ ድርጊቶች ራሱን ገልጧል።

አሜሪካን ስንመለከት በትውልድ 'የልቡና ውቅር' ውስጥ እንዲሠርፁ መንግሥት አበክሮ የሚለፋባቸው ሦስት የማይታለፉ የማዕዘን ድንጋዮች አሉ። በንድፈ ሀሳባዊ ንግግሮቹ እና ገቢራዊ ትግበራዎቹ ዙሪያ በሀገረ አሜሪካ ድርድር አይደረግም። እነዚህን በቀጥታ ወስዶ በሀገራችን አለመተግበር ከ'መከሸፍ' አይተናነስም። የመጀመሪያው፦ 'አንድ ከሆንን እንቆማለን፤ ከተከፋፈልን እንወድቃለን' (United we stand, divided we fall!) የሚለው መርሆ ነው። በየትምህርት ቤቶች ውስጥ መፈከሩ በጉልህ ይታያል። ከታዋቂው የ"ሲኤንኤን / CNN" ቴሌቪዥን ጣቢያቸው እስከ ግዙፉ የዓለም የፊልም ኢንዱስትሪያቸው 'ሆሊውድ' በአንድነታቸው ዙሪያ



t.me/OLDBOOKSPDF

አይደራደሩም። ጥበቦቻቸው አንድነትን ህብረትን መያያዝን ያንፀባርቃሉ። 'አንድነት ሁልጊዜም ኃይል ነው'፡፡

ሁለተኛው፡- 'አንድነታችንና ሕገ-መንግሥታችን ለዘላለም' / 'Our unity and the constitution forever' ሲሆን ልብ ብለን ካስተዋልነው አንድነቱ (Unity) በድጋሚ በጉልህ ተሰምሮበታል። አሜሪካ ውስጥ የዘጎቿ የትመጣዎች ብዙ ናቸው፡- 'ስፓኒሽ - አሜሪካን'፣ 'ፖርቹጊዝ - አሜሪካን'፣ 'አፍሪካን - አሜሪካን'፣ በካውካሶይድ (ነጭ)፣ ሞንጎሎይድ (ቢጫ)፣ ኔግሮይድ (ጥቁር)፣ ቀይ (ቱውቶኒክ)፣ ክልስ (ክለርድ) ... በስፋት አሉ። በአሜሪካም ቢሆን መለያየቶችና የዘረኝነት አዝማሚያዎች በተለያዩ ዳራዎች ጥርኝ ብርኝ ማለታቸው አሌ ባይባልም አንድነቱ ከልዩነቱ በላይ ጎልቶ እንዲወጣ ስለሚሠራ ዘረኝነቱን በወፍራም ከንዱ ለመደቆስ አስተማማኝ አቅም ተፈጥሯል።

ሁለተኛው የማዕዘን ድንጋይ ሕገ-መንግሥታቸው በሚጀምርበት ዓቢይ መልእክት ተጠናክሯል። ለዘመናዊ ሕገመንግሥታት መነሻ የሆነው የ1981 የአሜሪካ ሕገ መንግሥት መነሻ መሪ አንቀፅ (Preamble) ውስጥ፡- "ስለ ተዋጣለት (... a more perfect Union...) ሲታይ አንድነታቸው የተቀመጠ ሐረግ ህገመንግሥቱን ለአንድነት የቆረጠ ጠንካራ አገላለፅ ያቀፈ ሆኖ እናገኘዋለን። "ውህደት" የአሴታቸው ቃልፋና ምሚጋ እንዲሆን ተደንግጓል። የአሜሪካን ህገመንግሥት ቃላት ህጋዊ ውበት ያላበሰው ቶማስ ጀፈርሰን ከእንግሊዝ ጥገኝነት የተላቀቁበትን የአሜሪካ የነፃነት አዋጅ 'American Declaration of Independence' (1776) በወርቃማ ብዕሩ በጉልህ ማድመቁ ታይቷል።

ይህ ለአሜሪካ ሕገ-መንግሥት በር ከፋች የሆነ አዋጅ፡- "ሁሉም ሰው ከማይጣስ ከማይገሰስ በሕይወት የመኖር የነፃነትና ደስታን የማጣጣም ፀጋ ጋር በእግዚአብሔር እኩል ተፈጥሯል።" በማለት ይጀምራል። ቶማስ ጀፈርሰን ከ1789 - 1797 ከመራው የመጀመሪያው የአሜሪካ ፕሬዚደንት ጆርጅ ዋሺንግተን እና ከሁለተኛው ፕሬዚደንት ጆን አዳምስ (1797 - 1801) ተከትሎ ሦስተኛው የአሜሪካ ፕሬዚደንት በመሆን ከ(1801 - 1809) አሜሪካን መርቷል። መነሻቸው በመለያየት መንፈስ እንደ አፈዴሪ 'ህገ መንግሥት፡- "እኛ ... ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች" በማለት በመለያየት ርጉም መንፈስ ሳይሆን እኛ የአሜሪካ ሕዝብ" ("We, the People of the United States ...) የሚለውን የመሠረት ድንጋይ ነው። አሜሪካውያን



t.me/OLDBOOKSPDF

በጥምና ከስተዋልነው ሕዝቦች (Peoples) ላለማለት እጅግ ተጠንቅቀው ሕዝብ (People) በማለት ለአንድነት ያላቸውን ዋጋ አስምረውበታል።

የበለጠ አፅንዖት ሰጥቶ ለማሳየት፡- የ1995 የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢፌዴሪ) ህገመንግሥት የሚጀምረው አንድነትን በሚያላና በሚያፈርስ በከፍፍል ሐረግ ነው። ገና በመግቢያው፡- "እኛ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ህዝቦች..." ማለቱ ሰው ሁሉ ከዛፍ አልተላጠም፤ እያንዳንዱ ሰው የየራሱ የትመጣ አለውና (በዘሩ፣ ጎሳው ወይም ብሔረሰቡ የሚያፍር ጤነኛ አዕምሮ የያዘ የሰው ፍጡር የለም) ችግር ባልሆነ ነበር። ይሁንና ብሔረሰብን የማስቀደሙ ተልዕኮ የሚመነጨው ከሴራ በመሆኑ አጥብቆ ይኮነናል። ብሔረሰብ ከሰውነት ከዜግነት ከሀገር የሚቀድም ስላልሆነ የዓለም ተሞክሮ እንደሚያሳየን በከፍፍል የሚጀምር ህገመንግሥት ውጤቱ አይሰምርም።

ኢትዮጵያዊነት የሁሉም በመሆኑ ጎልቶ በመጠራቱ ኦሮሞነትን፣ ትግራይነትን፣ አማራነትን ወይም ከምባታነትን አያከስምም። እኛ ሰው እንጂ ብሔረሰብ አይደለንም። እኛ ሙስሊም፣ ክርስቲያን ወይም ዋቄፈና ነን። እኛ አማራ ኦሮሞ ሲዳማ ነን። እኛ ወንድና ሴት ነን። እኛ የብሔረሰባችንን ቋንቋ ላንናገር እንችላለን። እኛ ከሁለት ከሦስት ከዐራት ብሔረሰቦች የተገኘን ሚሊዮኖች ተገድደን አንዱን ብሔረሰባችንን እንድንክድ ተደርገናል። እኛ በሀይማኖት ከሌሎች፣ በብሔረሰብ ደግሞ ከነዚህ ከተለዩ ሌሎች ሰዎች እንስናኛለን። በፆታ ደግሞ ከተለዩ ሌሎች ምድቦች ጋር እንገናኛለን። አንድ የሚያደርገን ሰውነት ዜግነት ኢትዮጵያዊነት ሀገር "አንድ ህዝብነት" ነው። አንድ ህዝብ ነን ማለት ፆታችን ቀለማችን ሀይማኖታችን ጎሳችን የፖለቲካ ልዩነታችን ተጠቅልሎ ይዋሀዳል ማለት አይደለም። የተለያዩ ምግቦች ባህሎች ቋንቋዎች በውስጣቸው ያሉ ድምፆች (የመላውን ዓለም ድምፅ ስለሚወክሉ) በምንም የማይለወጡ ውርሶቻችን ናቸው።

ችግሩ ልዩነትን ለማለያያ ማዋሉ ነው። በሃያ አንደኛው ክፍለዘመን ከኢትዮጵያ ውጭ አስተሳሰብ እንጂ ብሔረሰብ መነሻ ሆኖ ፓርቲ የሚቋቋምበት ሀገር ሰምተን አናውቅም። የሠለጠነው ዓለም ብቻ ሳይሆን የአፍሪካ ሀገራት ህገመንግሥታትም የብሔረሰብ አደረጃጀትን ይከለክላሉ። እውነታውም ሲታይ በብሔረሰብ ከተደራጀ ቡድን ጋር መግባባት አይቻልም። ዶክተር ዳኛቸው አሰፋ በአንድ ታዋቂ ንግግራቸው፡- " ጭቅጭቅ ሰለቸኝ። አሁን አሁን ሰው ሲጠጋኝ መጀመሪያ የምጠይቀው አንድ ወሳኝ ጥያቄ አለ 'ብሔር ነህ ዜጋ' እለዋለሁ። ለምን እንደሆነ



t.me/OLDBOOKSPDF

ታውቃላችሁ? ከብሄር ጋር መግባባት አስቸጋሪ ነው።" ሲሉ የብሔረሰብ አደረጃጀት ምን ያህል ዴሞክራሲን እንደሚያቀጭጭ ዐሳይተዋል።

አሜሪካ በስምምነት በተደነገገው ህገመንግሥታቸው ላይ ተመርኩዞ የወጣው የወል እሴታቸው በታሪክ ትምህርት የዜግነት አምድ በመጠናከሩ ከ27 ጥቃቅን ማሻሻያዎች በስተቀር መሠረታዊ የይዘት ለውጥ ሳይደረግበት የተረጋጋ ሀገርና መንግሥት እንዲኖራቸው አድርጎ እስካሁን ዘልቋል። በዚህም የተነሳ የአሜሪካኖች የአንድነት ፍልስፍና ጠቀሜታው የጎላ በመሆኑ የሥጋት ሳይሆን የህብረታቸው ምንጭ ሆኗል። የፖለቲካ ፓርቲዎቻቸው የተረጋጋ አካሄድ እንደምን ባለ ሁኔታ እንደተደራጁ ጁድሰን ኢል. ጀምስ፡- "American Political Parties" በተሰኘው መጽሐፉ ዘርዘር አድርጎ አስቀምጦታል። 'በአሜሪካ የመድበለ ፓርቲ ሥርአት ሳይሆን የሁለት ፓርቲ ውድድር (Two-party competition) ልምድ ህግ መኖሩ ጠንካራ ፉክክር ሥርአት እንዲኖር የተሻለ እድል ፈጥሯል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ከደቡቡ ክፍል በመጣ ፍላጎት ምክንያት ሦስተኛ ፓርቲዎች (Third Parties) እንዲደመጡ የማድረግ ዝንባሌ አለ። ይሁንና ፓርቲዎቹ የአባላቱን የስነልቡና እርካታ ከማስፈን አልፎ ተፅዕኖ ፈጣሪዎች አይደሉም። (ገፅ 40 -48) ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ የአሜሪካ ህገመንግሥትና ህጎች ትኩረታቸው የተሻሉ የአሠራር ሥርአቶችን በመዘርጋት ህዝቡን የማገልገል ፍላጎት ላይ እንደሚያተኩሩ ነው።

በኢትዮጵያ ሁኔቴ በርካቶች ካዳበሩት የዘመናት የሥልጣን ጠኔና ከበዛ ድህነት በመነጨ ከ100 ፓርቲዎች በላይ የመኖራቸው ዜና ሲሰማ አለመጠን ያሳቅቃል። በመሆኑም ከዚህ የበዛ ቡራቡሬ የሥልጣን ጥማት ለመላቀቅ በአመለካከት ለውጥ ዙሪያ ብዙ መሥራት ያሻል። ይበልጥ የሚያሸማቅቀው መንግሥታት ሥልጣን ላይ ለመሟዘዝ ባላቸው ፍላጎት ቁጥራቸውን ወደ ሦስትና አራት ማውረድ ያለመፈለግ ዝንባሌ ማሣየታቸው ነው። ምክንያቱም ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ያለመኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድ ምርጫ ጣቢያ 14 ተወዳዳሪ ስለሚቀርብ 'ገዢው ፓርቲ' ከመራጮቹ 15% ድምፅ ብቻ ቢያገኝና 85እጁ ባይመርጠው 'የበለጠ ቁጥር ያገኘው ሁሉንም ጠቅልሎ ይወስዳል / First would pass in the post election system' የምርጫ ሥርአት 'ዘላለማዊ ሥልጣን ያቀዳጀኛል' በሚል ግልብ ስሜት ለፓርቲው የሥልጣን ጥማት ማሳኪያ የቀመሩት የስግብግብነት መንፈሳቸው የፈጠረው የስልጣን ጠኔ የፈጠረው ነው። 'የተመጣጠነ ውክልና / Proportional Representation የምርጫ ሥርአትን የሚከተሉ የበርካታ ሀገሮችን የተሻለ እና



t.me/OLDBOOKSPDF

ለሀገራችን የሚበጅ ዴሞክራሲያዊ ተሞክሮ ሥልጣንን ርስተ-ጉልት ላደረጉ አምባገነኖች አይመቻቸውምና አልተከተሉትም።

ከዚሁ ጋር አሜሪካ ዜግነት የምትሰጥበት የአፈር ሕግ - 'Jus Soli' የላቲን ቃል ወደ እንግሊዝኛው ሲመለስ (Law of the soil) :- ማንኛውም ሰው በአሜሪካ የብስ፣ የአየር እና የባህር ክልል ከተወለደ ዜግነትን ያጎናፅፈዋል። አተገባበሩ በሰውና በሀገር (አፈር) መሀከል ያለውን ቁርኝት እጅግ በጣም ያጠናክረዋል። ብሔረሰቡን፣ የትመጣውን፣ ዘውጉን በመፈለግ፣ ሰው ከሰውነት የዜጋ ደረጃው ተነስቶ አይቃትትም። ሀገር ማለት ከብሔረሰብ ደረጃ ሰፋ ያለ ህዝብ፣ አፈር፣ መንግሥትና ሉዓላዊነት ያካተተ ሰፊ ነው። በድምሩ የአንድነትና የሀገመንግሥት ቁርኝት አሜሪካ የተረጋጋ መንግሥትና ህዝብ እንዲኖራት አስቻይ ሁኔታ ፈጥሮላታል። ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ሀገሮች (Low Income countries) ገና በደም አስተሳሰብ ደረጃ ላይ ስለሚገኙ 'Jus Sanguins የደም ህግ (Law of the Blood) መከተላቸው ሁልጊዜም ከደም የመጣበቅ ዝንባሌ ላይ ያቆማቸዋል። ይህም ሀገርን እንደ ትርፍ ዕንዲያዩ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል።

ሦስተኛው የመሠረት ድንጋይ:- 'ፈጣሪ የሚያግዛቸው ለመለወጥ የሚፍጨረጨሩትን ነው ይላል።' (The Lord helps those who help themselves):- አፅንዖት የሚችረው ጉዳይ ቁጭ ብሎ ከሰማይ መና እንደማይወርድ በመግለፅ የሥራ ባህልን የማበረታታት የማዕዘን ድንጋይ ነው። 'ትልቁ መፅሐፍ' 'ሲሠራ የማይወድ አይብላ' ሲል መደንገጉና ለሰው ልጅ የተሰጠው ርግማንና በረከት:- "በወዝህ ጥረህ ግረህ ብላ" ከወሬና ተራ ቧልት ይልቅ ወደ ውጤት ለውጥ ትጋት እንዲያተኩሩ አግዟቸዋል። ትምህርቱም ሆነ ገንዘባቸው ላይ ፈጣሪን ማኖራቸው ከነውስንነቱ ለትንሣኤያቸው ሳያግዛቸው አልቀረም።

የአሜሪካ ልምድ ሳንከፍልበት ብዙ ያስተምረናል። አሜሪካ ውስጥ በ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ሁለት የማይታረቁ ማህበረ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሥርአቶች ነበሩ። ሰሜኑ በጣም ተራማጅ፣ በፈጣን ለውጥ የታጀበ፣ የአንድነትን ጥቅም የተረዳ፣ ወደ ኢንዱስትሪ ቀልጣፋ ሽግግር ጡዘት ውስጥ የገባ፣ በስኬት የታጀበ፣ በዓለማችን የመጀመሪያ የሆነውን ፌደራላዊ ሥርአት ለመዘርጋት በጀገኑ የለውጥ መሪዎች የተሞላ፣ የባርነት አያያዝን እጅግ የሚጠየፍ አወቃቀር ነበረው። የደቡቡ አወቃቀር ደግሞ ከዚህ ፈፅሞ ተቃራኒ እና ኋላቀር ዘይቤን የሚከተል ነበር። የጥጥ የሸንኮራ አገዳ እና በቆሎን ጨምሮ በባሪያ ጉልበት የሚያመርት ባልሰለጠነ የአስተራረስ ዘዴ የሚጠቀም፣ በኢትዮጵያ ውስጥ እንደ ዘመነ መሣፍንት የጎተ አስተሳሰብ



t.me/OLDBOOKSPDF

የተንሠራፋበት፤ ባለሀብት ርግጥ አይነት በቀንድ አውጣ ጉዞ የሚጓዝ ነበር። ሁለቱ እጅግ ተፃራሪ የሆኑ ሥርአቶች በአንድ ሀገር ጥላ ውስጥ የማይታረቁ ሆነው መቀጠላቸው አዳጋች የሆነበት ደባብ ተፈጠረ። የልዩነቶቹ መነሻት ያለቅማቸው የለውጥ ሐዋርያት በሰሜኑ ክፍል ተፈጠሩ።

የመለወጥ ፍላጎት ቁራጥ መሪ ሲያገኝ በስኬታማ ድሎች ይታጀባል። 16ኛው የአሜሪካ ፕሬዚደንቱ አብርሀም ሊንከን ገና ሴናተር ሳለ ሀረ ባርነት እንዲወገድ ፈርጠም ብሎ አስቀምጦ ነበር። ዘግይቶ ለፕሬዚደንታዊ ውድድር ሲቀርብ ከተመረጠ ከሚወስዳቸው እርምጃዎች የመጀመሪያው ባርነትን ከአሜሪካ ምድር ማጥፋት ስለመሆኑ በአስገራሚ ንግግሩ አስረግጦ ገልፆት ነበር። ከንግግሩ ይዘት ጎልቶ የሚታየው፦ " አሜሪካ ግማሽ ነፃ ግማሽ ባሪያ ሆና አትቀጥልም። አሜሪካ ከፍፍሉ አከትሞ በአንድ ጣራ ስር ግዛቱ ነፃ ሊሳው ባሪያ ሆና አትራመድም። ከፍፍሉ አከትሞ በአንድ ጣራ ስር ትቀሀዳለች እንጂ" በማለት ከተገንጣዮቹ የኮንፌደሬት መንግሥታት ግትር ፍላጎት የተለየ የአንድነት ፌደራላዊ መንግሥት አቋም ለድርድር እንደማይቀርብ ግልፅ አድርጓል። እንደ አሜሪካ 'ያልተፃፈ ህግ' በሌሎች ዴሞክራሲያዊ ሀገሮች በሙሉ ድርድር አስፈላጊ እና በህዝብ እንጂ በፓርቲ ወይም ግለሰብ ፍላጎት የሚወሰን ጉዳይ አለመኖሩ የዴሞክራሲ ሀሁ ሆኖ በአንድነት ዙሪያ ግን የማይሸረሸር አቋም እንዳለው ዐሳይቷል።

ጠጣር ንግግሩ የአካባቢ ገዢነት አጉል ስሜት ለወጠራቸው ጠባብ 'የደቡቡ ክፍል የአካባቢ ገዢነት ስሜት ለተጠናወተው ባሪያ ገዢ ፊንጋዮች' የሚዋጥላቸው አልሆነም። ገና ፕሬዚደንት ሆኖ በ1861 ነጩን ቤተ መንግሥት ተረከቦ መንበሩ ላይ ሲሠየም አስራ አንዱ የሰሜን አሜሪካ ደቡባዊ ግዛቶች ጊዜ ሳያባክኑ በጀፈርሰን ዴቪስ ፕሬዚደንትነት 'ኮንፌደሬት ስቴትስ ኦቭ አሜሪካ' መመሥረታቸውን አወጁ። ደቡብ ካሮሊና ቅድሚያውን ወሰደች።

ሃያ ሁለቱን የሰሜን ግዛቶች በመያዝ የሠላሳ ሦስቱ የአሜሪካ ግዛቶች መሪ የነበረው አብርሀም ሊንከን የአሜሪካን አንድነት ለማስጠበቅ ጦርነት ብቸኛው አማራጭ መሆኑን በማመን የከተት ነጋሪት አዋጅ ጎሰመ። ይህንን ተከትሎ ከ1861 - 1865 በዘለቀው የአሜሪካ የእርስ በርስ ጦርነት (American Civil War) ከሰሜኑ 360,000 ከደቡቡ 260ሺህ በድምሩ 620ሺህ አሜሪካውያን ህይወታቸውን አጡ። አሜሪካኖች ጦርነቱ ከተጠናቀቀ በኋላ የደረሰውን እልቂት በግዛቶች ወይም ከልሎች ደረጃ አውርደው በህዝብ መሀከል ጠላትነት ለማስፈን አልተጠቀሙበትም። ይልቁኑ 'ለአንድነት የተከፈለ መስዋዕትነት' በማለት መራራውን ትውስታ ለህብረታቸው



t.me/OLDBOOKSPDF

ማጠንከሪያ ተጠቀሙበት እንጂ። በድርድር ሜና በመፍጠር በግጥና በተለያዩ ዘዴዎች ግዛቶችን በመጨመር በአጭር ጊዜ ከ33 ወደ 50 ግዛቶች አደጉ።

የዓለም ሀገሮች የተገነቡት በኃብቻ ድግሥ በመተቃቀፍና በፍቅር ታሪክ ሳይሆን ለውህደት በተከፈለ መራራ መስዋዕትነት (ባይሆን መልካም የነበረ) ብዙ ደም ገብረው ነው። በዓለማችን የሀገሮች እና የመንግሥታት ምሥረታ ጠመዝማዛ መንገዶችን አልፎ በመስዋዕትነት የተገነባ ነው። ጦርነት በምንም ሁኔታ ይካሄድ መስዋዕትነት ያስከፍላል። ሆኖም በምዕራፍ አራት እንደምንመለከተው የአጼ ምኒልክን ያህል "አባት ሆንሃለሁ፤ ልጅ ትሆነኛለህ" በማለት አብዛኛውን ቦታ በሰላም አስገብሮ በጣት የሚቆጠሩ ሥፍራዎች ላይ ብቻ ተዋግቶ፤ ሀገርን ከቅኝ ገዢዎች ተናጥቆ፤ ህዝብን ከባርነት ቀንበር አላቅቆ፤ ታላቅ ሀገር የገነባ መሪ በዓለም ታሪክ ውስጥ አናውቅም። የሀገሮች ውህደት ያስከፈለውን ዋጋ ከድረገፆች ብንበረብር ብዙ የሚነገረን ጉዳይ አለ። እውነታን በጥላቻ ትርክት ማደብዘዝ ይቻል ይሆናል፤ እስከመጨረሻው መቅበር ግን አዳጋች ነው።

የአሜሪካኖች ሌላው ብቃት እንኳን ያሸነፉበትን የድል ታሪክ ይቅርና የተሸነፉበትን የቪዬትናም ጦርነት ሳይቀር እንደ ስኬታቸው ቆጥረው፤ ወኔ ከፊልሞቻቸውና ከፊጠራቸው በመበደር ትውልዱን ይሞሉበታል። እንደ እኛ ሀገር እኩይ የፖለቲካ ልሂቃን ቂም ተበድረው ወኔ ሰልበው የስነልቡና ስብራት አይፈጥሩበትም። 'ፍርሀትህን በውስጥህ ሸሽግ ወኔህን ለብዙዎች አካፍል' የሚለውን የአሸናፊነት ስነልቡና (The Winning Wisdom) በሚገባ ተጠቅመውበታል። አሜሪካኖች መበቃቀልን አሽቀንጥረው ጥለው ለትውልዱ የጀግንነት ስነልቡና በማላበሳቸው አብዝተው አትርፈውበታል። 'ላለው ይጨመርለታል ከሌለው ግን ያው ያለውም ይወሰድበታል' የመፅሐፌ ጥበብ መልዕክት ሥርቶ ማትረፍን የሚያበረታታ እንጂ የመንጠቅ ህግ አይደለም።

ከላይ የገለፅነው የአሜሪካ የዜግነት ህግ ከቅንሱላ ቤተሰብ አባላት በስተቀር ለሌሎች በግዛቷ ለሚወለዱ ዜጎች ያለልዩነት ዜግነትን ያጎናፅፋል። ትክክለኛው ሀብት የሰለጠነ ዕውቀት ከህሎትና ትጋት የተላበሰ የሰው ልጅ ነው። ህያው ሰብአዊ ሀብት ከተገኘ ግዑዝ ተፈጥሮን በተአምራዊ ጥበብ ይለውጣል። አሜሪካውያኑ አባቶች ለውጥ ከሰው እንደሚጀምር ተገንዝበው የብዝኃነት ቪዛ (Diversity Visa / DV) ለዓለም ሰጥተው ከምድር ማዕዘናት በዘመን የበለፀገ ጥበብ ያለ ከፍያ ይሸምታሉ። አብዛኞቹ ያደጉ ሀገሮች የሚከተሉት የዜግነት ህግ ከአፈር የተቆራኘ ነው። አንድ ታዋቂ ምሁር የጃፓንን እድገት አስመልክቶ ምስጢሩን ሲፈታ፡- የጃፓን ዋነኛ ሀብቷ በተፈጥሮ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሀብት አለመታደሏ ነው (Japan's main resource is its resource less ness) ሲል የገለፀው ሰው አእምሮው ከጎለመሰ ተፈጥሮን በሚፈልገው መልክ ለመቀየር የሚያስችል አምቅ ብቃት እንዳለው ለማመልከት አስቦ ነው። በምጣኔ ሀብት ያልበለፀጉ ሀገሮች ቀደም ብለን ለመግለፅ እንደሞከርነው የደም የዜግነት ህግ ያራምዳሉ። ደም ፍለጋ ደም ሲያፋስሱ ፈፅሞ አያንቀሳፉም።

አሜሪካ ለራሷ አንድነትን በላቀ ደረጃ ብትሰብከም ለሌሎች ሀገሮች ውስጣዊ አንድነት ፍላጎት አታሳይም። ለዚህም ይመስላል 'ለቤት አልጋ ለውጭ ቀጋ' ተብላ የምትጠቀሰው። ለራሷ የማትመኘውን የብሔረሰብ ፖለቲካ ውጭው ዓለም ያራምደው ዘንድ በስመ 'የነፃነት ትግሎችን መደገፍ' ፖሊሲዋ ለተቀናቃኞች የገንዘብ ድጋፍ ጭምር ታደርጋለች። የልዕለ ኃያሏን ሀገር ተፅዕኖ በውል የተገነዘቡ ሀገሮች አሜሪካን ላለማስቀየም የተቻላቸውን ጥረት ሁሉ ያደርጋሉ።

በተለያየ ጊዜ የአሜሪካን ቡራኬ አልቀበልም ብለው ያጣጣሉ ሀገሮች የማይሽር ጠባሳ በታሪካቸው አስተናግደዋል። አሜሪካ በትሯን ካሳረፈችባቸው ሀገሮች የሱቨየት ህብረት 15 ቦታ፣ የዩጎዝላቪያ ከ7- 9 ቦታ፣ የሶማሊ ከሁለት እስከ ሶስት ቦታ፣ የኢትዮጵያ ለሁለት መሠንጠቅ፣ የኢራቁ ሳዳም ሁሴን እና የሊቢያው ሙአመር ቃዳፊ አሳዛኝ ፍፃሜ፣ የሱዳኑ አልበሽር፣ የሶማሊያ የጦር አበጋዞች፣ የሶርያ ምስቅልቅል ጎልተው ሊጠቀሱ ይችላሉ። ሀገራችንን ኢትዮጵያን ከሚያተራምሱት ግዙፍ ስውር እጅ ያላቸው ኑሯቸውን ከነቤተሰባቸው አሜሪካ፤ ህሊናቸው ኢትዮጵያ ዱር ውስጥ የመሸገ ግለሰቦች ናቸው። የአሜሪካ በጥባጮቻችን ምክንያት ውስብስብ፣ ጥልቀቱ ሩቅ፣ እንቅሳቃሾቹ እጆች ማያርፉ ከመሆናቸው አንፃር፤ መሻቱ ድንበር ዘለል መሆኑ በውስጣችን ታላቅ ጥያቄ ያጭራል።

በመሆኑም የተደገሰልንን ሴራ ጠንቅቀን ተረድተን፤ በበለጠ ሁኔታ ከአሜሪካ የአንድነትን ጠቀሜታ ቀስመን አፍ ከልብ ሆነን ለሁላችንም የጋራ ለውጥ ልንፅም ይገባናል። ከግጭትና ከመለያየት የትኛውም ወገን አያተርፍም። የፖለቲካ ነጋዴዎችን ቁማር ማስቆም የሁላችንም ሃላፊነት ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል። መንግሥታትም የኃይል ሚዛኑን በመመልከት እንደ ገበቴ ውሀ ከመዋለል አቋም የለሽ አካሄድ ተላቅቀው ከህዝብ የአንድነት ፍላጎት ጋር ቢቆሙ ሊያነቃንቃቸው የሚችል ኃይል የለም። የወገንተኝነት ስሜት አንዱን የእንጀራ ልጅ፣ ሌላውን የጡት ልጅ፣ አበልጅ፣ የዐይን አባት፣ የበኩር ልጅ፣ የቤት ልጅ ካደረገ ይዋል ይደር እንጂ መውደቃቸው አይቀሬ ነው። ታሪክም መስተዋት ሆኖ እውነታውን እያመላከተን ቀጥሏል።



t.me/OLDBOOKSPDF

ዴሞክራሲ በባህርይው በቅፅበታዊ ሂደት (Revolutionary Process) የሚገኝ አይደለም። አዝጋሚ (Evolutionary) መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ እርምጃውን ለማቀላጠፍ ከሚወሰዱ እርምጃዎች የእንበሳውን ድርሻ የሚወስደው የሁሉንም ዜጋ ሃሳቦች በተሸከመው የመንግሥት ቁርጠኝነት ላይ የሚመሠረት ይሆናል። ዴሞክራሲያዊ ተቋማትን መገንባት፣ በህዝቡ ውስጥ ሥሬ የእስተሳሰብ አድማስን የሚያሰፉ ሥራዎች መሥራት፣ የትምህርት ሥርአቱ የለበጣ ሳይሆን ቁርጠኛ ለውጥ በሚያመጡበት መንገድ ማዋቀር፣ ሠፋፊና ግልፅ ሀሳቦችን የሚያንሸራሽሩ መድረኮችን በማመቻቸት መትጋት ቢችል ለፈጣን የእስተሳሰብ አድማስ መሥፋት አይነተኛ ሚና ይኖረዋል።

ከዜጎች መሀከል ተዕፅኖ ፈጣሪ የሆኑ ለምሳሌ:- በኢትዮጵያ ልዩ ሁኔታ አባ ገዳዎች፣ የሀይማኖት አባቶች፣ ምሁራን፣ ተዕፅኖ ፈጣሪ አረጋውያን፣ ሙምህራን፣ እና ሌሎች ልሂቃን በሀገር ደረጃ ሠፋ አድርገው ማሰባቸው እና በሁብረተሰቡ ውስጥ ያላቸውን ወሳኝ ቦታ ለዴሞክራሲ እድገት እንዲጠቀሙበት መንግሥት መድረኩን ቢያመቻችላቸው አዎንታዊ ፋይዳቸው ጎልቶ ይወጣል። በየትኛውም የመገናኛ መንገዶች የሚደረጉ ብሽሽቆች፣ የጥላቻ ንግግሮች፣ ከፋፋይ ዲስኩሮች፣ ሥርአተ አልበኛ ባህርያት (Anarchy)፣ በአጠቃላይ የህዝቡን አብሮነት የሚጎዱ ድርጊቶች ያለምህረት እንዲደፈቁ ምልዓተ ህዝቡ መረባረብ ይገባዋል።

የአሜሪካን ተሞክሮ ስንመለከት ጥቁሮች ከባርነት ቀንበር በከፊል በአብርሀም ሊንከን ጥረት በ1865 ነፃ ወጡ። የአሜሪካ የእርስ በርስ ጦርነት ሲጀመር (1861 - 63) በደቡቡ አገዛዝ ሥር አሣራቸውን ሲያዩ የነበሩ ጥቁሮች ፦ጽምር 'እንፃራዊ ነፃ አውጪዎቻቸውን' የሰሜኑን ጦር ከባሪያ አሳዳሪዎቻቸው አጠገብ በመሰለፍ ይወጉ ነበር። ሊንከን ሂደቱን ለመቀየር በ1863 ሁለት አዋጆችን አወጣ። እነዚህም፡- "Emancipation Proclamation" / "የነፃነት አዋጅ" እና "Homestead Law" / ጥቁሮች የሚያርሱት ቁራሽ መሬት የሚሰጣቸው መሆኑ ሲገለፅ የኃይል ሚዛኑ (1863 - 1865) ወደ ሰሜኑ አጋደለ። ለሁለተኛ ጊዜ አሜሪካን እንዲመራ የተመረጠው ሊንከን ግን ተጨማሪ የአመራር ዘመኑን በስኬት መምራት አልቻለም። በዚህ ድርጊቱ የተበሳጩ ነጭ ዘረኞች በ1865 ጆን ዊልከስ ቡዝ የተባለን ሰው በመቅጠር ሊንከን ከዋሺንግተን ዲሲ ፎርድ ቲያትር ቤት ሲወጣ አስገደሉት።

ጥቁሮች 'ከባርነት ቢላቀቁም' ቢሮ ውስጥ እንዲሠሩ፣ ከነጮች ጋር በአንድ የመማሪያ ክፍል ውስጥ እንዲማሩ፣ በአጠቃላይ ከነጮች ጋር እኩል እንዲታዩ አይፈቀድም ነበር። ሂደቱ ሳይሻሻል ለመቶ ዓመታት ቀጥሏል። ከመቶ ዓመታት በኋላ ከነጮች ጋር



t.me/OLDBOOKSPDF

መብት እንዲጋሩ በ1960ዎቹ በተደረገው ትግል የጥቁሮች መብት የነፃነት ታጋይ መብት እንዲጋሩ ጥቁር አሜሪካዊ ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር ህይወቱን አጣ። ሌሎች የሆነው ጥቁር አሜሪካዊ ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር ህይወቱን አጣ። ሌሎች የሆነው ጥቁር እንዲሁ ሆነው የዘረኝነት እንቅስቃሴ ተደምሮ ጆን ፊትዝጀራልድ ኬኔዲ ምክንያቶች እንዳሉ ሆነው የዘረኝነት እንቅስቃሴ ተደምሮ ጆን ፊትዝጀራልድ ኬኔዲ ክክለ. ሃርቪ ኦስዋልድ በተተኮሰ ጥይት ዳላስ ውስጥ ተገደለ። ይህ ሁሉ ሆኖ ጥቁሮች መመረጥ ሳይሆን መምረጥ እንኳ የተፈቀደላቸው በ1971 ነው። ከዚህ በ20ኛው ክፍለዘመን ማገባደጃ ከተወጠነ ጅምር በጥንቃቄ ተላቅቀው ማማሸ ከፍለ ዘመን ባልሞላ ጊዜ የመጀመሪያውን ጥቁር ፕሬዚደንት ባራክ ሁሴን ኦባማን ሁለት የአመራር ሙሉ የሥልጣን ዘመን ከስኬት ጋር ማየት ችለዋል። በአሜሪካ ውስጥ ጥቁሮች የደረሰባቸውን መአት ማሰብ ይከብዳል።

ዛሬ አሜሪካ ውስጥ ይህንን በደል በማሰብ ጥላቻ እንዲንሰራፋ አይሰራም። 'ታላቂ የማትለማ ገንዳ' አሜሪካ ያደገችበት ዋና ምሥጢር ከመላው ዓለም ፈልቅቃ የካበተችውን ልምድ ከሁኔታዎች ጋር አላምዳ ወደ ተግባር ምዕራፍ በመሸጋገሯ ነው። ከአንዱ የሰላ፣ ከሌላው የአስተዳደር፣ ከሶስተኛው የሳይንስ፣ ከአራተኛው የአብሮነት ልምድን አሰባስባ፦ የረቀቀ የስለላ ድርጅት ሲአይኤ (CIA) ላያንቀላፋ እየጠበቃት፣ የናሳ (NASA) ምርምር ማዕከሏ የህዋን ቅኔ እየፈታ፣ ወታደራዊ ተቋሟ 'ፔንታጎን' ተቀናቃኞቿን ብቻ ሳይሆን የሀገሪቷን አስኳል ፍላጎት ብሔራዊ ጥቅም (National Interest) ለማስጠበቅ እንዲያስችላት መላውን ዓለም ታምሳለች። ከአሜሪካ ከ1945 በኋላ ያዳበረቻቸውን በሀገሮች የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባትን ረግመን ሌሎች ልምዶቿን ግን እንወስዳለን። ከህዝቧ ከ3 እጅ በታች የሆነው ገበሬ አጥግቧት፣ ለዓለም የእርዳታ እጅ ዘርግቶና መዕወቶ የተረፈውን ለባህር አሶች ይሰጣል፡፡

እኛ 85 እጅ ገበሬ ይዘን በምን የተነሳ፦ 'ዳቦ ላይ ተቀምጠን እንደምንራብ፣ ውሀ ላይ እየሄድን እንደምንጠማ፣ ወርቅ ላይ ቁጭ ብለን እንደማናጌጥ' እና በየህይቆቻችን ውስጥ ከእኛ የገዘፉ አሣዎች በቁንጣን ብሥና ሲያገሡ ÷ ሀይቁ ዳር ወገናችን በረሀብ ስለሚሞትበት ጉዳይ የችግሮቹን ምንጮች አንጠይቅም። 'ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ አሜሪካ የምትዘረጋው' ሰው እያላት ሰው የሚሆን ሰው አጥታ ነው። 'ሰው ሆይ አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሣለህ' ላይቀር ለአፈር ግብር ሽሚያው ምንድነው? ኢትዮጵያዊነት እንዲደምቅ የሚሠሩትን ማወደስ፣ ሀገርን የሚያተራምሰውን ለመውቀስ፣ በየቦታው በችግር የሚንገላቱ ወገኖቻችን ለማዕናናት፣ የቀዘቀዘውን የሀገር ፍቅር ስሜት ለማነቃቃት፣ በአንድ በኩል በመሀከላችን የዐብ ግድግዳ የሚያቆሙትን እያፈረስን፣ በሌላ በኩል ሀገር ለማዳን የእለምጅችን ላብ ወበቅ እስኪሰማን እንቅልፍ ማጣት አለብን። ለመቀራረብ ዕናት ካለን አንዳችን ወደ አራምባ ሌላችን ወደ ቆቦ



t.me/OLDBOOKSPDF

ማሰብ ትተን ቢዮንስ ወደተቀራረበ አስተሳሰብ እንጠጋለን። ከሌሎች ተግባራ ብሔራዊ መግባባት ከፈጠርን ለብሔራዊ እርቅ ወይም በእርቅ ወደ መግባባት መሸጋገር ያስችለናል።

## ፍልስጤም እና እሥራኤል

እስራኤሎች በሮማ ንጉሠነገሥታዊ ግዛት ዘመን፣ በሰልጁክ ቱርኮች እና ዐረቦች በተለያዩ ጊዜያት ምድራቸውን ለቅቀው ተሰድደዋል። በሄዱበት ምድር በሙሉ እንደ መፃተኛ መቆጠራቸው የአገር ውስጥ እሳት ሆኗቸው ዘመናት ተቆጠሩ። መበታተን ያስከፈላቸውን ዋጋ ተገንዝበው ከመላው ዓለም ተሰባስበው 'ምድራችን' የሚሏትን ፍልስጤምን ለመያዝ ዓለማቀፍ ዘመቻ ጀመሩ። በ1898 በስዊዘርላንድ የዉ አይሁዳዊ ቴዎዶር ኸርዘል እንቅስቃሴ 'በኢየሩሳሌም የአይሁዶች (Jewish) እናት ምድር መመሥረት' የሚል መርህ በማንገብ ዘመቻ ጀመሩ። በምዕራባውያኑ ድጋፍ በረቀቀ ህቡዕ አደረጃጀታቸው ቀስ በቀስ ከአርብቶአደር ፍልስጤማውያን መሬት እየገዙ በቀደመ ምድራቸው መሥፈራቸውን አጠናከሩ።

ቁጥራቸው እያሻቀበ ሲመጣ በአረቦቹና በአይሁዶቹ መሀከል ግጭቶች እየተበራከቱ ሄዱ። ግለቱ በመጀመሪያው ዓለም ጦርነት (1914-1918) እየተከሰ መጣ። የፍልስጤሟ ቅኝ ገዢ ብሪታንያ በጦርነቱ ውስጥ የአረቦችን ድጋፍ ለማግኘት ስትል፦ በ1915 መሬቱ የፍልስጤሞች መሆኑን አወጀች። ትንሽም ሳይቆይ አሜሪካ ብሪታኒያ በምትመራው የቃልኪዳን ጎራ ጦርነቱን ተቀላቅላ የኃይል ሚዛኑ በአስተማማኝ ሲለወጥ ቃለ አባይ ሆነችና ተገልብጣ በ1917 ባልፎር ድንጋጌ ያንን መሬት የአይሁዶች ነው ስትል አወጀች። በዚያን ዘመን የቀበረቺው ጊዜ ጠብቆ የሚፈነዳ በምብ ቅርብ ምስራቅን የደም መሬት እንዳደረጋት እስከዛሬም ዘልቋል።

"People at Odds, Israel and the Arab World" በሚል ርዕስ ሄዘር ሌኸር ቫግነር ባዘጋጀው መፅሐፍ ከገፅ 8-9 እንደተገለፀው ሜይ ወር 1947 ብሪታንያ የፍልስጤምና የእስራኤል ጉዳይ ከአቅሟ በላይ ስለሆነ እንደፍጥርጥራችሁ አድርጉት ስትል ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጉዳዩን አቀረበች። ተመድ ሁናቴውን መርምሮ እስራኤልም ፍልስጤምም ሉዓላዊ መንግሥታት እንዲሆኑና ኢየሩሳሌም ዓለማቀፍ ከተማ እንድትሆን ወሰነ። በውሳኔው መሠረት ከፍልስጤም የቆዳ ስፋት ውስጥ 55 እጅ የሚሆነው መሬት ከአጠቃላይ ህዝቡ 30 እጅ ብቻ ለሆነው አይሁድ



t.me/OLDBOOKSPDF

ተብዬነ፡፡ ድንጋጊውን እሰፍስፋ ትጠብቅ የነበረቺው እስራኤል ቀልጠፍ ብላ የእሥራኤል መንግሥት ዋና ከተማውን ቴል አቪብ አድርጎ መመሥረቱን ለዓለም ማህበረሰብ አሳወቀች፡፡ የ62 ዓመቱ እስራኤላዊ ዴቪድ ቤን ጉሪዮን የሚከተለውን ዲስኩር አደረገ፡- "ታሪክ ወደዚህ ስፍራ አመጣን፡፡ መንፈሳዊና ፖለቲካዊ ኃይሎች ማንነታችንን በብሉይ ዘመን ኪዳን ቀረፁት፡፡ እነሆም የአይሁዶችን ሀገር ኢሬትዝ - መሠረትን፡፡"
እስራኤል (Eretz - Israel)

የተመድ ውሳኔ ለዐረብ ሀገሮች ፈፅሞ የሚዋጥላቸው አልሆነም፡፡ በዚህም ምክንያት ከእሥራኤል ጋር በተለያዩ ጊዜያት አራት ጦርነቶችን አድርገው በሁሉም ተሸነፉ፡፡ እስራኤል የምዕራቡን ድጋፍና የመሣሪያ የበላይነቷን በመጠቀም ዌስት ባንክ፣ የጋዛ ሠርጥ፣ የጎላን ኮረብታ፣ የሣይናይ አካባቢዎችንና ሌሎች አካባቢዎችን ራሷን ከጥቃት ተማናለሁ (Buffer Zone) ስትል አላግባብ መሬቶቹን ይዛ አልለቅም አለች፡፡ አረቦቹ በሌላ ጎን እስራኤል የምትባል ሀገር እናውቅም በሚለው አቋማቸው ፀኑ፡፡ ሌላው ዓለም ከእንግት በላይ ካልሆነ ሀገሮቹን ለማቀራረብ የረባ ሙከራ አላደረገም፡፡ ከምንም በላይ ፍልስጥኤምና የችግሩን እልባት ማግኘትም የሚፈልገው አይመስልም፡፡ ከምንም በላይ ፍልስጥኤምና እስራኤል ተቀራርበው የሁለትዮሽ ድርድር (Bilateral Agreement) በማድረግ ያለሦስተኛ ወገን ጣልቃ ገብነት (Negotiation) ወደ ሰላም ጠረጴዛ መቅረብ አልፈለጉም፡፡ በየጊዜው ደም እንደ ውሀ ይጎርፋል፡፡

የመፍትሔው ቁልፍ የጠፋው ከምንም በላይ በሦስተኛ ወገኖች ፍላጎት ነው፡፡ በሰላም ወጥቶ መግባት ህልም ነው፡፡ አረብ ሀገሮች እርስ በርሳቸው በማያባራ ጦርነት እየተፋጁ አጉል ለፍልስጤም ተቆርቋሪ መስለው መታየታቸው አያሳምንም፡፡ የግብፁ ፕሬዚደንት አንዋር ሳዳት በተናጠል በአሜሪካ የ'ካምፕ ዴቪድ' ስምምነት የእስራኤልን ነፃ ሀገርነት ተቀበለ፡፡ ይህ ውሳኔው ብዙም ሳይቆይ በአረብ ፅንፈኞች ህይወቱን አስከፈለው፡፡ ሁለቱ ሀገራት ተቀራርበው ችግራቸውን እንዳይፈቱ የተለያዩ ሳንካዎች ቀስፈው ይዘዋቸዋል፡፡ የአይሁድና የአረብ ብሔርተኝነት፣ የኃያላኑ ሀገራት የነዳጅና የስትራቴጂ ጥቅም የጋለ ፍላጎት፣ የሥፍራው ጂኦግራፊያዊና ጂኦፖለቲካዊ አቀማመጥ በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡ በድምሩ ከ100 ዓመታት በአጠቃላይና 70 ዓመታት ወዲህ በተለይ ዘወትር ለቅሶ ዋይታ ዕንባ ሚፈስስባት የደም መሬት (አኬልዳማ) ምድር ሆናለች፡፡

ለእሥራኤልና ፍልስጥኤም እናቶች ደረት ሚያስደቃ ቢሆንም ለጋዜጠኞችና ጠማሪዎች የረብጣ ማስገኛ ጠቅሟል፡፡ ከመቶ ዓመታት ለበለጠ ጊዜ ሁልጊዜ በግጭት እየተናጠ ከመወዝወዝ የሚያወጣቸው አንድ ሙሴ / ሙሳ ስለምን ጠፋ? እንደ



t.me/OLDBOOKSPDF

ኢትዮጵያውያን መገንዘብ ያለብን ታላቅ ቁምነገር እኛ መጠፋፋትን ካልገታን ዓለም ለፍልስጤምና እስራኤል፣ ለሩዋንዳ፣ ለደቡብ ሱዳን፣ ለሊቢያ፣ ለሶርያ፣ ለየመን ግድ እንዳልሰጣት ሁሉ እኛም ብንጠፋ ጆሮዋ ድፍን ነው። ወደ ታሪክ ውይይት ዘወ ብለን ከመግባታችን በፊት ሰፋ አድርገን አዕምሯችንን በማሠራት ዓለምን መቃኘት (Brain Storming) በጣም ያስፈልገናል። ይህንን ታሳቢ አድርገን እንደ ዓለም ማህበረሰብ አካልነታችን ለመነሻ ሰፋ ያለ ሐተታ መርጠናል። የፍጥረት ሰው ውሎ ሲመዘን ሁልጊዜም እንባና ሳቅ ጎን ለጎን ይጓዛሉ። የተሻለውን ለመምረጥ አሥር ጊዜ ለኩ አንድ ጊዜ መቁረጥ ይመከራል።

ከላይ የገለፅናቸው ተግዳሮቶች የፈጠሩት ችግር ተባብሶ እንዲቀጣጠል በችግሩ እሳት ላይ ቤንዚን የሚያርከፈከፉ በርካታ ሁኔታዎች፣ ቢኖሩም የእንበሳውን ድርሻ የሚይዘው የእስራኤልና የፍልስጥኤም መንግሥታት በትውልድ ውስጥ የሚያሠርፁት የጥላቻ ንግግር ነው። አዘውትሮ እንደሚታየው 'ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባል' እንዲሉ ችግሩን በሌሎች ኃይሎች ላይ ማላከክ ውሀ አይቋጥርም። የማስጠላት ፖለቲካውን ሥዕል በዚህ እውነታ ላይ ተመሥርተን ገቢራዊ ምናባዊ መግ በመጠቀም ግልፅ እናድርግ።

ሀ. ፍልስጥኤም፡- የሒሳብ መምህር ክፍል ውስጥ ይገባና፡- 'ተማሪዎች 7,000,000 እስራኤላውያን አሉ። ሙስጠፋ ስድስቱን አጥፍቶ ጠፋ፤ ስንት ቀሩ?' ይላቸዋል። ተማሪዎቹ በመሻማት እጅ አውጥተው ልክ እስራኤልን አግኝተው አይሁዳውያንን የገደሉ በሚመስል ስሜት እየተንዘፈዘፉ የመልሱን አነገ ለአስተማሪው ይገልፀሉታል። 'ማን ያጥፋቸው?' ሁለተኛውን ጥያቄ ያስከትላል። አሁንም እጅ ችቦ ሆኖ ይወጣል። 'እኔ እኔ እኔ ...' ስለሆነም በትውልዱ ህሊና ውስጥ የተቀረፀው 'ቦምብ'፣ 'እሥራኤልን ማጥፋት'፣ 'አይሁድን መግላት' ነው።

ለ. እሥራኤል፡- የአይሁድ መምህር ክፍል ገብቶ 'ተማሪዎች ቁጥራችን ትንሽ ቢሆንም ጠንካራ ህዝቦች ነን። በዚህ ስሌት ተንተርሥን አንድ አይሁድ በአረቦች ቢገደል በአፀፋው ስንት አረቦችን መግደል አለብን?' በማለት ይጠይቃል። የተማሪዎቹ ምላሽ፡- 1:300, 1:400, 1:500... ይቀጥላል።

በሁለቱም ወገን የመጠፋፋት ትምህርቱ መርዝ ፍሬ እያፈራ እስካሁን ለቀጠለው መጠፋፋት አይነተኛ ሚና አሳድሯል። 'ልጅን በሚያድግበት መንገድ ምራው' ከአርሱም ፈቀቅ አይልም።' የታላላቆቹ መፃሕፍት ምክር ልንጠቀምበት ይገባል። የራሳችንን የችግር ጡበደል ቋጥኞች ሳናንከባልል ኢትዮጵያውያን የህይማኖት



t.me/OLDBOOKSPDF

ዕንፈኞች ፍልስጥኤምና እስራኤልን በተመለከተ ያለን አቋም በአመዛኙ በምክንያት ሳይሆን በመንጋ አስተሳሰብ ላይ የተመሠረተ ነው። የመንጋ መገለጫ አስተሳሰብ ምንጭ በአብዛኛው የሚመነጨው እውቀት ከማጣት አሊያም ከድንቁርና ነው። የመንጋውን መተራመስ ምክንያት የሚያውቀው እረኛውና የእረኛው አሳዳሪ ብቻ ናቸው።በምክንያት ከሚወያዩ ጥቂቶች በስተቀር የእስራኤል ፍልስጥኤም ችግር ከኢትዮጵያ ጋር እንደማይያያዝ አውቀው አይወያዩም። ከመነሻው እንደ World Almanac 2010 አኀዛዊ መረጃ ገፅ 793 በእስራኤል ውስጥ፦

*የአይሁድ እምነት ተከታዮች ቁጥር 76%*

*የሙስሊም አረቦች ቁጥር 16%*

*የክርስቲያኖች ቁጥር 2% እና*

የተቀረው የተለያዩ እምነቶች ተከታይ ነው። የቅርብ መረጃዎችንም ብንፈትሽ የምናገኘው ተመሳሳይ ስብጥር መሆኑ አያጠያይቅም። እስራኤል ለክርስቲያኖችም ሆነ ለኢትዮጵያ መልካምም ሆነ ክፉ አመለካከት የሌላት እንዲኖራትም የማይጠበቅ የአይሁድ ሀገር ናት።

ሲቀጥል፦ ግጭቱ ሀይማኖታዊ ሳይሆን ምጣኔ ሀብታዊ የግጭቶቹ ምንጮችም የውጪዊ ኃይሎች ፍላጎትና የሁለቱ ህዝቦች የብሔርተኝነት ጉዳይ ነው። ሲሠልስ፦ የኢትዮጵያ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች በየትኛውም የዓለም ሀገራት ያልታየ (በምዕራፍ አራት) በማስረጃ አስደግፈን የምናየው ፍቅር እያለ 'ጠብ ያለሽ በዳቦ' የሚል ስሜት ይዘን ግጭት ለመበደር ወደሌላው ዓለም የምንዳዝበት አንዳች መነሻ የለም። ሁሌጊዜም በረባ ባልረባው በወል ከመውደም በጭንቅላት ማሰብ ይቅደም! በዓለማችን አብዛኛው ሰው የሚኖረው በማያገባው እየገባ ነው። የመረጃ ምንጮችን ከፍተን ስንመለከት የምናየው አሳዛኝ ትርኢት ጥሩ ተማሪ ካለ ይማራል። ባለቅኔ ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን፦

*"የሰው ልጅ ከሁለት ነገር ይማራል*

*እንድም ከፊደል "ሀ" ብሎ*

*እንድም በአሣር "ዋ" ብሎ"*



t.me/OLDBOOKSPDF

በማለት በተባ ኃያል ብዕራቸው የዘመናት ርቀት በማያስረጃቸው ዕንቁ ብዕር ዛሬም ሊያስተምሩን ብርቱ አቅም አላቸው። በአገልጋታቸው የምንጠየፋቸው አስተሳሰቦች ከፉ መሆናቸውን ለማየት ሊቢያን እንመልከት። አንዱን አምባገነን በሌላ ለመተካት ከሦስት ሚሊየን የማይበልጡ የአንድ ሀገር ልጆች በሁለት ጎራ በጥይት ይወድቃሉ። በርግጠኝነት መንጋው ነገ ምን ይዞ እንደሚመጣ አያውቅም። ከሆነሬው በላይ ተጥር ያለውን የውጭ ዜጋ አቅፋ እየተዘረፈች የኖረች ሀገር፤ ኪኪን ሰከን ብሎ መከፋፈል አቅቷት በቁጥር ስስ የሆኑ ዜጎቿን ታጋድላለች። ኃያላኑ ለከ እንደ ሰርዮ በየፊናቸው ተቃራኒ ጎራዎችን እያፋለሙ የመሣሪያቸውን አቅም በሰው 'ላቦራቶሪ' ይፈትሻሉ። አልቂትን ዕያዩ ለፍጅት ቃታ መሳብ የምክንያት ሳይሆን የመንጋ ፍሬ ነው። ከፍልስጤምና እስራኤል የምንማረው መራራ ሀቅ ችግሮችን ተቀራርቦ መፍታት አለመቻል በዋጋ የማይተመን የእድሜ ዘመን መከራ እንደሚያስከትል ነው።

## ኮንጎ

የቅኝ ግዛት መጥፎ አሻራ ካረፈባቸውና ሳያባራ ከቀጠለባቸው የዓለም ሀገራት መሀከል አፍሪካዊቷ ኮንጎ ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ናት። የኮንጎ ህዝብ ቢያውቅበት ከየትኛውም የአፍሪካ ሀገር በላይ እጅግ በጣም በድሎት ሊኖር በሚያስችለው የተፈጥሮ ሀብት የታደለ ነው። አዱኛው ላይ የተዘረፈጠው ግን በዕውቀትና ጥበብ ሳይሆን በኃያል ድንቁርና ነውና ከአፍሪካ የመጀመሪያውን ምድራዊ ሲዖል ፈጥሯል። በማስረጃ ለማስደገፍ የኮንጎ የውሀ ሀብት ለመላው አፍሪካ የ'ኤሌክትሪክ' ኃይል ማመንጨት የሚያስችል አቅም እንዳለው ይፋዊ ጥናቶች አረጋግጠዋል። የተፈጥሮ ደኗ በአፍሪካ አኩያ አይገኝለትም። የማዕድን እምቅ ሀብቷም በተመሳሳይ ከአፍሪካ ተስተካካይ የለውም። የተትረፈረፈ ፀጋዋ እጅን አፍ ላይ ያስጭናል በማለት ሳናበቃ አንደኛው በሌላኛው ላይ የተነባበረ ነው። በጂኦሎጂ ጥናት የወርቅ ክምችት እንደሚገኝ ምልክት ታይቶ አሰሳ ሲጀመር በየጣልቃው አልማዝና ሌሎች ማዕድናት ብቅ ጥልቅ እያሉ ፋታ ይነሳሉ። ከዚህ በመነሳት ተንታኞች ኮንጎ ውስጥ ጂኦሎጂ ማጥናት ዋጋ አጥቷል ሲሉ ይስማማሉ።

የዳራውን አስደናቂነት ለማሳየት ጥናቱን የጂኦሎጂ ቅሌት (Geological Scandal) ብለውታል። በ1960ዎቹ መጀመሪያ የኮንጎ ቅኝ ገገር የነበረቺው ቤልጂየም እንደሌሎቹ ቅኝ ገገሮቸ፡- ምርጫ አካሂዳ፤ ለቢሮክራሲያዊ መዋቅር የሚሆን የሰው ኃይል አሰልጥና ፤ ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር አመቻችታ ሳይሆን በዘፈቀደ ቀሳቀሶቿን ሸክፋ እንደ ፍጥርጥራችሁ በማለት (Mismanaged withdrawal) ሀገሪቱን

ለቀቀች። ይህንን ተከትለው የተለያዩ የጦር አበጋዞች ለገዢነት ጠበመንጃ እያነገቱ ሀገሪቱን ቁም ስቅሏን ዐሳዩ። ወደ ስድሳ ዓመት ለሚጠጋ ጊዜ የእርስ በርስ ጦርነት በአስር ሚሊየኖችን ህይወት እየቀጠፈ፤ ተጨማሪ ህይወት ሊቀጥፍ ጠበመንጃዎች ሰላማዊው ህዝብ ላይ ተደግነዋል። እናቶች ሴቶች ህፃናት ወንዶች ሳይቀር በየእለቱ በግዳጅ ይደፈራሉ። ደም እንባቸው ከመፍሰሱና ሞት እንደ ሰርከ ህይወት ከመለመዱ የተነሳ የእንባ ከረጢት ደርቋል።

ታያለኑ እንደተለመደው የኮንጎን አንጡራ ሀብት ከመቀራመት ውጭ እንደ ጤዛ ታያለኑ እንደተለመደው ለሚረግፈው አፍሪካዊ ደንታ የላቸውም። የሀገራቸውን ችግር አንጥረው ለይተው ለሚረግፈው አፍሪካዊ ደንታ የላቸውም። በአንተ ትብስ አንቺ ትብሽ ስሜት ቢወያዩና ለችግራቸው የኮንጎ ልሂቃን ተቀራርበው በአንተ ትብስ አንቺ ትብሽ ስሜት ቢወያዩና ለችግራቸው የሚቀምጋቸው አልነበረም። ደጋግመን እልባት ቢያስቀምጡ ከአፍሪካ ምድር መሪነቱን የሚቀማቸው አልነበረም። ደጋግመን እልባት ቢያስቀምጡ ከተማ ቢዘምን ሙሉ ዓመት እንዳነሳነው ሰብአዊ ሀብት ካልለማ የቱንም ያህል ከተማ ቢዘምን ሙሉ ዓመት እንዳነሳነው ሰብአዊ ሀብት ካልለማ የቱንም ያህል ከተማ ቢዘምን ሙሉ ዓመት እንዳነሳነው ሰብአዊ ሀብት ካልለማ የቱንም ያህል ከተማ ቢዘምን ሙሉ ዓመት እንዳነሳነው ሰብአዊ ሀብት ካልለማ የቱንም ያህል ከተማ ቢዘምን ሙሉ ዓመት እንዳነሳነው ሰብአዊ ሀብት ካልለማ የቱንም ያህል ከተማ ቢዘምን ሙሉ ዓመት እንዳነሳነው ሰብአዊ ሀብት ካልለማ የቱንም ያህል ከተማ ቢዘምን ሙሉ ዓመት እንዳነሳነው። የአረብ ሀገሮች ውብ ህንፃዎች ወደ ሚበዳ የተገነባን ለመፍረስ ወራት ብቻ ይበቃሉ። የአረብ ሀገሮች ውብ ህንፃዎች ወደ ሚበዳ የተገነባን ለመፍረስ ወራት ብቻ ይበቃሉ።

ምሁራን አሳዛኝ ገፅታ' በተሰኘው ፅሑፋቸው የገለፁት 'ስለሀገራቸው ኢትዮጵያ ከምሁራን ይልቅ ማይማን እንደሚጎዳቸው' በማስረዳት ነበር። "Ignorant are more concerned about Ethiopia than are intellectuals" በማለት ነባራዊውን እውነታ በትክክል ገልፀውታል። አባባላቸው 'ዓለም የምትጠፋው ከአኩያን መጥፎ ድርጊት ይልቅ በመልካሞች ዝምታ ነው' ከሚለው ብሂል ጋር ተመሳሳይ ነው። ይበልጥ የሚያሳዝነው የሀገራችን ሆድ አደር ልሂቃን 'መንግሥታዊ መና ይወርድልናል' ላይ እያማተሩ ለህቅ የቆሙትን እያሳደዱ በረጅም ጅራፍ ጀርባ የሚመልጡ መሆናቸው ነው።

ወደ ሲቢያ ፊታችንን ብንመለስ ደግሞ ተስማምተው የሀገርን ትሩፋት በፍትሀዊነት ለመካፈል ቢወስኑ በሳምንት ለአንድ ቤተሰብ በነፍስ ወከፍ አንድ በርሚል ድፍድፍ ነዳጅ ደርሷቸው ተምላቅቀው መኖር በቻሉ ነበር። ሶርያ የመን ኢራቅ መላው አረብ ዓለም ውስጥ የሚነሳው ግጭት፣ የአፍጋኒስታን የማያባራ ጦርነት ሲታይ አንድ ሀይማኖት መከተል፣ አንድ ቋንቋ መናገር ሰላም አላመጣላቸውም። ሶማሊያን እንደ መገለሚያም እንደ ማላገሚያም! መማሪያ ማድረግ ይቻላል። በሀዝ መስማማት ያልቻለ በኃላ መስማማት አይችልም። የሰላምን አስፈላጊነት፣ የአብሮ መኖርን ወርቃማነት፣ የመተሳሰብን ታላቅነት ሬዘም ባሉ ምሳሌዎች ማመላከት እሹምሮን አሟሽቶ ወደ ኢትዮጵያ ታሪክ ጥናት አፃፃፍ ምልከታ ለመሸጋገር አመቺ የገማጅት መሸጋገሪያ ይሆናል ብለን እምነን በሰፋት ሄደንበታል። የታሪክ ትምህርት ዓላማ መጥፎዎቹን ተሞክሮዎች አስወግዶ በጎዎቹን መቅሰምን በእጅጉ ያበረታታል። ታሪክ ካለፈው መማር ሲሆን ፖለቲካ ከዓላማው አንፃር ስንጠቀምበት ዛሬም ቢሆን ከጎረቤትና የዓለም ሀገሮች  ለመማር ያስችላል። 'ከራስህ ይልቅ በሌሎች ከሚደርሰው መጥፎ አደል ትምህርት ልትወስድ ይገባሀል' መባሉ ለዚህም አይደል?

## ኢትዮጵያ

በየዘመኑ ኢትዮጵያን ያስተዳደሯትን መሪዎችን የጭካኔም ደረጃ ሆነ የርህራሄ መጠን አስመልክቶ የሚነሳውን እተካራ በምዕራፍ አራት በሰፊው የምንዳስሰው በመሆኑ በይደር አቆይተን የህዝቡን ኑባሬ ብንፈትሽ የትም ሀገር ውስጥ በዚህ መጠን የማይገለፅ ድንቅ ተሞክሮ እናገኛለን። በወያኔ ህወሓት ህገ መንግሥት፡- ወላይታ ሀዲያ አማራ አሮሞ ሶማሊ ዛይ ባስኬቶ እየተባለ ለብሔረሰቦች ስያሜ ሲሰጥ አንድ ታላቅ 'የፍቅር ውጤት የሆነ ብሔረሰብ' ተገፍቷል። 'ሰው በአባቱ ዘር መጠራት

አለበት' በሚል ቅጥ ቀር  አሳቢ እና ታቅዶበት ለመሸሽ ከሁለት እና ከዚያ በላይ ብሔረሰቦች ፍቅር የተገኘው እና የተዋሀደው፤ በድምሩ ስንመለከተው ከየትኛውም ብሔረሰብ ቁጥር የሚተልቀው 'የፍቅር ብሔረሰብ' ኢትዮጵያ ውስጥ ሆነ ተብሎ ቦታ እንዳያገኝ ተደርጓል።

በእናቱ አማራ ነው፤ በአባቱ ኦሮሞ ነው፤ 'ክልስ' አልፍ ሲልም ፍቅር የአበው ወእመው ኑባሬ እንዳልሆነ ያህል 'ዲቃላ' ይሉትና በሚያሳፍር ሁኔታ 'መጋቢ ጥላሁ - ወእኪዶ ተልእኮ' የሆነውን ኤርትራዊውን ተስፋዬ ገብረአብን "ከበርቻ ዝምታ" ጀምሮ ለጥላቻ አብዝቶ መርዝ ስለበጠበጠላቸው 'ገዳ' ገብረአብ የሚል ቅዕል የዳቦ ስም ሰጥተው ትልቁን የጉዳን ስም ለሊቀ ጥላቻው ሽልመው አኩሪ ሥርአታችንን ያራከሱና ለአንድነት የሚጮኸውን የራሳቸውን ሰው ግን ጀግንነቱን ሳይመዝኑ 'ጎበና' ይሉታል።

አለማወቅን ማወቅ ለመማር ከሆነ ክብር፣ 'አለማወቅን አለማወቅ' እና ለመማር ክፍት አለመሆን ግን ውድቀት ነው። እንደ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ:- "A Modern History of Ethiopia, 1855 - 1991" የተባ የምርምር መፅሐፍ ገፅ 59 መሀዲስቶች ወሊጋ ውስጥ ነጆ ድረስ ዘልቀው ከገቡ በኋላ ራስ ጎበና ዳጨ ወደር በሌለው ጀግንነት ጉቴ ዲሊ በተባለ ስፍራ አረፋ ያስደፈታቸው ሳተና ነው። ጎበና በኃይል የሚመጡበትን በውጊያ ብቃቱ የሚረታ፤ አብዝቶ በፍቅር መማረክ የሚችል ስብእና ያለው የምኒልክ ቀኝ እጅ ነበር። እንደ ሀሮልድ ማርከስ ሥራ የታሪክ ምርምር መፅሐፍ ገፅ 79 ራስ ጎበና (1821 - 1889) ምኒልክ ከቴዎድሮስ የቁም እስር ካመለጡ በኋላ እጅግ በጣም ተቀራረቡ ይለናል። ይኸውም:-

> "...Menelik, however, enjoyed the services of ever faithful Gobena (ca. 1821 - 1889; dejazmach and ras), a high - born Oromo, who submitted to the king when he returned to Shewa in 1865. By 1876, he was devoted to conquering his fellow Oromo with his formidable cavalry and infantry.

በዚህም መሠረት ወሊጋን (ሌቃ ቄለም እና ሌቃ ለቀምት)፤ የጊቤ ኦሮሞ ግዛቶችን (ጂማ ጎማ ጉማ ጌራ እና ሊሙ ኢናርያ) በሰላም ከወንድም እህቶቻቸው ጋር ተሰናኝተው እንዲኖሩ ያስቻለ ጀግና ነው። እውነተኞቹ የጎበና ልጆች ስሙን በኩራትና በክብር ለመጥራት ከበቂ በላይ ምክንያት አላቸው።



t.me/OLDBOOKSPDF

ለንጠኞች ዘረኝነት ፍርቱናቸው ነው። ጥላቻ አጥንታቸው ድረስ ሰርስሮ ለመግባቱ በርካታ ማሳያዎች አሉ። ለምሳሌ:- አንድ ኢትዮጵያዊ በአባቱ አባት ኦሮሞ፣ በአባቱ እናት አማራ፣ በእናቱ ወገን በሁለቱም በኩል አማራ ሆኖ አማራ ክልል ቢያድግ 3/4ኛ አማራ፣ እድገቱም አማራ ሆኖ የአባቱ አባት በወንድ ወገን ኦሮሞ ስለሆነ ብቻ በእነርሱ ስሌት መሠረት ኦሮሞ ይሆናል። በዘመነ ወያኔ ህወሓት አንድ ዜጋ 'በየትኛውም ብሔረሰብ መጠራት አልፈልግም ኢትዮጵያዊ ነኝ' የሚለት መብቱ የተነፈገ ነበር። 'የእናቴንም ሆነ የአባቴን መገኛ ልለቅ አልችልም የእናቴ ዘመዶች ዘንድ ስሄድ እንኳ አከስቶቼ አማራ፣ ልጆቻቸውም አማራ ናቸውና በአባቴ በኩል ብቻ ትግራይ ተብዬ መሰየም አልፈልግም። ከሁለት ወገን ስለተገኘሁ ልዩ ልዩ በሉኝ' የሚለት መብት ከልከል ነበር።

የግለሰብ መብትና ምርጫ ሳይጠበቅ በግዴታ ማንነት ይሚገነበት ነበር። ይባስ ብለው ግለሰቡ የመረጠውን ማንነትም ለመካድ የሚዳዳቸው አበላ ባይ ካድሬዎች ነበሩ። በግለሰቡ ፍላጎት የተመሠረተ በብሔረሰብ የመጠራት መብት ትክክል መሆኑን አምነን ስናበቃ፤ ኢትዮጵያዊነት በቂዬ ነው የት መጣ ቢኖረኝም ብሔረሰቤ አይፃፍ ያለውን ግለሰብ መብት ያለማክበር ተገቢ አይደለም። የመጠቀ የአስተሳሰብ ደረጃ ላይ እስከንደርስ የግለሰብ መብት ምንነት አይገለፅልንም። በሌላ አገላለፅ ኦሮሞ ነኝ እያለ አማራ የእናቱን ዘመዶች ጥየቃ ጎንደር የሚጓዝ ሰው ጎንደሬ ቤተሰቦቹ መሀከል በእናት የአከስት ልጆች ተከብበ እያወጋ ድንገት 'ብሔረሰብህ ምንድነው?' ብንለው 'ኦሮሞ ብቻ ነኝ' ብሎ ሊመልስ ነውን? የሚያስገርመው አጋጣሚ የአንድ እናት ልጆች ጭምር በአባት በመለያየታቸው ምክንያት ራሳቸውን በሁለት ብሔረሰብ መሀከል ያገኙታል።

'ብሔረሰብህን በአባት በደም የምታገኘው ነው' የሚሉም ያጋጥሙናል። በተለመደው አባባል ማሕበረሰባችን 'አባት እምነት እናት እውነት ናት' ይላል:: እና የእናት ደም ምን ስለሆነ ከብሄረሰብ እሳቤ ወጣ? በሌላ በኩል 'ጉዲፈቻ'የግለሰብና፣ 'ሞጋሳ'፣ የጎሳ ወደ ኦሮሞ ወይም ወደ ትግራይ ተቀላቅሎ የብሔረሰብ ሙሉ አባል የሚሆነውን ምን ሊሉት ነው? ሊላው ቀርቶ የውጭ ሀገር ዜጎችና ስደተኞች ኢትዮጵያ ውስጥ ገብተው በመኖር በሰፋት የኢትዮጵያዊ ዜግነት ክብር ቢቀዳጁ በየትኛው ብሔር ይታቀፋሉ? ይህንን ስንል በቁጥር ስለማነስ የሚሟገቱ አይጠፉም። ስለዜጋ ወይም ስለግለሰብ መብት ሀሁ ማስረዳቱ ሳይጠቅም አይቀርም።

ፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶለሣ ጂግሳ:-"የአማራ እና የኦሮሞ እውነተኛው የዘር ግንድ" የተሰኘ መፅሐፍ ለንባብ ሲያበቁ፤ ለፅሑፋቸው ግብአት በአብዛኛው የተጠቀሙት



t.me/OLDBOOKSPDF

የመረ ራስ አማን በላይን መረጃዎች ነበር። የተለያዩ መግለጫዎችም አገላብጠው ከነውስንነቱ በአማራና ኦሮሞ መሀከል ፍቅርን በመመሥረት፣ ለዓመታት የተተከለውን አሸህ ለመንቀል ያግዝ ዘንድ ብዙ ርቀት ተጉዘዋል። በአንጻሩ ዘውጌዎች፡- በርካታ የፈጠራ ልቦለዶች ያለምንም አሳማኝ ማስረጃ (አረቄ እየጋበዙ ከሰየሟቸው ባልቴቶች፣ ከማራዮች እና ሥራ ፈቶች መረጃዬ ብለው ባልት ሰብሰበው) በታላላቅ አዳራሾች በዘፈን ታጅበው ልክ እንደእውነተኛ ታሪክ ሲመረቁ፣ በተቃራኒው የተለፋበት የፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሣ ጂግሳ መፅሐፍ ይፋዊ ጦርነት ታውጆበታል። ዘመቻው መጠነ ሠፊ ስለነበር የጨዋዎችን ልብ ከመፅሐፉ ለማስሸፈት ጊዜ አልፈጀም። በከፋ ደረጃ የዚህን ያህል ምታ ነጋሪት ከተት ሠራዊት የተረባረበበት መግር ስለመኖሩ እርግጠኛ አይደለንም። የዘመቻው ምንጭ የአጣቃሽ መግለጫት ጦማር ስለመኖሩ እርግጠኛ አይደለንም። የዘመቻው ምንጭ የአጣቃሽ መግለጫት አጥረት ወይም ከሌሎች የነተሰሩዬ ኅብረአብ የሀሰት ታሪካዊ ልቦለድ መርዘኛ ትርክቶች ያልተሻለ ባለመሆኑ አይደለም።

መፅሐፉ በምንም መልኩ 'ቀሽቶ በማሥታረቅም' ይሁን የትችት ናዳ ሰለባ የሆነው የነጠኞችን የማጋጨት ጎራ በወቅቱ ስላሸመደመደው ነው። በየሠፈሩ የሚገፉ የነጠኞችን የማጋጨት ጎራ በወቅቱ ስላሸመደመደው ነው። በየሠፈሩ የሚገፉ የነጠኞችን እርስ በርስ በመመጋገብ የሚፈጥሯቸው የማለያየ የከፋት የጥፋት ዕሉፎች ነጠኞች እርስ በርስ በመመጋገብ የሚፈጥሯቸው የማለያየ የከፋት የጥፋት ዕሉፎች ነጠኞች ያለ፣ ወገንን መሠረት ቢስ ቢሆንም ቅንጣት ዘመቻ አይከኄድባቸውም። ኢትዮጵያን ያለ፣ ወገንን ከወገን ያሰናኘ፣ ትክክለኛውን እምነት ያስተማረ መሰደዱ በታሪክም የተረጋገጠ ሀቅ ነው። በእኛ እምነት ፕሮፌሰሩ እንደ ስማቸው ፍቅርን ለመመሥረት ባደረጉት ጉዞ የአማራና የኦሮሞን የዘር ግንድ አንድነትና ማንነት ለማረጋገጥ ብዙ ርቀት መጓዝ አያስፈልጋቸውም ነበር። አንድ አዳራሽ ውስጥ ከሁለቱም (አማራና ኦሮሞ) በነፍስ ወከፍ 500 በድምሩ 1,000 ሰው ጋብዘው በዐይን እንዲለዩላቸው እድል በመሥጠት ፈጥጠው ሲቀሩ ምላሹ ኢትዮጵያውያን ላይለዩ ተገምደዋልና በማየት መለየት ባለመቻሉ ይገኛል። ለመሆኑ በዐይን በማየት ኦሮሞና አማራን መለየት ይቻላልን? የምናየው እውነት እኛ ራሳችን እያለን አስረጂ ፍለጋ መማሰንን ምን ይሉታል?

እኛ አብዝተን ሀቁን ለማረጋገጥ አጠገባችን ሰዎች በቀረቡ ቁጥር ትክ ብለን ማየት ጀመርን። አረባዊውን፣ ፈረንጁን፣ ሞንጎሉን፣ አፍሪካዊውን፣ ህንዱን መልኩን በማየት ከእኛ እንዳልሆነ ለመለየት ብዙም አልተቸገርንም። ምክንያቱም ከእኛ ጋር የማያመሳስላቸው ነገሮችን ማግኘት ስላልከበደን። በድጋሚ ኦሮሞና አማራውን በዐይናችን እንደ ጉድ አፍጥጠን ለመለየት ሞከርን ከቶውኑ አልተቻለንም። አማርኛ የሚናገር እያሌ ኦሮሞ፤ ኦሮምኛ የሚናገር እልፍ አማራ አስተዋልንና ፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሣን ስለልፋታቸው አመሰገንን። ኢትዮጵያዊ ማንነትን ፍለጋ በ2019 ቢሾፍቱ አካባቢ የወደቀውንና በርካታ የተለያዩ ሀገር ዜጎች ህይወታቸውን ያጡበትን የ'ቦይንግ



t.me/OLDBOOKSPDF

ስራት ማከስ 8' ጠያራ ከስተት እንመልከት። በአካባቢው የሚገኙ ተወላጆች ማጅቶች እያወቋቸውም። ሆኖም የሰው ዘር በመሆናቸው ብቻ ሰባት፣ አሥራ ሁለት ... እያሉ ከኢትዮጵያዊ የለትሶ ወግ እንዲ የሆነውን ስርአት ተከትለው በሀዘን ተሰብረው ዕንባ በጉንጮቻቸው ኮለል እያለ ሲወርድ ታይቷል። ዋናው ያልተበረዘው፣ ጎጠኞች ያልከለሡት፣ ያልረከሰ ማንነት እሱ ነው። ለዚህም ነው ከፋፋዮች ህገናትና ወጣቶች በማይደርሱበት ቦታ እንዲቀመጡ መወትወት ያለብን።

ምክንያቱም ከመቶ ሚሊየን ህዝብ ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ኑሮ እየነጠቁ ልጆቻቸውን ማያሳድጉ፣ በረብጣ በምዕራቡና ምሥራቁ ዓለም በቅንጦት እንደላቀቀው ዜግነት (ኢትዮጵያ 'ትርፍ ዶላሮቻቸው የውጭ ባንኮችን ያጨናነቁ፣ ባለሁለት ዜግነት የምዕራቡን ዓለም ሀገራቸው የሆኑት') የፖለቲካ ነጋዴዎች፣እንኳን የሚኖሩበትን የምዕራቡን ዓለም ሀገራቸው የሆኑት') የፖለቲካ ነጋዴዎች፣እንኳን የሚኖሩበትን ለዘመናት ያቆዩንን ሥልጣኔ እና የሀገር ፍቅር ሊያወርሱን ይቅርና አባት እናቶቻችን ፍቅር በሚፈስላቸው ነዋይ ልክ ቀመውን። በእነርሱ ከፋት ኢትዮጵያ በየእለቱ በመንጋ ፍርድ የዜጎቿ ሰቆቃ የሚሰማባት ሀገር ሆነች።

ትላንት መማር ያስከበረውን ያህል ዛሬ፡- 'ልጅህ ዱላ ይዞ ወደ ታች ሲሮጥ ዐየሁት። ዩኒቨርሲቲ ገባ እንዴ?' እስኪባልመዘባበቻ ሆነ፡፡ ከቡሩ ታላቁ መካነ ትምህርት ያለ ትላንት ብዙ ግነት 'የብሔረሰቦች ልጆች መፈናከቻ ተቋም' እስከመሆን አንሶ ታየ። ትላንት በጋራ ሆነው በወል ለነፃነት ለፍትህ ለእኩልነት ለለውጥ፡- "መሬት ለአራሹ"፣ የሾላ የየኔ ቢጤዎችን ማቆያ ጣቢያ በመቃወም "ድህነት ወንጀል ነውን?፣ የምዕራባውያንን የባህል ወረራ በመቃወም "ጆሊ ጃኪዝም ይውደም!" እና ሌሎች መፈክሮችን በማንገብ ድምፃቸውን ያሰሙ የነበሩ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች (በተለይ 1997 -2018) 'በሰለጠነው' ዘመናችን የ'ካምፓስ' ግቢ እንደረገጡ በብርሀን ፍጥነት በቋንቋ ተለያይተው በመመዳደብ፡-

በአንደኛው ማደሪያ፡- መግርሣ ወዩሣ ዲሣሣ ገቢሣ ጫልቺሣ ቀበኔሣ አራርሣ ሚልኪሣ አያንሣ እኔሣ...

በሁለተኛው 'ዶርም'፡- ኪሮስ፣ ሐጎስ፣ ሔኖስ፣ ታቴዎስ፣ ገረገርጊስ፣ ሐዳስ፣ ሥላስ፣ መለስ፣ እኔስ...

በሦስተኛው መኝታ፡- መሠለ፣ ታከለ፣ አከለ፣ እምቢአለ፣ ምናለ፣ በቀለ፣ አስካለ፣ ብቃለ፣ አየለ...



t.me/OLDBOOKSPDF

በአራተኛው ክፍል፦ ጠንከር፣ ዘበር፣ መንከር፣ ሸኩር፣ ደንድር፣ አብራር፣ ድራር፣ ወጥር፣ ሞከር…

ሆነው ግጭቱም፣ ኅብረቱም፣ ትግሉም፣ ውሎውም፣ የመረጃ ልውውጡም በብሔረሰብ አጥር ተከለለ። ከከበቡ ወጥቶ በምልዐት የሚያስብ ጠፋ። በፍላጎታችን አባል ባልሆንንበት ስብስብ በመንጋ በመጃመል፤ የእኛ ባልሆነ እና ፈቃዳችን ባልታከለበት (Involuntary Membership) ለምን ከታሪክና ከተፈጠርንበት ሰውነት ነባሪያዊ የመኖር ዓላማ ጋር እንጋጫለን?

በአጠቃላይ አገላለፅ ከፍተቱ መጉላቱን ስንዳስስ ለትውልዱ የሚያስፈልገው ታላቅ መፍትሔ በታሪክ ትምህርት ዓላማ ላይ በመመሥረት ያለፉ ከፉ አሠራሮችን አምርሮ በመኮነን ማስወገድና፤ በዚህ ዘመን በፈጠራ ከሰማነው ወሬ በባሠ ሁኔታ ልቦለዱ ኢልቦለድ ሆኖ እየተደገመ ነውና ከጥላቻ አመለካከቶች በመራቅ የጨለማውን ዘመን የታሪክ ምዕራፍ በእጅጉ መዝጋት ያስፈልገናል። መጥፎውን በማሥተዋል ማራቅ እና ይገራ ዘንድ ማረቅ ለሁሉም ኃላፊነት የሚሰማው ዜጋ የቀረበ ጥሪ ነው። ከእንግዲህ የሚጠበቀው በነውን ገንዘብ አድርገን፣ አክብረን፣ በኩራት ለቀጣዩ ትውልድ ወገናችን ማስተላለፍ፤ ዛሬ ልንፈጥረው በምንተጋው መልካም መሠረት ላይ ቆመን የነገውን ብሩህ ህይወት አሸጋግሮ ማየት ነው። በዚህ የታሪክ እውነተኛ አረዳድ ተመሥርተን ከተጓዝን ሁላችንም ከመጠን በላይ እናተርፋለን።



t.me/OLDBOOKSPDF


## የኢትዮጵያ ታሪክ ምንጮች (ማስረጃዎች እና መረጃዎች)


የአንድን ሀገር ታሪክ በሚገባ አበጥሮ ለማወቅ የታሪክ ምንጮች የጀርባ አጥንት ሆነው ያገለግላሉ። የታሪክ ማስረጃዎች ወይም መረጃዎች ከሌሉ ታሪክ የሚባል ነገር የለም። ምንጮች፤ በጊዜ ቅደም ተከተል ተሰድረው፤ አስተማማኝ መሆናቸው በታሪክ አጠናን ሳይንሳዊ መንገድ ተፈትሾና ተረጋግጦ፤ በእውነታ ላይ ተመርኩዞ፤ ተነባቢ በሆነ መንገድ እንዲቀርብ ሲሆን ታሪክ ይሆናል። በዚህ መሠረት ያልተሰናዳ እና ያልተሰነደ ታሪክ ልቦለድ (ልብ ወለድ፣ የግል ፍላጎት)፣ ፈጠራ፣ ፖለቲካ ወይም ስሜት እንጂ ታሪክ አይደለም። በዚህ ተገቢ አካሄድ መሠረት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የግጭት መነሻ የሚሆኑና እየሆኑ ያሉት የታሪክ ማስረጃዎች ሳይሆኑ የታሪክ መረጃዎች ናቸው። በሀሰት ላይ ተመሥርቶ ከተገተረው የአኖሌ ሐውልት ጀምሮ አፄ ምኒልክ 'አሮሞን እናንቀው ተናግረዋል' እየተባሉ እስከሚቀርቡ ስሜት ኮርኳሪ ፅሑፎች ድረስ በቅጥፈት የተሞሉ ስለመሆናቸው እንደ ዘውጌዎቹ በሀሰት የፈጠራ መረጃ ላይ ሳይሆን በእውነተኛ ማስረጃ ላይ ተመሥርተን ገለፃ አድርገናል።


'የኢትዮጵያ ታሪክ በደብተራዎች የተዘጋጀ ነው' ከሚለው ጀምሮ እስከ ማስረጃዎቹ ሂደቶች (አወዛጋቢ የታሪካችን ገፆች በምዕራፍ አራት የምንመለከተው ሆኖ በዚህ ክፍል ውስጥ ምላሽ እየሰጡ መደምደም የሚያስፈልጋቸውን ጉዳዮች አንስተን ምላሽ እየሰጠን እንጓዛለን። በመሆኑም ከሌሎቹ ክፍሎች በበለጠ ሁኔታ ይህንን ክፍል የላቀ አትኩሮት በመሥጠት መመልከቱ እጅግ በጣም ጠቃሚ ይሆናል። የግጭት አበጋዝ የሆኑ ኢወገኖች ህዝብን ለማናከስ በፈጠራ ድርሳናቸው እፍረት ካልተሰማቸውና መጨናነቅ (Diction) ቃላትን ለመሰደፍ ካልተጨነቁ በእኛ ቃላት በመምረጥ ማፍረስ አይሞከርም። 'እሾህን በእሾህ ለማማሽ ከፍለ ዘመን ያቆሙትን የጥላቻ ግንብ ስንነቅል' የጥላቻ ፈታውራሪዎቹ እሾህ በተቀበቀበበት አካል ውስጥ ከቆየ ጥዝጣዜው የማያስተኛ፣ እየቆየ የሚመረቅዝ እና ምናልባትም በሂደት አካል ተቆርጦ እንዲጣል የሚያደርግ ነቀርሳ ይሆናል። ይህንን እሾህ ነቅሎ ለማውጣት የምንጠቀምበት እሾህ ግን ጠንካራ፣ እያመመም ቢሆን ፈውስ የሚሰጥ፣ ጥላቻው ቤት ለሠራባቸው ብቻ ለጥቂት ቅፅበት የህመም ስሜት ደቅኖ እስከወዲያኛው ከበሽታቸው የሚገላግላቸው ፍቱን መድሀኒት ነው።




t.me/OLDBOOKSPDF











t.me/OLDBOOKSPDF

የኢትዮጵያን ታሪክ በደምሳሳው የታሪክ ምሁራን በሁለት ዋና ዋና እንጓዎች ከፍለው ቢይዟል። ይኸውም ከዓባይ በስተሰሜን ያለውን የታሪካችንን ከፋይ እና ከዓባይ በስተደቡብ የሚገኘውን የታሪካችንን ጎን ነው። የማስረጃ እና መረጃ ምንጮች መሠረት በማድረግ ለተሰጠው ብያኔ መሠረታዊ ምክንያቱ ከዓባይ በስተሰሜን ያለው ክፍል ከታች በዝርዝር እንዳስቀመጥነው በበርካታ ታሪካዊ ማስረጃዎች የበለፀገ ሲሆን ከዓባይ በስተደቡብ ያለው ክፍል ግን የታሪክ መረጃዎች እና ትውፊቶች ላይ የተመረኮዘ ከመሆኑ የተነሳ ነው። በዚህም ሳቢያ የደቡቡ ታሪክ ሲፃፍ መነሻው ፖለቲካዊ ዓላማ ከሆነ በአያሌ ፈጠራዎች ማጨቅ ይቻላል። በሰሜኑ ታሪክ ውስጥም ተመሣሣይ ፈጠራዎችን ማዳሰብ ቢቻልም ትርክቱን በአሳማኝ ማስረጃዎች ለማፍረስ ግን የደቡቡን ያህል ፈታኝ አይሆንም። ለማንኛውም የታሪክ ምንጮቻችን ያላቸውን ይዘት በሚከተለው መልክ ለመቃኘት ተጨማሪ ግብአት እናክል። የኢትዮጵያንም ሆነ የዓለምን ታሪክ ለማጥናት ሁለት አይነት የታሪክ ማስረጃዎች ወይም መረጃዎች ይሰበሰባሉ።

የመጀመሪያው ቀደምት የታሪክ ምንጮች (Primary Sources) የምንላቸው ማስረጃዎች ሆነው ስለሚፃፈው ታሪክ ድርጊቱ በተፈፀመበት ወቅት በጊዜው፣ በቦታው፣ በሰአቱ በድርጊቱ ውስጥ ተዋናይ የነበሩ ስብእናዎች በዚያንው ወቅት ትተውልን አልፈው በክብር የተቀመጡ፣ በሳይንሳዊ ፍለጋ የተገኙ እና በጥናትና ምርምር የተደረሰባቸው ናቸው። በሁለተኛ ደረጃ የታሪክ ምንጭነት (Secondary Sources) ምድብ የተበየኑት ደግሞ ድርጊቱ ከተፈፀመ በኋላ የተሰባሰቡ፣ በነበረው ላይ ተመሥርተው የሚገነቡ (Historical Reconstructions) ይሆናሉ። ቀዳሚ የታሪክ ምንጮች ጭምር አሻሚ የመሆናቸው እድል እንደተጠበቀ ሆኖ ሁለተኛ ደረጃ የታሪክ ምንጮች ለበሬ ወለደ ድርሰት እጅግ በጣም የተመቻቹ ናቸው። በተለይም 'አቶ አገሌ ነገሩኝ'፣ 'ከወይዘሮ እከሊት የተወሰደ'፣ የሚሉ ትርክቶች ማረጋገጫ ጭብጥ የሌላቸው በመሆናቸው ለከት የለሽ ለሆነ ቅጥፈት ያላቸው ቅርበትም ተጨምሮ የደራሲውን ምኞት ለማረጋገጥ የሚደረገውን ጥረት ውስብስብና አስቸጋሪ ያደርገዋል።

ሁለተኛ ደረጃ የታሪክ ምንጮች ሆነው ከሚያገለግሉን አብዛኞቹ የታሪክ መፃሕፍት ናቸው። ዘውጌዎች በዋናነት ለማስረጃነት የሚጠቀሙባቸው መፃሕፍት ከ1970ዎቹ ጀምሮ የተዘጋጁ ይሆኑና አንደኛው ዘውጊ ፈጥሮ የፃፈውን ሀሰት፤ ሌላኛው ዘውጊ የተቀበለ ሌላ ውሸት ያክልበትና እርስ በርስ በመመጋገብ የደረሱትን ልቦለድ



t.me/OLDBOOKSPDF

እውነት አስመስለው ያቀርቡታል። ይህ ደግሞ የታሪክ ዕውቀት፣ ለሌለው ወይም ተደጋግሞ ውሸትን በመጋት ለተላመደው የዋህ ወገን እውነት መስሎ ቢታየው አይፈረድበትም። ይህ የማይናቅ ቁጥር ያለው ወገን ታሪኩን የመረዳት እድሉን ካገኘ ተረኮቹ ያስከተሉበትን ተፅዕኖ ተረድቶ ወደ እውነታው ለመመለስ አይቸገርም።

በሁለተኛ ደረጃ የታሪክ ምንጭነት በማገልገል በኩል ከታሪክ መጻሕፍት በመቀጠል የቃል ትውፊቶች፣ ረጅም ልበለዶች እና በድራማ ቲያትር ወይም ጭውውት መልክ ታሪክ ላይ ተመሥርተው የተደረሱ ገቢሮች ሊያገለግሉን ይችላሉ። ለምሳሌ፦ በሀያውና ትውልድ ተሻጋሪ ሥራቸው ምክንያት የሚመጥናቸውን የክብር ዶክተር ማዕረግ ያገኙት ሀዲስ አለማየሁ የደረሱት "ፍቅር እስከ መቃብር" የተሰኘ ረጅም ልበለድ ፊውዳል ኢትዮጵያ የነበራትን መልክ ለመዳሰሥ ለሚደረግ ጥናት ግብአት የመሆን እድል አለው። በተመሳሳይ የባለቅኔ ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህንን "የቴዎድሮስ ስንብት ከመቅደላ" ሁለተኛ ደረጃ የታሪክ ምንጭ አድርገን ልንወስደው እንችላለን። ሁለተኛ ደረጃ (ድህረ) ታሪክ ምንጮች ከመጀመሪያ (ቀደምት) የታሪክ ምንጮች ሲመዘዙ በግልፅ መታዘብ እንደሚቻለው የስሚ ስሚ በመሆናቸው የተአማኒነት ደረጃቸው እጅግ በጣም ዝቅ ያለ ነው።

የኢትዮጵያ የታሪክ ምንጮችን እና ከጥንት እስከ 1270 ያለውን የኢትዮጵያ ታሪክ ዘመን ለማጥናት የፕሮፌሰር ሠርገው ኃብለሥላሴ፦ "Ancient and Medieval History of Ethiopia to 1270 AD" ተስተካካይ የለውም። ከምንጮች አኳያ በምርምር ሥራቸው ከገፅ 1-19 እጅግ ዘርዘር ያሉ ማስረጃዎችን ስለሠጡን በዚህ የፅሑፋችን ከፍል መረጃዎቻቸውንና ማስረጃዎቻቸውን የማይናቁ ግብአቶች አድርገን ተጠቅመንባቸዋል። (ነፍሳቸው በአፀደ ገነት በሰላም ትረፍ ብለን ፍተሻችንን እንቀጥል።) በመቀጠል ኢሜሪተስ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴና ፕሮፌሰር ተሰማ ተዓ በተባ የታሪክ ፍተሻቸው የሰነዷቸው ጠማሮች በፅሑፉ ውስጥ ሠፊ ድርሻ ይዘዋል። በማስከተል የተለያዩ የታሪክ መዛግብትን አገላብጠን እውነታውን ለመግለፅ በሚከተለው አኳኋን አቅርበናል።

## በኢትዮጵያ ታሪክ ፍለጋ ቀዳሚ የታሪክ ማስረጃዎች

1. የኢትዮጵያን ታሪክ ለማጥናት ጅማሬ ከሚሆኑት መሀከል ወደ 1700 ዓመታት ገደማ እድሜ ያስቆጠሩ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች እና በነዚህ ላይ ተመሥርተው የተገፉ



t.me/OLDBOOKSPDF

1500 ዓመታት አካባቢ ዘመን የተቆጠረላቸው ምንጮቻቸውን ከድንጋይ ላይ ፅሑፎች (Inscriptions) ያደረጉ ምንጮች ተገኝተዋል። በንጉሥ ኢዛና ዘመነ መንግሥት (330 - 360) በሳባውያን በግሪክ በአረብኛ እና በግዕዝ ቋንቋዎች የተፃፉት እነዚህ ማስረጃዎች በተለያዩ ጊዜያት በጥንቃቄ ተቀድተው ተሰንደዋል። ፅሑፉን ከሰሜን ማስረጃዎች በተለያዩ ጊዜያት በጥንቃቄ እንደቀዳውና በ547 አካባቢ ኢንዲኮፕለስቲዩስ የተባለው ፀሐፊ በ527 በጥንቃቄ እንደቀዳውና በ547 አካባቢ እንዳሳተመው ተሰንዷል። አሜሪካዊው የታሪክ ፀሐፊ ሀሮልድ ማርከስ፡- "A History of Ethiopia" በሚል ርዕስ በሰነደው መፅሐፉ ገፅ 9 ካሰፈረው ፅሑፍ ሙሉውን ማግኘት ይቻላል።

2. ሳንቲሞች፡- ኢትዮጵያ ለዓለማቀፍ ንግድ ግብይት በአክሱም ዘመነ መንግሥት የተጠቀመችባቸው የወርቅ ሳንቲሞች እንዲሁም ለሀገር ውስጥ ንግድ የብርና የነሐስ ሣንቲሞችን ለመሸጥና ለመለወጥ ሥራ ትጠቀምባቸው እንደነበረ ከበቂ በላይ ማስረጃዎች አሉ። በተለይ በሦስተኛው ክፍለ ዘመን አፈላስ አዛና ዋዚባ ኢንዴቢስ የተባሉ ነገሥታት ሣንቲሞችን በማተም በስፋት ይገለገሉባቸው እንደነበር ተመዝግቦ በድርሳናት ተሰንዷል። ይህም በወቅቱ የሳንቲም ማተም ሥራ (Minting of coins) በኢትዮጵያ ውስጥ ተጀምሮ እንደነበረ አመላካች ነው።

3. የተለያዩ መንግሥታዊ የዲብዳቤ ልውውጦች፡- አዋጆች ደንቦች መመሪያዎች ፅሑፎች ከበቂ በላይ ማስረጃዎች በቤተመዛግብቶችና ሙዚየሞች በስፋት ይገኛሉ።

4. ኪነህንፃዎች፡- ቅድመ አክሱም የሐውልቲ፣ ሚላዞ፣ ከስከሴ፣ መጣራ፣ አዱሊስ የሥልጣኔ አሻራዎች በዐይን በሚታይ ደረጃ ፍርስራሾቻቸው ወይም ሐውልቶች ይገኛሉ። የአክሱም ሐውልቶች ዛሬም በሥፍራው ላይ ይታያሉ። 33 ሜትር ርዝመት የነበረው ወድቆ የሚታየው ሐውልት፣ አሁንም ቆሞ የሚገኘውና በፋሺስት ኢጣልያ ወረራ ወቅት ሮም ተወስዶ በነፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት ያላሰለሰ ጥረት የተመለሰው ሐውልት 25 ሜትር ርዝመት፣ ሌላው ቆሞ የሚገኘው ሐውልት ርዝመት 24 ሜትር እና ሌሎች የአክሱም ሐውልቶች፣ በአባ ዮሴፍ ተራሮች ከሚገኙ ቀያይ ተራሮች የተፈለፈሉ አስራ አንድ የላሊበላ ፍልፍል አብያተ ክርስቲያናት (ቤተ መድኃኔዓለም፣ ቤተ ማርያም፣ ቤተ ደብረሲናና ጎልጎታ፣ ቤተ መስቀል፣ ቤተ ደናግል ቤተ ገብርኤል፣ ቤተ አባ መታ፣ ቤተ መርቆሬዎስ፣ ቤተ አማኑኤል እና ቤተ ጊዮርጊስ ይገኛሉ:: እንደ ሀሮልድ ማርከስ ገለጻ ቤተ መድኃኔዓለም ወርዱ 33.5 ሜትር፣ ጎ 23.5 ሜትር፣ ከፍታው 11 ሜትር እና ከሁሉም ግዙፉ ነው::



t.me/OLDBOOKSPDF

ከነዚህም ቀድመው በላሊበላ የሚገኙ እነ ይምርሐነ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን፣ በዚያው በላሊበላ ዘመነ መንግሥት የታነፀቺው አዳዲ ማርያም ቤተ ክርስቲያን፣ የጀጎል ግንብ (ሐረር)፣ የፋሲለደስ ቤተመንግሥት (ጎንደር)፣ የጢያ ትክል ድንጋዮች (በደቡብ ክልል) የአባጂፋር ቤተ መንግሥት (ጂማ)፣ የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ቤተመንግሥቶችና ትክል ድንጋዮች ዛሬም ከነዘመን ታሪካቸው ለአብነት ቆመው በየዘመኑ ለነበረው የኪነ-ሕንፃ ሥራ ምስክሮች ሆነዋል።

5. ንዋየ ቅዱሳት :- በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት፣ ሙዚየሞች፣ አኩስም፣ ላሊበላ፣ በጣና ቂርቆስ ገዳማትና በመላው ኢትዮጵያ ይገኛሉ። ከእነዚህም መሀከል መስቀሎች፣ ፅና፣ ኩስኩስት፣ ጽዋ፣ ስማ ጎንደር ነጋሪት፣ አልባሳት፣ ከበሮዎች፣ መንበሮች፣ መቋሚያዎች እና የተለያዩ ቅርሶች በብሔራዊ ሙዚየምና በየሥፍራው በሚገኙ ሙዚየሞች ውስጥ በብዛት በመትበኘት ላይ ናቸው።

6. መጻሕፍት:- የተለያዩ ወንጌሎች እና ቅዱሳን መፃሕፍት፣ ድርሳናት፣ ገድሎች፣ ድጓ፣ ጾመ ድጓ፣ መዋስዕት፣ ለሀይማኖት ተግባር የሚያገለግሉ፣ ወንጌለ ዘወርቅ:- በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተከናወኑ ልውውጦች ተሰንደው የሚገኙበት መዝገብ፣ ባህር መዝገብ:- የመንግሥት ታላላቅ ገቢሮች የተመዘገቡበት ሰነድ፣ አፄ ቴዎድሮስ የታሪክ ምዝገባ ሥርአት ዘርግተው በነበረበት ወቅት የተፃፉ ሰነዶች፣ በአዲስ አበባ የአራት ኪሎ ቤተመንግሥት አካል የሆነው "የወልደ መስቀል ታሪኩ ቤተ መዛግብት" ውስጥ የሚገኙ ሰነዶች፣ በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት በ1944/45 የተመሠረተው "የታሪክና ቤተ መንግሥት ዜና ማሠናጃ ፅህፈት ቤት"፣ ለእስልምና እምነት አገልግሎት በአረብኛ ቋንቋ የተዘጋጁ አያሌ ማስረጃዎች መኖራቸው ለኢትዮጵያ ታሪክ አዘገጃጀት ሠፊ ድርሻ ይኖራቸዋል።

7. የሙዚቃ መሣሪያዎች:- በገና ክራር እምቢልታ ዋሺንት ቱልቱላ የዘመናት ቅርሶቻችን ሲሆኑ የጎንደርን ሥልጣኔ ለዋቢነት ብናነሳ ሀሮልድ ማርከስ በተመሳሳይ ምንጭ ገፅ 42 ላይ:- ዋሺንት ክራር መለከት ከበሮ እና የትንፋሽ መሣሪያዎች ስለመኖራቸውና ስለጥበቦቹ አስደናቂነት በጥልቀት ሰንዷል።

8. በደቡባዊው የታሪካችን ክፋይ የሚታዩ ሲቄ፣ ቦኩ፣ ከለቻ፣ ሚጪራ፣ ሶሮራ፣ ቁዲ እና የተለያዩ የባህል አልባሳት እና ቅርሶች ይገኛሉ።

9. እስከዛሬ ህያው ሆነው የቀጠሉ የቦረና እና የጉጂ የገዳ ሥርአቶች ከታሪካችን ዓበይት ፍፃሚዎች መሀከል ሊጠቀሱ ይችላሉ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ከነዚህ ሀያው ቅርሶች አብዛኞቹ በዩኔስኮ (የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የትምህርት የሳይንስና የባህል ድርጅት) በሰው ልጅ የዓለም ቅርስነት ተመዝግበዋል። ከእነዚህም መሀከል በባህልና ቱሪዝም ሰህፈት ቤት የተገኘው መረጃ እንደሚያመላክተው፡-

ሀ. ዐሥራ አንዱ የላሊበላ ፍልፍል አብያተ ክርስቲያናት (1978)

ለ. የፋሲለደስ ግቢ እና ሌሎች ኅውልቶች ጎንደር (1980)

ሐ. የአኩስም ታሪካዊና የአርኪዮሎጂ ጣቢያ (1980)

መ. የ'ሆሚኒድ' ዐፅም የተገኘበት የታችኛው አዋሽ ሸለቆ (1980)

ሠ. የጢያ ትክል ድንጋዮች (1980)

ረ. የአሞ ወንዝ ሸለቆ አውስትራሎፒተከስ ኤቶፒከስ የተገኘበት (1980)

ሰ. የሐረር ጀጎል የምሽግ ታሪካዊ ከተማ (2006)

በተጨማሪም "ጨምበለላ"፣ "የገዳ ሥርዓት"፣ በሂደት ላይ ያለው "የሆራ አርሰዲ ኢሬቻ በዓል" ጎልተው ይወጣሉ።

**ሁለተኛ ደረጃ (ድህረ ታሪክ) ምንጮች**

ኢትዮጵያ የረጅም ዘመናት ታሪክ ባለቤት እንደመሆኗ ስለገናናነቷ የተጻፉ እያሌ ድህረ ታሪክ መረጃዎችን እናገኛለን። ዋነኞቹ እንደሚከተለው ተመርጠው ቀርበዋል። የታሪክ አባት በመባል የሚታወቀው ሄሮዶቱስ ስለ ኢትዮጵያ ሲፅፍ፡- 'ታላላቅ ዝሆኖች፣ ዘጲ የሚባል ጠንካራ ዛፍ፣ በየሸንተረሩ ብርቱካን፣ ትርንጎ፣ ፓፓያ፣ በኩረ ሎሚ ወዘተርፈ እንደነበሩባትና በተለይ የሐር ዛፍ ከኢትዮጵያ ውጪ እንዳላገኘ' መግለፁን አዕምሮ ንጉሤ "ጥንታዊ የኢትዮጵያ የሰላም ጥበቃ ታሪክ (ከቅራት - ዘመናዊ ፖሊስ)" የመጀመሪያው ገፅ ላይ ጠቅሶልናል።

በጥንቱ ዘመን የግሪክ ፀሐፊዎች ሄሮዶቱስ (የታሪክ አባት)፣ የኢሊያድና የኦዴሲየስ ደራሲ ዐይነ ሥውር ልበ ብርሀን ሆሜር ኢትዮጵያን በፅሑፋቸው ውስጥ ጠቅሰዋል።



t.me/OLDBOOKSPDF

በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ (እንደ ታሪክ ማስረጃ) ኢትዮጵያ ተደጋግማ ተጠቅሳለች። ያልታወቀ የግሪክ መርከብ 1ኛ፫፱ን፡-"The Periplus of the Erythrean Sea" በተሰኘ 'መፅሐፈ እድ' (ስለዘመኑ የአዱሊስና ስለአክሱም መስተጋብር የገፈው ፅሑፍ በውስጡ ከያዛቸው ቁም ነገሮች መሀከል ማርክስ 2002፤4 በ60 ዓ.ም ይኖር ስለነበረው የአክሱም ንጉሥ ዞስካለስ፤ የአዱሊስ ወደብ ከዞላ ባህረ ሠላጤ 20 ማይል ገባ ብላ የምትገኝ መሆኑንና ከተማዋ የነበራትን ዳራ፣ ስለ ንግድ ልውውጥ፣ ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ ተንትኖ ያወሳው ሊጠቀሱ ይችላሉ። ይህም በወቅቱ ለነጋዴዎች መፅሐፈ እድ ወይም የአቅጣጫና የግብይት መረጃ ምንጭ ሆኖ አገልግሏል።

በኢትዮጵያ ስለክርስትና አመጣጥ ለማመላከት የጣረው በሩፊነስ የተተወው ማስታወሻ፡-'Historia Ecelesias' እና በስድስተኛው ክፍለዘመን በግሪካዊው የመርከብ ካፒቴን ኮስሞስ ኢንዲኮፕለስቲዩስ የተተወልን፡- "The Christian Topography" በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በአመዛኙ (በታሪክ አጠናን ክፍል ተመልከተዋል።) እና በደቡቡ የሀገራችን ክፍል ሣሣ ባለ መልክ መረጃዎችን አበርክተውልናል።

## ክብረ ነገሥት (Glory of the Kings)

የዛግዌ ዘመን መንግሥትን አስመልክቶ የተዘጋጁ መፃሕፍት "የላሊበላ ሥጦታዎች" እና "የባሮክ መፅሐፍ"፤ በ1520 ላሊበላን የጎበኘው ፖርቱጋላዊው ቄስ አልቫሬዝ ያኖራቸው የአብያተ ክርስቲያን ማስታወሻዎች፤ በ1096 የተገፈ ማስረጃ በዛግዌ ዘመነ መንግሥት አይሁዶች የማህበረሰቡ አካል እንደነበሩና በተለይም ሲብዱ የተባለ የአይሁድ ቤተሰብ የንግድ ድርጅት መሥርቶ በሰፊው መታወቅ መቻሉን የሚያስረዱ ማስረጃዎች፤ በ'አፈ ታሪክ' የምትታወቀው ንግሥተ ሳባ (1013 - 987ዓ.ዓ) እና ቀዳማዊ ምኒልክ (982 -957 ዓ.ዓ) እንደነበሩ ገልፀው የተፃፉ መረጃዎች አሉ። (ዘመናቱ ብቻ ባዬ ፈለቀ "Questions About Kibre Negest" በሚል ካሰናዳው ጦማር የሽፋን የውስጥ ገፅ ተወስደዋል።)

እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው አስገራሚው ነገር፡- ስለንግሥተ ሳባ የተፃፉ እስራኤላዊ ምንጮች አያሉ፣ የእስራኤል የብሉይ ጊዜ ልምዶች / ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበሩና አሁን የሌሉ በኢትዮጵያ እስካሁን የቀጠሉ ትውፊቶች መኖራቸው እየታወቀ፣ ዘመናት ባስቆጠረውና ፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት፡- "Church and



t.me/OLDBOOKSPDF

State in Ethiopia, 1270 - 1527" በሚል ርዕስ ባዘጋጁት አስደናቂ መፅሐፋቸው በገፅ 64 በጉልህ እንደሚታየው በ1225 ወደ ግዕዝ የተተረጎመው ስለ ንግሥተ ሳባ ጭምር የሚጠቅሰው ከኮፕቲክ ቋንቋ ወደ ግዕዝ የተተረጎመው የ"ክብረ ነገሥት" ማስረጃ ይገኛል።

ሀሮልድ ማርክስ "የኢትዮጵያ ታሪክ" በተሰኘው መፅሐፉ ገፅ 17 እንዳሰፈረው "ቀዳማዊ ምኒልክ የኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ማከዳና የእስራኤሉ ንጉሥ ሰለሞን ልጅ እንደሆነ" መረጃዎች አግኝተን፤ የየቤተ ክርስቲያን አባቶች ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተቀባበሉት፤ 'ሰሎሞናዊ ሥርወ መንግሥት' በዚህ ትውፊት ላይ ተመሥርቶ ከ700 ዓመታት በላይ ኢትዮጵያን መምራቱ፡ እየታወቀና ሌሎች ምልክቶች ዕየታዩ ይህን በመረጃዎች የበለፀገ ትውፊት እና ኢትዮጵያን በዓለም ታሪክ ውስጥ ተጨማሪ ጉልህ ስፍራ ሊያሰጣት የሚችል ጉዳይ 'አፈ ታሪክ' ነው ብለው አጣጥለው፤ ዘውጌዎች የፈጠሩትን የመከፋፈል ድርሰት እንድንቀበል መሞከራቸው ነው። ይህ እውነት ሀገርን በመጥቀም ረገድ ያለውን ፋይዳ ጭምር ሆነ ብለው ዘግተውታል። በዚህ በኩል የታሪክ ምሁራኑም ታሪኩን ዝግ በማድረጋቸው ከተጠያቂነት አያመልጡም። በአዘጋጁ እምነት የታሪክ ምሁራኑ ያጠኑበትን ርዕስ "ሌላው እንዳይከፍተው ያልተፈቀደለት የግል ርስተ ጉልት" አድርገው አትመውታል። በመሆኑም አንዱ የቆለፈውን ሌላው እንዳይከፍተው እንቅፋት ሆኗል።

## የቃል ትውፊቶች

ከዓባይ በስተደቡብ ያለው የሀገራችን ግሚሡ ክፍል ታሪክ በሚገባ ተሰንዶ አልተያዘም። "የባለ መቶ ዓመት ታሪክ" ደራሲዎቹ ዘውጌዎች ታሪኩ ያልተመዘገበበትን ምክንያት ከነገሥታት ጫና ጋር ያያይዙታል። እውነታውን በቀጣዮቹ ክፍሎች ተንትነን የምናሳይ መሆኑን ጠቀስ አድርገን በዋናነት "የደቡቡ" የሀገራችን ክፍል ታሪክ ያልተሰነደው፡-

1. እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የፅሑፍ ታሪክ ልምድ ባለመዳበሩ፤

2. ለባህር በር በቀላሉ ተደራሽ ስላልነበረ፤

3. የውጭ ፀሐፍት በቀደመው ጊዜ እምብዛም ስላልጎበኙት፤



t.me/OLDBOOKSPDF

4. በአርኪዎሎጂ ቁፋሮ ረገድ የተገኙ ማስረጃዎች እንደ ሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በርከት ያሉ አለመሆናቸው እና

5. አውሮፓውያን የቃል ትውፊትን ፊዕም አይቀበሉና ቦታ የማይሰጡ ስለመሆኑ ከቀጣዮቹ ክፍሎች መረዳት ይቻላል።

ይሁንና የደቡቡን የሀገራችንን ክፍል ታሪክ ለማጥናት የቃል ትውፊቶች የጀርባ አጥንት ሆነው ስለሚያገለግሉን፤ የተመዘገቡ የትኞቹም ታሪኮች የጋራ መሆናቸውን ተገንዝበን፤ ባለፈው ተሚልቶ የተመዘገበ የጋራ ታሪካችን ባለመኖሩ እየተቆጨን እና መፍትሔው ዛሬ ለታሪክ ለውጥ መነሳት መሆኑን ልናመላክት እንወዳለን። ለአብነት፡- የቦረና እና የጉጂ ማህበረሰብ ታሪክ አዋቂዎች ወይም 'ሃዩዎች' ተንቀሳቃሽ ቤተ መግሕፍት ናቸው ቢባሉ ግነት አይደለም። ከ1460ዎቹ ጀምሮ እስከዛሬ ማህበረሰቡን የሚመሩትን አባ ገዳዎች፣ በየዘመኑ ያጋጠሙ ክስተቶችን፣ ሁለ ምሉዕ መስተጋብር፣ የእምነት ሥርአት፣ ወግ ባህል ልምድ፣ የቅራኔ አፈታት፣ የፍትህ ሥርአት እንዲሁም እድሜ ጠገብ አስተዳደራዊ ሥርአቱ ያሳየውን መሻሻል በላቀ ጥበብ ይተርኩልናል። ማህበረሰቡ ከሌሎች ጋር ያደርጋቸው የነበሩ ግንኙነቶችን፣ መገፋፋቶችን፣ የተገለሉ ማህበረሰቦችን ሁኔታ፣ የሴቶችን ድርሻ ወዘተርፈ ጠንቅቀው በአእምሯቸው ሰሌዳ በመመዝገባቸው ወርቃማ እድል የተነሳ የጎደለውን ለማሟላት ዋነኛ ምንጮች ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ።

በርግጥም ምንጮቹን በመጠቀም ሥፍር ቁጥር የሌላቸው የታሪክ፣ የ'አንትሮፖሎጂ'፣ 'የሶሲዮሎጂ'፣ የህግ፣ የባህል፣ የህክምና፣ የቱሪዝም እና ሌሎች አያሌ ጥናቶች መተግበር ችለዋል። ይሁንና በዚህ ረገድ ሁለት መሠረታዊ ችግሮች ይስተዋላሉ። የመጀመሪያው፡- በበርካታ ልፋትና ውጣ ውረድ የተዘጋጁትን የጥናትና ምርምር ሥራዎች ፈትሾና አረጋግጦ የታሪካችን አካል ያለማድረግ ችግር ሲሆን፤ ተያያዥ ምክንያት ደግሞ አጥኚዎቹና በተለያዩ ጊዜያት ጥናቱን የመሩ ግለሰቦች የመረጃ ምንጭ ሆነው የሚገለገሉባቸውን ግለሰቦች በገንዘብ በመደለል እና ከአእምሯቸው እንቅተው ለፖለቲካ ፍላጎታቸው የተዛባ መረጃ እንዲሰጡ ማድረጋቸው እና ያገኟቸውን መረጃዎች አጣምመውና አዛብተው የቡድን ፍላጎት ማራገፊያቸው ማድረጋቸው ነው። ድርጊቱ ታማኝነታቸውን የሚያደበዝዝ ቢሆንም የማይቀየሩ ታሪካዊ እውነቶችን በቀጥታ በመውሰድ፤ የተጣመመውን በታሪክ አጉዪ መነፅር አብጠርጥሮ በመፈተሽ ከዓላማው አኳያ በማሸትና በመግራት ስለ ሀገራችን ህዝብ ታሪክ የተሻለ ሥዕል መያዝ ይቻላል።



t.me/OLDBOOKSPDF

ከላይ ነካ አድርገን ለማሳየት እንደሞከርነው በኢትዮጵያም ሆነ በአፍሪካ ታሪክ ውስጥ የቃል ትውፊቶች የታሪክ አካል እንዳይሆኑ በማድረግ ረገድ የአውሮፓውያን ዘረኛ አመለካከት (Pseudoscientific racist notion) የፈጠረው ለአፍሪካ ያላቸው ንቀት ቀዳሚውን አሉታዊ ጫና ፈጥሯል። ከዚሁ ጋር የሚይከደው ተገቢ ትኩረት አለመስጠቱ፤ በተለይ ከራሱ ከሁብረተሰቡ የፈለቁ ምሁራን ሲላው ላይ ጣታቸውን ከመቀሰር ውጪ የሚያውቁትን የራሳቸውን ማህበረሰብ ታሪክ አዘጋጅተው በኢትዮጵያ ታሪክ አካልነት እንዲመዘገብ የሚያስችል ተነሳሽነት አላሳዩም።፡

የነዚህና የሌሎች ታሪክ ፀሐፊዎች የዳተኝነት ንፍገት ተዳልበው ከዓባይ በስተደቡብ የነዚህና ... ያለው የታሪካችን ከፋይ በቅጡ አልተሰናዳም። ሁልጊዜም ለመጀመር አይረፍድምና አውሮፓውያኑ በቅርቡ ባሳዩት የአመለካከት ለውጥ እና አፍሪካውያን ታሪካቸውን በደማቅ ቀለም ለማስፈር የነጮች ቡራኬ ስለማያስፈልጋቸው በዘርፉ ጉልህ ለውጥ ተመዝግቧል። ለዘውጉ ትኩረት በመስጠት የቃል ትውፊቶች እንደምን ባለ አኳኋን የታሪክ አካል መሆን እንደሚገባቸው እና ሰፍኖ የቆየውን የምዕራባውያኑን ተፅዕኖ አውቁና የአዘጋጁ የግል ምርጥ ፕሮፌሰር ተሰማ ተ'ዓ በዚህ ፅሑፍ በቀጣይ በስፋት እንደምንመለከተው፡- "Issues in the Historiography of Africa" በተሰኘውና ለህትመት በበቃው ስነዳቸው አብራርተው ዐሳይተውናል።

"Quran School System in Ethiopia" በሚል ርዕስ ዶክተር ኃይለገብርኤል ዳኜ ባሰናዱት የምርምር ሥራ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል እና ማዕከላዊ ኢትዮጵያ አካባቢዎች የቤተክህነት ትምህርት በመስፋፋቱ በቃል የተወረሱ ትውፊቶችን የምናገኘውን ያህል ሙስሊሙ ማህበረሰብ በስፋት በሚኖርባቸው አካባቢዎች፦ ወሎ፣ አርሲ፣ ባሌ፣ ሐረር፣ ካፋ እና የሱዳን ድንበር አካባቢዎች በአረብኛ የማንበብና አብዛኛውን የቁርአን ክፍል በቃል የመያዝ ልምድ ዳብሮ ስለነበር የኢትዮጵያን የትምህርት ታሪክ አስፍቶ ለመፃፍ በር ይከፍታል። በአጭር መዝጊያ ለማጠናቀቅ የኢትዮጵያ ታሪክ ምዝገባ በሰሜኑ የሀገራችንክፍል ዳኅስ ብሎ የደቡቡ ሳሳ ያለ ነው።

ችግሩ የዘውግ ፖለቲከኞች እንደሚሉት በነገሥታት ጫና የተፈጠረ ሳይሆን የዘመናት ነባራዊ እውነታ ውጤት ነው። (ከግብፅ ጋና ዚምባብዌና ውሱን የጥንት ሥልጣኔ ከታየባቸው ታሪካዊ ጣቢያዎች በስተቀር ልክ እንደ ደቡቡ የሀገራችን ክፍል ሁሉ የፅሑፍ ጥበብ ያላዳበሩ ማህበረሰቦች ታሪክ አልተሰነደም።) በደርግ እና የወያኔ 44 ዓመታት የአገዛዝ ዘመን ከማውራት ባለፈ በቁጥር አነስተኛ ከሆኑ ማህበረሰቦች በበቂ ደረጃ ከመጀመሪያ እስከ ሦስተኛ ዲግሪ የተማሩ ምሁራን ማፍራት ባለመቻሉ ልክ የነዚህን ወገኖች ታሪክ በአግባቡ መሠነድ አላስቻለም። ባለፈው መቆዘም ለመፍትሔው ጋት ያህል ስለማያራምድ የማህበረሰቦቹ ታሪክ በጀት ተመድቦ



t.me/OLDBOOKSPDF

እንዲጠና መትጋት ያስፈልጋል። የረጂም ጊዜ ግብ ነድፎ ታሪካቸው ባልተመዘገበ ማህበረሰቦች አካባቢ ትምህርትን ማድረስ በግድ አስፈላጊ ነው።

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎች

ስለ ኢትዮጵያ ቋንቋዎች ከማውሳታችን በፊት ስለ ኢትዮጵያ አኩይ ልሂቃንና ጭፍን ስለ ኢትዮጵያ ቋንቋዎች ከማውሳታችን በፊት ስለ ኢትዮጵያ አኩይ ልሂቃንና ጭፍን ጀሌዎቻቸው ባሕርይ ጥቂት እንበል:: እጅግ አብዝቶ ችግርን በመደራረብ ተላምዶ መኖር የኢትዮጵያ 'ፌደላውያን' መሠረታዊ ችግር ነው። ለችግር ሐውልት አቁሞ በ'ሰልፊ ስቲክ' በተገተረ ሐውልት ፊት ተደንቅሮ የግል ምስል በመውሰድ በጥላቻ ለመመፃደቅ ከመላላጥ በዘለለ፤ የዚያንው ማኅበረሰብ ባህላዊ እሴት፣ ምጣኔ ሀብታዊ መስተጋብር፤ ማኅበረሰባዊ አብሮነት፣ አስተዳደራዊ ዳራ፣ የቋንቋ ውበት እና መሠል ፀውዶችን ለመጸፍ ቅንጣት ጥረት ሲያደርጉ ዐይታይም። ለከፋት የሚሽቀዳደሙትን ያህል ለፍቅር ጠብታ አስተዋፅዖ የላቸውም። 21ኛው ክፍለ ዘመን የሚጠይቀው የላቀ የዕይታ ለውጥ እንጂ ድሮ ላይ ተገትሮ መቆዘም አይደለም። የችግር ተጨማሪ ቅርፊት ከመሆን የመፍትሔው አካል ለመሆን አንድ ጋት መራመድ ለለውጥ ጉዞ ጅማሬ ነው። 'ወደፊት መውደቅም ወደ ግቡ መቃረብ' ቢሆንም እኛ ወደፊት ለመሄድ እንቆማለን። የኢትዮጵያ ታሪክ ምሉዕ ይሆን ዘንድ ዜጎች የወጡበት ማኅበረሰብ ድርሻ በተገቢው ልክ መወከል አለበት። ምክንያቱም ሀገር የሁሉም እናት ናትና።

በኢትዮጵያ ውስጥ የሚነገሩ እና ታሪኳን ለማዳበር የሚረዱ ከ80 በላይ ቋንቋዎች እንዳሉ በዘርፉ ፍተሻ ያደረጉ ምሁራን ያስረዳሉ። ኢትዮጵያውያን አብዝተን ሀገራችንን መውደዳችንን መለፈፋችን ባይቀርም በተግባር ሲመዘን በአያት ቅድመ አያቶቻችን አብሮነት ልክ ኢትዮጵያውያን አንተዋወቅም። አብዝቶም የጋራ ታሪካችንን በውል የተገነዘብነው አይመስልም። ሀገር ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ፡- የተወሰነው ወገን 'ሰው ነው፤ ገሚሱ ብዝሀ ህይወታዊ ተፈጥሮዋ ነው፤ ሌላው ሁሉም ተጣምሮ ነው' አይነት ውይይት ከማካሄድ አልፎ ሀገርን በወጉ አልተገነዘብንም። ሀገር ማለት በእርግጥ ህዝብም ነው። ህዝብ ብቻውን ከመሬቱ ውጭ ግን ባይተዋር ነው። ሀገር ሰው ብቻ አይደለም፡- ሀገር በድንበር ውስጥ ያለ የብስ፤ ሀገር የአየር ክልል፣ ሀገር መንግሥት፣ ሀገር ሉዓላዊነት፣ ሀገር ነፃነት፣ ሀገር ባህልና እምነት ወዘተ ሀገር እንደ ስሟ ብዙ ናት ። ሀገር ብዙ ነገር የበርካታ ሀቆችድምር በመሆኗ ከነፍስና ስጋችን ጋር ተሸምናለች።



t.me/OLDBOOKSPDF

ወደ ቋንቋዎቻችን ምንጭ ስናማትር በአፍሪካ ውስጥ ከ1,000 በላይ ቋንቋዎች እንደሚነገሩ አያሌ ማስረጃዎች ይነግሩናል። እነዚህ ቋንቋዎች ደግሞ በአራት ዋና ልዕለ ቋንቋዎች ስር ተመድበዋል።

1. ኒጀር ኮንጎ፡- ከ300ሚሊየን እስከ 400ሚሊየን የቋንቋው ተናጋሪዎች እንዳሉት ይገመታል።

2. አፍሮ እስያዊ ቋንቋ፡- በአፍሪካ በሁለተኛ ደረጃ በስፋት የሚነገርና ከ200ሚሊየን እስከ 300ሚሊየን ተናጋሪዎች በመግባቢያነት የሚገለገሉበት ነው።

3. ናይሎ ሰሀራን፡- 30ሚሊየን የሚሆኑ የቋንቋውን ተጠቃሚ ማህበረሰቦች አቅፎ ይዟል።

4. ኮይሳን፡- በተሰኘው ቋንቋ ሥር ወደ 300,000 የሚጠጋ የቋንቋው ተናጋሪ ይገኛል። ኢትዮጵያውያን ከአራቱ ልዕለ ቋንቋዎች መሀከል አፍሮ እስያዊ እና ናይሎ ሰሀራን ብቻ የሚናገሩ መሆናቸው፣ እርስ በርሳቸው የሚዛመዱና ከአፍሪካውያን ልዕለ ቋንቋ ተናጋሪዎች ምድብ ውስጥ መገኘታቸው ያላቸውን ትሥሥር በአመዛኙ የመግለፅ ታላቅ ጉልበት አለው። በቋንቋዎች ዙሪያ እየተካሄደ ያለው ፍተሻ ባይቋጭም ኢትዮጵያውያን የሚናገሯቸው ቋንቋዎች በኢጣሊያዊው የታሪክ ምሁር ካርሎ ኮንቲ ሮሲኒ፣ M.L. Bender የተባለው ምሁር፡- "Languages in Ethiopia" በተሰኘው የምርምር ስራው ያኖራቸው ዝርዝሮች እና መሠል ምንጮች ባሰፈሩት ላይ በመንተራስ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ከታች ባለው መልክ ተዘርዝረዋል፡፡

1. አፍሮ - እስያዊ ልዕለ ቋንቋ፡- በሥሩ የተመደቡ የቋንቋ ቤተሰቦች የሚከተሉት ናቸው። እነርሱም፡-

1.1 የኩሽቲክ ቋንቋዎች

አፋር፣ አላባ፣ አርቦሬ፣ አውንጊ፣ ባይሶ፣ ቡርጂ፣ ቡሳ፣ ደሰነች፣ ገዉዳ፣ ጌዴኦ፣ ጊዶሌ፣ ሀዲያ፣ ሀምተንጋ፣ ኢሮብ (ሳሆ)፣ ካይላ፣ ከምባታ፣ ቀቤና፣ ቅማንት፣ ኮንሶ፣ ሊቢዶ፣ ኦሮሞ፣ ቋራ፣ ሲዳማ፣ ሶማሊ፣ ጠምባሮ እና ፀማይ ...



t.me/OLDBOOKSPDF

## 1.2 የሴማዊ ቋንቋዎች

አማራ፣ አርጎባ፣ ቻሀ፣ አዝኸ፣ ጉመር፣ ጉራ፣ ዶቢ፣ እንደጋኝ፣ እናር፣ እነሞር፣ ገይጦ፣ መስመስ፣ ጋፋት፣ ግዕዝ፣ ሐረሪ፣ መስቃን፣ ሙኸር፣ ስልጢ፣ ወርጂ፣ ሶዶ፣ ትግርኛ፣ ወለኔ፣ ዛይ...

## 1.3 የኦሞቲክ ቋንቋዎች

አንፊሎ፣ አሪ፣ ባምባሺ፣ ማኦ፣ ባስኬቶ፣ ቤንች፣ ቦሮ፣ ቻራ፣ ዳወሮ፣ ኩሎ፣ ኮንታ፣ ዲሜ፣ ዲዚ፣ ዶርዜ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ወላይታ፣ ጋንጁሌ፣ ጊዲቾ፣ ጋንዛ፣ ሐመር፣ ሆዞ-ሴዞ፣ ማኦ፣ ካቾማ፣ ከፊቾ፣ ኮሬቴ፣ ማሌ፣ ማሎ፣ መር፣ ሞቻ፣ አይዳ፣ ሼ፣ ሼኮ፣ የምሳ፣ ዘይሴ...

(አንዳንዶቹ ቋንቋዎች በጣም ከመቀራረባቸው የተነሳ የአንዱ ቋንቋ ተናጋሪ የሌላኛውን መረዳት ሲችል፤ ሌሎቹ ለመግባባት ሊቸገሩ ይችላሉ። ለምሳሌ፡- አሮምኛን እያስቀደምን ሶማልኛን እያስከተልን የቁጥሮቹን አጠራር ብናጤን ከፍተኛ ቅርርብ እናገኛለን።

1 ቶኮ= ኮው፣ 2 ለማ= ለቦ፣ 3 ሰዲ= ሰዳህ፣ 4. አፉር= አፈር፣ 5 ሸን= ሸል፣ 7 ቶርባ= ቶዶቦ፣ 8 ሰዴት= ስዴድ፣ 9 ሰገል= ሰጋል፣ ... 1000 ኩማ =ኩን... ፤ በተመሳሳይ የግዕዝ ቋንቋ ከአማርኛ እና ትግርኛ ጋር ያለው ቅርርብ በጣም ከፍተኛ ነው። ንዑ ኑ፣ ሰምዑኒ ስሙኝ፣ ኩልክሙ ሁላችሁም፣ ወእንግርከሙ ልንገራችሁ፣ ለነፍስየ ለነፍሴ፣ ዘፀራህኩ ጠራሁት፣ በአፉየ በአፌ፣ ዓመፃ ዓመፃ፣ ልብየ ልቤ ...፤ በተመሳሳይ በትግርኛ እና በግዕዝ መሀከል ብንፈትሽ የበለጠ ቅርርብ እናስተውላለን። በተመሳሳይ በወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ እና ዳወሮ መሀከል ባለው መቀራረብ የተነሳ አራቱን በማቀናጀት "ወጋጎዳ" የሚል ልዩ ቋንቋ የመፍጠር ዝንባሌም በወያኔ ዘመነ መንግሥት ታይቶ ነበር፤ ውጥኑ በመረረ ተቃውሞ መገታቱን ልብ ይሏል።)

## 2. ናይሎ ስሀራ ልዕለ ቋንቋ

የቋንቋ ቤተሰቦች፡- ቻሪ - ናይል እና ኮማን ሲሆኑ፤ ቋንቋዎቹ ደግሞ፡- አኙዋክ፣ በርታ፣ ፈዲሺ፣ ገባቶ፣ ገሚሊ፣ ቦዲ፣ ሚኤን፣ ቲሽና፣ ጉሙዝ፣ ትሊት፣ ኮማ፣ ኩናማ፣ ከዋማ፣ ከዌጉ፣ ሜባን፣ መሠንጎ፣ ሙርሌ፣ ሙርሲ፣ ኔራ፣ ኑዌር፣ ኛለም፣ ኛንጋቶም፣ ኦፖ፣ ሸቦ፣ ሳቡይ፣ ሱርማ፣ አዱክ... ናቸው።



t.me/OLDBOOKSPDF

3. በቋንቋ ከፍፍሉ ውስጥ ያልተመደቡ፡-

ካይላ፣ አንንታ፣ ሬር-በሬ፣ ወይጦ እና የኢትዮጵያ የምልክት ቋንቋዎች ናቸው።

በዚህም መሠረት የኢትዮጵያን ታሪክ በተሟላ ሁኔታ ለማጥናት በሚደረገው ሁለንተናዊ ጥረት ከሚከተሉት የትምህርት ክፍሎች ጋር ተቀናጅቶ መሥራት ይጠይቃል። በፍልስፍና ረገድ የአዜ ዘርዓያዕቆብ ምልከታዎች፣ የኦሮሞ ህግ ሴራ፣ በተመሳሳይ 'ሶሲዮሎጂ'፣ 'አንትሮፖሎጂ'፣ 'አርኪዎሎጂ'፣ ስነልቡና፣ ሆቴል፣ ቱሪዝም እና የተለያዩ ዘርፎች የምርምር ሥራዎች በታሪክ ምንጭነት አዎንታዊ ድርሻ ይኖራቸዋል። ቋንቋዎች በታሪክ ትምህርት ውስጥ ከቋንቋዎች ከፍፍል አኳያ፣ የየማህበረሰቡን የት መጣ ለማወቅ፣ የምርቃት ሁኔታ፣ ማህበራዊ መስተጋብር፣ የስብሰባ አመራር፣ የመሪዎች የማዕረግ ስምና የአስተዳደር አወቃቀር ለመገፍ ይረዳሉ። ያለ ቋንቋ የሚነገር ታሪክስ የት አለ?

## የኢትዮጵያን ታሪክ ለማዘጋጀት የሚረዱ የጽሑፍ ምንጮች

ከዓባይ በስተሰሜን የሚገኘውን የኢትዮጵያን የታሪክ ክፍል በመሰነድ የሀገሪቱን ታሪክ ለማዘጋጀት በሚደረገው ጥረት ጉልህ ሥፍራን የሚይዙት የፅሑፍ መረጃዎች ናቸው። ሰነዶቹ ወይም ማስረጃዎቹ ከድንጋይ ላይ ፅሑፎች እስከ ዘመናዊ የታሪክ ምሁራን የምርምር ሥራዎች ይዘልቃሉ። የተገፉባቸው ዓላማዎችና የተዘጋጁበት ዘመን የመለያየቱን ያህል በጥንቃቄ ሲመረመሩ የህብረተሰብ እድገት ከየት ተነስቶ የት እንደደረሰ የማሳየት አቅማቸው ከፍተኛ ነው። ዘውጎቹ ከሚያተኩሩበት ማዕከላዊ ይዘት ይልቅ ማጀቢያ ሆነው የሚካተቱት ነጥቦች ታሪክን በመሰነድ በኩል ፋይዳቸው ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም። ይሁንና ፅሑፎቹን ጠለቅ ብለው ሳይመረምሩና መነሻቸውን ሳይረዱ በደፈናው፡-

'የደብተራ ታሪኮች ናቸው'፣ 'የነፍጠኛ ታሪኮች ናቸው'፣ 'የአማራ - ትግራይ ታሪክ በመሆናቸው ይዘታቸው እኛን አይወክልም'፣ 'በፅሑፎቹ ውስጥ ብሔረሰብን የማንቋሸሽ ዝንባሌዎች ታይተዋል' የሚሉና ሌሎች ስሞታዎች፣ አቤቱታዎች እና ክሶች ይሰማሉ፡፡ በዚህም በመንተራስ የኢትዮጵያን ታሪክን የመጥላት እና መሠል ዝንባሌዎች ተንሠራፍተው ይስተዋላሉ። ዋናው ቁምነገር የቅሬታዎቹን መነሻ በቅጡ መረዳትና ችግሩን ማከም ነው።

በዘውግ ታሪክ ፀሐፊዎች የሚሰነዘሩት ሀሳቦች ግን ድርና ማጋቸው እያወቁ ታሪክን ለማጣመም እኩይ ተልዕኮ ከማዘል ስለሚመነጩ (ባለማወቅ የሚሳሳቱትንና አውቆ



t.me/OLDBOOKSPDF

እጥፋዎችን) ማንነታቸውን መለየት ያስፈልጋል። በመሆኑም የሚቀርቡት ቅሬታዎች ውህ የሚቋጥሩ ናቸው ወይስ ካለመረዳት የሚመነጩ፣ ለሚለው የህሊና ሙግት መልስ ለመስጠት 'ነገርን ከሥሩ' ጠልቆ በመበርበር መረዳት ከጅምላ ፍረጃ ይታደጋል። በሌላ በኩል በየእለት ኢመደበኛ ግንኙነቶችንም ሆነ በጠረጴዛ ዙሪያ ለምናደርጋቸው ውይይቶች በቂ ግንዛቤን መያዝ ይጠቅማል። የሚነሱ ሙግቶችን ታሳቢ በማድረግ፤ በታሪክ ዐተያይ ዙሪያ የሚከሰቱ ብዥታዎችን ለማጥራት፣ ታሪካችንን በደንብ እንድንረዳ ድጋፍ ለማድረግ፤ መልካም ተግባቦት ለመፍጠር፤ በአጠቃላይ ከድርሳኖቻችን አዘገጃጀት በመነሳት የተሻለ ምስል ለመያዝ እንዲያስችል ታስቦ በሚከተለው መንገድ ቀርቧል።

## 1. የገድል ጸሐፊዎች (Hagiographers)

ገድል፦ የሚለው የግዕዝ ቃል ወደ አማርኛ ሲመለስ ተጋድሎ ትግል ፅናት የሚሉ ትርጓሜዎችን ይይዛል። የገድል ታሪክ ፀሐፊዎች የግዕዝ ቋንቋ ክህሎትን በሚገባ የተላበሱ ሆነው ራሳቸውን ሙሉ በሙሉ ለሀይማኖት ተግባር የለዩ ናቸው። እልፋና ምሚጋቸው እምነትን ማፅናት፣ ለሀይማኖት ራስን አሳልፎ መስጠት፣ በገድሉ የተማረኩለትን ባለታሪክ የሀይማኖት አባት፣ ባህታዊ፣ ምዕመን፣ ንጉሥ፣ ካህን የሀይማኖት ተጋድሎዎች ከውልደት እስከ ሞት መመዝገብን የህይወት ዘመን ኑሮ አድርገው በመያዛቸው ይታወቃሉ። ወደኋላ በመዳዝ ተጋድሎውን ያደረገው 'ቅዱስ' በምን አይነት ቤተሰብ እና ማህበረሰብ ሥር እንዳደገ፤ አብዛኛውን ጊዜ ከደጋግ ወላጆች ስለመገኘቱ፣ በጊዜው የነበሩ የንግድ፣ የግብርና፣ የአስተዳደር ሁኔታና በየወቅቱ 'በዚህ ዘመን እንዲህ ሆነ' ከሚል ማጀቢያ ጋር በማያያዝ መዝግበው የሚያቆዩ ብእረ መልካሞች ናቸው። በፈቃዳቸው ለእምነታቸው ፅናት ራሳቸውን የለዩ በመሆናቸው የተነሳ ለሚፅፉት ፅሑፍ ምንም አይነት ክፍያ አይጠይቁም።

ስለባለ ገድሉ በሚፅፉበት ጊዜ እግረ መንገዳቸውን የመሪውን የአስተዳደር ዘይቤ፣ የማህበረሰቡን ወግ እምነት የአመራረት ስልት፣ የእፅዋት እንስሳት አለዋፍ እና የንግድ እንቅስቃሴ፣ የአመጋገብና ቤተ መንግሥታዊ ሥርአት፣ ባህል የሚመዘግቡ በመሆኑ ታሪክን በመፃፍ ሂደት ኃያል ከንድ በመሆን ይጠቅማሉ። በዘመናቸው የታዘቡትን ከዋኔ መዝግበው በጥንቃቄ ስላስረከቡ የላቀ ምስጋናና ክበሬታ ሊቸራቸው ይገባል። ስለ እምነታቸውና በወቅቱ አጠገባቸው የነበረውን እውነት በመፃፋቸው ማንን ጎዱ? በማን ላይ ተፅዕኖ አሳደሩ? አሉታዊ ጎናቸው ምንድነው? ጥያቄዎችን ብናጎርፍ በመላው ዓለም የክርስትና እምነት ዙሪያ ከተለመዱ አፃፃፎች የተለዩ አይደሉም። የሚፅፉት የብሔረሰብ ታሪክ ሳይሆን የእምነት ተጋድሎን ብቻ ነው። ለምሳሌ፦



t.me/OLDBOOKSPDF

"ገድለ ላሊበላ" (13ኛው ክፍለ ዘመን) - የኩሻዊ አገው መንግሥት መሪ፣ "ገድለ አቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ (13ኛው ክፍለ ዘመን) - ዝቋላ 'ሶርያዊ መነኩሴ'፣ እና አቡነ ተክለሀይማኖት (13ኛው ክፍለ ዘመን) በዋነኛነት ከሚታወቁት ገድሎች መሀከል ይገኙበታል።

ሁኔታውን ግልፅ ለማድረግ የገድል ፀሐፍቱ የትግራይ የአማራ የኦሮሞን ወይም ሌላውን ኢትዮጵያዊ ማህበረሰብ ወይም የህዝብ ታሪክ ወክለው፣ አንዱን ከሌላው ለይተው በማግዘፍ የማበላለጥ ዝንባሌ የላቸውም። ገድሎች መነሻቸውም ሆነ መድረሻቸው እምነትና ሀይማኖት ዙሪያ አጠንጥኖ ሲጀምሩ ስለ ባለ ገድሉ ሲፅፉ 'ልመናዋ ወይም ልመናው በኛ ላይ ይደርና ቅድስት እናታችን አሊያም ፃድቁ አባታችን ያደረገችው /ያደረገው ተአምር ይህ ነው' በሚል መከፈቻ ተነስተው ሲያጠናቅቁ 'በረከታቸው፣ ምልጃቸው እና ልመናቸው በእኛ ላይ ይደር' በማለት ያጠናቅቃሉ።

ይሁንና በቅርቡ ብቅ ያሉ የዘውግ ፖለቲከኞች አንዳንዶቹ ቢያንስ ግማሽ የሚሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ በሚከተለው፡ የኦርቶዶክስ ሀይማኖት ላይ ባላቸው ጥላቻ (የጥንታዊው የሮማ ግዛት ሲፈራርስ ህዝቡን አንድ አድርጋ የያዘቺው የሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን እንደመሆኗ በተመሣሣይ በኢትዮጵያ ውስጥ የህዝቡን አንድነት ከሚጠብቁ ተቋማት አንዷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ናትና አንድነትን ለማላላት ቤተ ክርስቲያኒቱን ዒላማ ያደርጋሉ። በኢትዮጵያ ታሪክም ውስጥ ከእምነት ጋር የተያያዙ ማስረጃዎችን ማጥፋት ጥበብን፣ ታሪክን እና አንድነትን መሸርሸር እንደሆነ በመገንዘብ በዚህ ዙሪያ አበክረው ይሰራሉ።)

በ2018 እና 2019 ቢያንስ ለ500 ዘመናት ያልታየ መስጊድንና ቤተ ክርስቲያንን ማቃጠል፣ ማፈራረስ እና መዝረፍ ዓላማው በየትኛውም መንገድ ተጠቅሞ ኢትዮጵያን ማዳከም መሆኑን አለመጠርጠር ከየዋህነት ያለፈ ጥፋት ነው። እነዚህ ወገኖች መነሻቸው ክፍፍልን መፍጠር ስለሆነ የእስልምና ሀይማኖት ተቋማትም ቀጣይ ዒላማዎቻቸው ናቸው። ምክንያቱም ከሰሜን ታዋቂው አልነጃሺ መስጊድ በደቡብ ጫፍ እስከ ዶሎ አዶ፣ መልካ ሱፍቱ እና ሞያሌ፣ በምዕራብ ከጋምቤላ እስከ ሐረር ጥግ ድረስ መስጊዶች እና የሚመለከባቸው እስልምና የኢትዮጵያን ህዝብ አንድነት በማስተሳሰር ረገድ ልክ እንደ ክርስትና አቻዎቻቸው የጎላ ሚና አላቸውና።

ዘውጌዎቹ ከገድል መፃሕፍት ገፅ መሀከል የተገኘ አስመስለው ዘመን የወለዳቸውን ጥበቦች (ቴክኖሎጂዎች) በመጠቀም የእምነት ድርሳናትን ሳይቀር በቅጥፈት ለከፋት



t.me/OLDBOOKSPDF

በማዋል እና የጥላቻ ፅሑፎችን ለማዘጋጀት ወገን ከወገን ለማጋደል ሲጠቀሙበት ማየት ያልተለመደ አይደለም። በደመ ነፍስ የሚነዳው ጀሌያቸው እውነታውን የሚገልጥለት በማጣት ሳቢያ አመክንዮአዊ ባለመሆኑ ከሚያየው እውነታ ይልቅ የመንጋው መሪ (ጣዖቱ) የሚነግረውን 'ከፈጣሪ ቃል በላይ' ሳያቅማማ አምኖ ይቀበላል።

እውነታው ሲገለጥ ወደ እምነት ሥፍራዎች ሄደን ከአያቶቻችን ጀምሮ ብንጠይቅ የትኛው ብሔረሰብ ወይም ወገን ተወቅሶ፤ የትኛውስ ብሔረሰብ ተለይቶ ተሞግሦ ያውቃል? የትኛው የእምነት አስተምህሮስ ከሀይማኖቱ ዶግማና ቀኖና አፈንግጦ በሌላው ላይ ያነጣጥራል? ከመፃሕፍት መደርደሪያ ሙሉ ድርሳናት ምን ለማግኘት ገፆችን በርብሮ መስመሮች ላይ በጧፍ ብርሀን ተፈልጎ የተደረሰበት 'ተገፈ የሚሉት ጥላቻ' ከጀርባው ያዘለው ደባ መነሻው ምንድነው? የሚሉ ጥያቄዎችን ብናነሳ ዓላማቸው በዚህ ምክንያት ጥላቻን ለመፍጠር ነው።

በኢትዮጵያ የከርስትና ምንጭ አክሱም ይሁን እንጂ ዛሬ አራቱንም የኢትዮጵያ ማዕዘናት ጨምሮ እስከ ማዕከል ከርስትናን እናገኛለን። (ለመሆኑ እንድ መስመር በበርካታ ገፆች መሀከል 'ተባሉ ከሚባሉ አቃቂሮች ጋር' በገፆች መሀከል ተሰንቅረው 'ተገኝተው ቢሆን' ዛሬ ማን ይጠየቅ? ማን ላልተፈለጉ ቃላት ፍርድ ቤት ይቆም? የማጭቶቻችን አብዛኞቹ ምንጮች አቅጣጫ የለሽ እና ትርጉም አልባ መሆናቸውን እያረጋገጡ መሄዱ መልካም ነው።) በደምሳሳው ከዘውጌዎች አመለካከት የምንረዳው ቁምነገር ፀያፍ ናቸው የሚሏቸው ፅሑፎች 'ተከስተው ነበር' ብለን ብንወስድ ዛሬ ላይ ፈልፍለው የሚያወጧቸው፡- ለተራበው ወገናቸው ዳቦ ሆነው ረሀቡን ሊያስታግሡ ነውን? ለታረዘው ልብስ፣ ለጠማው ውሀ፣ ላጣው ትርፍ ስለሚያስገኙ ነውን? ከምንም በላይ ግለሰቦቹ መሠል ድርጊቶች በዓለማችን ያስከተሉትን ቀውስ አይገነዘቡምን? በጥቅሉ እኩይ ሴራቸውን አጋልጦ ባለመረዳት የሚከተላቸውን ወገኖች ማዳን የየወቅቱ ጀንገበጋቢ ጥሪ ነው።

በዚህ መንደርደሪያ ተሸጋግረን ታሪክን ከመፃፍ አኳያ ከገድል ፀሐፊዎች ድርሳናት የምናገኛቸው ጠቀሜታዎች ምንድናቸው? ብለን 'ቦምቦሊኖ ሲቀርብልን ቀዳዳው ላይ ከማፍጠጥ' የሸር ፖለቲካ ተላቅቀን ታሪክን እንደ ታሪክ ብቻ ለመመልከት ብንታደሮ ለትውልዱ የሚበጁ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይገኙባቸዋል።



t.me/OLDBOOKSPDF

የዓላማ ፅናት፡- (የገድሎቹ ባለታሪኮች ላመኑበት ግብ እስከ ህይወት መስዋዕትነት ለመክፈል መጅገናቸው፤ ለህይወታቸው ሳይሳሱ ነገሥታት ፍትህን ያሰፍኑ ዘንድ ፊትለፊት መገሠፃቸው የተጋድሏቸው ታሪክ አካል እንደነበር፤ እየላሸቀ ያለውን የስነምግባር ደረጃ ከፍ ለማድረግ፤ ከራስ አልፎ ለሌሎች መሠጠትን (እምነት የግል ቢሆንም ከራስ አልፎ ስለወገን፣ ስለሀገር፣ ስለሰላም፣ ህዝብ ከአደጋ እንዲጠበቅ መጸለይ) በዕሑፎቹ ዘውትር መሀከል የሚገኙ እልማዞች ናቸው። ተመሳሳይ ታሪካዊ ለእምነቱ ተከታዮች ያላቸውን ፋይዳና ከመፅሐፍ ቅዱስ ውጪ ያሉ አዋልድ መፃሕፍት ለአማኞቹ ያላቸውን ጠቀሜታ መረዳት ለሁሉም ወገን ይበጃል።

ለእብነት፡- ገድለ ላሊበላ ሲገፍ ንጉሥ የነበረው ፍትሀዊነት በሚከተለው መልክ ቀርቧል። የላሊበላ አብያተ ክርስቲያናት ዛሬ ለትውልዱ ምን ተጨማሪ ጥንካሬ ሊያስገኙ እንደሚችሉ እንመልከት። 'ቅዱስ ላሊበላ' አብያተ ክርስቲያናቱን ሲያንፅ ለባለመሬቶቹ ተገቢውን ካሳ እየከፈለ፣ ህንፃዎቹ ለታነፁበትን መሬት ከመክፈል በተጨማሪ ባለቤቶቹን እያከበረ መጓዙን ገድሉም ሆነ የተፃፉ ማስረጃዎች ያረጋግጣሉ። በተጓዳኝ ሀገራዊ ጠቀሜታዎቻቸውን እንመልከት።

•ፍልፍል አብያተ ክርስቲያናቱ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የትምህርት የሳይንስ እና የባህል ድርጅት (UNESCO) ቅርስነት መመዝገባቸው (1978) የሚያመጣቸው በረከቶች፡-

•በየዓመቱ በቱሪዝም ዘርፍ የሚያስገኙት በሚሊዮኖች የሚቆጠር ዶላር ገቢ፤

•በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ የሚፈጥረው መነቃቃት፤

•በውጭ ምንዛሪ ረገድ የሚኖረው ፋይዳ፣

•ለአሸከርካሪዎች አስጎብኚዎችና በዘርፉ ለተሰማሩ ባለሙያዎች የሚፈጥረው የስራ እድል፤

•በየብስ እና አየር ትራንስፖርት ዘርፍ የሚፈጥረው የመስፋፋት ፀጋ፤

•ለሀገራችን የገፅታ ቅብ በዓለማቀፍ ደረጃ የሚኖረው ከበር

እና መሠል ጠቀሜታዎችን በማስተማር ለተማሪዎችም ሆነ ለህዝቡ እእምሯዊ እድገት፣ ስነልቡናዊ ጥንካሬ፣ የእውቀት አድማስ ለማስፋት እንዲሁም ሀገራችን



t.me/OLDBOOKSPDF

የበለጠ ለማወቅ የሚኖራቸውን ጠቀሜታ መገመት አያስቸግርም። እነዚህን በረከቶች ገፍቶ እና አጣጥሎ ጥላቻን ከሚዘራ፣ መከፋፈልን ከሚያስተምር በላይ ምን የሀገር ጠላት አለ? ምዕራባውያኑ በዘውጊዎች 'የደብተራ ታሪክ' የተባሉ ዕንቁ ሥጦታ ባለፈ የሰለጠነው ዓለም ደብተራዎች ያቆይዋቸውን መዛግብት፣ ንዋየ ቅድሳት፣ ቅርሶች ለመዝረፍ ሚሊዮኖች ረብጣዎች ማፍሰሳቸውን ማየት ለምን ተሳነን? 'እንቁዎቻችሁን በአሪዎች ፊት አትጣሉ' መልዕክቱ ይህን ለመሰሉ የሀገር መጋኛዎች ነው። ታሪካችንን እንወቅ! የሞላውን ትሩፋት ገፍተን የጎደለውን ከሚያሳይ የተዛነፈ አመለካከት እንላቀቅ። የምናየው እልፍ አእላፋት የሀገር ጥበቦች በአብዛኛው ደብተራ የሚሏቸው ሊቃውንት ውጤቶች ናቸው። በታሪካችን ችግር የሆነው ጠቢባን በክብር ደጉሰው ያቆዩት በጠይቦች መበላቱ ነው።

## 2. ጸሐፍተ ትእዛዛት (Chroniclers)

እንደ ፕሮፌሰር ሥርግው ኀብለሥላሴ "Ancient and Medieval History of Ethiopia to 1270" የተሰኘው የበሰለ እና የተተነተነ ጥናታዊ ጽሑፍ እንደሚነግረን፣ ጸሐፍተ ትእዛዛት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በሚገባ መታወቅ የጀመሩት ከዐፄ ዐምደፅዮን (1314 - 44) ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ነው። ጸሐፍተ ትእዛዛት ከትበው ያቆዩልን ለታሪክ ግብአት የሚያገለግሉ መዛግብት መዋዕለ ዜናዎች (Chronicles) በመባል ይታወቃሉ። በነጠላ እያንዳንዱ ጸሐፊ የተሰጠው የማዕረግ ደረጃ 'ጸሐፌ ትእዛዝ' / Chronicler ነበር። የፅሑፍ ዘውጎቹ ከገድል ፀሐፊዎች የሚጋሩት የጋራ ባሕርይ የላቸውም። ምክንያቱም ጸሐፌ ትእዛዝ ከመንግሥት ቀለብ የሚሠፈርለት፣ ድርጎ እና ምንዳ የሚያገኝ (ደመወዝና ጥቅማጥቅም የሚታሰብለት) ነው። ጸሐፍተ ትእዛዛት የሚመረጡት በቁም ዕሀፊት ብዕር አጣጣል (Calligraphic) ችሎታቸው፣ በነገር መተቸት ዕውቀታቸው፣ ለንጉሡ ባላቸው ታማኝነትና በዘመኑ በዕውቀታቸው የተመሠከረላቸው ሆነው ሲገኙ ነው።

ጸሐፍተ ትእዛዛት በሚጽፉት ነገር ሁሉ ነፃነታቸው የተገደበ ነው። ሀሳባቸውን በሚፈልጉት መንገድ እንዳያስተላልፉ የሚከለክሏቸው አሣሪ ምክንያቶች የበዙ ናቸው። ዋና ዋናዎቹ፦ ሁሉንም የሚጠረንፍ አለቃ 'አዛዥ' በሚባል ማዕረግ የሚመደብባቸው ይሆንና አዛገፉ ከሚሠጣቸው ትእዛዝ ውጪ አንዳችም የተዛነፈ መልእክት በማስታወሻቸው ላይ ማስፈር አይችሉም። በተጓዳኝ የፃፉት መልእክት ንጉሡ ጋ ቀርቦ ተቀባይነት ካላገኘ ውድቅ ይሆናል። የሚያስከትለው ቅጣት የፀሐፌ ትእዛዝነት ማእረጉንና እንጀራ ገመዱን እስከመበጠስ ይከፋል። በመሆኑም ያላቸው



t.me/OLDBOOKSPDF

ብቸኛ አማራጭ ንጉሡን ማግዘፍ እና ማወደስ ነው። ነቀፌታ ብሎ ነገር አይታሰብም። በአጭር አገላለፅ ፀሐፊ ትእዛዝ 'የንጉሡ አፍና ጆሮ ነው' ቢባል ገላጭ ነው። የሥራ መደቡም የንጉሡን የእያንዳንዱን እውድ እንቅስቃሴና የቤተ መንግሥቱን አሞቃል በጥንቃቄ መመዝገብን ታሳቢ ያደረገ ነው።

ንጉሡ የሚወልባቸውን የጦርነት ጀብዶች፣ የዙፋኑን አደረጃጀት፣ ያደረጋቸውን ሥጦታዎች፣ የበየናቸውን የፍትህ ውሳኔዎች፣ የተቀበላቸውን እጅ መንሻዎች፣ ያወጣቸውን አዋጆች ደንቦች እና መመሪያዎች በተጓዳኝም የንጉሡን ባህርያት ማፍ በሥራ መዘርዝሩ ውስጥ የተካተቱ ናቸው። ይኸውም መሪው የተንም ያህል ፈሪ ቢሆን የጀግንነት ውሀ ልክ፣ ምንም አይነት ንፉግ ስግብግብ እና ቆንቋና ቢሆን ሲጋሥ፣ የጭካኔው ደረጃ ፅንፍ የረገጠ ቢሆን የርህራሄ አባት ሆኖ ይሳላል።

በአንፃሩ የንጉሡን ተቀናቃኞች ጨካኝ፣ ሀይማኖት የለሽ፣ አረመኔ፣ ሲሸሹ ገደል የማይመልሳቸው እና ግንባራቸውን ሰማይ እስከሚገጨው የሚፈረጥጡ በማድረግ አለቅጥ አሳንሰው ያቀርቧቸዋል። ዕሑፎቻቸው የበዛ ግነት የገዘፈባቸው መሆኑ በተገኙት መዛግብት ላይ ተንፀባርቆ ተስተውሏል። የንጉሡን ሠራዊት ብዛት ሲገልፁ እንደ ባህር አሸዋ የበዛ፣ የፈረሶቹ ኮቴ ድምፅ እንደ ወቅያኖስ ሞገድ የሚያስደነግጥ፣ የሚያነሱት አዋራ የብዙ አውሎ ነፋሶችን ያህል እየተጥመለመለ የሚጎን፣ የነጋሪት ጉሰማ እንደሰማ ሀገር ተነቅሎ ተከትሎት ጎበዝ የተባለ ያልቀረበት አይነት ኩሸት አይነተኛ መገለጫቸው ነው። ይህ አይነቱ አፃፃፍ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ጭምር የተለመደ ለመሆኑ አፈወርቅ ገብረኢየሱስ በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያው በሆነው "ጦቢያ" በተሰኘው ልቦለድ መፅሐፋቸው ገፅ 40 ያሰፈሩት የሚከተለው መልከ ነበረው:- "ሠራዊቱ ... በምጽአት ጊዜ በቀርነ መለከት ተጠራርቶ የመጣ ይመስላል። ብዛቱ በሰው ኃይል እንኳን በጦር ተወግቶ የሚቸነፍ መሆኑ ይቅርና በክርስቶስም መዓት ሙቶ የሚያልቅ፣ ቢሞትም ምድሩ ለመቃብር የሚበቃው አይመስልም ነበር።"

እያይዘን የምንመለከተው ኢማም አህመድ ኢብን ኢብራሂም አልጋዚ በተለምዶ በኢትዮጵያ የልምድ ፀሐፊዎች አገላለፅ (ግራኝ አህመድ) ሠራዊት ዘወትር እድናቆት የሚያገኙደጉዱለትን ንጉሥ ልብነድንግልን ሽምብራ ኩሬ ጦርነት ላይ (1529) ድል ነሣ። ለፀሐፊ ትእዛዛቱ የአፄውን መሸነፍ መቀበል የሞት ያህል ስለነበር አህመድ ኢብራሂምን የተለየ ፍጡር አድርገው መሣላቸውን ተከለፃድቅ መኩሪያ "ከአፄ ልብነድንግል እስከ አፄ ቴዎድሮስ" በሚል ርዕስ ባዘጋጁት የታሪክ ጦማር ተሰንዶ ይታያል።

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደ ፀሐፊ ትእዛዛቱ ከሆነ ግራኝ አህመድ በነገሥታቱ ኃጢአት በፈጣሪ ቁጣ የተከሰተ አንዳች የርግማን ውጤት ነው። አርባ ከንድ ያህል ርዝመት ያለው ግዙፍ ፍጥረት፣ ኮረብታ የሚያህል ድንጋይ አንስቶ የሚወረውርና ቤተክርስቲያን የሚጨፈልቅ ልዩ ፍጡር ተደርጎ ተተርኳል። ለምሳሌ:- ደብረሊባኖስ ቀዘባ ማርያም ቤተክርስቲያን ትይዩ ከተራራው ላይ ያለው ግዙፍ ቋጥኝ ግራኝ ቤተክርስቲያኗን ሊያፈርስ የወረወረውና 'በፈጣሪ ምህረት ድንጋዩ የመከነ' እንደሆነ ይነገራል። ('በእምነት ሁሉም ነገር የሚቻል' እንደሆነ ቢታመንም የአህመድ ኢብራሂም ጉዳይ እ.ኤ. ሐብነድንግል የተሸነፉት በአቅም ማነስ ሳይሆን በኃጢአታቸው ብዛት ፈጣሪ ተቆጥቶ 'በፈጣሪ መአት ነው' የሚለው አይነት አገላለፅ የግነት ደረጃ ማሳያ ነው።)

የታሪክ ፀሐፊዎች በወቅቱ ጦርነቱን በተገቢው መንገድ ለመሠነድ በሚያደርጉት ጥረት የዘመኑን የአፃፃፍ ስልት መገንዘብ፣ ጦርነቱ የት እንደተካሄደ የሽምብራ ኩሬን መገኛ አካባቢ፣ ጂኦግራፊያዊ አቅጣጫው፣ ለምን ያህል ዓመታት ግጭቱ እንደቀጠለ፣ አውደ ውጊያዎች በየትኞቹ ሥፍራዎች እንደተካሄዱ፣ የተጠቀሙባቸውን የዘመን 'ቴክኖሎጂ' ውጤት የሆኑ መሣሪያዎች አይነት፣ የውጊያ ስልት ለመቃኘት ያስችላል። የሽምብራ ኩሬውን ጦርነት አስመልክቶ በወቅቱ የታዘበውን በስፍራው የነበረው የመናዊ የዘመኑ ታሪክ መዝጋቢ (ፀሐፊ ትእዛዝ) ሺሀብ አዲን ከፃፈው ሚዛናዊ ጦማር በመነሣት በፀሐፊው ያልተሸፈነውን የታሪክ ክፍል ለመሙላት ሊጠቀሙበት ይችላሉ። የፅሑፉ ርእስ "ፉቱህ አል ሀበሽ" ሲሆን ከአረብኛ ወደ አማርኛ እና እንግሊዝኛ ተተርጉሟል።

ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ በዘመነ ደርግ (1974 - 1991) እና በዘመነ ወያኔ (1991 - 2018) ዛሬም ቢሆን በ20ኛውና በ21ኛው ክፍለዘመን ጋዜጦች፣ሬዲዮ ጣቢያዎች፣ ቴሌቪዥኖች፣ መንግሥታዊ የመገናኛ አውታሮች በሙሉ የቃላት አመራረጣቸው ከመቀየሩ በስተቀር የሥርአቱን መሪዎች ይነቅፉሉን ብለን ብንጠይቅ መልሱ ተመሳሳይ ሆኖ እናገኘለን። አረመኔ የሆኑ መሪዎችን 'ቆራጡ'፣ 'ጀግናው'፣ 'አብዮታዊው'፣ "ባለራዕዩ፣' 'የህዝብ ልጅ'፣ 'ከፈጣሪ የተሰጠ ፀጋ' ወዘተርፈ ማለታቸው፤ የመሪዎችን ተቃዋሚዎች:- 'የፍየል ወጠጤ'፣'የእድህሮት ሀይላት'፣ 'የአብዮቱ ጠላቶች'፣ 'ጠባቦች፣ ትምክህተኞች፣ ተላላኪዎች፣ የጎዳና ላይ ነውጠኞች፣ አደገኛ ቦዘኔዎች፣ ዋልጌዎች...' በማለት አይገልፁምን?

ዘውጌዎቹስ ሀገር የሚያተራምሱ፣ ህዝብ የሚከፋፍሉ፣ ታሪክን የሚያቆሽሹ፣ ሚያገዳድሉ የየመንጋዎቻቸውን መሪዎች 'የነፃነት ታጋይ'፣ 'የሰውነት ውሀ ልክ'፣



t.me/OLDBOOKSPDF

'ልእለ ሰብእ' አስመስለው አያቀርቡምን? ታዲያ በየትኛው ሞራል ዛሬም መንግሥትን ወይም የነሳዎችን መሪ እንከን አልባ አድርገው በማወደስ የተጣመዱ የመንግሥት ተከፋዮች ወይም 'አክቲቪስቶች' እና የግንኙነት አውታሮች ይዘን ድሮ የነበሩ ፀሐፍተ ትእዛዛትን እንወቅሳለን?

በታሪክ አጻጻፍ ትልቁ ቁምነገር ከማግዘፍና ከማሳነስ ፀድቶ ሚዛናዊ በሆነና ከሁሉቱም ፅንፎች ባልወገነ አኳኋን ታሪክን መዘግቦ ለትውልዶች ጥቅም ማሥናዳት ነው። ከዚህ በከፋ ደረጃ በምዕራቡ ዓለም በሠለጠነ ህዝብ መሀከል ቁጭ ብለው እየተሞላቀቁ፣ ልጆቻቸውን በውጭ ሀገር አቅብጠው እያስተማሩ በተቃራኒው ለዘመናት አብረው በፍቅር የኖሩ የሀገር ፀጋዎችን ሲያጋድሉ፤ እነርሱ በውጭ ሀገር ግለሰባዊና በቅይታ የሚያገኙትን የዜግነት መብት እያጣጣሙ 'በትርፍ ሀገራቸው' ዜጎችን በግዛ ምድራቸው፣ ከአያት ቅድመ አያት ጀምሮ በኖሩበትና እትብታቸው ከተቀበረበት ውጭ ሌላ ቀዬ የማያውቁትን፤ ቢሰደዱ የሚሄዱበት ቦታ አዲስ ሆኖባቸው በባይተዋርነት የሚሰቃዩ ወገኖችን 'ሠፋሪ'፣ 'መጤ' የሚሉ ግለሰቦችና ቡድኖች እነዚያን ታላላቆች ለመውቀስ ምን የሞራል ልዕልና ይኖራቸዋል? ከቶውንስ ከተመሣሣይ የጥላቻ አበጋዞች በላይ የሀገር ፀር ከወደየት ይገኛል? ድርጊታቸው በንፁህ ህሊና ሲታሰብ በጣም ያሳፍራል።

ከዚህ አንፃር ታሪክን በሚገባ መረዳትና ፀረ ታሪክና ፀረ አንድነቶችን በጋራ በማውገዝ ሆድ ለሆድ ተገናኝቶና ተግባብቶ የተረጋጉ ሀገሮች የሚያጣጥሙትን የሰላምና አብሮነት ፀጋ ማጣጣም ወርቃማው የኑሮ ዘዴ ነው። ጥበብን ከ'ፈረንጅ' በአግባቡ ኮርጀን መጠቀም ያልቻልን፤ ከፈረንጅ አልባሳትን፣ መጫሚያዎቻችንን፣ የመመገቢያ ቁሳቁሶችን ሳይቀር የምንወስድ፣ ነጭ ባመረተው መሣሪያ ዳቦ የምንጋግር፣ የሸቀጥ ማራገፊያ የሆንን እኛ የድሮዎችን ለመተቸት ድፍረት ማግኘታችን ይገርመናል።

ከፀሐፍተ ትእዛዛት መረጃዎችእና በስፋት በሚታወቁ ማስረጃዎች እንደተረጋገጠው ኢማም አህመድ ኢብራሂም ከ1527 - 1543 በኢትዮጵያ ፖለቲካ የበላይነቱን የተቆጣጠረ ከመሆኑም በላይ መሀከለኛውን የኢትዮጵያ ክፍል፣ በሰሜን እስከ አክሱም፣ ወደ ደቡብ እስከ ወላይታ አካባቢ (ወላይታዎች ጠንካራ መከላከል አድርገዋል) በመንቀሳቀስ እንዲሁም ምስራቃዊውን አካባቢ ሙሉ በሙሉ በመቆጣጠር ተፅዕኖ ፈጣሪ መሪ እንደነበር አሻሚ አይደለም። ሆኖም በኢትዮጵያ መሪዎች ዝርዝር ውስጥ አልተቀመጠም። ኢማም አህመድን እልፎ ከቦታ ወደ ቦታ በመሸሽ ላይ የነበሩትን አፄ ልብነድንግልን የወቅቱ መሪ አድርጎ ማቅረብ ስህተት ይመስለናል። ቀደም ብለን እንደገለፅነው ከዘመኑ ፀሐፍተ ትእዛዛት ስለኢማም አህመድ ከተገኙ መረጃዎች



t.me/OLDBOOKSPDF

የየመኑ ሺሀብ አዲን፦ "ፉቱህ አል ሀበሽ" / "The Conquest of Habesha" ተስተካካይ የማይገኝለት ዕፁብ ድንቅ መፅሐፍ ነው። በሐፊው የሽምብራ ኩሬ (1529) ጦርነትን በዐይኑ በብረቱ ተመልክቷል። ከሞላ ጎደል ከመድልም ነገ በሆነ አግባብ የጦርነቱን ሂደት መዝግቦታል። የሺሀብ አዲን ፅሑፍ ለማስተማሪያ በእጅጉ የሚጠቅም ታሪካዊ መረጃ ነው፡፡

ይሁንና ወገንን ከወገኑ ለማቃቃር እንቅልፍ ያጡ ዘውጊዎች 'እንዴት "የግራኝ አሕመድ ወረራ" ብለው እነ ተከለጻድቅ መኩሪያ ፃፉ?' በሚል ቁጣት የሚመስል፣ ከበስተጀርባው በተንኮል የታጀበ አገላለፅ ሲጋጋጡ ስንመለከት ተገቢ ምላሽ ሰጥተን ማለፍ ፈለግን። ለመሆኑ ዘመናዊ ትምህርትና አስተሳሰብ ባልሰፋበት በዚያ የሩቅ ዘመን ከምስራቅ ወደ ሰሜን የተንቀሳቀሰውን ግራኝን 'ወራሪ' ተባለ የሚሉ ጎሠኞች በየትኛው የአስተሳሰብ ደረጃ ተመዝነው ነው ከመሀል ሀገር የቀድሞ ይዞታዎችን መልሶ አንድ ለማድረግ የተንቀሳቀሱ ከፍሎችን 'ወራሪ' ለማለት ድፍረት ያገኙት? (በምዕራፍ አራት በስፋት እንዳስሰዋለን)

በተያያዘ ሁኔታ የኢማም አህመድ ኢብራሂምን ምጣኔ ሀብታዊ ጦርነት ለእኩይ ዓላማ በመጠምዘዝ የሀይማኖት ግጭት አድርጎ በሁለት ጎራ እምነቶችን ለማቃቃር የሚደረገው ጥረት (በምዕራፍ ሦስት) ምላሽ ይሰጠዋል። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የሀይማኖት ጦርነት ተካሂዶ እንደማያውቅ በሚገባ የተረጋገጠ ነው። ይሁንና ዮዲት በ10ኛው ክፍለ ዘመን ለበቀል በመነሳሳት አብያተ ክርስቲያናትንና ንዋየ ቅዱሳትን መንዳቷ፣ በተመሳሳይ ኢማም አህመድ ኢብራሂም ከትሞ የነበረበት ወሎ ላይ አስገድዶ ህዝቡን ወደ እስልምና እምነት ማስገባቱ፣ ሌሎች ክርስቲያኖችን ከፍተኛ ግብር አየከፈሉ በእምነታቸው እንዲቀጥሉ ማድረጉ እና አፄ ዮሐንስ አራተኛ የወሎ ሙስሊሞችን አስገድደው ወደ ክርስትና እምነት መለወጣቸው ሊሸሽግ አይችልም። በ6,000 ዓመት ታሪክ ውስጥ በሦስት ወቅቶች የተፈጠሩ ክስተቶችን በማራገብ ለጥላቻ ማዋል ታሪካዊ ነውር ነውና ሊወገዝ ይገባል።

እንደ ሺሀብ አዲን ገለፃ ከሆነ የአፄ ልብነድንግል እና የኢማም አህመድ ሠራዊት በሁለት ጎራ ተከፍለው ከቀኑ 10:00 ሰአት ሲሆን ጦርነቱን ጀመሩ። እንደተለመደው የንጉሡ ሠራዊት አይሎ የኢማሙን ሠራዊት ማሳደድ ጀመረ። ይሁንና የክርስቲያን ሠራዊት በምሽት የመዋጋት ልምድ ስላልነበረው 12:00 ሰአት አካባቢ ጦርነቱ ተቋ አለ። በማግሥቱ ማልዶ 12:00 ሰአት ሲሆን ጦርነቱ ተፋፍሞ ተቀጣጠለ። ፈረሶች ያስካኩ። ሳንጃ ከሳንጃ ይሞሻለቃል። በርካታ ሰው ወደቀ። ደም እንደ ጎርፍ ፈሰሰ፡



t.me/OLDBOOKSPDF

የሚችች ቁጥር በየሰአቱ እየናረ ሄደ። እኩለ ቀን ሲሆን የኢማሙ ሠራዊት ማፈግፈግ ጀመረ። የሚደንቀው እስከዚህ ሰአት ድረስ ግራኝ አህመድ ጠንካራ ፈረሰኛ ሠራዊቱን ደብቆ ውጊያው ላይ በቀጥታ አልተሳተፈም ነበር። ሠራዊቱ መናድ ሲጀምር ትኩስ ጉልበት ያለውን ጦር ይዞ መሀከል ለመሀከል አጊጦን ገጠመ። ንጉሡ የነበራቸው ብቸኛ አማራጭ ሽሽት ነበር። የሠራዊቱ ሽሽት አቅጣጫ የለሽና የተዘበራረቀ ነበር ሲል ይገልፃል። የእንግሊዝኛው ትርጉም የንጉሡን ሠራዊት ሁኔታ ሲያትት (... in a complete disarray) ይለዋል።

የሽምብራ ኩሬው ጦርነት ሲጠናቀቅ የኢማሙ ሠራዊት ከፍተኛ ምርኮ አግኝቶ ስለነበር የጦሩ አዛዦች 'ወዚሮች' ጦርነቱን መቀጠል አልፈለጉም። ኢማሙ ያለፍላጎታቸው መጫን አልፈለገም በመሆኑም ጦርነቱን ለሁለት ዓመታት ገታው። (1529-1531) በማለት ተገልጿል። ዐሐፊው ኢማሙ ድሉን ያገኘበትን ምክንያት ሲያወጋን የበሰለ ትንታኔውን አኑሯል። ከእነዚህም መሀከል:- የጦር ስልት ውጤታማነት፣ ኢማሙ ከአረቢያ ያስመጣቸው ፈረሶች ረጃጅም መሆናቸውና ለውጊያ የተሻለ አቅም ስለፈጠሩለት፣ ኢማሙ ከፐርሺያ ያስመጣቸው ጎራዴዎች ጠንካራና በቀላሉ የማይሰበሩ መሆናቸው የተሻለ የመዋጋት ጥንካሬን ማላበሳቸው፣ የአፄ ልብነድንግል (1508 - 1540) ሠራዊት እርካብ የእውራ ጣት መሆኑና እየቆዩ ሲሄዱ ጣትን የሚከረከርና የሚሠረሥር፤ በአንፃሩ የኢማሙ ጦር የእግር እርካብ ስለሚጠቀም እንደልቡ ቆሞ መሠናዘር ያስቻለው ... መሆኑ ተጠቅሰዋል።

የታሪክ ጠቀሜታ ጦርነቱን አፍ በሚያስከፍት መንገድ በስሜት ገልፆ በተውኔቱ ረኩቶ የተመደበውን የንባብ ወይም የትምህርት ሰአት ማጠናቀቅ ሳይሆን፤ የጦርነት ሂደት የሚያስከትለውን ሰብአዊ ኪሣራ ማሣየት፤ የተሻለ መሣሪያና አደረጃጀት ለድል እንደሚያበቃ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ኢኮኖሚያዊ ፍላጎት ካልሆነ 'የሀይማኖት ጦርነት ተካሂዶ እንደማያውቅ'፣ የተወሰዱ የኃይል እርምጃዎች መወገዝ እንዳለባቸው አበክሮ ማስታወቅ ላይ ትኩረት ማድረግ ነው። በትላንት ከፋት ዛሬ ተጠያቂ አይኖርም። በኢማም አህመድ መሪነት ኢትዮጵያዊ የሆኑ የአርጎባ ሐረሪ ሶማሊ እና አፋር ጦረኞች ላደረሱት የአብያተ ክርስቲያናት መቃጠል፣ ለ15 ዓመታት ለደረሰው የሰዎች እልቂት፤ ከቢሾፍቱ እና አዳማ እስከ አክሱም ድረስ ባለው ሠፊ ግዛት ሰፊ ቁጥር ባለው ሰላማዊ ነዋሪ ላይ ላደረሱት በደል፤ ወሎን አስገድደው ሙስሊም በማድረጋቸው ዛሬ ኃላፊነት የሚወስድ ወገን ይኖራልን? መልሱ ተመሳሳይ ጥፋትና ውድመት ላለመፈፀም በየሀይማኖቶች አስተምህሮ እና በሰለጠነ አስተሳሰብ በማውገዝ ውስጥ ይጠናቀቃል።



t.me/OLDBOOKSPDF

## የዘመነ መሣፍንት ጸሐፊዎች (1769 - 1855)

ዘመነ መሣፍንት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የተለያዩ መገለጫዎች አሉት። ሲያሚው
በራሱ አፍ አውጥቶ እንደሚነግረን መሣፍንት እጅግ በጣም የገነኑበትና የነገሥታት
ሥልጣን ከመጠን በላይ ተዳክሞ የታየበት ነው። ንጉሦቹን በአሻንጉሊቶች ደረጃ
ለይስሙላ የሥልጣን መንበር ላይ በማስቀመጥ በወቅቱ ፈርጣማ ክንድ የነበራቸው
ንጉሥ አንጋሾች (ራስ ቢትወደዶች) በፈለጉት መንገድ ይሾሟቸውና ይሽሯቸው
ነበር። ራስ ቢትወደዶቹ ከንጉሦቹ ጀርባ ያሉ ቢመስሉም ሥልጣኑን ጠቅልለው
የያዙበት ወቅት ዘመነ መሣፍንት በመባል ይታወቃል።

ዘመኑ በየሥፍራው የነበሩ የየአካባቢው ገገርዎች ጉልበታቸውን በማጠናከር
ለማዕከላዊ መንግሥቱ ግብር መላክ አሻፈረኝ ያሉበት ወቅት ሆኖ አልፏል። በመገለጫ
ለማሣየት የሸዋው ንጉሥ ሣህለሥላሴ (1813 - 1847) አማካይ ዓመታዊ ገቢያቸው
85,000 ጠገራ ብር (ማሪያ ተሬዛ ታለር/ ዶላር ወይም ማርትሬዛ)፣ የእንደርታው ራስ
ወልደሥላሴ 75,000 ማርትሬዛ የወቅቱ በስፋት ሥራ ላይ የዋለ የመገበያያ ገንዘብ
በነበራቸው ወቅት የጎንደሩ ንጉሠነገሥት የነበረው አማካይ ዓመታዊ ገቢ 300 ጠገራ
ብር ብቻ ነበር። ሸዋ ሙሉ በሙሉ ከማዕከላዊ መንግሥቱ በመነጠል የራሷን
አስተዳደር መሥርታ ነበር። ሂደቱ የኢትዮጵያ ከመሪው ጥንካሬ ጋር ተያይዞ
የመስፋትና የመጥበብ ሂደት መገለጫ ነው።

ይህም ድንቅ አይደለም፤ አንድ ቋንቋ የሚናገሩ ጀርመኖች 300 ግዛቶች
እንደነበሯቸው፣ በ19ኛው ክፍለ ዘመን ሁለተኛ አጋማሽ ማብቂያ አካባቢ ወደ 38
አስተዳደሮች ተቀራርበው፤ በመጨረሻ በአይረሴው ኦቶቮን ቢስማርክ ጥበብ (1871)
አንድ መንግሥት መመሥረታቸውን፤ ኢትዮጵያን በ1896 የወረረቺው ጣሊያን
ከስምንት በተለያዩ የአውሮፓ ሀገራት ተፅዕኖ ሥር ከሚማቅቁ ግዛቶች ተላቅቃ አንድ
የሆነችው ከአስራ አምስት ዓመታት በፊት በካውንት ካሚሎ ቤንሶ ደ ካቮር ነበር።

ዐፄ ምኒልክ በተመሳሳይ ከጣሊያንም ሆነ ከጀርመን ከየትኛውም የዓለም ሀገራት በላይ
አንድ የሆነውን የኢትዮጵያ ህዝብ መልሶ የማቀራረብ ሂደት የጀመሩት በ1970ዎቹ
ነበር። አሜሪካ የነፃነት አዋጅ አውጃ ከብሪታንያ የበላይ አገዛዝ ተላቅቃ 13 ግዛት
የሆነችው በ1770ዎቹ፣ 33 ግዛት የደረሰቺው በኃይል በ1860ዎቹ፣ የማይተዋወቁ
ታሪክ ያላስተሳሰራቸው ህዝቦች ከናፖሊዮን ሉሲያና የተባለቺውን ግዛት፣ አላስካ
ከሩሲያ ገዝታ አንድነቷን ያጠናቀቀቺው በ20ኛው ክፍለዘመን ነው። አፍሪካዊ ሀገሮች



t.me/OLDBOOKSPDF

ፊፅሞ የማይተዋወቁ የተሰባሰቡት አውሮፓውያን በቅኝ ግዛት ገጣጥመው አበጃጅተዋቸው በተለይ ከ1960ዎቹ ጀምሮ መሆኑ ይታወቃል። አብዛኛ የሚያስቆጨው ከዚህ ሁሉ ነፃ ሆነው በአብሮነት በጋብቻ በመስዋዕትነት የደመቁ ኢትዮጵያውያንን ለመከፋፈል የሚተጉ የውጭ ዘጎች ጭምር ከብረው መታየታቸው ነው።

ወደ ተነሣንበት ነጥብ ስንመለስ፣ የነገሥታቱን ሥልጣን መዳከምና የነበራቸውን ክብር መውረድ ተከትሎ ፀሐፊ ትእዛዛት ተፈላጊነታቸው ቀዘቀዘ። የነገሥታቱን ያልነበረ ጅብድና ውሎ መመዝገቡ ሪብ የለሽ ከመሆን አልዘለለም። በምጣኔ ሀብቱ ማሽቆልቆል የተነሣ ቀለብ የሚሠፍርላቸውም አልነበረም። አጠቃላይ ድባቡ የቤተ ክህነት ትምህርት ለተማሩና ታሪክን መዝግቦ ለመፃፍ ፍላጎቱ ለነበራቸው ሁሉ የተሻለ በር ከፈተ። ከዚህ አኳያ ከየትኛውም የታሪክ ወቅት ይልቅ ሚዛናዊ የሆኑ ዕሑፎች በዘመነ መሣፍንት ውስጥ እናገኛለን። የአስተዳደራዊ መዋቅሩን መበላሸት፣ ማህበራዊ ምስቅልቅሉን፣ የጦርነቱን ውሎ እና የተፈጠረውን ውጥንቅጥ ፀሐፊዎቹ ፍፃ ፍንትው አድርገው ዐሳይተውናል።

የንጉሠነገሥት ኢያሱ ዳግማዊን ሞት ተከትሎ ባለቤታቸው እቴጌ ዋቢ የወሎ እሮሞ በሆኑ ወንድሞቻቸው ሉቦ እና ቢሪሌ በመታገዝ እንዲሁም 3,000 የኦሮሞ ጦረኞች የጎንደርን ቤተመንግሥት እንዲቆጣጠሩ በማድረግ ጠንካራ ኀራ ተፈጠረ። በሌላ በኩል የዳግማዊ ኢያሱ እናት እቴጌ ምንትዋብ ቋረኞችን በማደራጀት በጎንደር ቤተ መንግሥት አካባቢ የራሳቸውን ከበብ ፈጠሩ። በሁለቱ ቡድኖች መሀከል የተፈጠረው ፍጥጫ ያሰጋቸው እቴጌ ምንትዋብ ተጨማሪ ጉልበት ለማግኘት ያስችላቸው ዘንድ ከትግራዩ ራስ ሚካኤል ስሑል እርዳታ ጠየቁ። ራስ ሚካኤል ጠንካራ ጦር ይዘው በመከሠት የወሎ እሮሞዎችን ከቤተመንግሥት በማስወጣት ሁኔታውን አረጋጉ።

የወሎ እሮሞዋ እቴጌ ዋቢ ልጅ ንጉሠ ነገሥት ኢዮአስ ሁኔታዎች መረጋጋታቸውን በማየት ራስ ሚካኤል ሥሑልን አመስግኖ ወደ ትግራይ እንዲመለሡ አዘዛቸው። የኃይል ሚዛኑን የገመገሙት የትግራዩ ራስ ሚካኤል የኦሮሞዎቹና የአማራዎቹ መከፋፈል የፈጠረላቸውን ክፍተት በመጠቀም (ከኦሮሞና አማራ ውህደት የተገኘውን) ንጉሠ ነገሥት ኢዮአስን ገድለው በጉልበታቸው 'ራስቢትወደድ' (ንጉሥ አንጋሽ) ማዕረግን በመቀዳጀት በኢትዮጵያ ፖለቲካ አዲስ የመሣፍንት አመራር ምዕራፍ ተከፈተ። ሆኖም የራስ ሚካኤል የበላይነት ብዙም መቆየት አልቻለም። ከወሎ እሮሞ እናና ከወሎ አማራ እንዲሁም ከጎንደር እና ከጎጃም የተውጣጣ ሠራዊት



t.me/OLDBOOKSPDF

1771 ሰበርከሳ ጦርነት ላይ ራስ ቢትወደዱን አሸነፉቸው። ራስ ሚካኤል ሸሽተው ወደ ትግራይ በመመለስ (1771 - 1780) የትግራይ ገዢ ሆነው ቀጠሉ።

የዘመነ መሳፍንት አይነተኛ መገለጫ ከሆኑት ባህርያት ለላኛው ገፅ ከ2/3ኛ በላይ ለሆነው ጊዜ እንደ ዳግ ጠጠር የሚገፋ ንጉሥ ዙፋኑን ላይ አስቀምጠው ለ80 ዓመታት የመሩት የየጁ ኦሮሞዎች መሆናቸው ነው። ይህ ጊዜ በወቅቱ በነበሩ ፀሐፍት የየጁ ሥርወ መንግሥት ተብሎ ተገልጿል። በሥልጣን ላይ የነበሩት ከመጀመሪያው የሥርወ መንግሥቱ መሥራች አሊ ጓንጉል (አሊ ትልቁ) አንስቶ በካሳ ሀይሉ በ1853 አይሻል ላይ እስከ ተሸነፈው አሊ አሉላ (አሊ ትንሹ) ድረስ የወረሼህ በትረ መንግሥት የፀናበት ነበር።

አሊ እንደሚያሳየን የሙስሊም መነሻ ያላቸው መሪዎች የጎንደርን ቤተ መንግሥት ማስተዳደራቸውን ነው። ወረሼህ ለሚለው ስያሜ የተለያዩ መከራከሪያዎች ይቀርባሉ። ልክ ወረ ሂመኖ፣ ወረ ባቡ፣ ወረ ኢሉ እንደሚባለው ሁሉ መሪዎቹ ካላቸው የኦሮሞ እና የሙስሊም መነሻ መንጭቶ ወረ ሼህ (ሼክ) ከሚለው የተገኘ ነው። የመሪዎቹ ቤተሰቦች የወቅቱ መጠሪያ 'መሀመዶች' በሚል ቅጥል ስም የሚታወቅ ነበር። ይህ•አገላለፅ የተሻለ አሳማኝ ይመስላል። ሌሎች ደግሞ ወረሰህ (ኦሮሞ ወረሰህ /ተቆጣጠረህ) ለማለት ተፈልጎ ነው ብለውም ያስቀምጡታል። በተመሣሣይ 'ወረ ሼህ'፦ ሙስሊሞቹ ከአንድ በላይ ሚስት ስለሚያገቡ (የሼህዎች ቤተሰብ) ለማለት ተፈልጎ ነው የሚሉም አልጠፉም። ዋናው ቁም ነገር ዘመነ መሣፍንት የኦሮሞ አስተዳደራዊ የበላይነት በጎንደር ቤተመንግሥት ጎልቶ የታየበት መሆኑ ነው። የዘመነ መሣፍንት ሌሎች መገለጫዎች፦

1. ግብፅ ኢትዮጵያ መከፋፈሏንና መዳከሟን በማስተዋል ተደጋጋሚ ጥፋት የፈፀመችበት እና የኢትዮጵያን ድንበር በመሻገር ከጎንደሩ ካሳ ሀይሉ፣ ከጎጃሙ ንጉሥ ተክለሀይማኖት እና በተለያዩ ሥፍራዎች ኢትዮጵያን የመቆጣጠር ሙከራ ያደረገበት ወቅት ነው። (ይህ ኢትዮጵያ በውስጥ ችግር ስትታመስ ህልውናዋ መደፈሩ በቅርቡ በ1970ዎቹ ሁለተኛ አጋማሽ የተጋረጠብን የሶማሊያ ወረራ እና በ1990ዎቹ ማብቂያ ኤርትራ ኢትዮጵያን መውረሯ ተጠቃሽ ናቸው።)

2. ሽፍቶች ገበሬውን እየዘረፉና ቤተሰቦቹን በመዳፈራቸው አርሶ አደሩ ራሱ 'ከብሩን ለማስጠበቅ' መሸፈት የመረጠበት፣ በገዢፈያውና ሽፍታው መበራከት ምክንያት የረጂም ርቀት ንግድ የተቀዛቀዘበት፣ ምርት ያለ ቅጥ የወረደበት ዘመን ነበር።



t.me/OLDBOOKSPDF

3. የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በተዋህዶ፣ ቅባት እና የፀጋ ልጅ አካባቢያዊ ገፅታ በመያዝ የተከፋፈለቺበት፣ በማያባራ ጦርነት ምክንያት የሰው ህይወት እንደ ቅጠል የሚረግፍበት፣ ምርት ያሽቆለቆለበት እና ጭንቆት በርካታ ትንቢቶችን የወለደበት ጊዜ ነው። በሀይማኖት ረገድ ክርስቶስ "ሦስት ልደት" አለው፡- አንድም በዘላለም ውስጥ ተወልዷል፤ አንድም በመንፈስ ቅዱስ በድንግል ማርያም ማህፀን መወለዱ፤ አንድም በአካል ከኃጢአት ነፃ ሆኖ ተወለደ። በሚሉና የለም ልደቱ ሁለት ነው "ሁለት ልደት" ሀሳብ አራማጆች መሀከል የተነሳው የሀይማኖት ውዝግብ (አውራጃዊ አስተሳሰብ ትግራይ ጎጃም ጎንደር ሸዋ) በአካባቢ መለያየቱ ለዘመነ መሣፍንት ክፍፍል ተጨማሪ ጉልበት የሆነበት ዘመን ነበር።

4. የእርስ በርስ ጦርነት የበርካቶችን ህይወት የቀጠፈበት ሆኖ አልፏል። ንግድ ምርት አብሮነት ቀዝቅዞ የታየበት የታሪክ ጠባሳ እንደነበር ለመካድ ሙከራዎች ቢኖሩም እውነታውን የመሸፈን አቅም የላቸውም። ታሪከን በአግባቡ በመሠነድ በኩል ግን ዘመኑ በጣም ተሽሎ ታይቷል።

ሲጠቃለል የዘመነ መሣፍንት መቶ ሊሞላ እሥር ፈሪ ዓመታት ችግሮች በሚገባ ብጥር ተደርገው የተገፉበት ምክንያት ፀሐፊዎቹ አንፃራዊ ነፃነት በማግኘታቸው ነበር። ንጉሦቹ ጠንካራ ቢሆኑ ኖሮ ደፍሮ ድክመታቸውንና በአስተዳደራቸው ሥር የነበሩትን ትርምሶች ለመግለፅ ማን ይደፍር ነበር? ዘመነ መሣፍንት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ጥሩ ማስተማሪያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። በተለይ አሁን በኢትዮጵያ ያለው 'ዘመነ ብሔረሰብ' የሀገሪቱን አንድነት በእጅጉ የሚያላላና የሚፈታተን መሆኑን አለማስተዋል፡- "ከታሪክ የማይማሩ እንዲደግሙት ይፈረድባቸዋል" የሚለውን በራስ ላይ መተግበር መሆኑን አለማጤን ዋጋ ያስከፍላል።

የጦር አበጋዞች ጠብመንጃ እያነገቱ በቡድን የሚንቀሳቀሱ፣ ጠብመንጃ ይዘው ሰላማዊ ሠልፍ የሚወጡ፣ ነፍጥ አንግበው ባንኮችን የሚዘርፉ እና መኪና የሚያቃጥሉ፣ ጦር መሣሪያ አንስተው ሰላማዊ ነዋሪ የሚያፈናቅሉ፣ ሽፍታ በነዋሪ ላይ ሥጋት የሚደቅን ከሆነ ... የሶማሊያ ተስፋፊዎችና አልሸባብ በምሥራቅና ደቡብ የሀገሪቱ ከፍሎች አደጋ መሆናቸው፤ የ27 ዓመታት ጦስ ጥምቡሳት በየቦታው የተደራጁ ጦር ቀቤና ማረቆ አማራ ትግራይ ኦሮሞ ሲዳማ አርጎባ ኢሳ እና መላው የኢትዮጵያ ህዝብ የማይገምተው አደጋ ከፊትለፊቱ መደቀኑን መገንዘብ አያዳግተውም።

በታሪኩ ካጣጣማቸው የበዙ መልካም ጊዜያትና አልፎ አልፎ ከገጠሙት እልቂቶች በመነሳት ከፉውን ከደግ አመዛዝኖ የሰላምን ዋጋ እንደ ኢትዮጵያ ህዝብ የሚረዳ



t.me/OLDBOOKSPDF

የለም። ሶማሊያ እና ደቡብ ሱዳን ሲያልቁና ሲሰደዱ፤ (2018 - 2019) ሶርያውያን አህጉር አቋርጠው መጥተው አዲስ አበባ ውስጥ በየአደባባዩ ሲለምኑ ያየ በእሳት አይጫወትም። ሀገራቸውን ቀዬአቸውንና ጎጇቸውን ለቅቀው እጃቸውን ምፅዋት ፍለጋ ሲዘረጉ ኢትዮጵያውያን ከንፈራቸውን እየመጠጡ በኃዘን ዐይተዋቸዋልና። ሀገር ታምሳ ሀልውና እስኪ ደረጃ ላይ ሲደርስ ህዝቡ የመይሣው ካሳን አይነት ሣልሳዊ ቴዎድሮስ ከምሥራቅም ይሁን ከምዕራብ፤ ከሰሜን አቅጣጫ ወይም ከደቡብ ብቅ እንዲል መናፈቁ አይቀርም። የበለጠ መሻቱ ግን ያለ ምንም ደም ዘመንና ትግል ወደ ሥልጣን የከብር ወንበር ያመጣቸው ስብእናዎች 'ዘመነ መሣፍንትን' አከስመው ዘመነ ኢትዮጵያውያን/ ዘመነ አንድነትን ማሥፈን እንዲችሉ ነው። ኢትዮጵያ በፍቅር ለዘላለም ትኑር።

## የዳግማዊ ቴዎድሮስ ጸሐፍት ትእዛዝት (1855 - 1868)

ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ የዘመናዊ የኢትዮጵያ ታሪክ መነሻ ተደርገው ይወሰዳሉ። የዚህ አይነተኛ ምክንያት የኢንዱስትሪ አብዮት ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲያቆጠቁጥ በወሰዷቸው የደመቁ ታላላቅ እርምጃዎች ነው። (በምዕራፍ ሁለት በሰፊው ተዳስሷል።) ምንም እንኳ አፄ ቴዎድሮስ የዘመነ መሣፍንት ውጤት ቢሆኑም በየጊዜው ነገሥታት ሲጠነከሩ እስከ ቀይ ባህር እና ሶማሊያ ውስጥ ዘይላና በርበራ ድረስ የምትዘረጋውን፤ ኃይላቸው ሲዳከም እንደ ዘመነ መሣፍንት የምትቆራረሰውን ኢትዮጵያን መልሶ ለማሰባሰብ ታላቅ ራዕይ በመወጠን ተነስተዋል።

የየአካባቢው መሣፍንት በየአምባቸው ገንነው ገገር የመሆን ፍላጎታቸው ሀገር ስለሚያሳንስ በቸልታ ማለፉ ለቴዎድሮስ የሚዋጥላቸው አልሆነም። ከዚህ አኳያ ኃይል በተቀሳቀሰበት ያላሠለሰ ዘመቻ በተለይ ሸዋና ወሎ ላይ የቅጣት በትራቸውን አሳረፉ። ያሰቡትን ያህል መልሶ በማሰባሰቡ የተሳካላቸው እንዳልሆነ ከፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ፦ "A Modern History of Ethiopia, 1855 - 1991) ጭምር የተገለፀ ቢሆንም ዘመነ መሣፍንት ያለፕርፕር እንዲያከትምና ቀጣይ መሪዎች ወደ ማዋሀድ ተጉዘው ሦስተኛው ንጉሥ ምኒልክ ውጥናቸውን ዳር አድርሰዋል። ከዚህ አኳያ ቴዎድሮስ ከሚገባው በላይ ውጤታማ ነበሩ።

በዘመነ መሣፍንት ከንጉሦቹ መዳከም ጋር ተረስተው የነበሩ ፀሐፍተ ትእዛዛት ወደ ቀደመ የነገሥታቱን የእለት ከእለት ገቢርና ውሎ መመዝገብ ሥፍራቸው ተመለሱ። ዳግማዊ ቴዎድሮስ በዋናነት ሦስት የተለዩ ፀሐፍተ ትእዛዛት ነበሯቸው። እነርሱም



t.me/OLDBOOKSPDF

አለቃ ዘነበ፣ አለቃ ወልደማርያምና አንድ ስማቸው ያልተገለፀ ፀሐፊ ነበሩ። ሦስቱ ፀሐፍት ትእዛዛት ለመጀመሪያ ጊዜ የአፄ ቴዎድሮስን ጥንካሬ ብቻ ሳይሆን ድክመቶታቸውን ዘርዝረው በመዝገቦቻቸው ማሥፈር ችለዋል። ቴዎድሮስን በስህተታቸው ምክንያት ከመገሠፅም አልቦዘኑም።

በተለይ አለቃ ወልደማርያም የቴዎድሮስ እስረኛ ጭምር እንደነበሩ ስንገዘብ ቴዎድሮስ ታሪኩ ከፋም ይሁን ደግ እንዲመዘገብ ፍላጎት እንደነበራቸው እንረዳለን። ቴዎድሮስ ታሪኩ ከፋም ይሁን ደግ እንዲመዘገብ ፍላጎት አንደነበራቸው እንረዳለን። ቴዎድሮስ በሥልጣን ዘመናቸው መጀመሪያ የነበራቸውን የህዝብ ፍቅር ፅሑፎቹ ቴዎድሮስ በሥልጣን ዘመናቸው መጀመሪያ የነበራቸውን የህዝብ ፍቅር በሂደት የማጣታቸውን ምክንያቶች በዝርዝር መገንዘብ ያስችላሉ። አፄ ቴዎድሮስ በሥልጣን ዘመናቸው ጅማሬ በርህራኄ፣ ማህበራዊ ፍትህ፣ የደሀውን ህይወት ለማሻሻል ባላቸው ቁርጠኝነትና መሠል ምርጥ ስብእናዎች እንደሚታወቁ ሀሮልድ ማርከስ፦ "A History of Ethiopia" በተሰኘው መፅሐፉ ከገፅ 64- 65 አስፍሯል። ዋል አደር ሲል የቴዎድሮስ ከንድ አለቅጥ መከበድ ጀመረና ትካዜ እዚህም እዚያም ይታይ ጀመር። አንዱ ገበሬ ቴዎድሮስ በሚያልፉበት መንገድ ቁጭ ብሎ በራሮት ጭንቅላቱን ወደ መሬት ደፍቶ ያገኙትና፦

"ይህን ጊዜ በውስጥህ ምታገተመትመው ይህን ርጉም ንጉሥ በደፋው እያልህ ይሆናል" አሉት። ገበሬውም መልሶ፦

"አልሰማኝ አለ እንጂ ታዲያ ከዚህ በላይ ምን ጸሎት አለኝ?" በማለት ቅጭጭም ብሎ መለሠላቸው በማለት ተገልጿል።

በቴዎድሮስ ፀሐፍተ ትእዛዛት የተዘጋጁትን መዋዕለ ዜናዎች ከቀደሙት እኩዮቻቸው የሚለያቸው ዋነኛ ምክንያት የበሬቶቹ በግዕዝ የተፃፉ ሲሆን የአፄ ቴዎድሮስ ፀሐፍት በአማርኛ ቋንቋ ውሏቸውን ሰንደው ማቆየት መጀመራቸው እና በገለፅነው ትችትን የመድፈር ዝግጁነታቸው ነው። እንደ ፕሮፌሰር ሥርገው ሀብለሥላሴ (ከላይ የገለፅነው ምንጭ) የአፄ ቴዎድሮስ ዋናው ፀሐፊ ትእዛዝ አለቃ ዘነብ በማያወላዳ ሁኔታ በአማርኛ ቋንቋ ብቻ መልዕክቶችን መሠነዳቸው ሲታይ የአማርኛ ቋንቋ ሙሉ በሙሉ የመንግሥት የሥራ ቋንቋ ሆኖ ሥራ ላይ የዋለው ከአፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ እንደሆነ አመላካች ነው።

በርካቶች አማርኛ የቤተ መንግሥት የሥራ ቋንቋ ሆኖ እንደቆየ ግምት ቢኖራቸውም ለመጀመሪያ ጊዜ አማርኛ በይፋ የመንግሥት የመሥሪያ ቋንቋ ሆኖ አገልግሎት ላይ የዋለው በአፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት ነው። ሆኖም አልፎ አልፎ ከአፄ አምደፅዮን የንግሥና ዘመን ጀምሮ ብቅ ጥልቅ የማለት ሁኔታ እንደነበረው መዛግብት ያስረዳሉ።



t.me/OLDBOOKSPDF

በአፄ አምደፅዮን (1314-44) የአመራር ወቅት ብቅ ብለው ከነበሩ ንጉሡን የማሞገሻ ጽሑፎች በብዙዎች ዘንድ በቅብብል የተጠቀሰው ግጥም የሚከተለው ነው፡-

ሀርበኛ ዐምደፅዮን መላላሽ የወሰን

ወሐ እንደ መሰን መላላሽ የወሰን

ከወጅ ዜብዳንን ከገንገ ጠጦን

ምን ቀረህ በወሰን ከባሌ አሊን

ከደዋሮ ሄደራን ከፈጠጋር ዜላርድን

ከኢፋት አምበል አቦከርን

ከግድም የወሰይን

ከአንጎት ኀርን አሞራን

ከአገው ቤተ አገርርን

ከትግሬ ነገደ ክርስቶስ ይውረድን

አደረግኸው ገንዙን

እንዲሠራ ዳውጃውን

ማን ቀረህ በወሰን

አላፀፋኸው ፊቱን

አላስማረከኸው ልጅ ሚስቱን

ከጎጃም ጃን ከምርን

ከጋፋት ዎላይታን

ከዳሞት ሞታለሚን



t.me/OLDBOOKSPDF

ማን ቀረህ ከወሰን

ያላፀፋኸው ፊቱን

ያላስማረከኸው ሚስቱን

ሀርበኛ አምደፅዮን

መላላሽ የወሰን

ዐምደፅዮን ስም የዘራ

ከወጅ እስከ ጥር አሞራ

ቃራ ይነስነሰን ቃራ እንደ ጭራ

በወንዶች ገራገራ

ከሀድያ እስከ 'ከምባታ'

ከባሕር እስከ ኤርትራ

ዐምደፅዮን ስም የዘራ

ከላይ የተቋጠሩ ስንኞች ዐምደፅዮን በጊዜው ተቆጣጥሯቸው የነበሩ ግዛቶችን ስፋትና የስነፅሑፍ ደረጃ የማሳየት አቅም አላቸው። ከዚህ በኋላ ምንም እንኳ ዐማርኛ አልፎ አልፎ በሥነ ጽሑፍ ውስጥ መንጸባረቅ ቢጀምርም እስከ ዔጼ ቴዎድሮስ ዘመን ግዕዝ የቤተ መንግሥት የሥራ ቋንቋ ሆኖ ቀጥሏል፡፡

ተከለፃድቅ መኩሪያም ሆኑ ሌሎች በአፄ ቴዎድሮስ ዙሪያ የፃፉ ታሪክ መዝጋቢዎች የዘመናዊውን የኢትዮጵያን ታሪክ ጅማሬ ለማውሳት የፀሐፍተ ትእዛዛቱን ሥራዎች ምነሻ አድርገዋል። ቀጥሎ የነገሡት አፄ ተከለጊዮርጊስ (1868 - 1871) የረባ አቅምና የሌሎቹን ተቀናቃኞቻቸውን የሸዋውን ንጉሥ ምኒልክንና የትግራዩን ራስ ካሳ ምርጫ እንዲሁም የየአካባቢው ገገርዎች ይሁንታ አለማግኘታቸው ተዳምረው ሳይጀምሩ የተቋጩ ንጉሥ አድርጓቸዋል። የእህታቸውን ባል ካሳ ምርጫ (የፈረስ ስማቸው በዝብዝ ካሳ) ለማስገበር ያደረጉት ጉዞ በአሰም ጦርነት ተሸንፈው የሥልጣናቸው ዘመን ማብቂያ ሆኗል።



t.me/OLDBOOKSPDF

ዐፄ ዮሐንስ ዐራተኛ (1872 -1889):- የሥራ ቋንቋቸውን ዐማርኛ ከማድረጋቸውም ዐፄ ዮሐንስ ዐራተኛ ለውውጣቸውም በዐማርኛ ቋንቋ ነበር። ጠላቶች ኢትዮጵያን ሊላ የደብዳቤ ልውውጣቸውም በዐማርኛ ቋንቋ ነበር። ጠላቶች ኢትዮጵያን በወረሩበት ጊዜ የክተት አዋጅ ያወጁት በዐማርኛ ቋንቋ መሆኑ ግልፅ ነው። የአዋጁ መልእክት እንደሚከተለው ሠፍሯል:-

> "የኢትዮጵያ ልጅ ሆይ ልብ አድርገህ ተመልከት።ኢትዮጵያ የተባለችው ሀገር አንደኛ እናትህ ናት። ሁለተኛ ሚስትህ ናት። ሦስተኛም ልጅህ ናት። አራተኛ መቃብርህ ናት። አምስተኛም ዘውድህ ናት። እንግዲህ የእናት ፍቅር፣ የሚስት ደግነት፣ የልጅ ደስታ፣ የመቃብር አቃፊነት (ካባቲነት) እና የዘውድ ክብር ምን ያህል እንደሆነ አውቀህ ተከተለኝ።"

በዚህም መሠረት በንግድ መስፋፋት ምክንያት በርካቶችን እያግባባ ያስተሳሰረው የአማርኛ ቋንቋ ግዕዝን ተክቶ የቤተ መንግሥት የሥራ ቋንቋ መሆኑ በፈጠረለት ስፊ እድል ምክንያት:- በኢትዮጵያ ውስጥ የፌዴራሉን መንግሥት፣ የአዲስ አበባንና የድሬዳዋን አስተዳደር አካባቢዎች፣ የ56 የደቡብ ኢትዮጵያ ባለ ብዙ ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰቦች፣ የጋምቤላን የተለያዩ ቋንቋዎች ተናጋሪ ማህበረሰቦች እና የቤኒሻንጉል ጉሙዝ የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚናገር ህዝብ ከልሎች በህግ አውጪ፣ ህግ አስፈፃሚ እና ህግ ተርጓሚ አካላት አማርኛ የሥራ ቋንቋ ሆኖ በማገልገል ላይ ይገኛል።

ከዚህም በተጨማሪ በትግራይ ክልል የኩናማ ኢሮብ (ሳሆ) ማህበረሰቦች ከቋንቋቸው ውጪ ከሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር የሚገናኙት በአማርኛ ቋንቋ ነው። ከዚህም በተጨማሪ የራያ እና ወልቃይት ማህበረሰቦች ቀዳሚ ቋንቋቸው አማርኛ መሆኑ ለጥያቄ የሚቀርብ አይደለም። በድምሩ አማርኛ ከክልሉ ውጪ ጭምር አሮምኛን አስከትሎ በሚሊዮኖች የቋንቋው ተናጋሪዎችን ማስተሳሰር የቻለ የማንኙነታችን ሥጦታ ነው። ቋንቋ ደጋግመን እንደምናነሣው የሰው ልጆች መሻታቸውን ለመግለፅ እርስ በርሳቸው የሚግባቡበት መሣሪያ ሲሆን ከህሎትም ነው። በእንግሊዝኛ እና ሌሎች ባዕዳን ቋንቋዎች በደስታ እየተጠቀሙ ዐማርኛ የሚጎፈንናቸው ጥቂት ግለሰቦችን ብናይ ሊገርመን አይገባም። ምክንያቶቹን በሌሎች ክፍሎች ጠቅሰን መፍትሔዎቹን እናመላከታለን።

ከላይ የዐፄ ዮሐንስ የክተት አዋጅ ውስጥ እንደተመለከትነው ኢትዮጵያን ለመግለፅ የሞከሩት በአምስት ዋነኛ አህዶች ላይ ተመርኩዘው ነበር። ይኸውም:-



t.me/OLDBOOKSPDF

1ኛ. ተወዳዳሪ በሌለው ፍቅር ማለትም በ"እናት" በመመሠል ኢትዮጵያን ገልፀዋታል። ይኸውም "እናት ሀገር" የሚለውን የዘመናት የኢትዮጵያን መገለጫ በጉልህ አስምረውበታል።

2ኛ. ኢትዮጵያን በ"ሚስት" ወከሏት። ሚስት ገመና፣ ያላትን አዘጋጅታ የምታቀርብ፣ አካል እና ከፊል ማንነት ናትና የምስጢሩን ቁልፍ መከፈት ይገባል።

3ኛ. ሀገር በ"ልጅ" ተመስላለች። ወላጅ ለልጁ የሚያወርሰው ቅርስ፣ ከልጅ የሚገኘው ደስታ፣ ለልጆች የምትተላለፍ ሀገር እና አያሌ ተዛማጅ እውነታዎችን ያዘለ መልእክት አካትቷል።

4ኛ. የሰው ልጅ በመጨረሻ ዘመኑ በአብዛኛው በ"መቃብር" ይታቀፋል፤ ሀገርም መቀበሪያ ናትና። ኢትዮጵያን ለህዝቡ "መቃብርህ ናት"ና አቃፊነቷን አስተውል ማለታቸው ድንቅ ነው።

5ኛ. "ዘውድ"፦ የዘውድ ክብር እንደ ብሪታንያ ባሉ ሀገሮች ነገሥታቱ "የአንድነትና የዘመናት ታሪክ መገለጫ" ተደርገው እስከዛሬም ድረስ ቀጥለዋል። በብሪታንያ ታሪክ ውስጥ በርካታ ግፎች የተፈፀሙ ቢሆንም መልካሙን ለትውልድ ማውረስ የሚፈልገው ማኅበረሰብ ዛሬም ርእሰ ብሔራቸውን (Head of the State) ከነገሥታቱን የዘር ሐረግ በማድረግ (Constitutional Monarchy)፤ ለታሪካቸው ታላቅ ሥፍራ በመቸር ዘመን ተሻጋሪ ማድረግ ችለዋል። በአጠቃላይ የሀገር ፍቅር ስሜት በእያንዳንዱ ዜጋ ልቡና ውስጥ እንዲሠርፅ በመንግሥት በኩል ሠፋፊ መርሐ ግብሮች ተዘርግተው በፅናት ሊተገበሩ ይገባቸዋል። ምሁራንና ልሂቃን አንድነትን በማስፈን ረገድ የመምራት ሚናቸውን እንዲወጡ ታሪካዊ ጥሪ ቀርቧል።



t.me/OLDBOOKSPDF

## የጸሐፍት ትእዛዞችና የጸሐፍት ድርሻ ቅኝት

### ከዐፄ ምኒልክ እስከ ዐፄ ኃይለሥላሴ (1889 - 1974)

በዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረሥላሴ ወልደአረጋይ የቤተመንግሥቱ ታሪክ ዘጋቢ ሆነው ብቅ ብለዋል። የ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መባቻ በኢትዮጵያ ታሪክ አጻጻፍ ውስጥ አዲስ አቀራረብን ይዞ መጥቷል። ይኸውም ፀሐፊዎቹ በአዛገሮቹ ትእዛዝ መሠረት የንጉሦቹን ፍላጎት ብቻ ተከትለው ከመፃፍ ተላቅቀው የራሳቸውን ምልከታ ባሻቸው መንገድ መመዝገብ መጀመራቸው አንድ እርምጃ ወደፊት ሆኖ ተመዘገበ። ከነዚህም መሀከል አፈወርቅ ገብረኢየሱስ ጣሊያን ሀገር ሳሉ በራሳቸው ተነሳሽነት የዳግማዊ አፄ ምኒልክን ታሪክ መፃፋቸው፤ አለቃ ታየ ጀርመን ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በዳግማዊ ዊልያም ግብገር እና በዳግማዊ ምኒልክ ይሁንታ በዩኒቨርሲቲ ውስጥ መምህረ ጉባኤ ሆነው በማስተማርና ራሳቸውም ትምህርታቸውን በማሻሻል ታሪክን ለመፃፍ ሞካከረዋል። በተጨማሪ ብላቴን ጌታ ሀሩይ ወልደሥላሴ፣ ብርሀኑ ድንቄ እና ደጃዝማች ብርሀነ መስቀል ደስታ የበኩላቸውን አሻራ በታሪክ መዛግብት ተርታ አሳርፈዋል።

የኢትዮጵያን ታሪክ በተለየ መንገድ ተንትነውና መረጃዎችንም ሆነ ማስረጃዎችን በባትሪ ብርሀን አፈላልገው አብርሆት በመፍጠር ረገድ ቁንጮው ተከለፃድቅ መኩሪያ ናቸው። አፃፃፋቸው ዘመናዊውን አፃፃፍ የተከተለ እንዳልሆነ የመግለፅ አዝማሚያ ቢኖርም የተከለፃድቅን ሥራዎች ያህል በሌሎች የታሪክ ተመራማሪዎች የተጠቀሰና የኢትዮጵያን ታሪክ ለመፃፍ መነሻ በመሆን ያገለገለ ጦማር ስላለመኖሩ መስማማት ይቻላል። ፅሑፎቻቸው እስከዛሬም ድረስ በፍቅር የሚነበቡ፣ ታሪኩን ለማወቅ ፍላጎት ላለው ሁሉ ከምንጩ እየቀዱ ከማሣየት የማይቦዝኑ፣ ጠቀሜታቸው የትየለሌ ነው። 'ለተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ ሆኖ' ለሚተቹ ግን 'ከገነትም ቢሆን ግድፈት አያጡምና' ታሪክን ለማርከስ ባዘሉት እኩይ ፍላጎት እንከን በወረንጦ በመልቀም ከመተቸት አልታቀቡም። ከኋላ የሚዘውራቸው ገፊ ኃይል በመኖሩም እውነት እንዳይቦገዝ ከመሥራት ለአፍታ አይታከቱም።

ተከለጻድቅ መኩሪያ በኢትዮጵያ ታሪክ ዙሪያ ዐራት ታላላቅ ሥራዎችን አበርክተዋል።

እነርሱም:-

1. "ከዳግማዊ ቴዎድሮስ እስከ ዐፄ ኃይለሥላሴ" ከ1855 - 1974 ጀምሮ አንጋፋ ሥራቸው ሆኖ ተሰንዷል።



t.me/OLDBOOKSPDF

2. ቀጥሎ የመጣው ሥራቸው "ከዐፄ ልብነድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ (1508 - 1868) ይዳሥል። በተለይ ከ16ኛው ክፍለዘመን መጀመሪያ እስከ ዘመናዊ ታሪካችን መከፈቻ ላለው ጊዜ በቂ ሥዕል የማስያዝ አቅም አለው።

3. ከጥንቱ የኢትዮጵያ ታሪክ ጀምሮ እስከ ዛግዌ ሥርወ መንግሥት ያለውን ታሪክ ለማሣየት እንዲያስችል አብዝተው ደከመዋል።

4. ዐራተኛው ሥራቸው የሰሎሞናዊውን ሥርወ መንግሥት ታሪክ ከዐፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዐፄ ልብነድንግል (1270 - 1508) በዋና ዋና ታሪካዊ ክዋኔዎች ላይ ተንተርሦ ታሪከን ለመግለጥ ጥረት አድርጓል።

ይልማ ዴሬሣ በ1967 አስራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን ታሪክ ላይ በመመርኮዝ ታሪካዊ መፅሐፍ አዘጋጅተው ለንባብ አብቅተዋል። የመጀመሪያው ክፍል፦ በ16ኛው ክፍለ ዘመን በደጋማው የክርስቲያን መንግሥትና በቆላማው የሙስሊም ሡልጣናዊ አስተዳደር መሀከል የተደረገውን ምጣኔ ሀብታዊ ጦርነት ሲያመለክት፤ ሁለተኛው፦ በ16ኛው ክፍለ ዘመን ኦሮሞዎች በከፍተኛው ደጋማ አካባቢ ያደረጉትን እንቅስቃሴና የመሥፋፋት ዘመቻ ያሳያል።

ከላይበዝርዝር የተመለከትናቸው የታሪክ ማስረጃዎችም ሆኑ መረጃዎች ሲፃፉ መነሻና መድረሻቸው፦ የሀይማኖትን ዶግማና ቀኖና ማፅናት፣ የነገሥታቱን ክብር ማግዘፍ፣ ታሪከን የመመዝገብ ፍላጎት እና መሠል ዓላማዎችን ማገልገል ከመሆን አልፎ ዛሬ የሚፈጠረው በጎሣ የመከተፍ አባዜን ታሳቢ አድርገው አይደለም። ታሪኮቹ የሚያጠነጥኑት በነገሥታትና በሀይማኖት ዙሪያ እንደመሆኑ የትግራይ ብሔረሰብ ታሪክ ወይም የአማራ ብሔረሰብ ታሪክ አሊያም የአገው ብሔረሰብ ታሪክ አይደሉም። የፅሑፎቹ ይዘት፦ የነገሥታት የአስተዳደር ሥርአት፣ የንግድ ልውውጥ፣ የእምነት አርበኞች ተጋድሎ፣ የቤተመንግሥቱ ውሎ፣ የነገሥታቱ ከቦታ ቦታ መዘዋወርና ያጋጠማቸው ሁኔታ፣ የተደረጉ ጦርነቶች፣ ድሎችና ሽንፈቶች (ለመሸነፋቸው የቀረቡ መሸፈኛ ምክንያቶች)፣ ከውጪው ዓለም ጋርና በሀገር ውስጥ የተደረጉ መስተጋብሮች ... የተካተቱባቸው ናቸው። ፅሑፎቹ እንድን ብሔረሰብ መርጠው የማያገዝፉ ለይተውም የማያኅድፉ መሆኑ በሚገባ በጎልህ ብዕር ሊሠመርበት ይገባል።



t.me/OLDBOOKSPDF

## ሌሎች ጽሑፎች

ለኢትዮጵያ ታሪክ ግብአት የሚያገለግሉ ሰነዶች ገድሎችና መዋዕለ ዜናዎች ብቻ ሳይሆኑ ተዛማጅ ጽሑፎም ይገኛሉ። ከእነዚህም መሀከል ክብረ ነገሥት (Glory of Kings) ሲጠቀስ ክብረ ነገሥት ሰሎሞናውያን ነገሥታት እንዴት እንደመጡ የሚያትት በዛግዌ ዘመነ መንግሥት ከኮፕቲክ ቋንቋ ወደ ዐረብኛ ቋንቋ እና ወደ ግእዝ የተመለሠ ነው። ክብረ ነገሥት ጠለቅ ተብሎ ከታየ የአኩስም ንጉሥ 'የነበረቺው' ንግሥተ ሳባ (Queen Sheba) የእስራኤሉን ንጉሥ ሰሎሞን ጥበብ ለመቅሰም ከነተከታዮቿ ወደ እሥራኤል የዛሬ 3,000 ዓመት ገደማ መጓዟን፤ ለንጉሡ ያቀረበቻቸውን ሥጦታዎች፤ በቅርርባቸው መፀነሷን፤ ከንጉሥ ሰሎሞን አብራክና ከንግሥተ ሳባ ማህፀን ቀዳማዊ ምኒልክ (1003 - 974 ዓ.ዓ) ከክርስቶስ ልደት በፊት ስለመወለዳቸው ይገልፃል።

ክብረ ነገሥት ወደ ዐረብኛ በአበሊዝና አበፊጠርግ እንደተተረጎመ እና ወደ ግዕዝ ቋንቋ ደግሞ በንጉሥ ላሊበላ አዛዥነት በይስሐቅ መሪነት በተቋቋመ ቡድን በእነ ይምርሐነ አብ፣ ሕዝበ ክርስቶስ፣ እንድሪያስ፣ ፊልጶስና መሐሪ አብ የሚል መረጃ ስለመኖሩ ባዬ ፈለቀ "Questions About Kibre Negest" p.x ዐሳይቶናል። ሰርገው ገላው የግዕዙን ክብረ ነገሥት ወደ አማርኛ (እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር 1901) መልሶታል።

የክብረ ነገሥት አንኳር ፍላጎት፡- "ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ" - የይሁዳ (እሥራኤል) ነገድ ከሆነው አሸናፊው አንበሳ ንጉሥ ሰሎሞን 'የአንበሳ ክብር ሞገሥና ዝና ያለው አንበሳ ተገኘ' በማለት ይጀምራል። ይህ አይነቱ አመለካከት በጥንት ጊዜ በሠፊው ሥራ ላይ የዋለ ነበር። ለምሳሌ፡- በጥንታዊት ግብፅ ራስ ቅሉ የሰው መላ ሰውነቱ የአንበሳ የሆነ የነገሥታት ስነ ሐውልት 'ስፊኒክስ' ተቀርፆ እስካሁንም የጥንት ታሪካቸው አካል በመሆን ይጎበኛል። የዚህን መንግሥት መለኮታዊ ፈቃድ ለማሣየት "ሥዩመ እግዚአብሔር"፡- 'በፈጣሪ ፈቃድ የተሾመ'፤ የማይወቀስ፣ የማይከሰሥ - 'ሰማይ አይታረሥ ንጉሥ አይከሰስ' እንዲሉ።፤ አንዳንዶች "ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ" የሚለውን መንፈሳዊ ትርጉም በመስጠት ከይሁዳ ነገድ የሆነው አሸናፊ አንበሳ (ኢየሱስ ክርስቶስን) ከስማቸው አስቀድመው ለመጥራት ነው ይላሉ፡፡ ይኸውም በስመአብ ወወልድ ... ወይም ቢስሚላሂ......... ወይም በኢየሱስ ስም ብሎ



t.me/OLDBOOKSPDF

እንደመጀመር ነው ይላሉ:: ሆኖም የንድፈ ሀሳቡ ብቸኛ ምንጭ የሆነው ክብረ ነገሥት ይህንን የሚደግፍ ይዘት የለውም::

በመጨረሻ:- "ንጉሠ ነገሥት / የነገሥታት ንጉሥ" የሚል ቅፅል ይጨመርበትና በሚወጣለት የንግሥና ስሙ የመጀመሪያ ሆኖ ሌላ ንጉሥ በተመሣሣይ ስያሜ ከነገሠ ከቀደመው ለመለየት ከሁሉም የሚቀድመው - ቀዳማዊ፣ ሁለተኛ ከሆነ ዳግማዊ፣ ሣልሳዊ፣ ራብዓዊ እያለ ይቀጥላል። አክሱማውያን በዘግዌ ሥልጣናቸውን መነጠቃቸውን ተከትሎ ከኤርትራው ሺመዛና ገዳም እና ከአክሱም እንዲሁም ትግራይ አብያተ ክርስቲያናት ከፍተኛ ፀረ ዛግዌ ቅስቀሳ ነበር። እንደ ክብረ ነገሥት ገለፃ ማንኛውም ሰው የዘር ሐረጉን ከንጉሥ ሰሎሞንና ከንግሥተ ሳባ ከተወለደው ቀዳማዊ ምኒልክ የዘር ሐረጉን ወደኋላ ትውልዶች ቆጥሮ ካላያያዘ በስተቀር 'ቅብዓ መንግሥት' አይፈፀምለትም።

በዚህ የተነሳ አገዎቹን "ዲቃላ ገገሮች" ወይም "ሥልጣን ነጣቂዎች" አድርጎ መሣል በህቡዕ ውስጥ ለውስጥ ተጀመረ። በሂደት በምጣኔ ሀብታዊ አቅሙና በወታደራዊ ሀይሉ የደረጀው ተስፋ ኢየሱስ በአክሱማውያን በተደረገለት ድጋፍ ታግዞ ይኩኖ አምላክ በሚል የንግሥና ስም በትረ መንግሥቱን ከዛግዌዎች ነጠቀ። ክብረ ነገሥት ከ1270.-1974 ባለው ጊዜ ለ"ሰሎሞናውያን ነገሥታት" ሥልጣን ማጠናከሪያ ቀኝ እጅ ሆኖ አገለገለ። ይሁንና በኢትዮጵያ የረጂም ዘመን ታሪክ ሥልጣን በቀጥታ ከንጉሠ ነገሥቱ ሞት በኋላ እንደሚተላለፍ የሚገልፅ ህግ (Law of Primogeniture) ባለመኖሩ ከነገሥታት ህልፈት በኋላ የእርስ በርስ ጦርነቶች የተለመዱ ነበሩ።

**ፍትሐ ነገሥት** (Justice of Kings):- በነገሥታቱ የፍትህ ሥርአት ውስጥ የተቀመጡ የሲቪል ህጎች ተዘርዝረው የተቀመጡበት ሰነድ ሆኖ አገልግሏል።

**ሥርአተ መንግሥት** (Administration of Kings):-

የመንግሥታት አስተዳደር ዘይቤ፣ አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች የተቀመጡበት ሰነድ በመሆኑ ለታሪክ በማስረጃነት በማገልገል ረገድ አይነተኛ ድርሻ አላቸው። ስለዚህም ይኽን ሰነድ ከምንም በላይ ዛሬ ኢትዮጵያውያን የምንኮራባቸው ከደረታችን ነፋ፣ ከትከሻችን ጀነን፣ ከውስጣችን ቀብረር ብለን የምናከብራቸው አባቶቻችን ያቆዩልን ጥበቦች ፅሑፎች የሽመና እና የእደ ጥበብ ውጤቶች በርካቶች



t.me/OLDBOOKSPDF

ናቸውና ዛሬ ለዓለም በገሀድ ቀና ብለን ከጀግንነት ገድሎቻችን ጋር አዳምረን ማሳየት እንችላለን።

አዕምሯችን ከተጠቀጠቀበት ከፋት ፀድቶ የሰሜኑ የደቡቡ የምዕራቡ የምሥራቁ እና የመሀከሉ ታሪክ የእኛ የጋራችን ነው ብለን ወደ ምንቀበልበት የምጥቀት ደረጃ ስንደርስ፤ ከቁጥቁጥ ትንሽ አስተሳሰብ ወጥተን ወደ አንድነት ትልቅ አስተሳሰብ ስናድግ፤ ያ ቀን ይቀርብና በአባት እናቶቻችን የወል ታሪክ አብረን እንደምቃለን። በቀጣይ የሁሉንም ኢትዮጵያዊ ማህበረሰብ ታሪክ በጋራ ቁጭ ብለን ስናዘጋጅ ያለጥርጥር ሰነዶቹ የደማቅ ታሪካችን ሰበዞች ውስጥ ይካተታሉ። እስከዚያው ድረስ ሳንረዳ ሳንገነዘብ ሳንመዝን ሳንፈትሽ እንደ በቀቀን የተነገረንን ብቻ እየደገምን ውብ ታሪኮቻችንን 'የደብተራ ታሪክ' ብሎ ማጣጣል ራስን ከማስገመት ውጪ ለማናችንም አይጠቅምም።

ደብተራ ማለት ከወቅቱ ቀድሞ ፊደልን እና የቁጥር ቤትን በመሠረታዊ ደረጃ ተምሮ፤ በደረጃ ሽግግር ወደሚቀጥሉት ከፍታዎች ማለትም ዜማ ድጓ ቅኔ መጻሕፍት ቤት የሊቅነት ጥግ ድረስ የተማረ (ከአሁኑ ፕሮፌሰር ባልተናነስ በ'JTV እንድሮሜዳ መርሐግብር' የምንከታተላቸውን ጥበቦች ለዓለም ያበረከተ ጠቢብ ነው። ከወቅያኖሱ ለመቅሰም ዛሬ እነ ጀርመን በግዕዝ እስከ ሦስተኛ ዲግሪ (PhD) እያስተማሩ መሆኑን ልብ ይሏል። ከእውቀቶቹ ሳይንስ የደረሰባቸው ጥቂቶቹን ብቻ ሲሆን ወደ ሌሎቹ ምሥጢሮች ለመድረስ ከፍተኛ በጀት መድቦ እየመረመረ ነው። የአባቶቻችን የሳይንስ ምጥቀት በቀላሉ የሚደረስበትም አይመስልም። እስመስሎ መገልበጥ የተሳነው፣ ዳቦ እንኳ 'በፈረንጅ ማብሰያ' የሚጋግር ተደግሟል ቡድን በምን ወኔ ወደ ታላላቆቹ የማይደርስበት ልሀቀት ይንጠራራል?

ኑረዲን ኢሳ የተባለ ገጣሚ፦

"አልሆንልህ ካለህ ማደግና መግዘፍ

ከትልቆች መሀል አንዱን መርጠህ ገለፍ"

የሚለው የሰንኝ ቋጠሮ እንዳይሰራብን ወደ ማንችለው ከምንንጠራራውዝ፤ በልካችን የምንችለውን ብንሠራ ይመረጣል። በታሪካቸው ህያው የሆኑ ባለ ታሪክ ሙታንን - የሚያወርሱት ታሪክ የሌላቸው፤ ቁም በድኖች ሲወቅሷቸው ማየትና መስማት እጅግ ይቀፋል።



t.me/OLDBOOKSPDF

## ግለ ታሪኮች (Biography)

ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ፡- "Society, State and History, Selected Essays" በሚል ርዕስ ባዘጋጁት ጥልቀት ያለው የምርምር ሥራ "ግለ ታሪኮች በኢትዮጵያ ታሪክ አፃፃፍ ጥናት ውስጥ ጉልህ ድርሻ መያዛቸውን ያስረግጡልናል። እንደ ፕሮፌሰሩ የኢትዮጵያ ታሪክ ሙሉ ለሙሉ ሊባል በሚችል ደረጃ የልሂቃን ታሪክ ነው። ታሪክን መልሶ በፈርጅ በፈርጁ ለማሠናዳት በሚደረገው ጥረት አልፋና ያሚጋው በታዋቂ ስብእናዎች ዙሪያ ማጠንጠኑ የማይጠበቅ አይደለም" ሲሉ ሃሳባቸውን ያጠናክራሉ። የሀሳባቸውን ጠጣርነት ለማጎልበት "ወደ 14ኛው ክፍለ ዘመን ጭምር አንገታችንን አጠማዝዘን ለማየት ብንሞክር ሀቁ ከዚህ የራቀ አይደለም" ሲሉ ይሞግታሉ።

ፕሮፌሰር ባህሩ እንደ ፕሮፌሰር ሥርገው ሀብለሥላሴ ሁሉ የፀሐፍተ ትእዛዙ ዕሑፎች ከዋነኛ ተግባራቸው (የነገሥታቱን ውሎ መዘገብ) ጎን ለጎን ፈርጀ ብዙ ምጣኔ ሀብታዊ ባህላዊ የእምነት ማህበራዊና ፖለቲካዊ ዱራዎች (ድርቅ ረሀብ የመሬት መንቀጥቀጥ ንግድ እምነት...) አካትተው መሠነዳቸው እጅግ የምናተርፍበት ትሩፋት ነው ይሉናል። በተለይ ፀሐፍተ ትእዛዛቱ፡- "በዚህም ዘመን" የሚል ቅጥል እያስገቡ ይህ ሆነ፣ ያ ሆነ ... ማለታቸው በፅሑፎቻቸው ውስጥ በጉልህ የተካተተ መሆኑ ከጊዜ ልኬት አኳያ ጠቀሜታቸው የትየለሌ ነው ሲሉ በአፅንዖት አውስተዋል።

ግለታሪኮች በ19ኛው ክፍለዘመን በስፋት የቀረቡ ሲሆን በ20ኛው ክፍለ ዘመንም ቀጥለው ተንፀባርቀዋል። ግለ ታሪኮች ከ(Memoirs) ከታዋቂ ሰዎች የዕለት ውሎ በማስታወስና ከመዛግብት በመቅዳት ሊተሳሰፉ ይችላሉ። ግለ ታሪኮች በባለ ታሪኩ ፈቃድ (Authorized Biography) ወይም ያለ ግለሰቡ ይሁንታ ( Non/ unauthorized Biography) ሆነው ይሰነዳሉ። ታሪክ ስለ አንድ ርዕሰ ጉዳይ በምሁራን ወይም በሌሎች ግለሰቦች የተፃፉ ከመፅሐፍ አነስ ያሉ ሆነው የተዘጋጁ (Tracts)፣ የእለት ውሎ ማስታወሻዎች (Diaries) እና ሌሎች ዕሑፎች ወፈር ያለ ታሪካችንን ለመደጎስ አብዝተው ይረዱናል።

ከነዚህ በተጨማሪ በብላቴን ጌታ ማህተመሥላሴ ወልደመስቀል የተዘጋጁት "ዝክረ ነገር" (አዋጆች፣ ድንጋጌዎች፣ መመሪያዎችንና ደንቦችን የያዘ)፣ "የኢትዮጵያ መሬትና የግብር ስም" (የመሬት ይዞታና ግብር ሁኔታን የሚያትት) ፅሑፍ፣ የመርስዔ ኃዘን ወልደቂርቆስ ሦስት ማስታወሻዎች፡-



t.me/OLDBOOKSPDF

1) "በዳግማዊ ምኒልክ ዘመን ካየሁትና ከሰማሁት"፤

2) "የዘመን ታሪክ ትዝታዬ በአቤቶ ኢያሱ ዘመነ መንግሥት"

3) "የዘመን ታሪክ ትዝታዬ በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት"፤

ዱሬሳ አመንቴ፣ አናሲሞስ ነሲብ፣ ሀኪም ወርቅነህ እሸቴ፣ ደጃች ከበደ ተሰማ፣ ከንቲባ ገብሩ ደስታ፣ አለቃ ታዬ፣ ገብረህይወት ባይከዳኝ ተጠቃሽ ናቸው። (ከዘጋጁ ከዶክተር ተካልኝ ወልደማርያም ማስታወሻዎች ያገኘውና ከሌሎች ማስታወሻዎች የተገኘ)፤ በ20ኛው ክፍለ ዘመን ተጠቃሽ ከሆኑ ታሪክ ቀመስ ጦማሮች ፀሐፍት መሀከል፡- ስቨን ሩበንሰን፣ ዘውዴ ገብረሥላሴ፣ ኮፊ ዳርከዋሀ፣ ሀጋይ ኤርሊች፣ ሀሮልድ ማርከስ ተጠቃሽ ናቸው።

## የምረቃ ማሟያ ጽሑፎች

በቀድሞው ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ) ሥር በ1962 "የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም / Institute of Ethiopian Studies" ሦስት ክፍሎችን (ታሪክ፣ ሥነፅሑፍ እና ሥነጥበብ) አካትቶ መመሥረቱ ለኢትዮጵያ ታሪክ ወርቃማው ዘመን እንደሆነ መበየን ይቻላል። በሂደት የታሪክ ትምህርት ክፍል ራሱን ችሎ ሲደራጅ ለታሪካችን ጥናት አዲስ ብሥራት ሆነ። የኢትዮጵያን ማህበረሰቦች ታሪክ በተሻለ ደረጃ ለመመዝገብም ታላቅ ተስፋን ሰንቆ መጣ። እንደታሰበውም በሺህ የሚቆጠሩ የምርምር ሥራዎች 'ሼልፎችን'፣ ቤተመፃሕፍትንና ቤተመዛግብትን አጥለቀለቁ። (ዓባይን በጭልፋ ቢሆንም)

ከ1963 - 2019 በአዲስ አበባ (ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ) ከተዘጋጁ በሺህ የሚቆጠሩ የመጀመሪያ ዲግሪ እና ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ፅሑፎች (እስከ 2002 ከተገኙት መሀከል) 59 የሚሆኑት ግለ ታሪኮች ናቸው። በተለያዩ የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች በታሪክ ብቻ ሳይሆን ሀግን ጨምሮ በብዙ የማህበራዊ ሳይንስ ዘርፎች፣ አልፎ አልፎም በተፈጥሮ ሳይንስ ዘርፍ የተደረጉ የምርምር ሥራዎች ከሞላ ጎደል የተሟላና የሚያስማማ ታሪክ ለመፃፍ ያግዛሉ።



t.me/OLDBOOKSPDF

## ታሪካችን በዐዳዲስ መስኮች ሲቃኝ

የታሪክ ጥናትና ምርምር ሥራው አዲስ በተከፈቱ የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች ጭምር መቀጠሉ ታሪካችን ደኅስ እንዲል ተጨማሪ ጉልበት ሆነ። የምረቃ ፅሑፎች ከተለመዱት ዘውጎች ወጣ ብለው ዘመኑ በወለዳቸው ፍፃሜዎች ላይም ማተኮር ጀመሩ። ዋነኞቹ ዳራዎች ያጠነጠኑት፦

ሆስፒታሎች፣ ሆቴሎች፣ መሬት (የመሬት ሥሪት)፣ መንደሮች (ሠፈሮች)፣ መንግሥታዊ ድርጅቶች፣ መገናኛ፣ ሚሲዮናዊ እንቅስቃሴ፣ ማህበራዊ ታሪክ፣ ምጣኔ ሀብት፣ ሠፈራ፣ ሥራ (ጉልበት)፣ ሥነፅሑፍ፣ ሥፖርት፣ ረሀብ፣ ባህላዊ ታሪክ፣ አብያተ ክርስቲያናት፣ብሔረሰብ፣ ትምህርት፣ አለማቀፍ ግንኙነት፣ አርበኞች (ተጋድሎ)፣ እሥልምና፣ እርሻ፣ እርዳታና ማህበራዊ አገልግሎት (በጎ አድራጎት ድርጅቶች)፣ አደጥበብ (ባህላዊ)፣ ከተማ፣ ውጭ ግንኙነት፣ ግለ ታሪክ፣ ፋብሪካዎችና የንግድ ተቋማት፣ ፖለቲካዊ ታሪክ እና ፈርጀ ብዙ መስተጋብሮች ላይ ነው።

በነዚህ የተለያዩ አውዶች የተሰናዱ የምርምር ሥራዎች ከቃል ትውፊቶችና ከገድል ጀምሮ ከተዘጋጁ የፅሑፍ መዛግብት ጋር ተዳምረው በወል የሚሠሩት የታሪክ ሀብር ለሀገራችን ታሪክ ዝግጅት የተበረከተ ታላቅ ፀጋ ነው። እውነተኛ መሠጠት ለተላበሱ ምሁራን በሁሉም መስክ በቂ የሆኑ ታሪካዊ ግብአቶች ተዘጋጅተዋል።

ከተደረደሩት መሀከል ከውዝግብ በፀዳ አግባብ ለትውልዱ ቢሰኑዱ አያሌ ትሩፋቶችን ለትውልዱ ማውረስ ይቻላል። በታሪካችን አፃፃፍ ውስጥ በጉልህ የሚታዩ ከፍተቶችን ለመሙላት ብርቱ አቅም ይፈጥራል። ኢትዮጵያውያን በሚገባ እንድንተዋወቅና የበለጠ እንድንሠናሠል ይረዳል። በታሪክ አረዳድ ከፍተት የተፈጠረውን ቅሬታ ይደፍናል። ሁሉም ኢትዮጵያዊ የራሱን ማህበረሰብ በታሪኩ ገፆች ውስጥ ፈልጎ ስለሚያገኝ አንድነቱን ያጠናክራል። ታሪካችንን ለዓለም ለማስተዋወቅ ሠፊ እድል እናገኝበታለን። በታሪካችን ዙሪያ የምንፈጥረው ስምምነት በሀገር ደረጃ ብሔራዊ መግባባት (National Consensus) ፈጥረን ወደ ብሔራዊ እርቅ (National Reconciliation) ወይም በግልባጩ በብሔራዊ እርቅ ሆድ ለሆድ ተገናኝተን ወደ መግባባት ሊወስደን ይችላል። ሁለቱም መንገዶች ጋሪውን ከፈረሱ አያስቀድሙም። የሚያስፈልገን በ"አቸናፊ" እና "አሸናፊ" ልዩነት፣ በ"ላብአደር" እና "ወዛደር" የንድፈ ሀሳብ ቁርቁስ ወግ እየለመጥን መገዳደል ሳይሆን ሀገርና ወገንን ለማዳን ንፁህ ልቡናን መላበስ ነው።

## ቃላዊ ትውፊቶች (Oral Traditions)

ከዓባይ በስተደቡብ ያለውን የታሪካችን ክፋይ ለማጥናት የጀርባ አጥንት ሆነው የሚያገለግሉን የቃል ትውፊቶች መሆናቸውን በቀደሙት ትንታኔዎች ከነውስንነታቸው ለማሳየት ሞክረናል። 'በቃል የተነገረ ይረሳል - የተፃፈ ይወረሣል' የሚለውን ብሂል ተሻግረው ሳይዘቡ በትውልድ ታሪክ ነጋሪዎች የተላለፉ የቃል ታሪኮች (Oral Historiography) ዳራ ውስጥ መኖኘት የሚችሉበት አቅም እምቅ ነው። በነጮቹ ዐይን በባእድ አምልኮ በተንሻፈፈ አረዳድ በጣኦት አምልኮ የተፈረጁ ሀገር በቀል የአንድ አምላክ አምልኮዎች (Monotheistic Religions) አጀብ በሚያሰኙ ታሪካዊ እውቀቶች ደምቀው ከፊት ለፊታችን አሉ። በደቡብ የሀገራችን ክፋይ የተገኙ የቃል ትውፊቶች በተለይ ከ14ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የነበሩ የታሪክ ውሎዎችን የማሳየት አቅማቸው እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው።

በመላው ኢትዮጵያውያን ተጋድሎ እና በምኒልክ መሪነት በቅኝ አገዛዝ ሥር ላለመውደቃችን ምስጋና ይሁንና ድንግል ታሪካችን፣ ቱባ ባህሎቻችን፣ ወግ እምነት እና ልምዳችን ህያው ሆኖ ቀጥሏል። በተለያዩ የትምህርት መስኮች 'አንትሮፖሎጂ' 'ካርቶሎጂ' 'ሶሲዮሎጂ' 'ቋንቋ' እና ተጓዳኝ ሥፍር ቁጥር የሌላቸው ጥናቶች በር ከፍቷል። በቅኝ ግዛት መዳፍ ስር ብናርፍ ኖሮ በፈረንሳይ፣ በጣሊያን፣ በብሪታንያ፣ በፖርቹጊዝ ሥር ወድቀን ቢሆን ኖሮ እንድም በሌላ ቋንቋ ተውጠን፣ ስማችን ተቀይሮ፣ ታሪካችንን ተነጥቀን ... ለመሆኑ ይህ ሁሉ በረከት ከየት ይገኝ ነበር? ልብ ልንለው የሚገባው ጉዳይ ዘመናዊ ትምህርት ለመላው አፍሪካውያን መዳረስ የጀመረው ድህረ 1960ዎቹ (ከቅኝ ግዛት በኋላ) ነው።

አወዛጋቢውን ጉዳይ ለምዕራፍ አራት አቆይተን የኢትዮጵያ ዘመናዊ ትምህርት አባት ዳግማዊ አጤ ምኒልክ በ1908 የመጀመሪያውን ትምህርት ቤት ከፍተው ዘመናዊ ታሪክ ለሀገር እስኪያቋድሱ ድረስ ከቤተ ክህነትና የመድረሳ ቅዱስ ቁርአን ትምህርት ቤቶች በስተቀር የፅሑፍ እውቀት አልነበረም። ከመላው አፍሪካ የራሷ ሆሄያት ያላት ብቸኛ ሀገርም ኢትዮጵያ በመሆኗ ለጥበበኞቹ ክብር ይሁን። ወላጆቻችን ባቆዩን አመስግነን ከዓባይ በስተደቡብ ያለውን የታሪክ ክፍል ያለመመዝገብ ሌላ መሠረታዊ ምክንያት እንመልከት።



t.me/OLDBOOKSPDF

ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ ስድስት ኪሎ የሚገኘውን ቤተ መንግሥታቸውን ለዩኒቨርሲቲነት ካበረከቱ በኋላ በ1963 የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ተመሥርቶ በሥሩ የታሪክ ትምህርት ክፍል ተወጠነ። በሒደት ታዋቂ የታሪክ ጠበብት የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በሀገር ውስጥ እየተማሩ ለሁለተኛ እና ሦስተኛ ዲግሪያቸው ወደ ውጭ ሀገር በመሄድ ትምህርታቸውን መከታተል ቀጠሉ። በዚህ ወርቃማ የእውቀት ሥጦታ መሠረት እና ከውጭ ሀገራት ጋር በተደረገ ጠንካራ ግንኙነት ፕሮፌሰሮች ዶክተሮችና ምሁራን በታሪካችን ላይ አሻራቸውን አሣረፉ።

'ኢሜሪተስ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ "Society, State and History" በተሰኘው ጠማሪቻቸው (ገፅ 1 - 20) በኢትዮጵያ የታሪክ ጥናት ዙሪያ በተለያየ መልክ እንደገለፁት ሪቻርድ ፓንክረስት፣ ዶናልድ ክረሚ፣ ካርል በረንትዜን፣ ስቬን ሩበንሰን፣ ዴቪድ ሃፕል የየድርሻቸውን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ አበርክተዋል። ከሀገር ውስጥ በተመሣሣይ መዘንጋት የሌለባቸው አለሜ እሸቴ፣ ባይሩ ታፍላ፣ ከነፈርግብ ዘለቀ፣ ፀሐይ ብርሀነሥላሴ፣ አብዱልሰመድ ሀጂ አህመድ፣ ሹመት ሲሻኝ፣ ዳንኤል አያና፣ ተሰማ ተዓ፣ ጉልማ ገመዳ፣ በንቲ ጌታሁን፣ ህዝቅኤል ገቢሣ፣ ጉብሩ ታረቀ፣ መሀመድ ሀሰን እና እያሌ ምሁራን የተለያዩ ጥናቶችን አካሂደዋል። (አንዳንዶቹ በዘውግ ፖለቲካ ተዘፍቀው አፍራሽ ሚና መጫወታቸው ሳይዘነጋ) ጥናቶቹ በአብዛኛው ታሪካዊ የጽሑፍ ማስረጃዎች ወደ ሚያገኙበት የሰሜኑ ኢትዮጵያ ክፍል ያመዘኑ ናቸው። በኢትዮጵያ የቃል ጥናት ታሪክ ላይ አፍራሽ አሉታዊ ተፅዕኖ ካሳደሩ ሁናቴዎች የአንበሳውን ድርሻ የሚወስደው የአውሮፓውያን የቃል ትውፊትን ያለመቀበል ዝንባሌ ነበር። በተጓዳኝ ለጥቁሮች ታሪክ የነበራቸው ዘረኛ አመለካከት የራሱን ጠባሳ አሳርፏል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ትምህርት ክፍል ሠራ ጥናትና ምርምር ያደረጉት ፕሮፌሰር ተሰማ ተዓ፡- "Issues in the Historiography of Africa" በተሰኘ ርዕስ ለንትመት ባበቁት መጽሐፍ ገፅ 6-7 እንዳመለከቱት ሊላው ቀርቶ የዘመናዊ ታሪክ ትምህርት ጥናት መሥራች የሚባለው ሊዎፖልድ ቮን ራንኬ ጭምር፦ "አፍሪካውያን ታሪክ የሌላቸው ህዝቦች ናቸው። ታሪክ መሥራት የሚችለው ነጩ የሰው ዘር ብቻ ነው። አፍሪካውያን ለሰው ልጅ ሥልጣኔ ምንም አይነት አስተዋጽኦ አላበረከቱም።" በማለት ሲያትት የብሪታንያው ታሪክ ተመራማሪ ትሬቨር ሮፐር በተመሣሣይ፡-



t.me/OLDBOOKSPDF

> *አፍሪካ ታሪክ አልባ ናት። ወደፊት ምናልባት ታሪክ ሊኖራት ይችል ይሆናል። ለጊዜው ግን ምንም ታሪክ የሌላት ናት፡፡ የጨለማ ዘመን ታሪኳም የታሪክ አካል ተደርጎ አይወሰድም። ምክንያቱም ታሪክ በዓላማ የሚከናወን እንቅስቃሴ እንጂ የደመ ነፍስ ጉዞ ምዝገባ አይደለም። የሆኑ ዘለኖች በአንድ ረብ የለሽ የዓለም ዳርቻ እንዳሉ ማሰብ በቂ ነው።*

የሚል ኢሳይንሳዊ ስሜቱን አጋርቷል።

በሌላ በኩል ታላቁ የጀርመን ፈላስፋ ሄግል አፍሪካን ሲገልፅ፦

> *አፍሪካን መርሳት ቢቻልም ደግመን ማንሣት የሌለብን የዓለም ታሪክ አካል ባለመሆኗ ብቻ ሳይሆን የምታሳየው መነቃቃትም ሆነ እድገት የሌላት በመሆኑ ነው። ... ከአፍሪካ የተረዳነው ታሪክ አልባ፣ ኋላ ቀር መንፈስ የተጠናወታት ደመ ነፍሳዊ መሆኗ ነው። ስሁንም የጠቀስናት በዓለም ታሪክ ውስጥ ውዳቂ መሆኗን ለማሳየት ነው።*

ይላል። ከዚሁ ጋር የተያያዘ አንድ ማስረጃ ለማከል ኤ. ፒ. ኒውተን ደግሞ፦

"አውሮፓውያን ወደ አህጉሪቱ ከመድረሳቸው በፊት አፍሪካ ታሪክ አልነበራትም" ማለቱ የፅሑፍ ክህሎት ያላዳበረች ከመሆኑ ጋር ተያያዥነት አለው። ጉዳዩ በዚህ ብቻ የሚቋጭ አይደለም። በርካታ አውሮፓውያን እጅግ በፅንፈኝነቱ የሚታወቀውን የቻርለስ ዳርዊንን የዝግመተ ለውጥ አስተምህሮ በማጠናከር የአፍሪካውያንን ታሪክ ዋጋ ለማሳጣት ተረባርበዋል።

ሐሩን ያህያ በተሰኘ የብዕር ስም በዓለማቀፍ ደረጃ ታዋቂ የምርምር ሥራዎችን ያበረከተው ሊቅ፦ "The Evolution Deceit" በተሰኘ የምርምር ሥራው የዳርዊን ሀሳብ እንደምን ባለ ሁኔታ ዘረኝነትን እንዳስፋፋ በገፅ 5 የሚከተለውን ጠቅሷል፦

> *ለመኖር የሚደረገው ትግል በሰው ዘርም መሀከል ይሠራል። በፍልሚያው ውስጥ የተመረጡ ዘሮች ድል ያደርጋሉ። ዳርዊን የተለዩ ዘሮች በማለት የሚገልፃቸው ነጭ አውሮፓውያንን ነው። እንደ ዳርዊን ከሆነ አፍሪካዊ እና እስያዊ ዝርያዎች በሚደረገው የማሸነፍ ትንቅንቅ ውስጥ ዘገምተኛ አካሄድ ይከተላሉ። በመሆኑም በስተመጨረሻ ይሸነፉ ሙሉ በሙሉ ይጠፋሉ።*



t.me/OLDBOOKSPDF

በማለት የነጮን ካውካሰይድ ዝርያ ኃያልነት፤ በተቃራኒው ቢጫው የሞንጎሎይድ እና ጥቁሩ የኔግሮይድ ዝርያዎች ደካማዎች መሆናቸውን የሚገልፅ ግልፅ ንቀት አሳድረዋል። በቻርለስ ዳርዊን አስተሳሰብም ሆነ እስካሁን የቀጠለው ነጭ ዘረኛ ምሁራን የተዛነፈ ዐተያይ በማህበራዊ ሳይንስ ቲምህርቶች የዘረኝነት አስተሳሰብ እንዲንሠራፋ ምክንያት ሆኗል። የሚያሳፍረው የኛ ሀገር የጎሣ ፖለቲከኞች በዝንጀሮ ደረጃ ዝቅ አድርገው በሚመለከቷቸው ነጮች ሀገር ሾተ፣ ሾር፣ ሲደላቸው ደግሞ ሽር ብትንብለው እየኖሩ፤ ለምፅዋት ደጅ እየጠኑ፤ ልጆቻቸውንና ቤተሰቦቻቸውን በነጮች መሀከል ሸጉጠው አፍሪካ ውስጥ ዳቦ ጠግቦ ያላደረ ምስኪን ወገናቸውን በፈጠራ ትርክት በማናከስ መጠመዳቸው ነው። ይህ "ታላቅ ሴራ" በሀገር ደኅንነት እና በሕዝቦች አብሮነት ላይ የተነጣጠረ ጠላትነት ነውና በየምዕራፉ መዋጋት ግድ ይለናል።

በ1960ዎቹ መጀመሪያ በርካታ የአፍሪካ ሀገሮች ከቅኝ ግዛት መንጋጋ መላቀቃቸውና 'ነፃነቷን' ተከትሎ በሂደት አውሮፓውያን የአፍሪካን ህልውና እና ታሪክ መቀበል ጀመሩ። 'የአፍሪካን ነፃነት' ተከትሎ አዲስ የበቀለው የአስተሳሰብ ለውጥ አውሮፓውያን ጭምር የቃል ትውፊትን የታሪክ አካል አድርገው መቀበላቸውን እና በተመሣሣይ ወቅት "የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም" በ"ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ" መከፈቱን ተከትሎ ከዓባይ በስተደቡብ ላለው የሀገራችን ታሪክ ጥናት አይነተኛ የዕይታ ለውጥ አስገኘ።

አስቸጋሪው ነገር የታሪክ አጥኚዎቹ የቃል መረጃዎችን እንዳለ ከመቀበል ይልቅ መረጃ ሰጪ አዛውንትን በማባበያ እየጠመዘዙና እንዳሻቸው ያለማረጋገጫ "የበደል ታሪኮችን መፈልሰፍን" ሥራዬ ብለው ለፖለቲካ ፍላጎት ማዋላቸው ነው። በመሆኑም በተዛባ ታሪክ (አስቀድሞ ሊደረስበት የተፈለገ ድምዳሜ) ላይ ተመርኩዘው የተደረሱ ስንከሳሮች በታሪክ አውድ ውስጥ ለመደርደሪያ ፍጆታ ቢውሉም በታሪክ ውስጥ ከመካተታቸው በፊት ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ያስፈልጋል። የሀሰት ምንጮችን እየተቀባበሉ በመድረስ እውነት ለማሥመሥል የሚሰራው ደባ በእንጭጩ ሊቀጭ ይገባል።

በግልፅ እንደሚታወቀው የብሔረሰብ ታሪክ ጥናትና ምርምር የሚያደርጉ ወገኖች መነሻቸውን ከነርሱ ቀድመው በተዘጋጁ የዘውግ ታሪክ ፅሑፎች እና 'ማርክሲስት' አመለካከት ያጠቃቸው ሰነዶች ስላደረጉ አንዳንዶቹ ፈልገውት፤ ሌሎቹ ያላመኑበትን ጭምር እንደሚከትቡ ከሥራዎቻቸው ተነስቶ መደምደም ይቻላል። 'በሠፊው የታሪክ መስታወት እንከንን በመመልከት ጉድፉን ከማንሳት' ይልቅ በመደቡ ላይ ጭረትና



t.me/OLDBOOKSPDF

ሰንጥቆ ወደ መፈለግ ቀንጨራ ሀሳብ ማማገር መገለጫቸው ሆነ። የታሪክ እጅግ የበዙ መልካም ገፆች እንዲሸፈኑ እና እንከን የተባሉት እየተጋነኑ ለጥላቻ ማራጋቢያ እንዲያገለግሉ በመሠራት፣ ተበደልሁ ያለው ወገን በዳዩን ፊት ለፊት፣ ላያገኝ የማይመለከተውን የብሔረሰብ አባል፦ ገበሬ፣ መምህር፣ ሀኪም፣ የግብርና ባለሙያ፣ ነጋዴ፣ ሾፌር፣ የመከላከያ ባልደረባ፣ እናጢ፣ ሸማኔ፣ ሎተሪ አዟሪ፣ የፐብሊክ ሰርቪስ ባለሙያ፣ የቀይ መስቀል ባልደረባ … ወገኑን በደረናው መጥላቱ የአደባባይ ምስጢር ሆነ።

በአንዳንድ የፖለቲካ ፍላጎት የተቃኙ የታሪክ ጥናቶች ውስጥ ከገበሬው ተወሰዱ የተባሉ መሬቶች ሲደመሩ አስደንጋጭ ሥዕል ይሰጡናል። አንድ ወረዳ ላይ በባላባቶች ተወሰዱ የተባሉ ሄክታሮች ጥናቱ ከተካሄደበት ዞን አልፎ የክልሉን ያህል ይሰፋሉ። በአንድ ቀበሌ በተደረገ ግጭት ሞተ የተባለው ሰው ዜሮ በዘፈቀደ ከፊት ተደርድሮ ዛሬ በብዙ ዞኖች ካለው ህዝብ ይበልጣል። ተበድረንም ቁጥሩን ማሟላት አንችልም። እንደዚህ በግነት እና ውሸት የታጀሉ ፅሑፎችን ለታሪክ ፍጆታ ከማዋል በፊት ብርቱ ጥንቃቄ መደረግ አለበት። ጃን ቫንሲና፦ "Oral Traditions as History" በሚለው መፅሐፋቸው ትውፊቶች በታሪክ ውስጥ መካተታቸው በጣም አስፈላጊ መሆኑን በአሳማኝና ማራኪ አቀራረብ ተንትነው አስረድተዋል። ሆኖም ታሪኮቹ ከተፋለሱ አደገኛ ስለሚሆኑ የበዛ ጥንቃቄ ይፈልጋሉ።

ሲጠቃለል የታሪክ ሙያ ራሱን የቻለ ከቡር የትምህርት ዘርፍ እንደመሆኑ የኢትዮጵያ ታሪክ በባለሙያዎቹ ምሁራን መዘጋጀት እንዳለበት የሚታመን ሆኖ ሳለ (የመፅሐፉ አዘጋጅ በዚህ ዙሪያ የሀሳብ ተአቅቦ ይዟል። ምክንያቱም የሚዘጋጀው ታሪክ በተለያዩ አቅጣጫዎች በስነልቡና ህግ ማህበራዊ ሳይንሶች እና ሌሎች ምሁራን ከሚያስከትለው ተጓዳኝ ተፅዕኖ አኳያ ቢመዘን የተሻለ ይሆናል የሚል ፅኑ እምነት አለውና።) ቆርጦ በመቀጠል የሚዘጋጅ ታሪክ የአብሮነት ነቀርሣ ነው።



t.me/OLDBOOKSPDF

## አርኪዎሎጂ በኢትዮጵያ ታሪክ (Archaeology)

በታሪክ ትምህርት አጠናን እንደ ማዕዘን ድንጋይ ከሚያገለግሉ የጥቡብ ዘርፎች አንዱ 'አርኪዎሎጂ' ነው። የሰው ልጅንና ቅድመ ዝርያዎቹን፣ የተጠቀመባቸውን የተግባር መገልገያ መሣሪያዎችን፣ ቅሪተ አካሎችን እና አፅሞችን በቁፋሮ በማውጣት የሚያጠና ዘርፍ እንደመሆኑ ያ'አርኪዎሎጂስቶችን' የምርምር ውጤቶች ታሪክን በማዘጋጀት ሂደት አብዝቶ ይጠቅማል። የአርኪዎሎጂ ጥናት በዋናነት የፅሑፍ ጥቡብ ከመዳበሩ በፊት (ቅድመ ታሪክ) የሰው ልጅ አኗኗር ምን መልክ እንደነበረው ጉልህ አስረጂ ነው።

የኢትዮጵያንና የዓለምን ታሪክ ለማጥናት በማሰብ የተካሄዱ የአርኪዎሎጂ ምርምር ሥራዎች አመርቂ ፍሬ አፍርተዋል። ከአርኪዎሎጂስቶች (የቅሪተ አካላት ጠበብቶች) በተገኙ የጥናት ውጤቶች መሠረት ኢትዮጵያ የሰው ልጅ መሠረተ ግንድ "ምድረ ቀደምት" መሆኗን የሚያረጋግጡ ግኝቶች ይፋ ሆነዋል። በየጊዜው ከዜናዎች ከምናደምጣቸው መረጃዎች እና ከድረገፆች ከምንበረብራቸው መረጃዎች በመነሳት ብዙዎቻችን አርኪዎሎጂ በኢትዮጵያ ዘለግ ያለ እድሜ ያስቆጠረ እንደሆነ ይገምታሉ። በተጨባጭ መሬት ላይ ያለው ሀቅ የሚያሳው እውነታ ግን ከሚታሰበው የተለየ ነው።

ፕሮፌሰር ሥርግው ኃብለሥላሴ (በመነሻው በተጠቀሰው ጥናታቸው ከገፅ 9-10) እንደገለፁልን አርኪዎሎጂ በኢትዮጵያ ያለው ንጥር እድሜ ጨቅላና ከግማሽ ክፍለ ዘመን ብዙም ፈቀቅ ያለ አይደለም። በ19ኛው ክፍለ ዘመን ማብቂያ አካባቢ ሄንሪ ሳልት በግሉ ለአርኪዎሎጂ ጥናት ባላደረው ፍላጎት የተመለከታቸውን የድንጋይ ላይ ፅሑፎች በአንክሮ ለመገልበጥ ሞክሯል። በተመሳሳይ ሁኔታ ቴዎዶር ቤንት አክሱም አዱሊስ የሀ እና ኮሀይቶ (ኮሎኤ) በተባሉ ሥፍራዎች የአራት ወራት ቆይታ ባደረገበት ወቅት በሳቢያን ግሪክና ግዕዝ ቋንቋዎች የተቀረፁ የድንጋይ ላይ ፅሑፎችንና ሌሎች ታሪካዊ ቅርሶችን በትኩረት መገልበጧቸዋል።

በ1906 የጀርመኑ ቄሣር ዳግማዊ ዊልያም የተለያዩ ቅርሶችን ለማሰባሰብ በነበረው ፍላጎት በኢ. ሊትማን መሪነት የአርኪዎሎጂ ጥናት ምርምር ቡድን ወደ ኢትዮጵያ ላከ። የልዑካን ቡድኑ ለሦስት ወራት ጥልቀት ያለው ፍተሻ አድርጎ ወደ ጀርመን ከተመለሠ በኋላ ለስድስት ዓመታት ዝግጅት አድርጎ በአይነቱ ለየት ያለ ዘገባ አሰናዳ። መረጃው በአራት ጥራዞች የተደጎሰ ነው። የመጀመሪያው ስለ ጉዞቸው፣ መልክዓ ምድርና የአክሱም ታሪክ ያወሳል። ሁለተኛው ጥራዝ ስለ ጥንት ኪነህንፃችን ለተጻ



t.me/OLDBOOKSPDF

አቅርቧል። ሶስተኛው ሰነድ ስለ ጥንታዊቷና ዘመነኛዋ ኢትዮጵያ ቁሳዊ ሀብትና የግንባታ ሥራ ዘገባ ያቀረበ ነበር። አራተኛው ሥራ በሳባውያን ግዕዝና ግሪክ ቋንቋ የተፃፉ የድንጋይ ላይ ፅሑፎችን ትርጓሜ ከአስተያየት ጋር አኑሯል።

በ1907 የጣሊያን መንግሥት በበርካታ ሰነዶች ስለ ጥልቀቱና ርቀቱ የተነገረለትን የአዱሊስ ሐውልት ለማግኘት የሚያስችል ቁፋሮ እንዲካሄድ ለጣሊያን አርኪዎሎጂስቶች ትእዛዝ አስተላለፈ። ቁፋሮው ሲጠናቀቅ በእቅዱ ላይ የተገለፀውን የአዱሊስን ሐውልት ማግኘት ባይቻልም አግረ መንገዱን ለታሪክ ፅሑፋችን ጠቃሚ የሆኑ ሳንቲሞች፣ ቢቶች፣ የተለያዩ ሰነዶች እና ቁሳቁሶች ተገኝተዋል። እዚህ ላይ ሊያስቆጨን የሚገባው ጉዳይ ጠንካራ አቅም ብናደረጅ በሥፍራው በጥናት ላይ የተመሠረተ ጥልቅ ቁፋሮ በማድረግ ዓለም እጁን አፉ ላይ እንዲጭን የሚያደርጉ ቅርሶች ማግኘት ስንችል አለመቻላችን ነው።

የተቀበረ ጥበብ አውጥተን መግለፅ ቢሳነን እንኳ ለወገኖቻችን ጉድጓድ ከመቆፈር ብንላቀቅ ታላቅ የሀሊና ጠገግ ነው። ከተባበርን እንኳን ሚሊየኖች ሆነን 'በትንሽ ማገሻ ትልቅ ሜዳ ይታረሳል'። በሌላ በኩል ከፈረንሳይ መንግሥት በተገኘ ድጎማ ሁለት የፈረንሳይ መነኮሳት አዛይስና ቻምባርድ በምሥራቃዊና ደቡባዊ ኢትዮጵያ ከፍሎች ያደረጉት ጥናት ስለ ኢትዮጵያ ቅድመ ታሪክ ለማወቅ ከፍተኛ ድርሻ አለው። በማዕከልና በአራቱም ማዕዘናት የሚደረገውን የኢትዮጵያን ታሪክ በምልዐት የመፃፍ ሒደት የውስጥን አቅም አሟጥጦ መጠቀምና በሠፊ ምልከታ ርቀን መጓዝ እንችላለን።

በሀገራችን ካሉብን አንኳር ችግሮች አንዱ ጊዜ ጉልበት ሀብትና አእምሮን አስተሳስሮ ለላቀ ለውጥ ከመሥራት ይልቅ ለሴራ ፖለቲካ የበለጠ ቦታ መሠጠቱ ነው። አርኪዎሎጂን በተመለከተ በተናጠል ከተደረጉ ከላይ የተዘረዘሩ ጥቂት ጥረቶች ውጪ እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን ሁለተኛ አጋማሽ አርኪዎሎጂ ተቋማዊ ቅርፅ አልያዘም ነበር። በ1952 ከፈረንሳይ መንግሥት ጋር በተደረገ ስምምነት የአገሪቱን ቅርሶች ማጥናትን ዓላማ አድርጎ የአርኪዎሎጂ ምርምር ተቋም እውን ሆነ። በአርኪዎሎጂ ጥናት የተገኙ የምርምር ውጤቶች፡- "Annales d' Ethiopia" መፅሔት ላይ ታትመው ይፋ ሆነዋል።

### የኢትዮጵያ ታሪክ በውጭ ጸሐፍት ዐይን

የኢትዮጵያን ታሪክ በተሻለ መንገድ ለማዘጋጀት የውጭ ፀሐፍት ሥራዎች ትልቅ ድርሻ አላቸው። ከጥንት ጀምሮ በርካታ ምዕራባውያን፣ የመሀከለኛው ምስራቅ፣ የሩቅ



t.me/OLDBOOKSPDF

ምስራቅ፣ የቅርብ ምሥራቅ እንዲሁም ከመላው ዓለም ኢትዮጵያን ለተለያዩ ዓላማዎች የጎበኙ ተጓዦች፣ አሳሾች፣ ነጋዴዎች፣ የእምነት ሰዎች፣ ጠረኞች፣ ተመራማሪዎች እና የተለያዩ ግለሰቦች ሀገራችንን ለመቃኘት እድል አግኝተዋል። ከመሀከላቸው ጥቂቶቹ በጉዟቸው የተመለከቱትን፣ ከግለሰቦች በመጠየቅ የተረዱትን፣ መረጃዎችንና ማስረጃዎችን በማገላበጥ የበረበሩትን ለበጎም ሆነ ለክፉ ዓላማ ተጠቅመውበታል። ከማህበረሰቡ ጋር በመኖርና በመሣሠሉት መንገዶች የታዘቧቸውን በማስፈራቸው ታሪክ የሆኑና ለታሪክ ምንጭነት የሚረዱ አያሌ ጠማሮች አበርክተውልናል። ሥራዎቹ እስከወለዳቸው የቴክኖሎጂ ውጤቶች ድረስ ይዘረጋሉ። ዘመኑ

ከእነዚህም መሀከል ከተለያዩ ማስታወሻዎች ከተሰበሰቡት መሀከል በግልፅ የሚታወቁትንና ፀሐፍት የተቀባበሏቸውን እንደሚከተለው አስናድተናል። የጥንቱ ግሪክ ፀሐፊ ሆሜር ሁለት ታዋቂ ፅሑፎችን "ኢሊያድ" እና "ኦዲሴይ" የተባሉ ፅሑፎችን አበርክቷል። ቀዳሚው ፅሑፍ ግሪኮች ያደረጉትን ጦርነት ሲገልፅ፣ ኦዲሴይ ደግሞ ኦዲሲየስ ስለተባለው የጦር ሜዳ ጀግና እና መሪ የሚገልፅ ነው። በፅሑፎቹ ውስጥ ስለ ኢትዮጵያ ጥንታዊነት ቢገለፅም "ኢትዮጵያ" የሚለው ስም ምንጭ ግሪኮች እንደሆኑና የትመጣው "aitho" (I burn) እና "ops" (face) "የተቃጠለ /የጠቆረ ፊት ያላቸው" ከሚለው ነው የሚለው ትርክት ውህ እንደማያነሳ አያይዞ መደምደም አስፈለገን።

ፋዘር ማርሻል ደ ስላቪክ፡- "An Ancient People In the State of Menelik, The Oromo (said to be of Gallic Origlin" በተሰኘው መፅሐፋቸው ገፅ 31 ላይ 'ምንም እንኳ የቃሉ መነሻ ግሪክ ነው የሚሉ ቢኖሩም ሌሎች ኢትዮጵያ የሚለው ቃል ከግሪኮች የሚቀድም እንደሆነ ይናገራሉ። "..., but others believe that this word 'aitho - ops') precedes Greek"

መረጃቸውን በመቀጠል፡- "... such as the land of Ethiopia which the apostle Saint Matthew evangelized, and the one of the eunuch of the Queen of Candace, baptized by the deacon Saint Philip."

በማለት ያትታሉ።



t.me/OLDBOOKSPDF

በርግጥ ስለ ኢትዮጵያ ግሪኮች ከዚህ ቀደም ብሎ በሆሜር ጽሑፍ መዝሙር 423 "የግሪክ አማልክቶች ንጉሥ የሆነው ዜውስ ኃያል እና ብርቱ የሆኑ ኢትዮጵያውያንን ለማየትና ገበታ ላይ አብሯቸው ለመሳተፍ ወደ ታላቁ ወንዝ ይወርዳል" ሲል ገልጿል። (ጥንት ግሪኮች ዜውስ የተባለው የጣዖቶቻቸው ንጉሥ ሌሎች አማልክትን አስከትሎ በኦሎምፒስ ተራራ ጫፍ ባለው ደመና ይረብባል ብለው ስለሚያስቡ፤ ለጣዖቱ ክብር ሲባል በአራት ዓመት አንድ ጊዜ በተለያዩ ውድድሮች ይዘከሩት ነበር። የኦሎምፒክ ውድድር ይህንን መሠረት አድርጎ እንደተጀመረ ይነገራል።) የታሪክ አባት የሚባለው ሄሮዶተስም "ኢትዮጵያውያን ውብና ቆንጆዎች ናቸው።" በሚል ይገልፃቸዋል።

ይሁንና በጥንታዊ ጥበብ የረቀቁት ኢትዮጵያውያን የዳቦ ስም ለሀገራቸው ከውጪ የማይዋሱ ከመሆኑም ሌላ የቃሉን መገኛ "በመፅሐፈ አብርሂት" ውስጥ እንደሚከተለው አኑረውታል። ይኸውም፦ ኢት" ማለት "ሥጦታ" የሚል ትርጉምና "ዮጵ" ብርሀናማ (ቢጫ ቀለም ያለው) ወርቅ 'የጣታችንን ወይም የፀጉር ወርቅ አንመልከት' "ዮጵ" አልማዝ ወይም ዕንቁ የሚል ትርጉምም ይይዛል። ጥቁረት ውበት ቢሆንም ግሪኮች ያገኟቸው የነበሩ ሀበሻት ኢትዮጵያውያን ቀለማቸው 'የተቃጠለ ፊት' የሚመስል እንዳልነበር ማስተንተን አያስቸግርም።

በ1ኛው ክፍለ ዘመን ያልታወቀ የግሪክ መርከብ ካፒቴን፦ "The Periplus of the Erythrean Sea" በተሰኘ ርዕስ የሰነደው መፅሐፈ እድ በኢትዮጵያ ታሪክ ጥናት ውስጥ ሌላው ዐይን ገላጭ ሥራ ነው። በ60 ዓ.ም የአክሱም ንጉሥ የነበረው ዞስካለስ ግሪክኛ ቋንቋን አቀላጥፎ ይናገር እንደነበር፤ አዱሊስ ዋነኛ ወደብ እና ከተማ እንደነበረች፤ ስለንግድ ልውውጡ፤ የእንስሳትና ዕፅዋት ስብጥር፤ የጀልባ ሥራ እድገት እና መሠል ዳራዎችን አፍታትቶ ዕፏል። በወቅቱ ግሪክኛ የምሥራቅ ሜዲትራንያን አካባቢ አፍ እንደነበር ሲዳሰስ የውጭ ግንኙነት ታሪካችንን በማዳበር የላቀ ሚና ይኖረዋል።

የውጪ ፀሐፍት ከሚደነቁበት ከሀሎት አንዱ የሚመለከቷቸውን ሁነቶች ዕፅዋትና እንስሳት ጭምር መመዝገባቸው ነው። ከዚሁ ጋር ኢትዮጵያ በዘመናት ታሪኳ ውስጥ የሚገበኙ እና ለታሪካዊ ቱሪዝም የሚያገለግሉ በሌላው ዓለም የማይገኙ በማህፀኗ ብቻ የታቀፉትን እንመልከት (30 አይነት ጡት አጥቢዎች፣ 16 የዕፅዋት ዝርያዎች፣ 10 ተሳቢና ተራማጅ እንስሳት፣ 30 አይነት የውሀና የየብስ እንስሳት፣ 42 አይነት የአሣ ዝርያዎች ይገኛሉ። በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ የሚገኙ ታላላቅ አጥቢ የዱር እንስሳት



t.me/OLDBOOKSPDF

(የምኒልክ ድኩላ፣ የስዌን ቆርኪ፣ ቀይ ቀበሮ፣ ኒያላ፣ ዋልያ እና ጭላዳ ዝንጀሮ) ናቸው።

በ5ኛው ክፍለ ዘመን የላቲን ክርስትና ፀሐፊ የሆነው ሩፊነስ፡- "Historia Ecclesistica" በተሠኘ ሥራው በኢትዮጵያ ውስጥ የክርስትናን አመጣጥ አስመልክቶ መጠነኛ ሐተታ አሰናድቷል። ሌላው የክርስትና ሀይማኖት ግሪካዊ ፀሐፊ ኮስሞስ ኢንዲኮፕለስቲዩስ፡- "The Christian Topography" በሚል ርዕስ በወቅቱ የተረዳውን እንቅስቃሴ ሰንዶ አኑሯል። የአረብ ታሪክ ፀሐፊ የነበረው ኢብን ሀውቃል በ10ኛው ክፍለ ዘመን እንደነበረች ስለሚነገረው የአገው ንግሥት ዮዲት ፅፏል። ምክንያቱ ግልፅ ባይሆንም መረዋን 'ባኑ አልሀምዊያህ' የሚል ስያሜ ሰጥቷታል። ይህቺንው ንግሥት የጣሊያኑ ታሪክ ፀሐፊ ካርሎ ኮንቲ ሮሲኒ 'ባኑ አልዳሙታ ማለቱ ምናልባት ከዳሞት ሊሆን ይችላል የሚሉ አልታጡም። የኢትዮጵያ ፀሐፍት 'ጉዲት' በሚል የቅጥል ስም ሰይመዋታል። 'ጉደኛ' ከቃሉ የትመጣ አንፃር ጉድ መአት የፈጠረች እንደማለት ሲሆን 'እሳቶ/ እሳቷ' የሚሏትም አልጠፉም። ይህም አብያተ ክርስቲያናትን ከማቃጠሏ ጋር የተያያዘ እንደሆነ ተወስቷል።

ልብ ልንለው የሚገባው ጉዳይ በአራቱም የኢትዮጵያ ማዕዘናት ሀይለኛ የነበረች ጨካኝ ያለች ንግሥት አፈ ታሪክ መስማት ያልተለመደ አይደለም። ለምሳሌ፡- ከአዲስ አበባ በስተደቡብ 600 ኪሎ ሜትሮች ርቀት ላይ ቦረና አካባቢ 'አኮ መኖዬ' ስለምትባል ሀይለኛ እንስት አፈ ታሪክ ይነገራል። በስፍራው ከ27 ዓመታት በላይ በሚሲዮናዊ አገልግሎት የቆየው ቶን ሌዊስ፡- "Aadaa Boraanaa" በሚል ርዕስ ባዘጋጀው በሠፊ ማብራሪያ የተደገፈ መፅሐፉ ገፅ 27 ላይ 'አኮ መኖዬ የምትባል አስተዋይ እንደነበረች እና ጎሽ ስለመግደሏ እናቷን ቅቤ እየተቀባች ወንዶች ላይ በማላገጧ ምክንያት ትጠላ እንደነበር በዚሁም ምክንያት ወንዶች ተሰባስበው ታላቅ ገደል እንደቆፈሩ እና ላዩን በአፈር እንደሸፈኑ፣ በጠራችው ስብሰባ በጉድጓዱ ላይ የተለየ ወንበር አስቀምጠው ጉድጓድ ውስጥ ገብታ እንደሞተች' የሰማውን አፈ ታሪክ ጠቅሶ ከትቧል። ቶን ሌዊስ አይጥቀሰው እንጂ በስፍራው ባለ አንድ ትልቅ ጉድጓድ በስፍራው የሚያልፍ ሁሉ ለዘመናት ድንጋይና ጠጠር እየተጣለ እስካሁን አለመሙላቱን ዛሬም ላይ ማየት ይቻላል። በሲዳማ አካባቢም ስለ ንግሥት ፉራ ይነገራል።



t.me/OLDBOOKSPDF

የዚህ ተመሳሳይ አፈ ታሪክ እና የዮዲት እውነታ በየስፍራው መነገር ወሬ እየተዛመተ የፈጠረው ምናባዊ ሥዕል ወይስ አንዳች የኢትዮጵያውያን መተማሠሪያ ምስጢር ይኖረው ይሆን? በ16ኛው ክፍለ ዘመን በአፄ ልብነ ድንግልና ኢማም አህመድ ኢብራሂም መሀከል ስለተደረገው ጦርነት የዐይን ምስክርነቱን፦"ፉቱህ አል ሀበሽ" በሚለው ጦማሩ ካበረከተልን የሺሀብ አዲን ሥራም በርካታ ቁም ነገሮችን የምናገኝ ስለመሆኑ በቀደመው ክፍል ታትቷል።

## የኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ አጻጻፍ አጀማመር

ከ1624 - 1706 የኖረው ጀርመናዊው ጆብ ሉዶልፍ "የኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ አባት/ ወጣኒ" ስለመሆኑ በታሪክ ትምህርት ምሁራን ዘንድ ተደንግጓል። የሚያስደንቀው ነገር ሉዶልፍ የኢትዮጵያን ዘመናዊ ታሪክ ሲፅፍ ሀገሪቱን በአካል አንድም ጊዜ ዐይቷት የማያውቅ መሆኑ ነው። ከኢትዮጵያ ወደ ጀርመን ከተጓዘች ኢትዮጵያዊ መምህሩ አባ ግሪጎሪ እየጠየቀ ያዘጋጀው የኢትዮጵያ ታሪክ በአይነቱ ለየት ያለ በመሆኑ የኢትዮጵያ ታሪክ አፃፃፍ በተነሳ ቁጥር ተጠቃሽ ያደርገዋል።

ከ1823 - 1894 የምድር ቆይታውን በክብር የሸኘው ሌላው ጀርመናዊ አገስት ዲልማን ከሉዶልፍ ይልቅ እጅግ ዘመናዊ በሆነ አግባብ ከድንቅ ትንታኔ ጋር የኢትዮጵያን ታሪክ ከሽኖ ፅፎታል። ፅሑፉ በዘመናቱ ከሁለት መቶ ዓመታት የሰፋ ልዩነት ጋር ተያይዞ ከቀደመው አምሳያው በረቀቀ መልክ ሳይንስና ጥበብ በእጅጉ ተዋህደው የታዩበት ነው። ከዚህ አኳያ በታሪክ ትምህርት ክፍል ምሁራን "የኢትዮጵያ ታሪክ ሳይንሳዊ አፃፃፍ ዘዴ አባት" የተሰኘ የክብር ካባ ተጎናፅፏል። ከአገስት ዲልማን በኋላ የኢትዮጵያን ታሪክ የመፃፉ ሥራ ወደ ሌሎችም የአውሮፓ ሀገሮች መሥፋት ችሏል።

ከ1810 - 1898 ህይወቱን በዋዘ ያላሳለፈው ፈረንሳዊ ምሁር አንቶኒዮ ዲ አባዲ ከወንድሙ አርናውድ ጋር ለረጅም ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሳለፈ ከመሆኑ ጋር ራሱን ለኢትዮጵያ ታሪክ ጥናት አሳልፎ የሰጠ ነበር ቢባል ይመጥነዋል። በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች በአጠቃላይ እና በኢትዮጵያ ታሪክ ዙሪያ በተለይ ያሰባሰባቸውና ያደራጃቸው ሰነዶች በ"Bibliotheque Nationale" ፓሪስ ውስጥ ይገኛሉ።



t.me/OLDBOOKSPDF

በሌላ በኩል ከዚህ ቀደም ባለው ክፍል ከጠቀስናቸው ፀሐፍት በተጨማሪ ጄ. ማሪዬ፣ ኤ..ካማረር፣ ካርሎ ኮንቲ ሮሲኒ፣ ኢ.ኤ. ዋሊስ ባጅ፣ ጄ. ቢ. ኮልቢያንስ የበኩላቸውን አበርክቶ አድርገዋል። የፖለቲካ ሳይንስ ልሂቃኑ ጆን ማርካኪስ፣ ክሪስቶፈር ክላፕሀም እና ሪቻርድ ግሪን ፊልድ፤ አንትሮፖሎጂስቱ ኸርበርት ሌዊስ፣ ጋዜጠኞች ፒ. ጊሊክስ እና ጂ ዱጋን ላፎሬ፣ኢታሚያዊ ኤም ፔርሀም እና ሲ. ፕራውቲ ሮዘንፊልድ ለበርካታ ፅሑፎች የማጣቀሻ ምንጮች ሆነው እስካሁን’ንም እያገለገሉ ይገኛሉ። በመሆኑም ለኢትዮጵያ ታሪክ ምጥቀት ካበረከቱት አስተዋፅኦ አንፃር ከበሬታ ሊቸራቸው ይገባል።

ይሁንና አብዛኞቹ ሥራዎች ከዓባይ በስተሰሜን ባለው የታሪካችን ክፋይ ላይ የተንጠለጠሉ ናቸው። ጥቂት ጥናቶች በደቡቡ የሀገራችን ክፍል ላይ ከመጻፍ ያልበዙ ቢሆንም በቂ ነው ለማለት ግን አያስደፍርም። በዝርዝር ለመመልከት እንደቻልነው ሥራዎቹ ወደ ሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ያጋደሉት የዘውግ ታሪክ ልሂቃን በመቆዘም እንደሚያነሱት በሰሜኑ አስተዳደር በተደረገባቸው ጫና አለመሆኑን የዘረዘርናቸው እውነታዎች ዋቢ ሆነው በአመክንዮ ያሳዩናል።

የአርኪዎሎጂ ምርምር ሥራ አፋር ላይ መመሥረቱ የምስራቅ አፍሪካ ስምጥ ሸለቆ በባህርይው (Sedimentary Rock) የተባለው የአለት አይነት የበዛበት ከመሆኑ ጋር አፅሞች ሳይበላሹ ለረጂም ጊዜ ከማቆየቱ አኳያ ለጥናት አመቺ በመሆኑ ነው። በተመሳሳይ በሰሜኑ ክፍል ከጥንት ጀምሮ ከጂኦግራፊያዊ አቀማመጡ አንፃር ለውጭው ዓለም መቅረቡ፣ ከክርስትና መምጣት ጋር ተያይዞ የዘርፉ ታሪክ ፀሐፊዎቹ ፍላጎት ማሣደር፣ ከድንጋይ ላይ ፅሑፎች ጀምሮ የፅሑፍ ሥራ የበለፀገ መሆን፤ የኪነ ሕንፃ እና የእደ ጥበብ ውጤቶች በእጅጉ ዳብሮ መገኘት፤ የአውሮፓውያን ትውፊቶችን የማገናኘት አባዜና ሌሎች ተዳምረው የተፈጠረ ክፍተት ስለመሆኑ አያከራክርም። 'ከዓባይ በስተደቡብ ያለው ታሪክ ያለመፃፉ ምክንያት በሰሜኑ ነገሥታት ጫና ነው' ከተባለ ከግብፅ ጋና ዚምባብዌ እና ጥቂት ሥልጣኔዎች በስተቀር የአፍሪካ ታሪክ (ኬንያ ሶማሊያ ታንዛኒያ ቡሩንዲ እና ሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች ትላንት) እንዳይፃፍ ያገዱትስ 'የአቢሲኒያ መሪዎች ናቸው'? ብለን ሀሳቡ ራሱ የጥላቻ በመሆኑ ጨው እንደበዛበት ምግብ እየጎፈነነን እናልፈዋለን።

ወጣም ወረደ ያለፈውን ዘመን ታሪክ መልሰን እንኖረውም። በእኛ ፍላጎት ላይ ተመሥርተን ልናስተካክለው አንችልም። የሰው ልጅ እንደኖረባቸው ከሚገመተው ዘመን ውስጥ 99.9 እጅን ያሳለፈው በፍራፍሬ ለቀማ እና አደን (የስብአ ትካት አኗኗር ዘይቤ) ነው። በጊዜ ሂደት ድንጋይና ድንጋይን ሲያጋጭ የእሳትን ብልጭታ፤ እንጨትና



t.me/OLDBOOKSPDF

እንጨትን ሲያፋጭ የብርሀንን ቦግታ እያስተዋለ የድንጋይ፣ የእንጨት፣ የነሀስ የብር እና የብረት ዘመንን መሸጋገር ቀጠለ። በዚህ ዘመን የመንግሥት እና የህገ ፅንሠ ሀሳብ ወደ ሀሊናችን ሊመጡ አይችሉም። ሰው አኗኗሩ ከእንስሳት ብዙ የራቀ አልነበረም። ቋንቋን ሳይቀር በሂደት እንዳዳበረ የቋንቋ ምሁራን (Linguists) ያስረዱናል።

በመቀጠል የተከሰተው የታሪክ ዘመን የባሪያ አሳዳሪው ስርአት ነው። በዚህ ሥርአተ ማህበር ባሪያዎች ሳይከፈላቸው የሚሠሩ፣ እንደ ተናጋሪ እንስሳ የሚቆጠሩ፣ እንደ ሸቀጥ የሚሸጡና የሚለወጡ፣ እንደ ግብፅ ባሉ ሀገሮች ደግሞ ንጉሥች (ፈርዖኖች) ሲሞቱ "ከሞት በኋላ ባለው ህይወት" እንዲያገለግሏቸው ታስበ ከነህይወታቸው አብረው ይቀበሩ ነበር። በ"ታላቋ" ሰሜን አሜሪካ ውስጥ ባርነት እስከ 1865 በደቡብ የሀገሪቱ ክፍል እንደ ሥርአት መቀጠሉን እንደ ዋቢ መጥቀስ ይቻላል።

ለዓላማችን ደጋግመን እንዳነሳነው 16ኛው የአሜሪካ ፕሬዚደንት አብርሀም ሊንከን ያወጣውን የነፃነት አዋጅ (1863) - "Edict of Emancipation" ተከትሎ ጦርነቱ ሲጠናቀቅ 1865 ቁራሽ መሬት ተሰጥቷቸዋል። ይህም ቢሆን በ1863 የተደነገገውን "Homestead Law" ተከትሎ ነው። ይሁንና ጥቁሮች ከነጮች ጋር አንድ ክፍል አብረው መማር የጀመሩት በ1960ዎቹ የመጀመሪያ አጋማሽ ጆን ኤፍ. ኬኔዲ በወሰደው እርምጃ ነው። አብርሀም ሊንከን እና ኬኔዲ ህይወታቸውን ያጡት በዚሁ ሳቢያ በነጭ ዘረኞች መሆኑ አይዘነጋም። በተለይ አብርሀም ሊንከንን ከዋሺንግተን ዲሲ ፎርድ ቲያትር ቤት ሲወጣ ፊት ለፊት ጥይት ተኩሶ የገደለው ጆን ዊልከስ በግዝ ነጭ ዘረኛ በተቀነባበረ ሁኔታ በቀኝ ዘረኞች ተልኮ ነው። ጥቁሮች ለመምረጥ እንኳ መሣተፍ የተፈቀደላቸው በ1971 ነው። ዛሬ ያ አልፎ አሜሪካ ጥቁር ፕሬዚደንቷን ባራክ ሁሴን ኦባማን ተቀብላ "ከጥቁረት ውበት ኃይል" ትሩፋቷን ተቋድሳለች። አሜሪካ ውስጥ እጅግ በጣም ብዙ የሚሠራ ፋታ የማይሰጥ የህይወት ግብግብ ስለጠመዳቸው - ሰው ጠምደው ግብግብ ለመግጠም ስአት የላቸውም። እንሠልጥን!

ለጥቆ የመጣው የታሪክ ዘመን ፊውዳሊዝም በመላው ዓለም የመሬት ከበርቴዎችንና ጪሰኞችን በሁለት ጎራ ከፍሎ ግንኙነቱ በመሬት ላይ የተመሠረተ ነበር። ባላባቶቹ መሬትን በጉልበታቸው ይዘው Tenant/ Serf (እንግሊዝኛው የገባው ቃሉ በመላው ዓለም የተለመደ መሆኑን ለማሳየት ነው) - እኩል ሲሦ ወይም እርቦ እየሰጡ እንደ መሬት ስሪቱ የሚጠቀሙበት ነው። ጪሰኞቹ ከመሬቱት ምርት አላግባብ ከመሥጠታቸው ሌላ ነፃ የጉልበት አገልግሎት እንዲሰጡ ይገደዱ ነበር። እንኳን



t.me/OLDBOOKSPDF

በቀደመው ዘመን ይቅርና ካፒታሊዝም ማቆጥቆጥ ሲጀምር ለፋብሪካዎች ግብአት የሱፍ ምርት በእጅጉ ስላስፈለገ የእንግሊዝ ካፒታሊስቶች በጎቻቸውን በደረሰ የገበሬዎች ቡቃያ ላይ ለቅቀው አርሶአደሮችን ከመሬታቸው ነቅለዋቸዋል። ሁኔታው ያሳዘነው እንግሊዛዊው ደራሲ ቶማስ ሙር በሽሙጥ ወይም አግቦያ "በጎች ሰዎችን እየበሉ ነው!" ሲል ፅፏል። አሽሙሩ ወይም ሾርኒው በውስጡ ያመቀው አንኳር ይዘት ያ ዘመን የነበረውን የሙብት መረገጥ ደረጃ ያሳያል። ሰው የዘመኑ አስተሳሰብ ውጤት ነውና ለምን? ብለን መጠየቅ ጊዜውን አለመዋጀት ነው።

ዓለም ዛሬ ያለችበት የካፒታሊስት ሉላዊነት ሥርአት ነው። ካፒታሊዝም ሠፊ ፅንሠ ሀሳብ ቢሆንም መነሻው ካፒታል ነው። ካፒታል ጉልበትን በመጠቀም (ለሥራ ተገቢውን ክፍያ ባለመፈፀም) ወይም ትርፍ ሰአት ተመጣጣኝ ክፍያ ባለመሥጠት የሚካበት ሀብት ነው። የሀብቱ ባለቤት ካፒታሊስት ሲሆን የብዝበዛው ሥርአት ሠልጠንና ረቀቅ ያለ ነው። ሠራተኛው (ላብአደሩ) እንዲሁም በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማራው ወዶ ፈቅዶ ተሰልፎ ተቀጥሮ ጣፋጭ ብዝበዛን የሚያስተናግድበት የመጠቀ የዘረፋ ሥርአት ነው። በመሆኑም የዓለም አንደኛው ቱጃር ሀብት ሃያ የኢትዮጵያ ታላቁ ህዳሴን ግድብ ያህል የሚያስገነባ ገንዘብ አለው። እዚያው ሀገር ምግቡን ከቆሻሻ ገንዳ ላይ የሚለቅም ዜጋ አለ። ከዓለም 2/3ኛው ቁምጥና ዛሬ በሚታይባትና ዛፍ ሥር ተማሪ በሚማርባት ህንድ ሀገር መኖሪያ ቤቱን ብቻ በቢሊየኖች ዶላር የገነባ ባለ ሪብጣ ሀብታም አለ።

ሀገራችንም እንደ ዓለም ማህበረሰብ አካልነት፤ ህንፃ እንደ ሳሙና የሚደረደሩ ቅልጥጤዎች እና ጎዳና ዳር 'ማስቲሽ' የሚስቡ ወገኖችን ጎን ለጎን ታጋፋለች። ዓለም በዚሁ መንገድ ወደፊት ትጓዛለች። ዘውጌዎች 'የድሮ ሥርአት ናፋቂዎች' ሲሉ ከንፈር እንመጥላቸዋለን። ወደ ኋላ ወደ ፊውዳሊዝም እንቆለመግምግ ወደፊት በፍትሐዊነት እንደ ታለመው 'ኮሙኒዝም' ባይሆንም ሁሉም ዜጋ በእኩልነት የሚታይባት ሀገር እንፈጥራለን የሚሉ ዜጎች በሁሉም ማዕዘናት መፈጠር አለባቸው። የኢትዮጵያ የታሪክ ማስረጃዎች በደርግ "ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት" ፍልስፍና እና በወያኔ "የአልባኒያ ሶሻሊዝም" እና የገነገነ የጎሳ ፖለቲካ አልፈዋል። በቀጣዮቹ ክፍሎች በስፋት እንቃኛቸዋለን። ለጊዜው የኢትዮጵያን ታሪክ ተስማምቶና አዋድዶ ለመፃፍ በቂ መረጃዎች በየሰንዱቁ ስለሚገኙ ከጥርጣሬና ሽፍጥ፤ ከጥላቻና ተንኮል፤ ከእኔ እኔ 'ኬኛ' ስሜት ጠርምሶ በማፈትለክ በአዲስ አስተሳሰብ የጋራ ታሪካችንን ለወል ጎጇችን እናት ኢትዮጵያ በሚበጅ አግባብ ማዘጋጀት ይቻላል።



t.me/OLDBOOKSPDF

## የኢትዮጵያ ታሪክ ጸሐፍት ተቃርኖ

የኢትዮጵያ ታሪክ አፃፃፍ ቁልፍ ችግር የፖለቲካ ፍላጎት ከታሪክ ትምህርት ዓላማ በተቃረነ መልኩ መዘነቁ ስለመሆኑ በቅርብ ጊዜያችን ታሪክ በተዘጋጁ ሰነዶች ውስጥ በጉልህ ይታያል። በተለይ ባለፈው ግማሽ ክፍለ (1970ዎቹ - 2018) ዘመን ባጠቃላይና ሩብ ክፍለ ዘመን (1991 - 2018) በተለይ "ታሪክን ለፖለቲካ አጀንዳ" መጠቀም ከየትኛውም ጊዜ በላይ መርሆ ሆኖ እና ገንኖ ታይቷል፡፡ የታሪክ ዝንፈትም በታሪክ ቀመስ ዕሑፎች ውስጥ በገሀድ ተንፀባርቋል። አካዳሚያዊ ነፃነትና ሙያዊነት በሚጋፉ ፖለቲካዊ ስርአቶች፤ የቡድን ብሔረሰባዊ ስሜት፣ የመንግሥታት መሻት እና በተፈጠሩ አውዶች ምክንያት መግባባት ባለመቻሉ የታሪክ ምሁራን በኢትዮጵያ ታሪክ ትንተና ዙሪያ 'ነገሩ ይዋል ይደር' የሚል ዝንባሌ ፀሳዩ።

የተፈጠረው ድባብ ለደፋር ፖለቲከኞች፣ በውጫዊ ገፊ ሀይል ለሚንቀሳቀሱ መርዘኞች እና ለቡድን ፍላጎት ራሳቸውን አሳልፈው ለሰጡ 'ፊደላውያን' ታሪክን አውሸልሽለው ባሻቸው መንገድ ለመፃፍ እድል ሰጣቸው። መንግሥታዊ ካድሬዎች ባሻቸው መንገድ ታሪክን ማዛባት ብቻ ሳይሆን ሥልጣን ያጎናፀፋቸውን አስቻይ ሁኔታ በመጠቀም "ለከፋፍለህ ግዛው ሥርአታቸው" መደላድል በሚያግዝ አግባብ የበትረ ሥልጣናቸው ማጠናከሪያ አድርገውታል። በዚህም የተነሳ በስመ አቅም ግንባታ የተከተሉት የመከፋፈል፣ የልዩነት፣ የመጠራጠር፣ ሀገርን እና ታሪክን የመጥላት መርዝ ሰንኮፉ በቀላሉ የሚነቀል አይደለም። የኢትዮጵያ ታሪክ ቀመስ ፅሑፎች በዘመናት ውስጥ የነበራቸውን ይዘት ከዚህ ቀደም ባለው ክፍል ለማሳየት ሞክረናል። በቅርብ ጊዜያችን ታሪክ ውስጥ ተዋናይ የሆኑ ፀሐፍትን በተመለከተ በበርካታ አንጓዎች ከፋፍሎ ማሣየት የሚቻል ቢሆንም ለተደራሲያን ግልፅ ለማድረግ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ምሁራን በሚሰጡ የታሪክ ትንተናዎች ላይ ተመርኩዞ እና በተለየ ምልከታ በመፅሐፉ አዘጋጅ ዳብሮ በአራት አፅቆች እንደሚከተለው ለመመደብ ተሞክሯል።

### 1.የቤተ መንግሥት ታሪክ መዝጋቢዎች (Establishment Historians)

በዚህ ዘውግ ሥር የምናገኛቸው ታሪክ ፀሐፊዎች ማዕከላቸው መንግሥት እንደመሆኑ የተለያዩ ስሜቶች ይስተናገዱባቸዋል። አንዳንዶቹ መንግሥታዊ መናን በመከጀልና



t.me/OLDBOOKSPDF

በሥርአቱ ውስጥ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ የመንግሥትን ገቢር አግዘፎ ለማሣየት አብዝተው ሲማስኑ ይታያል። ከፊሉ መንበሩን የተቆናጠጠውን መሪና ቢተ መንግሥቱን ለማግዘፍ የቀደመውትን ማንኳሰስ አብዝቶ ይንፀባረቅባቸዋል። በመሆኑም ዕሉፎቻቸውን በሁለት ገምሡን መመደቡ አብርሆት ይሰጣል።

የመጀመሪያው ምድብ፡- ቀጣዩ መሪ ያለፈው ወራሽ ከሆነ ምንም እንኳ የራሱን ግለ ስብእና ለመትከል ዐሐፊዎቹ የገፅታ ቅብ እንዲሡሩለት ተዘዋዋሪ ተፅዕኖ ቢያሳድርም የቀደሙትን የመውቀስ አዝማሚያ እንዳይኖር ጥንቃቄ ይደረጋል። በወቅቱ መንበሩ ላይ የተቀመጠውን መሪ የአመራር ጥበብ፣ የበዛ ርህራሄ፣ ደግነት ጥንካሬ አጋንኖ በማስቀመጥ የስብእና ግንባታ (Personality Cult) መፍጠርን ቀዳሚ ተግባሩ አድርጎ ይቆማል። ከዚህ አዙሪት በቀላሉ መላቀቅ ዛሬም የሚቻል አይመስልም። መሪው ሥልጣኑ ላይ ተደላድሎ የሙከራ ጊዜውን እንኳ በቅጡ ሳይከውን ከኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ ታሪክ የበለጠ ድርሳን ይደጎሥለታል።

ሁለተኛው ምድብ፡- መሪው የቀደመውን አቻውን በኃይል ገርሥሦ የተቀመጠ ከሆነ በተራው እስኪገረሠሥ ድረስ ደራሲዎቹ ራሱን ልእለ ሰብእ (ከሌላ 'ፕላኔት' ላይ የወረደ ልዩ ፍጡር) አድርገው በመሣል እና ቀድሞት የነበረውን ጭራቅ አድርጎ በመቅረፅ ተጠምደው ይታያሉ። ደርግ 17 ዓመታት (1974 - 1991) ከቀበሯቸው አፄ ኃይለሥላሴ ጋር ሙጭጭ ብሎ ሲፋለም ቆይቶ ታሪኩን በጥቁር ቀለም ለሚያጠለሸው ባለ ሳምንት በመጣበት የኃይል አግባብ ለቀቀ። ወያኔ (1991 - 2018) ዚምባብዌ ከተቀመጠው ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም እና ከርቸሌ ከቀረቀበቻቸው የደርግ ባለሥልጣናት ጫንቃ ላይ ሳትወርድ ለ27 ዓመታት ገዘፈች። ይባስ ብላ ራሱን ከጣለው ደርግ ርቃ ሄዳ ኃይለሥላሴን ጠንከር አድርጋ ጠምዳ፣ኢያሱን እና ዘውዲቱን ባላየ አልፋ፣ጧት ማታ እንቅልፍ ከነሳት ዳግማዊ ምኒልክ (ከመቶ ዓመታት በፊት ከነበሩ መሪ) ጋር የታሪክ ንትርክ ይዛ በውርደት ወደ መቃብሯ ወረደች። የህወሓት (TPLF) ዘመን ድርሰት ሌሎችን በመርገም የተካነ ከመሆኑም በላይ በ'መለስ አምልኮ' እንደናወዘ አልፏል።

በአፍቃሬ ሥልጣን ላይ የነበሩ መንግሥታት ፅሑፍ ውስጥ ገንኖ የሚታየው አገላለፅ መሪውን፡- "ዐሐዩ መንግሥት፣ አምዬ፣ ጀግናው፣ ቆራጡ፣ ባለ ራዕዩ፣ የህዝብ ጠላት የሆነውን የህዝብ ልጅ፤ ጉድፍ የሌለበት፣ ሰህ የማይወጣለት፣ እንከን የለሽ፣ ገእፈ.ገፀሙ ወደር አልባ" አድርገው ያሞካሹታል። የበዛ ውዳሴ የሚጎርፍለትና



t.me/OLDBOOKSPDF

"ወርቃማ ትንፋሽዎ ይድረሰኝ" የተባለው መሪ በዚህ ዕሑፍ ውስጥ በተለያዩ ሥፍራዎች እንደተጠቀሰው መሪውን 'ከእኔ ወዲያ ላሣር' እንዲልና አምባገነን ሆኖ እንዲወጣ ጥርጊያ መንገድ ይሆነዋል። በዚህም የተነሳ መሪው የታሪክ ሊቅ፣ ጉምቱ ፖለቲከኛ፣ የምጣኔ ሀብት አዋቂ፣ የግብርና ተመራማሪ፣ የውጭ ግንኙነት አታሼ፣ የህግ ልሂቅ፣ የህዳሴ መሀንዲስ፣ የአበባ ሥራ 'ኤክስፐርት' ብቻ ሥልጣኑን ጠቅልሎ ይዞ (Authoritarian and totalitarian) አድራጊ ፈጣሪ ይሆናል። 'አበጀህ ጎሽ በርታ' እያለ ለሆዱ የሚከተለው አጃብ ሲበዛ የሚነቅፉትን የጎሪጥ ማየቱን ሥራዬ ብሎ ይያያዘዋል። 'የመሪው አመራር የሬት ልግ ሆኖ የመረረው ሲቃወም ምላሱ ይቆረጥና ጣዕም መለየት የማይችልና የሰጡትን ሳያላምጥ የሚውጥ በቦታው ይተካል።' ሺህ መካሪ ቢሰበሰብ መሪው የሚፈልገውን የሚነግረው እንጂ እውነቱን የሚገልጥለት ሲያጥጥ 'መካሪ የሌለው ንጉሥ ያለ አንድ ዓመት አይነግሥ' ይከተላል።

እኖን የተባለው ምሁር አበክሮ እንደሚያሳስበው፡- "የብዙዎች ችግር በነቀፋ/ ሂስ ከመዳን ይልቅ በሙገሣ መጥፋታቸው ነው።" አፍቃሬ መንግሥት ፀሐፊዎች "ለሠፊው ህዝብ ጥቅም" በሚል ሽፋን ያኖሯቸውን ከታቦች ከእውነታው በእጅጉ ያፈነገጡ ስለሆኑ የዘመናቸውን ውሎ 'ሠፊውን ህዝብ በመግደል' በሚል አሻሽሎ የታሪኩን ስካር በማረቅ መፈወስ ይቻላል። በምዝገባው ሂደት በመሪው ዘመን የተሠሩትን ጥንካሬዎች መመዝገቡና ማድነቁ ዓብይ ተግባር ቢሆን ትውልድ ያተርፍበታል። የተደበቀ ጥፋት ካለ ግን ድክመቱ ጥላቻን ለማቀንቀን ሳይሆን ሀቁን ፍንትው አድርጎ ፅፎ ለመማማሪያ ቢውል ጠቀሜታው የትየለሌ ነው።

## 2. የማርክሲስት ሌኒኒስታዊ አመለካከት ታሪክ ጸሐፊዎች

በዚህ ዘውግ ሥር የተመደቡ ታሪክ ፀሐፊዎች ቀዳሚ ሙነሻ "Das Capital" በሚል ርዕስ በሦስት ክፍሎች እጅግ በጥልቀት ተተንትኖ የተቀመጠው ድንቅ መፅሐፍ፣ በዚሁ ላይ ተመሥርተው የቀረቡት የነ ሄግል፣ ፊዩርባህ፣ ፍሬድሪክ ኤንግልስ፣ ቭላድሚር ኢሊች ኡልያኖቭ (በብዕር ስሙ ሌኒን) ማእና መሠሎቻቸው ይሁን እንጂ አረዳዳቸው በጣም ቁንፅልና አንድ ቅርንጫፍ ላይ የተጣበቀ መሆኑ በኢትዮጵያ ታሪክ አፃፃፍ ላይ አጉል ጠባሳ ጥሏል። ለዚህ ምድብ ደራሲዎች፡-

"የሰው ልጅ ታሪክ በሙሉ (በእኩልነት ላይ ከተመሠረተው የጥንታዊ ጋርዮሽ አደኗር / Primitive Communal Society በስተቀር) በገዢዎችና ተገዢዎች መሀከል



t.me/OLDBOOKSPDF

የተካሄደ የማያቋርጥ የመደብ ትግል ነው። እንደ ከሰረው ትንታኔያቸው ከሆነ በመጨረሻ ሠራተኛው መደብ አሸንፎ ይወጣል። በመሆኑም በየስርአቱ ባሪያ አሳዳሪው ሥርአተ ማህበር (Slave Owning Society)፣ የመሬት ከበርቴው ሥርአት (Feudal Mode of Production) እና በካፒታሊዝም ስልተ ምርት ውስጥ በአቀማመጣቸው ቅደም ተከተል መሠረት ትግሉ የሚከተለውን መልክ እንደያዘ ያብራራሉ። የጋርዮሽ ህብረተሰብ መደብ አልባ (classless) ሆኖ አልፏል። በቀጣዩ ማህበረሰብ ባሪያ አሳዳሪው ከባሪያው፣ የመሬት ከበርቴው ከጪሰኛው፣ እና ቡርዧው ከላብአደሩ ጋር በጭቆና ቀፍድዶ ለመያዝና የብዝበዛውን ቀንበር ሰብሮ ለመውጣት የማያቋርጥ ትግል ይካሄዳል። በምህረት የለሽ ትግሉ ማብቂያ ለ'ሶሻል አብዮተኞች' (Social Revolutionaries) የላብአደሩ መደብ (Workers / Proletariat)፤ ለ'ሶሻል ዴሞክራቶች' የአርሶአደሩ መደብ አሸንፎ መሪነቱን ይረከባል።"

መነሻውን በዚህ ቅኝት ላይ ያቆመው ማትር ማርክሳዊ ትንተና ሰለባ የሆነው ታሪክ ፀሐፊ ተብዬ ቡድን የቀደሙ መሪዎችን ጥንካሬ በደምሳሳው ጥላሸት በመቀባት፦ ጠንካራውን ከደከማው፣ ለለውጥ የተደረገውን ትግል ከቆሞ ቀርነት፣ ተጋድሎ ውስጥ ያለፈውን የመሪዎችን ሚና በደፈናው ገደል ጨምሮ ህዝብ ብቻውን ያለ መሪ ይጓዝ ይመስል ያለፈውን የታሪክ ሂደት በአንድ ቅርጫት ለማጨቅ ብዙ ርቀት ተጉዟል።

ያለፉትን የሚያደንቅ ስብእና ቢኖር 'ፀረ - አብዮት'፣ 'የፊውዳሉ ሥርአት ርዝራዥ'፣ 'የቀድሞ ሥርአት ናፋቂ'፣ 'ነፍጠኛ'፣ 'ትምክህተኛ'፣ በእነርሱ እምነት ጭቁን ከሚሉት ብሔረሰብ የተገኘ ከሆነ ደግሞ 'ጥገኛ'፣ 'ተስፈኛ'፣ 'የስብእና መሸርሸር የተጣባው' ወዘተርፈ የሚሉ አብዮት ወለድ የዘቀጡ ቃላትን ያዘንቡበታል። ከዚሁም አልፎ በዘመነ 'ባነር' እና ዘመነ መፈክር ለለውጥ የታገሉ ተረሹ። መንግሥቱ ኃይለማርያም ከጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደርግ ደርግ ሊቀመንበርነት ጀምረው፤ የቅርፅ እንጂ የአይነት ለውጥ ባላመጡበት ሂደት ሥልጣኑን እንደ መጎናፀፊያ ጠቀለሉ። ቀስ በቀስ የኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ዋና ፀሐፊ፤ የኢትዮጵያ ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚደንት፣ እና የአብዮታዊው ጦር ጠቅላይ አዛዥ ... (ከዚህ በተጨማሪ የአንድ ለእናቱ ባለ 835 ሰው ፓርላማ - ብሔራዊ ሸንጎ ሊቀመንበር) ህግ አውጪውና ህግ አስፈፃሚውን ከመምራታቸው ባሻገር ህግ የሚተረጎመው በፍርድ ቤት ሳይሆን ከቀበሌ አብዮት ጥበቃ (የየአካባቢው ታጣቂዎች/ ደንብ አስከባሪዎች) እስከ ላዕላይ መዋቅሩ ባሉ ካድሬዎች ነበር። ሲጠቃለል ማርክሲስት ሌኒኒስት ፀሐፊዎች



t.me/OLDBOOKSPDF

በመደርደሪያ ላይ የገሸሯቸው ሰነዶች ለታሪክ ማስረጃነት እንደ አማራጭ ዕይታ እንደመሆናቸው የማይናቅ ድርሻ ቢኖራቸውም ከግነታቸውና ታሪክን በአንድ ቅርጫት ከመዶላቸው አኳያ በታሪክ አፃፃፍ ወቅት የጸሐፍቱን መረጃዎች ለመጠቀም ልዩ ጥንቃቄ የሚሹ ናቸው።

## 3. የዘውግ ታሪክ ፀሐፊዎች (Ethno nationalist Historians):-

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው የማርክሲስት ሌኒኒስት ፀሐፍት በቀጥታ የሚያተኩሩት ገገርው መደብ ላይ መሆኑ ተስተውሏል። ከዚሁ ትንተና ሀሳቦችን በመጋራት የአመለካከት ዝንፈቱ ፅንፍ የረገጠው፤ በኢትዮጵያ ታሪክ አፃፃፍ ውስጥ ከሁሉም አደገኛው ምድብ የዘውጌ ፀሐፊዎች ጎራ ነው። ሌኒኒስቶች በትንታኔያቸው ተጠያቂ የሚያደርጉት "ገዢ መደብ" የሚሉትን ስለሆነ ትኩረታቸው በአመዛኙ ሥርአት ላይ ነው። በየትኛውም ማህበረሰብ ጭቁኖች እንዳሉ በመገንዘብ በጅምላ እንደ አልቅት ህዝብ ላይ አይጣበቁም። ገዢዎችን ዒላማ በማድረግ ለሥርአት ለውጥ የሚታገሉ ናቸው።

የዘውጌዎች ጎራ-ያለልዩነት በጣም አደገኛና ኢትዮጵያን የማፍረስ ዓለማቀፋዊ ጥቅል ሴራ አካል ነው። በስብስቡ ውስጥ የምናገኛቸው ፀሐፊዎች አብዝቶ የኢትዮጵያ ታሪክ ጠልነት አባዜ የተጠናወታቸው፣ ብሔረሰብን እንደ ማህበረሰብ በጠላትነት ፈርጀው የተነሱ፣ 'ወክልንህ' ያሉትን ህዝብ ከሌላው ለመነጠል እንዲያስችላቸው በአሉታዊ ስሜት ቀስቃሽ ፅሑፎቻቸው የሚታወቁ፣ የፈጠራ ታሪክ ሊያውም ለጥፋት በመፍጠር ተቀራራቢ የሌላቸው፤ ታሪክን ለማነወር የተሰለፉ ቁጥር አንድ የኢትዮጵያ ታሪክና የኢትዮጵያ ህዝብ ጠላቶች ናቸው። የጥርቅሙ አደገኛነት ስሜት ኮርኳሪ የሆኑ የጥላቻ መልእክቶችን በማስተላለፍ ከመጠመዱ በላይ ከሚጠቀምባቸው የቅስቀሳ ስልቶች የተነሳ ተከታዮቹን እንደፈለገ የሚጋልባቸው መሆኑ ነው።

ከዚህው ጎን እና ከበስተጀርባው በረብጣ ብሮች የሚደገፍና ህልውናው በዘረፋ ላይ ተመሥርቶ እንደመገንባቱ የሚያስከትለውና ያስከተለው መዘዝ ቀላል አይደለም። አውዱን ታሳቢ አድርጎ ሠፋ ያለ ማብራሪያ በማቅረብና መነሻቸውን በማሣየት ተከታታይ ትውልዶችንና ሀገርን ለማዳን በጥንቃቄን በመጓዝ የሚደቅኑትን አደጋ መቀነስ ይቻላል። ለህዝብ አንድነት እና ሀገርን ለማፅናት የቆረጡ ዜጎች በሙሉ የስብስቦቹን የማጥቃት ስልት ለማክሸፍ እጅ ለእጅ መያያዝ፣ በታሪክ ዙሪያ የሚረጩትን መርዝ በጥበብ ማርከስ እና ከዘመን አስተሳሰብ ጋራ በመራመድ ታላቅ የአመለካከት ለውጥ ንቅናቄ ዘመቻ ማድረግ ይኖርባቸዋል።



t.me/OLDBOOKSPDF

የዕሑፋቸው መገለጫ:- የከፋ የታሪክ ሽሚያ ውስጥ መነከር፣ የኢትዮጵያን ታሪክ ማሳነስ፣ አንድ ብሔረሰብ ላይ ማነጣጠር እና ከላይ የገለፅናቸው አኩይ አሳቤዎች ድምር ነው። በአንድ ሀገር ውስጥ የሚገኝን ህዝብና ታሪክ "የእኛ" ሆኖ ሳለ ዘውጌዎች "የእኛ" / "Ours" የሚሉትን ወገን:- 'ርህሩህ ደግ ወርቅ የተለየ' አድርገው በማቅረብ ሳይወሰኑ "የእነርሱ" / "Theirs" የሚሉትን ደግሞ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ 'ከፉ አረመኔ' ከማድረግ ጀምሮ በተለያዩ አኩይ አገላለፆች አከፋፍተው ያቀርቡታል። በታሪክ ውስጥ የተፈጠሩ ጠንካራ ግለሰቦችን የአያት ስም ለውጠው ወይም አቀራርበው ወደ መንደራቸው ያሳንሱትና ከራሳቸው ማህበረሰብ የወጣውን ስብእና ከቀደሙ ነገሥታት ጋር በመሥራት ልክ እንደ ባንዳ ቅጥል ስም ይለጥፉበታል። ይህ ስብስብ በመንጋ የተጠረነፈ በመሆኑ ለአመክንዮ ክፍት አይደለም። 'ሆ' ብሎ መነሳትን የ(Mob) አስተሳሰብ የሚያበረታታ እጅግ በጣም አደገኛ መጃመል የሚያጠቃው ቡድን ነው።

ይኸ አካሄድ ከሚያደርሰው ጉዳት መጠን ጋር ተመዝኖ መስተካከል ካልቻለ እስካሁን የሄደባቸው መንገዶች በህዝብ ላይ ጅምላ ጭፍጨፋ ለማድረግ የሚታለፉ ደረጃዎችን ይመስላል:: ለማሳያነት ግሪጎሪ የተባለ ፀሐፊ (2012) "10 Stages of Genocide, Genocide Watch" በሚል ርዕስ በዓለም ላይ በተፈጠሩ ቀደምት የጅምላ ጭፍጨፋ ሂደቶች ላይ ተመስርቶ ያደረገውን ጥናት ውጤት በድረገፅ ከለቀቀው ዋናዎቹ፣ እንጓዎች ከሚከተሉት የጅምላ ጭፍጨፋ 10 ደረጃዎች ማነፃፀሪያዎች ጋር ተመሳከረው ዘውጌዎቹ የደቀኑትን አደጋ ብቻ ሳይሆን በተጨባጭ መሬት ላይ ብልጭ ያሉ ምልክቶችን በመገምገም ከታሪክ መማር ይቻላል።

**እንደ ግሪጎሪ አከፋፈል "የጅምላ ጭፍጨፋ ደረጃዎች:-**

**1. ህዝብን እኛና እነርሱ በሚል የመከፋፈል ምደባ ይካሄዳል።** በግልፅ ለማመላከት እንደሞከርነውና በቀጣይ ተከታታይ ከፍሎች እንደምንመለከተው ህዝቡን ከፋፍለው በእኛ እና እነርሱ ጎራ ፈርጀዋል። (ለምሳሌ:- የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በድፍረት በሰነድ ላይ "አማራው ነፍጠኛ ነው ማለት ይቻላል።" ማለቱ በማስረጃ ተደግፎ በቀጣይ ከፍሎች ቀርበዋል። 'ኦሮሞ ሲፋቅ አነግ ነው' አይነት ንግግሮች በቀጥታ 'እኛ እና እነርሱ' የሚለው ደረጃ አንድ ማሳያ ነው። የአንድ ብሄረሰብን አባላት ጠላት ብሎ መፈረጅ በግልጽ ታይቷል::)



t.me/OLDBOOKSPDF

2. **ህዝብ ማንነቱን እንዲገልፅ ማስገደድ።** (ከአራትም ከሶስትም ከሁለትም ብሔር የተገኙ ሳይቀሩ በግዳጅ አማራ ኦሮሞ ትግሬ ጉራጌ ... ነኝ እንዲሉና ይኸውም በፈቃዳቸውም ያለፈቃዳቸውም ብሄረሰባቸው መታወቂያቸው ላይ እንዲጻፍ ይገደዳሉ። ከአንድ እናት ከተለያዩ ሁለት አባቶች የተገኙ ወንድማማቾች ሳይቀር የተለያዩ ብሔረሰቦች ይኖራቸዋል። መለያ መስጠት- ታግ ማድረግ (እንኳን ዜጎች ተሽከርካሪዎች (Dehumanized Materials) "አር"፣ "አማ"፣ "ትግ"፣ "ሐረ" ... የሚል ሠሌዳ ተለጥፎባቸዋል። በተሽከርካሪዎቹ ውስጥ የሚጓዙ ግለሰቦች በማንኛውም ጊዜ የጥቃት ሰለባ ሊሆኑ ይችሏሉ፤ ችለዋልም።)

3. **ሰዎችን በማንነታቸው በተጠና መንገድ ማግለልና ማጥቃት።** (ወለጋ፣ ሀረር፣ ጊዶአ፣ ቡራዩ፣ ጣና በለስ፣ ጂግጂጋ፣ ጎንደር፣ ራያ፣ ሐዋሳ፣ አሶሳ አካባቢ፣ ቀቤና፣ አጣዬ፣ ከሚሴ፣ ሞያሌ፣ ወልቃይት...)

4. **ህዝብን ሰብአዊ ባልሆኑ መንገዶች ሰዋዊ ካልሆኑ በሽታዎች እንስሳት እና ባህርይ ጋር መሳል** (ቆማጣ፣ እባብ፣ አህያ፣ ጊንጥ ወዘተርፈ.) ከብራቸውን ማዋረድ።

5. **መንግሥት የራሱን ፖሊስ ሚሊሺያ የፀጥታ ሀይል ሌሎችን ለመምታት ማደራጀት።** (ለምሳሌ:- ጀርመን የሂትለር 'ብራውን ሽርትስ' / 'ስቶርም ትሩፐርስ'፤ የሩዋንዳ 'ኢንተርሀምዌይ ሚሊሺያ'፤ የአብዲ ኢሌ ሄጎ እና የወያኔ አግአዚ የየክልል ልዩ ኃይሎች ... ሊጠቀሱ ይችላሉ።)

6. **በመንግሥት አማካይነት በተወሰነ ቡድን ላይ ሚዲያ በመጠቀም ህዝብን ማነሳሳት፤ ተመሳሳይ በውጤት ተገፋፊ ዋልታዊነት መፍጠር።** (የጎላ ባይሆንም በትግራይና በአማራ መገናኛ ብዙኃን አላስፈላጊ ቅስቀሳዎች መደረጋቸው ሊጠቀስ ይችላል።)

7. **ቡድኖችን ከነበሩበት ስፍራ ለመንቀል እና ለማስወገድ ለሚያስችሉ እርምጃዎች መዘጋጀት።** (በኢትዮጵያ በስፋት ታይቷል)

8. **ግድያዎችን ማካሄድ፣ ንብረቶችን መዝረፍ፣ የሙከራ እልቂቶች መፈፀም፣ ማሳደድ።** (በኢትዮጵያ በስፋት ታይቷል)



t.me/OLDBOOKSPDF

9. ህዝብን ወይም ቡድንን በጅምላ መጨፍጨፍ። ይህ ወንጀል ተደርጎ አይወሰድም ምክንያቱም መጀመሪያውኑ ሰዎቹ በአባብ በአራዊት እና በበሽታ መልክ ተስለዋልና ርህራሄ አይታሰብም።

10. መዋሸት፡- መንግሥት የትኛውም ወንጀል መፈፀሙን ሽምጥጥ አድርጎ ይክዳል።

(በምዕራፍ ሃስት አዶልፍ ሂትለርን አስመልክቶ የቀረበውን ትንታኔ በማስተያየት ሙሉ ሥዕሉን ማግኘት ያስችላል የሚል እምነት አሳድረናል።) የዘውግ ታሪክ ፀሐፊዎች ተመሳሳይ መገለጫ የታሪክን መልካም ገፅታዎች 'የራሴ' ላሉት ብሔረሰብ ለብቻ ለማሸከም መላላጥ እና አሉታዊ ክስተቶችን 'የእነርሱ' በሚሉት አንድ ወይም ሁለት ብሔረሰብ / ብሔረሰቦች 'ማላከክ' ነው። ይህ የገነነ የህዝብ ጠላትነት ለዘመናት በሚያስደንቅ ኑባሬ እጅና ጓንት ሆኖ የኖረውን ህዝብ እጋምና ቀጋ ወደ ማድረግ የማዳማት ጉዞ ለመውሰዱ አመላካች ሁኔታዎች ብቅ ብቅ ማለት ጀምረዋል።

ዘውጌዎቹን በተናጠል ከመመልከታችን በፊት ተጨማሪ የጋራ መለያዎቻቸውን መግለጡ ጠቃሚ ሆኖ አናገኘዋለን። አብዛኞቹ የልጅነት ህይወታቸው ወይም አሁን ያሉበት ደረጃ በስነ ልቡና ቀውስ የአእምሮ መረበሽ ሰቅዞ የያዛቸው መሆናቸውን ቀረብ ብሎ በመመርመር ማረጋገጥ አይከብድም። እድገታቸው አዶልፍ ሂትለርን ጨምሮ በማንነት ማነስ ቀውስ ውስጥ ያደገ ነው። ብዙዎቹ ከቤተሰብ ተለይተው መጠለያ ውስጥ ያደጉ፣ እናትና አባቶቻቸው በልጅነት የተለያዩ፤ በመሠረቱት ጋብቻ መፍረስ ሳቢያ ቀውስ ያጋጠማቸው፤ ከሀገር መኮብለላቸው የፈጠረባቸውን የመለየት ጭንቀት በፖለቲካ ውስጥ በመደበቅ መርሳት የሚፈልጉ፤ ኢትዮጵያን ለማፍረስ ከሚተጉ ኃይሎች መሀለቅ የሚወረወርላቸው ... በሚገባ ቢፈተሹ በአንዳች የስነልቡና ድቀት የሚሰቃዩ ናቸው።

በጎጥ ጥላቻ መሳሳብ (Gene Pool) አካባቢ በወለደው ክፋት እና ከኑሯቸው መንሳቆል ጋር ተያይዞ የተመረዘውም ቁጥራቸው ቀላል አይደለም። አንዳንዶቹ የራሳቸው ወገን ሥልጣኑን ተቆናጥጦ ጭምር ለችግራቸው ማምለጫ ያገኙ ይመስል 'የሌለ የጠስ ዶሮ ፍሊጋ' አብዝተው ይኳትናሉ። ከሚያንኳቸው ነጥቦች መሀከል፡ 'ማንነቴን የማትቀበል ኢትዮጵያ አትኑር!' ሲሉ ይደመጣሉ። ለመሆኑ ማንነት በስጦታ እቃ ተጠቅልሎ የሚሰጥ ነውን? የበላይ ሆኖ ማንነትን ሰጪ ማነው? የበታች ሆኖ ማንነትን ተቀባይስ? 'የእናንተ ኢትዮጵያ' - የሚል ራሮት ሲበጭቃቸውም ይስተዋላል።



t.me/OLDBOOKSPDF

አንድ ሀገር ኢትዮጵያ የወል ሆና በውስጧ የተለያዩ አመለካከቶች እንደሚስተናገዱባት መመልከት አይፈልጉም። ለንፊኛው ቡድን ወደ ሥልጣን ወንበር ወጥቶ ሀገር ከልፈረሰች "የእኔ" ከሚሉት ብሔረሰብ አባል ሥልጣን ላይ ቢደላደልም፣ ጭቆና ካለ የጋራ ትግል በማድረግ አያምኑም። ሥልጣን ላይ ቁጭ ብለውም ጎናቸው በአነስተኛ ቁጥር አብሯቸው ወደሚኖረው ወገን ጣታቸውን ይቀስራሉ። ዘውጊዎችን እጅግ በጣም የሚያመሳስላቸው ሌላው መገለጫ ባህርይ - በየትም ዓለም በመሀከለኛው ዘመን ካልሆነ በዘመናዊ አስተሳሰብ የማይታለመውን የኔ ጎሳ ይቅደም አመለካከታቸው ነው:::-"ትግራይ ፈርስት፣ ኦሮሞ ፈርስት፣ አማራ ፈርስት፣ ሲዳማ ፈርስት ..." ነጠላ ዜማ በማቀንቀን ተስተካካይ አይኖራቸውም። ለእነርሱ ሀገር ሰውነት ዜግነት ሁለተኛ ሦስተኛና ትርፍ ነገር ነው። የማርንቢጥ ኢትዮጵያ ሀገሬ ሰውነቱ ዜግነቱ ያለ 'የድሮ ሥርአት ናፋቂ' ነው። ከዚህ በላይ ሀገርን የማፍረስ ደባ ምንድነው? በማስከተል በኢትዮጵያ ውስጥ ጨለማው ዘመን መባቻና በጨለማው ዘመን የተነሱ የዘውጊዎችን ገመና (ማንነት) በየተራ እንደሚከተለው ተገልጿል።

### 3.1. የኦሮሞ ዘውግ ታሪክ ጸሐፊዎች

የኦሮሞ ዘውግ ታሪክ ፀሐፊዎች ዋነኛ አስኳል የኦሮሞ ነፃነት (ግንባር) አንግ መሆኑ አሌ አይባልም። የትግሉ መነሻ "የኦሮሞ ብሔረሰብ "ብሔራዊ ጭቆና" ደርሶበታልና ከኢትዮጵያ መነጠል አለበት" የሚል ታሳቢ ነው። ዓላማውን ለማሳካት ከትግሉ ጅምር አንስቶ የተከተላቸው ስልቶች የኢትዮጵያን ህዝብ የስነልቡና ውቅር ያልተከተለ እና በማይበጠስ ስጋና መንፈስ የተሳሰረውን የኢትዮጵያን ህዝብ ለመነጣጠል ዒላማ በመቀስቀ፣ ለግማሽ ከፍለ ዘመን ያደረገው ትግል ያስገኘው ውጤት በንፅፅር ሲመዘን አሉታዊ ጎኖቹ ያመዝናሉ። እንደ ሌሎቹ የዘውግ ፀሐፊዎች ሁሉ የአንግ ትግል የመሬት እንጂ የሰው ክብር የለውም።

በየጊዜው የሚያዘጋጇዋቸው የፖለቲካ ካርታዎች እና የበዙ ምኞቶች ታሪክን በሚፈልጉት መንገድ በማጣመም እና በመጥቀስ፦ "የኦሮሞ የመጨረሻው ድንበር በሰሜን በኩል እስከ ደቡባዊ የትግራይ ከፍል አሻንጊ ሐይቅ ድረስ "የኛ" ነው፤ በደቡብ ኬንያ የሚባለው ሀገር በቁቢ አፃፃፍ ሲነበብ "ኬኛ" የሚል ድምፅ ስለሚፈጥር "የኛ" ነው። መተከል የኛ፣ ጎጃም የኛ የበዙ የኛዎች የመንጠራራት ጫፍና ለህዝብ ያለው ንቀት አይነተኛ መገለጫ ነው። ይህ አብሪት ስፍር ቁጥር የሌላቸውን የኩሽ ነዋሪዎች ከአገው ጀምሮ በመጥቀስ የኦሮሞን መነሻ በቋንቋ ዝርዝር በኩሽ ሥር ያሉትን



t.me/OLDBOOKSPDF

አካባቢዎች በማድረግ ኦሮሞ 'ሁሉንም' ይጠቅልል" አይነት ስሜት የሌሎችን ማንነት እስከ መጨፍለቅ የሚጓዙ የተንሸዋረሩ አመለካከቶች ሲያራምዱ ይታያል።

በቅርቡ የተስተዋሉ አስቀያሚ ዝንባሌዎችን መታዘብ እንደቻልነው መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ተሳትፎበት የተገኘውን የአድዋ ድል "ለኦሮሞ ብቻ የመሸለም አብሮነትን የሚሸረሽር ዝንባሌ ገዘፎ ወጥቷል። የአክሱምና መሠል ሥልጣኔዎችን የኩሽ ሥልጣኔ የማለት የታሪክ ፈጠራ ጥቅምና ማስረጃ ባይኖረውም የሚፈጥረው ስሜት ቀላል አይደለም። እነ የ"መገንጠል" መርሁ የኦሮሞ ብሄረሰብ አባላት ካላቸው ኢትዮጵያዊ ፍቅር የተነሣ እንደማይሳካ ግልፅ ሲሆን ውስጥ ለውስጥ ጥላቻን ወደ መዝራት በቅርቡም "የኩሽ መንግሥት" ዓላማን ማንገቡ የአደባባይ ምስጢር ነው። የኦሮሞ የዘውግ ፅንፈኛ ፖለቲከኞች የቀን ቅዠት ትኩረት "የአቢሲኒያ የበላይነት / Habesha Hegemony" የሚለውን ትርክት የሙጥኝ በማለት "የቀድሞዋ ኢትዮጵያ" የምትባል 'ጭራቅ' ፈጥረው "ዘሬም አለች" ይሉናል።

ለመሆኑ ከ1974 - 1991 የነበረውና በኦሮሞው መንግሥቱ ሀይለማርያም ወልዴ አያና ፕሬዚደንት፤ በምክትል ፕሬዚደንት ሌላው የኦሮሞ ተወላጅ ደበላ ዲንሳ የተመራው መንግሥት፣ በመገዳደል ቢወገዱም ብርጋዲየር ጀነራል ተፈሪ በንቲ (ኦሮሞ) ሌተናል ኮሎኔል አማን ሚካኤል አምዶም (ኤርትራ)፣ ሌተናል ኮሎኔል አጥናፉ አባተ (አማራ) በወታደራዊ ስብስብ የተፈጠሩ አመራሮች ነበሩ። መሬት ለአራሹን በማስፈን፣ የከተማ ትርፍ ቦታና ቤቶችን በማደል፣ ባንክና ኢንሹራንስ ሌሎችንም በቁጥጥር ስር በማዋል እርምጃዎችን ወስዷል። የግለሰቦች የሀብት ጣራ ከ500ሺህ እንዳይበልጥ አገዳ አድርጓል።

በቀይ ሽብር በወሰደው እርምጃ ከተሞች ላይ በማተኮሩ በቅደም ተከተል አማራና ኦሮሞን ጨፍጭፏል። ሥርአቱ ለየትኛውም ብሄረሰብ ያደላ እንዳልነበር እና ሁሉንም መጨፍጨፉ ለጥያቄ አይቀርብም። በመቀጠል ከ1991 - 2018 የቆየው የወያኔ መንግሥት የጥቂቶች የበላይነት የሠፈነበት (Oligarchy / Aristocracy) አይነት ሥርአት መሥርቶ በደረጃ ቅደም ተከተል በአማራ እና ኦሮሞ ማህበረሰብ ላይ መጠነ ሠፊ በደል ፈፅሟል። እነዚህ ጀሌዎቹ ለ50 ዓመታት የሚታዩ ጥቃቶች ቀዳሚ ሰለባ በሆነው የአማራ ብሄረሰብ ላይ የማተኮራቸው ምክንያት ጋብ ያላለውን ኢትዮጵያን የማፍረስ ፍላጎት መሆኑን አለመጠርጠር ይቅርታ የማያሰጥ ተላላነት ነው።



t.me/OLDBOOKSPDF

## የደራሲው እነግ ፅንሠት እና እድገት

የመረጃው ምንጭ መሆናቸው ይፋ እንዳይሆን ከጠየቁ አካላት በተገኘው መረጃ መሠረት በምኢሶን ውስጥ ከደርግ ጋር በመሞዳሞድ ከወለጋ ውጪ ያሉ ኦሮሞዎችን ያስጨፈጨፈው እነግ መነሻውና ዛሬም ገሞራ ሆኖ ለምን ወለጋ ውስጥ ሆነ? የወለጋ ልሂቃን የተለየ የቁጭት ስሜት እንዴት በረታ? የምስጢሩ ቁልፍ ሲፈተሽ፦ ከየትኛውም የኦሮሞ ክፍል እጅግ በጣም በተለየ ሁኔታ አንድም ጥይት ሳይተኩስ ከምኒልክ ጋር እፍ ከልብ ሆኖ የተሰናኘው የወለጋ ኦሮሞ ነው። የሌቃ ቄለም እና የሌቃ ለቀምት ጆቴ ቱሉና ኩምሳ ሞሮዳ ከአፄ ምኒልክ ጋር እፍ ከንፍ ያሉ ወዳጆች እንደነበሩ የታሪክ ሠነዶች ያለልዩነት ይገልፃሉ። (ማስረጃዎቹ በዝርዝር በመፅሐፉ ውስጥ ቀርበዋል።)

ይህ የኢትዮጵያዊነት ዋልታና ማገር የሆነው ወለጋ ምን ነካው? የተለየ በደል ደርሶበት ነው እንዳይባል ከጎረቤቱ ጎጃም ሲነጻጸር እንኳን የደረሰበት በደል በጣም አነስተኛ ነው። ለጥያቄው መልስ ይሆነን ዘንድ የሚከተለውን ታሪክ እንመዝን። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት በአይሁዶች ላይ የከፋ ግፍ የፈፀሙት የናዚ ወንጀለኞች ጦርነቱን የቃል ኪዳኑ ሀገሮች (Allied Powers) በድል ሲደመድሙ በተቃራኒው ተሸናፊ ጎራ (Axis Powers) በመሪነት ተሰልፈው አይሁድን የጨፈጨፉት ናዚዎች ተጠያቂነታቸው አይቀሬ ሆነ። በመላው ዓለም የሚሸሸጉበት ጥግ አልነበራቸውም። (ጠፍተው ሲታሰሱ የነበሩት እህምጥ ይግቡ እስምጥ ዓለም አላወቀም።) ዓለምን በሀሳባቸው ሲያስሱ ቅኝ ገዢዎች ያልያዟት ብቸኛ ሀገር ኢትዮጵያ ሆና ተገኘች። በመቀጠል ለመደበቅ ሻል ያለ ሥፍራ ሆኖ ወለጋ ላይ አነጣጠሩ። የያዙትን ገንዘብ በመጠቀም ራሳቸውን የተለያዩ ሀገሮች ዜግነት እንዳላቸው አድርገው በመግባት የሀይማኖት ሚሲዮናዊነት እንቅስቃሴ ጀመሩ። በዚሁ ሚሲዮን ትምህርት ቤቶችና የእምነት ተቋማት የቀረቧቸውን ባለ ብሩህ አእምሮ የወለጋ ልጆች ከኢትዮጵያ የመነጠልን መርዝ በማር እየለወሱ ያቀርቡላቸው ጀመር።

ይባስ ብለውም ኦሮሞ ከጀርመን ጋር የዘር ሐረግ ግንኙነት እንዳለው በጠይብ የሰብከት መንገድ መሙላት ጀመሩ። ጀርመኖቹ በአውሮፓውያን ከባ ሆነው ያሰራጩት ሌላው ሁኔታ ኢትዮጵያና እስራኤል ያላቸውን ግንኙነት በመጥቀስ ልክ ጀርመን ውስጥ ያደርጉት እንደነበረው ሁሉ "ፀረ-ሴማዊነት" እንቅስቃሴን አቀጣጠሉ። የእነግ ፀሐፊዎች የኢትዮጵያን ፖለቲካ ሲገልፁ "የአማራ-ትግሬይ ትርከት" /Amhara-Tigrean Tradition ያልተለመደ አይደለም።



t.me/OLDBOOKSPDF

በተመሳሳይ የአይሁድ ዝርያ ያላቸውን የውጭ ሀገር ፀሐፍት ሥራዎች በአደባባይ ሲረግሙ ይስተዋላል። ቀረብ ብሎ ላስተዋላቸው ሁለት አይነት ስልቶችን እያጣቀሱ ይጠቀማሉ። አንደኛው፡- "ኦሮሞ ፈርስት" የሚል ሲሆን፤ ሁለተኛው፡- ግድ ሆኖባቸው ኢትዮጵያን ሲጠሩ "የእናንተ ኢትዮጵያ እና የእኛ ኢትዮጵያ" የሚል የከፋፍል መንገድ ይጠቀማሉ። በቅርብ ጊዜ የስልት ለውጥ አድርገው እንጂ በቀደመው ጊዜ የኢትዮጵያ የጋራ ጀግኖች የነበሩትን የኦሮሞ ልጆች፡- አብዲሳ አጋ፤ ገረሱ ዱኪ፤ በቀለ ወያ፤ ጃገማ ኬሎ፤ ጎበና ዳጨ፣ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ፤ ባልቻ ሳፎ፤ አቡነ ጴጥሮስ፤ ጸጋዬ ገ/መድኅን ... የመጥራት ፍላጎት አልነበራቸውም። የፖለቲካ ትኩሳቱን በመከተል እንደ እርጥብ ቁጣ እየተገላበጡ ከተነሱበት መነከል ፈቀቅ ሳይሉ በስልት ለውጥ ብቻ ብዙ ተጉዘዋል። ከጀርመን ቋሚ ድጋፍ የሚያገኙበት ምክንያትና ልሂቃኑም ወደ ጀርመን ማማተራቸው በጥንቃቄ ቢመረመር የሚነግረን ጉዳይ አለ።

በኢትዮጵያዊነታቸው አልደራደር ያሏቸውን የሸዋ ኦሮሞዎች "ጎበና" በማለት (የጅግንነት ተምሳሌት የሆነውን ኩሩ ኢትዮጵያዊ ልክ እንደ ባንዳ በማስመሰል) እና ኦሮሞነታቸውን ባለመቀበል እስከ ቅርብ ጊዜ ደረስ መዘለፋቸው የሚካድ አይደለም። ይህ አካሄድ ጀርመኖች ከነገዳቸው የተቀላቀሉ ከፖሊሾች፣ ጂፕሲዎች፣ ስላቮች በተጋቡ ወገኖች ላይ ከወሰዱት እርምጃ ጋር ተመሳሳይነት አለው። በኢትዮጵያ ፖለቲካ ትልቁ ችግርና መፍትሔ ያሳጣን ጉዳይ መሸፋፈን ማለባበስ መደባበቅ - "ብዙ እናውቃለን፤ ብንናገር እናልቃለን" ሰሚት ነው። የእናቱን ጡት ጠብቶ ያደገውን የአርሲ ኦሮሞ ልጅ "የእናትህ ጡት ተቆርጧል" የሚል ትርክት ሲመግቡት ሳናላምጥ ውጠን፤ በትንሽ ጥናት የሚደረስበትን እውነት አለመግለጥ አያግባባም።

ለዚህም ነው 27 ዓመት ሙሉ በዐይኑ ዕያየ በወያኔ አግአዚ ሰናይገር ይገደል የነበረ፤ እናት ልጁ, አስከሬን ላይ ስትቀመጥ የተመለከተ፤ እነግ እየተባለ በእስር ቤት ተዘቅዝቆ የተሰቀለ እና በርካታ ግፎችን ያስተናገደ፤ እርቲስት ከነህይወቱ በመኪና ሲገተት ያየ፤ ከአምቦ ቀጥሎ የስቃይ ሰለባ የሆነው የወሊጋ ልጅ 132 ዓመታት ተጉዞ፤ እርሲ አኖሌ ጣቢያ ላይ ሄዶ ከምኒልክ ጋር አልፋታ ሲልና በድርጊቱ ሚና የሌለውን ወገኑን ሲጠላ እያስተዋሉ - ምን አዚም ተደርጎበት ነው? ብሎ አለመጠየቅ የሌለ የዋህነት ነው። (ሁልጊዜም እኩይ ልሂቃን ዘንድ እንጂ ከበሩ የኢትዮጵያ ህዝብ አካል የሆነ የትኛውም ማህበረሰብ ላይ ችግር የለም።)



t.me/OLDBOOKSPDF

ዓለም ከነሳ ስሜት ወደ ብሔረሰብ ተሸጋግሯ አልፋ ከካፒታሊዝም መደርጀት ጋር ሆዙን ወደ ምታስተደምበት የዜግነት ደረጃ ተሸጋግራለች። የአውሮፓ ሀገሮች ከዚህም አልፈው ከአሜሪካ ቻይና ጃፓን እና ሌሎች (Multi Polar Powers) ጋር ለመወዳደር ድንበራቸውን የወሰን ያህል ቆጥረው ተሳስረዋል። የሰው ልጅ ከዚህም ተሸጋግሮ ዓለማቀፍ ዜጋ (Global Citizen) ወደ መሆን ከተሸጋገረ ቆየ። ኢትዮጵያውያን በከፍተኛ ረሀብና ድርቅ በተጎዳንበት ወቅት ቦብ ጊልዶልፍ "እኛ ዓለም ነን / We are the World" የሚል 'ላይቭ ኤይድ ኮንሰርት' አዘጋጅቶ ድጋፍ ማድረጉ በኢትዮጵያውያን ልብ ውስጥ እንዲታተም አድርጎታል። በዚህ በ21ኛው ክፍለ ዘመን በጎሣ ፖለቲካ ደረጃ ማሰብ - ከሶማሊያና ደቡብ ሱዳን ትምህርት ለመውሰድ ይጋብዛል። ኢትዮጵያን ለመበተን ስለሚሠሩ ሀይሎች የሴራ ትንተና ግመታ ውስጥ ሳንገባ ድርጊታቸው የሚታይና ከበቂ በላይ ዝህድ ነው።

## 3.2 የትግራይ ዘውግ ታሪክ ጸሐፊዎች

አነግ እና ወያኔ ከምዕራብና ከሰሜን መንትያ ሆነው የበቀሉት በ1970ዎቹ አጋማሽ ሲሆን የሁለቱም መነሻ በፀረ-ኢትዮጵያዊነት መድረሻቸው ኢትዮጵያን ማፍረስ ነው። ለመሆኑ በተቀራራቢ ወቅት ድርጅቶቹን የፈጠራቸው ማነው? (ጥናት ይጠይቃል።) ሆኖም የነጠኞቹ አደረጃጀት በጥሞና ሲታይ በአንድ በኩል በወጣት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ደረጃ በሌላ በኩል ምንጩ ውጭ ሀገር ከመሆኑ አኳያ የምንገነዘበው ምን ትዳይ ይኖራል? እንደሚታወቀው በ1970ዎቹ መጀመሪያ ከሚበተኑ የተቃውሞ በራሪ ፅሁፎች አንዱ "ዴሞክራሲያ" ሆኖ "ዴሞክራሲያ" የተባለው አደረጃጀት የተመሠረተው ከኢትዮጵያ ተሰደው ወጥተው በምዕራብ ዓለም (አሜሪካና አውሮፓ) ይኖሩ በነበሩ ግለሰቦች ነው። በነዚህ ግለሰቦች የተጠራው ጉባኤ በ1971 በጀርመን በርሊን ውስጥ ተካሄደ።

በጉባዔው ፍፃሜ የኢትዮጵያ ህዝቦች አርነታዊ ግንባር (ኢህአግ) ተቋቋመ። (ስያሜው ላይ "አርነታዊ" የሚለውን ያልተለመደ አገላለፅና "ህዝቦች" ስናጤን ድርጅቱ በእነማን ተመሠረተ ለሚለው ጥያቄ ፍንጭ የሚሰጥ ይመስለናል። *ምስረታው ጀርመን ውስጥ መካሄዱና ከዚህ በኋላ የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር (አነግ) መመሥረቱ ነጠብጣቦችን በማገናኘት /Joining the dots በሴራ ግምት ትንተና ላይ ተንስተን ሳይሆን ዓለማቀፋዊውን ሥውር እጅ ለመገንዘብ ይረዳናል።)



t.me/OLDBOOKSPDF

የህወሓት መሥራች ተማሪዎችበመጀመሪያ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማህበር ገስገስቲ ብሔረ ትግራይ (ማገብት) በመሆን ተመሥርቶ ቀስ በቀስ ወደ ደደቢት ተራራ በመዛወር በ1970ዎቹ ፈፅሞ ማይጣጣሙ ርዕዮተ ዓለሞችን ብሔርተኝነት (ጎሰኝነት) ሶሻሊዝም (ዓለማቀፋዊነት) አጣምሮ የተወለደው ማርክሲስት ሌኒኒስት ሊግ ትግራይ (ማሌሊት) ግልፅ ርዕዮተ ዓለም አልነበረውም። በሂደት ወደ ማይተወው ህወሓት ስሙ ሽግግር ያደረገው ማገብት - ማሌሊት - ህወሓት በመሆን ነው። በድምሩ ስናየው ጎሰኞችን አንድ የሚያደርጋቸው አይነተኛ ባህርይ ለሀገርና ለህዝብ ፈፅሞ ደንታ የሌላቸው መሆኑ ነው። ለምሳሌ፡- አነግም ሆነ ወያኔ በባንክ ዝርፊያ እና የውንብድና ተግባር መታወቃቸው እና ንፁሐንን መግደል የካርታ ጨዋታ ያህል ቀላል እንደሚሆንላቸው በተጨባጭ ታይቷል።

ድርጅቱ ስያሜውን ለሦስተኛ ጊዜ በመቀየር ህወሓት (TPLF) በማለት ሲቋቋም ድርጅቱ እንድም ጊዜ ትርጓሜውን በአማርኛ እንደሌሎቹ አህትና አጋር ድርጅቶች ሳያስቀምጥ የመኖሩ ምስጢር በጥያቄ ምልክት የሚታለፍ ይሆናል። እንዴትስ አስከወዲያኛውኢትዮጵያን ተቆጣጥሮ እያስተዳደረ እንኳን "የትግራይ ነፃነት ሕዝባዊ ግንባር" ሆኖ እንደቀጠለ ስናይ ግንባሩ ባሰኘው ጊዜ ከሌሎች በጥምረት ከቀረባቸው ድርጅቶች መለየት እንደሚችልና ሀሳቡ ገር ካገኘ "ትግራይን ለመገንጠል" ከመጀመሪያው ይዞት የነበረውን ዓላማ በድንግዝግዝም ቢሆን ሙጥኝ የማለቱ ማመላከቻ ነው። አሥራት አብርሀም የተባለ የትግራይ ተወላጅ፡- "ከአገር በስተጀርባ፣ የትሮይ ፈረስና የባለ ፈረሱ ተልእኮ" በሚል ርዕስ ያዘጋጀው መፅሐፍ የህወሓትን አነሳስ ሂደትና ባህርይ በጥልቀት ለማሳየት ሞክሯል። በገፅ 77 ከላይ የጠቀስነውን ሀሳብ የሚያጠናክር ሀሳብ እንደሚከተለው አትሯል።

> *ህወሓት የትጥቅ ትግሉን ከጀመረ በኋላም በኤርትራ ጥያቄ ላይ ምንም ለውጥ አላሳየም። ምንም እንኳን በትግራይ ህዝብ ትግልና ጥያቄ ላይ የነበረውን የቀኝ ግዛት ትንተናና ከኢትዮጵያ ተገንጥሎ የትግራይ ሪፐብሊክ የመመሥረት ሀሳቡን በመተው በመጀመሪያ ለዴሞክራሲያዊ አንድነት ቅድሚያ እንደሚሰጥ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ማምጣት ካልተቻለ ግን መገንጠል እንደሚችል "የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት እስከመገንጠል" የሚለውን መርህ ተግባር ላይ እንደሚያውል ይህንንም በሁለተኛ አማራጭነት እንደሚወስደው አሳወቀ። በኤርትራ ላይ የነበረው*



t.me/OLDBOOKSPDF

*አቋም ግን መጀመሪያ ይለው እንደነበረው "የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው" የሚለው ነው ይዞ የቀጠለው።*

ለምን ህወሓት ከ18 - 22 ዓመት እድሜ ባላቸው ወጣቶች ተመሥርቶ ጫካ ገብቶ 'እናሸንፋለን' ብሎ መቀጠሉ አስምሮ ውስጥ የሚያጭረው ግምት ያቆየንና የውጭም የውስጥም ከፍተኛ ድጋፍ እንደነበረው ግን እያከራከርም። ህወሓትን መልከ በማስያዝና ሰይጣናዊ አቅሟን በማጠናከር በኩል ለገሥ ዜናዊ አሥረስ (መለስ)ን የሚስተካከል የለም። ይሁንና የመጀመሪያ ፈጣሪዎቿ ሙሴና ጃማይካ 'ኤርትራዊ' እና ከኤርትራ ፕንባይ ኃይሎች' ተልዕኮ የተቀበሉ ናቸው። ፀሐፊው (ከላይ ባለው ምንጭ ከገፅ 52 - 53) የነበረውን ውጥን ሲገልፅ "… ገና ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በማንብት ደረጃ እያሉ የኤርትራ ጉዳይ ከቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው።" ማለታቸውን ይገልፅና በመቀጠል፦ "ለዚህ አቋም ያደረሳቸው በአመራር ደረጃ ላይ የነበሩት በግልና በቡድን ከኤርትራ ሀይሎች አመራር (በዋናነት) ሻዕቢያ ጋር በነበራቸው ማንነታዊና ስነልቡናዊ ትስስር ምክንያት …" በማለት ሀሳቡን ያጠናክራል። ከራሱ የትግራይ ልጅ ከሆነው ከአስራት አብርሀም መሰሐፍ ገፅ 59 ላይ ረዘም ያለ ሀሳብ በቀጥታ መውሰድን የመረጥነው በጠቅላላ በምዕራፍ ሦስት በስፋት ለምንዳስሰው ርእስ መንደርደሪያ ስለሚሆንንና የትግራይ ዘውግ ፀሐፊዎች ለትግራይ ማህበረሰብ ጭምር ያላቸውን እደገኛነት ለማሳየት ነው፦

> *በአርግጠኝነት ሻዕቢያ በሙሴ አስተባባሪነትና በጃማይካ አማካሪነት ህወሓትን አሰልጥኖና ኢደራጅቶ ከሌላ ሀይል ጋር በማቀናጀት በኢትዮጵያ ውስጥ ይካሄድ የነበረውን ፀረ መንግሥት የተቃውሞ ትግል ለማጠናከርና የኢትዮጵያን የሀይል ሚዛን በማዛባት በኩል የራሳቸው አስተዋጽኦ ይኖራል ብሎ በማመኑ ነው። … ሙሴና ጃማይካ የህወሓትን ሰልጣኞች ይዘው ወደ ትግራይ ሲነሱ ለሁለቱ የተሰጣቸው ከሌሎቹ የተለየና ዘመናዊ የሆነ የትጥቅ መሣሪያ ስንመለከት ነገሩ በደንብ ግልፅ ይሆንልናል። የህወሓት ድርጅቶች ግን ከኤርትራ ድርጅቶች ጋር ስለነበራቸው ግንኙነትና ሙሴ ስለነበረው ሚና እውነታው እንዳይታወቅ ስለሚፈልጉ ብቻ ያልነበረ ያልሆነ ታሪክ ፈጥረው ሀቁን ለማድበስበስ እየጣሩ ነው ያሉት።*

(ወረድ ብሎ ገፅ 60 ላይ፦ "ሙሴ ለምንድነው ከሻዕቢያ ተነስቶ ከህወሓት ጋር መታገል የፈለገው?") እያለ ይጠይቃል። በተመሣሣይም በ2018 የኦሮሞ ነፃ አውጪ



t.me/OLDBOOKSPDF

ግንባር በ"አዲሱ የለውጥ አመራር" በተደረገለት የሰላም ጥሪ ወደ ሀገር ሲገባ ምን ተፈጠረ? ከ1991 - 2018 የአማራና የኦሮሞን ህዝብ አብዝቶ ከጨፈጨፈው፣ የራሱን የአነግን ታጋዮች ሳራ በረሀ ላይ ተከታትሎ አጥፍቶ "የሳራ በረሀ ምሥጢር የሚል 'ዶኩመንተሪ' በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን (ኢቢሲ) ለህዝብ ይፋ ካደረገው ህወሓት ጋር በምን ትስስር ተገናኝቶ ትግራይ ውስጥ ለመንባበዝ ቻለ? የሚሉ ጥያቄዎችን ብናነርፍ፤ የኢትዮጵያ ህዝብ ለዘመናት የቆየበት ፍቅር ባያስተሳሰረው "በዓለማቀፋዊው ፀረ ኢትዮጵያ ጥምረት" ምን ሊፈጠር ይችል ነበር? ከሰኔ 16 (ጁን 23/ 2018) የጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዓብይ ግድያ በስተጀርባ የተጠረጠሩት የፌዴራል ደህንነት ዋና ኃላፊ የትግራዩ ጌታቸው አሰፋ፣ የደህንነት ዳይሬክተሩ ኦሮሞው ተስፋዬ ኡርጌ እና ኬንያ ሆና ግድያውን አቀነባበረቺው በተባለቺው የአነግ አንስት መሀከል ምን ትስስር አለ? በማለት ወደ ሌላው ነጥባችን እንለፍ።

ከህወሓት ምስረታ ጥቂት ዘግየት ብሎ ኤርትራዊና ኢትዮጵያዊ ዝርያ ያለው መለስ ዜናዊ አስረስ የሽፍቶቹን ቡድን የመምራት ሃላፊነት ተረከበ። በመቀጠል ባለው ታሪካዊ ወቅት ህወሓትን ከመለስ / መለስን ከህወሓት መለየት እስኪያስቸግር የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች ሆነው ቀጥለዋል። ህወሓትን ከአነግ የሚለያት ባህርይ "አማራ ጠላታችን ስለሆነ መጥፋት አለበት" በማለት ሽፍትነትን የጀመረችበት የ'ማኒፌስቶዋ' መርህ ሲሆን፤ አነግ አማራን ከማጥላላትና ተዘዋዋሪ ቅስቀሳ ከማድረግ ውጪ በቃልም ይሁን በተግባር የታየ ኃላፊነቱን የወሰደበት ግልፅ ጥቃት ቢያንስ እስከ 2018 አለማድረጉ ነው።

ከ2018 ጀምሮ ቢደብቃቸው የማይሸፈኑ ወንጀሎች በይፋ በህዝብ ላይ ፈፅሟል። በበደኖ ማንቁፍቱ ገደል አማራ በመሆናቸው ብቻ ከነህይወታቸው የወረወራቸው አካል ማነው? ምላሽና ሦስተኛ ወገን ሳያስፈልግ በአነግና ወያኔ መሀከል እንደተሸከረከረ፤ ለኢትዮጵያውያን የእግር ውስጥ እሳት እንደሆነ - ለታሪክ ፍርድ እንደተተወ አለ። ወያኔ በምንም አመክንዮ ህዝብ ለየትኛውም ጥፋት ተጠያቂ እንደማይሆን እየታወቀ ከኢትዮጵያ ህዝብ ሲሦ የሚሆነውን አማራውን (መቼም አይሳካም እንጂ) ጭዳ ለማድረግ የሄደችባቸውን ርቀቶች በምዕራፍ ሦስት የምንዳስሰው ሆኖ የዕሑፎቿ መነሻ በዚህው ዙሪያ ማጠንጠኑ አይቀሬ ነው።

መለስ ዜናዊ ለኢትዮጵያ ህዝብ ግድ እንደማይሰጠው የረጂም ጊዜ ህልሙን "የትግራይ ሪፐብሊክን መገንባት" እና ኢትዮጵያ የባህር ወደብ ብታጣ ቅንጣት



t.me/OLDBOOKSPDF

እንደማይሰማው፤ ኢትዮጵያ ትግራይን ለይታ እስካልጠቀመች "ባልበላውም ጭሬ እበላሸዋለሁ" ቀመር ቆምሮ ወራሾቹ ተግባራዊ እንዳደረጉት ለዚህ ትውልድ ህብረ እምሳል ቅኔ ቢሆንም ለታሪክ ፍጆታ ማቅረቡ አስፈላጊ መስሎ ተሰምቶናል። የትግራይ ተወላጅ የሆነው አሥራት አብርሀም:- "ከአገር በስተጀርባ - ህወሓትና ሻዕቢያ - የትሮይ ፈረስና የባለፈረሱ ተልዕኮ" በሚለው መፅሐፉ የህወሓትን ደባ እንደሚከተለው አስቀምጦታል:-

> *ህወሓት በኤርትራ ጉዳይ ላይ ያለውን አቋም ገና ከጧቱ ለይቶ አስቀምጧል። ኤርትራ በጠቅላላ ወይም በከፊል የኢትዮጵያ አካል ሊይደለቺም። የራሷን አገራዊ ማንነት ያጠረች አገር ነች የሚል እምነት ነው ከመጀመሪያው የነበረን። ህወሓት በዚህ አቋሙ አንዲት ቀንም ቢሆን ተጠራጥሮ አያውቅም።...*

የማኅበት አባላት ገና የትጥቅ ትግል ከመጀመራቸው በፊት አቋማቸው ይህ እንደነበር ስንረዳ የኢትዮጵያም ሆነ የኤርትራ ማህበረብ ፍላጎት ሳይጠየቅ በአንድ ታላቅ ሀገር ዕጣ ፈንታ ላይ መወሠንና ለዚሁ መሥራት ከጠላትነት ሌላ ምን ትርጉም ይሰጠዋል?

የህወሓት መሥራቾች ከሻዕቢያ፣ የሻዕቢያ መሥራቾች ከግብፅና አረብ ሀገራት ያላቸው ቅንጅትና ያገኙ የነበረው ድጋፍ እና በመጨረሻ ከምዕራባውያን ሀገሮች በተለይም አሜሪካና ብሪታንያ ያገኙትን ድጋፍ ዕናያለን። የአሥራት አብርሀም መፅሐፍ በሀገር ውስጥ እንዳይታተም ተከልክሎ 'እኛ እያለን አንገትህን አትደፋም' ባሉት ሦስት የትግራይ ተወላጆች ትብብር ክልከላ የተደረገበት መጽሐፍ ውጭ ሀገር ሊታተም ችሏል። አቶ ሀይላይ ሓድጉ:- "ፅንዓት" በተሰኘው ጦማሩ የህወሓት አመራሮች አጀንዳ የትግራይ ህዝብ አጀንዳ እንዳልነበር አረጋግጧል። (ትግራይ የሚለውን የግለሰቦቹን የትመጣ የጠቀስነው በህዝብና በቡድን አመለካከት መሀከል ተዛምዶ እንደሌለ ለማመላከት ነው። በኢትዮጵያ ታሪክ እስካሁን ህዝብ የወከለው ቡድንም ሆነ ስብስብ የለም። ወኪል ነኝ ብሎ መንጠራራቱ ግን የየእለት ተውኔት ሆኗል።) የትግራይ ዘወግ ታሪክ ፀሐፊዎችን መሠረታዊ ይዘት ማሣያ እንዲሆን ለህፃናት አገልግሎት ታስቦ የተዘጋጀውን የአታኽልቲ ሐጎስ:- "ሓቅ ሓቁን ለህፃናት" የተሰኘ መፅሐፍ ብቻ መመልከት ድርብርብ ትርጉም አለው። ገፅ 12 ላይ:-

> *በደርግና በኃይለሥላሴ ሥርአቶች የነበረው ልዩነት የስም ብቻ ነው።... ሁለቱን አንድ የሚያደርጋቸው ግን በምኒልክ በተመሠረቱ ሸዋዊ*



t.me/OLDBOOKSPDF

አስተሳሰብ የሚመሩ መሆናቸው ነው። ... ያለውን ሀገመንግሥት የሚቃወም ትግሬዎችን በመጥላት ብቻ በስሜት የሚነጉዱ ሸዋዊ የምኒልክ አስተሳሰብ አስተሳሰብ ጠፍቶባቸውና ጨልምባቸው የሚባዙ ናቸው።

በማለት፦

1) የደርግና የኃይለሥላሴን ፊዕም ተዛምዶ የሌላቸውን ሥርአቶች ሸዋ በመሆናቸው ብቻ አንድ ማድረጉ፤

2) የደርግ ሥርአትን በምኒልክ የተመሠረተ አድርጎ መሣል፤

3) ሀገመንግሥትን መቃወም ትግሬዎችን መጥላት አድርጎ ማስቀመጥ እና

4) ለሕፃናት ታስቦ የተዘጋጀው የፖሎቲካ መፅሐፍ የቱን ያህል ታዳጊዎችን ለመመረዝ የተዘጋጀ እንደሆነ የሚጠቀሱ ሲሆን (ይኸው ምንጭ ገፅ 19 ላይ) የሚከተለውን ከትቧል፦

የኢሜሪተስ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴን "የኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ" በሚል ርዕስ በዘመናዊ የኢትዮጵያ ታሪክ ዙሪያ ተወዳዳሪ በሌለው መንገድ ተተንትኖ የቀረበውን የላቀ የምርምር ሥራ እና በኢትዮጵያ ታሪክ ዙሪያ በርካታ አበርክቶ ያደረጉትን ተከለፃድቅ መኩሪያ "ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት" ያነፃዕርና በሚያሳፍር መልከ፦ "ሁለቱም የደቂቀ ምኒልክ ዘር ስለሆኑ አይራሩቱም" የሚል ዐረፍተ ነገር በማጠናከሪያ መልከ ያቀርባል። መፃሕፍቱን ባላቸው ጉንካሬ ወይም ድከመት ሳይሆን "በዘራቸው" ይፈርጃል። መፍለቂያቸው አነጋዊ እና ጠያኒያዊ አስተሳሰብ የሆነው ፀሐፊዎች አይነተኛ መገለጫ የትኛውም ከእነርሱ አስተሳሰብ ውጭ የሆነ ዕሑፍን ከዘር ከብሔረሰብ ከሀይማኖት ከስብእና ጋር በማገበት በአንድ በኩል የመንጋው አባላት ገልጠው እንዳይመለከቱት መከላከል በሌላ በኩል እንዲሁም ከሚጠሏቸው ወገኖች የሚፃፉ ሀሳቦች እንዳይኖሩ ስነልቡናዊ ጫና መፍጠር ነው።

እኩይ ሀሳባቸው ገዝፎ በመውጣቱና ገገር በማግኘቱ ተሳከቶላቸው የዜግነትና የኢትዮጵያዊነት ፖለቲካ እንዲቀጭጭ፤ የኢትዮጵያዊነት ስሜት እንዲደበዝዝ መጥፎ ጫና ማሳደር ችለዋል። (የትግራይ ዘውግ ፀሐፊዎች በቅርቡ ከ2018 ጀምሮ ኦሮሞ ላይ ያተኮረ አፍራሽ ቅስቀሳ በተዘዋዋሪ የጀመሩ ሲሆን፤ አማራና ኦሮሞን ለማለያየት



t.me/OLDBOOKSPDF

ጥምር ታሳቢ በማድረግ የሁለቱን መለያ ለብሰው ለሙተውን "ዲጂታል ወያነ" የሚል የማህበራዊ ሚዲያ ዘመቻ መከፈታቸው ይታወቃል። የፖለቲካ ታሪኩ በማህበራዊ ትምህርት ድረገፆችና በሁሉም አይነት ሚዲያ የሚደገፍ ተዕለጥውም ቀላል እንዳልሆነ መገንዘቡ ይጠቅማል።) የህወሓቱ ቡድን አብሮት ለየትኛውም ዓላማ ይሁን በመሰለፍ መስዋዕትነት የከፈለውን የኢትዮጵያ ህዝቦች ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ዘግይቶ ብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ) የትግል ሂደት ትኩረት ነፍጎታል። የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ መኮንኖች አንድነት ንቅናቄ (ኢዴመአን) የአጭር ጊዜ የትግል አስተዋፅዖም ቢሆን ተቀብሯል።

ብአዴን በአንፃራዊ መልኩ 25ኛ ዓመት የልደት በዓሉን ሲያከብር በሰነደው "ፅናት" የተሰኘ ሰነድ ቅፅ 2፣ ገፅ 12 የኢህዴን አማራ ታጋዮች አደረጃጀት በሚከተለው መልክ ተገልጿል።

> *በ1980 ዓ.ም ደርግ በኢህዴንና ነፃ በወጣው የጎንደርና የወሎ ህዝብ ላይ የሰነዘራቸውን ከስምንት ብርጌዶች በላይ የተሳተፉባቸውን ተደጋጋሚና ሰፋፊ ወረራዎች በመመከት አረጋግጧል። ... ድርጅታችን ኢህዴን - ላባደር፣ ቴዎድሮስ፣ አዋሽ፣ ሰንገደ፣ ዋለልኝ የሚባሉ ክፍለጦሮችና የከባድ መሣሪያ ሬጅመንቶች (ሻለቃዎች) ነበሩት። ከዚህም በተጨማሪ ለዚህ ግዙፍ ሠራዊት ድጋፍ የሚሰጡ የመገናኛ የትጥቅና ስንቅ የህክምናና የመሣሠሉት የተጠናከረ ድጋፍ ሰጪ አካላት አሉት።*

ከይዘቱ እንደምንመለከተው የአማራ ልጆች ደርግን በመፋለም መራራ መስዋዕትነት ከፍለዋል። ደርግም ከማንም በከፋ ደረጃ የአማራን ወጣቶችና ምሁራን እንደ ቅጠል እንዲረግፉ አድርጓል። በተማሪዎች ትግልም ጭቆናን 'አምቢኝ' ብለው ከተነሡ መሪዎች ጥላሁን ግዛውና ዋለልኝ መኮንን ይጠቀሳሉ። የትግራይ ዘውግ ፀሐፊዎች አማራውን በተመለከተ የሚፈጠሩ መልካም ነገሮችን 'ዐናይም! አንሰማም! አንናገርም!' ማለታቸው የፀረ ብሔረሰብ አቋማቸውን ገላልጦ የማሳየት አቅም አለው። ደርግን ለመጣል ከወያኔ ጎን የተሰለፉ የአማራ ታጋዮችን ጉዞ መግለፅ የሚችለው "በሬ ከአራጁ ይውላል" ነው።

የዘውግ ታሪክ ፀሐፊዎችን ግድ የለሽነትና የከፋ 'የዘር ጥላቻ' እና የመከፋፈል ክፉ አቋም በማሳየት ለመጠቅለል የአታኽልቲ ሓጎስ ድርሰን ከሆነው "ሓቅ ሓቂን



t.me/OLDBOOKSPDF

ለህዝቦች" የ2005 (1998) መፅሐፍ ዘለግ ያለ ማጠቃለያ ከገፅ 169 መውሰድ የአደገኝነታቸውን ደረጃ በመጠኑ ያመላክትልን ይሆናል፦

> *ኢትዮጵያን ካለፈው 100 ዓመት ታሪካችን የምንማረው የሸዋ ተንኮል ከሁሉም መጨረሻ እንዳስቀረን ነው። አሁን ሀገራችን ወፍታት ያስቸገራት የተመሰቃቀለ ችግር የምኒልክ ተንኮል ወጥመድ አጥማጅውብን ስለቀየ ነው። አሁን ብቅ ጥልቅ የሚሉት ደቂቀ ምኒልክ የሞተውን ስርአት ለመመለስ ነው። እንደተለመደው ለተበዳዩ የትግራይ ህዝብ ያለ ስሙ ስም የሚሰጡት፡ ከዚህ በባሰ መልኩ ሊያዳክሙት ዘረኝነት ቅንቅብ የሚያደርጉት። ደቂቀ ምኒልክ ኢድል ከተሰጣቸው ችግሩ በጣም ከባድ ይሆናል። ከእንግዲህ የትግራይ ህዝብ ያለ አግባብ ተጨማሪ መስዋዕት አይከፍልም። ሁሉም በአግባቡ ሊያስብበት ይገባል። የደቂቀ ምኒልክ ተንኮል የብሄር ብሄረሰቦች ሀልውና ለማጥፋት ያለመ መርገዝ ነው። ኢትዮጵያችን ለዘላለሙ ለመበታተን ነው። እዚህ ላይ እንዝህላልነት አያዋጣም።*

ከላይ እንደተመለከትነው ህወሓት በጥላቻ አጥራ በያዞቼው ልሂቋና ተንኮሉ ባልገባው ወጣት እየነገደች ቀጥላለች። እነግ በተለይ ውጭ ሀገር ለትምህርት የሚሳኩ የኦሮሞ ምሁራን ላይ መረብ በመዘርጋትና ከወለጋ በሚነሳው የህዋስ ጠርናፊ አደረጃጀት በመጠቀም፤ ሁለቱም በሚያገኙት ዓለማቀፋዊ ድጋፍና ስምሪት ለኢትዮጵያ ህልውና ስጋት እንደሆኑ ቀጥለዋል።

## 3.3, የዐማራ የዘውግ ታሪክ ጸሐፊዎች

የዐማራ የዘውግ ታሪክ ጸሐፊዎችን በተመለከተ ያለን አረዳድ በብኸርታ የታጠረ ይመስላል። የዐማራ የዘውግ ታሪክ ጸሐፊዎችን ከኦሮሞና የትግራይ አቻዎቻቸው ነጥሎ ማየት በሰው ዐይን በሚከናወን የውበት ውድድር 'ከዝንጀሮ ቆንጆ የመምረጥ' ያህል ነው። ከዝንጀሮዎች መሀከል ቆንጆ ለመምረጥ ዝንጀሮ መሆን ይጠይቃል፣ ዘውጊዎች የአካሄድ ስልታቸው ይለያይ እንጂ ሥሪታቸው አንድ አይነት ነው፣ ከውጤት አኳያም መዳረሻቸው ሀገርን መበተን ነው። የትኛውም ዕንፍ 'የከረረ መበጠሱ አይቀርምና' ለሀገር አይጠቅምም። በምድቡ ሥር የሚያርፉ ዘውጊዎችን በሁለት ከፍለን ልናያቸው እንችላለን።



t.me/OLDBOOKSPDF

### 3.3.1 ወግ አጥባቂዎቹ፡-

የወግ አጥባቂዎቹ ዋነኛ መለያ ራሳቸውን ብቸኛ የሀገርና የታሪክ ጠባቂ አድርጎ መቁጠር ነው። ባለፉ የታሪክ ወቅቶች የተከሰቱ እንከኖች በተነሱ ቁጥር ይጎፈንናቸዋል። ነገሥታቱ የኢትዮጵያ ህዝብ የጋራ መሪዎች እንደነበሩ ይዘነጉና ወደ ራሳቸው ጉያ በመውሰድ ለመከላከል የሚያደርጉት መላላጥ ከሌላው ወገን አኳያ "ጠቅላይ አግላይ" ስሜት ይፈጥራል። ስህተትን ረግመው ስኬትን መውቀስ አለለመዱም። ታሪክን በጭፍን ከሚጠሉት የሚለያቸው ባህርይ ያለፈውን በሙሉ በጭፍን መውደዳቸው ነው። የእነርሱ 'አጉል መቆርቆር' ሌላው ላይ ገፊ ስሜት ከመፍጠሩ ባለፈ ጉዳታቸው ከሌሎቹ አንፃር የበዛ ላይሆን ይችላል።

### 3.3.2 "ከእኛ ወዲያ ላሣር" ፅንፈኞቹ፡-

የአነግ እና የወያኔ ቀጥተኛ ግልባጮች ናቸው። ራሳቸውን የኢትዮጵያ ታሪክ አልፋና ዖሜጋ አድርገው ይኮፈሳሉ። ወያኔዎቹ፡- "ወርቅ ከሆነው የትግራይ ህዝብ በመፈጠሬ ኮራሁ" ሲሉ፤ የአማራ ፅንፈኞች፡- "አማራነት የሰው ውሀ ልክነት ነው" በሚል ጅል ቅኝት ይንጀባረራሉ። የትግራይ ፅንፈኞችና የአማራ ፅንፈኞች ደጋግመው በተመሣሣይ ቅላጼ የሚወረውሯት ልደፋ አንድ አይነት ይዘት አላት። የትግራዮቹ፡- "ትግራይ የኢትዮጵያ ፈጣሪ ናት። ያለ ትግራይ ኢትዮጵያ ትርጉም የላትም" የሚል አገላለፅ ሲጠቀሙ፤ የአማራዎቹ አቻቸው ደግሞ፡- "ኢትዮጵያ ፈጣሪዋን አማራን ማክበር አለባት" ሲሉ ይደመጣሉ። የኦሮሞ ፅንፈኛ ጠቅልሌዎቹም "ሁሉም ኬኛ" የኛ ከማለት አልሰነፉም። ሦስቱም ፅንፈኛ ቡድኖች እርስ በርስ እየተመጋገቡ በመፋፋት የኢትዮጵያን ህልውና አደጋ ላይ ጥለውታል። መለያቸው ገጀራ ድንጋይ ዱላ ጠብመንጃ እና ስናይፐር ነው።

በዘውጎች መንደር ምክንያት ቦታ የለውም። የሚፈጥሩት ጀሌ ለምን እንደሚከተላቸው፤ ዓላማቸው ምን እንደሆነ፤ እነርሱን በመከተሉ ምን እንደሚያተርፍ፤ ከኋላቸው ያለው ገፊ ኃይል ምን እንደሆነ እና የመጨረሻ ግባቸውን ቢጠየቁ ተንትኖ ማስረዳት አይችልም። ብቻ ተነስ ሲሉት ሽመሉንና ጠብመንጃውን ወልውሎ ይነሳል። ማንን ልትጥልበትና ምርኮ ልትሰበስብ ነው? ቢባል 'ነፍጠኛውን'፣ 'ወያኔን'፣ 'አነግን' ይልሀል። ዱላ ተሸክሞ፣ ላብ በላብ ሆኖ ግም ግም፣ ድው ድው፣ ድብ ድብ፣ መሬቱን ደብለቅ ደብለቅ ... አድርጎ ሲደርስ፡- ገበሬው እያረሰ፣ ሌላው ሎተሪ እያዞረ፣ ሌላዋ ምጣድ እያሰፋች፣ እንዱም ቀዶ ጥገና እያደረገ፣ ሌላዋ ለእለት



t.me/OLDBOOKSPDF

ጉርሷ ደፋ ቀና ስትል፣ ሌላዋም ቆሎ ገዝታ ለመብላት ቆሎ ስታዞር ያገኟታል። ጭንቅላቷን በላት'፣ 'እናቱን በለው'፣ 'ቀጥቅጠው' ... አብደት፣ አእምሮ ሀመሙን ሀከምና ማእከል የማይፈውሰው የቡድን አብደት፣ ደም የሚያስፈስስ አብደት።

የአማራ ፅንፈኞች በሚና መደበላለቅ ረገድ አቀጣጫ ለማስቀመጥ ጥምር አስቸጋሪዎች ናቸው። ዋለልኝ መኮንን በ"ታገል መፅሔት" ያሰፈረው ፅሑፍ እንደሚያሳየው "በኢትዮጵያ የብሔረሰቦች ጥያቄ ዙሪያ" የነበረው አቋም መገንጠልን የሚደግፍ ነበር። ሀሳቡን ፕሮፌሰር መረራ ጉዲና፡- "Ethiopia: From Autocracy to Revolutionary Democracy, 1960s - 2011" በሚል ርዕስ ለህትመት ባበቁት የጥናትና ምርምር ሥራቸው ገፅ 64 ላይ አስቀምጠዋል።

ይህንን በሚያቀነቅንበት ወቅት በኋላ ላይ የኦነግ ቁልፍ ሰው ሆኖ የወጣው ኢብሳ ጉተማ ከኢትዮጵያዊነቴ ውጪ ብሔረሰብ የሚባል መከፋፈያ ልሰማ አልፈልግም የሚል ጠንካራ አቋሙን በዚሁ መፅሔት ላይ በግጥም አስፍሯል። በራንዲ ሮኒንግ ባልስቪክ፡- "የኃይለሥላሴ ተማሪዎች ወደ አብዮቱ ጉዞ ማህበራዊና ስነአእምሯዊ መነሻ" 2005:283 ወይም ገፅ 283 የሚከተለውን ሀሳብ እናገኛለን፡-

የኢትዮጵያ አንድነት ኤርትራውያንን ጨምሮ በአብዛኞቹ ተማሪዎች ልቡና ውስጥ ትልቅ ሥፍራ ነበረው። ኤርትራውያኑ የሥርአቱ አስቀያሚነት የመገንጠል አማራጭ ብቸኛው መንገድ እንዲመስለን በማድረጉና ይዘን በቆየነው የመገንጠል አቋም ይቅርታ እንጠይቃለን" ሲሉ ዋለልኝ ግን የአንድነት አቀንቃኝ በነበረው የትግራይ የተማሪዎች መሪ ጥላሁን ግዛው ላይ ያሳድም ነበር።

በዚሁ መፅሐፍ ገፅ 282 ላይ በባልስቪክ ምንጭ ተጠቅሶ እንደተቀመጠው፡-

> *በተማሪዎቹ ውይይት ላይ አብዱልመጂድ ሁሴን የተባለ አማራ ያልሆነ ተማሪ ኢትዮጵያ ውስጥ ቋንቋ አንጂ ብሔር የለም። አማርኛ (በተገቢው ወይም ባልተገባ መንገድ ተስፋፋ) ሌላ ነገር ሆኖ በብሔራዊ ቋንቋነት በማገልገሉ ላይ ተቃውሞ የለኝም ይላል።*

የሚል ሐተታ ተቀምጧል። በወቅቱ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎቹ አቋምና የበሰለ ውይይት ገላጭ በሆነ መንገድ እንደሚያስረዳን ከብሔረሰብ መንጋ አመለካከት ወጣ ባለ መልኩ ሁሉም የመሠለውን በነፃነት ያራምድ እንደነበረ ነው። (ይህ ከውጭ ሀገር ተልዕኮ



t.me/OLDBOOKSPDF

ተቀብሎ የመጣውን የአዞዎቹ (Crocodiles) አሰኳል (Squad) አይመለከትም። ይልቁን ፍትህ እኩልነት አንድነት አገብሮት ፊትለፊት የሚፋለመውን (Front Figures) እንጂ ልናዳብረው የሚገባውም መሠረታዊ ነገር ሀሳብና ስብዕናን፤ ሀሳብና ብሔርን ነጣጥለን አሸናፊው አሳማኝ ሀሳብ እንዲሆን መታገል ነው።

## 3.4 የሶማሊ የዘውግ ታሪክ ፀሐፊዎች

የሶማሊ ማህበረሰብ የኢትዮጵያን ድንበር በመጠበቅ ረገድ እና የኢትዮጵያዊነት ፍቅሩ በታላት የማይገለፅ ነው። ከሶማሊ ጋር አብሮ ለመኖር የታደለ ሰው የሚሰማው ምቾት/ እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው። ያለውን ተካፍሎ በመኖር በኩል ወደር የለውም። በታሪኩ የታየው ብቸኛ ጠባሳ በሶማሊያ ወረራ ወቅት ጥቂት የማህበረሰቡ አባላት ቀጥተኛም ሆነ ተዘዋዋሪ ድጋፍ ማድረጋቸውና የኦሮሚያን እመፅ ተከትሎ ሆነ ተብሎ በወያኔ እና የወቅቱ የክልሉ ፕሬዚደንት በነበረው አብዲ ኢሌ በተቀነባበረ ሴራ በክልሉ በሚኖሩ የኦሮሞ ማህበረሰብ አባላት ላይ (2016 - 2018) የከፋ ጥፋት መፈፀሙ እና በቀጣይም በጂግጂጋ ከተማ የሚኖሩ ሁሉም ብሔረሰቦች ተወላጆች ላይ (2018) የተነጣጠረው ጥቃት ነው። አብዲ ኢሌ በሠራው ወንጀል በቁጥጥር ስር ሲውል ተከትሎ በርዕሰ መስተዳድርነት ማዕረግ የተሰየመው ሙስጠፋ ዑመር (2018) በትክክል የሶማሊን ስነልቡና በተላበሰ መንገድ ከሶማሊ ተፈናቃዮች አስቀድሞ ለተፈናቀሉ የሌላ ብሔረሰብ አባላት በጀት መድቦ እርዳታ በማድረጉ አረጋግጧል።

የሶማሊ ዘውግ ፀሐፊዎች መነሻ ከብሪታኒያ ቅኝ አገዛዝ ዘመን እንቅስቃሴ ጋር በቀጥታ ተያያዥነት አለው። ብሪታንያ በቅኝ ግዛት ዘመን ትከተል የነበረው ስልት ከፋፍለህ ግዛው "Divide and Rule" ከመሆኑም ሌላ ጊዜ ጠብቆ የሚቀጣጠል ፍንዳ የሚዳፈን "Time bomb" ሴራ በመቅበር ትታወቃለች። ሶማሊያ በወቅቱ ከደረሰችበት ደረጃ አንፃር በጎሳ ንዑስ-ጎሣ እንድትከፋፈል አሉታዊ ሚና ተጫውታለች። መሪህን ዲጎዲያ ሀበርግድር ደቃል መሠሪ ሀዋልዶ ወራርሰሜ ሐውያ መጀሬ ገብራ ዳሮድ ኢሳቅ ገሪ እና ሌሎች ጎሳዎች በስፋት መኖራቸው ከፍፍል ለመፍጠር አመቺ መደላድል ሆኗል፡፡ (የሶማሊያ ህዝብ እንደሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች ሁሉ በተለያዩ ቅኝ ገገሮች ሥር መቆየቱ የሚዘነጋ አይደለም።)

የፀሐፊዎቹን መነሻ ከማስፈራችን በፊት የኢትዮጵያ መሪዎች ጠንካራ በነበሩበት ጊዜ ሁሉ የኢትዮጵያ የግዛት ድንበር ሜፍ እስከሆነው ዘይላ እና በርበራ ድረስ በመዳዝ ወደብነቱን የሚያስከብሩ እንደነበረ እና ሲዳከሙ መቆጣጠር እንደሚሳናቸው



t.me/OLDBOOKSPDF

የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ። በቅኝ ግዛት ዘመን ብሪታንያ ሶማሊያን በሙሉ አንድ ላይ አድርጋ ለመግዛት በነበራት ፍላጎትና ከቅኝ ግዛት በኋላም በሚከተለው ዓለማዊ ሁኔታ ፍላጎቷን ለማስከበር "ባለ አምስት ኮከብ ታላቋ ሶማሊያ" /"Five Stars Greater Somalia" ዓላማን ሰነቀረች። ይኸውም:-

1. በኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ ስር የወደቀውን ሶማሊላንድ፣

2. በብሪታንያ ቅኝ አገዛዝ ስር የዋለውን ፑንትላንድ፣

3. በፈረንሳይ ስር የነበረቺውን ጅቡቲን

4. በእንግሊዝ የቅኝ ግዛት አስተዳደር ምክንያት አሁንም ከኬንያ ጋር የተቀላቀለውን የኬንያ ሰሜናዊ የድንበር ግዛት "Northern Frontier District of Kenya" /NDF እና

5. ለዘመናት የኢትዮጵያ አካል የሆነውን ኦጋዴንን በአንድ ዣንጥላ ጠቅልሎ የመያዝ ፍላጎት ነበር።

በቅኝ ግዛት ዘመን ከተራ ቁጥር 1 - 4 የተዘረዘሩትን ከቅኝ አገዛዝ ነፃ ለማውጣት የሶማሊ የነፃነት ትግል በሰይድ መሀመድ አብዱላሂ ሀሰን መደረጉ እና ልጅ ኢያሱ ለመሀመድ አብዱላሂ ከፍተኛ ድጋፍ ማድረጋቸው ከመነሻው በሶማሊ በኩል ኦጋዴን ሀልውናዋ ከኢትዮጵያ ጋር መተሣሠሩን ለመቀበላቸው አንድ ማረጋገጫ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

ይሁንና የእንግሊዝን "የታላቅነት" መሻት ተከትሎ ዚያድ ባሬ በ1970ዎቹ አጋማሽ ኢትዮጵያን ከመውረሩ ሌላ የዘውጊዎች ሌላ መገለጫ የሆነውን የተፈጥሮ ሀብትን የአንድ አካባቢ ገዢ የመሆን ፍላጎት ተከትሎ የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃ አውጪ ግንባር (ኦብነግ) ተመሥርቷል።

ልብ ሊባል የሚገባው ነገር በአፄ ልብነ ድንግል እና ኢማም አህመድ መሀከል ሞጆ አዳማ ወይም ቢሾፍቱ አካባቢ የተደረገውን ጦርነት ተከትሎ በወቅቱ "በሰፍራው ኦሮሞ አልነበረም፣ ታሪካዊ ማረጋገጫም ማቅረብ የሚችል የለም" በሚል ስሜት በሶማሊ ዘውጊዎች በኩል 'እስከ አዋሽ ጫፍ የእኛ ነው' የሚለው ፍላጎት አሁንም



t.me/OLDBOOKSPDF

ያላበራ ከመሆኑ ጎን ለጎን በአማራ ዘውጌያኖችም ናገሬት ደብረዘይት አካባቢዎች የእኛ ናቸው የሚለው ፍላጎት ማቆጥቆጥ ጀምሯል። ያለመታደል ሆኖ እንጂ ሁሉም የእኛ ሆኖ ሳለ "የእኔ ብቻ" የሚለው ኋላቀር አመለካከት ዘመኑን አይዋጅም። "የነፃነት ግንባር" የሚል ቅዕል በሽታ ከተደነገረ ሁልጊዜም ስለሀገር ማሰብ ይከብዳል። "ግንባር" ሲቆይ እንደ አሚባ የመቆራረጥ የመጋጨት እና የመነጠል ደዌ በውስጡ ያዘለ ነው። በቅርቡ ኦብነግ ኢትዮጵያ ውስጥ በሀሳብ ወደ ተደራጀ ፓርቲ ለመለወጥ የወሰነው ታላቅ ውሳኔ እጅግ ወሳኝ እመርታ ነው። ሁልጊዜም ግንባር ካለ የግንባሩን ዓላማ የሚያቀነቅኑ ፀሐፊዎች ይኖራሉ።

አፅንኦት ሊሰጠው የሚገባው ነገር የሶማሊ የዘውግ ፀሐፊዎች መልእክታቸውን የሚያስተላልፉት በሶማልኛ በመሆኑ ከሁለት ጎራ የሚፈጠር ግጭት ስለማናዳምጥ ግለቱ አምብዛም አይሰማንም። የትግራይ ዘውግ ፀሐፊዎች ከጅምሩ አንስቶ የሚደቅኑት አደጋ በአማራ እና በኦሮሞ ስም መስለው ከመተውን ጎን ለጎን የሁለቱም ቋንቋ ተናጋሪዎች በብዛት በመኖራቸው በአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን) እና አንግ ስም ሀገር አፍራሽ መልእክቶች የሚያስተላልፉ መሆናቸው ነው።

የመጽሐፉ አዘጋጅ ከሶማሊዎች ጋር ከሃያ ዓመታት በላይ የመኖር እድል ስላጋጠመው እና ሶማሊዎች በሶማሊያ ያለውን መመሰቃቀል በመታዘባቸውና ከቀድሞ ጀምሮ በኢትዮጵያዊነታቸው ያጣጣሙትን ፀጋ ጠንቅቀው ስለሚገነዘቡ በሀገራቸው እንደማይደራደሩ በሚገባ ይገነዘባል። ምንም እንኳአንዳንድ የዘውግ ጸሀፊዎች የእንግሊዝን የታላቋሶማሊያ ህልም የሚያራምዱ ቢሆንም:: ሆኖም የእናታቸው ኢትዮጵያና የጎረቤታቸው ሶማሊያ ድንበር በሰላማዊ መንገድ ተሰምሮ እፎይታን ማግኘት እና መልካም ወዳጅነት መፈጠሩን ሊያሰምርበት ይፈልጋል። ፒዬሬ ፔትሪዲሽ፦ "The Boundary Question Between Ethiopia and Somalia" በተሰኘው ጦማሩ በአድዋ ድል ማግሥት የድንበር ማካለሉ ፍላጎት ከኢትዮጵያ ይልቅ በአካባቢው ያሉ ሀገሮችን ከተቆጣጠሩ ቅኝ ገዢዎች (ብሪታንያ ፈረንሳይና ጣልያን) መመንጨቱን አስረግጦ ጽፏል።

በአሁኑ ሰአት ሶማሊያ የአልሸባብ መፈንጫ እና ሥርአተ አልበኝነት (Anarchy) አስተዳደር የሰፈነባት ከስም በዘለለ ጠንካራ አስተዳደር መመሥረት ያልቻለች (Failed State) አቋም ላይ ትገኛለች። በቀጣይም በሶማሊያ ከሶማሊያ ውጪ የራሳቸውን ጠንካራ መንግሥት የማቋቋም ፍላጎት ያላቸው ሶማሊላንድ እና ፑንትላንድ ፍላጎት ተጠንቶ የማይደረግ ስምምነት ፍፃሜው ስለማይሠምር የትኛውም



t.me/OLDBOOKSPDF

ስምምነት ዘሩያ ገባውን ቃኝቶ እና በበቂ ሥጋት ላይ ተመሥርቶ በሚደረግ ትንተና የታገዘ መሆን ይገባዋል። ለብሔራዊ ጥቅሞችን (National Interest) ቅድሚያ የመስጠታችንን ያህል የጎረቤቶቻችንንም ዘላቂ ጥቅምና ሰሚት ማጠንን ይጠቅማል። ምክንያቱም የትኛውም ስምምነት ነገን ታሳቢ ሳያደርግ ከደከሙ ኃይሎች ጋር 'የጊዜን አንፃራዊ ምቹ እድል በመጠቀም' ከተደረገ ውሎ አድሮ 'ተጠቃን' ከሚሉ ወገኖች ችግር መደቀኑ አይቀርም።

### 3.5 ሌሎች የዘውግ ጸሐፊዎች

የሲዳማ አርነት ንቅናቄ (ሲአን)፣ የጋምቤላ፣ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ እንዲሁም በተለይ ስያሜዎች የሚንቀሳቀሱ ቡድኖች መጠኑ ይነስም ይብዛ ከላይኞቹ የሚጋሯቸው ባህርያት አሏቸው። አንዳንዶቹ በድንበር ወሰን አካባቢ የሚገኙ ከመሆናቸው የሚዘመድ የራሳቸው መለያ መገለጫዎች ይኖራቸዋል። በድምሩ ሲታይ ዘውጎችን የሚያመሳስሏቸው መገለጫዎች የራሳችን ከሚሉት ቡድን ውጪ ሌሎችን የመግፋት፣ ፍላጎታቸውን በሀይል ለመጫን መሞከር፣ በውይይት ሳይሆን የመንግሥትን እጅ በመጠምዘዝ ዓላማቸውን የማሣካት ፍላጎት፣ በተዕዕኖ ፈጣሪ ግለሰቦች የሚዘወሩ መሆን፣ ህቡዕ አደረጃጀት መያዛቸው፣ በውጭ ሀይሎች ፋይናንስ የሚደገፉ መሆናቸው፣ ነገ እርስበርስ የሚጋጩ መሆኑን እየተረዱም ጊዜያዊ ጥምረት መፍጠር፤ አብሮነትን የሚያቀጭጩ መሆናቸው፣ ለሀገር ደንታ የለሽነታቸው ሊወሱ ይችላሉ።

ከታሪክ ጠቀሜታዎች አንዱ ያለፈውን በማጥናት ደካማና ጠንካራ ጎኑን በመፈተሽ ከዛም ትምሕርት በመውሰድ ለመጪው ትውልድ የተሻለ ዓለም መፍጠር ነው። የዘውግ አደረጃጀትበተቃራኒው ከታሪክ አንከን በመፈለግ የተበዳይነት ስሜት መፍጠርና ያንንም ለጥላቻና ቂምበቀል በማዋል ወደ መጠፋፋት ሕዝብን የሚመራ ነው።ዘውጌነት በብዙ መመዘኛዎች ዘመኑን ያልዋጀ፤ ለቀጣዩ ትውልድ ከጠቀሜታው ጉዳቱ እጅግ ያመዘነ በመሆኑ በጊዜ መላ ሊበጅለት ይገባል። ሀገርን በመከፋፈል ብቻ የሚጠናቀቅ ሳይሆን በመሬት ይገባኛል ጥያቄና በጥላቻ በቀላሉ ወደማያባራ የእርስበርስ ጦርነት የሚከት ነው። በመሆኑም የብሔረሰብን ፓርቲዎችን በአንድ ጊዜ ሳይሆን በሂደት (ባልፈጠነ ባልዘገየ) በቂ መግባባት ፈጥሮ በህግ ከማገድ ጀምሮ አፍራሽ እንቅስቃሴያቸውን ተደራጅቶ በጋራ መመከት ያስፈልጋል።

ሀገራዊ አንድነትን የሚደግፈው ህብረተሰብ በዘውግ መደራጀት ከሚፈልገው የበዛ መሆኑ ቢታወቅም እንደ ዘውግኞቹ በበቂ ጥንካሬ የተደራጀና በቀላሉ በስሜት የሚነዳ



t.me/OLDBOOKSPDF

አይደለም:: ሥርአቱ አገራዊ አደረጃጀት ላይ ከፍተኛ ጫና ያደርስ ስለነበር ኢትዮጵያን እንደሀገር በአንድነት ለማስቀጠል የሚፈልገው ብዙሀን የረባ አደረጃጀት የለውም:: ስለዚህ በሕገ መንግሥት የተደገፈውን ሀገርን በተፈለገ ጊዜ ብዙ ትናንሽ ሀገሮች የማድረግ የጥፋት አካሄድ ለመመከት ያለው ምላሽ ተጠናክሮ አይታይም:: ኢትዮጵያ እስካሁንም እንደሀገር ጸንታ የቆመችው በዘመናት በጥበብ የተገመደ የሕዝብ ለሕዝብ ትስስር ስላለና በእግዚአብሔር ጥበቃም ጭምር እንጂ ኢትዮጵያን ለማፍረስ እንደተነሳው የወያኔ መንግሥት ሴራና እንደፈጠረው አደረጃጀት፤ እንዳስፋፋው የጥላቻና የዘውጌነት ትምሕርት ኢትዮጵያን እንደሀገር ማስቀጠል የማይታሰብ ነበር::

ያለቺን አንድ ሀገር ኢትዮጵያ ብቻ የሆነችና ለህልውናዋ ዘብ የምንቆም ሁሉ ልብ ልንለው የሚገባን ጉዳይ ዓለም ሰላሙን ያረጋገጠው በጎሳ ፖለቲካ ሳይሆን በአመክንዮ ላይ የተመሠረቱ ፓርቲዎችን በመፍጠር ነው። በሰለጠነው ዓለም እንዳለው ሪፐብሊካን፣ ዴሞክራቲክ፣ ሊበር፣ ሊኪውድ፣ ወግ-አጥባቂ፣ ሶሻል-ዴሞክራት ወዘተርፈ አይነት በአመለካከት ላይ ብቻ የተደራጁና የአንድነት መንፈስን የሚያጠናክሩ ፓርቲዎችን አደረጃጀት መከተል ይበጃል። በሀሳብ ከተደራጀን ልዩነቱ በምክንያት ላይ የተንተራሰ፣ ፍጭቱ ከአመለካከት፣ መነጋገሪያው ተጠየቃዊ አካሄድ ይሆናል። በአንፃሩ በብሔረሰብ ስንደራጅ ልዩነቱ መንጋዊ፣ ሀቡ ከማህበረሰብ ጋር፣ መነጋገሪያው ነፍጥ ዱላ ገጀራ እና ሜንጫ ይሆናል:: ከመሀከለኛው ዘመን በጎሣ የመጀመል ጉዞ ተላቅቀን ወደ 21ኛው ክፍለ ዘመን የሰውነት የዜግነት የተሻለ አስተሳሰብ አሸናፊነት ሽግግር ውስጥ እንድንገባ ጠንካራ መንግሥትን አቅጣጫ የሚያሳዩ ቡድኖችን መፍጠር ያስፈልጋል።

## የዘውግ ታሪክ ጸሐፊዎች 'የታሪክ ሽሚያ'/ መቀራመት

የጎሣ ታሪክ ጸሐፍት የሚከተሉት የታሪክ አጻጻፍ መነሻ "ሞዴል" የላቸውም። እንኳን እንደ ኢትዮጵያ የተሠናሠለ፣ ለመለየት የሚያስቸግር፣ የአንዱ ታሪክ ከሌላው ለዘመናት በሥልጣኔ፣ በእምነት፣ በባህል፣ ሀገርን በወል በመታደግ፣ በጋብቻ፣ በአንድ አስተዳደር ስር በመተቃቀፍ የተሣሠረ ህዝብ ቀርቶ በቅርቡ ቅኝ ግዛት ገጣጥሞ የሠራቸው ሀገራት ታሪክ የጋራቸው ነው። ኢትዮጵያውያን ከሌላው ዓለም ተለይተን



t.me/OLDBOOKSPDF

በጤፍ ጭምር አስደናቂ ህብር አለን። የእንሰት ባህል፣ ክትፎ፣ ዶሮ ወጥ፣ አምባሻ፣ ጨጨብሳ፣ ቋንጣ፣ ጥሬ ስጋ፣ ጠላ፣ ድፎ ዳቦ፣ የባህል አልባሳት፣ ተነግሮና ተዘርዝሮ የማያልቅ ህያው ጥምረት አለን። አባት እናቶቻችን መሪዎች ምን ቢከፉ በህብረታቸው ተደራድረው አያውቁም።

የቀድሞ የዩኒቨርሲቲ፣ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች፣ መምህራን፣ ላብአደሮች ሲያምፁ አንድ ላይ - ሲነሡም በጋራ ነው። በኢህአፓ አደረጃጀት መዱ ሺህዎች መስዋዕትነት ሲከፍሉ ደማቸው የፈሰሰው በብሄረሰብ ተለይቶ ሳይሆን በህብረት ነው። ሀገርን በመጠበቅ ብቻ ሳይሆን በዓላማ አንድነትንም ተነባብረው ወድቀዋል። ሀገርና መንግሥት በአንድ ድንበር አልተገነቡም። ታሪካዊ መገፋፋት በመላው ዓለም እና እንቅስቃሴዎች ሲኖሩ የማይቀር ነው። እንደመታደል ሆኖ የኢትዮጵያውያን ታሪክ ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል ደረጃ የፍቅር ሆኖ ስለሆነ የጦር አበጋዞች በውስን ጊዜና በጥቂት ቦታዎች ያደረጓቸው ግጭቶች ሊሸፍኑት አቅም የሚያጡበት እውነት ነው። በጋራ ታሪካችን መድመቅ ሲቻል በተናጠል ታሪክ መውተፍተፍ ለምን አስፈለገ?

የዘውግ ታሪክ ፀሐፊዎች በአብዛኛው ፅሑፎቻቸውን የሚያዘጋጁት ህዝብንና ሀገርን አማከለው ሳይሆን በአንድ ጎሳ/ብሔረሰብ ላይ ተንጠልጥለው ነው። 'የበታችነት ስሜት' አብዝቶ ስለሚያጠቃቸው አንዳች አስተዋጽኦ ያላደረጉበትን የትላንት ደማቅ የጀግንነት ታሪክ ፈፃሚ ትንታግ ጎትተው ወደነርሱ ቅርጫት ለመክተት ይጋጋጣሉ። ሽንቁር ስብእናቸውን ጀግና በመበደር ይሞሉት ይመስል ታሪክን መዋስ ላይ ይጠመዳሉ። የደካማነታቸውን ልክ በተወሰኑ ማሳያዎች እናስረዳ፡-

**1. ደጃዝማች በላይ ዘለቀ ላቀው (የፈረስ ስሙ አባ ኮስትር)**

አባ ኮስትር በላይ ከ1936 - 1941 የጣሊያን ፋሺስት ሠራዊት ኢትዮጵያን በወረረበት ወቅት እንደ አርበኞች ሁሉ ሀገር ለመታደግ በዓባይ በረሀ ውስጥ መራር ተጋድሎ አደረገ። ለአምስት ዓመታት በጣሊያን የጦር ሠፈር አደጋ በመጣል፣ እንቅስቃሴያቸውን በማስተጓጎል፣ 'ካሚዮኖቻቸውን' (ከባድ የጦር መጓጓዣ መኪናዎቻቸውን) በማቃጠል፣ በከፍተኛ ወኔ አኩሪና አንፀባራቂ ገድል ፈፅሟል። "አባ ኮስትር" በሚል ርዕስ በተገፈ ጦማር እንዳነበብነው፡- 'ጣሊያኖች ሴት ልጅን በማገት እጅ ካልሰጠ እንደሚገድሉት ሲዝቱበት እንቅጩን የነገራቸው 'የኢትዮጵያ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሲያት ልጆች በሙሉ የእኔ ናቸው። ለአንድ ልጄ ስል መላውን የኢትዮጵያን ሴቶች፣ ከምንም በላይ ሀገሬን ኢትዮጵያን አሳልፌ አልሰጥም በማለት ነበር።

በላይ ዘለቀ ኢትዮጵያዊነት ከነፍስና ሥጋው ጋር የተሸመነች ናት። የወረደ ማንነትና ለበላይ ሥነልቡና አይመጥንም። በቅርቡ እንደሚታየው የበላይን የትውልድ በመፈለግ ዘውጌዎች የበዛ የታሪክ ሽሚያ ውስጥ ተነክረዋል። በመግለጫ ለማሳየት፦ የኦሮሞ ዘውጌዎች "በላይ ዘለቀ ቁልጡ የተባለ የወሎ ኦሮሞ ነው" በማለት ለጀግናው ኢየት ብድር ፍለጋ ሲዳክሩ፣

የትግራይ ዘውጌዎች ደግሞ፦ "እየው፣ ከትግራይ ወደ ጎጃም ለአደን ሄደው ጎጃም ቀሩ።" ይሉናል። በላይ ዘለቀ ጣሊያን አሻራውን እንዳያሳርፍ ያደረገው ምሥራቅ ጎጃም ውስጥ ነው። በላይ የተዋጋው ጎጃም (ከኢትዮጵያ ውስጥ በአንዱ) አፈር ላይ ቆሞ ለኢትዮጵያ መሆኑ አያጠያይቅም። የበላይ የአመራር ጥበብና ጀግንነት የሚያጠያይቅ ሆኖ ከእስር ቤት አምልጦ ለመጥፋት በሞከረበት ወቅት ወደ ገበያ የሚሄዱ ገበሬዎች ይዘው ለዐፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት አስረከበውታል። ብርታቱ፣ አምስት ዓመት ሙሉ ከጎኑ የተሰዉ የጎጃም ፋኖዎች መሆናቸው ማምት አይገባም። ማንነት ከመኖሪያ አካባቢ መስተጋብር (Nurture) እንጂ ከደም (Nature) እንደማይያያዝ ለመረዳት አስቸጋሪ አይደለም። ሲጀመር በላይ የተዋደቀው ለኢትዮጵያ ነው። ሲቀጥል የታገለው ከጎጃሞች ጋር በመሆን ነው። ሲሠልስ ደሙም ማንም ጎጃም ነው።

ለመሆኑ ኦሮሞ ከአብዲሳ አጋ፣ ገረሡ ዱኪ፣ ጃገማ ኬሎ፣ አቢቹ፣ አቡነ ጴጥሮስ ጀምሮ ዛሬ እስካሉት ሚሊየኖች ጀግኖች መሀከል መች ጀግና አጥሮት ታሪክ ብድር እንዞራለን? በሌላ በኩል ከትግራይ የበቀሉ እነ ካሳ ምርጫ፣ አሉላ እንግዳ(አባነጋ) … የመሰሉ ጀግኖች እያሉት ለምን ጀግና ፍለጋ ሌላ መንደር ይኬዳል፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ጀግና ያላበቀለ ብሄረሰብ ማግኘት ፈጽሞ አይቻልም፡፡ ማሳየት የተፈለገው የእኩያኑ ዓላማ ታሪክን ማወቅ ሳይሆን በአንድ በኩል 'የዐማራ ታሪክ' የሚሉትን ባዶ ማድረግ እና 'የኦሮሞ ታሪክ'፣ 'የትግራይ ታሪክ' ያሉትን ማግዘፍ፣ መነሻው ጥላቻ፣ መድረሻው የኢትዮጵያን የጋራ ታሪክ በመሸርሸር ኢትዮጵያን ለማፍረስ የሚረዳቸው የተናጠል ታሪክን ማጠናከር ነው። ለዚህ ነው ደጋግመን በወል የኢትዮጵያ ታሪካችን ሳንደራደር የእናት ሀገራችንን ታሪክ ለመጠበቅ መፋለም ያለብን።



t.me/OLDBOOKSPDF

## ፪. መድሎው ጻማግዊ እንዲ ቴዎድሮስ (በፈረስ ስም ታጠቅ)

በየምክራቱ ቦታዎች በአዳራት የተሰጡት ሆኖ በስብስባቸው መንግሥታት ላይ በመንቀሳቀስ የቅማይዎ ፅንፈኛ በሌሊዎች "መንግሥታቸው ከእኛ ነው" ሲሉ መስማት ፈጽሞ ያስገኛል። ቴዎድሮስ ጳት "እኔ የኢትዮጵያ ባሪያ፣ የኢምፔሪያሊዝም አፈርሳጊ" ራዕዮቸው የሚታወቁ እንጂ የጎጥ ማንበር የመሠረት አይደሉም። የማንነት ተጠሩስ ሲታዩ በጣም ብዙ ነው። የቻግሩ ምንጭ የከረረ "የብሔርተኝነት ስሜት ነው።" በማንስ ስሜት መሰታየት የሁሉም ጎሳዎች የጋራ መገለጫ ነው።

## ፫. ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ (የፈረስ ስም ጠቅል)

ከአብዛኛው ምሁሩ ጀምሮ የኛ ብቻ ነው የሚሉት፣ የአማራ ፅንፈኛ ዘውጎች ተፈሪ መኮንን ዋሚ ጉዲሣ እናታቸው የሺመቤት አሊ አባጅፋር መንሽታቸው ከኤጀርሳ ጎሮ አድጊቶቻቸው ሐረርና የሁሉም በሆነችው አዲስ አበባ የሆነ፣ የትውልዳቸው በማያሻማ መልኩ ኦሮሞ የሆነና ጥቂትም ቢሆን ስሜታቸው ወደ ሸዋ አያደላ፣ ዙፋናቸውንም በአመቻቹ በሸዋ ገቢ እና ሊቀ መኳንንቶቻቸው ግልፅ ሆኖ ሳለ በሁሉም ዘውጎች "አማራ ናቸው" በማለት የሚያንፀባርቁት የጠቅላይ ስሜት "ከብሔርተኝነት" የሚመነጭ 'ሁሉም የእኔ' ስሜት ነውና አጠንክረን ልንታገሠው ይገባል።

ዓለም የዘመናት ቁርሾውን አስወግዶ በፍቅር በሚኖርበት 21ኛው ክፍለዘመን (እንግሊዝና ፈረንሳይ የመቶ ዓመታቱን ጦርነት ከ1337 - 1453 እና የዘመናት ግጭቶቻቸውን ላያስታውሱ ዘግተው እና ድንበራቸውን የአስተዳደር ወሰን ያህል ቀንሰው ጠንካራ ሁለንተናዊ ግንኙነት መሥርተዋል። ሩዋንዳ በ1994 የሁቱ ብዙኃን በመቶ ቀናት ብቻ 800,000 ቱትሲዎችን ጨፍጭፈው ወላፈኑ ሳይሆን ረመጡ ለብልፅግናቸው ዛሬ ስለ ብሔር መናገር ነውር መሆኑን ደንግገዋል። ደቡብ አፍሪካ ከ1948-90 የቆየውን አጅግ አሰቃቂ ጭፍጨፋ "የጥቂት ነጮችን አገዛዝ የምጠየፈውን ያህል - የብዙኃን ጥቁሮች አገዛዝ ያቅለሸልሸኛል" ጠንካራ መልዕክት ባስተላለፉት እና 27 ዓመት ሮቢን ደሴት በታሠሩት ማንዴላ ተዘግቶ ዛሬ ሚሊየኖች ነጮች ከሚሊየኖች ጥቁሮች ጋር በፍቅር ይኖራሉ።) የኛ ዘውጎች ቁልቁል ወደ ጥንት አስተሳሰብ ተመልሰው ከዘመን ባፈነገጠ መንገድ ሀገር ሲያተራምሱ ስናስተውል ከኋላ የሚያንቀሳቅሳቸውን ፔትሮ ዶላር፣ ካፒታሊስታዊ እና ግብፅ - አረብ ኃይል ፍላጎ አሠሣችንን አጠናክረን እንቀጥላለን።



t.me/OLDBOOKSPDF

### ፪. ሙያተኛ ታሪክ ጸሐፊዎች (Professional Historians)

በዚህ ምድብ ሥር የሚጠቃለሉት በታሪክ ትምህርት ዘርፍ የመጀመሪያ ዲግሪ፣ ሁለተኛ ዲግሪ እና ሦስተኛ ዲግሪ ከነሙሉ ክብሩ ጥቅሙና ጉዳቱ እውቀና ካላቸው ከፍተኛ መካከ ትምህርት በክብር በመመረቅ በዘርፉ የተመረቁ ናቸው። እነዚህም በታሪክ ዘርፍ የተባበ ጥናትና ምርምር በማድረግ ሥራዎቻቸውን በተለያዩ የአቅመው መጋዘኖችና በውጭ ጥናቶች በማቅረብ ለዘርፉ መጎልበት ታላቅ አስተዋፅኦ አድርገዋል።

ቀደም ብለን ለማሳየት እንደሞከርነው የኢትዮጵያ ታሪክ እንደዚህ ቀጥ አድርጎ ለመፃፍ ደርግሰው ገብተው የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት በሚጥሩበት መካከል ለማረቅ ጥረት ባለማድረጋቸው ግን ከተወቃሽነት አይድኑም። በታሪክ ትምህርት ዘርፍ የሚገኙ ምሁራን ከአብዛኞቹ የትምህርት ዘርፎች ምሁራን ጋር ሲነፃፀሩ ራሳቸውን ከመዘግብት ጋር በማቆራኘት ረገድ ተስተካካይ አይኖራቸውም ብንል ይህንን አይመስለኝም። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ታሪክ ትምህርት ክፍል ገብቶ የተማረ ብቻ ሳይሆን ጎረቤትም ያለ እንደሚገነዘበው ምሁራኑ የመጽሐፍት፣ መረጃዎችና ማስረጃዎች ማህደር (Bookworm) ናቸው። ፖለቲካ አካዳሚያዊ ነፃነትን በሚጋፋበት ሀገር የታሪክ ምሁራን ከሙያው እንግዳ ጥንቃቄ የሚያደርጉ ቢሆንም የውድን ፍላጎት የሚያጠቃቸው አልፎ አልፎ መታየታቸው አለመን ነው። ምሁራኑ በሁለት ሲከፈሉ፡-

የመጀመሪያው ምድብ፡-

የዘመኑ ፖለቲካንና የሶሻሊስታዊ ፍልስፍናን እያጣቀሰ የሚጓዝ ሆኖ አብዛኛው ከሙያው ርቆ ፖለቲካን መተዳደሪያው ያደረገ፣ ውሎው ከመጻሕፍት ሳይሆን ከፖለቲከኞች ጎራ የሆነ፣ ከብርና ዝና ያገኘ መስሎት በራሱ ስብሰብ የሚወደስ በጅማው የሚወገዝ፣ የስብእና ችግር ተጠቂ ነው።

ሁለተኛው ክፋይ፡-

በተቻለ አቅም ሁሉ ራሱን ከጎሣ ፍላጎት እና ከፖለቲካ መሻት ተላቅቶ በታሪክ ትምህርት ዓላማ መሠረት የሚታገሉ (Liberal Historians) ናቸው። የልዕልና ደረጃቸው ከፍ ያለ እንዲሁም አብዛኞቹ በሀገር ውስጥ ባሉ መካነ ትምህርቶች ለለውጥ የሚማስኑ ቢጠቀሱ ሲያንስባቸው ነው። ከነዚህ መሀከል፡- ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ፣ ፕሮፌሰር ተሰማ ተዓ፣ ፕሮፌሰር ሺፈራው በቀለ፣ ፕሮፌሰር አየለ በከሪ፣ 'ተባባሪ ፕሮፌሰር' / ዶክተር ተካልኝ ወልደማርያም፣ 'ረዳት ፕሮፌሰር' አበባው



t.me/OLDBOOKSPDF

አይደለም እና ዕውቅና የሚሰጡአቸውን የማርክሲስቶችን ትንታኔ ሊጠቀሱ ይችላሉ። በሀገራችን ከሌሎች መካከል ፕሮፌሰር ሺፈራው በቀለ፣ ፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት፣ ፕሮፌሰር ሙሉጌታ እና ፕሮፌሰር መርዕድ ወልደአረጋይ ፈለግ ከሚያዘነብሉት መካከል ናቸው።

ሌላ አመለካከት ደግሞ ታሪክ ሲፃፍ በዘረ-ቀደ መሆን እንደሚገባው ይታመናል። ከዚህ አንፃር የታሪክ ጉዳዮች የማህበረሰቡና የመሪዎች የግንዛቤ ደረጃ፣ የግል ፍላጎቶች፣ የተወሰዱ እርምጃዎች እንዲከሰቡ ገፊ የነበሩ ምክንያቶች፣ ርዕዮተ ዓለም ሊያስከትል የሚችለው አሉታዊ ተፅዕኖና በመፈፀሙ የነበረው አንድምታ በጥልቀት፣ የነበሩ ምክንያቶች፣ የጠቀሙ ማለፊያ ግብኑቶች ያላደረጉ ... የርዕዮተ ዓለማዊ ፅንፍ መካከር እና በነርሱ ማህበረሰብ ውስጥ ቆም ማለት አስፈላጊ በሆነበት ይጠቀሳል። የታሪክ ምንጮችን ሳይመዝኑና ሳያመዛዝኑ በምንተረጎም መንገድ የሚፃፉ ድርሳናት የሚደቅኑትን ፈርጀ ብዙ አደጋ አለማጤን መዘንጋት ነው።

ታሪካችን በቀደሙ ክፍሎች በገለፅነው መሠረት ተሟልቶ አልተፃፈም። ፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ "Society, State and History" በተሰኘው ሥራ ያለ የምርምር ሥራቸው እንዳብራሩትና መሬት ላይ ያለው ሀቅ እንደሚነግረን በሀገር ውስጥ በከፍተኛ ዲግሪ ደረጃ የታሪክ ትምህርት መሰጠት የተጀመረው በ1979 ሲሆን እና የዶክትሬት ዲግሪ ትምህርት ደግሞ በ1990 ከመሆኑ አንፃር የጥናት ሥራው በጨቅላ ደረጃ ነው። የታሪክ ትኩረት በፖለቲካ ላይ ያጠነጠነ ከመሆኑ ተላቅቆ በተወሰነ ደረጃ ወደ ማህበራዊ ታሪክ ማማተር ቢጀምርም፣ ምጣኔ ሀብታዊ (ኢኮኖሚያዊ ታሪክ) በሚል ተገቢና አፍን ሞልቶ ለመናገር የሚያስችል ሥራ የለም። (ገፅ 28)

የታሪክ ፀሐፊዎች ፖለቲካው ላይ መንጠልጠላቸውና ሌሎች፣ ባህላዊና ማህበራዊ ታሪኮች መዘንጋታቸው፣ በተለይም ምጣኔ ሀብታዊ ታሪክ መገፋቱ በታሪክ ትምህርት ክፍል ግንዛቤ ተደርጎ ነበር። ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ ሁኔታውን በዕሎሳቸው ሲያብራሩ በ1983 በተካሄደው ሁለተኛው የታሪክ ትምህርት ክፍል ጉባዔ፡- "There is nothing more solid than land and there is nothing more concrete than food" የውይይቱ መሪ ቃል ነበር። ይህም ተመራማሪዎች ወደ ምጣኔ ሀብት ታሪክም እንዲያዘነብሉ አድርጓል። እስካሁን የተገፉት "የኢኮኖሚ ታሪክ" የሚል ርዕስ ቢሸከሙም ይዘታቸው ግን ከርዕሳቸው አብሮ አይሄድም ሲሉ ያስገነዝባሉ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ከዚሁ ጋር ባህላዊ ታሪክ ላይ የራሳቸውን ድርሻ የተወጡትን በትድሳት ሥላሴ ከቴድራል አስማቾቸው ያረፈውን ወይዘሮ ሲልቪያ ፓንክረስትን፣ በማህበራዊና ሲሉቻ ከቴቻ ዘሬያ ዳናቸውን ያሳረፋትንና እናታቸው ጎን አስማቸው በክብር የኖረውን ልጃቸውን ፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስትን እና በ"ተገለሉ ህዳጣን ማህበረሰቦች" ላይ በመመርኮዝ አሻራቸውን እያተሙ የቀጠሉትን የልጅ ልጃቸውን ዶክተር አሉላ ፓንክረስትን በወፍራሙ አለማመስገን ንፉግነት ነው። እንደ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ እምነት የኢትዮጵያ ታሪክ አፃፃፍ መሠረታዊ ችግሮች፦ ማዕከላዊ መንግሥት ላይ ማተኮር፣ ፖለቲካ ላይ የተንጠለጠለ አቀራረብ፣ ወደ ርዕዮተ ዓለም ማዘንበል፣ የአውሮፓውያንን 'ሞዴል' (የአፃፃፍ ዘይቤ.) መከተል እና የውጭ የታሪክ ምንጮች ላይ መመርኮዝ ነው። (*በነገራችን ላይ ታሪክን ወደ ዓላማው ለማድረስ የተለየ የአፃፃፍ ስልት መከተላችን መልካም መስሎ ታይቶናል።)



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ሁለት

# የደማቅ ታሪካችን ሰበዞች

## የታሪኩ መነሻ

በኢትዮጵያ የረጂም ዘመናት ታሪክ አበው ወእመው ታላቅ ሀገር ያስረከቡን ያለ ውጣውረድ መንገዱ አልጋባልጋ ሆኖላቸው አይደለም፡፡ ዱዋ ጥሰው፣ ጤዛ ልሰው፣ ድንጋይ ተንተርሰው፣ በአስቸጋሪ የጦርነት ውሎ ከአንድ ኮዳ ጠብታ ውሀ ተቃምሰው፣ ደረቅ ቆሎ ተጎራርሰው፣ በአንድ የቀበሮ ጉድጓድ ወይም ተራራ እና ሸንተረር ጎን ለጎን ወድቀው፣ አጥንታቸውን ከመሀከል ሀገር ጀምሮ በአራቱም ማዕዘናት ከስከሰው፣ ደማቸው በየፈፋዎች ፈስሶ ጅረት ሠርቶ በላባቸው እንጥፍጣፊ ኢትዮጵያ የምትባል የብዙኃን እናት ሠርተው ነው። የሀገርና የመንግሥት ምሥረታ ወመሠረት ዋልታ ማገር ወጪ ወራጅ ጣራ እና ከፈፍ በዋዛ ዛሬ ቁጭ ብለን እንደምናወጋው በቀላሉ የሚከወን አይደለም። እንኳን ሀገርን በአንድ ጥላ ሥር አሰባስቦ ማፅናት ይቅርና አንድ የዘመመ ጎጆ ማቆም ቀላል አለመሆኑን ለመግለፅ የሀገራችን ሰው 'ቤት ሠሪ ደም የለውም' ይላል።



t.me/OLDBOOKSPDF

አባት አናቶቻችን ከወረሷቸውም የበቀሉ ጠቢባን በሥነቃል እና በአደጥበብ ከብረው ባለፀጋ እንደመሆናቸው 'አጃኢብ' የሚያሰኝ የገዳ ሥርአት ዘርግተው፣ የሚያስደንቅም ንድፍ ነድፈው ያቆዩልን ዛሬም የምንደምቅባቸው የጥበብ ልብሶች (ጋቢ ነጠላ ኩታ ጃኖ በርኖስ ካባ ቀሚስ) ሠርተው፣ ሥዕል ስለው፣ ቁም ፅህፈት ፅፈው፣ ሐረግ ጥለው፣ ድጓ ጾመ-ድጓ መዋስዕት ዕፈው፣ ግዕዝ ዕዝል እና አራራይ ዜማ ደርሰው (ምልክት 'ኖታዎች' አበጅተው)፣ መስቀል ኩስኩስት በናዕል መቋሚያ በኩሌቁ ከለቻ መከዳ ሶሮራ ቁዱ ማጨራ ቀርፀው፣ መፃሕፍትን ጠርዘው ደጉሰው፣ ብረት አቅልጠው አፍስሰው፣ የወርቅ የብር የነሐስ ሳንቲሞችንና ገጣጌጥ ሠርተው፣ ሉል አዘለል ዘውድ ቆብ አበጅተው፣ ወላንሳ ስጋጃ ብሰጥባሳጥ ዳህኒ ቅጥኒ መከሞኒ ሐር ሠናፊል ሠርተው፣ ነፍጥ ጠርቀው፣ ቀስት መሶብ ጋሻ መስጎድ ጨቢ ሰይፍ ጎራዴ ሜንጫ አዘጋጅተው፣ ድንጋይ አለት ወቅረው፣ በገና ደርድረው፣ ከራር ከርከረው፣ ዋሺንት ቱልቱላ መለከት እና እምቢልታ ነፍተው፣ ነጋሪት ነስመው፣ ከበሮ መትተው፣ ከዋክብት ቆጥረው የዘመን ቀመር ሰይተው፣ ጀርባቸውን ሳይሆን ግንባራቸውን ለጥይት አረር ሰጥተው፣ ለሀገራቸው ሉዓላዊነት እንደ ሻማ ነድደው፣ እንደ ጧፍ ቀልጠው በፀጋ አልፈዋል። ያልተዘመረላቸው በርካታ የሀገር አውራዎች ባከበሯት ሀገር እኛ የዘመን ተረኞች ለታሪክ ፍርድ በትላንትና በነገ መሀከል ቆመናል።

ኢትዮጵያ ሀገራችን በዓለም ታሪክ ሁለት ዋነኛ የዘመን ብያኔዎች ያላት ድርሻ ምን መልክ አለው? የሚለውን መሠረታዊ ጥያቄ መመለሥ ለቀጣይ ገለፃችን እብሪ ጥይት በመሆን ያገለግላል። በዓለምአቀፍ የታሪክ መከፈያ ድንጋጌ መሠረት የሰው ልጅ ታሪክ በሁለት ዋና ዋና አዕቆች ቅድመ ታሪክ እና ታሪክ ተብሎ ተለይቷል። የመጣመሻው መሠረት የዛሬ 6,000 ዓመት በጥንቷ ሜሶፖታሚያ የዛሬዋ ኢራቅ የተጀመረው 'ኩኒይፎርም' የተባለው ሥዕላዊ የአፃፃፍ ዘዴ ነው። ከዚህ አኳያ ከ6,000 ዓመት በፊት ያለው ጊዜ "ቅድመ-ታሪክ" - ከድንበሩ ወዲህ እስከ ቅርብ ጊዜያችን ያለው ትላንትና ደግሞ "ታሪክ" ይባላል።

## ቅድመ ታሪክ

የአርኪዎሎጂስቶች ጥናትና ምርምር ውጤት እንደሚያመላክተው የምሥራቅ አፍሪካ ስምጥ ሸለቆ ባጠቃላይና ኢትዮጵያ በተለይ የሰው ልጅ መሠረተ-ግንድ "ምድረ-ቀደምት" የሚል ስያሜን በሚያሻማ መንገድ ተጎናፅፋለች። በሀገራችን የአርኪኦሎጂ ምርምር ተቋም በ1952 ከተመሠረተ ወዲህ በዘርፉ አስደናቂ ውጤቶች ተመዝግበዋል። ተቋሙ የሁለት አሥርት ዓመታት ጉዞን እንዳገባደደ በ1974 ዓለም



t.me/OLDBOOKSPDF

ጋዎ በኋላ

የሚኮሩበት ግኝት ይፋ ሆነ። በአፋር ክልል ልዩ ስሙ ሀዳር በተባለ ሥፍራ በዶ/ር ጆሀንሰን የሚመራ የጥናት ቡድን 3.18 ሚሊየን ዓመት እድሜ ያስቆጠረች በግምት 23 ዓመት የሚሆናት ኮረዳ አፅም አግኝቷል። የተገናኘው ቅሪት አካል 40 እጅ የተሟላ የአጥንት አወቃቀርና 52 አካባቢ የአጥንት ክፍሎቿ መገኘታቸው እጅግ ተጠቃሽና አስገራሚ እንድትሆን አስችሏታል። የምርምር ቡድኑ አፅሟን ባገኘበት ወቅት ያዳምጥ በነበረው የ'ቢትልስ' ዘፋኞች አልበም "ሉሲ ... አሊማገ" የሚል ዜማ የተነሣ ስያሜዋ "Lucy" ሆኗል።

እንደ መፅሐፉ አዘጋጅ እምነት ለኢትዮጵያውያን ፍጆታ ብቻ የተቀመጠው "ድንቅነሽ" የሚለው ስም በሀገር ተገድቦ ስለቀረ በዚሁ ፈንታ ሉሲ 'አውሮጳዊ ስላልሆነች' ከአፋር እንስቶች ታዋቂ ታሪክ ባላት ሴት ስም ተሰይማ ዓለም ቢያገ ከሉሲ ጎንለጎን ስሟን አስቀምጦ "ሉሲ ከሀገራችን ስም ጋር እንዲተዋወቅ መደረግ አለበት። ከ20 ዓመታት በኋላ በ1994 (እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በመስከረም ወር 1987) ሉሲ ከተገኘችበት 10 ኪሎሜትሮች ርቀት ላይ ከሉሲ በአንድ ሚሊየን ዓመት የሚተልቅ 4.4 ሚሊየን ዓመት ዘመን ያስቆጠረ አፅም 'ራሚደስ' ተገኝቷል። የመጠሪያ ስያሜው 'ራሚድ' በአፋርኛ ታላቅ ትርጓሜ መያዙ ከተገቢ በላይ የሚያስማማ ነው። በግኝቱ ቡድኑን ይመሩ የነበሩት ኢትዮጵያዊው ተመራማሪ ዶክተር ብርሀኔ አስፋው፣ አሜሪካዊው ጠቢብ ፕሮፌሰር ፒን ሁዋይት እና ጃፓናዊው ተመራማሪ ዶክተር ጄኔስ ሁዋ ከነ የስራ አጋሮቻቸው ታላቅ ምስጋና ሊቸራቸው ይገባል።

በሰው ልጅ አመጣጥ ስያሜ 'Genus' ዋና የዘር ግንድ እና ዝርያዎች (species) መሠረት ሌሎች ክፍፍሎች ቢኖሩም ዋነኛው ከ'ጀነስ' እንነገር፦

ሀ. 'አውስትራሎፒተከስ' - 'አውስትራሎ' ደቡባዊ፣ እና 'ፒቴከ' ጦጣ የሚል ትርጓሜ ይዘዋል። በዚሀ ሥር ደግሞ ከሌሎቹ ከፍፍሎች ይልቅ ጎልተው በመውጣት ሦስት ዋነኛ ዝርያዎች ተመድበዋል። እነዚህም

A. ramidus h4 - 5 ሚሊየን ዓመት እድሜ (ኢትዮጵያ)

A. afarensis h3 - 4 ሚሊየን ዓመት እድሜ (ኢትዮጵያ)



t.me/OLDBOOKSPDF

A.africanus 2.6 ዓመት እድሜ (ደቡብ አፍሪካ)

መሆናቸውን ስንገነዘብ "ቅድመ-ታሪክ" በሚለው የዓለም ታሪክ ከፋይ ኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ ቀዳሚ መሪ እንጋፋ ብቸኛ ተጠቃሽ ሆናለች። ("A." የሚለውን ቅጥል ከፊት የጨመርነው የ"Genus" ስያሜ የሆነው ቅድመ ቅጥያ "Australopithecus" አብሮ እንደሚጠራ ለማመላከት በማሰብ ነው። በዚህም መሠረት በማያከራክርና በማያሻማ ሁናቴ (እስካሁን ይፋ በተደረገ ግኝት) የዓለም መነሻ የምስራቅ አፍሪካ ስምጥ ሸለቆ ባጠቃላይ፣ ኢትዮጵያ በተለይና አፋር እጅግ በጣም በተለይ መሆኗን ስናረጋግጥ ከእኛነት ይልቅ እኔነት በነገሠበት 'የጎሳ ፖለቲካ ደባብ'፣ ለአገላለፃችን ይቅርታ እየጠየቅን የሉሲ መገኛ ትግራይ አማራ ወይም ኦሮሞ "ከመሆን ርቃ አፋር መሆኗ" እፎይታን ሳይሰጥ ይቀር ይሆን? ለማለት ይዳዳናል።

አፋር፦ የሰው መሠረተ ግንድ፣ አፋር የመሠናኛችን ምሥጢር፣ አፋር የመገመዳችን ቅኔ፣ አፋር የመሰናሰላችን የተገለጠ ገመና፣ አፋር የሙብቀያችን ማህፀን፣ አፋር ብዙ እጅግ በጣም ልዩ ምድር። የኤርታሌ ገሞራ ህፅም እየፋመ ሲግም፣ ገሞራ ቆሬው፣ ገሞራ ዋድያት፣ ገሞራ ዋድያት ቅንብብ የፈጠረውና የሚፈጥረው ህብር ድንቅ ውብት፣ በሙቀት መጠኑ አቶን ሆኖ ከሚፈትነው በረሀ ጋር በዓለም የሚገኝ የሰው ዘር መብቀያውን እየቃኘ እየተንተከተከ ብርሀናዊ ፍቅሩን እየተፈነጣጠቀ በሚረጨው ብርሀን በሚለግሰው ተፈጥሮ፣ የኤርታሌና ፈንታሌ ዱቢ እሳተ ገሞራ ድምቀት ውብት፣ ከጠራው ሰማይ፣ ቀልብን ከሚማርከው ያማረ ተፈጥሮ፣ ከበረሀው መርከብ ሳብ ረገብ ጠብሰቅ ቾሰሰስ ጉዞ ጋር እየተመለከተ የእርካታ ጫፍ ላይ ይደርስ ዘንድ የሚከተሉት ቢከወኑ ምክረ ሀሳብ እናቀርባለን።

1. ደረጃውን የጠበቀ ሙዚየም፣

2. ለአፋር ኢትዮጵያዊነት ክብር የሚመጥኑ ሆቴሎችና የመናፈሻ ስፍራዎች እና

3. የአርኪዎሎጂ ምርምር ጣቢያ መገንባት ይጠይቃል። እነሆ የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የዓለም ቅድመ ታሪክ ከአፋር መነሻውን አደረገ። ታሪካችን ከአፋር ይጀምር እንጂ ዛሬ በዓለም የሉሲ ሀገር ተብላ የምትጠራው ኢትዮጵያ ኩራቱ ደግሞ የሁላችንም ነው።።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ታሪክ

የሰው ዘር በምድር ላይ ከኖረበት ረጅም እድሜ ከ99.9 እጅ በላዩን የኖረው አደን በማደንና ፍራፍሬ በመለቀም / የሰብአ ትካት አኗኗር ነበር። የዛሬ 10ሺህ ዓመት አካባቢ እንስሳትን ማርባትና ዕፅዋትን መትከል ጀመረ። የእርሻ ሥራ መጀመር ሰው ከቦታ ወደ ስፍራ ምግቡን ፍለጋ ከመዘዋወር ይልቅ በአንድ ሥፍራ ረግቶ እንዲኖር አስቻለው። የከተሞች ማቆጥቆጥ እና ህብረተሰባዊ የሥራ ክፍፍል እየሠፋ ሄደ። የዚህ ድምር ሥልጣኔ ተብሎ ይጠራል። የሥልጣኔ እናት የእርሻ ሥራ መጀመር ነው። የሰው ልጅ ታሪክ መነሻ የዛሬ 6,000 ዓመት ሲጀምር በኢትዮጵያ ውስጥ ጤፍ ዳጉሣ ኑግ እና እንሰት ማምረት ተጀምሯል። ፕሮፌሰር አየለ በከሬ፡- "Ethiopia: An African Writing System, Its History and Principles" በተሰኘው የምርምር ሥራቸው ገፅ 46 "African Archaeology" ፊሊፕሰን ጠቅሰው፡- ኢትዮጵያ ውስጥ ኅበደራ፣ አከሰዎምና በሰቃ ሀይቅ በሺህዎች ዓመታት እድሜ የተቆጠረላቸው የአርኪዎሎጂ ግኝቶች መኖራቸውን አውስተዋል። ከፅሑፉ ቀንጨብ አድርገን የሚከተለውን ወሰድን፡-

> *Ethiopia, as a matter of fact, has been identified as one of the major centers of origin for some plants and animals. Crops like Teff (Eragrostis teff), Noug (Guizotia abyssinica), False Banana (Musa ensetta) ... Teff in particular is cultivated only on the Ethiopian plateau, where it is native.*

በማለት ማስረጃ ጠቅሰው ያሠፈሩት ፅሑፍ በማያሻማ መልክ ጤፍ በሁሉም አቅጣጫ ኢትዮጵያውያንን የሚያስተሳስር ሰብል መሆኑን አበክረን እንገነዘባለን። የአንድነታችን መገለጫ ከሆኑት መስተዋድዶች የሆነውን ጤፍ ጥቂት የኔዘርላንድና ሌሎች ኩባንያዎች "የባለቤትነት መብት" አስመዝግበው የቆዩ ቢሆንም ሀገራችን በዓለማቀፉ ፍርድ ቤት "ዘ ሄግ/ ኔዘርላንድስ ከስ አቅርባ ለመርታት የሚያስችላት እድል እንዳለ የቅድመ ምርመራ ውጤቶች አመላክተዋል። ዳጉሳ ለምግብነትና ለጠላ ጠመቃ አገልግሎት ይሰጣል። ኑግ ዘይትን ለማምረት የላቀ ጥቅም በማስገኘት ላይ ነው። እንሰት በደቡብ በመሀከል እና ምዕራብ ኢትዮጵያ ከጤፍ ባልተናነሰ በሲማውያን



t.me/OLDBOOKSPDF

ከሰሜናውያን የአጎራባች ማህበረሰቦች የመተሳሰሪያ ገመድ ሆኖ አገልግሏል። በሚያስደንቅ መገጣጠም የሰው ልጅ ታሪክ ሲጀምር የኢትዮጵያውያን ሥልጣኔ አብሮ ሆኗል። በዚህ ሳንወስን ፕሮፌሰር አየለ በከሬ ከቢስኮፕ፣ "Axum" ከገፅ 126 - 132 በመጥቀስ ሌላ ነጥብ አክለዋል። እንዲህ ይነበባል:-"Coffee (Coffee arabica) is also indigenous to Ethiopia. In fact, the word coffee comes from the name Kaffa, an Ethiopian region that is the home of uncultivated coffee."

በአጠቃላይ ኢትዮጵያ ውስጥ የጋራ ታሪካችን ሲደመር ተአምር መሥራት የሚችል አቅም ይፈጥራል። ስለ ኢትዮጵያዊ ጥንታዊ ሥልጣኔ ዋቢ የሚሆኑ ቅድመ አክሱም ሥልጣኔዎች አያሌ ናቸው። ዘግይቶ የተፈጠረው የአክሱም ሥልጣኔ እንኳ ከሮማ፣ ፐርሺያና ቻይና ሥልጣኔ ጋር ለመዛ (በእኩነት) በጥንቱ ሥልጣኔ ተርታ መሠለፍ ችሏል።

## ሆሄያት / ፊደላት እና አኀዞች

በዓለማችን ታሪክ ሥዕላዊ የአጻጻፍ ዘዴዎች ከኪዩኔፎርም በሚስፖታሚያ፣ 50ሺህ አይነት ምልክቶች ያለው ሎጎግራፊክ በቻይና፣ ሂሮግሊፊክስ በግብፅ እና በስትሮፊደን በሳባውያን ተጀምረዋል። ሆሄያትን መልክ በማስያዝ በኩል በሰሜናዊቷ የአፍሪካ ክርቲጅ ሥልጣኔ ፎኒሺያንስ ወጣኒዎች እንደሆኑ ይታመናል። ግሪኮች ፊደላቱን ወስደው ማሻሻያ ካደረጉበት በኋላ ላቲኖች ቀስመው ለዛሬዎቹ የእንግሊዝኛ ፊደላት መሠረት ሆነዋል። ተኒዚያ ውስጥ የነበረው የፎኒሺያን የሆሄያት ጥበብ ግን ሳይበለፅግ ከስሟል።

ኢትዮጵያ የራሷ ፊደላት (ሆሄያት) ያሏት ብቸኛዋ አፍሪካዊት ሀገር መሆኗ በማያሻማ መልኩ ግልፅ ሆኗል። ይህ ደግሞ ለመላው ኢትዮጵያውያን የጋራ ኩበርና ኩራታችን መገለጫ ነው። አስገራሚው ነገር የፊደል መነሻ ኢትዮጵያውያን መሆናችንን አለመገንዘባችን ነው። የእንግሊዝኛ (የላቲን) ፊደላት መነሻ ተብለው የተቀመጡ ምልክቶችን በንመለከት ከላቲን /እንግሊዝኛ ፊደላት ጋር አምባዛም ቅርርብ የላቸውም።



t.me/OLDBOOKSPDF

መነሻ የመሰለውን ሆሄ "F"፣ "ቀ" የሚመስለውን ቅርፅ "Q" ሳተባለው ... ጋዩ በኋላ ነው ቢሉ ይደመጣሉ። ሆኖም የኢትዮጵያውያን ከሳባውያን "ግዕዝ የተገኙ ሆሄያት" ከእንግሊዘኛ ፊደላት ጋር ያላቸውን ተመስሎ ለማሳየት ከፊት (በስተግራ) እንግሊዘኛውን በኩል የግዕዙን ከኋላ (በስተቀኝ) የላቲኑን ለንፅፅር አቅርበናል። ሀU ሃy ሰh ሠw ፈ CC ርe ሬG በn ቲt ዐO ዑQ ዘH የp ደR ጠm ጦE ጊz ... ከዚህ አንፃር ከሳባውያን እየተሻሻለና እያደገ የመጣው የግዕዝ ፊደል በዓለማችን የገነነው ላቲን ፊደል መነሻ ሳይሆን ይቀራልን? (አዘጋጁ ከዓመታት በፊት በአንድ ሰማችውን የማያስታውሳቸው ከሀን ከቀረበው ገለፃ በመነሳት ፊደላትን በጥንቃቄ በመመርመር ተጨማሪ ሆሄያትን በማከል ለተጨማሪ ጥናት አድሉን ከፍት አድርጓል።)

ከላይ ባለው መነሻ ቁጥሮችን (አኃዞችን) በማስተዋል መመርመርን በሚያፈቅሩ ልቡናችን ቀጣዩን መግለጫ አቅርበናል። በዓለማችን የዜሮ "0" መነሻ ሚስጥቃሚያውያን እንደሆኑ ሲታመን፤ 1,2,3 ...9 ያሉት ዘጠኝ አኀዞች በህንዶች ተፈጥረው በአረቦች አማካይነት ለዓለም ስለተዋወቁ "የአረቦች አኀዞች" (Arabic Numerals) ስያሜን ተላብሰዋል። ይሁንና የእኛን አኀዞች በከፍተኛ ጥልቀት ቃኝተን አረባዊ አኀዞች የእኛ ለመሆናቸው ጥርጥር ይኖረን ይሆን? እስቲ የሚከተሉትን ማነፃፀሪያዎች እናስተውል፡-

"0" የቁጥሮች መነሻ በግዕዙ አራት ፬ ቁጥር መሀከል ተከፍሶ ይታያል። በተመሳሳይ፡-

1 ቁጥር በግዕዙ ዐሥር ፲ መሀከል፤

2 ቁጥር በሰባት ፯ ቁጥር ውስጥ፤

3 ቁጥር ከሠ ወይም ጠ አቀማመጡ ተገልብጦ፤

4 ቁጥር ከፊት ብሎ በተገቢው መንገድ ሲቀመጥ ፋ፤

6 ቁጥር በ አንድ ፩ እና ፮ ቁጥር መሀከል፤

7 ቁጥር በሰባት ፯ ቁጥር ውስጥ፤

8 ቁጥር ከ"ወ" ፊደል ውስጥ እና



t.me/OLDBOOKSPDF

9 ቁጥር የስድስት ግልባጭ ናቸው።

ይህንን በአፅንዖት መመልከት የቻለ ሰው እውነት ኢትዮጵያውያን ቁጥሮቹን ወስደው ከላይ ከታች ከጎን ቅጥልጥል አሸንክታቦችን ጨመሩ ወይስ የፊደሎቹ ፈጣሪዎች ከኢትዮጵያ ወስደው አጥፍቶቹን ቆራርጠውና ከርክመው አኀዞቹን ፈጠሩ? ብንል ወደ እውነታው ብዙ ርቀት እንጓዛለን። ከዚህ በተጨማሪ ኢትዮጵያውያን ቢኮርጁ ኖሮ የ"አረብኛ አኀዞች" ቁጥር ከ0-9 አሥር ቅርፆች (ተለዋውጠው የሚቀመጡ) ብቻ ሊሆኑ የግዕዙ 20 ፳ ሰ፤ 30 ፴ ራ፤ ፵ 40 ሣ፤ 50 ፶ ሃ፤ 60 ፷፤ 70 ፸ ሮ፤ 80 ፹ ገር፤ 90 ፺ ን፤ 100 ፻ የ፤ በውስጣቸው ያዘሉ ሳይሆኑ በአሥር አኀዞች ወይም ምልክቶች ብቻ በተገደቡ ነበር። ከዚህ አንፃር ቁጥሮቹ የተኮረጁ ናቸው የሚለው ክርክር ውሀ የማይቋጥር ከንቱ መሆኑን በመግለፅ ሳናበቃ የዓለም ቁጥሮች ምንጫቸው ኢትዮጵያ ነው ብለን በድፍረት እንሞግታለን።

ከዚህ በተጨማሪ ዛሬ በዘፈቀደ የምንፅፋቸው የአማርኛ ፊደሎች እንደየሁኔታው አጠቃቀማቸው ሥርዓት ያለውና የትርጉም ለውጥ ጥምር እንደነበረው በሚከተሉት ምሳሌዎች እንመልከት፦

"ሀ" ሀሌታው ሀ፣ "ሐ" ሐመሩ ሐ፣ "ኀ" አኀዙ ኀ፣ "ኃ" ብዙኃኑ ኃ

"ሠ" ንጉሡ ወይም ሠራዊቱ ሠ፤ "ሰ" እሳቱ፤

"አ" አልፋው አ፣ "ዐ" ዐይኑ ዐ፣ "ዓ" ዓመቱ ዓ

"ጸ" ጸሎቱ ጸ፣ "ፀ" ፀሐዩ ፀ

እነዚህ ፊደላት በከንቱ የተፈጠሩ አይደሉም። የየራሳቸው ምክንያትና የትመጣ አላቸው። ለምሳሌ፦

አመት፦ አመቴ አገልጋይ፤ ዓመት፦ ዘመን/ ጊዜ፤

አባይ፦ ዋሾ ቃለ-አባይ፣ ዓባይ፦ ትልቅ /ዓብይ፤

ሳለ፦ ጉንፋን ያዘው፣ ሣለ፦ ሥዕል ቀረፀ...



t.me/OLDBOOKSPDF

በዚህ ሂደት ከሚነሱ መጣጥፎች አንዱ የአማርኛ ፊደላትን መደጋገም ለማስቀረት ከተመሣሣይ የድምፅ ወካዮች አንዱን ብቻ "ሀ" "ሰ" "አ" "ጸ" ብቻ ተወስዶው ሌሎቹን አንተውም? የሚሉ ምሁራን ጥቂቶች አልነበሩም። በመጀመሪያ ደረጃ የአምስት ፊደላት ሐ፣ ሠ፣ ኸ፣ ዐ፣ ጸ መጨመር እና መቀነስ ተአምር አይፈጥርም። ቻይናዎች ከ50,000 ቀንሰው ዛሬ ከ5,000 ያላነሱ ፊደላት ይጠቀማሉ። ጃፓኖች ከ3,000 ያላነሱ ምልክቶችን ይጠቀማሉ። በጣም ወሳኙና የሚያከራክረው ነገር በመቀጠል ነገ የሚተካው ትውልድ፤ የቀደመው ትውልድ የፃፋቸውን ስሑፎች እንዴት ማንበብ ይችላል? ለማሳያ ያህል:- "ዐሐይ በምሥራቅ የሥሥት ያለሐ ሠረቀች" የሚለውን ዐረፍተ ነገር ለማንበብ ፊደሎቹ በመቀነሳቸው የተነሳ እንደምን ሊረዳው ይችላል? ለአንባቢው የሚታዩት ፊደላት የሚከተሉት ናቸው:- ("ይ በምራቅ የት ያል ረቀች")

ከላይኛው ዐረፍተ ነገር ቀጣዩ ትውልድ የሚረዳው ነገር አይኖርም። 'ሥሥት' ከሚለው ቃል "ት" ብቻ ትታየውና ለቃሉ ባዕድ ይሆናል።

አማርኛ በሀገራችን ለምርምር ከሚረዱ ቋንቋዎች አንዱ ሆኖ ሳለ ለምን አዲስ ነገር ከመፍጠር ይልቅ የራሳችንን ለመናድ እንደምንውተረተር ግልፅ አይደለም። የላቲን ፊደልን ለተለያዩ ቋንቋዎች በፊደልነት መጠቀምን አስመልክቶ የሚነሱ መጣጥፎች አሉ። በዚህ በኩል ታላቁ ቁምነገር የቋንቋው ተጠቃሚዎች ስምምነት ሆኖ የግዕዙ ፊደል የተወሰኑ ቅርፆች ተጨምረውበት ማገልገል እንደሚችል አሻሚ አይደለም። ይህም ድንቅ አይደለም በደርግ ጊዜ የኦሮምኛ ዜናዎችና ጋዜጦች ይነበቡ እንደነበር፣ መሠረተ ትምህርትም በኦሮምኛ ቋንቋ ይሰጥ እንደነበርና አናሲሞስ ነሲብ መፅሐፍ ቅዱስን በግዕዝ ፊደላት በኦሮምኛ ተርጉመው በግዕዝ ፊደላት ማቅረባቸው ግልፅ ነው። ላቲን ባይኖር ኖሮ በግዕዝ መጻፉ አይቀርም ነበር።

"የሚያጥሩና የሚረዝሙ የሚጠብቁና የሚላሉ አናባቢና ተነባቢዎች አሉ" ለሚለው መከራከሪያ ምላሹ - ቃላት የሚነበቡት ከአገባባቸው ተነስቶ ሲሆን አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ሁሉ በፊደላቱ ላይ ምልክቶችን መጨመር ይቻላል፡፡ በእንግሊዝኛ አንድ ቃል በርካታ ትርጉሞች እንደሚሰጥ፣ በአነባበብ እንደሚስተካከል ማሰቡ አይከብድም። ምንም ይሁን ምን የተለያዩ የሀገራችን ቋንቋዎች ሲዳምኛ ሶማሊኛ ኦሮምኛ እና በርካታ ሌሎች በጥናት ሳይሆን ድንገት በወያኔ ውሳኔ የተቀየሩ መሆኑን ስንመለከት



t.me/OLDBOOKSPDF

በለሆሳስ ማለፍን መርጠናል። ሌላው ቀርቶ በላቲን ቋንቋ ውስጥ 'ጨ' የሚል ድምጽ በለመኖሩ የሚይገናኘውን 'C'ን ለመጠቀም ተገደናል፡፡

የሚያስደምመው ከናፃፎች ኤርትራ ውስጥ በላቲን፣ ትግራይ ውስጥ ደግሞ በግዕዝ እያለገለ መሆኑ ነው። ልዩነቱ የፊደሎቹ ማነስና መብዛት ላይ የተመሠረተ ነው። መፍትሔው ከጥላቻ ስሜት ፀድቶ ሳይንሳዊ ውይይት አድርጎ ወደ ድምዳሜ መድረስ ነው። በተላለ መተማመን ላይ ስለማይደረስ ለጊዜው በይደር አልፈነው ቀጣዩ ትውልድ መደማመጥ እንዲችል በምንጥለው መሠረት ወደ መፍትሔው ይደርሳል የሚል እምነት አለን። (ለአከራካሪ የታሪካችን ምዕራፎች ይቆዩን።)

## የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት

የውጭ ግንኙነት ማለት በሁለት እና ከዚያ በላይ በሆኑ ሀገሮች መሀከል የሚደረግ ፈርጀ ብዙ ግንኙነት ነው። በውጭ ግንኙነት ዘርፍ ኢትዮጵያ ረጅም ዘመናትን ያስቆጠረ ግንኙነት እንደነበራት በርካታ የታሪክ ሰነዶች ያስረዳሉ።

## የግብፅና የፑንት ምድር ግንኙነት

ከክርስቶስ ልደት በፊት 2800 ዓመተ ዓለም አካባቢ (የዛሬ 5,000 ዓመት) ግብፆች በስተደቡብ አቅጣጫ ርቀው በመጓዝ ከፍተኛ የሸቀጥ ልውውጥ ያደርጉ እንደነበር ሂሮግሊፊክስ (ሂሮግላፊክስ) በተሰኘው ሥዕላዊ የአፃፃፍ ዘዴያቸው ተገልጿል። አባስ ቻላቢ የተባለ ፀሐፊ

"EGYPT" በሚል ርዕስ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ባሳተመው መፅሐፍ ገፅ 92 ላይ፦ "Queen Hatshepsut ... the expedition she organized to the mysterious country of Punt..." በማለት ቀጥሎ ስፊ ሐተታ አኑሯል። ከሥፍራው ግብፆች ይረከቧቸው የነበሩ ሸቀጦች እጣን ከርቤ የዝሆን ጥርስ የአውራሪስ ቀንድ የአነር ቆዳ የስጎን ላባ ቀጭኔ ዝንጀሮዎች መሆናቸውን ይገልፅልናል። በታሪክ ምሁራን ስምምነት መሠረት ምንም እንኳ የግዛቱን ስፋት



t.me/OLDBOOKSPDF

በትክክል ማስቀመጥ ቢከብድም ኢትዮጵያ ኤርትራ ጂቡቲ እና ሶማሊያ የፑንት ምድር አካላት ናቸው። ይኸው የታሪክ ምንጭ በገፅ 72 ላይ:- ከክርስቶስ ልደት በፊት በ27 ዓመተ ዓለም ታላላቆቹ የታሪክ ሊቃውንት ስትራቦኒየስ ታሲተስ ሉሲያነስ እና ፊሎስትራተስ ባደረጉት ያልተለመደ ዘገባ በአፈ ታሪክ የአውሮራ እና ቲቶን ልጅ የግብፅና የኢትዮጵያ ንጉሥ ሚኖንን የሚወክለው "ዘማሪው ድንጋይ" የሚል ሀገብ አስፍረዋል።' በማለት ያትታል።

ከዚሁ ጋር በመፅሐፍ ቅዱስ በአንደኛው ክፍለ ዘመን ስለነበረችው የኢትዮጵያ ንግሥት ህንደኬ፣ በዚህው ክፍለ ዘመን ስላስተዳደረው ሀስካለስ ሲወሳ ኢትዮጵያ ግብፅን አስተዳድራ ይሆንን? የሚል ጥያቄን ያጭራል። ፕሮፌሰር አየለ በከሬ (በጠቀስነው ምንጭ ገፅ 53 - 54) በግብፅና በፑንት ምድር መሀከል ስለነበረው ግንኙነት በጥናታቸው ካካተቱት ቁምነገር የሚከተለውን እንመልከት:-

"1) Sahure (2743 - 2731 BCE) sent an expedition to the land of Punt returning home with great quantities of myrrh, ebony and electrum

2) አሶሲ ድንኮችን ይወስድ ነበር።

3) Pepi (2625 - 2475 BCE) ካፒቴን ስብኒ የተባለውን ነጋድራስ በመላክ ዕጣን የዘሆን ጥርስ ወርቅ እና ቆዳዎችን ከፑንት ምድር ይወስድ ነበር።

4) ማዕድናት:- 'ኤሌክትረም'፣ ወርቅ፣ lapis lazali፣ 'qohl'፣ ነሀስ እና 'ማላቻይት'፣ ከእንስሳት:- ጦጣዎች፣ የሜዳ አህያ፣ ኮርማዎች (በሬዎች)፣ አነር፣ የተለያዩ የእንጨት አይነቶች፣

5) (1501 - 1447 BCE) ተትመስ ሣልሳዊ እና ንግሥት ሀትሸፕሱት ጠንካራ የንግድ ግንኙነት መፍጠራቸውን ገልፀዋል። በተጨማሪም በመፅሐፍ ቅዱስ ኢትዮጵያ ደጋግማ መነሳቷ የጥናታችንን ወሰን እስከምን ድረስ እንድናሰፋ ያነሳሳን ይሆን? በስሜት ሳይሆን በስሌት ከደበተን የታሪክ ዶብርት እንድንላቀቅ በርካታ የማንቂያ ደወሎች አሉ።



t.me/OLDBOOKSPDF

## ደሙት (ዳማት / ደአማት)

የኢትዮጵያ ሊሂቃዎች ላጠራር እንዲመቻቸው "ዳማት" በማለት የሰየሟት በፅሑፍ የተገኘው ስሟ "ደሙት" ከአክሱም አስቀድሞ ከነበሩ ኢትዮጵያዊ ሥልጣኔዎች ኮሎኤ ከሀለሰ ኢዲሰግለማን ሐውልቲ ሚላዘ ወዘተርፈ አንዷ ናት። የዳማት መሪዎች በደቡብ ዐረቢያ የማአረግ መጠሪያ ስም የነበረውን "ሙካሪብ" መጠቀማቸው በኢትዮጵያና ደቡብ ዐረቢያ መሀከል መልካም ግንኙነት እንደነበረ ምስክር ነው። ዳማት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያዋ የታወቀች መንግሥት መሆኗ ተገልጿል።

አክሱም፡-

በላይ ግደይ የተባለ ጸሐፊ፡- "Axumite Civilization" በተባለው መፅሐፉ በርካታ ቁም ነገሮችን አንስቷል። ብእረ መልካሙ ፕሮፌሰር ሥርገው እና ተከለፃድቅ መኩሪያም አክሱምን አስመልክቶ ዘርዘር ያሉ መረጃዎች አጋርተውናል። በታሪክ ትምህርት ክፍል በእንግሊዝኛው የተለመደው አፃፃፍ "Aksum" የሚል ሲሆን፤ የሆቴል እና ቱሪዝም ዘርፍን ጨምሮ በአብዛኞቹ ትምህርት ክፍሎች ደግሞ የሚዘወተረው "Axum" የሚለው አፃፃፍ መሆኑ ልዩነቶችን ሲያዩ ግር ለሚላቸው አንባቢዎች መልስ ለመስጠት፡- አክሱም የሚለውን ቃል የትመጣ በተመለከተ ግልፅ ያለ መደምደሚያ ባይኖርም፥ "አክ" በኩሻዊ ቋንቋ ውሀ ማለት ሲሆን "ሱም" ሹም አለቃ ማለት ስለሆነና አክሱማውያን በባህር ላይ ታዋቂ መሆናቸውን ለማመልከት ነው የሚለው አንድምታ የበለጠ ሚዛን ይደፋል። ምናልባትም የአክሱም ሥልጣኔ የሴም እና የኩሽ መነሻ ኖሮት የአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ጥምር አሻራ ያረፈበት የመሆን እድሉ ሰፊ ነው። (አክሱም ጠለቅ ያለ ጥናት ቢደረግባት ተዝቆ የማያልቅ ጥበብ በማህፀኗ አካትታለች። ለዘርፉ ተመራማሪዎች ይቆይ።) አክሱም ማለት 'ለምለም መስክ፤ የአልማዝ መገኛ ወይም አክሱማዊ ከተባለው ንጉሥ ስም የተወሰደ ቢሆንስ?' የሚሉ ተጓዳኝ መላ ምቶች አሉ።

ስለአክሱም ባልታወቀው የግሪክ ነጋዴ የተፃፈው "The Periplus ..."፤ በኮስሞስ የተፃፈው "ዘ ክሪስቲያን ቶፖግራፊ" እና ቀደምት ምንጮች እንደሚነግሩን አክሱም ከህንድ ቻይና ፐርሺያ ባይዛንታይን እና የመሀከለኛውና ቅርብ ምሥራቅ ሀገሮች ጋር የንግድ ትሥሥር ነበራት። (ከግብፅ አሌክሳንድርያ ጳጳሳት የማስመጣት ልምድ ከ340



t.me/OLDBOOKSPDF

- 1958 መቀጠሉን ታሪክ ያስረዳናል።) በወርቅ ሣንቲሞቿ ዓለማቀፍ ንግድን ታቀላጥፍ ነበር።

## የዛግዌ ሥርወ መንግሥት (1150 - 1270)

ከቅርብ ምሥራቅ ሙሥሊም ሡልጣኖች ጋር የነበረውን ግንኙነት በቀጣዩ ክፍል ማየታችን እንደተጠበቀ ሆኖ በአክሱም ጊዜ የተጀመረው መልካም የንግድና የሀይማኖት ትሥሥር ቀጥሏል።

## የሰሎሞናዊ ሥርወ መንግሥት (1270 - 1974)

ለፖርቱጋል መንግሥት ከተፃፈው የአፄ ዘርዓያዕቆብ ሚስት የንግሥት እሌኒ ደብዳቤ እና የአፄ ገላውዴዎስ ደብዳቤ ጀምሮ እስከ አፄ ኃይለሥላሴ የዓለም ጉብኝት ከተደረጉ ግንኙነቶች የተመረጡትን በነገሥታት ታሪክ ውስጥ የምንመለከተው ይሆናል።



t.me/OLDBOOKSPDF

## ቀቁፈና፤ ክርስትና እና እስልምና

በሀይማኖቶች መከባበር ረገድ ሀገራችን ኢትዮጵያ ለዓለም የሚተርፍ የተምሳሌትነት ታሪክ አላት። የምዕመናን መልካም ግንኙነት አንዱ ሌላውን ሳይጫን አክብሮ እስከ ሚኖሩበት በተግባር የተገለፀ ነው። በዚህ ረገድ የተመዘገበታሪክ የምናገኘው የመጀመሪያዎቹ የሙስሊም ስደተኞች ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ ንጉሳችን አክብሮ በመቀበል ማስተናገዱን ነው:: ይኸው መልካም ልምድ እስከዚህ ትውልድ ሳይቋረጥ የዘለቀ ነው:: የሩቅ ዘመኑን ትተን አሁን እኛ ባለንበት ዘመን እየተደረገ ካለው በእምነት ተከባብሮ የመኖር ባህል ጥቂቱን እናንሳ::

የራጉኤል ቤተክርስቲያን ምዕመናንን ከጥቃት ለመታደግ (1970ዎቹ) የአንዋር መስጊድ ምዕመናን 'ሆ' ብለው መነሣታቸው፤ ለአብነት በ2018/19 ከተከናወኑ በርካታ ፍፃሜዎች ጥቂቱን ብንጠቅስ በፀረ ሽብር ህግ በግፍ ታስሮ በነበረው በሚሰባህ ከድር የሚመራው "የፍቅር ያሸንፋል ማህበር" ሙስሊም አባላት በአዲስ አበባ ጃን ሜዳ በጥምቀት ዋዜማ ተገኝተው የክርስቲያኖችን መስገጃ ስፍራ ሲያፀዱ የመፅሐፉ አዘጋጅ በአካል ተገኝቶ በማህበራዊ ሚዲያ ገፁ "Taye Bogale Arega" ዘግቧል።

የጎንደር ክርስቲያኖች ለሙስሊሞች ኢድ በዓል የመስገጃ ሥፍራዎችን ማፅዳታቸው በመገናኛ ብዙሃን ተወስቷል። የአዲስ አበባ ክርስቲያንና ሙስሊሞች በቢሾፍቱ ሆራ አርሰዲ ኢሬቻ በአግባቡ እንዲካሄድ ከበዓሉ አንድ ቀን ቀደም ብለው በመገናኘት የፅዳት ተግባር አከናውነዋል። በሐረር ገጠር ውስጥ ቀርሳ አካባቢ አባ አከሊለብርሃን የመስጊድ ህንፃ አሠሪ ኮሚቴ ሰብሳቢ ሲሆኑ፤እዛው ያሉት ሼክ ደግሞ የህንፃ ቤተ ክርስቲያን አሠሪ ኮሚቴ ሰብሳቢ በመሆን እርዳታ ለማሰባሰብ አዲስ አበባ በተገኙበት ወቅት የመፅሐፉ አዘጋጅ አግኝቷቸው ክርስቲያኑ የሙስሊሙን፤ ሙስሊሙ የክርስቲያኑን ህንፃ የሚያንፅበት ምክንያት ምን እንደሆነ ሲጠይቃቸው የመለሱለት መልስ፦ 'ይህ ለኢትዮጵያ አዲስ ነገር ሆኖ እኛ እየጀመርነው አይደለም። አዲሱ ትውልድ ስለመከፋፈልና ጥላቻ ብቻ እየተሰበከ ስላደገ እውነታውን ልናሳየው ፈልገን ነው። ሁለታችን የእምነት አባቶች ለ35 ዓመታት የዘለቀ የቅርብ ጓደኝነት አለን። በየትኛውም ማህበራዊ ፍፃሜ አንለያይም። 'ሀይማኖት የግል ሀገር የጋራ ነውና'



t.me/OLDBOOKSPDF

ለሰላትና ለጸሎት እንለያያለን። በመንፈስ ግን ሁላችንም ለሀገር ከመጸለይ ጎን ለጎን አንዱ ስለአንዱ ፈጣሪውን ይለምናል።

ሙስሊሙ 'አልሀምዱሊላህ ታቦት በሰላም ገባ' ማለቱ እንደ ክርስቲያኑ በታቦቱ ምስጢር ዙሪያ ባለው ጉዳይ በመስማማቱ ሳይሆን ህዝበ ክርስቲያኑ በሰላም አምልኮ ወደየቤቱ መግባቱ የደስታው አካል ስለሆነ ነው' የሚል ነበር። ይህንን መልካም ተምሳሌትነት እንደ BBC, Aljazeera, CNN በመሳሰሉ ጣቢያዎች ተጠቅሞ ለዓለም ሰላም እንደመሥራታችን በስፋት ማሣየቱ ጠቃሚ ይመስለናል።

## የዋቄፈና እምነት እና ዋቄፈታዎች

ዋቄፈና፡- በሀገራችን ታሪክ ወግ ልምድ ትውፊት እምነት ፍልስፍና ባህል ... ላይ ዕውቀት መያዝ መረዳት፤ የተገነዘቡትን በቀናነት አውጥቶ ማሳየት፤ ጉዳቱ ምንም ጠቀሜታው ግን የትየለሌ ነው። ከታሪክ ጎጆ አለላ ሰበዝ ውስጥ የወየበውን (የጠቆረውን) እየመዘዙ፤ በጎውን አሳንሰው፥ ክፉውን አጉልተው የሚጽፉ በበዙባት ምድር፣ በጎውን መልካሙን ደግ ደጉን ማየቱ ምንኛ መታደል ነው። በተለይም ታሪክን በተሰራበት ዘመን ራስን አስገብቶ ከማየት ይልቅ፥ በዛሬ መሳሪያ መመዘን፥ ፍርደ ገምድልነት ነውና ነገሮችን ሰለለስ አድርገን ዕናይ ዘንድ ውስጣችን ያስገድደናል።

ኦሮምኛ ከዐረብኛና ፋሳኒ ቀጥሎ በአፍሪካ በስፋት የሚነገር ቋንቋ ነው። ኦሮሞ ሁለት መንትያ ስርዓቶች አሉት። የገዳ አስተዳደራዊ ስርዓትና የዋቄፈና ሀይማኖታዊ ስርዓት፤ በዚህ ውስጥ dhahaa የተባለው አስትሮኖሚያዊ የዘመን አቆጣጠር (calendar) ያስደምማል። የቱለማ ጉዲፈቻ (ጉዲፈቻ) እና ወደ ማህበረሰብ መቀላቀል ሞጋሳ (ሞጋሳ)፣ ወላጅ አልባ ልጃገረዶችን መንከባከብ ዳረ ባሱ፣ በቦረና ጉጂ አርሲና ባሌ አካባቢ የሴቶችን መብት የሚያስከብሩ ስርዓቶች ሲንቄ (ሲቄ) እና ቀነፋ፣ የግጭት አፈታት ስርዓቶች ከስን በማከሰም ረገድ የማጫወቷቸው ሚናዎች በስፋት ተጠንተው ሰፋፊ ሰነዶች ይገኛሉ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ወደ "'ዋቄፈና" እምነት እንመለስ። በርካቶች ዋቄፈና የጣዖት አምልኮ አሊያም በአንድ አምላክ ላይ ያልተመሠረተ እንደሆነ አድርገው ዕሬዋል። ሌሎች እስካሁንም ቁመንሳሮ ብዥታ እንደያዙ አያጠራጥርም። በመሆኑም አብርሆት ለመስጠር እንደሚከተለው ሰንደናል። ዓላማችን መራራውን እውነት ለአሁኑና ለመጪው ትውልድ ማጠጣት ነውና ለማንም የታሪክ ጣዕም ቁበ አንሰጥም።

## ዋቄፈና ምንድነው?

ዋቄፈናን አስመልከቶ *ፕሮፌሰር ተሰማ ታ'ዓ፡- "Ethiopian Journal of the Social Sciences and Humanities, Vol. VIII, No. 1 ገፅ 87 የሚከተለውን አስፍረዋል፡-

> *"The annals of the Oromo reveal that the Oromo religion was neither Christianity nor Islam but was an indigenous religion known as Waaqeffanna. The Oromo Waaqa is similar to the God of the Christian and Allah of the Muslims. ... Whether the Oromo have become Christians or Muslims, however, a true belief in one God (Waaqeffanna dhugaa) remains the basic tenet of Oromo identity."*

በማለት ሀይማኖቱ ሀገር በቀል፣ በክርስትና እና በእስልምና እምነት እግዚአብሔር ወይም አላህ ከኦሮሞ 'ዋቃ' ጋር አንድና ያው እንደሆኑ አረጋግጠው ያሳያሉ። *አበባው ቦጋለ ሀሳቡን በማጠናከር፡- "The Culture of Pastoralist Guji of the Borena Province" በሚል ርዕስ ባቀረበው ጥናት ገፅ 26 "Guji believe in Waqa, creator of human beings. It is comparable to God."

ከኦሮሞ ማህበረሰብ አንዱ ክፍል የሆነው ጉጂ ሰዎችን በፈጠረ አምላክ - 'ዋቃ' እንደሚያምንና በሌሎች እምነቶች ለፈጣሪ ከሚሰጠው ቦታ ልዩነት እንደሌላቸው ከሰፊ ትንተና ጋር ዐሳይቷል።



t.me/OLDBOOKSPDF

•ሀሮልድ ማርከስ "የኢትዮጵያ ታሪክ" በተሰኘው የምርምር ሥራው ገፅ 37:-

*Some Oromo became Muslim, others Christians, and many retained the faith of their fathers, even if they incorporated Allah, Jesus, and the Virgin Mary into their rituals.*

ማለቱ ዋቄፈና በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ሥፍራ ያመላክታል።

•ፋዘር ማርሻል ደ ሳልቫይክ (ቀድሞ በተገለፀው የምርምር ሥራቸው) ገፅ 144:- "With the idea of the divinity, they have preserved the true name, God, in the Oromo language means: Waaqa." የሚል ገለፃ አስፍሯል። ዋቄፈናን በተመለከተ ሠፊ ሥራ በማበርከት የላቀ ምስጋና ሊቸረው የሚገባው:- "Oromo Wisdom in Black Civilization" *ድርቢ ደምሴ የሰነደው መፅሐፍ ነው። በዚህም መሠረት በሰበሰብናቸው መረጃዎችና ማስረጃዎች ላይ በመንተራስ 'ዓባይን በጭልፋ' ሆኖ የሚከተለውን አቀረብንላችሁ።

**የዋቄፈና የእምነት መነሻ ፍልስፍናዎች:-**

ፈጣሪ ሁለት ሶስት አራት ወይም ከዚያ በላይ ህላዌ የለውም፣ አንድ ነው። ፈጣሪ ሰዎችን ፈጠረ፥ ሰዎች ደግሞ ሀይማኖቶችን ሠሩ። የኛ አባቶችም ዋቄፈናን አቆዩልን ዋቄፈታ ነን። ሰዎች ሀሊናቸው ካመላካታቸው አምላክ ጋር ይገናኙ። ለኛ ሙናፊቅ (መናፍቅ) የለም፤ ስለዚህ በሀይማኖቱ ወይም ማንነቱ ምክንያት አንድም ሰው መሞት የለበትም። ፈጣሪ ምስጋና ይግባው ዋቃ ጉራቻን ሳንቀላቅል እናምናለን። በዓለም ጥሩና መጥፎ መናፍስት አሉ። እኛ ደግ ከሚያሳስቡት፤ ከበጎዎቹ ጋር እንተባበራለን። ዋቃ፥ አያና (ቅዱሳን):- ከርኩስ መናፍስት የሚቃረኑ የሰው ጠባቂዎች ናቸው።

አባ ሙዳ (ቃሉ)፣ ቃሉ (ወንድ ካህን)፣ ቃሊቲ (አማሆይ) እና ምዕመናን በቅደም ተከተል ከፈጣሪያቸው ጋር የሚገናኙበት መንፈሳዊ የዕዝ ሰንሰለት አለ። ዋቃ ህዋ (Cosmos)ን ለሰው በሚጠቅም መንገድ ስርዓት አበጅቶ ሰው የቻለውን ያህል ይጠብብ ዘንድ ፈቃዱን ሰጠው። ፈጣሪ ጥበብን ለሰው ስላደለው በተፈጥሮ አብዝቶ ጣልቃ አይገባም። ፈራጅ ፈጣሪ ነውና በእምነት ጣልቃ አንገባም። አምላክ ቀድሶ በፈጠረው የትኛውም የሰው ልጅ ላይ እጃችንን አናነሳም። ሰንበድል ወዲያው



t.me/OLDBOOKSPDF

ቃየ በኋላ

እንፀጸት፣ የልምላሜ አምላክ ነውና እርጥብ ይዘን፣ የህይወት ምንጭ ሳሆን ሳር ልምናችንን እናቀርባለን።

የዋቄፈና እምነት መሰረቱ፦ "በፈጠረን በአንድ አምላክ እናምናለን። ወደ ፈጣሪ ጸሎት እና ምልጃ ምናቀርበው ተፈጥሯዊ በሆነ አግባብ ነው። በአንድ አምላክ የምናምን /monotheists ነን" የሚል ጅማሬ አለው። *Dursila D. Houston ባሳተመቺው መጽሐፍ "Wonderful Ethiopians of the Ancient Cushite Empire" በሚከተለው መልክ ይነበባል፦ "The Cushite race, its institutions, customs, laws, and ideas were the foundation upon which our modern culture was laid" ... ዋቄፈና ምናልባትም በአንድ አምላክ ላይ የተመሰረተ የመጀመሪያው የሰው ልጅ ሀይማኖት ሆኖ ልክ እንደ ገዳ ስርዓታችን በዩኔስኮ እንደሚመዘገብ እምነት አለን።

የተለያዩ የተደነሱ የታሪክ ድርሳናት የግብፅ ስልጣኔ ፒራሚዶችን ጨምሮ መሰረቱ ጥቁር ኩሾች መሆናቸውን ያሳያሉ። ለአብነት፦ በ*አኑ ዋቆ "Barruulee Waaqeffanna" በሚል ጽሁፍ እንደተዘጋጀው፣ የአፍሪካ ቀንድ የሰው ልጅ ስልጣኔ ሳይንስ ፍልስፍና ሂሳብ ምህንድስና የረቀቁና ውስብስብ እምነቶች መፍለቂያ ነው። የሰው ዘር መነሻ (cradle of mankind) መሆኑ ሳይዘነጋ! በአሳዛኝ ሁናቴ ግን አፍሪካውያን የስልጣኔ ባለቤትነታቸውን መቀማት ብቻ ሳይሆን እንደ አራሚ (ፓጋን) ተቆጠሩ።

ወደ በኩረ ሀሳባችን ዋቄፈና ስንመለስ ፈጣሪ በልዩ ከሂል ፍጥረታትን እንደመፍጠሩ ይወዳቸዋል። በሰው ዘር መሀከልም የተመረጡና ታናሽ የሚባል ደረጃ አላስቀመጠም። የኦሮሞ እምነት መሰረት ዋቄፈና እንደመሆኑ ሌሎች ህዝቦችን መውደዱ ከዚህና ከዘመናት ታሪኩ ይመነጫል። አንድ የኦሮሞ ትንታግ የኢትዮጵያን ህዝቦች ህብር ሲገልጽ፦ "እኛ አንድም ሰማንያም ነን" በማለት የኢትዮጵያን ህዝብ መተሳሰር ሀሳይቷል። *George G. M፦ "Stolen Legacy" በሚል ርዕስ ባሳተሙት መጽሐፍ ገጽ 141 ላይ፦ "ዋቄፈና ፈጣሪ ፍጥረታት በሙሉ ሳይፈጠሩ በዘላለም ውስጥ ነበረ፣ የሁሉም ነገር የህይወት ምንጭ የሆነውን የወላቡን ውሀ ፈጠረ" በማለት የዋቄፈናን እምነት መነሻ ገልጸውታል።



t.me/OLDBOOKSPDF

በእምነቱ ውስጥ አንድ ክፍል የሆነው ወላቡ ሁለት ክፍሎችና አምስት ንዑሳን ክፍሎች አሉት። ሁለቱ ክፍሎች:- ሰማያዊ እና ምድራዊ ሲሆኑ፣ ፈጣሪ ሰማያዊውን በስት:- የከዋክብት ከዋክብት፣ ዐሐይና ጨረቃ፤ ምድራዊውን ደግሞ በሁለት:- የብስና ውሀ አድርጎ ከፋፈለው። ከሚለው ንድፈ ሀሳባዊና ገቢራዊ ንጣፍ በመነሳት አምስት (5) ቁጥር በኦሮሞም ሆነ በዋቄፈና ከላይኛው፤ አምስት ዋነኛ ክፍሎች በመነሳት ልዩ ቦታ አለው። አምስቱ ምስጢራት ዋቃ፣ አምስቱ ጥበቦች፤ አምስት አሰደናቂ ቁጥር ... በመሆኑም የኦሮሞ ምርቃት ፈጣሪንና አፈጣጠሩን በመንተራስ :-የአምስቱ ፍጥረታት ፈጣሪ ይባርካችሁ፤ የአምስቱ የኦሮሞ ገዳዎች ፈጣሪ ይባርካችሁ ማለትን ያስቀድማሉ። ኦሮሞና አምስት ቁጥር ጥብቅ ቁርኝት አላቸው።

1) አምስቱ ገዳዎች:- ሚልባ፣ ሙደና፣ ኪሎሌ፣ ቢፎሌና ሚቺሌ፤

2) የኦሮሞ ቤት አምስት ክፍሎች:- ኢቢዳቢራ (ሳሎን)፣ ጎርዱባ (ማዕድ ቤት)፣ ዲንቃ (የአባወራና ሃdha መና መኝታ ክፍል)፣ ጎላ ሚርጋ (በቀኝ በኩል የወንዶች መኝታ ክፍል) እና ጎላ ቢታ (የሴቶች መኝታ በግራ በኩል)፤

3) የኦሮሞ አምስት የግልግል ዳኞች፤

4) አምስቱ ህጎች:- ሰፉ በሰቄሳ ጎሮ አሳሳ እና dhoዋ / ሴራጀቢ ቢፋ፤

5) አምስቱ የስሜት ህዋሳት፤

6) አምስቱ ጣቶች...

የአምስት ስነመለኮታዊና የህዋ ፍልስፍናዎች 'Yayyaba Shanan' አጀብ የሚያሰኝ ረቂቅ ምጡቅ ውስብስብና ድንቅ ነው።

የዋቄፈና ነጽሮተ ዓለም:-

እንደ ጥንታዊ የሰው ልጆች እምነት ሁሉ አማኞቹ (በዚህ አገላለጽ ዋቄፈታዎች) ከእምነቱ መሰረታዊ ዶግማና ቀኖና ጋር አብረው የማይሄዱ ድርጊቶች ሲያከናውኑ ይስተዋላሉ። ይህ በፈጠረው ብዥታ ዓመቱን በሙሉ ከፈጣሪ ጋር መኖርን ከአንድ ቀን የአንድ ስፍራ (የተለዩ የእምነቱን መሰረት ያልተረዱ ሰዎችን አጓጉል ባህርያት በማየት) ከባዕድ አምልኮ ጋር አቆራኝቶ መገንዘብ የሰዎችን አዕምሮ ሰቅዞ ይዟል።



t.me/OLDBOOKSPDF

በነዚህ ወገኖች መፍረድ አይቻልም። ማያውቁትን ነገር በሚያዩት ቢመዝኑ ስለምን ይወገዛሉ? ድርሳናት አዋቂዎች ሃየዎች ጃርሳ አርጋ dhaጊ፡ (wise old men) ሲገለጡ ሰምና ወርቁን እናያለንና እነሆ፡- *M Bernal "Blach Atena" በሚለው ጦማራቸው የዋቄፈናን አምልኮ እንደሚከተለው ይገልጹታል። 'የዋቄፈና አማኞች እምነታቸውን በፍጹም ጽናት እንዲህ ይናገራሉ፡-

በፈጠረን አንድ አምላክ ለማመን ሰባኪ አያሻንም ፍጥረታት ስለርሱ ይመሰክራሉና፤ ዝናም ያንጠበጥባል፤ አየር ይናኛል፤ ፀሐይ ታንጸባርቃለች፤ ሚዳው ጋራው ሸንተረሩ ይሆኑ ዘንድ ዕፅዋትና አዝርዕት ያፈራሉ። እናም ህያዋን ምግብና መጠጥ፤ መፍለሚያቸውን ተከትለው የተለያዩ ስሜቶችን እንደየሁኔታው እንደሚያንፀባርቁ እኛም ተፈጥሯችን ደመነፍሳችን ወደ ፈጣሪ ይመራናል።

ያለ ውሀ አየር ፀሐይ ፍጥረታት ጥምረትና በስነምህዳር ውስጥ ባለ ሰንሰለት ፤ ድር መኖር እንደማይቻል ሁሉ፤ ከፈጣሪ አምልኮ ከተለየህም ሞተሃል። ፈጣሪን ስንለምን በተፈጥሯዊ መንገድ ወደ ተፈጥሮ መገለጫ እየሄድን እናመልካለን። እኛ ወደ ተፈጥሮ ወላቡ ውሀ ሄደን ከፍታ ተራራ፤ ዝቅታ ሄደን፤ አረንጓዴ ልምላሜ ይዘን ፈጣሪ እነዚህን ስለሰጠን በመሀከላቸው ሆነን በልዩ ተመስጦ እናመሰግናለን።

የሰው አፈጣጠር፡- በዋቄፈና እምነት ውስጥ ዋቄፈታዎች ሰው ሲፈጠር "ወንድም ሴትም ያልሆኑ አንድ አካል እንደነበሩ" ያምናሉ። ከእለታት ባንዱ ቀን ሰው ውሀ ሊጠጣ ወደ ጅረት በመውረድ ላይ ሳሉ ድንገት ድምጽ ሰሙ። ዘወር ሲሉ የፈጣሪን ዐይን አዩ፤ በድንጋጤም ለሁለት ተከፈሉና በተለያዩ አቅጣጫዎች ሮጡ። በሂደት ወንድና ሴት ቢሆኑም ወንዝ በመሀከላቸው ስለነበረ የልባቸውን መሻት መግለጽ አልቻሉም። ወንዱ በስስት ድምፀት "ሃዌ ሃዌ!" ወደኔ ነይ በማለት ጮኸ። "ሃዌ" በኦሮምኛ መሻቴ ምኞቴ 'ከልቤ ወድጄሻለሁና የኔ ሁኚልኝ' የሚል ትርጉም ያዘለ ነው። ወንዱ አስከትሎም ሐረግን እንደ ገመድ በመጠቀም ወደርሱ ትመጣ ዘንድ ሳባት፤ ሴቷ አመነታች። ተስፋ ባለመቁረጥ ወደ ጠባቡ የወንዝ ክፍል ሲያማትር፤ ወደ ሰፊው አቅጣጫ በመሄድ "አዴም! አዴም!" ትርጉሙ "ና" ማለት ነው ስትል ጠራቺው። የታዘዘውን ፈጸመ። ሴቷ የገመዱን አንድ ጫፍ በጀርባዋ ጠምጥማ ለወንዱ በተመሳሳይ ሊላውን ጫፍ ሰጠቺው። ወደራሱ ስቦ ማረካት። በዚህም የተነሳ ኦሮሞ ጋብቻ ሲመሰርት አሁንም ድረስ "ሴት ወሰድሁ" ይላል።



t.me/OLDBOOKSPDF

ወንድና ሴት ከአንድ አካል እኩል የተከፈሉ በመሆናቸው በመሀከላቸው መበላለጥ የለም። የሰው ሁሉ መገኛው ከአዴም እና ሃዌ ነው። የቆዳ ቀለምና የተከለሰውነት ልዩነት የአየር ንብረት፣ ከአካባቢ ጋር የመላመድና የተፈጥሮ ሂደት ውጤት ናቸው። ኦሮሞ ለምለም ለሆነ ተፈጥሮ ተራራ ሸንተረር ደን ጅረቶች ወዘተርፈ ልዩ ፍቅር አለው። በአንድ በኩል የሰው ልጅ ፍቅርና የዘር ቀጣይነት የበቀለበት ስፍራ፣ ኤደን ገነት 'ኤዴዓ ገናሌ; ሲሆን፤ የሰው መሰረታዊ ፍላጎቶች ምግብ (አጽዋትና እንሰሳት)፣ ውሀ፣ ልብስ፣ መጠለያ፣ ፍቅር ጥምር መቡቀያቸው ልምላሜ ባለበት ውብ ተፈጥሮ ነው። የጉጂ ኦሮሞ ዛፍ ያለመቁረጥ ልምድ ዛፎች በኦሮሞ ሁነት ልዩ ትርጉም ስላላቸው ነው።

የፈጣሪ አምልኮ ለምለም ቄጠማ 'ጮቆርሳ' ተይዞ፣ ኮርማ ወይም ወይፈን በለምለሙ መስክ የሚታረደው "ፈጣሪ ሆይ ለምግብ ይሁኗችሁ ብለህ ስለሰጠኸን ተመስገን" ለማለት እንጂ የሚታየውንም ሆነ የማይታየውን ግዙፍ ፍጥረተ ዓለም ካለመኖር ወደ መኖር ላመጣ ፈጣሪ በሬ በመስዋዕትነት ማቅረብ ላይ የተመሰረተ አይደለም። ዋቄፈና የሌሎችን አምልኮ ያከብራል። የውድድር መንፈስም የለውም። ሆኖም ብኸርታ ለሚፈጠርባቸው ሰዎች በአምልኮው ውስጥ የሚታዩ 'ጨሌ ሜጬና ከለቻ' ዝቅ ተደርገው ሊታዩ አይገባም። የክርስቲያኖች 'ጽላት'፣ የሙስሊሞች 'ታስባ' የዋቄፈና ተመሳሳይ መነሻ አላቸው። ወደ ሆራ ወንዞች ተራሮች በመሄድ የሚደረገው መንፈሳዊ ጉዞ (Pilgrimage) መካና ኢየሩሳሌም ከመጓዝ የተለየ አይደለም። በፈጣሪ ተባርኮ የተሰጠን ለምለም መሬት ቅዱስ ነው። ሀዋስ ገናሌ አባያ ዴዴሳ ጊቤ ዋቤ የተቀደሱ ናቸው። የምንመገብባቸውን መብሎች ያፈራሉ። ሆራ (ማዕድን ውሀዎች) ለከብቶቻችንም ሆነ ለኛ ፈውስ ይሰጣሉ።

የሰው ልጅ ነጭ ቀይ ቢጫና ጥቁር ቀለም አለው። ኦሮሞ የቆዳ ቀለሙ ጥቁር ነው። አምላኩም ጥቁር ነው። ኦሮሞ "ጉራቻ ገረ ገርባ፣ ሴሞ ገረ ተሊላ" / ጥቁሩን ሰማይና ንፁህ ውሀ የፈጠርህ አምላክ ሆይ ይላል። (አፍሪካዊ የአርበኝነት ስሜት) ሴማዊው ዓለም የአብርሃም የይስሀቅና የያዕቆብ አምላክ ሲል፤ ዋቄፈታዎች የእናት የአባቴ አምላክ የዝናብ አምላክ የጉዮ አምላክ ወዘተርፈ ይላሉ። ዋቄፈና በአምላክ አንድነት አይደራደርም፤ ፈጣሪውን በበርካታ ስሞች ይጠራል እንዲህ እያለ፡- "ቶኪቻ መቃ dhiባ ጉዲች ሂሪያ ሂን ቁበኔ, ከን ዋን ሁንዳ ቤኩ፣ ከን ሂንዱኔፌ ከን ሂንጨብኔ" አንድ ፈጣሪ በብዙ ስሞች ትጠራለህ አምሳያ የለህም ሁሉን ታውቃለህ ከሃሌ ኩሉ ሁለምሉዕ ዘላለማዊ ኃያል ጉልበቶችህ የማይገዘሉ፤ ፈጣሪ ሁሉም የእጁ ስራ ነውና



t.me/OLDBOOKSPDF

እኩያም የለውምና ሰው ጣኦት ቢያመልክ አይቀናም። ቅናት የሚወዳደርህ ነገር ሲኖር ያለ ስሜት ነው። ፈጣሪ በፍጡሩ ይቀናል'ን?

ዋቄፈና ሰው በራሱ ንፁህ አዕምሮ የመያዙን ያህል፤ ከፉ ድርጊቶችንም ለማድረግ የሚያስችል የረቀቀና ውስብስብ አንጎል አለው። ከፉትም ሆነ ደግነት ከዚሁ አዕምሮ ውስጥ ይፈልቃል እንጂ ሰውን ያሳስቱ ርኩሳን መናፍስት ወይም አጋንንት የሚባሉ የማይታዩ ፍጥረታት የሉም። ሰው ከፉም ጥሩም ፈቃድ የሚኖረው በራሱ መሆኑ እንጂ ከሰው እየመረጡ ሰውን የሚያጠቁ ሰይጣኖች ስላሉ አይደለም የሚል ብርቱ እምነት አለው። እያወራን ያለነው ስለዋቄፈና እምነት መሰረት እንጂ ሰዎች በእምነቱ ወይም በሌላ እምነቶች ውስጥ ሆነው ስለሚያደርጓቸው ባዕድ አምልኮዎች አይደለም። ዋቄፈና ከፈጣሪ ውጪ ለየትኛውም አካል ወይም የሌለ መንፈስ ተገዢ አይደለም። ተገዢነቱ ለዋቃ ጉራቻ ብቻ ነው።

እንደ ዋቄፈና እምነት ፈጣሪ ቅዱሳን ሰዎች (Ayyantuu) በሰዎች መሀከል እንዲኖሩ አደረገ። ቅዱሳኑ ዋነኛ ተልዕኳቸው ሰዎችን ፈጣሪ ወደሚሻው መልካም ተግባር እንዲጓዙ መምከርና ማስተማር ነው፤ አያንቱዎች እኛ የፈጣሪ መልእክተኛ ነን አይሉም። ስለሆነም ሌሎች ትዕዛዛቸውን እንዲቀበሉ አያስገድዱም። እንኳን መልዕክተኛ ነን ሊሉ አምላክንም አይተን እናውቃለን የሚሉ አያንቱዎች በታሪክም ዛሬም ተሰምተው አይታወቁም። *Lambert Bartels በ1990 በደረሰው መጽሐፍ "Oromo Religion Myths and Rites of the Western Oromo of Ethiopia: An Attempt to Understand" ገጽ 92 አያንቱዎች ፈጣሪን አይተነው አናውቅም ስራዎቹን ግን እንረዳለን እናያለንም እንደሚሉ አብራርቶ አስናድቶታል።

አያንቱዎች ከመጥፎ ተግባራት ራሳቸውን ያቀቡ፣ በእለት ተለት ድርጊታቸው ምሳሌ የሆኑ፣ ጭምት በዝግታ የሚናገሩ፣ የስነምግባር ደረጃቸው የላቀ ናቸው። ፈጣሪና ቅዱስ መንፈስ አንድ አይደሉም የቅድስና መንፈስም ሰዎች ውስጥ አብሯቸው ያለ የፈጣሪ ስራ ነው። አያንቱዎች ፈጣሪ መልካምነትን ይወዳል በማለት ሰዎችን ወደ በጎ ምግባር የሚመሩ መንፈሳዊ መንገድን አመላካቾች ናቸው። የየአካባቢያችንን መልካም ነገር ቀንጨብጨብ እያደረግን እንማማር፤ በጥላቻ የምናጠፋውን ጊዜ በፍቅር እንለውጠው። እንደ ቆሼ ድንገት ድፍት ለሚሊብን ህይወት ከፉትን እንጠየፍ፣ ባለን መጨረሻውን በማናውቀው እድሜ ለመበላላት አበጋዝ አንሁን። በጥቢኛ ለሚነፋ ሆድ ሌሎችን አንብላ። ፈጣሪ ኢትዮጵያን በማያልቀው በረከቱ ያትረፍርፋት።



t.me/OLDBOOKSPDF

በዋቄፈና (ሀይማኖት) ዙሪያ ገለፃ ስናደርግ የእምነቱ ተከታዮች (ዋቄፈታዎች) ቁጥር በእነዚህ መረጃዎች ከሚገለፀው የተለየና የበዛ ሆኖ እናገኘዋለን። እንደ "The World Almanac (2010)" መረጃ:- ከኢትዮጵያ ህዝብ መሀከል 61 እጁ የክርስትና እምነት ተከታይ፣ 33 እጁ ሙስሊም እና 5 እጁ ዋቄፈና እና መሠል ሀይማኖቶች ተከታይ ነው። (እነዚህ መረጃዎች የሚያሳዩት ቁጥር ማነስም ሆነ መብዛት በእማኞች ወይም በእምነቱ ላይ የሚያመጣው ለውጥ የለም። እንደሚመታደል ሆኖ በሀገራችን የቁጥር ከፍ ማለትና ማነስ ላይ የሚነሱ እሰጥ አገባዎች የተለመዱ ናቸው። ሆኖም ለታሪክም ሆነ ለኑሮ አይጠቅሙንም።)

የሰውን ልጅ ማንነትና አብሮ የመኖር እሴቶች በመቅረፅ ረገድ ቤተሰብ፣ ማህበረሰብ፣ ተሞክሮ፣ ዳራ፣ መፃሕፍት፣ ጓደኞች፣ ትምህርት ቤቶች፣ የመገናኛ አውታሮች፣ የመንግሥት አመራር ዘይቤ፣ ትውፊቶች እና ዓለማዊ ሁኔታ የሚኖራቸው ድርሻ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። እምነት ስብእናን በመቅረፅ በኩል ሰው ስለምድራዊ አጭር ኑሮው ብቻ ሳይሆን እጅግ በጣም አሻግሮ ዘላለማዊ ህይወቱን ስለሚመለከትበት፤ በሚሠራው ግፍ ልክ ጊዜው ይጠርም ይርዘም 'የፈጣሪ ቁጣ ከእርሱም አልፎ ወደ ትውልዱ የሚሸጋገር እንደሆነ በፅኑ በማመኑ ምክንያት ኑሮውን በሀይማኖት እሴቶች ላይ ተመሥርቶ እንዲመራ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያበረክታል።

ደርግ ሥልጣን እስከያዘበት 1974 ድረስ ሀይማኖቶች የሰው ልጅ በፈሪሀ ፈጣሪ ላይ የተመሠረተ አኗኗር ይከተሉ ስለነበር በጦርነት ውስጥ ወይም በከፋ ግላዊ በደል ካልሆነ ጨከኖ በአምሳያው ላይ እጅ ማንሣቱ የተነወረ እና ህዝብ የሚፀየፈው ነበር። ደርግ ይከተለው በነበረው ኢ-ሀይማኖታዊ ርዕዮተ ዓለም ምክንያት ኢትዮጵያውያን አዳብረውት የነበረው መልካም ስነምግባር መሸርሸር ጀመረ። ወያኔ በ1991 ደርግን በከፋ ሁኔታ ተክቶ በትረ መንግሥቱን ከተረከበ በኋላ ከሀይማኖት አስተምህሮ ውጪ በመጓዙ ሁኔታዎች በፍጥነት ከድጡ ወደ ማጡ አሽቆለቆሉ።

በኢትዮጵያ ህዝብ መሀከል ሆን ብሎ ዘረኝነትን እንደ ነቀርሳ ተከለ። "ዘረኝነት ጥምብ ናትና ተዋት" የሚለው የእስልምና የመጨረሻውና ታላቅ ስብእና ነቢዩ መሀመድ ሰ.ዐ.ወ አስተምህሮ ተዘነጋ። የክርስትና እምድ ከሆኑት መልዕክቶች አንዱ:- "የሚያየውን ወንድሙን የማይወድ ፈጣሪውን አይወድም" ተረስቷል። ከፋፋይነት፣ ፀረ-ፍቅርነት፣ ጉበኝነት፣ አራጣ ማበደር፣ ዝርፊያ፣ በሰው ልጅ መነገድ፣ አድሏዊነት እጅግ በከፋ ደረጃ ተንሠራፉ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ያም ሆኖ ምዕመናን ባዳበሩት የዘመናት አብሮነትና ከውስጣቸው ተፈልቅቆ የማይነጠቅ እምነት የተነሣ አብያተ ጉዳማውያን እና አውነተኛ የእምነት አርበኞች ባደረጉት ተጋድሎ የመንግሥት ካድሬ የሆኑ የእምነት አባቶች ሴራ ብዙ ቢያፈርስም ግንቡ በዐና አለት ላይ የቆመ ሆነና ሊገረሠሥ አልቻለም። ከነተግዳሮቱ በዘመን እድሜ የበለፀገው ፍቅር በማህበራዊ መሠረቱ ውስጥ ብርቱ ከንድ ሆኖ ኢትዮጵያን ሊያፈርሱ የሞከሩት በየተራ እየፈረሱ ሀገር ቀጥላለች። በደማቅ ታሪካችን ሰበዞች ሀይማኖቶች ያበረከቱት አስተዋፅዖ ወቅያኖስ በመሆኑ መጠመር አይቻልምና 'ዓባይን በጭልፋ እንዲባል ለማሳያ እነሆ።

## ከርስትና

ክርስትና በኢትዮጵያ ሥነምግባር፣ ግብረገብነት፣ ቅርስ፣ ሥልጣኔ፣ የውጭ ግንኙነት፣ ትምህርት እና ታሪክ ውስጥ የላቀ ሚና ተጫውቷ፡፡ በመጫወት ላይም ይገኛል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልፅ እንደተቀመጠው በአንደኛው ክፍለ ዘመን የንግሥት ሕንደኬ ጃንደረባ እና በገንዘብዋ የሠለጠነ ሰው በሐዋርያው ፊልጶስ ስለመጠመቁ ተመልክቷል። ባዬ ፈለቀ፡- ""Questions About Kibre Negest" በሚል ርዕስ ለንባብ ባበቃው ሰነድ ንግሥት ሕንደኬ (ከ34 - 42) የመራች ንግሥት እንደሆነች በልዩ ገፅ P.X ይገልፅልናል። በመቀጠልም በግለሰቦች ደረጃ ከአንደኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ክርስትና መስፋፋት መቀጠሉን የክርስትና ታሪክ ፀሐፊ ከሆኑት ሩፊነስ እና ኮስምስ ጀምሮ በመስኩ ጥናት ባደረጉ ገለፃዎች ተወስቷል። ክርስትና የመንግሥት ሀይማኖት ሆኖ ብቅ ያለው በፓትርያርክ አትናቴዎስ የተላኩት አባ ፍሬምናጦስ (አባ ሰላማ እና አባ ከሣቴ ብርሀን በሚባሉ ስሞችም ይታወቃሉ) ንጉሥ ኢዛናን እና ሳይዛናን (ከንጉሡ ቀጥሎ ከፍተኛ ባለሥልጣን ምናልባት የኢዛና ወንድም ሳይሆን አይቀርም) በእምነቱ ህግጋት በቅደም ተከተል አብርሀ እና አፅብሐ በሚሉ የክርስትና ስሞች ካጠመቋቸው በኋላ ነው።

በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የቅዳሴ አገልግሎት በግሪክ ቋንቋ በውጪ ካሕናት ከተጀመረ በኋላ ቀስ በቀስ ወደ ግእዝ ቋንቋ ተሸጋግሯል። ይሁንና በስፋት ወደ አብዛኛው የኢትዮጵያ ክፍል የተስፋፋው ከ475 - 480 ከሶርያ ወደ ኢትዮጵያ በመጡ "ዘጠኙ ቅዱሳን"የዘጠኙ ቅዱሳን ቅዱሳን ዝርዝር፡- አባ ዘሚካኤል (አረጋዊ)፣ አባ ጰንጠሌዎን፣ አባ ይሳቅ (ገሪማ)፣ አባ አፍፄ፣ አባ ጉባ፣ አባ አሌፍ፣ አባ ይማታ፣ አባ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሊቃኖስ እና አባ ዕሀማ አማካይነት ተሰፋፍቷል። 'ተሰዓቱ ቅዱሳን' መፅሐፍ ቅዱስን ወደ ግእዝ ቋንቋ በመተርጎም እና በርካታ አብያተ ክርስቲያናትን በማነፅ ታላቅ አበርክቶ አድርገዋል። ክርስትና በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከተጫወታቸው ዓበይት ሚናዎች መሀከል፦ ታሪክ አዘል ቅዱሳት መፃሕፍት፣ ዛሬ በጎብኚዎች የሚያጥለቀልቁን ንዋየ ቅድሳት፣ የመስቀል በዓል፣ የጥምቀት በዓል፣ አክሱም ፅዮን ማርያም ቤተክርስቲያን፣ የላሊበላ ውቅር ፍልፍል አብያተ ክርስቲያናት፣ የጎንደር እና የላሊበላ የማጥመቂያ ሥፍራዎች፣ የአዳዲ ማርያም ቤተ ክርስቲያን (በዩኔስኮ የተመዘገቡ ቅርሶችና በዓላት) ይጠቀሳሉ።

"ማህሌታይ ቅዱስ ያሬድ" በስድስተኛው ክፍለ ዘመን በአፄ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግሥት የደረሳቸው መፃሕፍት፦ ድጓ፣ ጾመ ድጓ፣ ዝማሬ፣ መዋስዕት፣ እእጋረ ፀሐይ፣ መፅሐፈ ቅዳሴ እና መፅሐፈ ብርሀን ናቸው። ያሬድ ከምንም በላይ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የሚታወቀው በተለዩ ዘመን ተሻጋሪ ጣዕመ ዜማዎቹ ነው። በአገልግሎት የሚዜሙት የያሬድ ሦስቱ ታዋቂዎች ግዕዝ እዝልና አራራይ በመሆናቸው ሊቃውንት፦ 'ያሬድ የቤተ ክርስቲያን መቀነቷ (ድጓ) ነው' ሲሉ ይገልፃሉ።

1. ግዕዝ፦ ቀጥተኛ (ርቱዕ) ቀዳሚ ዜማ ተብሎ ይወሰዳል። የዜማው መጀመሪያ "ሃሌ ሉያ ለአብ" / ለአብ ምስጋና ይገባዋል ሲሆን፤ ከዚህው በመነሣት፦ 'ዝማሬ በሃሌ፣ ነገር በምሳሌ፣ ጠጅ በብርሌ' የተለመደ አባባል ሆኗል።

2. ዕዝል፦ (የታዘለ) በግዕዝና አራራይ ዜማዎች መሀከል የታዘለ ነው። ጠለቅ ያለ ምስጋና ይቀርብበታል።

3. አራራይ፦ በትዝታ የታጀበ፣ በጣዕሙ የሚመስጥ፣ ርህራሄ የሚንፀባረቅበት ዜማ ነው። ጣዕመ ዜማዎቹ ከመንፈሳዊ አገልግሎት ፈፅሞ የማይለዩ ከመሆናቸው ጎን ለጎን በሙዚቃዎቻችን ውስጥ ጭምር በሚገርም ሁኔታ በጉልህ ተንፀባርቀው ይታያሉ። ዜማዎቹ በዜማ ምልክቶች (ኖታዎች) የተዋቡ መሆናቸው በእድናቆት እጅን በአፍ ላይ ያስጭናል። የ'ቅዱስ' ያሬድን የዜማ ምልክቶች ሊቃውንት ስምንት፦ (ድፋት ሂደት ቅናት ይዘት ቁርጥ ጭረት ደረት ርክርክ) በማለት ያስቀምጧቸዋል። በጣና ቂርቆስ ገዳም የመፅሐፉ አዘጋጅ የተመለከተው ድጓ ምልክት አልተደረገበትም። ሊቃውንት በዘመን ብዛት በማሻሻልና በማከል የዜማ ኖታዎቹን አስራ ሁለት አድርሰዋቸዋል። ክርስቶስ ላይ ከደረሱ ሁኔታዎች ጋር ተሰናኝተው እንደሚከተለው ቀርበዋል።



t.me/OLDBOOKSPDF

1. ድፋት፦ የእሾህ አክሊል ከመድፋቱ ጋር የተያያዘ

2. ሂደት፦ መስቀሉን ተሸክሞ ወደ ቀራንዮ ከመሄዱ

3. ቅናት፦ አይሁድ በቅናት የተነሳሱበት መሆኑ

4. ይዘት፦ መያዙ

5. ቁርጥ፦ የሞት ፍርዱ ቁርጥ መሆን

6. ጭረት፦ ሲገረፍ ሰውነቱ ላይ ጭረት መታየቱ

7. ደረት፦ ደረቱ ላይ ቆመው በሃምስማር መቸንከራቸው

8. ርክርክ፦ የደሙ ነጠብጣብ አወራረድ

9. አዙር፦ ከሀና ወደ ቀያፋ፤ ከጲላጦስ ወደ ሄሮድስ ማዟዟራቸው

10. ዘንጥል፦ ልብሱን ዘንጥለው ስለመቅደዳቸው

11. አንብር፦ ሦስት ቀንና ሶስት ሌሊት በመቃብር ነበረ

12. ድርስ፦ በነቢያት የተነገረው ትንቢት ስለመድረሱ

ቀደም ብለን በስፋት ለማሳየት እንደሞከርነው ቤተ ክህነት ከዜማዎች፣ ገድሎች፣ መዋዕለ ዜናዎች ጀምሮ እስከ መፃሕፍት ቤት የጠለቀ ዕውቀት አበርክታለች። ዘመናዊ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት አንዷ የዕውቀት ከህሎትና ትጋት ምንጭ ሆና አገልግላለች።



t.me/OLDBOOKSPDF

## እስልምና

እስልምና በኢትዮጵያ ውስጥ መስፋፋት የጀመረው እጅግ በጣም በሰላማዊ አኳኋን ከመሆኑም ሌላ የኢትዮጵያን ህዝብ አብሮ የመኖር ልምድ በማጠናከር፣ ስነምግባርን በማስረፅ፣ የንግድ እንቅስቃሴዎችን በማሣለጥ፣ በውጭ ግንኙነታችን ቁልፍ ድርሻ በማበርከት፣ በቅርስ እና ፈርጀ ብዙ ሁነቶች በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የላቀ ሚና እየተጫወተ ቀጥሏል። ጄ. ስፔንሰር ትሪሚንግሀም፡- "Islam in Ethiopia" በተሰኘው መፅሐፉ እንደጠቀሰውና ከተለያዩ የተረጋገጡ የበይነመረብ ማስረጃዎች እንደተገኙ ማስረጃዎች ከቁሬሽ አረቦች የዘር ሐረጋቸውን የሚመዘዙት ነቢዩ መሀመድ ሰዐወ (570 - 632) ከቅዱስ ቁርዓን ጋር የእስልምናን "የሰላም ሀይማኖት" መርሆዎች መስበክ ጀመሩ። 'በአንድ አምላክ እንጂ በብዙ ጣዖቶች ማመን የለብንም' የሚለው አስተምህሯቸው በአጭር ጊዜ ውስጥ በመካ አካባቢ ተከታዮችን አበራከተላቸው። የጣዖቶቹ ካዳሚዎች የአማኞቻቸው ማሽቆልቆል እና የገቢያቸው መዳከም ቡብርቱ ስላሳሰባቸው በሙስሊሞቹ ላይ ጥቃት መሠንዘር ጀመሩ። ነቢዩ መሀመድ ተከታዮቻቸውን በ615 በመሰብሰብ የሚከተለውን ታሪካዊ ንግግር አደረጉ ሲል ትሪሚንግሀም በገለፀነው መፅሐፍ ገፅ 44 እንደሚከተለው አስነብቦናል፡-

አላህ ጥንካሬ እስኪሰጠንና አምልኳችንን በተገቢው መንገድ የምንከውንበት ያ ቀን እስኪመጣ ወደ ሀበሻ ምድር (ኢትዮጵያ) ሂዱ። የአቢሲኒያ ንጉሥ ሀይማኖተኛ ፍትሐዊ እና ጉዳያችንን በቀናነት የሚመለከትልን ነው። በእርሱ ስም የሚሰደድ የለም። ፈጣሪ ከስቃያችሁ እረፍት ይሰጣችኋል። ምድሪቱም በደጋግ ሰዎች የተሞላች ናት።

ከሚል የተስፋ ቃል ጋር ላኩዋቸው። ይህም ነቢዩ መሀመድ ከመካ ወደ መዲና ሀይማኖታዊውን የስደት ጉዞ "ሂጅራ" በ622 ከማካሄዳቸው ከሰባት ዓመታት በፊት ነው። እንደ ትሪሚንግሀም ገለፃ በ615 የተካሄደውን ይህንን ጉዞ "የመጀመሪያው ሂጅራ" ይሉታል። እንደተጠበቀው ኢትዮጵያ በንጉሥ አርማህ አማካይነት በፈገግታ ተቀበለቻቸው። ይሁንና ደስታቸው ብዙም ሳይዘገይ ቁሬሽ አረቦች እግር በእግር በመከታተል ክስ አቀረቡባቸው። ቁሬሾቹ ከፍተኛ የወርቅ ሥጦታ ለንጉሡ በማቅረብ ሙስሊሞቹን አሳልፎ እንዲሰጣቸው ጠየቁ። ንጉሡ በችሎት ተቀምጦ የኢትዮጵያን ካሕናት ጨምሮ በመሰብሰብ የሁለቱንም ወገን ጉዳይ አደመጠ። የቀረበባቸው ክስ 'አዲስ ሀይማኖት በማምጣት' የሚል ሆኖ ተገኘ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ኋዋ በኋላ

የግዖት አምላኪዎቹን የእምነት መሠረት እና የሙስሊምን አምስቱን ዋነኛ አላማዎች፡- በአንድ አምላክ ማመን፤ በቀን አምስት ጊዜ ሰላት መስገድ፤ ምፅዋት መስጠት (ዘካት እቅም ካለ ሰደቃ)፤ በህይወት ዘመን ወደ ቅዱሳን መካናት መጓዝ (ሃጅ) እና በዘጠነኛው የረመዳን ወር በፆም መወሰን መሆናቸውን የነቢያትን ሁኔታ ገልፆ አስረዳቸው። እንደ ትራሚንግሃም ደግሞ (በተመሣሣይ ምንጭ ገፅ 45) ጃፋር የተባለው የሙስሊሞቹ ተወካይ ለንጉሡ ከቅዱስ ቁርዓን (iv 169; xix 16 - 34) በመጥቀስ እስልምና የክርስትና ሊላው መልክ እንደሆነ ገልፆለታል። ነጃሺ ይህን ሲሰማ መልሰም ሳይጠብቅ ሙስሊሞቹን ሊታደግ ያለማቅማማት ወሰነ። አሳዳጆቹንም ከሀገሩ ምድር እንዲወጡ አዘዘ። በበርካታ ምንጮች እንደተረጋገጠው ንጉሡ ጉዳዩቸውን በጥሞና ካዳመጠ በኋላ የወሰነው ውሳኔ የሚከተለው ይዘት ነበረው።

> *ቁሬሽ አረቦች እንዷን የበዛ ወርቅ ተራራ ያህል ጉብታ ብታቀርቡ ፍትህ በወርቅ አትለወጥም። የሁብት ችግርም የለብንም። በአንድ ፈጣሪ የሚያምኑት እነዚህ ወገኖቹ አንዳች እንኳ ጥፋት አልተገኘባቸውምና አሳልፌ አልሰጣችሁም። ስለዚህ እናንተ ወደ መጣችሁበት ተመለሱ። እንግዶቹ በሀገሬ ግዛት ባሻቸው ሥፍራ ይኑሩ።*

በማለት የመኖሪያ ፈቃድ ሰጣቸው። ንጉሥ አርማህ ለሙስሊሞቹ ባሳየው ፍቅር ምክንያት ወደ እስልምና ተቀይረዋል በሚል አህመድ ነጋሽ እና አል ነጃሺ በተሰኙ ስሞች ስለንጉሡ የፃፉ ከመኖራቸውም ሌላ በመቀሌ ውስጥ የአል ነጃሺ መስጊድ ይገኛል። ይሁንና ንጉሥ አርማህ ወደ እስልምና ስለመቀየሩ የተፃፉ ታሪካዊ ማስረጃዎች አላገኘንም። ቀጣዮቹ የአክሱም ነገሥታት በሙሉ ክርስቲያን መሆናቸው ሲታይ የንጉሡን እስልምናን መቀበል አጠራጣሪ ያደርገዋል። (በጉዳዩ ዙሪያ ጥልቅ ጥናት ቢደረግ ምናልባት ከኢማም አህመድ ኢብራሂም አስቀድሞ አህመድ ነጋሽ የመጀመሪያው ሙስሊም መሪ ስለሚያደርጋቸው በታሪካችን ላይ ተጨማሪ ድንቅ ነገር ይሆናል፤ ኢትዮጵያ የሙስሊም የክርስቲያን እና የተለያዩ እምነቶች የጋራ ቤት ናትና።)

በ624 ነቢዩ መሀመድ በያትሪብ (መዲና) ከተማ አቅራቢያ በተካሄደው "በድር ጦርነት" ቁሬሽ አረቦች ላይ አንፀባራቂ ድል ተቀዳጁ። በ629 በድል አድራጊነት በአዲሷ ስያሜዋ ከመዲና 'መዲናት አል ነቢ' (የነቢዩ ዋና ከተማ) ወደ መካ ተመለሡ። አስከትሎም አብዝተው ከሚወዷት ልጃቸው ሩቂያ ጀምሮ ወደ ኢትዮጵያ



t.me/OLDBOOKSPDF

ለመጣት ተከታዮቻቸውና ቤተሰቦቻቸው 'ተመልሳችሁ ኑ' የሚል ጥሪ አደረጉ። በነገራችን ላይ የመጀመሪያውን 'አዛን' - የጸሎት ጥሪ ያደረገው ቢላል ኢትዮጵያዊ መሆኑ አይዘነጋም። በ632 የነቢዩ መሀመድ ጤንነት መልካም ሁኔታ ላይ አልነበረም። በመሆኑም ሙስሊም ወገኖቻቸውን ሰብስበው ግልፅ መመሪያ አስተላለፉ።

ውድ ሙስሊም ወገኖቼ በዚያ ክፉ የስደታችን ጊዜ የአቢሲኒያ ወንድሞቻችን መጠለያ ሆነውናል። በአያያዝም ከክብራችን አንዳች ስንኳ አላጓደሉም። ከቁሬሽ ሰይፍ ወገኖቻችንን አትርፈዋል። አስቸጋሪ ሁኔታ ተፈጥሮ ጦርነት ግድ በሆነበት ጊዜ ጭምር የሀበሻ ክርስቲያን ወንድሞቻችሁ ላይ ጦርነት አታውጁ። በችግራቸው ጊዜ እገዛን አድርጉላቸው። ምርቃቱን 'ነአም አሚን' ብላችሁ ተቀበሉ።

ለዚህ ትውፊትና በሰነድ የበለፀገ እውነት ማስረጃ የሚሆነን ሙስሊም ዐረቦች በጣም ኃያል ሆነው በስምንተኛው ክፍለ ዘመን ከግብፅ በስተምዕራብ የሚገኙ የመግርብ ግዛቶችን ቱኒዚያ ሊቢያ ሞሮኮ አልጄሪያ ሰሀራዊ በሀይል በመቆጣጠር፣ የግዛቶቹን ነዋሪዎች በርበሮችን ወደ አረብነትና እስልምና ሲቀይሩ ኢትዮጵያን በተመለከተ በተመሣሣይ ጊዜ በንግድ ውድድር ምክንያት የአዱሊስን ወደብ ብቻ በማፈራረስ ሰብአዊ ጉዳት ሳያደርሱ መመለሳቸው ገላጭ ነው። እስልምና በሌላ በኩል በኢትዮጵያ ምድር የተስፋፋው እንደ ክርስትናው ሁሉ በሰላማዊ መንገድ ነው።

ሂደቱም በመጀመሪያ ሙስሊም ነጋዴዎች ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ በሥራ ያግዟቸው የነበሩ ወገኖችን ስለ ሀይማኖቱ ሰበኳቸው። ከዚሁ መሣ ለመሣ ከኢትዮጵያዊ እንስቶች ጋር በመሠረቷቸው የጋብቻ ግንኙነቶች የሙስሊም ቤተሰቦች ተፈጠሩ። በተናጠል ከግለሰቦች ወደ ቤተሰብ ደረጃ ያደገው ሂደት የሙስሊም አስተማሪዎችን 'ኡላማዎችን' በማገገ ወደ ሙስሊም ማህበረሰብ 'ኡማ' ደረጃ አደገ። በተለይም በዘይላ ወደብ አካባቢ ወደ እምብርት የንግድ ማዕከሎች በመስፋፋት የመጀመሪያው ኢስላማዊ የሡልጣን አስተዳደር "የሸዋ ሡልጣናዊ ግዛት" በ829 ተመሠረተ። የሥርወ መንግሥቱ ስም 'ማኽዙማይት' ነበር። ይህ የሡልጣናዊ ግዛት በቅርቡ በነበረ ሌላ ጠንካራ አስተዳደር "የኢፋት ሡልጣናዊ አስተዳደር" በ1285 ተጠቀለለ። በሸዋ ሡፊ ግዛት ኢፋትን ጨምሮ ተመሥርቶ የነበረው ይህ አመራር "ወላዝማ ሥርወ መንግሥት" የሚያስተዳድረው ሆኖ መሥራቹ ዑመር ወላዝማ ነበር።

ከ1270 እስከ 1285 ከአምባሰል እስከ ሸዋ ተዘርግቶ የነበረው የአጼ ይኩኖ አምላክ አመራር ከኢፋት ሡልጣን ጋር ጎን ለጎን በመገፋፋት ቢቆይም ለቀጣዮቹ 47 ዓመታት



t.me/OLDBOOKSPDF

አይሉ የሚወጣ ሀይል አልነበረም። ከ1314 - 1344 የመራው ኃያል አመራር አፄ አምደጽዮን በ1332 የኢፋትን ሡልጣናዊ ግዛት ሲያሸንፍ ሸዋ ከተማው የነበሩት የወላዝማ መሪዎች ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ በማፈግፈግ የአዳልን ሡልጣናዊ ግዛት በ1364 አቋቋሙ። የአዳል አመራር በሂደት በመጠናከር ከ1527 እስከ 1543 በኢማም አህመድ መሪነት መሀከለኛውን የኢትዮጵያ ክፍል የአማራና የትግራይን ግዛት በሙሉ እስከ አከሱም መቆጣጠር ቻለ።

በአፄ አምደፅዮንና በተከታዮቻቸው ፋሪ ዝቋላ ወጨጫ መናገሻ አንኮበር ዳሞት ሀዲያ አልፎም በደቡብ እስከ ሶማሊያ ዘይላና በርበራ፤ በሰሜን እስከ ቀይ ባህር ተቆጣጥሮ የዘለቀው የደጋማው ሰሎሞናዊ ሥርወ መንግሥት በ16ኛው ክፍለ ዘመን በአፄ ሚናስ ዘመነ መንግሥት እየገፋ በመጣው የኦሮሞ እንቅስቃሴና ያላባራ የአዳሎች ጥቃት መሠረት ወደ ወሎ ተንቀሳቅሶ በስተመጨረሻ የጎንደርን ዘመነ መንግሥት መሥርቷል። ይሁንና የሸዋ አስተዳደር መሠረቱን ሳይለቅ ቆይቶ በ1696 በነጋሢ ክርስቶስ አማካይነት የተጠናከረ አስተዳደር መመሥረት ችሏል። የነዚህ ሁነቶች ድምር የሸዋ ፖለቲካ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የበርካታ መስተጋብሮች ድምር እና የሁሉም ወገን አሻራና መገፋፋት የጎለበተበት ቦታ ያደርገዋል።

እስልምና በዳህላክ በኩል በ10ኛው ክፍለ ዘመን "የዳህላክ ሡልጣናዊ መንግሥት" ሆኖ ቢመሠረትም በሥፍራው ክርስትና ቀድሞ በመጠናከሩ የተነሣ ወደ መሀል በሌሎቹ አቅጣጫዎች በተስፋፋው ልክ ጎልቶ መታየት አልቻለም። በጋምቤላ እና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ አካባቢ በርካታ በሼክ የሚመሩ "የሼክደም ግዛቶች" ተፈጥረዋል።

እስልምና በኢትዮጵያ ሥነፅሑፍ ታሪክ የመድረሳ ትምህርት ቤቶች ማደግ የተለያዩ አስተዳደራዊ ሥርአቶች በመመሥረት ታላቅ ሚና ተጫውቷል። በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት በተዘጋጀ "Ethiopia Today Education" ገፅ 7 ላይ የሚከተለው ተመዝግቧል፦

> *There is a close parallel between the church schools of the Orthodox Church and the Koranic schools of the Muslim faith... Koranic schools appeared later - probably in the eleventh century in Ethiopia At this*



t.me/OLDBOOKSPDF

*period, the center of Islamic learning in Ethiopia was in Ifat later moved to Harer.*

ገፅ 9 ምንጩ፡ የሚጠቅሰው ጉዳይ፡- "Education of the type already described was offered only through Church, Koran and Mission schools.

መረጃው በጉልህ እንዳሰመረበት በኢትዮጵያ ሁለንተናዊ እሴት እስልምና ከክርስትና ጋር ተደጋግፎ የሚደነቅ ጥበብ አስተላልፎልናል። ዘወትር አያቶቻችን ላቆዩን መልካም ውርስ በትህትና እያመሰገንን እንቀጥላለን።

## እስልምና እና የዛግዌ ሥርወ መንግሥት

በአክሱም ዘመነ መንግሥት የፍቅር አቀባበል የተደረገለትና ከዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ሠፋፊ አስተዳደሮችን የመሠረተው እስልምና የሸዋ ኢፋት የሀዲያ የባሊ የደዋሮ የፈጠጋር እና አያሌ አስተዳደሮችን በመመሥረት ከክርስትና እና ሀገር በቀል እምነቶች ጎን ለጎን የበለጠ እየደረጀ ሄደ። የአርማህ አቀባበል፣ በኢትዮጵያ ውስጥ በፍቅር መሠበኩ የፈጠረው ምቹ አጋጣሚ፤ በዛግዌ የሥልጣን ዘመን (1150 - 1270) በድጋሚ ከውጪው ዓለም ጋር የበለጠ ተሣሠረ። ይኸውም ከ1095 - 1097 በአውሮፓ ከፍተኛ ጠኔ ተከሰተ። ከረሀቡ መከፋት የተነሣ ሰዎች የዛፍ ቅርፊትና የሸክላ አፈር ከመመገባቸውም ሌላ ጉልበት ያለው ሌላውን መመገብ (አስቃቂው ሰዎች ሰዎችን መብላት / Cannibalism) ደረጃ ተደረሠ። ዳግማዊ ኧርባን የተባሉት የካቶሊክ ጳጳስ በ1095 ድሆችን በመሰብሰብ በግልፅ ቋንቋ ዲስኩር አደረጉ፡-

የክርስቶስ ቅዱስ ሀገርና የክርስቲያኖች ቅዱስ መሬቶች የሆኑት ፍልስጥኤምና ሶርያ በማያምኑ ቱርኮች በግፍ ተይዘዋልና ነፃ እናውጣቸው። ይህንን በማድረጋችሁ ከየትኛውም ኃጢአት ስርየት ታገኛላችሁ። በሁብትም የተትረፈረፈ ንብረት ታፈራላችሁ በማለት መርቀው ላኳቸው።

ለስሙ "ቅዱስ" የሚል ቅጥል የተሰጠው የመስቀል ዘመቻ "ክሩሴድ" ከ1095 1291 ተካሄደ። ዘማቾቹ የተጓዙበት ዓላማ ቅንጣት ሀይማኖታዊ ተልዕ



t.me/OLDBOOKSPDF

እንዳልነበረው የሚያስገነዝበው በጉዟቸው ከባይዛንታይን ጀምሮ የክርስቲያኖችን ሀገሮች እየዘረፉ በመጓዛቸው ከመሆኑም ሌላ 'ጦርነት ቅዱስ የለውም'ና ነው። ዘመቻው የታለመለትን ግብ መምታት አልቻለም። ይልቁኑ በየሥፍራው መሸነፍ የዘማቾቹ እጣ ፈንታ ሆነ። በተለይ 1187 ላይ የተነሣው ሳላዲን የሠነዘረው መልሶ የማጥቃት ዘመቻ የመስቀል ዘማቾቹን አሽመደመዳቸው።

የመስቀል ዘማቾቹ ሽሽት ያስጋቸው የዘመቻው አቀናባሪዎች በትውፊት ይነሳ የነበረውን ጠንካራ የክርስቲያን መንግሥት 'ፕሬስተር ጆን ኦብ ኢንዲስ' / 'ቄስ ንጉሥ ዮሐንስ' በ1177 'ለአውሮፓ ክርስቲያን መንግሥታት ደብዳቤ ፅፎ እንደነበር' የተወራውን ወሬ በመከተል፤ የመስቀል ዘመቻ አስተባባሪዎቹ፡ መገኛውን ማፈላለግ ጀመሩ። እስከዚያው የመስቀል ዘማቾቹን ወኔ ለመመለስ በማሰብ 'ሰልጁክ ቱርኮችን ከእኛ በተቃራኒ አቅጣጫ እየወጋ ያለ የክርስቲያን ንጉሥ ስለተነሳ፤ ቱርኮቹ ያበቃላቸዋልና በርቱና ተዋጉ' የሚል የሀሰት ወሬ ነዙ። ይልቁንም ወደ ኢየሩሳሌም ለሀይማኖት ከኢትዮጵያ የሚሄዱ ምዕመናንና መነኮሳት ስለኢትዮጵያ ይገልፁ ከነበረው መረጃ በመነሣት ኢትዮጵያ "የቄስ ንጉሥ ዮሐንስ ሀገር" እንደሆነች በማመን ወደ ዛግዌ መሪዎች የእግዛን ጥሪ አቀረቡ። የደብዳቤው ይዘት "ክርስቲያናዊ ወንድማማችነት" ላይ ያነጣጠረ ነበር።

ይሁንና የዛግዌ መሪዎች የሠጡት ምላሽ አጭርና ግልፅ፡- 'ከሙስሊም ወንድሞቻችን ጋር የምንዋጋበት አንዳችም ምክንያት የለም' ሆነ። የሙስሊም ሡልጣኖች ሁኔታውን በአንክሮ ከተከታተሉ በኋላ ለኢትዮጵያ በቋሚነት በቅርብ ምሥራቅ (Near East) ውስጥ "ዴር ሡልጣን ገዳም" አበረከቱ። ይህ በተደጋጋሚ የኢትዮጵያ መሪዎች ከሙስሊም ሀገሮችና መንግሥታት ጋር የሚያደርጉት የፍቅር ግንኙነት መገታ ውጤት ነበረው። በአንድ በኩል በኢትዮጵያና በሙስሊም ሀገሮች የተጠናከረ ቅርርብ መፈጠሩ እና በሌላ በኩል በኢትዮጵያ ውስጥ የሙስሊም - ክርስቲያን ትሥሥር ያለማቋረጥ መደርጀት አስከተለ።



t.me/OLDBOOKSPDF

## እስልምና እና ጎንደር

የጎንደር ዘመነ መንግሥት (1632 - 1769) በኢትዮጵያ ሥልጣኔ ውስጥ በርካታ አሻራዎቹን አሳርፏል። የፋሲለደስ ግንብ፣ የመዋኛ ሥፍራዎች፣ ከ60,000 ያላነሰ የከተማ ነዋሪ፣ ድልድዮች፣ ቋሚና ሳምንታዊ ገበያ፣ የምግብና መጠጥ ቤት አገልግሎት፣ የማህሌት አቋቋምና በርካታ ዕሑፎች ተጠቃሽ ናቸው። በዘመኑ ፈላሻዎች አዲስ ዓለም እና ሙስሊሞች ቤል ኤል ኢስላም የተለዩ የመኖሪያ ሠፈሮች ነበሯቸው። ከ1622 - 1632 (የካቶሊክ አስር ዓመታት) የተፈጠረውን ቀውስ ተከትሎ ፋሲለደስ አውሮፓውያን ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገቡ የሚከለከል ህግ "Close Door Policy" በመከተል የማያፈናፍን አቋም ሲይዝ የመንና በአካባቢው ከሚገኙ የሙስሊም መንግሥታት እንደ ሱዋኪን ካሉት ጋር የጠነከረ ግንኙነት ማካሄዱ በኢትዮጵያ የሙስሊምና ክርስቲያን ግንኙነት የፀና የፍቅር ግንብ መሆኑን ፍንትው አድርጎ ያሳየናል።

## እስልምና እና ዘመነ መሣፍንት (1769 - 1855)

በዘመነ መሣፍንት ውስጥ እስከ 1853 በቆየው የታሪክ ዘመን በተጨባጭ ኢትዮጵያን ለ80 ዓመታት የመሩት ከአሊ ጓንጉል አንስቶ እስከ አሊ አሉላ የ'ወረሺህ' ሙስሊም መነሻ ያላቸው መሆኑ እስልምና ቤተ መንግሥት ውስጥ ጭምር ከክርስትና ጋር እጅ ለእጅ ተያይዞ መራመዱን ያሳያል። በተለይም ዘግይቶ በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በአዲስ አበባ ውስጥ መስጊዶች መበራከታቸው፤ በልጅ ኢያሱ ዘመነ መንግሥት 1911/13 - 1916 መንግሥት ለሙስሊሞች መስጊድ መገንባትና በአመራር ውስጥ መመደብ በበጎ ጎን የሚጠቀሱ ናቸው። (ይህ ሲባል እስልምና በሚፈለገው ደረጃ ተገቢው ተደርጎለታል ለማለት አያስደፍርም። ሙስሊሞች በአክሱም ከተማ ውስጥ መስጊድና መቀበሪያ ከማጣታቸው፤ በአፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት በወሎ ሙስሊሞች ላይ የተፈፀመው አሳዛኝ ድርጊት እና በየጊዜው የተንፀባረቁ አመለካከቶች ከደርግ ጊዜ ጀምሮ መከሠም መጀመራቸውን መገንዘብ አያዳግትም።)

ትልቁ ቁምነገር መሪዎች የትኛውንም አይነት አድልዎ ያንፀባርቁ ጊዜ የማያደበዝዘው የክርስቲያንና ሙስሊም ፍቅርና እንደ ወሎ ነጊሌ ቦረና (ነጌሌ) እና በሠፊ ቁጥር የሙስሊምና ክርስቲያን ነዋሪዎች በሚገኙባቸው ሥፍራዎች በጋብቻ ጭምር የሚገለፅ፣ በዓላትን አብሮ ማክበር፣ በዋና ዋና ፍፃሜዎች የሠርግ ሥርአት፣ የቀብር ሂደት፣ እድር፣ ደቦ እና አብሮነት ትሥሥሩ እጅግ ጠንካራ ነው። ለመሆኑ በአደጋ ጊዜ



t.me/OLDBOOKSPDF

ነፍሳችንን ለማዳን ከቀይ መስቀል የምንወስደው (የሚሰጠን) ደም የሙስሊም ነው ወይስ የክርስቲያን፣ የኦሮሞ የአማራ የጋምቤላ የትግራይ የሶማሊ የስልጤ የወላይታ የወንድ የሴት የወጣት የጎልማሳ ... ? ለቅፅበት አስበነው እናውቅ ይሆን? የውጭ ጠላት ቢመጣስ በየትኛው ልዩነት ተለይተን እንፋለም ይሆን? ሁልጊዜም ቀዳሚው አንድነታችን ነው።

በአንድ ሀገር ውስጥ ከሁሉም የሚቀድመው ነገር ፅኑ ፍቅር ነው። ፍቅር ሲኖር የመዋደድ ውጤቶች የሆኑት፦ መተሳሰብ መከባበር መቀራረብ ሰላም ብልፅግና አንድነትና መልካም ነገሮች ሁሉ ተከትለው ይመጣሉ። "ሰላም ያስፈልገናል" የሚለው ምኞት ነው። ሰላም ይሻለናል በሚል ዲስኩር ሀገር አይረጋጋም ሰላም ውጤት ነውና። መሠራት ያለበት ሰላምን የሚያጠፋው ጉዳይ ላይ ነው። ሰላም ለምን ጠፋ? ፍቅር ስለደበዘዘ። የሁሉም ዜጋ ጥሪ የሚሆነው ለፍቅር መሥራት ነው 'ፍቅር ያሸንፋል'ና። 'እስልምና' ትርጉሙ 'የሰላም ሀይማኖት' ነው የሚል ነው። ስናጠቃልለው ለሰላም የማይሰራ እውነተኛ ሙስሊም አይደለም።



t.me/OLDBOOKSPDF

# የገዳ ሥርዓት (የዴሞክራሲ ውኃ ልክ)

በዓለማችን የዴሞክራሲ ሥርዓት ታሪክ ውስጥ ከገዳ ሥርዓት ጋር ሊወዳደር ቀርቶ ሊነፃፀር የሚችል አንዳችም ተሞክሮ የለም። ደረታችንን በደስታ ከሚያሠፉ ታላላቅ የታሪካችን ሰበዞች መሀከል አንዱ የገዳ ሥርዓታችን ነው:: እንዲህም ሆኖ ተገቢው ትኩረት ሳይሰጠው ማየት ግን ያሳዝናል:: ተሞክሮው በቂ ትኩረት እንዳልተቸረው ከሚያሳዩ ማስረጃዎች አንዱ በሀገራችን በዘመነ ወያኔ የተቀረፀው "የሥነ ምግባርና የሥነዜጋ ትምህርት" ስለዴሞክራሲ በሚያወሳው ክፍሉም ሆነ በየትኛውም ይዘቱ ለገዳ አስተዳደራዊ ሥርአት አንድ ንዑስ ርእስ ቦታ እንኳ አለመስጠቱ ነው። በታሪክ ትምህርት ውስጥም ቢሆን በርካታ አላስፈላጊ ነጥቦች ታጭቀው በስሱ የገዳ ሥርአት ዴሞክራሲያዊ መሆኑን ከማውሳት ራቅ ብሎ በሚገባ ለማንሳት አልተደፈረም።

በመሆኑም ሥርአቱን እጅግ ረቀቅ ብለው ከተዘጋጁ ጠማሮች ለመረዳት ስለሚያዳግትና በንፅፅርም ተገቢ ስፍራ ተሰጥቶት ገላጭ በሆነ መንገድ አለመዘጋጀቱን ታሳቢ በማድረግ፤ ውስብስብ አደረጃጀቶችን በመተው፤ በቀላሉ መጨበጥ የሚችሉ ሀቆችን በግልፅ አቀራረብ በማሳየት ታሪካችንን ሙሉ ለማድረግ በሚደረገው ጥረት አንድ እርምጃ ወስደናል:: ስለሥርአቱ ረቂቅነት ከ1,000 ያላነሱ የአንትሮፖሎጂ የህግ እና የማህበራዊ ሳይንስ ጥናቶች የተካሄዱ ሲሆን አቀራረባቸው ጥቅል በመሆኑና ውስጣዊ ይዘቱን በመግለፅ ረገድ ተደራሽ ስላልሆነ በዚህ መፅሐፍ ውስጥ የፕሮፌሰር አስመሮም ለገሠ:- "Gada: Three Approaches to the Study of African Society" እጅግ የበሰለ የምርምር ሥራ እና በቅርቡ ለህትመት ከሚበቃው የታየ ቦጋለ አረጋ:- "የቦረና ኦሮሞ የታሪክ ቅኝት እስከ 1974" ፅሑፍ የተቀነጨቡ እውነታዎች በፍቅር ቀርበዋል።

የገዳ ሥርአት በስፋት እንዳይታወቅ በማድረግ በኩል የኦሮሞ የዘውግ ልሂቃን በመጀመሪያው ረድፍ ይሰለፋሉ። ወገንን ከወገን ለማናከሥ ከሚረጩት መዋዕለ ነዋይ፤ ለጥላቻ ከሚያባክኑት አእምሮና ለማለያየት ከሚያፈሱት ጉልበት፤ በተንኮል ከሚያመነጩት ጥላቻ 1/10ኛ ያህሉን የገዳ ሥርአትን ለማስተዋወቅ ቢሠሩ ኖሮ



t.me/OLDBOOKSPDF

ትውልዱ ላይ ምን ያህል ለውጥ ማምጣት ይችሉ እንደነበር ሲታሰብ ያስቆጫል። አሁንም ስላልረፈደ ከፋትን በጅምላ አምርቶ በችርቻሮ ከማከፋፈል፣ የየማህበረሰባችንን ታሪክ በፍቅር ገበያ አውጥተን መሸጥ ብንችል የተትረፈረፈ ሰላም እናገኛለን።

የአቴንስ ዴሞክራሲ የመላው ዘግይተው በአንድ ሀገር ጥላ ሥር የተሰባሰቡ የግሪክ የተለያዩ መንግሥታት ነዋሪዎች ተደርጎ ከቀረበው፣ እጅግ በላቀ ደረጃ የገዳ ዴሞክራሲ ለዘመናት አብረን የዘለቅንና በታላቋ ኢትዮጵያ ውስጥ የምንኖር ኢትዮጵያዊ ዜጎች ያለልዩነት የጋራ ታሪካችን አካል ነው። በዚህ ልክ የማያስብ ቀንጨራ አእምሮ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ውስጥ ማየት ያስቆጫል። ጥሬውን ለማብሰል ማገዶ መጨረስ በጣሙን አስፈላጊ ነው። ዓለም ለዘመናት በአያሌ ችግሮች ተተብትቦ የተያዘውን የአቴንስ ዴሞክራሲ እንደ ጥንት ዴሞክራሲ ጣሪያ ቆጥሮ ሲግር በአርምሞ መመልከታችን ሳያንሥ፤ ገዳ በእናት ምድሩ በሥርአተ ትምህርቱ ውስጥ ሥፍራ ሲያጣ በለሆሳስ ማለፉን እንደምን ያለ አእምሮ ሊቀበለው ይችላል?

የገዳ ዴሞክራሲን በሰፊው ያስተዋወቁትና እጅግ አድናቆት ሊቸራቸው የሚገባው ኤርትራዊው ፕሮፌሰር አስመሮም ለገሠ ናቸው:: ይሁን እንጂ"Oromo Democracy, An indigenous African Political System" በሚል ርዕስ በሰነዱት ሌላ ታላቅ የምርምር ሥራ ገፅ 254 ላይ ከጠቀሱት የገዳ ሥርአት ድክመቶች (1. ሴቶችን ከመደበኛው የፖለቲካ ሥርአት ማግለል፣ 2. የፖለቲካ ሥርአቱ ግትርነት፣ 3. በፖለቲካ ሥርአት ውስጥ የሚንፀባረቅ 'ኮራፕሽን'፣ 4. ባህላዊ ተቋማት እና ዘመናዊ መንግሥታት አለመጣጣም) ጋር የዚህ መፅሐፍ አዘጋጅ ተቃርኖ አለው። ምክንያቱም ኀልቆ መሣፍርት ዘመናት ያሳለፈውና በውስጡ እጅግ የተረጋጋ ሥርአት የፈጠረው ገዳ ምን መልከ አለው? የገዳ ዲሞክራሲ ከዘመኑ አንጻር ምን ያህል የረቀቀ እንደነበር እስቲ ብዙ ከተጻፈለት ( ከአቴና) ዴሞክራሲ ጋር አነፃፅረን እንፈትሸው።

የአቴንስና የገዳ ዴሞክራሲ ንፅፅር:- የአቴንስ ዴሞክራሲ ከግሪክ መንግሥታዊ ከተሞች (Polis) በአንደኛዋ አቴንስ ብቻ የተደረገ ልምምድ ነበር። ዛሬ በግሪክ ውስጥ በአንድ ሀገር የተካተቱ ጎረቤት ሀገራት ስፓርታ ሚሌቱስ ሳሞስ አራጎን ቴብስ እና በርካታ ሌሎች ከተሞች የዴሞክራሲ ገቢር ሽውታ ስንኳ አልነበራቸውም። በመሆኑም በአንክሮ ልዩነቱን እንግለጥ:-



t.me/OLDBOOKSPDF







t.me/OLDBOOKSPDF

## ማነፃፀሪያ አህድ አንድ፡- (የቆይታ ዘመን)

ዓለም የሚያወራለት የአቴንስ ዴሞክራሲ እንደ "The World Almanac, 2010" መረጃ ገፅ 653፡- "ዴሞክራሲ በአቴንስ ውስጥ ከክርስቶስ ልደት በፊት (ከ495 - 429) መሪ በነበረው ፔሪክለስ ጊዜ ብልጭ ብሎ በ404 ዓ.ዓ አቴንስ በስፓርታ ስትሸነፍ ከስሟል።" *በቦረና እና በጉጂ፡- ለዘመናት የመቆየቱ ግምት እንዳለ ሆኖ በመረጃ በተደገፈ መልክ ከ1460ዎቹ ጀምሮ እስካሁን ድረስ የገዳ ዴሞክራሲ ህያው ሆኖ ቀጥሏል። ለአብነት የቦረና አባ ገዳዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

### የቦረና ኦሮሞ

በኬንያ ፡- መርሳቢት ፥ ሶሎሎና ኢሲዮሎ ጠቅላይ ግዛቶች ውስጥ በከፍተኛ ቁጥር የሚገኝ ሲሆን ፤ የዚህን ቁጥር 5 ጊዜ እጥፍ የሚሆነው ደግሞ በኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ አከላለል በረናና ጉጂ ዞኖች ውስጥ ይገኛል ። ይህ ማህበረሰብ የሚገርም ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ፥ የዘመን አቆጣጠር ፥ አስደናቂ ባህላዊ እሴቶች ፥ ፍልስፍና ፥ ከጎረቤት ህዝቦች ጋርም ሆነ በውስጡ የሚፈጠሩ ተቃርኖዎችን የሚፈታበት መንገድ አለው ። ከጦርነት ሰላምን ይመርጣል ። ለዚህም ነው 'ኑ ወረ ነጊ' እኛ የሰላም አምባሳደሮች / የፍቅር ሰዎች ነን የሚለው ። እነሆ ከ1467 - 2016 የሥልጣን ዘመናቸውን ያጠናቀቁትንና አዲስ የተመረጠውን አባ ገዳዎች ዝርዝር በላቲንና በአማርኛ ፊደሎች በማቀላቀል ከማስታወሻችን አቅርበናል።

1. ገደዮ ገልገሎ ያያ ከ1467 - 1475

2. ያያ ፉሌ ያያ 1475 - 1483

3 ጃርሶ ባቦ ጋኖ 1483 - 1491

4 ደዌ ቦርቦር ደዌ 1491 - 1499

5 ዲዳ ነምዱሪ አና 1499 - 1507

6 አሬሮ ቦሩ በልከቻ 1507 - 1515

7 ቲቲሌ ዱለቻ ያያ 1515 - 1523



t.me/OLDBOOKSPDF

8 ሶሎ ጃርሶ ባቦ 1523 - 1531

9 Borbore Dawwee 1531 - 1539

10 Aga Raage Kalee 1539 - 47

11 Dagale Yaayyaa Diidaa 1547 - 55

12 Ososo Tiitiilee Dullachaa 1555 - 63

13 Borro Lukuu Jaarsoo 1563 - 71

14 Abbaya Horroo Dullachaa 1571 - 79

15 Bido Dhoqee Rassoo 1579 - 87

16 Horro Dullacha Guyyoo 1587 - 95

17 Yaayyaa Holee Bonayaa 1595 - 1603

18 Doyo Borro Lakuu 1603 - 11

19 Baaco Nadho Hachuu 1611 - 19

20 Urgumeessa Igu Beeree 1619 - 27

21 Baabo Horroo Dullachaa 1627 - 35

22 Baabo Sibu Beeree 1635 - 43

23 Hindhale Doyo Boru :1643 -1651

24 Hachu Abbiyu Baachoo :1651-1659

25 Aabu Laku Mormaa :1659-67

26 Abbayi Baabo Horroo :1667-74

27 Alle Kura Yaayyaa 1674-82

28 Wayyu Uru Malelee 1682-90

29 Morowwa Abayye Aasi1690 -98

30 Gobba Alla Nurra 1698-1706

31 Dawwe Gobbo Yaayyaa 1706-14

32 Jaarso Iddo Yaayyaa 1714-22

33 Wale Waccu Rooqaa 1722-30

34 Sora Dhadacha Iluu 1730-37

35 Dhadacha Roble Guyyoo 1737-45

36 Halake Doyo Hareree 1745-53

37 Guyyo Gedo Wallee 1753-61

38 Madha Boruu Dadoyii 1761-68

39 Sora Diida Qarsaa 1768-76

40 Bule Dhadacha Roblee 1776-83

41 Liban Wata Namfurii 1783-91

42 Wayyu Rale Canaa 1791-98

43 Boru Madha Boruu 1798-1806



t.me/OLDBOOKSPDF

44 Ungule Halake Saddee 1806-14

45 Saqqo Dhadácha Gaamadu 1814-21

46 Jilo Nyenco Soraa 1821-29

47 Sokore Anna Borboree 1829-37

48 Liban Jilo Hadhawa 1845-52

50 Jaldeesaa Guyyo Dabassaa 1852-60

51 Doyo Jilo Nyencoo 1860-68

52 Haroo Adii Liban 1868-76

53 Dida Bitata Maamoo 1876-83

54 Guyyo Boru Ungulee 1885-91

55 Liban Jaldeessa Guyyoo 1891-99

56 Adi Doyoo Jiloo 1899-1906

57 Boru Galma Doyoo 1906-13

58 Liban Kuse Liban 1913-21

59 Arero Gedo Liban 1921-29

60 Bule Dabassa Bulee 1929-36

61 Aga Adii Doyoo 1936 - 44

62 Guyyo Boru Galmaa 1944 - 52



t.me/OLDBOOKSPDF

44 Ungule Halake Saddee 1806-14

45 Saqqo Dhadácha Gaamadu 1814-21

46 Jilo Nyenco Soraa 1821-29

47 Sokore Anna Borboree 1829-37

48 Liban Jilo Hadhawa 1845-52

50 Jaldeesaa Guyyo Dabassaa 1852-60

51 Doyo Jilo Nyencoo 1860-68

52 Haroo Adii Liban 1868-76

53 Dida Bitata Maamoo 1876-83

54 Guyyo Boru Ungulee 1885-91

55 Liban Jaldeessa Guyyoo 1891-99

56 Adi Doyoo Jiloo 1899-1906

57 Boru Galma Doyoo 1906-13

58 Liban Kuse Liban 1913-21

59 Arero Gedo Liban 1921-29

60 Bule Dabassa Bulee 1929-36

61 Aga Adii Doyoo 1936 - 44

62 Guyyo Boru Galmaa 1944 - 52



t.me/OLDBOOKSPDF

63 Madha Galma Torree 1952 - 60

64 ጀልዴሳ ሊበን ጉዮ 1960 - 1968

65 ጎባ ቡሌ ደበሳ 1968 - 1976

66 ጂሎ አጋ አዲ 1976 - 1984

67 ቦሩ ጉዮ ቦሩ 1984 - 1992

68 ቦሩ መዳMadha ገልማ 1992 - 2000

69 ሊበን ጀልዴሳ ሊበን 2000 - 2008

70 ጉዮ ጎባ ቡሌ ከ2008 - 2016 ሃላፊነቱን

71. ኩራ ጃርሶ ኩራ 2016 - 2018 አስረከቧል።

(እጅግ አስገራሚው ነገር የሥልጣን ርክክቡ በሰላማዊ መንገድ ሳይዛነፍ የተከናወነ ሲሆን 71ዱንም አባ ገዳዎች ከነዓመተ ምህረቱ፣ ስማቸውን ፥ ጎሳቸውን ፥ ንዑስ ጎሳቸውን ፥ ከየትኛው የጎጌሳ መስመር እንደሆኑ አንዳች ሳያዛንፉ የሚነግሯችሁ የማህበረሰቡ ታሪክ አዋቂዎች ከሊበን ኢትዮጵያ እስከ ኢሲዮሎ ኬንያ መኖራቸው ነው ።) የበለጠ የሚያስደምመው በየትኛው የገዳ ዘመን ምን እንደተፈጠረም ሳያዛንፉ የሚነግሯችሁ ብልህ አዛውንቶች ሃዩዎች መኖራቸው ነው ። በዚህ ጊዜ የምክር ቤቱ አመራሮች በሙሉ ስልጣናቸውን ለአዲሶቹ አመራሮች አስረከበው ፥ ለቀጣዩ ስምንት ዓመት በአማካሪነት ያገለግላሉ ። አመራሮቹ ፦

አባ dheeዳ - የግጦሽ አጠቃቀም አስተናባሪ

አባ ዱላ - የጦሩ መሪ

አባ ኤላ - የውሀ አጠቃቀም ስርዓት አስከባሪና ባለቤት

አባ ፈርዳ - ፈረሰኛ



t.me/OLDBOOKSPDF

አባ ጉያ - በውሀ አጠቃቀም ዙሪያ የእንስሳትን አጠጣጥ ቅደም ተከተል ፈር የሚያስይዝ ፤

አባ ገዳ - የመሪው ሉባ ወይም ጎጊሳ መሪ ፤

አባ ጎሳ - የጎሳ / ነገድ መሪ ፤

አባ ሄሬጋ - የጋማም ሆነ የቀንድ ከብቶች በኩሬም ሆነ በጅረቶች በተገቢው መንገድ ስለመጠቀማቸው የሚቆጣጠር

አባ ጂላ - የጂላ ስርዓት መሪ

አባ አላ - የመንደር መሪ

አባ ቆ'ዬ - የንዑስ ማህበረሰብ መሪ

አባ ሴራ - የፍትህ ስርዓት መሪ

አባ ወራና - የጦር አበጋዝ በተለያዩ እርከኖች በአባ ዱላው ስር ጦር መሪ

አባ ሆኮ፡- በልዩ የአመጋገብ ስርዓት ወጣቶችን የሚያስተናብር አጋፋሪ ነው።

የገዳ ስርዓት፡- ገዳ የቦረና የትውልድ ቅብብሎሽ አጠቃላይ ስርዓት ሲሆን ይህም ፡- አጠቃላይ ማህበረሰባዊ ጥንቅሩን ፤ የአንድን ገዳ ደረጃ ስርዓት ፤ በገዳ እርከን ደረጃ ያለ ግለሰብን ፤ በየስምንት ዓመቱ ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ ያለ ሽግግርን የሚያሳይ ፅንሰ ሀሳብ ነው።

## ማነፃፀሪያ አሀድ ሁለት፡- የተሣታፊዎች ስብጥር

በአቴንስ ዴሞክራሲ፡- ከ95 እጅ በላይ የሚሆነው ነዋሪ ባሪያ ነው። ባሪያ ማለት እንደ ሰው የማይቆጠር፣ ሳይከፈለው የሚያገለግል፣ እንደ ተናጋሪ እንስሳ የሚቆጠር፣ እንደ ሸቀጥ የሚሸጥና የሚለወጥ፣ ለገደላቸው ባሪያዎች የተጠያቂነት ግዴታ የማይጣልበት፣ መሪ ሲሞት ከነህይወታቸው የሚቀበሩ፤ በዚህ መሠረት የአቴንስ ዴሞክራሲ ከሩብ ከፍለ ዘመን የዘለለ እድሜ የለውም። ዴሞክራሲው ከነዋሪዎቹ 5%



t.me/OLDBOOKSPDF

ለሚሆኑት ብቻ የሚሠራ ነበር። ለንፅፅር የተመረጠውን የቦረናን ማህበረሰብ መዋቅር እንመልከት።

በቦረና የገዳ ዴሞክራሲ፦ አስተዳደሩ ለሁሉም የማህበረሰቡ አባላት ያልተማከለ በእኩልነት ላይ የተመረኮዘ አስተዳደራዊ ዘይቤን የተላበሰ (Egalitarian) ነው። ባሪያ በቦረና ስሙ እንኳን አይታወቅም። በአቴንስ ዴሞክራሲ በስመ የብዙኃን ውሳኔ (50% + 1) በስብሰባ ተሳታፊ ቆጠራው ከተገኙት ከግማሽ በላይ ለምሳሌ ከ10,000 ሰው 5,001 ቢስማሙበትና 4,999 ሰው ቢቃወመው ውሳኔው የፀና ይሆናል። (ዛሬም በዓለም ላይ ያለው ልምድ ይኸው ነው።)

በገዳ ዴሞክራሲ ግን በተማከለ ፍልስፍና ውስጥ ባልተማከለ አደረጃጀት ማንኛውም የህብረተሰቡ አባል ፍላጎቱን ሌሎች ላይ እንዳይጭን ልጓም የሚያበጁለት ደንቦች ህጎችና መመሪያዎች አሉ። ወደ ዋናው ጉባኤ እንደ አቴንስ በደመ ነፍስ መግተልተል የለም። ይልቁኑ በየደረጃው ባሉ ሸንጎዎች ወሣኝ ጉዳዮች በሚገባ ይብላላሉ።

የመጀመሪያው የማህበረሰቡ መሠረታዊ መዋቅር በጎሣ ደረጃ ካለ ሸንጎ "ኮራ ጎሣ" ይጀምራል። የቦረና ጎሣዎች የዘር ግንድ በሁለት ይከፈላል።

1. የሰቦ ምድብ፦ በሥሩ ሦስት ንዑስ ጎሳዎችን ያቅፋል። እነርሱም፦ ዲገሉ መጠሪ እና ከረዩ ይባላሉ።

2. የጎና ምድብ ራሱ በሁለት ሌሎች ንዑሳን ከፍሎች ተዋቅሯል።

2.1 ሀሮሬሳ፦ አርሲ ሀውቱ ቀርጪብዱ ወረ-ጂዳ መሊዩ ደምቢቱ እና ኖኒቱ፤

2.2 ፉሌሌ፦ ደጪቱ መጪቱ አዲቱ ገላንቱ ሲረዩ በጪቱ እና ኮኒቱን ይይዛል።

መዋቅሩ የሚያደርገው ስብሰባ እንደ ነገሩ ሁኔታ እስከ አንድ ወር ሊዘልቅ ይችላል። ከዚህ አስቀድሞ በሰዓታት ውስጥ ሊጠናቀቁ የሚችሉ የመንደር ጉባዔዎች የሚነሱ ጉዳዮችን ለማቃለል በሚያስችል አግባብ ይደረጋሉ። በኮራ ጎሳ እንዳይሳተፍ ከልክላ የሚደረግበት የማህበረሰቡ አባል የለም። ዋናው መሠረታዊ ጉባዔ ከመካሄዱ በፊት ለአቅመ ደካሞች ወላድ ከብቶችን የተሻለ ሀብት ያላቸው እንዲያከፍሉ በማድረግ የሚደገፉበት አሰራር፣ የውርስ ጉዳዮች፣ ለተለያዩ ጎሳውን የሚመለከቱ ምሥጢራዊ



t.me/OLDBOOKSPDF

ለሚሆኑት ብቻ የሚሠራ ነበር። ለንፅፅር የተመረጠውን የቦረናን ማህበረሰብ መዋቅር እንመልከት።

በቦረና የገዳ ዴሞክራሲ:- አስተዳደሩ ለሁሉም የማህበረሰቡ አባላት ያልተማከለ በእኩልነት ላይ የተመረኮዘ አስተዳደራዊ ዘይቤን የተላበሰ (Egalitarian) ነው። ባሪያ በቦረና ስሙ እንኳን አይታወቅም። በአቴንስ ዴሞክራሲ በሰመ የብዙኃን ውሳኔ (50% + 1) በስብሰባ ተሳታፊ ቁጠራው ከተገኙት ከግማሽ በላይ ለምሳሌ ከ10,000 ሰው 5,001 ቢስማሙበትና 4,999 ሰው ቢቃወመው ውሳኔው የፀና ይሆናል። (ዛሬም በዓለም ላይ ያለው ልምድ ይኸው ነው።)

በገዳ ዴሞክራሲ ግን በተማከለ ፍልስፍና ውስጥ ባልተማከለ አደረጃጀት ማንኛውም የህብረተሰቡ አባል ፍላጎቱን ለሎች ላይ እንዳይጭን ልጓም የሚያበጁለት ደንቦች ህጎችና መመሪያዎች አሉ። ወደ ዋናው ጉባኤ እንደ አቴንስ በደመ ነፍስ መግተልተል የለም። ይልቁኑ በየደረጃው ባሉ ሸንጎዎች ወሣኝ ጉዳዮች በሚገባ ይብላላሉ።

የመጀመሪያው የማህበረሰቡ መሠረታዊ መዋቅር በጎሣ ደረጃ ካለ ሸንጎ "ኮራ ጎሳ" ይጀምራል። የቦረና ጎሣዎች የዘር ግንድ በሁለት ይከፈላል።

1. የሰቦ ምድብ:- በሥሩ ሦስት ንዑስ ጎሳዎችን ያቅፋል። እነርሱም:- ዲገሉ መጣሪ እና ከረዩ ይባላሉ።

2. የጎና ምድብ ራሱ በሁለት ሌሎች ንዑሳን ከፍሎች ተዋቅሯል።

2.1 ሀሮሬሳ:- አርሲ ሀወቱ ቀርጨብዱ ወረ-ጂዳ መሊዩ ደምቢቱ እና ኖኒቱ፤

2.2 ፉሌሌ:- ደጪቱ መጪቱ አዲቱ ገላንቱ ሲረዩ በጪቱ እና ኮኒቱን ይይዛል።

መዋቅሩ የሚያደርገው ስብሰባ እንደ ነገሩ ሁኔታ እስከ አንድ ወር ሊዘልቅ ይችላል። ከዚህ አስቀድሞ በሰዓታት ውስጥ ሊጠናቀቁ የሚችሉ የመንደር ጉባዔዎች የሚነሱ ጉዳዮችን ለማቃለል በሚያስችል አግባብ ይደረጋሉ። በኮራ ጎሳ እንዳይሳተፍ ክልክል የሚደረግበት የማህበረሰቡ አባል የለም። ዋናው መሠረታዊ ጉባዔ ከመካሄዱ በፊት ለአቅመ ደካሞች ወላድ ከብቶችን የተሻለ ሀብት ያላቸው እንዲያካፍሉ በማድረግ የሚደገፉበት አሰራር፣ የውርስ ጉዳዮች፣ ለተለያዩ ጎሳውን የሚመለከቱ ምሥጢራዊ



t.me/OLDBOOKSPDF

ጎሳዎች የሚሰበሰቡ መዋጮዎች እና ከምንም በላይ ትኩረት ተሰጥቶት ለከብቶች የመጠጥ ውሀ ጉድጓዶችን የመቆፈር ጉዳይ ውይይት ይደረግበታል።

በመቀጠል "የያአ ገዳ ጉባዔ":- ቦረና የራሱ በአንድ ቦታ የከተመ የአኗኗር ዘይቤ ብቻ ሳይሆን ውሀና ለከብቶች ግጦሽ ፍለጋ ከአንድ ሥፍራ ወደ ሌላ ቦታ በመንቀሳቀስ ላይ የተመሠረተ ህልውና አለው። ለእያንዳንዱ ሥርአትና ችግር መፍትሔ በመሥጠት ረገድ ባለው የተባ ልምድ ለአንድ የገዳ ዘመን (ስምንት ዓመታት) የሚቋቋመው ሸንጎ "ያአ ገዳ" በመባል ይታወቃል። የሚያስገርመው ነገር የወቅቱ ባለ ሳምንት ከሆነው የገዳ ትውልድ ስድስት ባለሥልጣናት በተመጣጠነ ውክልና ከየጎሳው ይሰየማሉ። ለእያንዳንዱ ተዘዋዋሪ መንደር (በነፍስ ወከፍ) አራት ሊቆች ወይም 'ሃዩዎች' በመምህርነት እና አማካሪነት ሃላፊነት ይወስዳሉ። ሀዩዎች የስብሰባ አካሄድ አሠራርን ያሳያሉ።

በልምድና በሺበት አንቱ የተባሉ ሽማግሌዎች "ጃርሌ አርገ ደጌቲ" በንግግር ወቅት የተሻለ እድል ይሰጣቸዋል። ነገር ማሥረዘምና ማሠልቸት ፈፅሞ አይፈቀድም። አንድ ሰው ሲናገር ሀሳቡን ማድመጥን ለማስረገጥ የአረፍተ ነገሩ (የአንቀጽ ያህል ርዝመት ሊኖራቸው ይችላል) ማሣረጊያ ቃላት በተሰብሳቢው ይደገማሉ። በማህበረሰቡ ኃይለ ቃል መናገር ነውር ነው። ሀዩዎች:- የስብሰባ ሊቃነ መናብርት እና አመቻቾችም ናቸው። ውሳኔ የሚሰጠው በጠቅላላ አባላት ስምምነት ነው። ከ500 ሰው 10 ያህሉ ብቻ እንኳ ባይስማሙ ለየብቻ በአዋቂዎች እንዲያምኑ የማድረግ ሥራ ይሠራል። አንድ ሰው ተለይቶ አልስማማም ቢል እጅግ ከሚወደው ሰው ጋር በተናጠል እንዲወያይ ተደርጎ 'ባይዋጥለት' እንኳ 'አንተ ካልሽኝ መቼስ ምን አደርጋለሁ?' በማለት ወደ ጀማው ተቀላቅሎ የጋራ ስምምነት ላይ ይደረሳል።

የቅጣት አቀባበል ሥርአት:- በአንድ የቦረና አባል ላይ ቅጣት ሲጣል እንደ ዘመናዊ የህግ ሥርአት በግድ አይጫንበትም። አንዳንድ ጊዜ ወንጀለኛ ተደብቆ ንፁሑ የሚቀጣበት ሁኔታ ሊያጋጥም ይችላልና። ንፁህን የመቅጣት ጭቡን ለማስወገድ የመጨረሻ ደረጃ ድረስ ተሂዶ ጥንቃቄ ይደረጋል። አንድ ጎሣ (ማህበረሰብ) አጥፍቷል የሚል ግምት ከተያዘ በተመሳሳይ የጎሣው አባላት ስለማጥፋታቸው አምነው ሊቀበሉ ይገባል። ጥፋትን አምኖ መቀበል በቦረና እጅግ የተለየ የከበሬታ ማማን ያቆናጥጣል። ዓላማው ውሸትና ከህዲነትን ማስወገድ እንደመሆኑ "አጥፍቻለሁ" በማለት የሚሰጠውን ቅጣት ለመቀበል ለተዘጋጀ:-



t.me/OLDBOOKSPDF

1) ቅጣቱ በጣሙን እንዲቀልለት ይደረጋል።

2) ቅጣቱ የፍቅር ማስተማሪያ ይሆናል።

3) ሌላ ብቀላ እንዳይኖር ሙሉ ዋስትና ይሰጣል።

4) እምነታዊ ምርቃት "ኤባ" እስኪረሰርሥ በየተራ ይጎርፍለታል።

5) ግለሰቡ ያጠፋው ጥፋት ሳይነሳ "ከብር" ያገኛል። ጥፋቱ በአውጫጪኝ (አፈርሳታ) ስለሚደረስበት እስከ ጉሚ ጋዮ ድረስ ቀርቦ እስከመጨረሻው ሽምግልና አድርጎ ከካደ የእርግማን መአት ይወርድበታል። በ"አባርሳ" ጠንካራ ርግማን "የተረገምህ ሁን! ፈጣሪ ይፍረድብህ!" ተብሎ ከማህበረሰቡ ወጥቶ እንዲባረር "ቆሌ" ይፈረድበታል። አዋራጅ ተብሎ እስከ ወዲያኛው ከቦረና የተቆራረጠ ይሆናል።

**ሦስቱ የመንግሥት ሥልጣን አካላት**

1. ሕግ አውጪ:- በየስምንት ዓመቱ በቦረና የሚገኙ ወንዶች በሙሉ የሚሣተፉበት ታላቅ ጉባኤ "ጉሚ ጋዮ" ስብሰባ ያካሂዳል። ብቸኛው ቦረና የሚተዳደርበት ህግ አውጪ አካል ነው። በዝቅተኛ ደረጃ ስምምነት ላይ ያልተደረሰባቸው ውሳኔዎች ውሳኔ የሚያገኙት በዚሁ ሸንጎ ነው።

2. ህግ ተርጓሚ:- 'ጉሚ ጋዮ' አዚያው ሳለ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሆኖ ያገለግላል። የህግ አውጪና የህግ ተርጓሚነት ጣምራ ሃላፊነት በዚህ አካል ትከሻ ላይ የወደቀ ነው። አባ ሴራ ህግን የመምራት፣ ህዩዎች ሂደቱን የመከታተል፣ የህዩዎች አማካሪ አቃቢ ህጎች "ጀለባዎች" ሆነው ሃላፊነታቸውን ይወጣሉ።

3. ህግ አስፈፃሚ:- በዝርዝር የሥልጣን ሃላፊነት የተሰጣቸው "አባ" የሚል ሃላፊነት የተረከቡ አካላት በየፅህፈት ቤታቸው ተግባራቸውን ያከናውናሉ። የአቴንስ ዴሞክራሲ ተሰብስቦ ከመወሠን ውጪ በዚህ ደረጃ ያልቆመ ተሞክሮውም ከ25 ዓመታት ያልበለጠ ነው።



t.me/OLDBOOKSPDF

**የማንፃፀሪያ አሀድ ሦስት፡- የሥልጣን ዘመን**

በአቴንስ ዴሞክራሲ መሪው (ሶሎኑ) በተደጋጋሚ መመረጥ ይችላል። ይህም ሥልጣንን የርስት ያህል በእጁ በማስገባት በባሪያዎች ላይ ለመፈፀም ያስችለዋል። በመሆኑም ለአምባገነንነት ምቹ ሁኔታን ይፈጥርለታል። በገዳ ዴሞክራሲ ቀደም ብለን በዝርዝር የአባ ገዳዎችን የቆይታ ጊዜ እንዳየነው የትኛውም አመራር ከስምንት ዓመት የሥልጣን ዘመን በኋላ ለአንድም ቀን ሊያሳልፍ የሚችልበት መፈናፈኛ መንገድ የለም። ሁሉም አመራሮች በሥልጣን ዘመናቸው ማብቂያ ሃላፊነታቸውን ለሚቀጥለው የአመራር ትውልድ አስረክበው በአማካሪነት ብቻ ያገለግላሉ።

በተሰጣቸው የማማከር ቦታ ከአባት ወደ ልጅ መተላለፍ የሚችለው የሃዩዎች (ታሪክ አዋቂዎችና የስብሰባ አመቻቾች) ብቻ ነው። ምክንያቱም የቦረናን ታሪክ ከ"ሀ" እስከ "ፖ" (ከ 'ሀ' እስከ 'ፐ') ሳይዛባ ለማስተላለፍ እንዲያስችል በጥበብ የተወሰነ ነው። ምክር ቤቱ (ጉሚ ጋዮ / ጨፌ) ወይም አጠቃላይ ሸንጎው በወሳኝ ጉዳዮች ላይ ስለሚወስን፤ የሃዩዎች ሃላፊነትም ስለሚታወቅ ለተለየ የበላይነት አመቺ ሁኔታ አይፈጥርም። በተመሣሣይ አባ ሙዳ (ቃሉ) የሀይማኖት መሪነት ቦታ ለቤተሰብ መተላለፍ ይችላል። ሌላው ቀርቶ የማህበረሰቡ መሪ ተደርጎ የሚወሰደው አባ ገዳ (አባ ቦኩ) ከየትኛውም የቦረና ማህበረሰብ አባል እኩል (First among equals) የአፈ ጉባዔ አይነት ተግባር እንዲያካሂድ ሆኖ ሥልጣኑ በእጅጉ የተገደበ ነው።

**ማነፃፀሪያ አሀድ አራት፡- የመሪው ማህበረሰባዊ ስፍራ**

በአቴንስ ዴሞክራሲ መሪው በባሮች ጉልበት በሠረገላ እየተንተተ የሚንቀሳቀስ፣ በሀገሪቱ ሀብት የሚያዝ፣ በአስተዳደራዊ ጉዳዮች ፈላጭ ቆራጭ ነው። በገዳ ዴሞክራሲ ውስጥ አባ ገዳው ከላይ እንዳየነው አፈ ጉባዔ ብቻ ሆኖ የሚያገለግል፣ ከብዙ እኩያዎች አንዱ ብቻ ነው። በሀብት የሚበልጡት በርካታ የማህበረሰቡ አባላት አሉ።

**ማነፃፀሪያ አሀድ አምስት፡- የውጭ ዜጎች መብት**

በአቴንስ ዴሞክራሲ የትኛውም የውጭ ዜጋ ከማህበረሰቡ በምንም መንገድ አይቀላቀልም። ግልፅ መገለል እና መድልዎ በውጭ ዜጎች ላይ ይፈፀማል። በገዳ ዴሞክራሲ ለምሳሌ፡- በቦረና የሚከተሉትን መሥፈርቶች ያሟላ ግለሰብ በቀጥታ



t.me/OLDBOOKSPDF

ከማንኛውም የቦረና ጎሣ አባል ጋር እኩል ሙበትና ገዱብ የማይጣልበት ማንነት ይኖረዋል።

ሀ. የቦረናን ባህል ደንብ ህግና መመሪያዎች ተቀብሎ በሴራ (ህግ)፣ አዳ (የቦረና አጠቃላይ አጠቃላይ እሴቶችን ያቀፈ ሰፊ ፅንሰ ሀሳብ ነው። ሰፉ (የስነምግባር ልኬት) ተጣጥሞ ለመኖር የወሰነና ራሱን ያዘጋጀ

ለ. የቦረናን ቋንቋ (አፋን ቦረና) መናገር የሚችል (ከማህበረሰቡ ጋር ለመግባባት የሚያስችል መሠረታዊ የቋንቋ ክህሎት ያለው)

ሐ. ትዳር የያዘ የቦረና ማህበረሰብ አባል ስለግለሰቡ ተገቢ ምስክርነት ከሰጠ "ምግም በተሰኘ የሥም አወጣጥ ሥርአት ቦረና ይሆናል። ከቦረና የስም ስያሜዎች መሀከል ተሰይሞለት አንዱን ይይዛል። ለምሳሌ፡- የግለሰቡ ስም 'ኪሾ' ቢሆን ከቦረና የወንድ ስሞች መሀከል አንዱን ገልገሎ ጠዴቻ ቦሩ ሁቃ ሊበን ... ሴት ከሆነችም ሶቦ ዲረሙ ደርሚ አያጉዶ ወዘተርፈ ይሰየማል። (በቦረና እና ጉጂ ግለሰቦች ስማቸውን በሀይማኖት ወይም በከተሜነት የሚቀይሩበት ሁኔታ የተለመደ አይደለም። የስም አወጣጥ በዘፈቀደ ሳይሆን ራሱን በቻለ ሥርአት የሚካሄድ ነው። ቦረና እና ጉጂ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ስሞች ከ95 እጅ በላይ ከሌሎች ኦሮሞዎች ስያሜዎች ጋር አይመሳሰሉም።)

**የማነፃፀሪያ አሀድ ስድስት፡-**

የሴቶች መብት፡- በአቴንስ ዴሞክራሲ ሴቶች ፈፅሞ እንደ ዜጋ አይቆጠሩም። በሥርአቱ ውስጥ የሚሳተፉበት አግባብ ካለመኖሩም ባሻገር ከለላ የሚሰጣቸው የአሠራር ደንበ የለም። በገዳ ዴሞክራሲ ውስጥ እንስቶች "ሲቄ" ወይም "ሲንቄ" ለሴቶች የተለየ ሥርአት መብቶቻቸውን ያስከብራሉ። በተለይም ቤት በላቀ ደረጃ የሴቷ ነው "የቤት እናት/ ሃደ' መና" ስለሆነች ልዩ ክብር አላት። በርግጥ በሀብረተሰባዊ የሥራ ክፍፍል ሴቶች ለራሳቸው የተመደቡ ልዩ ልዩ ሥራዎች አሉ። መብታቸውን ለማስከበር የትኛውም በደል ወይም ጥቃት በወንዶች ቢደርስባቸው የማስቀጣት ወሳኝ በሆነ ጉዳይም አብሮ የመምከር እድል አላቸው።

በሌሎች ሀገሮች የሴቶችን ሁኔታ በመገለጫ ስንመለከት፡- በጥንት አሲርያ ሴት ልጅ ባሏን ሀይለ ቃል ከተናገረች ባሏ በህዝብ መሀከል ጥርሶቿን በጡብ እንዲያረግፍ



t.me/OLDBOOKSPDF

ወይም በጉሯን መሬት ላይ አስተኝቶ እንዲነቅል ይደረጋል። ሴቶች ከወንድ ጋር ዝምድና የሌላቸውን ካሉ ሰብ ጋር መገናኘት ከፈፀሙ በድንጋይ ተወግረው የሚገደሉባቸው ሀገሮች በርካታ ናቸው። ለወንዱ ድንግል ሆነው እንዲቆዩ የሚሰፉ፣ ጥፍሮቻቸው እንዲነቀል የሚደረግበት ሁኔታ እና ሴቶች ላይ የሚደርሱ በደሎች የትየለሌ ናቸው። በአሜሪካ ሴቶች መመረጥ ይቅርና ለመምረጥ እድል ካገኙ ገና መቶ ዓመት ነው ሲያውም ለወንዶች የመምረጫ እድሜ 21 ዓመት፣ ለሴቶች 30 ዓመት ነበር። የአሜሪካ ሴት ፕሬዚደንት ከ1789 - 2019) ለ230 ዓመታት ታይቶ አይታወቅም። (የወይዘሮ ሂላሪ ክሊንተን በሥልጣን ላይ ከሉት ፕሬዚደንት ዶናልድ ትረምፕ ጋር ጠንካራ ውድድር አድርገው እንደነበር የሚታወስ ነው።)

በአጠቃላይ የገዳ ሥርአት በምዕራፍ አራት የምናየው ከሌሎች ጋር በተደረገ ታሪካዊ መገፋፋት የታየ ከፍተት ካልሆነ ከዘመናዊው ዴሞክራሲ የሚተልቅባቸው ተሞክሮዎች ጭምር አሉት። ከዘመናዊው ዴሞክራሲ ጋር ለማጣጣም ሲባል መነካት የሌለበት መሆኑን አበክረን እያሳሰብን፤ ጎን ለጎን የቀበሌ፣ ወረዳ፣ ዞን፣ ክልል እና ሀገር አስተዳደር ውስጥ ያለው ሚና ተጣጥሞ መቀጠል የሚችል መሆኑን ለማስመር እንሻለን። ሃላፊነቱ፡ የመላው ኢትዮጵያዊ ሆኖ በዘመናዊ ትምህርት የገፉ የማህበረሰቡ ልጆች ሥርአቱ ሳይበረዝ ለተከታታይ ትውልዶች እንዲተላለፍ እና ዓለማቀፍ ታዋቂነት እንዲያተርፍ (እንደ አውራምባ ማህበረሰብ የሚጎበኝ እንዲሆን) የማድረግ ከፍተኛ ሃላፊነት አለባቸው።

የገዳ ሥርአት በተመሣሣይ ሁኔታ በጉጂ ኦሮሞዎች ዘንድም በራሱ አጀብ የሚያስኙ ተቀራራቢ አሴቶች ጎልብቶ የሚተገበር ሲሆን በአሁኑ ሰአት ጉጂዎች 72ኛውን አባ ገዳ ጂሎ ማንዶ'ን መርጠዋል። ጉጂ ለተፈጥሮ ካለው ልዩ ክብር የተነሣ ዛፍ እንኳ ካልደረቀ መቁረጥና ለማገዶ ማዋል ከልክል ነው። ስለሆነም በልምላሜ በኢትዮጵያ ውስጥ አሉ ከሚባሉ ደኖች አንዱ በጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ ዞኖች ውስጥ የሚገኝ መሆኑ በዋቢነት መጠቀስ ይችላል። ፈሪሀ ፈጣሪ እና ነገሮችን በጥበብ ማስተዋል የሥርአቱ መገለጫ መሆኑን ለማሳየት አንድ አብነት እናንሳ። በ2017 በአንድ የጉጂ አባት የተፈፀመ አርአያነት ያለው ተግባር እናካፍላችሁ። ቦታው ከነጌሌ ቦረና 30 ኪሎሜትር ርቀት አካባቢ ሀርቀሎ መዳረሻ ላይ ነው። ግለሰቡ አመሻሽ ላይ ከብቶቻቸውን እየነዱ ወደ መንደራቸው ሲዋቡ አንድ ከአዲስአበባ ተነስቶ ሲጓዝ የዋለ ሾፌር በድንገት አለ የለም የተባለ (ከሁሉም በመጠን የሚልቅ ታላቅ ሰንጋ በሬ) በመኪና ገጭቶ ይገድልባቸዋል።



t.me/OLDBOOKSPDF

ከበሬው ግዝፈት አኳያ መገደሉ በተለይ ለሾፌሩ እጅግ አስደንጋጭ ነበር። ድንገት የወጣ ሾፌር ከየት አምጥቶ ይከፍላል? ይበልጡኑ ስለስፍራው የሰማው 'አይለቁህም' አይነት ስሜት በጣም አስጨንቆታል። አደጋው መድረሱ ሲሰማ በፈጣን የመረጃ ልውውጡ መሠረት ጦር የያዙ የአካባቢው ነዋሪዎች ወደ ስፍራው ከየአቅጣጫው ብቅ ብቅ ሲሉ የአሽከርካሪው ጭንቀት እየናረ ሄደ። ያለው ብቸኛ አማራጭ ወደ ሀረቀሎ ተመልሶ በሽምግልና መግፀን ነው። በርግጥም ሀርቀሎ አድሮ በማግስቱ ሽማግሌዎች ተመርጠው ሽምግልና ተቀመጡ። ለበሬው ዋጋ ባይመጥንም 12,000 ብር እንዲያዘጋጅ ተነገረውና ከዚህም ከዚያም አፈላልጎ ከአማላጆች ጋር በስፍራው ተገኘ።

ከድርድሩ በሁዋላ አቅሙ ከግምት ገብቶ 10ሺህ ብር እዲከፍል ተወሰነበት። ያዘጋጀውን ብር ካሳ ሊከፍል ከኪሱ አወጣ።

የጉጂ ማህበረሰብ አባል የሆኑት ጎልማሳ ገንዘቡን በእጃቸው ይዘው የሚከተለውን ጥያቄና መልስ ከ'ሾፌሩ' ጋር አደረጉ፦

* ትኩር ብለው እየተመለከቱት፦ "ወዳጄ በሬው ያውቅህል?" ጠየቁት

* "ኧረ አያውቀኝም" ሾፌሩ መለሰ።

* ሌላ ጥያቄ አስከተሉ፦ "አንተስ በሬውን ታውቀዋለህ?"

* ሾፌሩ ግራ በተጋባ መንፈስ "በፍፁም አላውቀውም" በማለት መለሰ።

ጎልማሳው የጉጂ ሰው ከመቀመጫቸው ተነሡና ጉሮሯቸውን ጠራርገው 'ወገኖቼ' በማለት ቀጠሉ። 'በሬው ወደ ቤቱ፣ ሾፌሩም ወደማደሪያው ሲሄዱ ግጭት ተፈጠረና አደጋው ተከሰተ። ይህ ችግር ወይ በራሴ፣ አሊያም በባለቤቱ፣ ካልሆነም ከቤተሰቤ በአንዱ እና በንብረቴ ላይ ሊደርስ ይችል የነበረ ነው። ፈጣሪ በዚህ ይለፍልህ ብሎ ሾፌሩን አዘዘልኝ። በመሆኑም ባለውለታዬ ነው። ብሩን እንካ ውሰድ። ልከፍልህ የሚገባኝ እኔ ነኝ እንጂ አንተ አይደለህም። አሁንም ለሽምግልና የወጣውን ወጪ እኔ እከፍላለሁ' - በማለት ከራሳቸው ኪስ ተጨማሪ ወጪ አውጥተው በሽምግልናው ላይ የተገኙ አዛውንቶች የተጠቀሙበትን የምግብና የመጠጥ ወጪ ሸፈኑ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ይህ ዓይነቱ የማህበረሰባችን የምንማርበት እሴት በየአቅጣጫው ሞልቶ ተትረፍርፎ እና ከቶዎች መሆናችን አብዝቶ ያሳዝናል። ለይቅርታ የተዘጋጀ ልብ ማጣታችን ልብን ያደማል። የማይመለከተው ወገናችን ላይ ጉዳት ስናደርስ ያማል። ሾፌሮችም ቀስ ብላችሁ አሽከርክሩ በፍጥነት ለመድረስ እስከመጨረሻው አለመድረስ መኖሩን አትዘንጉ። ዋነኛ የመልዕክታችን ጭብጥ ግን የጉጂው አባት ሰው ያልዘራውን ለማጨድ፤ ንብረቱ ላይ አደጋ ሲደርስ እጥፍ ለመውሰድ በሚንደረደርባት ምድር፤ ይምቡሎ ቢሳ ቢስቲን ሳይሹ ከራሳቸው ኪስ ማውጣታቸው ነው።

የጉጂን ማህበረሰብ ቀረብ ብላችሁ ለማየት ብትሞክሩ ወጉ ባህሉ ልምዱ ይኸው ነው። እርጎውን በካውን ብቻ ቤትና ተፈጥሮ ያፈራውን ይለግሳል። ንፍገት የሚባል ነገር አያውቀውም። በጉጂ ማህበረሰብ ደን መመንጠር፤ ዛፍ መቁረጥ ሰው ከመግደል በላይ ነውር ነው። ለዚህ ነው ሁሌም ያልተማሩ ምሁራን ያቆይዋትን ሀገር፤ የተማሩ ማይማን ሲያፈርሷት እየተንደረደሩ ነው የምንለው። የገዳ ሥርአት በዓለም የሰው ልጆች ልዩ እሴት አካል ሆኖ መመዝገቡ ብቻ በቂ አይደለም። ቢያንስ በአፍሪካ ሥርአተ ትምህርቶች ውስጥ ተካትቶ የሰው ልጅ ያተርፍበት ዘንድ፡- የቆይታ ዘመኑ፣ የማህበረሰቡ ተሳትፎ፣ የሴቶች መብት መጠበቅ፣ ያልገለፅነው ከህፃንነት እድሜ እስከ 80 ዓመት በየስምንት ዓመቱ የሚታለፍባቸው ደረጃዎች፣ የሥልጣን ዘመን፣ በሥልጣን የባለገ አመራር የሃላፊነት ዘመኑን ሳይጨርስ የሚወገድበት "ቡቂሱ ሰርአት"፣ የሚደንቀው ፍትህዊ የሀብት ክፍፍል፣ የዜግነት ህግ፣ የሦስቱ ሥልጣን አካላት መናበብ፣ የብዙኃን ውሳኔ በሚል ስም የጥቂቶች መብት የማይረገጥበት መሆኑ እና ከሠለጠነው ዓለም ዴሞክራሲ የሚልቅባቸውን ሥርአቶች ... ወዘተርፈ በዓለማቀፍ አውደ ጥናቶች፣ የተመድ ድርጅቶች፣ በፊልሞች በድረገፆች በይነመረቦችና የመገናኛ አውታሮች እና የሚዲያ አይነቶች ሁሉ የማስተዋወቅ ሥራ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ተረባርቦ ሊሠራበት ይገባል።

በመጨረሻም በዚህ ፍቅር ውስጥ ገብቶ የወጣ ሳይሆን የምር ሰርፆ የተዋሀደውና ከነፍሰና ከሥጋው ጋር የሸመነ፤ በዚህ ሥነምግባር ልክ የኖረ የሰው ፍጡር እንደምን ከፉ መሆን፣ በሌሎች ቀንቶ በበታችነት ሊያንስ፣ በጥላቻ በቀላሉ ሊመረዝ ይቻለዋል? በፍቅር ያደገ መልሶ ፍቅርን ከመከፈል ውጪ ከፋት እንዴት ፍርቱናው ይሆናል? ፍቅር ሁልጊዜም ያሸንፋል። (*ኢሜሪተስ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ እንደገለፁት "የአውሮፓውያንን የታሪክ አፃፃፍ ዘዴ ስለምንከተል"፣ ታሪኩን ከተለያዩ ምንጮች ለጣጥሮ መደረት፣ አንዱ የፃፈውን ሌላው በመተቸት የአዋቂነት ጫፍ አድርጎ መገመት፤ ከዓላማው አንፃር ዘሬንና ነገን ታሳቢ ሳያደርጉ ጭብጦችን ማዳለብ የታሪክ



t.me/OLDBOOKSPDF

እያየፍ ያነሳሳት ዘደቢ ተደርጎ ተመሰዷል። የምንዕፈው የፖለቲካ ታሪክ በመሆ
መጣረቱን ሳንለቅ የተለየ የአየየፍ ስልት ይዘን መቅረባችንን በየጣሊያው እንደ
ማሲታወቂያ መግለፃችን ተገቢ መሆኑን እናምናለን።)

## ካሌንደር / የዘመን መቁጠሪያ

ቦረናች ከዛሬ 2300 ዓመት አካባቢ ጀምሮ ውስብስብና የተራቀቀ የዘመን አቆጣጠር አላቸው። በርግጥ በሰሜን ኬንያ ቱርካና ሀይቅ አካባቢ፣ በናሞራቱንጋ የአርኪዮሎጂ ምርምር ጣቢያ የተገኙ ማስረጃዎች ኬንያ ውስጥ መሆናቸው ባይካድም ምንጫቸው የቦረና ማህበረሰብ ነው። ኬንያ ውስጥ ቦረና መርሳቢት ሶሎሎና ኢሲዮሎ ግዛቶች ውስጥ ይገኛሉ። በምርምር ጣቢያው ፊታቸውን በቦረና ቀን መቁጠሪያ ተለይተው ወደሚታወቁት ሰባት ከዋክብት ያጋደሉ ሰባት አምዶች በትይዩ አቅጣጫ ፊታቸውን መለሰው ዘመናትን ተሻግረው ቆመዋል። እነዚህ ሰባት አምዶች ከባዛልት ከተሰሩ ሌሎች 19 ቋሚዎች ጋርም በሚያስደምም ህብር ተቆላልፈዋል። ሰባቱ አምዶች ፦ ትሪያንጉለም ፥ ፕሊያዴስ ፥ ቤላትሪክስ ፥ አልዴባራን ፥ ማዕከላዊ ኦሪዮን ፥ ሳይፕ እና ሲረስ ተብለው ተሰይመዋል።ግኝቶቹን ተከትሎ በርካታ የናሳ ምርምር ማዕከልና ሌሎች የስነ ፈለክ ባለሙያዎች ወደ ስፍራው ጎርፈዋል።

ተመራማሪዎቹም ያለ ልዩነት ከዛሬ 2300 ዓመታት ጀምሮ ያለማቋረጥ እስካሁንም ይህንን የቀን አቆጣጠር እየተጠቀሙ ያሉት ቦረኖች መሆናቸውንና ይህም ከሰሀራ በታች ከሚገኙ የአፍሪካ ሀገሮች ቦረኖችን ቀዳሚ የዘመን አቆጣጠር ተጠቃሚ እንዳደረጋቸው አስረግጧል። (ምንጭ፦ Isiolo News Wire) ይህ ከዘመናዊው የግሪጎሪያን አቆጣጠር በ 1800 ዓመታት እንጋፋ ነው። አብራሳ፦ በረጅሙ የቦረና ደረቅ ወቅት (በና) ኢጋማሽ ፥ በአውሮፓውያኑ 'ጃኑዋሪ' አካባቢ የሚጀምር ሲሆን፣ የአብራሳ ስያሜ የትመጣ ሲታይ አደይ አበባ በመስከረም ወር በተለያዩ የሀገራችን አካባቢዎች እንደምትፈካ ሁሉ፣ በጥር ወር በቦረና አካባቢ የምትፈካ ልዩ አበባ ስለሆነች ነው።

በቦረና ዛሬም ቢሆን የከዋክብት እንቅስቃሴን በማጥናት ቀናትን ሳያዛንፉ የሚቆጥሩ ሴቶች 'አያንቱ' (አስትሮሎጂስት) አሉ። በወር ውስጥ 27 ቀናት የየራሳቸው እያና

አላቸው። የቀናት አቆጣጠር ዘይቤውና የማይጠሩ ቀናት ተጨምረው ያለምንም ዝንፈት ጥር (አብራሳ) የምትፈካበት ወቅት የዓመቱ መጀመሪያ ይሆናል። የ30 ቀናት የማይገለፅ ምሥጢር (በቀዳዳ የሚወከሉ ቀናትን) እንመልከት ፊታችን ላይ ሰባት ቀዳዳዎች አሉ። (ሁለት የዐይን፣ ሁለት የጆሮ፣ ሁለት የአፍንጫ፣ አንድ የአፍ)፤ ሃያ ጣቶች (አስር የእጅና አስር የእግር)፤ ሦስት የተለዩ ለመግለፅ የማንደፍራቸው ቀዳዳዎች (የወንድ መፍልዔ ዖታ፣ የሴት ማህፀንና ከኋላ የመቀመጫ)፤ በዚህ ውስብስብ አቆጣጠር ውስጥ ቀሪዎቹ በኢትዮጵያ የተለመደ አቆጣጠር የጳጉሜን አምስትና ስድስት (በአውሮፓውያኑ 31/28)

በቦረና አያንቱዎች በየወራቱ ጣልቃ እየገቡ ሲሄዱ በግማሽ ሚለኒየም (500 ዓመታት) የአንድ ቀን ልዩነት እንደተፈጠረ ይናገራሉ። ይህም በ500 ዓመታት ጳጉሜን ሰባተኛ ቀን ከመምጣቱ ጋር የሚያያዝ ይመስለናል። "አያና ቦረና" በመባል የሚታወቁት በወር ውስጥ ያሉ ቀናት የሚከተሉት ናቸው። አያናዎች በጠቅላላ 17 ሆነው አምስቱ በከዋክብት፣ ሌሎቹ አስሩ ደግሞ በእንስሳት የተሰየሙ ናቸው። የተወሰኑ አያናዎች የሚደገሙ ይሆንና ሁለቱ ደግሞ ሦስት ጊዜ ይቀመጣሉ። ቀናቱ:- ቀራ (አነስተኛ)፣ በሎ (ሠፊ)፣ ዱራ (የላቀ) እና ዱለቻ (ጥንታዊ) በመባል ይከፈላሉ። ቀናቱም:- አሬሪ ዱራ፣ አሬሪ በሎ፣ አዱላ ዱራ፣ አዱላ በሎ፣ ገርባ ቀራ፣ ገርባ በላ፣ገርባ ዱለቻ፣ ቢታ ቀራ፣ ቢታ በላ፣ ሶርሳ፣ አልጋጂማ፣ አርበ፣ ወለ፣ በሳ ዱራ፣ ባሳ ዱሎ፣ መገነቲ ጨራ፣ መገነቲ ጃራ፣ መገነቲ ቢሪቲ፣ ሰልባን ዱራ፣ ሰልባን በላ፣ ሰልባን ዱለቻ፣ ገርዱዱማ፣ ሶንሰ፣ ራሩማ፣ ሉማሰ፣ ጊዳዳ እና ሩደ ናቸው።

የቀናት አቆጣጠር ዘዴዎችን ቀረብ ብሎ የማጥናት እድሉን ላገኘ ምናልባትም ተወዳዳሪ በሌለው ሁኔታ አድናቆትን ማላበሱ አይቀርም። ተመሳሳይ የቀን አቆጣጠር ዘዴ በሲዳማ እና ሌሎች ማህበረሰቦች (ወቅቱ በጣም ይለያያል) መኖሩና በመላው ኢትዮጵያ የሚታወቀው የቤተ ክህነት የከዋከብት አቆጣጠር፣ የጋራችን የሆነው ሌላው የሂጅራ አቆጣጠር ተደምረው ሀገራችንን "የቀናት መቁጠሪያዎች ህብር" ያደርጋታል። "የብሔረሰቦች ሙዚየም"፣ "የብሔረሰቦች ሞዛይክ" ... ባለ ብዙ ፀጋዎች ሀገር ኢትዮጵያ።

በሀገራችን ዕውቅ ከሆኑ የህዝብ እንደራሴዎች አንዱና ጉምቱ ፖለቲከኛው አቶ ቡልቻ ደመቅሳ ታሪክ የሁላችንም የጋራ ክብር ነውና በአንድ ወቅት ባደረጉት ንግግር:- "ዘር ቆጠራውን ተዉት። የአባቶቻችሁን ሀገር ኢትዮጵያን አክብሩ። ኢትዮጵያን የሚያህል



t.me/OLDBOOKSPDF

ታዮ በኋላ

የተከበረ ሀገር አታገኙም። ህዝቧም ታሪኳም ከቡር ነው።" ማለታቸውና አድማጩን ለበጎ ያኖረው የስብእዊ መብት ልእለ ስብእ ታማኝ በየነ፡- "ሁላችንም የምንኮራበት የየራሳችን መገኛ አለን። ኢትዮጵያዊነትን የምናደምቀው የጋራ ኩብራችን ስለሆነ ነው።" ብሏል። አብዛኛውን ሰው በአስተሳሰብ ወደነዚህ ታላላቅ ሰዎች የአመለካከት ከፍታ ለማቃረብ ብንሰራ ብዙ እናተርፋለን። አውግዞን ማንጠግበውና ማንጨርሰው ታሪክ እያለን በተራ የታሪክ ንትርክ ጀርባችንን ማገብጣችን ከማሳዘን አልፎ ያሳፍራል።

የገዳ ሥርአቱ በምዕራብ፣ በምስራቅና በመሀከለኛው የኢትዮጵያ ክፍል (በምዕራፍ አራት እንደምናየው) በመከስምም በተለያዩ አካባቢዎች ከማህበረሰባዊ የአኗኗር ሁኔታ ጋር ተያይዞ ቀጥሎ ነበር። ማህበረሰቡ ታላቅ ሥፍራ የሰጣቸው፡- 'ደገሉ ሰቋ' ጥቅጥቅ ያሉ ዛፎች በበዙበት ስፍራ የደን ፋና ወጊ፣ 'አባ ቀቢዬ' - የመሬት ይዞታ አባት፣ 'አባ ለፋ' - የመሬት አባት፣ 'አባ ጎፌ' - ገመና ከታች የሆነቺው ጎጆ አባት እና ሌሎች እያሉ ተምከሮዎች ፍፁም ኢትዮጵያዊ መልክ ያላቸው ናቸው። በመጨረሻ ጀማው ሲገናኝ በማይነገር ፍቅር ተቀራርቦ በመጨረሻ በባርኮት ምርቃትና ጸሎት ስለሚለያይ የሚከተለውን አካፈለን።

'ዮያ' ስንተቃቀፍ 'ዮያ' ብንባባል አቤት ማስደሰቱ፡ ልጆች አብዝተው፣ ወጣቱም ሆነ አዛውንቱ ሲገናኝ 'ዮያ' ይባባላል - እቅፍ አድርጎ ከመሳሳም ጋር። 'ጉሚ ሰከህንኒ ሂን ደ'ቀብዱ፣ ጉሚ ዮያ' - ደርሼ ሁላችሁንም አስማችሁ ዘንድ አልደርስም፤ ጀማው እንዴት አላችሁልኝ? 'በረ ፊያ ባርተ፡ ፊያ ነጌኒ (ነጌኛ) ቡዳ'ዳ' - ጤናችሁ እንዴት ነው፤ ሰላም በዛላችሁ። ዋን ሀምቱ ኑራ ዶ'ዊ - ከፋውን አርቅልን። 'ኢጆሌ ኑ ደ'ልቺሲ' - ልጆች ይወለዱልን። 'ነመ ጉዳሌ ኑ ቡልቺ' - ታላላቆች ውለው ይደሩልን። 'ኤላ ኑ ቡርቂ፣ መዳ ኑ ገቢሲ፣ ኤላ ኑ ቡርቂሲሲ' - ኩሬው፡ ምንጩ ይፍለቅ ይጥለቅለቅ።

* ገዳን ነጋ - ገዳው ሰላም ነው። ምላሹ፡- ነጌ - ሰላም።

* 'ያ'ኢ ነጋ' - 'ነጌ'። ያኢው ሰላም ነው። ሰላም።

* 'ጉሚን ጋዮ ነጋ' - 'ነጌ' መሰባሰባችን ጀማው ነው። ሰላም።



t.me/OLDBOOKSPDF

* ዋቃ ገለታ ከ ነጋን ወሊቲ ኑ ፊዴ - እዚህ ላሰባሰበን ፈጣሪ ምስጋና ይግባው። 'ነጌ' - ይገባሃል።

* ኑ ነጋ ፊያ ቀበና - ሰላምና ጤና አለን። 'ነጌ'።

* ጉሚን ነጋን ኢዳ ጉቱፌ - ህጉን በሰላም እናሟላ። 'ኢጂኒ' - ሰላም ይሁንልን።

* ዋቂ ዋን ደንሳ ኑ ዱቢሲና - ፈጣሪ እውነቱን እንድንናገር ይርዳን። 'ኤጄኔ'

* እዳፍ ዱ'ጋን አረባ ኑ ቀጂልቺና - ፈጣሪ እውነቱን እንድንናገር ይርዳን። 'ኤጄኔ;

* ዋቂ ገዳ ነጋ ኑ ጉቲና - ፈጣሪ ጉዳውን ይሙላልን። 'ኢጂኒ'

* ገዳን ሰዴን ነጋ - ለሦስቱ ገዳዎች ሰላም ይሁን። 'ነጌ'።

* ለዱን ሸነን ነጋ - ለአምስቱ የእምነት አባቶች ሰላም ይሁን። 'ነጌ'።

* በዳን ሰዴን ነጋ - ለሦስቱ ኮረብታዎች ሰላም ይሁን። ነጌ። (ሦስቱ ኮረብታዎች ሂዲ ለላ፣ ሚጋ እና ስሩዳ ናቸው።)

* ዲሬን ነጋ፣ ዲሪ ሊበን ነጋ - ለዲሬና ዲሪ ሊበን (ዲሮ ሊበን ተደምሮ) ወረዳዎች ሰላም ይሁን። ነጌ።

* መልቢን ነጋ፣ ጎልቦ'ን ነጋ - ለመልቢ ሜዳዎችና አካባቢው ሰላም። ነጌ።

* ቱላን ሰግለን ነጋ - ለዘጠኙ ጥልቅ የውሀ ጉድጓዶች ሰላም። ነጌ።

* ሬባ ገዳን ነጋ - ለራባ መሪዎች ሰላም። ነጌ።

* ገዳ ግሚጂን ተ' ረባ ነጋ - ለገዳ ግሚጂዎች (ለጡረተኞች) ሰላም። ነጋ።

* መራ ቢሳን ሚኟ - ግጦሽ ወሀ ይሙላ። ነጌ።

* ሰ'ዓ ነግ ሀ ሆፋ - ከብትና ህዝብ ይብዛ። ነጌ።



t.me/OLDBOOKSPDF

* ሰቦ ጎኒ ነጋ - (ለሰቦ እና ጎና ጎሳዎች) ሰላም። ነጌ።

* ኑ መራፍ ቢሳን ቆፊ ቀብና - ከሰላምና ዝናብ ሌላ ምን አለ።

ምርቃቱ ከዚህም የሰፋ ሆኖ ለእያንዳንዱ የፃምርቃት ሐረግ ምላሹ ሰላም፣ ሰላም፣ ሰላም ... ነው። በረና አብዝቶ 'ኑ ወረ ነጌ' - እኛ የሰላም አምባሳደሮች ነን ማለቱ ለሰላም ከፍ ያለ ዋጋ መስጠቱንና ለድርድር እንደማያቀርበው መመልከት ይቻላል። በሰላም ከመኖር የሚልቅ ምንም የለም። ሰላምን ለማግኘት የሰላም ፀሮችን ማራቅ አለብን።

ሆራ ቡላ ዴበና።

## የዘመናዊ ታሪካችን ፈርጦች

በቀደመው ታሪካችን ወላጆቻችን በከብር ያኖሯቸው ኪነህንፃዎች፣ ስነጥበብ፣ ህግ፣ እና በርካታ የሚዳሰሱም ይሁኑ የማይዳሰሱ ውርሶች የትየለሌ ቢሆኑም በተግባር ሲመዘን ለትውልድ በሚያስተምሩበት አግባብ በበቂ ደረጃ አልተደጎሱም። ይሁንና በመጠኑም ቢሆን ለመሰነድ ለተደረጉ ሙከራዎች ምስጋና ይገባቸዋል። ሆኖም ብዙ ስለሚቀረን ፍለጋው መቀጠል አለበት። ጅምሩ በመኖሩ የመፅናናታችንን ያህል የሚያስቆጨው ከጥንቱ ዘመን እስከ ቅርብ ጊዜያችን ሀገር ያቆየቻቸው ታሪኮች እንዲታወቁ ምን ተሰራ? ስንል እጅግ በጣም ትንሽ ከማለት ውጪ የሚቀርብ መልስ ቢኖር ሀሰት ነው። በታሪክ ሀገር ያለ እነርሱ ያልቆሙችና የማትቀጥል አስገራሚ እንስቶች የወል ሐውልት ሊቆምላቸው ሲገባ ሴቶች አያቶች፣ እናቶች፣ እህቶች ልጆች (ግማሽ የእኛነታችን መሠረቶች) በታሪክ ውስጥ አሉ ለማለት አያስደፍርም ።

ከእነዚህ ውስጥ፦ "ንግሥተ ሳባ"፣ ህንደኬ፣ ፋራ፣ ዮዲት፣ አኮ መናዬ፣ የቃቄ ወርዶት፣ ሎኮ፣ እሌኒ፣ ሰብለወንጌል፣ ባቲ ድል ወንበራ፣ ምንትዋብ፣ ዋቢ፣ ጣይቱ፣ ዘውዲቱ ሸዋረገድ ገድሌ፣ ሸዋነሽ አበራ፣ ስንዱ ገብሩ፣ አበበች ጎበና፣ ሲስተር ዘቢደር/ ሜሪ ጆይ፣ ሙዳይ... ሊጠቀሱ ይችላሉ። መንደርደሪያችን፦

"መቅደላ አፋፍ ላይ፥ ጩኸት በረከተ፣



t.me/OLDBOOKSPDF

የሴቱን አናውቅም፥ ወንድ አንድ ሰው ሞተ።"

የሥባለላቸው ገና በሰባት ዓመት ለጋ እድሜያቸው አባታቸውን በሞት ተነጥቀው እናታቸው ለልጃቸው ሲኖሩ ቅመም እየሸጡ ዳግማዊ ቴዎድሮስን በፈጠሩ እናት ወይዘሮ አትጠገብ ተሻግረን መይሣው ጋ ለመድረስ ነው። ቴዎድሮስ በአግብዖ ሲሸንቆጡም "የኮሶ ሻጭ ልጅ" ይባሉ ነበር። ይህ ዓለምን ያለልዩነት በእድልዎ ሚያስወቅሳት ሴቶችን የማሣነስ ይትበሃል ለማጥፋት ብዙ ቢወራም ብዙ አልተሠራምና "የሴት ልጅ" ተብሎ ሀቅ ቢነገርላቸው የሚመጥናቸውን ቴዎድሮስን እንቃኛለን። ሁላችንም ከታደልን በማያጠራጥር ሁኔታ 'የሴት ልጆች' ነን። የሴት ልጅ በመሆናችን ክብርና ምገሥ ለእናቶቻችን እንሳለን። አባ ታጠቅ ሚስታቸው ተዋበች ስትለያቸው፡-

"እስቲ ጠይቁልኝ፣ ርቃ ሳትሄድ፣

እቴጌ ተዋበች ሚስት ናት ገረድ?"

በማለት በኀዘን በተሰበረ ልብ፡- ገመና፣ አካላቸው ሦስት ነገሮችን አጣምራ መያዟን መስከረዋል (ሚስት፣ እናት እና አገልጋይ)። ቅኔውን አልፈን አወዛጋቢውን የቴዎድሮስን ማንነት እንግለጥ።

## ዳግማዊ ቴዎድሮስ (1855 - 1868)

ዐፄ ቴዎድሮስ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የነበራቸውን ቦታ ለመበየን በቅድሚያ ታሪካቸውን በሚገባ ማወቅ ይቀድማል። አውቆ (በአውቀት) መፍረድ ጥበብ ሲሆን፣ ሳይመረምሩ ድምዳሜ ላይ መድረስ ደግሞ ድንቁርና ነው። አጫጭር መግለጫዎች፡- ካሳ ኃይሉ በቀጥታ የደም ግንኙነት (ቤተሰቦቻቸው ጭምር የነገሥታት ደም አለባቸው ቢሉም) የታሪክ መዛግብት እንደሚገልጡት የነገሥታት ዘር አልነበሩም። በ1820 ተወልደው በ1827 አባታቸውን ተነጥቀዋል። በልጅነታቸው በተከለሀይማኖት ገዳም የቤተ ክህነት ትምህርት መከታተል ቢጀምሩም በዘመነ መሣፍንት ጦርነት ምክንያት ትምህርታቸውን ለማቋረጥ ተገደዱ። በ'ወንድማቸው' ከንፉ ሀይሉ ሥር እና ጎጃም በመሄድ ደጃች ጎሹ ሥር ሆነው አገለገሉ። በ1837 የቋራ ገዢ የነበሩት ከንፉ ሀይሉ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሲሞቱ (የቋራን ገዢነት ወይ ለከንፋ ልጆች አሊያም ለራሳቸው ቢመኙም) ራስ ቢትወደድ አሊ አሉላ ግን ለእናታቸው መነን እንደራሱ፤ ደጃች ቢተዋ አሳልፈው ሰጡ። ውሳኔው ያስቆጣቸው ካሳ ሀይሉ ዘጠኝ ተከታዮችን አስከትለው የኩርፊያ "የፖለቲካ ሽፍትነት" በቋራ ጀመሩ።

ሕይወት በልጅነታቸው የፈተናቸው ካሳ ለየት ያለ ስብዕና የነበራቸው የፖለቲካ (የኩርፊያ) ሽፍታ ነበሩ። ለተከታዮቻቸው የበዛ ክብር የነበራቸውና ራሳቸውን ማይኮፍሱ እንደነበሩ በቴዎድሮስ ዙሪያ የተፃፉ ድርሳናት ያመለክታሉ። ከገበሬዎች ጎን ያርሳሉ። ከባላባቶች ነጥቀው ለገበሬዎች ያከፋፍላሉ። መልካም ዝናቸው በመግነኑ በሥራቸው የሚያድረው ጦረኛ ቁጥሩ እየናረ መጣ። በ1948 ኢትዮጵያን ለመያዝ ድንበር እየጣሰ ከሚገባው የግብፅ ጦር ጋር ደባርቂ ላይ ተዋግና ቆስለው ተሸነፉ። በሀይወት የተረፉትም በእድል ነው። ካሳ የተሸነፉበትን ምክንያት ሲመዝኑ የወኔ መሳሳት ወይም የውጊያ ብቃት ሳይሆን የዘመናዊ ጦር መሣሪያ ብልጫ መሆኑ ገባቸውና ራሮት ቦጨቃቸው። አለመሠልጠን መሸነፍ መሆኑን ተሞክሮ ሲያሳያቸው ወጣት አእምሯቸው የቴከኖሎጂ ራዕይ ሰነቀ።

በሂደት የካሳ ጡንቻ እየፈረጠመ ሲመጣ ወሬው ጎንደር ቤተ መንግሥት ደረሰ። "እረ ሰውየው ተራ ሽፍታ አይነት አይደለም ደርጅቷል' ሲል ለራስ አሊ ወሬ ነጋሪ እውነቱን ሹክ አላቸው። የጦር አበጋዞቻቸውን ሰብስበው ስለነገሩ ሁኔታ ሲመክሩ የጎጃሙ ደጃች ጎሹ:- "ይህንን የኮሶ ሻጭ ልጅ አንጠልጥዬ ባላመጣው እኔ ጎሹ አይደለሁም" የሚል ዛቻ ሰነዘሩ። በ1852 ጉር አምባ ላይ በተደረገ ውጊያ ካሳ ድል በእጃቸው ሆነች። በብሩ አሊ ጋዝ መሪነት የተመመውን በአራት ራሶች የሚመራ ጠንካራ ጦር በ1853 ጎርጎራ ቢቸን ገጥመው በለስ ቀናቸው። የራስ አሊ እናት እቴጌ መነን:- "ቆይ ይሄ ቆለኛ የፍየል እረኛ፤ ልክ ባላስገባው እኔ አይደለሁም።" በማለት ፎከሩ።

ካሳ ሀይሉ ምላሹን ሲሰጡ:- "ይህቺን ቆፍጣጣ አሮጊት በጦሬ ጫፍ ወግቼ ባቁላ ያላስፈጩኋት እንደሆነ እኔ ካሳ ሀይሉ አይደለሁም።" የሚል ምላሽ ሰጡ። (በዘመኑ ከጦርነት አስቀድሞ መፎከር የተለመደ ነበር።) አስከትሎም መነን ከነባላቸው (የሐንስ ሦስተኛው) እጣ ፈንታቸው ከቀደሙት የተለየ አልነበረም። ሽንፈትን ተከናንበው በምርኮ ተያዙ። ካሳን በጉልበት ሳይሆን በጥበብ ለማለመድ የቋራ ገዢነትና የራስነት ሥልጣን ደርበው፣ የራስ አሊን ልጅ ተዋበችን መርቀው "የፖለቲካ ጋብቻ" ቢመሠርቱም፤ ውለው አድረው በመነን የቅርብ ተቆጣጣሪነት ሥር



t.me/OLDBOOKSPDF

ሲያሳድጉቸው ካሳ በድጋሚ የቋራን በረሀ ናፍቀው ሸፈቱ። የመጨረሻውን የዘመነ መሣፍንት ራስ በ.ትወደድ ራስ አሊ. አሉላን በአይሻል ጦርነት ድል ነስተው በ1854 ንጉሥ ካሳ ሀይሉ ተባሉ።

በ1855 ደረስጌ ጦርነት ላይ የትግራይና የሰሜን ገገር የነበሩትን ደጃዝማች ውቤ ኃይለማርያምን አሸንፈው ንጉሠነገሥት ዳግማዊ ቴዎድሮስ ተባሉ። የንጉሡ ድብረፅጌ ማርያም በአቡነ ሰላማ ተቀብተው ነበር። "ፈጣሪ የህዝቡን መገፋት በይቶ ከትቢያ ላይ አንስቶ በአባቶቼ ነገሥታት ዙፋን ላይ አስቀመጠኝ።" (ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ታሪክ ከተከለፃድቅ መኩሪያ ጀምሮ ስለቴዎድሮስ በፃፉ ፀሐፍት በጋራ የተገለፀ እና የተለመደ በመሆኑ ለመግቢያ አጠር አድርገን አቅርበነዋል። ወደ ዋናው የንግሥና ዘመን ታሪካቸው አልፈን በፈርጅ በፈርጁ የአስተዳደር ዘይቢያቸውን ከታች በተዘረዘረው አኳኋን አሰናዳን።)

በአፄ ቴዎድሮስ የህይወት ዘመን ዙሪያ በርካታ ድርሳናት ተፅፈዋል። ጥናታዊ ፅሑፎች ቀርበዋል። ተውኔቶች ተደርሰዋል። ግጥሞች ተፅፈዋል። ከዘውጎቹ መሀከል የአፄ ቴዎድሮስን ስብእና በተመለከተ አወዛጋቢ ሆነው የቀረቡት የሀትመት ውጤቶች፣ የበይነመረብ እና ድረገፅ የመገናኛ መንገዶች ናቸው። ለአብዛኛው ህዝብ ቅርብ ከመሆናቸው አኳያ "ተነባቢ ሚዲያዎች" ተፅዕኖ በመፍጠር ቁንጮዎች ናቸው። ምንም እንኳ ተንቀሳቃሽ ምስሎች ኃያል መሆናቸው አከራካሪ ባይሆንም ከስፋታቸው እና ጥልቀታቸው ማነስ እና ከአቀራረብ ውስንነት አንፃር ማራኪነታቸው እምብዛም ስለሆነ ተደራሽነታቸው በሚፈለገው ደረጃ አይደለም። በተፈለገ ወቅት በቀላሉ ካለመገኘታቸው ጋር ተያይዞም በፅሑፍ የሚቀርቡ ሚዲያዎችን ያህል አእምሮን ለመቆጣጠር አልቻሉም። ከሁሉም በላይ አጣቃሽ ማስረጃዎችን ስለማያቀርቡ ተቀባይነታቸውን ጎዶሎ ያደርገዋል።

በተለያዩ ሁናቴዎች ስለአፄ ቴዎድሮስ ሥራዎች ከፃፉት እና ሚዛናዊ ትችት ካቀረቡት መሀከል ስዊድናዊው ፕሮፌሰር ስቨን ሩበንሰን፣ ፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት፣ ፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ፣ ፕሮፌሰር መርዕድ ወልደአረጋይ፣ ፕሮፌሰር ሺፈራው በቀለ፣ ፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት፣ ዶክተር አምሳሉ አክሊሉ ሊጠቀሱ ይችላሉ። በሌላ በኩል ተክለፃድቅ መኩሪያ፣ በ1967 ብብርሀኑ ዘሪሁን የተፃፈው "የቴዎድሮስ ዕንባ" ታሪካዊ ልቦለድ፣ በ1969 የአቤ ጉበኛ "አንድ ለእናቱ"፣ ከትውልድ ሀሊና የማይጠፋው የባለቅኔ ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን የ1963 መድብል "እሳት ወይ አበባ" ውስጥ ሰፈ ስፍራ የያዘው "የቴዎድሮስ ስንብት ከመቅደላ"፣ የደረሰብት



t.me/OLDBOOKSPDF

የመጨረሻው የትምህርት የማዕረግ ደረጃቸው ባለመታወቁ በስም ያቀረብናቸው አማኑኤል ሳህሌ፣ ሥዩም ወልዴ፣ ታየ አሰፋ፣ ስቴፈን ቢል፣ ሪታ ፓንክረስት እና ጆአና ማንቴል-ኖኮ እንዲሁም አያሌ ያልተጠቀሱ የምርምርና የጥናት ሥራዎች የአፄ ቴዎድሮስን ህይወት ዳስሰዋል። ወደ አፄ ቴዎድሮስ ሥራዎች ጠልቀን ከመግባታችን በፊት 'ክብር ለሚገባው ክብር ሠጥተን' እንለፍ።

በታሪክ የትምህርት ዘርፍ አንቱ ከተባሉ ምሁራን አንዱ የሆኑትና የዘር ሐረጋቸው ከትግራይ የሚመዘዘው ፕሮፌሰር ገብሩ ታረቀ በebs ቴሌቪዢን በታዋቂዋ ጋዜጠኛ ሀሊና አዘዘ ቃለ መጠይቅ ቀርበላቸው ነበር። ጥያቄውም፡- "ፕሮፌሰር፡- ከኢትዮጵያ መሪዎች ማንን ያደንቃሉ?" ፕሮፌሰር ገብሩ ታረቀ ምላሽ ሲሠጡ፡- "የቀደመውን ዘመን መሪዎች አልፌ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ባነፃር ቴዎድሮስን የሚያህል የለም።" በማለት ነበር ግዙፍ ልዕለ ሰብእ መሆናቸውን ለማመላከት የደፈሩት። ፕሮፌሰሩ አሜሪካ በሚገኘው ዬል ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያውና ቃለመጠይቁ እስከተደረገበት እለት ድረስ በአካዳሚያዊ ብቃት የተሸለሙ ብቸኛው ጥቁር ናቸው።

(የምሁሩን ብሔረሰባዊ የት መጣ የገለፅነው የጎሣ የዘውግ ስሜት በረበበት የሀገራችን የታሪክ ዳራ ብሔረሰብ ሳይሆን ህሊናቸው ልቆ ወጥቶ፣ በብሔረሰብ ታሪክ ሽሚያ ሳይዘፈቁ በዚህ መልክ ሀቁን የሚገልጡ፣ አርአያ የሆኑ ሰብእናዎችን ብናደንቅ፣ እውነትን ማገልገል እንደሚያስከብር ለሌሎችም ማስተማሪያ ይሆናል ብለን ስላመንን ነው። በቀጣይ ክፍሎችም አስፈላጊ ሆኖ ባገኘነው ጊዜ ይህንንው አካሄድ መከተልን መርጠናል።)

የአፄ ቴዎድሮስ አመራር ዘመን ለምን የዘመናዊ ታሪክ መነሻ ሆኖ በታሪክ ልሂቃን ተደነገገ? ስንል ለጭካኔያቸውም ለፍልሚያቸውም አልፋና ዖሜጋው "የዘመናዊነት ታላቅ ፍላጎታቸው" እና ለዚህም የከፈሉት መስዋዕትነት ነው። ስለአፄ ቴዎድሮስ የአድማ ዘመን ሥራዎች ጠለቅ ያለ ምርምር ያደረጉት ፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት በ1990 በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም በተዘጋጀው እና ዳጎስ ያሉ ዕይታዎችን አካትቶ፡- "KASA AND KASA" በሚል ርዕስ በተደጎሰው መፅሐፍ የተካተቱ ሀሳቦችን ይዘታቸውን ሳንለቅ፣ ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ መልሰን አሳጥረን በሚከተለው መልክ አቅርበናል።



t.me/OLDBOOKSPDF

በምግቢያቸው ከሌሎች ምሁራንና ዐለፈዎች የተበረከቱ ሥራዎችንም በተመክሳሳይ ጠይ አማርኛ ቋንቋ በመተርጎም አትትተናል። ፓገዛረስት እንደሚገልበት በቴዎድሮስ ዙሪያ ጥናት ያደረጉ አውሮፓውያን ከተዛቢ ልዩታ ተነስተው፣ የሀገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ ሳያገናዝቡ፣ የቴዎድሮስን ሰብእና ጠለቅ ብለው ሳይረዱ፤ በዘፈቀደ ከተንኮሬያቸው ደልቅ ድክመቶቻቸው ላይ አትኩረው ፅፈዋል። በተቀደደልን ቦይ የመፍሰስ አባዜ ስለተጠናወተንና የንጉሳ ፖለቲካ ቴዎድሮስን ከአፍ ማህበረሰብ ውጪ አድርገን እንድናስብ በፈጠረብን ተፅዕኖ ባቢያ አንዱ የተባሉ የቴዎድሮስ ዓብይ ፍፃሜዎች ተሸፍነዋል። ስለዚህ በስሜት ላይ ሳይሆን በማስረጃ ላይ ተመስርተን ሥራቸውን ማሳየት መቻል አለብን ይላሉ። በ1861 የቴዎድሮስን የበዛ የጥበብ ፍላጎት የተረዳው የፈረንሳይ የብረት ሥራ ባለሙያ ጃኩዊስ በአካባቢው ያሉ የአይ ጥበብ ባለሙያዎች እርዳታ እንዲያደርጉለት ከተፈቀደለት የሚፈልጉትን አይነት መድፍ ሠርቶ ማስረከብ እንደሚችል ለቴዎድሮስ አሳወቀ።

በዚህም መሠረት ቀጥሎ የነበረውን ሂደት ሚሲዮናዊው ቴዎፊላስ ቫልዳሚር እንደሚከተለው ገልፆታል።

በታዘዝነው መሠረት ጥበቡ ብቃት እና ዕውቀት ያላቸውን አገሊጋዮች መርጠን ተግባሩ ተጀመረ። ባለሙያዎቹን በማስተባበር የብረት ማቅለጫና ማብሊያውን መሣሪያ ተከላ አካሄድን። ከብዙ ድካምና ጥረት በኋላ የደረስንበት ደረጃ አበረታች ስለመሆሉን ግሚሡ ውጤቱን ለማየት በመጓጓት እና ሌላው ከንጉሡ ነጋሥት ሽልማት ለማግኘት በመጓጓት በርካታ ሰው ተሰበሰበ። ተስፋ በሚያስቆርጥ ሁኔታ ማብላያው የተሠራው ከመናኛ ብረት ስለነበር እንዲቀልጥ የታሰበው ብረት መቅለጫ ነጥብ ላይ ከመድረሱ በፊት ራሱ ማብላያው ቀለጠና ሥራውን አዳጋች አደረገው። ጃኩዊስ ሙከራው በመምከኑ ንጉሡን አስፈቅዶ ወደ ሀገሩ ተመለሡ። ቴዎድሮስ ግን በቀላሉ ተስፋ የሚቆርጡ አይደሉም። ነጭ ባዩ ቁጥር አንዳች ጥበብ ለኢትዮጵያውያን እንዲያወርሱ ፍላጎት ነበራቸው። አንዳች ተጨባጭ ውጤት ዐይተው እስኪረኩ ሕሊናቸው እረፍት የሚያስብ አይነት ሰው አይደሉም።

ቫልዳሚር ከመጀመሪያው ውድቀት በኋላ የነበረውን ድባብ በሚከተለው መንገድ ገልፆታል።



t.me/OLDBOOKSPDF

የቴዎድሮስ የመጀመሪያው ስኬት፡- ፈረንሳዊው ጃክዊስ ወደ ሀገሩ ከተመለሰ በኋላ ቴዎድሮስ ወደ ጋፋት መጡና፡- 'እኔ ልሙት በምንም ጉዳይ አልደራደርም። በሉ ሥራውን ቀጥሉና በፍጥነት ዳር አድርሱት' አሉን። እኛም 'ጃንሆይ የመሣሪያ አሠገኛጅነት ጥበቡም ልምዱም የሌለን ሚይማን ነን። ያሠሡን ተግባር ከአቅማችን በላይ ስለሆነ ይቅርብንና' በማለት መለስንላቸው። ተስፋ ሳይቆርጡ 'ባይሳካላችሁ ምንም ማለት አይደለም። ብቻ እናንተ ሞክሩ።' አሉንና ማግሥራራቸውን ለማሳየት አገልጋዮቻችንን በመያዝ መልክ በአሥር አቆዩዋቸው።

ከበርካታ ሙግት በኋላ ምሬዝ ሃል አነስተኛ መድፍ እና ጥቂት ጥይቶች ማምረት ቻለ። አጼው ፈጣሪያቸውን አመስግነው በደስታ ዘለሉ። አርኪታቸው ግን ብዙም አልቆየም። 'ምሬዝ በል ትልቅ መድፍ አዘጋጅ ብለው አዘዙት። ምሬዝ ሌላ መፈናፈኛ እንደሌለው ሲገነዘብ 'ውጤታማ ሥራ እንዠራ ዘንድ ጋፋት ያሉት ሚሲዮናውያን እንዲያግዙኝ ይፍቀዱልኝ' በማለት ለንጉሡ ያቀረበው ጥያቄ ይሁንታ አገኘ። ንጉሡ እረፍት አልባ ናቸው። 'ሥራውን ከምን አደረሳችሁት?' የሚል ይዘት ያዘለ ደብዳቤ በማከታተል ያንርፉልን ነበር።

እውነቱን ለመናገር የቴዎድሮስ ትዕግስት ከእኛ የተሻለ ነበር። ባልተሳካልን ቁጥር፡- 'ማለላችሁ ከመጀመሪያው ጀምሩ' ይሉንና አንዳች ተጨባጭ ለውጥ ይጠብቃሉ። እኛም አቅም በፈቀደልን መጠን ጥረታችንን ቀጥለን ወደ ፍፃሜ ስንደርስ ዳር ቆም ያወከና ይሳለቅ የነበረ የደስታችን ተካፋይ ለመሆን ተሰበሰበ። የመድፉ ፍንዳታ ድምፅ እንደተሰማ የንጉሡ አርኪታ ወደር አልነበረውም። በደስታ ብረቱን ተሸከሙና በእንባ ተጥለቅልቀው በከንፈራቸው ሳሙት። በሣግ በታፈነ የደስታ ሳግ ባፈነው ድምፅ፡- "ዛሬ በሀበሻ ምድር የትኛውንም ስኬት ልንጎናፀፍ እንደምንችል አመንሁ። ለፈጣሪ ምስጋና ይግባው በመጨረሻ ረድቶናልና።

" ንጉሡ በአንድ ስኬት የሚረኩ አይደሉም፤ ሌላ ውጤት ለማየት ትጋት ይጨምራሉ። ከዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ እልህ፣ ቁጭት፣ ቁጣ፣ ትጋት፣ ቆርጠኝነት፣ የጋለ ስሜት፣ ክትትል፣ የአመራር ብቃት፣ ለሳይንስ



t.me/OLDBOOKSPDF

ቴክኖሎጂ ያላቸውን መንግሥት፣ ኢትዮጵያ የላቀ ደረጃ ላይ እንድትደርስ የነበራቸውን ታላቅ ምኞት ተስፋና የሩቅ ግብ ነው።

ሻለቃ ማርከስ ከስኬቱ ቀጥሎ የነበረውን ድባብ ሲያብራራ፦

'ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ከዘውዳቸው እና ዙፋናቸው በስተቀር በግዛታቸው ውስጥ የምንፈልገውን ማንኛውንም ነገር እንድንጠይቃቸው ፈቃድ ሰጡን። እኛም 'ከእርስዎ ፍቅር እና ቋሚ ወዳጅነት በስተቀር ሌላ መሻት የለንም አልናቸው። አፄ ቴዎድሮስ በአፀፋው የጠየቅነውን ከበሬታና ወዳጅነት አብዝተው እንደሚለግሡን ቃል ገቡልን። በዚህም ሳይወሰኑ ለኢየንዳንዳችን በነፍስ ወከፍ 1,000 ዶላር ሸለሙን። ለመናገሪያ ቢታችን የሚያስፈልጉንን ቁሳቁሶች ለማሟላትም ቃል ገቡልን

በማለት በማስታወሻው ከትቦታል።

የብሪታንያው ተጓዥ ሄነሪ ዱፍተን ከ1862 - 63 ኢትዮጵያን ሲጎበኝ ያስተዋለውን ደግሞ እንደሚከተለው መዝግቧል።

'የመድፎችና የሞርታሮች ሥራ ተጧጡፏል። በሥራው ተሳታፊ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ረዳቶችና ሠልጣኞቻቸው ጥበቡን ቀስመው ለሙያቸው መሻሻል አትርፈውበታል።' እጅግ ከተደነቀበት ምልከታው እንዲጋራው አፄ ቴዎድሮስ ተግባሩ በሚከናወንበት ሥፍራ በመገኘት ዜጎቻቸው እያንዳንዱን ሂደት ልቅም አድርገው እንዲከርጁ እና ጥበቡን በሚገባ እንዲቀስሙ ያበረታቱ፣ እንደነበር በጉልህ አስምሮበታል። ከማስታወሻው ላይ ሪቻርድ ፓንከረስት ከጠቀሰት የሚከተለውን እንደወረደ አቀረብነው፦

*Tewodros, an innovator in this as in other matters, "also contemplated" sending a batch of Ethiopians to England and France "for the purpose of learning useful trade".*



t.me/OLDBOOKSPDF







t.me/OLDBOOKSPDF

ዘመናዊ የፍትሕ ሥርዓትን ማቆም፡- 'ፍርድ ተጓደለ - ሀገር ተበደለ' የሚል አሮር መሰማት እንኳን በዚያ የሩቅ ዘመን በ21ኛው ክፍለ ዘመን ሁለተኛው ዓሥርት ዓመት ማገባደጃ ላይ ሆነንም የተለመደ ነው። በየሥፍራው ያለው ባላባት ባሻው መንገድ መመገለጃ እየተቀበለ ፍትሕ መዛባቱ ቅሬታ እየፈጠረ የተሻለ አቅም ያለው በእጅ እየሄደ 'ረብጣ ገንዘብ መናገር ሲጀምር እውነት ዝም እያለች' ወገን ተበደለ። ሁኔታውን ለማስረዳት፡- በአንድ ወቅት ተከሳሽ ለባላባቱ ጠገራ ብር ከፍሎ እንደሚፈረድለት ተማምኖ ተዘልሎ ተቀመጠ። ከሳሽ ባላጋራውን ለመርታት በጎን ሄዶ በቅሎ በጉቦ መልክ ለገገሮው አቀረበ። በፍርዱ እለት ተከሳሽ በራስ መተማመን ስሜት ይፈረድልኛልን ሲጠብቅ ተፈረደበት። በቅሬታ አንገቱን እንደደፋ፡- "ምነው በእጄ ብዬ መጥቼ"

ሲል አጉተመተመ። ዳኛውም መለስ አድርገው፡-

"መጭ ብሎ ቀደመህ" በማለት መለሱለት። (እውነታው በእጄ ጉቦ ሰጥቼ ምነው ተፈረደብኝ? የሚል ሲሆን፤ የዳኛውም ምላሽ መጭ / በቅሎ አቅርቦ ረታህ እንደማለት ነበር።) ይህንን የበሸቀጠ የፍትሕ መዛባት ለመግታት በሥነምግባር ደረጃቸው ላቅ ያሉ እና የተሻለ ነገር የመተቸትና የመዳኘት ችሎታ ያላቸውን ዳኞች በመሾም የዳኝነት ሥርአቱን ለማዘመን ሠርተዋል። ከዚህም ባለፈ የረጂም ርቀት ንግድ እንዲያንሰራራ ተግተዋል። በኢትዮጵያ ምጣኔ ሀብት ከአክሱም ዘመን ጀምሮ የረጂም ርቀት ንግድ ሢራራ ነጋዴዎች በመሪያቸው ነጋድራስ (ነጋዴ ራስ / የነጋዴዎች ራስ) በመመራት ያከናውኑ ነበር። አፍቃላ ጀበርቲ ጀለባ አፋር ሰፈሬ እና አያሌ ነጋዴዎች በአራቱም ጫፍ የተጧጧፈ ንግድ ያካሂዱ ነበር።

ይህም በሀገራችን ምጣኔ ሀብት ከእርሻ ቀጥሎ ሀገርን በማቆም ረገድ ከፍተኛ ድርሻ ነበረው። በዘመነ መሣፍንት በሽፍቶች ምክንያት የተቀዛቀዘውና የለም በሚባል ደረጃ የተዳከመውን የንግድ ሥራ በአዲስ መልክ ለማንቀሳቀስ እና ከዚሁ ጋር የህዝቡ የተመሰቃቀለ ህይወት እንዲለወጥ ሁሉም በየአባቱ (በየሙያው) ገብቶ እንዲኖር በማሰብ አስለፈፉ። 'ገበሬ እረስ፣ ነጋዴ ነግድ፣ የእደ ጥበብ ባለሙያ ከሂልህን አሳድግ፣ ካሊት የምትቸረችርም ተግባርህን ቀጥል...' ይህንን መመሪያ ተከትሎ ሽፍቶች ከየስፍራው ተሰባስበው፡- 'ሁሉም በየሙያው እንዲተዳደር ፈቅደዋል። እኛም



t.me/OLDBOOKSPDF

ከሽፍትነት ውጪ ልምዱ የለንምና ዘርፈን እንድንበላ ይፍቀዱልን' አሏቸው። አፄ ቴዎድሮስም በምላሹ፡- "የእናንተ ሙያ በጣም አደገኛ ነው። በእንፃሩ እርሻ በጣም ያተርፋል። ወደ መስከ ወርዳችሁ እርሳችሁ ብሉ። እኔ ራሴ የምታርሱባቸው በሬዎች ከነመሣሪያው አሟልቼ ሰጣችኋለሁ" ሲሉ ቃል ገቡላቸው። ዘርፎ መብላት የለመደ ላቡን ጠብ አድርጎ መተዳደር ይቸግረዋልና ሽፍቶቹ ደስታ ፊታቸው ላይ አልተነበበም። ሊጃን የተባለው ፀሐፊ እንደሰነደው፡-

'እስቲ ለውሳኔውም እንዲመቸኝ ተሰባሰባችሁ ኑ' በማለት ሸፍቶቹን ተማልተው መገኘታቸውን ካረጋገጡ በኋላ አንድም ሳያስተርፉ ሞት ፈረዱባቸው ይለናል። (ዳግማዊ ቴዎድሮስ ሰላም ሰፍኖ፣ ህዝብ በየሙያው ያርር እና ንግድ ይዳብር ዘንድ ገዳይ ሽፍቶችን ገድለዋል። ሽፍቶቹን አስረው ማስተማር ሲችሉ መግደላቸው ተገቢ ባለመሆኑ ልምድ ቀስሞ - ሽፍታ ከተኮሰ እጅ እስኪሰጥ ምላሽ መስጠት፣ እጅ ከሰጠ ግን ምህረት አድርጎ እና አስተምሮ ወደ ሰላማዊ ህይወት መመለሡ ይመረጣል።)

የመንገድ ሥራ ፕሮገር፡- አፄ ቴዎድሮስ በመንገድ ሥራ ዘርፍ ደብረ ታቦርን ከጎንደር፣ ደብረ ታቦርን ከጎጃም እና ደብረ ታቦርን ከመቅደላ ጋር የሚያያይዝ አይነተኛ የመንገድ ሥራ አከናውነዋል። የመጀመሪያው ሠረገላ ተሠርቶ አገልግሎት ላይ መዋሉም ለላ ድል ነው። ሲባስቶፖል የተሰኘው መድፍ ከደብረ ታቦር ወደ መቅደላ የተጓዘው አዲስ በተሠራው መንገድ ነበር። የቴዎድሮስ ምርኮኛ የነበረው እንግሊዛዊው ሄነሪ ብላክ በመንገድ ሥራው ላይ የቴዎድሮስን ተሣትፎ አስመልክቶ የሚከተለውን ማሥታወሻ አስፍሯል።

ቴዎድሮስ ማልደው ጧት ጎህ ሲቀድ ይነሡና እስከ ምሽት ድረስ በጉልበት ሥራ ይጠመዳሉ። በእጃቸው ድንጋይ እያነሱ፣ ኮረት እየተሸከሙ በመደልደል እና በሙሉት ሥራ በቀጥታ ተሳትፈዋል። እሳቸው በሥፍራው እስካሉ ድረስ ቢመሽም ማንም ከሥፍራው ንቅንቅ አይልም። ንጉሡ በሥራ ወቅት ስለማይመገቡ ሌላውም ሰው ስለመብል እና መጠጥ አያስብም።

የአፄ ቴዎድሮስ የሥራ ተነሳሽነትና ትጋት ከቃላት ይልቅ መሬት የነካ በተግባር የተመሠከረለት ነበር። 'መሪ ለመምራት ሲጀግን ተከታዮች ቁርጠኛ ይሆናሉ' በአመዛኙ እውነትነት አለው። ማርካም የተባለ የብሪቲሽ ዜጋ የመንገዱን ሥራ አስመልክቶ የብላንከን ሀሣብ በሚያጠናክር አግባብ "እጅግ በጣም የሚያስደምም" በማለት አድናቆቱን ሲያሠፍር፤ አሌክሳንደር ሺፐርድ "እፁብ ድንቅ" በማለት



t.me/OLDBOOKSPDF

አምከሽቶታል። ቴዎድሮስ በእያንዳንዱ ዘርፍ የነበራቸውን ሠፊ ውጥን በመገለፅና ሠፊ ራዕያቸውን በማስቀጠል ረገድ ቀጥለው የመጡ፥ መሪዎች ዳተኝነት ዐሳይተዋል።

የሚያሳዝነው ታሪኩ ለሁሉም የሚያኮራ ሆኖ ሳለ ጨርሶ አልተነገረም ቢባል ይቀላል። ጆርጅ ዋሺንግተን (1789 - 97)፣ ቶማስ ጀፈርሰን (1801 -1809)፣ አብርሀም ሊንከን (1861 -65) እና ጆን ፊትዝገራልድ ኬኔዲ (1961 - 63) በሚቀጥሉት የሀገረ አሜሪካ መሪዎች መሞገሣቸው ለአድናቂ መሪዎች ሞገሥ እንጂ ውርደት አልነበረም። ራሳቸውን በማድነቅና በማሥሞገሥ ተጠምደው 'የሚቀልሱ; የኢትዮጵያ መሪዎች ከዚህ ታላቅ ትምህርት መውሰድ ይኖርባቸዋል። 'የኋላው ከሌለ - የለም የፊቱ!' ካላከበርህ ዛሬም አትከበርም። ምን ጥሩ ብትሠራ አንተ ዛሬ አድንቀህ ያላቆየኸውን ማን ተከትሎህ ማሞገሥ ይችላል? ሁልጊዜም መሠረት ጣል።

የባህር ኃይል፦ ስኬት የሚጀምረው 'ይቻላል' ብሎ ከማቀድ ነው። የመይሣው አእምሮ እንበለ እረፍት ሽምጥ ከመጋለብ በገዛኖ አያውቅም። ሄነሪ ብላንክ የቴዎድሮስን የላቀ ፍላጎት ሲያስተነትን፦ "አፄው በማያጠራጥር መልክ አነስተኛ የባህር ኃይል ለማቋቋም ፍላጎት ነበራቸው። ህልማቸው እውን ሊሆን ይችል እንደሆን ሄርመገ ራሳምን ጠየቁት። ባህር ኃይላቸውን ለመመሥረት ያቀዱት ጣና ሐይቅ ላይ ነበር።" ትንታጉ አፄ አጠገባቸው ያለውን ሀብት አሟጥጠው ለመጠቀምና እንዳች ተአምር ለመፍጠር የማያመነቱ መሆናቸው እንዲህ ተፈትፍቶ ቀርቦለት አለውጥ የሚል የአእምሮ ሆድ ቢኖር - በእሠሥ ገሠሥ የተሞላ ከርሥ ነው ብለን ከማለፍ ሌላ ምን ማለት ይቻላል? ፀረ የባርያ ንግድ አቋም ላይ የነበራቸው ጅምር ላይደነቅ አይገባም።

ባሪያ ፍንገላ በኢትዮጵያም ሆነ በዓለም ታሪክ ውስጥ ረጂም ዘመን አስቆጥሯል። አሜሪካ ውስጥ እንኳ እስከ 1865 መቀጠሉን ዐይተናል። በተለያዩ ዓመታት የባሪያ ንግድን ለማስቀረት አዋጅ ቢወጣም ውስጥ ውስጡን ቀጥሏል። ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ "ዘመናዊ የኢትዮጵያ ታሪክ" በሚለው መፅሐፋቸው በኢትዮጵያ የባሪያ ንግድ እስከ 1930ዎቹ መቀጠሉን ሀሳይተዋል። ቴዎድሮስ የሀገር ውስጥ ባርነትን ለማስቆም ያደረጉት ጥረት ያልተገለፀ ቢሆንም፤ የባሪያ ንግድን ለማስቆም አዋጅ አውጥተው የነበራቸውን ፍላጎት አመላክተዋል። የማተሚያ ቤትም ውጥን ነበር። በምሥራቅ አፍሪካ የመጀመሪያው ማተሚያ ቤት የተቋቋመው በአፄ ቴዎድሮስ ዘመን ነው። አባ ሉሬንዞ ቢያንጄሪ የተባሉ ቄስ በአንቶኒዮ ዲ አባዲ ተቀርፀው የነበሩ ፊደሎችን



t.me/OLDBOOKSPDF

በመጠቀም የመጀመሪያውን የዕሀፊት መሣሪያ በምፅዋ በኩል በ1863 ይዘው ገብተዋል "የዳግማዊ ቴዎድሮስ አሳታሚ ነኝ" በማለት ይኩራሩ ነበር። (ከግል ማስታወሻ የተወሰደ።)

የመሬት አጠቃቀም፡- መሬት በኢትዮጵያ ህዝብ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ከንዋኔዎችና የትግል መነሻዎች ውስጥ የአንበሳውን ድርሻ ይዞ ዘልቋል። በየዘመኑ መላው ህዝብ የሚያተርፍበት ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል እንዲኖር ለማስቻል መሬት ላይ መሥራት አዋጪ ነው። ምንም እንኳ መሬት ላይ ያለው እውነታ ገለፃ አሻሚ ቢሆንም "ከሰሎሞናዊው ሥርወ መንግሥት" አንስቶ የመሬት ስሪት 'ሢሦ ለነጋሽ፣ ሢሦ ለቀዳሽ / አወዳሽ እና ሢሦ ለአራሽ' በሚል መርህ ይከናወን እንደነበረ መዛግብት ያስረዳሉ። ከመሬት ጋር ተያይዞ በርካታ አጠቃቀሞች ነበሩ። ይኸውም፡-

1) ርስት - የማይሸጥና የማይለወጥ በዘር ሐረግ የሚያዝ፣ ማህበረሰባዊ፣ በብዙ ሽንሽና ምክንያት የበሬ ግንባር ወደሚያህል ኩርማን መሬት በየጊዜው እያሽቆለቆለ የሚሄድ ነው።

2) ጉልት - በደመወዝ ምትክ የሚሰጥ የመሬት ይዞታ ሆኖ ባለ ጉልቱ በመሬቱ ላይ አንዳች መብት የማያገኝበት፣ ለመንግሥት አገልግሎት እስከሰጠ ጊዜ ብቻ ከአገልግሎቱ የመጠቀም መብት የሚያስገኝ፣ ጡረታ ሲወጣ መልሶ ለመንግሥት የሚያስረክበው የመሬት አገልግሎት ማግኛ መብት ነው።

3) ርስተ-ጉልት - በሂደት የጉልት መሬት ከነማእረጉ ለልጆች ጭምር ማውረስ የሚቻልበት የመሬት ይዞታ ሆኖ ተከስቷል። መሬት ላይ ለመቆጣጠር የሚሰየሙ ሹማምንት፡- ባላባት፣ ጭቃ ሹም፣ ምስለኔ፣ ተጠሪ (ቆሮ) እናገኛለን። ከመሬት በጉልት እና ርስተ ጉልት ተጠቃሚ የሚሆኑት መሣፍንት (ሲቪል አመራሮች) እና መኳንንት (የጦር አበጋዞች) እንዲሁም ለመንግሥት አገልግሎት የሚሰጡ ነበሩ።

አፄ ቴዎድሮስ ራዕያቸውን ለማሣካት ከመጠን በላይ መሬት 'ሰሞን ጉልት' አከማችታ ይዛ ወደነበረቺው ቤተ ክህነት ከማማተር ውጪ አማራጭ አልነበራቸውም። በጣት ከሚቆጠሩ ሽፍቶች ተነስተው 60,000 ሠራዊት የያዙት ቴዎድሮስ የገበሬው ወዳጅ እንደነበሩ ሁሉም ፀሐፍት ሊባል በሚችል ደረጃ ይስማሙበታል። ማርከስ "የኢትዮጵያ ታሪክ" በተሰኘው መፅሐፉ ከገፅ 64 - 65 'በመጀመሪያዎቹ ዓመታት በርህራሄ፣ በማህበራዊ ፍትህ፣ የደሀውን ህይወት በማሻሻል ረገድ እንቁ የተባሉ



t.me/OLDBOOKSPDF

ተግበራት ማከናወናቸውን' ፅፏል። ቴዎድሮስ በአንድ ቤተ ክርስቲያን የተከማቸው ኃይል አምራች አለመሆኑ የሀገርን እድገት ሰቅዞ ይዞ እንዳቀጨጨው በውል ተገንዝበው ነበር። በመሆኑም የማይደፈር ቦታ ይዞ ከቆየው ቤተ ክህነት ጋር ሊጋፈጡ የግድ ብሏቸዋል። ከዚህ አኳያ ሥር ነቀል እርምጃዎች ወሰዱ። ከእነዚህም መሀከል፡-

1) በአንድ ቤተ ክርስቲያን 2 ቀሳውስት እና 3 ዲያቆናት ለአገልግሎት በቂ መሆናቸውን ሌሎች አገልጋዮች ግን መሬት አርሰው በፈቃዳቸው እንዲያገለግሉ፤

2) የቤተ ክህነት 'ሰሞን ጉልት' ከግብር ክፍያ ነፃ መሆናቸው እንዲነሳ እና

3) መሬት ለገበሬው ማከፋፈል ይጠቀሳሉ። በዚህም የተነሳ "ስውር መሀዲ" (Hidden Mahdi) ተብለው መጠራታቸውን (ማርከስ፡- ገፅ 64)

ዐፄ ቴዎድሮስ ለመጀመሪያ ጊዜ "መሬት ለአራሹ/ Land to the Tiller" የሚል መፈክር ቤተ መንግሥት ውስጥ ያነሱ ፈር ቀዳጅ ናቸው። የኢትዮጵያ ተማሪዎች ትግል "መሬት ለአራሹ" በሚል መፈክር እንግቦ ሲነሳ "ዳግማዊ ቴዎድሮስ" የጥቅሱ መጨረሻ አድርጎ ቢጨምር እንዴት ያምር ነበር! ይህ እርምጃቸው ግን በዘመኑ ከነበረው አስተሳሰብ አንፃር 'አዲስ ወይንጠጅ በአሮጌ አቁማዳ የማኖር' ያህል ነበርና ዋጋ አስከፍሏቸዋል።

የጋብቻ ሥርአት፡- ነገሥታቱ የተለያዩ ሚስቶችን (ቀዳሚ ንግሥት- በወርቅ ወንበር ላይ የምትቀመጥ፣ የቀኝ ንግሥት- በብር ወንበር ላይ የምትቀመጥ፣ የግራ ንግሥት - በነሐስ ወንበር ላይ የምትቀመጥ፣ የተመረጡ ቅምጦች - በእንጨት ላይ የሚቀመጡ እና የ'ጭን ገረድ') የመያዝ' ከእስራኤል ነገሥታት የተወረሰ 'ሰሎሞናዊ ልምድ' እንደነበራቸው ይነገራል። ይህም ንጉሡ ነገሥቱ ሲሞት 'እኔ ልንገሥ - የእኔ ይንገሥ' ግጭት እና የእርስ በርስ ጦርነት ምንጭ በመሆኑና ኢሀይማኖታዊ ስለነበር ቴዎድሮስ ራሳቸው እቴጌ ተዋበችን በቁርባን አግብተው በአንድ የመወሰን እርምጃ ወስደዋል። እርምጃው ለህዝቡ ሥነምግባር ጭምር አርአያነት ያለው ነበር። የአለባበስ ሥርአት፡- ልውላን የቀሚስ አይነት ዘርፋፋ ካባ ለብሰው እንዲዋቡ የሚያስገድደውን ደንብ አስቀርተዋል። ሥርአት ያለው አለባበስ መከተል በቂ እንደሆነ የሚያሳስብ ማሻሻያ አድርገዋል።



t.me/OLDBOOKSPDF

ከዚህም ሌላ የመፃሕፍት ትርጓሜን በተመለከተ በግዕዝ ቋንቋ ብቻ ተፅፈው የሚገኙ መፃሕፍት ለህዝቡ ግልፅና ተደራሽ ባለመሆናቸው በሰፋት የማህበረሰቡ መግባቢያ በሆነው የአማርኛ ቋንቋ እንዲተረጎሙ አድርገዋል። ለአብነት መፅሐፍ ቅዱስን በተሻለ ደረጃ መረዳት እንዲችሉ ለራሳቸው አገልግሎት የማቴዎስ ወንጌልንና የማርቆስ ወንጌልን አስተርጉመዋል። የደብዳቤ ልውውጥ ቀደም ብሎ በቃል ብቻ ይተላለፍ የነበረው የመልእክት ሂደት ቀርቶ መደበኛ የደብዳቤ ልውውጥ እንዲጀመር በር ከፍተዋል።

ቤተ መፃሕፍት ቀደም ብሎ በጎንደር ዘመነ መንግሥት በአፄ ፋሲል በግሩም ሁኔታ ተጀምሮ በዘመነ መሣፍንት የተቋረጠውን በአዲስ መልክ እንዲያንሰራራ መንፈሳዊ እና ተጓዳኝ መፃሕፍትን ከየሥፍራው በማሰባሰብ ድርሳናቱ በመድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን ግቢ በተሠራ ታላቅ ቤተመፃሕፍት እንዲሰደሩ አድርገዋል። ቴዎድሮስ ያሰባሰቧቸው አብዛኞቹ መፃሕፍት የሮበርት ናፒየር ዘመቻን ተከትሎ (ኤፕሪል 1868) ተዘርፈዋል።

በዚያ የሩቅ ዘመን፡- ዘመናዊ ትምህርት ባልተጀመረበት፣ ለመረጃ ልውውጥ አመቺ ባልሆነበት፣ በጦርነት ይታመሥ በነበረው የዘመነ መሣፍንት ድብብ ውስጥ በአመለካከት ልቀው በመውጣት ወደ ሃያ የሚጠጉ ታላላቅ ስኬቶችን ያስመዘገቡ መሪ በሌላው ዓለም ቢገኙ ታሪካቸው የፊልም ኢንዱስትሪውን በተቆጣጠረ፣ ትውልዱ በታሪኩ ኮርቶ የሀገር ፍቅሩ በዳበረ፣ አብዝቶ ባተረፈ ነበር።

ተዐምር የሚያስብሉ እነዚህ ስኬቶች ግን በረቀቀ ተንኮል ትቢያ እንዲሸፍናቸው ተደርጓል። በወናና ግልብ አእምሮ 'ኪነት እንዳገነናቸው' አስመስለው የሚፅፉ ካድሬዎችም ተስተውለዋል። ሠርቶ በማሳየት ሳይሆን ሀገር እነገደሉ 'እኔ የተሻልኩ ነኝ' ለማለት ኃያላኑን ለማራከሥና የተጉ እኩይ ምግባራቸው ነገ ሊያዋርዳቸው ታሪክ ሲተናነቃቸው ታይቷል። አሳ አንበሪ የሚያካክሉ ብርታቶችን ደብቆ፤ ቁጫጭ የሚያህሉ ድክመቶችን በባትሪ ብርሀን እየፈለጉ ማጉላት ለትውልድም ሥልጣን ላይ ላለ መሪም አይጠቅሙም። ለጥላቻ ፍጅታ ታሪክን በከፋ ከማራገብ ተላቅቀን ለተሻለ መግባባት በር መክፈት ሀገር ያረጋጋል። የመሪን ወንበር ያረጋል፣ ያፀናል። ስለአፄ ቴዎድሮስ ልእለ ሰብእና በስሜት ሳይሆን በስሌት፣ በመሠለኝና ደሳለኝ ሳይሆን በተገቢ የታሪክ ፍተሻ ላይ ተመሥርተው ከፃፉ ምሁራን ሥራ ውስጥ ቃል በቃል የጻፉላቸውንና ያወሱትን አቋድሰን እናጠቃልል፡-



t.me/OLDBOOKSPDF

ፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ፡- "... A giant ahead of his time/ ከዘመናቸው የቀደሙ ታላቅ" ሲሏቸው፤

ፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት፡- "... Tewodros as a totally nevertheless stands out as something different and special - a giant in Ethiopia's age - old history / ምንም ይሁን ምን ቴዎድሮስ ልዩ እና አፁብ ድንቅ በኢትዮጵያ የረጅም ዘመን ታሪክ ግዙፍ፤

ፕሮፌሰር ገብሩ ታረቀ፡- "ከቴዎድሮስ እስከ መለስ ባወዳድር ቴዎድሮስ ንዑድ ናቸው።"

ፕሮፌሰር ሺፈራው በቀለ፡- "... Tewodros was one of the towering figures in the 19th century Ethiopia ... a turning point in the history of the country/ በ19ኛው ክፍለ ዘመን በከፍታው ማማ ላይ ከምናገኛቸው መሪዎች አንዱ ... በሀገሪቱ ታሪክ የአዲስ ምዕራፍ ከፋች ይሏቸዋል።

በአፄ ቴዎድሮስ ዘመን ዙሪያ የተደጎሱ መፃሕፍት ያለልዩነት የቴዎድሮስን መንትያ መዳረሻዎች፡- ዘመናዊነት እና አንድነት ገልፀዋል። አፄ ቴዎድሮስ በመጨረሻው ቀናቸው በሥራ ቁጥር ለሚርመሠመሠው በብሪታኒያው ናፒየር ለሚመራው ሠራዊት እጅ ሲሠጡ ቅንጣት ፍላጎት አልነበራቸውም። ቀኝ ከንዳቸው ገብርዬ ኤሮጌ ላይ 'ኤፕሪል' 10, 1868 ተፋልሞ ሲሠዋ ማብቂያቸው መድረሱን አመኑ። ጉዳዩን በሰላማዊ መንገድ ለመጨረስ በእጃቸው የነበሩ አውሮፓውያንን ከእሥር ፈትተው ከሥላሳ በቅሎ ስጦታ ጋር ላኳቸው። እንግሊዞቹ ግን እጃቸውን እንዲሰጡ ጠየቋቸው። የዐይን እማኝ ብሪቶኖች እንዳረጋገጡት እጅ እንዲሠጡ የተለያዩ ሙከራዎች አደረጉ። ቴዎድሮስ ግን ከብሪታንያ በስጦታ በተበረከተላቸው ሽጉጥ አንድያ ሀይወታቸውን በራሳቸው እጅ ቀጠፏትና መቅደላ አፋፍ ላይ በክብር ወደቁ። "Tewodros committed suicide on 13 April, 1868"

('አፄ ቴዎድሮስ ራሳቸውን አሳጠፉም ሴት ናት ያጠፋቻቸው' የሚሉ ደካሞች ተረት ለአቅመ ክርክር ስለማይበቃ እዚሁ መልስ ሰጥተነው እንለፍ። ሲጀመር ለሴት ያላትሁን ተራ ንቀት ተዉት። ሲቀጥል የብሪታንያ ጦር ኤፕሪል 10 ከመቅደላ ተራራ ግርጌ ከሦስት ቀናት በፊት ከናፒየር ሲዋጋ ያቺ ሴት የት ነበረች? ሲሠልስ የተባለቺው



t.me/OLDBOOKSPDF

ሴት ጭልፊት ናት ወይስ የጦስ ዶሮ ከረብታ ላይ ሮጣ የምትወጣ? *ታሪክ ጣላ በሴት ተቃምጦ በጥላቻ ስካር የሚደረስ ልበለድ ሳይሆን በማስረጃ ላይ ተመስርቶ የሚነገር እውነታ ነው። ለማንኛውም ቴዎድሮስ ከብሪታኒያውያኑ ጋር ለመዋጋት ሲባስቶፖልን ሲሞክሩት ለገመ። (ሀሮልድ ማርከስ፡- "የኢትዮጵያ ታሪክ" ገፅ 72) ላይ 'ራሳቸውን አጠፉ።' በማለት እውነታውን አስቀምጦታል። የቴዎድሮስን ባለ ብዙ ፈርጅ ገበር ጠበብት በቀለማቸው ንድፍ ሊያኖሩት ሞክረዋል። ሙዚቀኞች በዝማሬ አሸብሸበውላቸዋል። ጀግኖች ስማቸውን እየጠሩ ወኔያቸውን ሊላበሱ አንጎራጉረውላቸዋል። ቀራጊዎች ሐውልት አቁመውላቸዋል። ስታላቁ ቴዎድሮስ ከብር የተፃፉ መፃሕፍት በቂ ናቸው ብለን አንወስድም። የራሳችንን 'ኢትዮውድ' አስከናቋቋም ድረስ 'ሆሊውድ' ጎራ ብሎ የመቅደላን ገቢር የሚያስተነትን ጀግና ኢትዮጵያ ትጣራለች።

መዝጊያ፡- በወቅቱ ከተደረደሩ ስንኞች ሁለቱ፡-

"ጥይት ስለ ውሀ ማነው የሚጠጣ?

ቴዎድሮስ ብቻ ነው ጥሙን የሚወጣ"

በተለይም የአምበው ፈርጥ ባለ ቅኔ ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን (ጠቢባን ብቻ ጥበብን ያዩልና፤ ገልቱዎችም ከአፍ እስከፍንጫ) የኛ የጥበብ ሰው በፀጋቸው ለቴዎድሮስ የልቢን ቢገልፅልኝ ብለው ያኖሩትን ግጥም እንውሰድ።

**የቴዎድሮስ ስንብት ከመቅደላ**

ተስፋ ባጣ ምድረ በዳ

ያንድ እውነት ይሆናል እዳ

እና ትንፋሽም ሆኜብሽ መራር መከሬ

"ሩቅ አሳቢ ቅርብ አዳሪ፣"

እውነት ላንቺ ተስፋ ናት ጉስቁል ልሳንሽን ነከሳሽ

ከንድሽን ካዘለ ቅርሰሽ መጠላለፍ ሲሆን እጣሽ



t.me/OLDBOOKSPDF

ከእንግሊዝ የሞት አማልክት መተናነቅ ሲሆን ድርሻሽ
መልመጥመጡ፣ መሽቆጥቆጡ ድንገት የሚያቀጣሽ
የኔ እውነት ሆነብሽ ዕዳሽ።
ወራሪም ፈጣሪን ላያቅ
የጣለውን በስሏል እንጂ ወድቋል ብሎ ግፉ ላያልቅ
መች ትተርፊያለሽ ኢትዮጵያ ሕዋስሽ አብሮኝ ካልሠራ
አንገትሽ ብቻ መቅደላ አፋፍ ወጥታ ብታበራ
የቀረው ሠራ አካላትሽ በየጥሻው ተዘርሮ
ከአባት በወረስሽው ንፍገት ኑብዞ ደንዝዞ ተቀብሮ
ባጉል ወጌሻ ታጅሎ
እጅና እግርሽ ታሽቶ ዝሎ
እኔን ለጥንብ አንሳ ጥሎ፤
ከደቀቀ ከደከመ ከንድሽ አልነሣ ካለ
ሞት እንጂ ለኔስ ምንአለ?
ሆኖም ጎስቋላ አልምሰልሽ የሚያዝንልኝ አልፈልግም
ጠላትሽን በከንድሽ እንጂ በእንባሽ ወዝ ባላሸንፍም
የልቤን ፍቅር በስተቀር አማወርስሽም ውል የለኝ
የኮሶ ሻጭ ልጅ ደሃ ነኝ።
ደሞም ያላንች የለኝና



t.me/OLDBOOKSPDF

ድሊም የተሰፋ ጎሕ ባይሆን ከሞት ጋር ትግል ነውና
ከዚህ ሌላ ትእዝብት ውረሽ ሳይነጋ እንዳስመሸሽብኝ
ጊዜና ትውልድ ይፍረደን ሳልነቃ እንዳስረፈድሽብኝ።
ያም ሆኖ ለራስሽ እንጂ ለኔ ከቶም አታልቅሺ
አንቺ ነሽ እንባ እምትሺ፤
የእምነትሽ መተሳሠሪያ፤ ውልሽ ለተላቀቀብሽ
ላንቺ ነው እንባ እሚናስፈልግሽ።
አዎ ይኸን እወቁልኝ ምስክር ሁኑኝ ሰማዕታት
ለሷ ነው እንባ እሚያስፈልጋት።
ከጠላቶቼ ጭብጥ ውስጥ ትንፋሼን በጄ ስነጥቃት
ሞቴን ከመንጋጋቸው ውስጥ መንጭቄ እኔው ስሞታት
ላገሬ ብድር ልከፍላት
የነፈገቺኝን ፍቅር በራሴ ሞት ልለግሳት
ዳግም ከሞቴ ባንኜ በመንፈስ ጣር ስሞግታት!
ያኔ ነው እንባዋ የሚያጥራት።
ስለዚህ ለራስሽ እንጂ ልቅሶሽ ለኔ ምን ሊረባ
ብቸኛ ምሬት ነው ኃይሉ፣ ወኔ መስለቢያው ነው እንባ።
እና ለራስሽ አዘኚ
እንጂ ለኔ ከቶ አትባከኚ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ይልቅስ ተረት ልንገርሽ፣ የተላከ ከእንግሊዝ ዘንድ
እጅህን ስጥ አለኝ ፈረንጅ እጅ ተይዞ ሊወሰድ
ምን እጅ አለው የእሳት ሰደድ?
አያውቅም ከንዴ እንደሚያነድ።
ዳዊት እንዲያ በበገናው፣ ማልቀስ ማላዘን መያዙ
ይኸ የጎልያድ ውላጅ፣ ቢበዛበት ነው መዘዙ
ምንጩ እንደ አሸን፣ እየፈላ አገር ምድሩን ማንቀዙ
ቸግሮት ነው፣ መጋፈጡ፣ ከስንቱ መወናጨፉ
በባላንጣው ሳቢያ ምክንያት፣ የራሱን ወገን ማርገፉ።
ታዲያ እንግዲህ አንቺ ኢትዮጵያ፣ እኛስ ልጆችሽ፣ ምንድነን
አመንኩሽ ማለት የማንችል ፍቅራችን የሚያስነውረን
ዕዳችን የሚያስፎክረን
ግፋችን የሚያስከብረን
ቅንነት የሚያሳፍረን ቂማችን የሚያስደስተን
ኧረ ምንድነን? ምንድነን?
አሚከላ እሚያብብብን
ፍግ እሚለመልምብን፣
ከአረም ጋር ያፈራን ጊንጦች ከእንክርዳድ ያልተለየን ዘር
ግርዱን ከምርቱ ተማጥቆ፣ ከቶ ያልተበራየን መከር



t.me/OLDBOOKSPDF

ምንድነን? ምንድነን እኮ?

አረጋዊውን ባንቀልባ፣ ከምንሸከም እንኮኮ

ጎልማሳውን ከወኔ ጣር፣ ካልፈታን ከፍርሀት ምርኮ

እንደወዶ ገባ ወደል፣ መጠለሉን ከሰነት ቃኮ

ካቃተን ምንድነን እኮ?

አየሽ አንቺ እማማ ኢትዮጵያ አየሽ አንቺ እናት ዓለም

ቃል የእምነት እዳ ነው እንጂ፣ ያባት የናት እኮ አይደለም።

ያም ይቅርና መርዶ ላርዳሽ፣ ስሚው እኔ እንደሰማሁት

እርም በልተሽ ከምትቀሪ ስሚ ገብርዬንም ጣሉት።

እስቲ እንግዲህ በይ ፍረጂኝ፣ ከእንግዲህ እኔ ፍሬ ዐላይም?

"ዘርቶ መቃም ወልዶ መሳም"

አባባል ለኔ አይባልም?

እስቲ ገብርዬን መሰል ዘር፣ ፍሬው ከቶ አይለመልምም?

እኔስ ዘር ዘራሁ አልልም?

ምነው ፍንጭትህን ገብርዬ፣ ያን ፍንጭትህን አጨለሙት

እንደሬት ልግ አከሰሉት

እንደኮሶ አስመረሩት?

ከጡቶችሽ እቅፍ ነጥቀው፣ ከማህፀንሽ ፍቅር ቆርጠው

እውነትን ሲገሉ እንዲህ ነው፣ ፈገግታውን አጨልመው።



t.me/OLDBOOKSPDF

እስቲ አባከህን ገብርዬ የዛሬን እንኳ ስቀህ ሙት

በዕድል ጥቀርሻ እንዳጀሉት

እንደወላድ ጣውንት ጡት

አርማ ጉሳ እንዳቀለሙት

ፈገግታህን አያጥቁሩት።

እምቢ በላቸው ገብርዬ፣ በአባት ሴራ እንዳስገዘቱት

በመሀላ እንዳሳገዱት

የነፍስህን ጮራ ብርሀን፣ ከገፅህ እንደቀበሩት

ዘለዓለም ሳያጨልሙት

ወንድምዬ እምቢ በላቸው፣ የዛሬ እንኳ ስቀህ ሙት።

ያለፈ ጥረታችንን፣ ሳስታምመው ትዝ ሲለኝ

ከሞከርነው ነገር ይልቅ፣ ያልሞከርነው ነው እሚቆጨኝ።

እና በኔ ይሁንብህ፣ መጣሁ ተቀበለኝ፤

እኔም ላዋይህ እድምጠኝ

እጅህን ስጥ አለኝ ፈረንጅ፣ እጅ ተይዞ ሊወሰድ

ምን እጅ አለው የእሳት ሰደድ?

አያውቅም ከንዴ እንደሚያነድ?

ፀጋዬ ገብረመድኅን

"እሳት ወይ አበባ" (ከገፅ 204 - 208)



t.me/OLDBOOKSPDF

## ዐፄ ዮሐንስ ዐራተኛ (1872 - 1889)

ከ1868 - 1871 የአፄ ቴዎድሮስን ሞት ተከትለው ጳጳስ ከእስክንድርያ ሳያስመጡ በእጨጌው እጅ ራሳቸውን ንጉሠ ነገሥት በማለት የሰየሙት አፄ ተክለጊዮርጊስ፤ እንዳች የተመዘገበላቸው ታሪክ ሳይኖር በ1871 አሰም ጦርነት ላይ በትግራዩ ካሳ ምርጫ (በዝብዝ ካሳ) ተሸነፉ። ካሳ ምርጫ ለስድስት ወራት ያህል የሁኔታዎችን አካሄድ ከገመገሙ በኋላ በ1872 በትረ መንግሥቱን አፄ ዮሐንስ አራተኛ ተሸኝተው በአክሱም ጽዮን ማርያም ንግሥና ተቀበሉ። ወደ ሥልጣን የመጡበት ወቅት ከምንጊዜውም በላይ ኢትዮጵያ በሦስት አቅጣጫ የተወጠረቺበት ነበር። በሰሜን አቅጣጫ በቅደም ተከተል ግብፅና ጣልያን፤ በስተምዕራብ አቅጣጫ ደግሞ መሀዲስት ሱዳን ኢትዮጵያ ላይ ወረራ የፈፀሙበት ጊዜ ነው።

አፄ ዮሐንስ በ1875 ግብፆችን ጉንዲት ላይ እና በ1876 ጉራ ላይ በአስደናቂ ጦብብ ድል አድርገዋል። ይሁንና እንደ ታሪክ ምሁራን ከሆነ ድሉ የተሟላ አይደለም። ምክንያቱ ደግሞ ከ1876 - 1885 ባሉት አሥር ዓመታት ግብፅን ከያዘቻቸው የኢትዮጵያ ግዛቶች ለማስወጣት ቅንጣት ሙከራ ባለማድረጋቸው ነው። ሌላው ቀርቶ ዋናዋ ወደብ ምፅዋ ጭምር በግብፆች እጅ ቆይታለች። (ዳህላክ ላይ ከሚገኙ ደሴቶች ዋነኞቹ የሚከተሉት ናቸው። ሓራት ደሴት፣ ደሂ ደሴት፣ ኖራን ደሴት፣ ደር ኤት ቱን ደሴት፣ ሬጊአማ ደሴት፣ ቶሪ ደሴት፣ ኡም አን ኤም ደሴት፣ አንጋል እና ምፅዋ)

አፄ ዮሐንስ አራተኛ ጠላት ኢትዮጵያን በወረረበት ወቅት ለችግሮቹ ዲፕሎማሲያዊ ጥረት በማድረግ ብቻ ሳይወሰኑ ለከተት ዘመቻ ትውልድ ተሻጋሪ የሆነ መልዕክት ያዘለ ንግግር አድርገው ነበር። ይኸውም፦

> *የኢትዮጵያ ልጅ ሆይ ልብ አድርገህ ተመልከት። ኢትዮጵያ የተባለችው ሀገር አንደኛ እናትህ፣ ሁለተኛ ሚስትህ፣ ሦስተኛ ልጅህ፣ አራተኛ መቃብርህ፣ አምስተኛም ዘውድህ ናት። እንግዲህ የእናት ፍቅር፣ የሚስት ደግነት፣ የልጅ ደስታ፣ የመቃብር አቃፊነት (ካባቲነት) እና የዘውድ ፍቅር ምን ያህል እንደሆነ አውቀህ ተከተለኝ።*







t.me/OLDBOOKSPDF

ለአዋጁ ኢትዮጵያውያን የሠጡት ምላሽ ከውስጥ የመነጨ ነበር። በ10ሺህዎች የሚቆጠር ሠራዊት በሆታ ተከተላቸው። ይሁንና ጣሊያን ምሽግ ቆፍሮ ከተቀበረበት አልወጣ በማለት ስላስቸገረ ለአንድ ወር በሙሉ በርቀት ሆነው ከመቃኘት ውጭ ለጦርነት ምቹ ሁኔታ ያገኙ አይመስልም። በጣልቃው የኤርትራ አስተዳዳሪ እና የአፄ ዮሐንስ የጦር መሪ የነበረው አሉላ እንግዳ (አባ ነጋ) በርቀት ቅኝት ሲያደርግ ምሽግ ሊያጠናከር የተላከውን 500 የጣሊያን ጦር በ1887 ዶጋሊ ላይ ሙሉ በሙሉ ደምስሷል። የሚደንቀው ግጥጥም ከድሉ 12 ዓመታት በፊት አሩሮች በስዊዝ ጀርመናዊው ቨርነር ሙንዚንገር የሚመራውን 500 የግብፅ ጦር (1875) ለወሬ ነጋሪ ሳያስተርፉ ማውደማቸው ነው።

ከጣሊያን ጋር ያለውን ጦርነት እርግፍ አድርገው ትተው ስለምን ወደ ጎጃምና መሀዲስቶች ዞሩ? (በምዕራፍ አራት ሰፋ አድርገን ዕናየዋለን) አፄ ዮሐንስ አስተዳደራዊ መርሆ አድርገው የያዟቸው ሁለት መንትያ መተከሎች ነበሩ፤ የመጀመሪያው የዮሐንስን የንጉሠ ነገሥትነት ደረጃ ተቀብለው ግብር መክፈል፤ ሁለተኛው በሀገሪቱ አንድ አይነት ሀይማኖት (ክርስትና) ብቻ እንዲኖር እና በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በዘመነ መሣፍንት ተባብሶ የነበረው የተዋህዶ፤ የፀጋ ልጅ እና የቅባት ክፍፍል ጠፍቶ ተዋህዶ ብቻ እንድትፀና ነው።

ከዚህ አንፃር ለእስልምና ሀይማኖት እንዲሁም በክርስትና ውስጥ በስነመለኮት ለልዩነት አራማጆች (ቅባት፣ የፀጋ ልጅ እና ሦስት ልደት) እምነቶች ምህረት የለሽ ነበሩ። አፄ ዮሐንስ ግብሯችን ከያዟቸው የኢትዮጵያ ግዛቶች ለማስለቀቅ በተከተሉት እጅግ በጣም የተሣሣተ አቅጣጫ ሳቢያ መሀዲስቶች ለብቀላ በመነሣታቸው መተማ ጦርነት ላይ (1889) ሀይወታቸውን አጥተዋል። በየትኛውም አውድ ቢነፃሩ የአፄ ቴዎድሮስን የ13 ዓመታት የሥልጣን ቆይታ ከአፄ ዮሐንስ የ20 ዓመታት አስተዳደር ጋር ማነፃፀር እጅግ በጣም አዳጋች ነው። (ይህኛውንም በምዕራፍ አራት እንቃኘው።)



t.me/OLDBOOKSPDF

## የአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት (1889 -1913/1911)

ወያኔ የአፄ ምኒልክን ታሪክ በማጠልሸት ረገድ ከ (1991 - 2018) ኢትዮጵያን ለማፍረስ ያባከነችው ገንዘብ፣ ጊዜና አእምሮ ከጥፋት ጎዳና መልሰን ለሰውጥ ቢውል ኖሮ የኢትዮጵያን እድገት ምን ያህል ያስወነጭፍ እንደነበረ ሲታሰብ በጣም ያስቆጫል። በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ እንደ አፄ ምኒልክ የአመራር ዓመታት አከራካሪ የለም። (መግቱን በከፊል ለምዕራፍ አራት አቆይተን፤ የደማቅ ታሪካችንን ለበጎ እንቃኝ።) አፄ ምኒልክ በአፄ ቴዎድሮስ ተማርከው ከ1856 - 1865 የቆዩበትን አመራር በቅርበት መከታተላቸው እና የዮሐንስ አራተኛን አመራር መታዘባቸው ድክመቶችን አስወግደው ጥንካሬዎችን አጎልብተው እስከ ህይወታቸው ፍፃሜ በአብዛኞቹ አካባቢዎች "እምዬ ምኒልክ" እየተባሉ እንዲጠሩ አስቻይ ሁኔታ ፈጥሮላቸዋል።

### ከአፄ ምኒልክ ከንውኖች

### በከፊል የተበታተኑ ማህበረሰቦችን ማሰባሰብ

፩ የሸዋ ንጉሥ ሣሉ (1880ዎቹ መጀመሪያ እስከ 1889):- "አባት እሆንሀለሁ ልጅ ትሆነኛለህ። ጠላት ዙሪያችንን ከብቦናል። አንድነታችንን እናጠንክር። ሠራዊቴ ኃያል ለሆነ ብትገጥመኝ ወገን ታጨራርሳለህ። በሰላም ለእኔ አድረህ ገብር። ራስህን በራስህ ታስተዳድራለህ፤ በውስጥህ ጉዳይ ጣልቃ አልገባም።" መልእክት በአዋጅ ነጋሪ እያስነገሩ ስትጠብ እና ስትሰፋ የነበረቺውን ታላቅ ሀገር (መገመት የማይቻል የቆዳ ስፋትና በ1,000 የሚቆጠር የተጠናከረ ማህበረሰብ) ከአሥር ባነሰ ሥፍራ ብቻ ተጋጭተው ዛሬ ከ2016 - 19 ባለው ጊዜ እንኳን ማስፈን ያልተቻለ የተረጋጋ ሰላም ፈጠሩ። ለአንዳንድ ማህበረሰቦች ነፃ አውጪ ጭምር ነበሩ።

በ1880ዎቹ መጀመሪያ የራስ ጎበና ዳጬ በደጃዝማች ደረሱ የሚመራውን የጎጃም ጦር ጎጃምን ሊሙ ላይ መታ። በመቀጠልም የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ እና የጎጃሙ ንጉሥ ተክለሀይማኖት እምባቦ ጦርነት ላይ ተዋግተው ንጉሥ ተክለሀይማኖት ቆስለው ተያዙ። የጎጃም ጦር ከፉኛ ተጎድቶ ነበር። እንደ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ "Modern History of Ethiopia, 1855 - 1991" ገፅ 62 :- "ከ1882 - 1886 የኦሮሞ ግዛቶች በሰላማዊ መንገድ የምኒልክ የጦር መሪ ለሆኑት ራስ ጎበና ዳጬ እጅ ሰጡ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ከእነዚህም መሀከል እስከ መጨረሻው የምኒልክ ቀኝ እጅ የነበሩት የሊቃ ለቀምት ደጃዝማች ኩምሳ ሞሮዳ (ገብረ እግዚአብሔር)፤ የሊቃ ቄለም ደጃዝማች ጆቴ ቱሉ፤ የጂማው ዳግማዊ አባ ጂፋር በዋናነት ይጠቀሳሉ። (ከጎጃም አምባቦ፣ ሰልጢ፣ አርሲ አኖሌ እና ሐረሬ ጨለንቆ በስተቀር የሸዋ ንጉሥ በነበሩበት ወቅት ያለ ግጭት እጅግ በጣም ሠፊ የምዕራብ ደቡብ እና ምሥራቅ አካባቢዎች መልሰው ማሰባሰብ ቻሉ። በነዚህ ጦርነቶች ጎጃም ጎንደር እና ወሎ በአፄ ዮሐንስ አራተኛ ሥር ስለነበሩ አልተሳተፉም። ዋነኛ ተዋናዮቹ ሸዋ፣ ጊቤ፣ ሊቃዎች እና "የደቡባዊ አካባቢዎች" አስተዳደሮች ነበሩ።) ጳውሎስ ኞኞ "አጤ ምኒልክ" በተሰኘው መፅሐፋቸው ገፅ 26 ላይ የሚከተለው ይነበባል።

ምኒልክ የኦሮሞ ተወላጅ የሆኑትን 'ራስ' ጎበናንና ሌሎቹንም ረዳቶቻቸውን አማከረው ... የተነሱበት አንዱ ምክንያት ኢትዮጵያን ዙርያዋን የከበቧት ቅኝ ገዢዎች ለእያንዳንዱ ባላባቶች ስጦታ በመስጠትና በማባበል የኢትዮጵያን ግዛት እየቆረሱ ወደ ራሳቸው ቅኝ ግዛትነት ይደባልቁ ስለነበር እነኚያን ቅኝ ገዢዎች ለማቆም ነበር።

ሲሉ ይገልፃሉ። ከዚሁ ጋር አብዛኛውን የኢትዮጵያ ክፍል በሰላም ስለመያዛቸው ገፅ 30 ላይ ያኖሩት ሀሳብ በሚከተለው አኳኋን የተሰናዳ ነበር።

> *ንጉሥ ምኒልክ በ1878 ጎበና ዳጬን ወደ ወለጋ ልከው ከኩምሳ ጋር እንዲነጋገሩ አደረጉ። ጎበናም የምኒልክን ሀሳብ ለኩምሳ ሲናገሩ "በሰላምና በፍቅር ብትገቡ መሬት የናንተ ነው። በወለጋም ከኩምሳ በላይ የሚሾም ሰው የለም። አገሩንም የምታስተዳድረውና የምታስገብረው አንተው ባላባቱ ኩምሣ ነህ። ለምኒልክ መገዛትህን የምታስታውቅበት በዓመቱ ለምኒልክ ትገብራለህ። ከዚህ በተረፈ በበላይነት እንጂ በውስጥ ግዛታችሁ አንገባም' ብለው በዚህ ከተስማሙ በኋላ ባላባቱ ኩምሳ ገቡ። ... ከዚያም በኋላ የደጃዝማችነት ማዕረግ ሰጥተው የወለጋ ገዢ ብለው ሾሙዋቸው።*

ምኒልክ በመላው ኢትዮጵያ ባደረጉት መልሶ የማዋሀድ ሂደት የተከተሉት መንገድ ይኸው ነው። ሆኖም ለመሰባሰብ ፈቃደኛ የማይሆኑ አካባቢዎች ሲኖሩ ወደ ግጭት መግባቱ አልቀረም። በመሆኑም ከላይ ከጠቀስናቸው ቦታዎች በስተቀር እጅግ በርካታ የሆነውን የኢትዮጵያን ማህበረሰብ በአመዛኙ በአንድ ጥላ ስር ለማሰባሰብ አስችሏቸዋል።



t.me/OLDBOOKSPDF

አፄ ዮሐንስን ተከተው የኢትዮጵያ አፄ ከሆኑበት እስከ አድዋ ጦርነት (1889 - 1896)፡- በዚህ ወቅት ከወላይታው ንጉሥ (ካዎ) ጦና (1894) በስተቀር ደም መፋሰስ ሳይኖር ሠፊ ሥፍራዎችን በሰላም ተቆጣጥረዋል። የተለየ ዓላማው ለአድዋው ጦርነት ሠፊ የሰው ሀይል ማደራጀት ነበር።

ከአድዋ ጦርነት በኋላ (1896 - 1900) በኢትዮጵያና አጎራባች ቅኝ ገዢዎች ጋር ለሚደረገው የድንበር ማካለል ወገኖቻችን ወደ ሌላ ሀገር እንዳይወሰዱ ለማመቻቸት አሰብ በረና እና የሶማሊ ጠረፍ አካባቢዎችን ወደ እናት ሀገራቸው አሰባስበዋል። ምኒልክ በዚያ ትራንስፖርት ባልነበረበት ዘመን ኢትዮጵያውያንን ባያስተባብሩ ምን ሊፈጠር ይችል ነበር? (በምዕራፍ አራት እንዳስሰዋለን።)

አንፀባራቂው የአድዋ ድል ካስገኛቸው ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ውጤቶች መሀከል ተጠቃሾቹ በአጭር መግለጫ የሚከተሉት ነበሩ፡- የውጫሌ ውል መሠረዝ፣ የአዲስ አበባ ስምምነት ከጣሊያን ጋር መፈረም (1896) - ጣሊያን የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት መቀበሏና በተመሳሳይ ዓመት የመጀመሪያውን ቆንስላ በአዲስ አበባ መክፈቷ፣ ፈረንሳይና ብሪታኒያ (1907)፣ አሜሪካ (1903)፣ ጀርመን (1905) ኤምባሲ መክፈታቸው፣ 1900 የመጀመሪያው የፓን አፍሪካኒዝም እንቅስቃሴ በመላው ዓለም ጥቁሮች መጀመር፣ የደቡብ አፍሪካ ሀገሮች ኢትዮጵያኒዝም እንቅስቃሴ (ወደ አፍሪካ እንመለስ ንቅናቄ)፣ የኔግሪቲዩድ 'ጥቁረት - ውበት' መነሳሳት፣ የኢትዮጵያ ሊግ ኦቭ ኔሽንስ 1923 መሣተፍ ቀጥተኛ ውጤቶች ሲሆኑ፣ የኢትዮጵያ የአፍሪካ ህብረት እናትነትና የአዲስ አበባ ከአራቱ ዓለማቀፍ የዲፕሎማቲክ መናኸሪያዎች አንዷ መሆኗ ተዘዋዋሪ ውጤቶች ናቸው።

አፄ ምኒልክ በአድዋ ላይ ያስመዘገቡትን ደማቅ ገድል ተከትሎ በዓለማቀፍ ደረጃ የነበረውን ድባብ አስመልክቶ ንጉሤ አየለ ተካ፡-

**"ታላቁ ጥቁር**

**ኢትዮ አሜሪካ**

**ዘዳግማዊ ምኒልክ"**



t.me/OLDBOOKSPDF

በሚል ርዕስ በማስረጃዎች አስደግፎ ለኅትመት ካበቃው ሥራው፣ ገፅ 90 - 91 የሚከተሉት ሀሳቦች ተወስደዋል። የአድዋ ድል ማርች 1,1896 የተገኘ ሲሆን የተለያዩ ጋዜጦችና መፅሔቶች ድሉን አስመልክተው ፅፈዋል። ኒው ዮርክ ታይምስ ማርች 7,1896 ባወጣው እትሙ:-

."SLAUGHTERED BY THE ABYSSINIANS" ከማለቱም በተጨማሪ የተለያዩ የህትመት ውጤቶች በሚከተሉት ርዕሶች ዘገባዎችን ይዘው ወጥተዋል። "Overwhelming Defeat of the Italian Troops by Menelik"; "Generals Dabormida, and Albertone Among the Officers Who Perished"

."BARATIERI's FATAL BLUNDERS"; "It Is Reported That the Retiring Commander - in - Chief Committed Suicide After Defeat" ... የሚሉ ዜናዎች ከማስተጋባታቸውም በተጨማሪ:- ማርች 4, 1896 የካሊፎርኒያው ጋዜጣ፤ ኤፕሪል 4,1896 ሀርፐርስ ዊክሊ የተሰኘ ሳምንታዊ መፅሔት፤ ማርች 29,1896 የሎስ አንጀለስ ሄራልድ ጋዜጣ ... የአድዋን ድል በውብ ቀለማት እና አገላለፅ አትመው ማውጣታቸው ብቻ ሳይሆን በዚያው ዓመት በመፃሕፍት ገፆች ጭምር ተካትቶ ነበር። ምኒልክ በአሜሪካ ሀገር እንዲገኙ ተጋብዘው የነበረው የአጠባበቅ ሁኔታ የነበረው መልክ በፕሬዚደንት፥ አማካሪ ስኪነር በሚከተለው መልክ ተካትቷል።

የአፄ ምኒልክ መገኘት በእጅጉ የአሜሪካን ህዝብ ትኩረት አግኝቷል። ከማንም በህይወት ከሚገኝ የዓለማችን ንጉሥ ምናልባትም ከጀርመኑ ቄሳር ጭምር የተሻለ ትኩረት የሚስብ ይሆናል። የበለጠ የህዝብ ቁጥርም በትርዒቱ ላይ እንዲገኝ ያደርጋል። ንጉሡ ከይሁዳ አንበሳ በመወለድ የንጉሥ ሰሎሞንና የንግሥተ ሳባን ዘሩን ታሪክ ይዘዋል። ... ረጅም እድሜ አላቸው የሚባሉ የጀርመን የኢጣሊያና ሌሎች የአውሮፓ ነገሥታት ቤተሰቦች የዘር ሐረግ ከንጉሡ ጋር ሲወዳደር እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። ... ምኒልክ የሰሎሞንን ጥበብ ለማየት ኢየሩሳሌም ድረስ የሄደች ቅድመ አያት ያሉቻቸውና በህይወት የሚገኙ ብቸኛው ሰው ናቸው።

ይህንን ታሪክ ስናስብ አንድ ቀን ኢትዮጵያ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ቤተሰብ ርእሰ ብሔር / Head of the State አድርጋ እንደ ብሪታንያ ታሪኳን የምታጎላበት ጊዜ



t.me/OLDBOOKSPDF

ይኖር ይሆን ብለን እናስባለን። የበለጠ ደግሞ ከንጉሡ ነገሥቱ ጎን አንድ የአባ ገዳዎች አባ ገዳ ኖሮ ከ አንድ ንጉሥ አመራር / Monarchy ወደ ጣምራ ነገሥታት / Diarchy እናድግም ይሆናል። 'የንጉሡ ቤተሰብና አባ ገዳው የሚተኩት የፕሬዚደንቱን ቦታ ነው። የምንጠላው የአንድ ሰው አምባገነን አመራር Monocracy) መሆኑ ይሰመርበት።'

በ1901 የአሜሪካ 26ኛው ፕሬዚደንት ቴዎዶር ሩዝቬልት ያደረጉትን ዲስኩር አስመልከቶ ሮበርት ስኪነር ሲገልፅ፡-

> ፀናይትድ ስቴትስ ይሄ ነው የሚባል የንግድ ልውውጥ ከማይደረግባቸው ትናንሽ አገሮች ጋር ኦፊሴላዊ የወዳጅነት ግንኙነት ሲኖራት፤ በአንፃሩ ለማይታወቅ ዘመን ያህል የንግድ ልውውጥ በራሱ መንገድ ከሚካሄድባት ኢትዮጵያ ጋር አንዳችም የኦፊሴል ግንኙነትና ወዳጅነት ሳይኖራት መቆየቱ አንግዳ ነገር ነው። ... ከዳግማዊ ምኒልክ ጋር መደበኛ የዲፕሎማሲ ግንኙነት መመስረቱ እንዲያውም በጣም ዘግይቷል የሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ አስችሎኛል። ... ሩዝቬልት ራሳቸው ወደ ኢትዮጵያ መሄድ ቢችሉ ኢጅግ በጣም እንደሚመኙ ገለፁ።

የተለያዩ የዓለም ጋዜጦችና ሚዲያዎች ስለዐምኒልክ የተለያዩ ዘገባዎች ይዘው ወጥተው ነበር። ከእነዚህም መሀከል፡- ኒው ዮርክ ታይምስ በጁላይ 29 ቀን 1903 እትሙ 'ፈረንሳይ ውስጥ በተከሰተው የሀይማኖት ክርክር ሳቢያ አገር እንዲለቁ የተፈረደባቸው መነኮሳት ወደ አሜሪካ ወይም ኢትዮጵያ መሰደድ እንደሚፈልጉ ገልፀው ነበር።' ኒው ዮርክ ታይምስ ያወጣው ሌላ ዜና 'የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ምኒልክ የራሳቸው የገንዘብ መሀለቅ ማተሚያ መሣሪያ ሲኖራቸው ነው። በአሁኑ ሰአት አጤ ምኒልክ 110,230 ፓውንድ ከብደት ያለው ወርቅና በርካታ የብር ማዕድን አከማችተው ይገኛሉ' የሚል ሐተታ ይዞ ወጥቷል። ሩዝቬልት የንግድ ግንኙነት መመሥረትን አስመልከቶ በገፋት ደብዳቤ በሌሎች ሀገሮች ላይ እንደሚያደርጉት 'የአሜሪካን ጥቅም ለማስጠበቅ' የሚል አገላለፅ አልተጠቀሙም። ይልቁኑ 'የሁለቱን ሀገሮች ጥቅም እኩል የሚያስጠብቅ' የሚል ሐረግ ተካትቷል። ይህንን አይነት አገላለፅ አሜሪካ በወቅቱ ትጠቀም የነበረው 'አብልጦ ለሚወደድ አገር / Most Favored Nation, MFN ነበር።



t.me/OLDBOOKSPDF

## ዘመናዊ ሥልጣኔዎች፦

ከበርካታ ምንጮች በተለያዩ ጊዜያት ያሰባሰብናቸውን እውነተኛ ማስረጃዎች በመንተራሥ የተከናወኑ ዓበይት ፍፃሜዎችን እንደሚከተለው አቅርበናል። ማስረጃዎቹ ሙሉ በሙሉ አስተማማኝ፣ የተፈተኑ እና የተረጋገጡ ናቸው።

'በ1876 የሸዋ ንጉሥ እያሉ በአራዚዮ አንቲኖሪ ከሚመራው የጣሊያን ጂኦግራፊያዊ ልዑካን ቡድን ጋር ባደረጉት ስምምነት ሸዋ ውስጥ "ለት ማረፊያ" የሚባል ሥፍራ ሰጡ። ጣሊያኖች ዓላማቸው ምንም ይሁን ምን ምኒልክ ለጥበብ የነበራቸው ፍላጎት በተከታታይ ባስመዘገቧቸው ለውጦች ውስጥ ተረጋግጧል።

1. በ1883 ከጣሊያናዊው ካውንት ፔትሮ አንቶኔሊ ጋር የሰላምና የወዳጅነት ስምምነት ተፈራረሙ። ካተኮሩባቸው ነጥቦች መሀከል ንግድ እናዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ይገኙበታል።
2. በ1897 የሩሲያ ቀይ መስቀል ሆስፒታል፣ በኋላ ምኒልክ ሆስፒታል ተቋቋመ። (1910)
3. በ1898 በኢጣሊያ እና ፈረንሳይ ለጋሲዮን ከሊኒኮች ለብዙ ሺህ ህዝብ የፈንጣጣ ክትባት ተሰጠ።
4. በ1898 የመጀመሪያው ሲኒማ ቤት ተከፈተ።
5. በ1898 በቤተ መንግሥት ግቢ የሚከተሉት ተሠሩ። የሚኒስትሮች (ካውንስለሮች አዳራሽ)፣ ፍርድ ቤት (ምኒልክ በየእለቱ ከቤተ ክርስቲያን መልስ የዜጎችን አቤቱታ ይመለከቱ ነበር።)፣ ቤተ ክርስቲያን፣ የፖስታና የስልክ ቢሮዎች፣ የጌጣጌጥ መሥሪያ ቤቶች፣ የጦር መሣሪያ ግምጃ ቤቶች፣ የምኒልክ ፍራንክ ማተሚያ የማሪያ ተሬዛ ገንዘብ ማኖሪያ ግምጃ ቤት፣ የአትክልት ሥፍራ የውሀ ገንዳ፣ የአንበሳና የሰጎን መኖሪያ፣ የከብትና የበግ በረቶች፣ የጠጅና ጠላ ቤቶች፤ ባህር ዛፍ ወዘተርፈ የነበሩት ሲሆን፤ የቤተ መንግሥቱ ስፋት 2 ኪሎሜትር × 1.5 ሜትር ሆኖ ከ7,000 - 8ሺህ የሚገመት ነዋሪ ይኖርበት ነበር።
6. 1900 ዘመናዊ ጋዜጣ በሣምንት አንድ ጊዜ (60 ቅጂ በብላታ ገብረእግዚአብሔር እንደሚዘጋጁ አባ ጀሮምን ጠቅሶ ኢ. ዲ. ሮበርትስ



t.me/OLDBOOKSPDF

ዘግቧል። የጋዜጣው ትኩረት አንድነት፣ ሥልጣኔ እና ሥነምግባር ላይ ያተኩር ነበር። ከይዘት አንፃር "አእምሮ" የተሰኘውን የመጀመሪያ ጋዜጣ ግሪካዊው ነጋዴ አንድርያስ ከዋዲያ በዋና አዘጋጅነትና ባለቤትነት፤ የውጭ ሀገር ዜናዎችን ተርጉመው በማቅረብ ሥራ ጀምረዋል። ምኒልክ በአማርኛ የመዘጋጀቱን አስፈላጊነት አምነው ቁጥር 1 ጥር 17/1901 የመጀመሪያው እትም ተዘጋጅቶ በምኒልክ አማካይነት ለመሣፍንቱና መኳንንቱ ታደለ።)

7. በ1902 የቀበና ወንዝ ላይ የድንጋይ ድልድይ ተሠራ።
8. ሁለተኛው የድንጋይ ድልድይ የራስ መኮንን ድልድይ ነው። በአድዋ ጦርነት የተማረኩ ጣሊያኖች በመንገድ ሥራ ላይ ይሳተፉ ነበር።
9. ከ1905 - 1906 ከ50,000 ያላነሱ የቤት ከዳን ቆርቆሮዎች ተሠርተዋል።
10. ከ1900 - 1913 መቶ የሚሆኑ ዘመናዊ ቤቶች ግንባታ ተከናውኗል።
11. 1903 የመጀመሪያው ሀኪም ወርቅነህ እሸቴ ክሊኒክ ተቋቋመ።
12. 1905 መረብ በተባለው የዳግማዊ ምኒልክ ሀኪም ራስ መኮንን ጎዳና ላይ የመጀመሪያው የግል ክሊኒክ ተከፈተ።
13. 1905 አቢሲኒያ ባንክ ተከፈተ።
14. 1907 እቴጌ ሆቴል (ጣይቱ ሆቴል) አገልግሎት መስጠት ጀመረ።
15. 1908 የመጀመሪያው የምኒልክ ትምህርት ቤት ተከፈተ። (ዘመናዊ ትምህርት የተጀመረው ሙሴ ኢልግ የተባሉ የአፄ ምኒልክ ስዊዘርላንዳዊ አማካሪ ይኖሩበት የነበረው ቤት እሪ በከንቱ አካባቢ ቀይ ባህር ሆቴል የነበረው ነው። በኋላ ወደ ዛሬው ምኒልክ ትምህርት ቤት ተዛወረ። መሣፍንቱና መኳንንቱ ዘመናዊ ትምህርት ፈሪ ያደርጋል ብለው ስለሚያስቡ በአብዛኛው የሚማሩት የደሆች ልጆች ነበሩ። ለተማሪዎች ምግብ እና ብርዝ ከቤተ መንግሥት ይቀርብላቸው ነበር። በተጨማሪ በየወሩ በነፍስ ወከፍ 3 ብር ለተማሪዎች ማበረታቻ ይሰጥ ነበር።)
16. በ1909 አሜሪካዊው ዶክተር ላምቢ በአሁኑ የብሔራዊ ጤና ምርምር ኢንስቲቲዩት የሆስፒታል ሥራ ጀመሩ።
17. በ1909 ምግብ ቤቶች፣ የልብስ ስፌት ማሽን በ150 ብር ይሸጥ ነበር።
18. 1910 ሉኳንዳ ቤት ሥራ ጀመረ።
19. 1911 የመንግሥት ማተሚያ ቤት የህትመት ሥራ ጀመረ።
20. በ1913 ቤተ ሳይዳ የአሁኑ የካቲት 12 ሆስፒታል በአንድ ስዊድናዊ ሀኪምና ሁለት ነርሶች ሥራ ጀመረ።



t.me/OLDBOOKSPDF

21. 20ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ላይ በሦስቱ ታላላቅ ጎዳናዎች ምኒልክ ጎዳና፣ ራስ መኮንን ጎዳና እና ሩሊአን ቼፍኑክስና ጎዳናዎች ላይ የትራፊክ መብራት አገልግሎት ጀመረ።
22. በምኒልክ ትእዛዝ የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና አሰጣጥ ዘዴዎችን የያዙ በራሪ ወረቀቶች ወደ አማርኛ ቋንቋ ተተርጉመው ለህዝብ ተሠራጩ።
23. የሬዲዮ አገልግሎት ባልነበረበት በሩቁ ዘመን ለከተት ዘመቻ ወይም አዋጅ ከሡገነት ላይ ነጋሪት ተጎሥሞ:- "አዋጅ አዋጅ የደበሎ ቅዳጅ የሰማህ ላልሰማ አሠማ" የሚለው የአዋጅ ወይም የከተት ጥሪ ሲደረግ የሰማ ሁሉ "ንጉሥ በሠፊ ነጋሪታቸው በቆላፋ እንጨታቸው ያስነገሩት አዋጅ ነው" በሚል የበለጠ አፅንዖት እንዲሰጠው ይሆን ነበር።
24. የፖስታ አገልግሎት፣
25. የየብስ ትራንስፖርት፣
26. የባቡር ሀዲድ ዝርጋታ፣
27. የኦዲት አገልግሎት፣
28. የዱር እንስሳት አጠባበቅ ህግ ከማውጣታቸው በተጨማሪ በርካታ አገልግሎቶች ተከፍተዋል።

ፈጣን የሆነው የለውጥ ሂደት በዚያን ዘመን ለነበረው ወገን በቀላሉ ቅቡል አልነበረም። ሥልጣኔን ማላመድ ከፍ ያለ እርአያነት ይጠይቅ ነበር። ስለሆነም አጤ ምኒልክ ለለውጥ ሲተጉ ከህዝቡ የሚያጋጥማቸውን ተቃውሞ በብልሀት በአስተማሪ መንገድ ይፈቱት ነበር። የእህል ወፍጮ ሲያስመጡ 'የሚፈጨው ሰይጣን ነውና አናስፈጭም' ሲሉ ራሳቸው ከቤተ መንግሥት እህል አስፈጭተው አመለካከቱን አስተካከለዋል። ውሀ እንጦጦ ላይ ሲተከሉ:- 'እንጣጣም የሰይጣን ሥራ ካልሆነ ውሀ እንዴት ሽቅብ ይወጣል?'፣ 'በሰይጣን ምትሀት ካልሆነ በሽቦ ውስጥ እንዴት ድምፅ በስልክ ያልፋል?' የሚሉና ሌሎች የአስተሳሰብ ዝንፈቶችን ራሳቸው አርአያ ሆነው በማስተማር ተምሳሌት ሆነዋል።

ለምኒልክ ከተገጠሙላቸው መሀከል አንዱ:-

እንዲህ ያለ ንጉሥ የንጉሥ ቁናጣ

ውሀ በመዘውር አቀበት የሚያወጣ



t.me/OLDBOOKSPDF

## ያደፈው ሲታጠብ የጠማው ሲጠጣ

## አሁን ከዚህ ወዲያ ምን ጥበብ ሲመጣ?

በርግጥ አጤ ምኒልክ እጅግ ፈጣንና ለለውጥ የሚተጋ አዕምሮ እንደነበራቸው በርካታ የውጭ ሀገር ሰዎች ስለአፄው የሰጡት አስተያየት "አጤ ምኒልክ" ከገፅ 445 - 446 ከሰፈሩት የተቀነጨበ:- ሲ. ሩ:- "የመጀመሪያው የአንፋሎት መኪና አዲስ አበባ እንደገባ ምኒልክ 15 ቀን ሙሉ ከመኪናው ጋር ሠርተው በኩራት ለመኳንንቶቻቸው አስተዋወቁ::" ዶክተር መረብ:- "የመጀመሪያው የገንዘብ መሥሪያ አዲስ አበባ እንደገባ ምኒልክ እንዴት እንደሚሠራ ሲመረምሩ ሰዓታት ያሳልፋሉ። ዓለም ታላቅ ኢንጂነር ማጣቷን መሠከራለሁ::" ጣሊያንያዊው ደ ካስትሮ:- "በዓለም ያሉ ትልቅ ተራማጅ ሰው ናቸው። ከሰማይ ፕላን ወርዶ ከመሬት ጨረቃ የሚደርስ ፕላን ነው ቢሏቸው፤ የሚቻል ከሆነ እንሥራው የሚሉ ናቸው::"

በሌላ በኩል:- 'መኳንንቱና መሣፍንቱ ምርጡን ቦታ ተከፋፍለዋል ለእርስዎ የሚሆን ቦታ አልተዉ.ምና ምን ይሻላል?' ሲባሉ ምላሻቸው:- "የኔ ርስት ኢትዮጵያ ነች። የግል ርስት የለኝም። ደምስ እኛ ርስት ከተከፋፈልን ለህዝቡ ማን ያከፋፍለዋል?! ማለታቸው እና አጤ ምኒልክ እስከ ህይወታቸው ፍፃሜ የግል ርስት እንዳልነበራቸው ቀቀዮ ታችበሌ (አአ 100ኛ ዓመት ልዩ እትም ላይ አስፍሯል።)

አጤ ምኒልክ በብሔር መሀከል ልዩነት የማያደርጉ ሆኖም በአንፃራዊ መልኩ አንዳች ጥይት ሳይተኰሱ ለተቀበሏቸው 99% የኢትዮጵያ አካባቢዎች ልዩ ከብር ነበራቸው።

መወቀስ ካለባቸው ግን ለኦሮሞ እያዳሉ አማራን የመግፋት ሁኔታ ይታይባቸው ነበር። ቀድመው ባይሞቱ፡ አልጋ እንዲወርሱ ያደረጓቸው መኮንን ወሚ ጉዲሳ፤ የጦር ሚኒስትራቸው ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ

ሀገር በማደርጀት የጦር መሪያቸው ጎበና ዳጬ ነበሩ። ጳውሎስ ኞኞ "አጤ ምኒልክ" በተሰኘው መፅሐፋቸው ገፅ 34 እንዳኖሩት:- '(ጎበና ዳጬ የሰላሌው ኦሮሞ ባላባት የቢሩ ነገዎ ልጅ ናቸው።) የሜታው ባላባት ቢራቱ ጎሌ የምኒልክ ከንድ ነበሩ። እናታቸው የአዲያሞ የልጅ ልጅ ናቸው።



t.me/OLDBOOKSPDF

ምኒልክ ኦሮሞዎችን፦ "ያሳደጋችሁኝ ልጆቻችሁ፥ አብረን ያደግን ባልንጀራችሁ ነኝና በአባቴ አልጋ ከተቀመጥሁ አግዙኝ" ማለታቸው በማያወላዳ ማስረጃ ተደግፎ ተቀምጧል። ለአብነት፦ ወለጋ (ሲቃ ቂለምና ሌቃ ነቀምቴ)

አስተዳዳሪዎቻቸው ጆቴ ቱሉና ኩምሳ ሞሮዳ፤ ጂማ አባጂፋር ጎማ ጉማ ሊሙ - አስተዳዳሪዎቻቸው ጆቴ ቱሉና ኩምሳ ሞሮዳ፤ ጂማ አባጂፋር ጎማ ጉማ ሊሙ ኢናርያ እና ጌራን በመያዝ (የሸዋ አማራና ኦሮሞ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታ መሆናቸው ይታወቃል)

አጣምረው በተባበረው ጦር "የአማራውን የጎጃም ጦር"

ሊሙና አምባቦ ላይ አሸነፉ። 9/10ኛ በኦሮሞ እና 1/10ኛ በአማራ የተገነባውን ጦር ይዘው አርሲ ላይ 1886 ዘመቱ። በተመሳሳይ ስልጢና ሐረሪ ላይ1887 ዘምተው አካባቢውን ተቆጣጠሩ። (በዚህ ጊዜ የኢትዮጵያ ንጉሠነገሥት የትግራዩ አፄ ዮሐንስ አራተኛ ስለነበሩ እና ጎጃም ጎንደር ወሎ ከምኒልክ ጋር መልካም ግንኙነት ስላልነበራቸው በአኖሌና ጨለንቆ ግጭት ተሳትፎ አልነበራቸውም።

**ፍትሐዊነት**

ከዚሁ ጋር አጤ ምኒልክ በወገናቸው ላይ ግፍ እንዲፈፀም ፈፅሞ አይሹም ነበር። ለማሳያ ያህል፦ ጅማ አባጂፋር የተሰኙት የጅማ ኦሮሞ ንጉሥ በባሪያ ንግድ የታወቁ ነበሩ። በተለይም ጃንጀሮ (በአሁኑ አጠራር የም) በወቅቱ 'ጋላ' ይባሉ የነበሩትን ይሸጡ ስለነበር (ምኒልክ ኦሮሞን በዚህ ስም ጠርተው አያውቁም። ራሳቸው የኦሮሞ ልጅ፤ ባለቤታቸው ኦሮሞ፤ ከፍተኛ አመራሮቻቸውም ኦሮሞዎች ነበሩ።) የጂማ ኦሮሞ ንጉሥ የነበሩትን (*የጂማ ያልሁት የቦረናና የጉጂ ኦሮሞ በገዳ ስርአት በራሳቸው ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ስር ከ1460ዎቹ ጀምሮ ስለነበሩ፤ ሌሎቹም የየራሳቸው ንጉሥ ወይም መሪ ስለነበራቸው ነው።) ጂማ አባጂፋርን ቃልበቃል በጠማርም በማስረጃም ተደግፎ በሚገኝ መንገድ አጤ ምኒልክ እንዲህ በማለት ገሰጿቸው፦



t.me/OLDBOOKSPDF

"ይድረስ ካባ ጅፋር

ይህንን የደንብ ወረቀት ጽፌንልሀል።

ከጃንጀሮ ወደንተ ሀገር የመጣውን ጋላ እንግዲህ ከጀ ከገባልኝ ብለህ ቀምተ አድርገህ ባሪያዬ ነህና አንተንም ልበድልህ፤ ልጅህንም አምጣና አንደከብት ልሸጠው ልለውጠው አትበል። ይህን ያህል ዘመን አባቶቻችው ከአባቶችህ፤ ልጆቹ ካንተ ጋር አብረው ኑረው ባርያ ሊባሉ አይገባም። በደባበይም ባሪያዬ ነው እያልክ አትሟገት። የሰው ባርያ የለውም። ሁላችንም የእግዚአብሔር ባርያዎች ነን፤ እግዚአብሔር ከሰው መርጦ ከሰው አልቆ ሲያስገዛ ጊዜ በሰው መጨከን አይገባም። ለሰው ቢያዝኑ አይሟ ይሰጣል። ከኔም ጋር በእግዚአብሔር ቸርነት ጎንደሬ ሁሉ ተሰብስቦ እዚህ ሸዋ መጥቶ ተቀምጧል። አገሬ ልግባ ያለ እንደሆነ ባርያ ነህ ተብሎ ሊያዝ ነውን? ዳግም አወደደበት አተመቸው ቦታ ላይ ይቀመጣል እንጂ ካንተ አገር ተነስቶ ወደ ጃንጀሮ ቢሄድ፤ ወደሌላው ወደ ወደደው አገር ቢሄድ የኔ ዜጋ ነው ብለህ ልትይዝ አይገባም። የጃንጀሮው የሌላም አገር ሰው አንተን ወዶ ወዳንተ አገር ቢገባ የጃንጀሮም ገዢ፤ ሌላውም ገዢ ሁሉ የኔ ዜጋ ነው ብሎ አይያዝ። ደህው አወደደው አተመቸው ቦታ ይደር።"

የካቲት 8 ቀን 1902 ዓመተ ምሕረት አዲስ አበባ ከተማ ተፃፈ።

ከደብዳቤው ይዘት በግልፅ እንደምንመለከተው ምኒልክ ደብዳቤውን የፃፉት ለኦሮሞው ጅማ አባ ጂፋር ሲሆን (*ጋላ በማለት የጠቀሱት በወቅቱ *ጃንጀሮ ተብሎ የተጠቀሰውን ወገን ነው። *ጃንጀሮውንም ከፉ እንዳይደረግበት (እንዳይበደል) በማሰብ ለመከላከል የተደረገ ስለመሆኑና አገላለፁ ሊያስመሰግናቸው እንደሚገባ በግልፅ ቋንቋ ከላይ ተመልከቷል። በትክክል የተፃፈው በኩረ ፅሑፍ ቁልጭ ብሎ ተቀምጦ ዘውጌዎች፡- "አሮሞን እንዲህ እንዲያ ብለዋል" በማለት ለጥላቻ ከዛሬ (2019) ብንነሳ ከ100 ዓመት በፊት የተፃፈን ግልፅ ደብዳቤ በሀሰት አጣምመው ማቅረባቸው ምን ያህል ሀላፊነት የጎደላቸው እንደሆኑ ያረጋግጥልናል። "የአኖሌን ትርክት" ሆን ብለው ለመፍጠራቸው አንድ ማሳያ ይሆናል።



t.me/OLDBOOKSPDF









t.me/OLDBOOKSPDF

"አጤ ምኒልክ" ገፅ 34 ላይ ደብዳቤውን ለአባ ጅፋር ከመፃፋቸው በፊት የባርያ ንግድ እንዲቀር ከወጣት አዋጅ መሀከል፡-

> "የባርያ ነገር ከዚህ ቀደም አትሸጥ አትግዛ ብዬ ባዋጅ አስከልክዬ ነበር። አንተ ግን ውስጥ ለውስጥ መሸጥህን መግዛትህን የማትተው ሆንክ። ይልቁንም በዳር በዳር ያለው ሚስቱንም ልጁንም ይሸጥ ዝመር ማለትን ሰማሁ። አሁንም በዳር አገርም በሌላም አገር ቢሆን ባርያ መሸጥና መግዛትህን ተወኝ። እንግዲህ ባርያ ስትሸጥ፣ ስትገዛ የተገኘህ ሰው እስከ ዘመድህ አያስርሁ ሥራ ለሚሰራ ሰው እሰጥሀለሁ።"
>
> (የካቲት 29 ቀን 1900 ፣ አዲስ አበባ)

ሀቁ ይህ ሆኖ እያለ እውነቱን ደብቆ ታሪኩን አዛብቶና አጣምሞ ማቅረብ የሚያስገኘው ጠቀሜታ ምን ይሆን?

በታሪክ የመጀመሪያውን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ማቋቋም፡- እንደ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ "የኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ ምኒልክ የሚከተሉትን የሚኒስትር ማዕረጎች ሹመት ሰጥተዋል።

1. አፈ ንጉሥ ነሲቡ መስቀሎ - የፍትህ ሚኒስትር

2. ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ - የጦር ሚኒስትር

3. ፀሐፊ ትእዛዝ ገብረሥላሴ ወልደአረጋይ - የፅህፈት ሚኒስትር

4. በጅሮንድ ሙሉጌታ ይገዙ - የፋይናንስ ሚኒስትር

5. ነጋድራስ ኃይለጊዮርጊስ ወልደሚካኤል - የንግድ እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር

6. አለቃ መታፈሪያ መልከፄዴቅ - የንጉሥ ችሎት ሚኒስትር

ከነዚህ ዝርዝሮች ጳውሎስ ኞኞ (በተመሳሳይ ምንጭ፡-



t.me/OLDBOOKSPDF

7.ከንቲባ ወልደፃድቅ ጎሹ - የእርሻና የመሥሪያ ሚኒስትር

8. ሊቀ መኳስ ከተማ ያገር ግዛት ሚኒስትር አድርገው ተጨማሪ መረጃ ሲሰጡን፣ *በጅሮንድ ሙሉጌታ - የገንዘብና የጓዳ ሚኒስትር መሆናቸውን ይገልፁልናል፡ ይሁንና አዛዥ መታፈሪያ መልከጼዴቅን አላካተቱም።)

9. አቡነ ማቴዎስ የትምህርት ሚኒስትርነትን ደርበው ይሠሩ እንደነበርና ልጅ ኢያሱ እንዳስቀሩት ከግል ማስታወሻቸን አግኝተናል።

በአጠቃላይ አፄ ምኒልክ ከነውስንነታቸው በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ግዙፍ አሻራቸውን አኑረው ያለፉ መሪ ናቸው። (ይሁንና ጎጃም አርሲ ጨለንቆ ስልጢ ከፋ ወላይታ እና ሸካ ላይ የወሰዱትን የኃይል እርምጃ እንዳይደገም እንከንናለን። እግረ መንገዳችንንም ባዕዳን ኃይሎች ፈረንሳይ ጂቡቲን፣ ብሪታንያ ኬንያንና ሶማሊያን፣ ጣሊያን ኤርትራና ሶማሊያን ይዘው ወደ ኢትዮጵያ እየገሰገሱ፤ ከሌሎች አካባቢዎች ተለይተው በኃይል የተፋለሚቸውን አካባቢዎች በተመለከተ ምን አማራጭ ነበራቸው? ብለንም መጠየቃችን አይቀሬ ነው።)

## የልጅ ኢያሱ ዘመነ መንግሥት (1913 - 1916)

ከአድዋ ድል በኋላ ከ1896 - 1906 ያለው ጊዜ በኢትዮጵያ ታሪክ "የሰላምና መረጋጋት አሥርት ዓመታት" በመባል ይታወቃል። በምኒልክ የአመራር ጥበብ ልህቀትና በየአካባቢው ገዢዎች አመራር ውስጥ ጣልቃ ባለመግባታቸው የጎላ የተስተዋሉ ችግሮች አልነበሩም። በ1906 አፄው ታመው አልጋ ላይ ከዋሉ በኋላ በኢትዮጵያ ውስጥ በተለይ ለረጂም ዘመን ሥልጣን ላይ የቆየ መሪን ሞት ተከትሎ የሚፈጠረው የሥልጣን ሽኩቻ እንዳያገረሽ መላ መዘየድ ነበረባቸው። በተለይ በ1906 የምኒልክን በህመም አልጋ ላይ መዋልና ከዚሁ ተከትሎ አልጋ ወራሽ ይሆናሉ ተብለው ሙሉ በሙሉ እምነት የተጣለባቸው የተፈሪ መኮንን (በኋለኛው ዘመን አፄ ኃይለሥላሴ አባት) ዋሚ ጉዲሣ ሞት ስጋቱን ከፍ አደረገው።

ይበልጡንም ጎረቤት ሀገሮችን በቅኝ ግዛት ይዘው የነበሩት ብሪታንያ ፈረንሳይና ጣሊያን ሁኔታውን በመገምገም በ1906 ኢትዮጵያን ለመቀራመት ለንደን ውስጥ



t.me/OLDBOOKSPDF

የሦስትዮሽ ውል (Tripartite Agreement) ከነማደናገሪያው፡- የተፈራረሙት 'እርስዎ ድንገት ቢያርፉ ሀገር እንዳትበጠበጥ ሦስታችን መንግሥታት የበላይ ጠባቂ ሆነን ሀገር ለማረጋጋት' የሚል ይዘት ያለው ደብዳቤ ለምኒልክ ሲደርሣቸው፤ ፈጣን አእምሯቸው በመስዋዕትነት የቆየቺውን ሀገር ለጅቦች አሣልፎ ላለመሥጠት መላ ዘየዱ። የሀገር ጉዳይ በችልታ የሚያልፉት አይደለምና በማያሻማ መልክ ለሦስቱም ቅኝ ገዢዎች ግልፅ ያለ መልእክት አስተላለፉ። 'እኔ ብሞት ኢትዮጵያ በአልጋ ወራሽ አማካይነት ትቀጥላለች። የተረጋጋ ሥርአትም እናቆማለንና አታስቡ።' ካሉ በኋላ እርምጃዎች ወሠዱ።

ይኸውም በ1907 በሀገሪቱ ታሪክ የመጀመሪያ የሆነውን የሚኒስትሮች ምክር ቤት አቋቋሙ። አስከትለውም ከልጅ ልጃቸው ሸዋረገድ እና ከወሎው ኢማም መሀመድ አሊ (ራስ ሚካኤል) የተወለደው ልጅ ኢያሱ አልጋ ወራሻቸው መሆኑን በይፋ አወጁ። ጎን ለጎንም ለልጅ ኢያሱ ሞግዚት አድርገው የሸዋውን ራስ ተሰማ ናደውን ሾሙ። የራስ ተሰማን ሞት ተከትሎ በሸዋዎች የታቀደውን ሌላ ሞግዚት የመሾም ውሳኔ አልቀበልም በማለት ልጅ ኢያሱ በራሳቸው ኃይል ከ1911 ጀምሮ ማስተዳደር ጀመሩ።

ስለሆነም በኢትዮጵያ ታሪክ ጸሐፊዎች የጋራ ስምምነት የተደረሰበት የነገሥታት የሥልጣን ዘመን (የዐፄ ምኒልክ እስከ 1913 ተብሎ መቀጠሉ አሳማኝ አይመስልም።) ምክንያቱም በ1910 ጣይቱ በሸዋ ፖለቲካ ፈላጭ ቆራጭ ለመሆን በወሠዷቸው የሹም ሽር እርምጃዎች ምክንያት ከኃላፊነት ተወግደው ምኒልከን እንዲያስታምሙ በግዞት እንጦጦ በቁም እሥር ከተወሰዱ በኋላ ስለ ምኒልክ የተባለ ምንም ነገር የለም። የእውነት በህይወት ቢኖሩ በከፋ ህመማቸው እንጦጦ ባለው ብርድ እና አመቺ ያልሆነ የአየር ጠባይ የሚላኩበት አሳማኝ ምክንያት የለም። ይበልጡኑ ምኒልክ መናገር እንኳ ቢችሉ ኖሮ ኢያሱ ሸዋዎችን 'በምን ታመጣላችሁ' አይነት ንቀት ማስተዳደር ባልቻሉ ነበር። ከዚህ አኳያ የኢያሱ ዘመን በ1911 እንደጀመረ አምነን ታሪኩ እንዳይፋለስ ስንል 1913 የሚለውን ተቀብለን ወደ ልጅ ኢያሱ ስኬቶች እንለፍ። (የምኒልክ ሞት ያልተገለፀባቸው ምክንያቶች አንድም ጎረቤት ሀገሮች ውስጥ ያደፈጡት ቅኝ ገዢዎች አደጋ እንዳይደቅኑ በመስጋት፤ ሁለትም በተለያዩ አካባቢ ያሉ ገዢዎች ሊያስከትሉ የሚችሉትን አደጋ በመፍራት ሊሆን ይችላል የሚል ግምት አለ።)



t.me/OLDBOOKSPDF

ወደ ልጅ ኢያሱ ሥልጣን ዘመን ስናልፍ ኢያሱ በነበሩባቸው ስድስት ዓመታት የሚከተሉትን እርምጃዎች ወስደዋል፦

1. በንጉሥ ምኒልክ የተጀመረውን የአዲት (ሂሣብ ምርመራ ሥራ) እንዲጠናከር አደረጉ። በተለይ ሹማምንቱ እንዳሻቸው ሀብት እንዳይመዘብሩ ከፍተኛ ፀረ ሌባ አቋም ይዘው ቀጥለዋል።

2. ታከስ ገማቾች ገና አዝመራው ተሰብስቦ ሳይወቃ - 'ይህንን ያህል ኩንታል ምርት ይገኛል ብለን እናስባለንና በዚህ መጠን ግብር ታስገባለህ' - አይነት የዘፈቀደ ግምት የአሥራት 1/10ኛ ግብር ሥርአት አስቀርተው 'ገበሬው ምሎ ባመነው ይከፈል' በሚል አሻሽለዋል።

3. ትምህርት ከቤተ ክህነት ስር ተላቅቆ በሥርአት እንዲመራ ('ሴኩላሪዝም' እውን እንዲሆን) አድርገዋል።

4. ምኒልክ የአራዳ ዘበኛ የሚባሉ ሥነሥርአት አስከባሪዎች የፀጥታውን ሥራ እንዲቆጣጠሩ የጀመሩትን ተግባር በማሻሻል "ጡሩምቡሌ" የተባለ ዘመናዊ የፖሊስ ሠራዊት ገንብተዋል።

5. "ሌባ ሻ (ሊባ ሻይ)" በመባል ይታወቅ የነበረውን አንድ ወጣት አብርሾ (አብሾ) አጠጥቶ በረጂም ገመድ በመልቀቅ አዙሮት የወደቀበትን ቤተሰብ በሌብነት የመፈረጅ ህግ አስቀርተው 'ቤቱ ተፈትሾ የጠፋው ንብረት የተገኘ እንደሆነ' የሚል ሐረግ በማስገባት እንዲሻሻል አድርገዋል። ከዚሁ ጎን ለጎን ከሳሽና ተከሳሽ ፍርድ እስኪሰጥ እጃቸው ተቆራኝቶ የሚታሰሩበትን "የቁራኛ ሥርአት" ሙሉ በሙሉ አስቀርተዋል።

6. መስጊዶችን በመገንባት እና ሙስሊም አመራሮችን ወደ ሥልጣን በማምጣት ረገድ አዎንታዊ ሚና ተጫውተዋል። ጎን ለጎንም ወላጅ አባታቸውን ራስ ሚካኤልን የወሎ ብቻ ሳይሆን የትግራይ የጎጃም እና የጎንደር ንጉሥ አድርገው ሾመዋል። ይህም በኢትዮጵያ ታሪክ ትግራይን ከራሷ ውጪ ከሌላ ሥፍራ የተመደበ ሰው በሃላፊነት ሲያስተዳድራት የመጀመሪያው መሆኑ ነው።

7. ለሶማሊያው ፀረ-ብሪታንያ፣ ፀረ-ፈረንሳይ እና ፀረ-ጣሊያን የነፃነት ታጋይ መሀመድ አብዱላሂ ሀሰን ድጋፍ አድርገዋል።



t.me/OLDBOOKSPDF

8. በመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ከቃል ኪዳኑ ጎራ ይልቅ ለ'ማዕከላዊ ኃይሎች' ጀርመንና ቱርክ ድጋፋቸውን ዐሳይተዋል።

ልጅ ኢያሱ አብዛኛውን ጊዜያቸውን በጉብኝት ማሣለፋቸው፣ የሸዋን የፖለቲካ የኃይል ሚዛን ወደ ሰሜኑ ክፍል በማከማቸታቸው፣ የምኒልክን ሹማምንት አለቅጥ ገፍተው የራሳቸውን ኃይል ኢያደረጁ በመሄዳቸው እና ከብሪታንያ ፈረንሳይና ጣሊያን በተፃራሪ አቅጣጫ የሚታዩ እርምጃዎች በመውሰዳቸው ምክንያት አዲስ አበባ የሚገኘው የብሪቲሽ ኢምባሲ፣ ሸዌ እና የግብፁ አቡነ ማትያስ በቅንጅት ባቀነባበሩት 'መፈንቅለ መንግሥት' የመስቀል በዓል ቀን ኢያሱ ከሥልጣን መውረዳቸው ታወጀ።


የለጃቸውን ሥልጣን ለማሥከበር ከትግራይ ወሎ ጎንደር እና ጎጃም የተውጣጣ 80,000 ጦር ይዘው ወደ ሸዋ የገሠገሡት ራስ ሚካኤል ቶራ መስከ ላይ የሸዋን ጦር ድል ነሥተው ወደ አዲስ አበባ ግሥጋሴያቸውን ቀጠሉ። ይሁንና ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ (አባ መላ) የሸዋን እና የሰለጠነውን የማዕከላዊ ኃይል በማደራጀት በወሰዱት የአፀፋ እርምጃ ሸኖ አካባቢ በተካሄደ "የሰገሌ ጦርነት" 16,000 ሰው ከሁለቱም ወገን አልቆ ድሉ ወደ ሸዋ አመዘነ። ልጅ ኢያሱ ወደ አዲስ አበባ ለመመለስ ባደረጉት ጥረት መኤሶ ላይ ጨሮ (አሰበ ተፈሪ) አካባቢ ተሸንፈው ወደ ትግራይ አፈገፈጉ። ሆኖም በ1921 ተይዘው ፊቼ እና ስድስት ኪሎ ቤተመንግሥት ከታሠሩ በኋላ ወደ ጋራ ሙለታ እስር ቤት ተዘዋውረው በ1936 ህይወታቸው አለፈ። ልጅ ኢያሱ ምንም እንኳ የሥልጣን ዘመናቸው ከስድስት ዓመታት ያልበለጠ ቢሆንም በምኒልክ የተጀመሩትን ውጥኖች ለማስቀጠል በሚያስችሉ አበረታች እርምጃዎች ግሥጋሴ ላይ እንደነበሩ ማየት ይቻላል።

(ይሁንና እንደ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ "A Modern History ..." ገፅ 93 መረጃ ከሆነ፦ ልጅ ኢያሱ ራሳቸው በ1912 በመሩት አስቀያሚ ዘመቻ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ይኖሩ የነበሩ 40,000 ዲዚ የተባሉ የማህበረሰብ አባላት ከመሬታቸው ተፈናቅለው በሀገሪቱ ሠፊ ክፍሎች እስከ አዲስ አበባ ተበትነዋል።



t.me/OLDBOOKSPDF







t.me/OLDBOOKSPDF

## የንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት (1916 - 1930)

በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ነገሥታት ከተለያዩ ብሔረሰቦች ጋር መጋባታቸው እጅግ በጣም የተለመደ ነው። በዚህ የታሪክ ዘመን እንኳ አፄ ምኒልክ ራሳቸው በእናታቸው ኦሮሞ ከመሆናቸውም በላይ ራሳቸውም ከኦሮሞዋ ባፈና ጋር መጋባታቸው፤ ልጃቸውን ሸዋረገድን ለወሎው ኦሮሞ ኢማም መሀመድ አሊ (ራስ ሚካኤል) መዳራቸው ሊጠቀሱ ይችላሉ። (በምዕራፍ አራት በስፋት እንሄድበታለን) - ይህ መሰከም የአንድነትና የፍቅር ጉዞ ዘመናት ያስቆጠረና አሁንም ከየትኛውም ብሔረሰብ ብዛት በበለጠ ደረጃ እስከ ቅድመ አያት ብቻ ያለውን የዘር ሐረግ ብንቆጥር ከሁለትና ከዚያ በላይ ብሔሮች የተወለደው ህዝብ ቁጥር ከፍተኛውን ቁጥር እንደሚይዝ አከራካሪ አይደለም።

በደመ ነፍስ ለሚከራከሩ የአዲስ አበባ፣ ሐዋሳ፣ ባህርዳር፣ አዳማ፣ ቢሾፍቱ፣ ጂጂጋ፣ ሰመራ ... በመላው ኢትዮጵያ ያለውን ህዝብ በአንድ አዳራሽ አስገብቶ 'በመልክ በማየት ብቻ በየከልሉ መድብልኝ' ቢባል ማንም አይችልም። ለዚህ ነው የአርሲ አባቶች ሠርገኛ ጤፍ አስቀምጠው 'እስቲ እነዚህን በየወገናቸው ለዩና መድቡ። የዚህን ያህል ኢትዮጵያውያንን መለየት ይከብዳል።' ያሉት። ሠርገኛ ጤፍን ሰአት ወስዶ መለየት ይቻል ይሆናል የኢትዮጵያን ህዝብ ግን በፍፁም አይሞከርም። የንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት በአዳዲስ ክስተቶች የታጀበ ነበር። የኢያሱን እጅ መከበድ የተረዱት ሸዋዎች የኃይል ሚዛኑ የተመጣጠነ እንዲሆን ከወሰዷቸው እርምጃዎች መሀከል፦

1. የመጀመሪያዋ ሴት ርእሰ ብሔር (Head of State) ዘውዲቱ ሆነው ተሹመዋል።

2. ለመጀመሪያ ጊዜ መሪና አልጋ ወራሽ አብረው ተሰይመዋል። ራስ ተፈሪ መኮንን ርእሰ መንግሥት (Head of the Government) እና የዘውዲቱ ሞግዚት በመሆን የመንግሥቱን ሥልጣን ሙሉ በሙሉ የሚመሩት አልጋ ወራሹ ራሳቸው ነበሩ። እንደውም በ1928 ንጉሥ ተፈሪ መኮንን የሚል ሥልጣን መቀዳጀታቸው ቀድሞውኑ እውነተኛው ሥልጣን በእጃቸው እንደነበር አመላካች ነው።

3. ሁለት ቤተ መንግሥቶች እና ሁለት የጦር ኃይል ተቋቁሞ ነበር። አራት ኪሎ የዘውዲቱ ቤተ መንግሥትና የቤተመንግሥቱ ጦር (Palace Guards) እና ስድስት ኪሎ የተፈሪ መኮንን ቤተ መንግሥት (ገነተ ልዑል) ከዋናው የሀገሪቱ ጦር "መሀል



t.me/OLDBOOKSPDF

ሠፋሪ ጦር" ጋር በተሻለ አደረጃጀት ነበሩ። (*መሀል ሠፋሪ የሚለው ስያሜ ብዙዎችን ሲያምታታ ይስተዋላል። በዚህ አገባብ 'መሀል ሠፋሪ' የሚያመለክተው በፊትአውራሪ /ፊታውራሪ፣ ቀኝ አዝማች / ቀኛ ዝማች፣ ግራ አዝማች/ ግራዝማች እና ኋላ ደጀን መሀከል የሚሠፍር መሀል ላይ ሠፋሪ የንጉሥ ጦር) አቀማመጥ ነው። በዚህም ምክንያት ዘመኑ የጣምራ አገዛዝ (Dual Rule / Diarchy) በመባል ይታወቃል። ከዚህ በተጨማሪ በፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ የሚመራ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የራሱ ሃላፊነት ነበረው።

በአፄ ምኒልክ የተጀመሩ እና በልጅ ኢያሱ ዘመን የቀጠሉ ሥራዎች በዚህ ዘመን ውስጥም በቅብብሎሽ መጎልበታቸው አዳዲስ ለውጦችም መመዝገባቸው ታይቷል። ከእነዚህም መሀከል፦ በ1917 የጦር ሀይሎች ሆስፒታል ተቋቋመ።

1917 ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ተከፈተ። (የ1924 ፀረ ባርነት እንቅስቃሴን ተከትሎ ከባርነት ነፃ የሆኑ ቤተሰቦች ልጆች በሀኪም ወርቅነህ እንዲመራ በተከፈተ ቢሮ አማካይነት ከትትል እየተደረገበት ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ተደረገ። *ከላይኛው ምንጭ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ መፅሐፍ ገፅ 94 የተወሰደ)

1917 በአፄ ምኒልክ ከጂቡቲ የተጀመረው የባቡር ሀዲድ ተጠናቅቆ አአዲስ አበባ ጂቡቲ ሥራ ጀመረ።

በ1918 የመጀመሪያው የመሀል ሠፋሪ ጦር ፀረ-ሚኒስትሮች ሰላማዊ ሠልፍ ተካሂዶ ከፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ በስተቀር ሌሎቹ ሚኒስትሮች ከሥልጣናቸው እንዲወርዱ ተደረገ። (ሰላማዊ ሰልፉ በ1910 እቴጌ ጣይቱን በመቃወም ከተደረገው በኋላ በሀገሪቱ ታሪክ ሁለተኛው ነው።)

በ1922 ዘነበ ወርቅ ሆስፒታል ተመሠረተ።

በ1923 ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ብቸኛዋ የመንግሥታቱ ህብረት አባል ሆና ተመዘገበች።

በ1923 ፀረ - የባሪያ ንግድ አዋጅ ታወጀ።

በ1923 በዘመናዊ መንገድ "ብርሀንና ሰላም" የተባለ ጋዜጣ እየታተመ በሠፊ ሥርጭት ወደ ብዙዎች መድረስ ጀመረ። (በ1934 በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚታተሙ



t.me/OLDBOOKSPDF

በድስት ጋዜጦች መሀከል ሦስቱ በአማርኛ ቋንቋ የሚዘጋጁ ነበሩ። እነርሱም "አእምሮ"፣ "ብርሀንና ሰላም" እና "የአጥቢያ ኮከብ" ነበሩ።

በ1924 ራስ ተፈሪ መኮንን በ10 የዓለም ሀገሮች ጉብኝት አደረጉ።

ከ1924 - 1925 የንግድ ሚኒስቴር 'ዳይሬክቶሬት ጀነራል'ተመድቦለት አጅግ ውጤታማ ተግባር ማከናወን ጀመረ። (*የተጠቀሰው መፅሐፍ ገፅ 99)

በ1924 ፀረ ባርነት አዋጅ ተደነገገ። (የባሪያ ንግድ፣ ባሮችን ወደ ውጭ ሀገር ማሻገር ወይም በረጂም ርቀት ንግድ አሳልፎ መሸጥን ሲመለከት፣ ባርነት በሀገር ውስጥ በሰሎች ሥር በባሪያነት መያዝን ያሳያል።)

በ1924 በጣሊያን ካቶሊክ ሚሲዮን አማካይነት የራስ ደስታ ሆስፒታል ሥራ ጀመረ።

በ1925 የዘውዲቱ ሆስፒታል ተከፍቶ አገልግሎት መሥጠት ጀመረ።

1925 በሀገሪቱ የሚገኙ ኬላዎች በማዕከላዊ የጉምሩክ አስተዳደር ሥር እንዲሆኑ ተደረገ።

በ1930 በአዲስ አበባና በየክፍላተ ሀገራቱ በርካታ ትምህርት ቤቶች ተከፈቱ።

በ1920ዎቹ በርካታ ወጣት ኢትዮጵያውያን ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ወደ ውጭ ሀገር አሜሪካ፣ ብሪታንያ፣ ስዊዘርላንድ እና በከፍተኛ ቁጥር ደግሞ ወደ ፈረንሳይ ተልከዋል።

በአጠቃላይ የንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ እና የተፈሪ መኮንን ጣምራ አመራር ዘመን ከልጅ ኢያሱ የአመራር ዘመን ጋር ሲነፃፀር በጉልህ የሚቆጠሩ የእድገት ምልክቶች የተመዘገቡበት ነበር።



t.me/OLDBOOKSPDF











t.me/OLDBOOKSPDF

## የዐፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት (1930 - 1974) ወይም (1916 - 1974)

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ለረጂም ዓመታት ማለትም 44 ዓመታት ወይም ለ60 ዓመታት ያህል በትረ መንግሥቱን ጨብጠው የቆዩትና ከዐፄ ምኒልክ በመቀጠል የመወዛገቢያ ርዕስ የሆኑት ዐፄ ኃይለሥላሴ መሆናቸው አከራካሪ አይደለም። በተለይም ከኃይለሥላሴ ቀጥለው ወደ ሥልጣን የመጡት መንግሥታት፦ ደርግ ለ17 ዓመታት (1974 - 1991) እና ወያኔ ለ27 ዓመታት (1991 - 2018) በማያባራ መልኩ የራሳቸውን የሌለ 'ቁንጅናቸውን' ለማሣየት የአፄ ኃይለሥላሴን ታሪክ በማጠልሸት ሠፊ ጊዜያቸውን ስላባከኑ፤ የአፄው ጣፋጭ ገድሎች ደብዝዘው ታይተዋል። (የሚነሱ የመወዛገቢያ ጭብጦችን ለምዕራፍ አራት አቆይተን፤ የተወሰኑትን እየመለስን በዋናነት ስኬቶቻቸውን ወደ ማሳየት እንለፍ)።

አፄ ኃይለሥላሴ በዓለማቀፍ ደረጃ ገናና ስም ካተረፉ የአፍሪካ መሪዎች አንዱ ሲሆኑ በዘመናቸው ከታዋቂ የዓለም መሪዎች ጎራ የተሰለፉ ነበሩ። በተለይም የኢትዮጵያን የገፅታ ቅብ በዓለማቀፍ ደረጃ በማግዘፍ ረገድ አጠገባቸው ድርሽ የሚል መሪ የለም። ለተለያዩ ታዋቂ ሀገሮች ጭምር የእርዳታ እጃቸውን በመዘርጋታቸው ኢትዮጵያ "የዳቦ ቅርጫት" ሲያሚን ተቀዳጅታ እንደነበር አይዘነጋም። ከ1916 - 1930 የታዩ ለውጦች በዋናነት በኃይለሥላሴ የአመራር ጥበብ የታዩ መሆናቸውን ታሳቢ አድርገን ከ1930 በኋላ በታዩ ለውጦች ላይ አትኩረናል።

የመጨረሻው የ'ሰሎሞናዊው ሥርወ መንግሥት' ንጉሠነገሥት አፄ ኃይለሥላሴ በአፄ ቴዎድሮስ ተወጥነው የነበሩና ከአፄ ምኒልክ ጀምሮ እየተጠናከሩ የመጡ ተግባራትን አጠናክረው ቀጥለዋል። በዓለማቀፍ ደረጃ ካከናወኗቸው ተግባራት የሚከተሉት ጎልተው ይጠቀሳሉ።

1. በ1945 የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሲመሠረት ኢትዮጵያ ከመጀመሪያዎቹ ሃምሣ ያህል መሥራች ሀገሮች አንዷ እንድትሆን ሚናቸው የላቀ ነበር።

2. ከ1945 - 1990 በምሥራቁ እና ምዕራቡ ዓለም መሀከል በተጧጧፈው "የቀዝቃዛው ዓለም ጦርነት" ዓለም በሁለት ጎራ ተከፍላ ስትናጥ ከሁለቱም አቅጣጫ የሚመጣውን ጫና ለማስቀረት እና ዓለም በሁለት ተከፍላ ከምታደርገው መበላላት ወጣ ያለ ገለልተኛ ሦስተኛ ጎራ ተመሥርቶ ነበር። በዚህ በ1955 ኢንዶኔዢያ



t.me/OLDBOOKSPDF

ባንዱንግ ውስጥ በተካሄደው የገለልተኛ ሀገሮች ንቅናቄ (Non Aligned Movement) ቁልፍ ከሆኑ ሰብአናዎች አንዱ ነበሩ።

3. በ1963 የአፍሪካ አንድነት ድርጅት አዲስ አበባ ውስጥ እንዲመሠረት የኃይለሥላሴ ሚና በምንም ሊለካ የማይችል ታላቅ ነበር። ዛሬ አዲስ አበባ ከኒው-ዮርክ፣ ጄኔቫ እና ቪዬና ጋር ከዓለም አራቱ የዲፕሎማቲክ መናኸሪያዎች አንዷ መሆኗ ከኃይለሥላሴ ውጪ በፍፁም አይታሰብም። ለዚህ ታላቅ ሥራቸው በቀድሞው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት / አአድ - (የአሁኑ አፍሪካ ህብረት) አዲስ አበባ በሚገኘው የድርጅቱ ዕህፈት ቤት ሐውልት እንዲቆምላቸው ከአፍሪካ መሪዎች ጥያቄ ቀረበ። በሚያሳቅቅ ሁኔታ ጥያቄውን የተቃወሙት የዘመኑ ህወሓት የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ነበሩ። ደጋግመን እንደገለፅነው ታሪክን ለጊዜው ማደብዘዝ ካልሆነ ቀብሮ ማስቀረት አይቻልምና በ2018 እርካቡ ላይ ቆመው መንበሩ ላይ በተሠየሙት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዓብይ ጥረት ሐውልቱ ሊቆም ችሏል። (መታሠቢያው የሚቆመው አከራካሪ ለሆኑ የታሪክ መገፋፋቶች ሳይሆን በአፍሪካ ደረጃ ላበረከቱት አስተዋጽኦ መሆኑ ለአፍታ መዘንጋት የለበትም።

በዓለም ላይ የነበራቸው ተሰሚነት በጣም የማየሉ ማሳያ በጃማይካውያን ዘንድ የተፈጠረው ልዩ ስሜት ነበር። ለመሆኑ ጃማይካዎች ራስተፈሪያውያን (ራስታ)

ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን እንደ መሲህ በመቁጠር

ስለምን ያገዘፏቸዋል?! የኢትዮጵያን አፈር ቅድስት ሀገር በማለት የማይረግጡበት ምክንያት ምንድነው? ሀሳቡን ስናቀርብ ወደ አንባቢያን ህሊና የሚመጣ አንድ የተለመደ መልስ አለ። ከዚህ አለፍ ብለን ተጨማሪ ምስል እስቀመጥን። ጃማይካዎች በሰቆቃ ውስጥ ባሳለፉባቸው ዘመናት በሙሉ በነቢያቶቻቸው ስለ አንዲት የጥቁሮች የነፃነት ቀንዲል የሆነች ምድር ይሰሙ ነበር። ከዚህም አልፎ ለጃማይካዎች የምህረት መልእክተኛ ከዚያች የተስፋ ምድር እንደሚወጣ ጭምር ይተረከላቸዋል። 'ማርና ወተት ስለምታፈስሰው ለምለም ቅድስት ሀገር።' ከዚህች ሀገር ደግሞ ወደ ምድራቸው ከሰቆቃቸው ሊታደጋቸው የሚመጣ መሲህ እንደሚኖርና ስለመለያዎቹ ይሰማሉ።

ከእነዚህም መሀከል:- መልካም ስነምግባር ያለው፣ የታመነ ቃሉ ጠብ የማይል ነቢይ፣ ሳይሞት ከነህይወቱ የሚያርግ፣ በታላላቆች መሀከል የሚቆም፤ ሀገራቸው ሲመጣ



t.me/OLDBOOKSPDF

በተአምራት የሚታጀብና ልእለ ሰብእ እንደሆነ በስፋት ከመናኘቱ ባለፈ በግለሰቡ ዙሪያ አራቱ አሳማኝ ምልክቶች ሲታዩ ያኔ የፈጣሪ መልእክተኛ መሆኑን በመቀበል፤ በእርሱ ውህ ልክነት፥ የሞራል ደረጃውን ተከትሎ መኖርን መርሀ ማድረግ፥ የጃማይካዎች የሀይማኖት ቀኖና ነው። የትኛውንም ጃማይካዊ ቀረብ ብሎ የመጠየቅ እድል ያገኘ ቢያመልኳቸው እንኳ ንጉሠ ነገሥቱ በምድር ሲመላለሱ ባረማመዳቸው፣ በነምግባራቸው፣ አኗኗርና አነጋገራቸው ህፀፅ እንደሌለ ማመን እና በንጉሡ የህይወት ውህ ልክነት መኖር አስፈላጊ እንደሆነ ይስማማሉ። ትርክቱ በሚከተለው መልክ ቀርቧል።

የእምነቱ አጠናካሪ አህዶች፦ እኤአ 1896 ዓ.ም አውሮፓዊቷ ሀገር ጣሊያን በጥቁሮች ተረታች። ይህንን ተከትሎ 1896 ጣሊያን፣ 1897 ፈረንሳይና ብሪታኒያ፣ 1903 አሜሪካ፣ 1905 ጀርመን አስከትሎም በርካታ ሀገሮች ቆንስላዎቻቸውን አዲስአበባ ውስጥ ከፈቱ። የአድዋን ድል ተከትሎ የአጤ ምኒልከና የእቴጌ ጣይቱ ምስሎች በአውሮፓና በምዕራቡ ዓለም ጋዜጦችና መጽሔቶች የፊትለፊት ገጽ ታተሙ። ጣሊያን ውስጥ ሰላማዊ ሰልፎች፦ "ቪቫ ምኒልክ፣ ቪቫ ጣይቱ፣ ቪያ ደ ላ አፍሪካ" መፈክሮች የትንታጎቹን ምስል በመያዝ ደመቁ። የፓን አፍሪካኒዝም እንቅስቃሴ በአድዋ አራተኛ ዓመት በእነ ዱ ቧይ እና ጃማይካዊው ማርከስ ጋርቪ በአውሮፓና በአሜሪካዎች ተቀጣጠለ። (1900) ስለዚህች አፍሪካዊ ሀገር ሲወራ፦ "ጥቁሮች በነፃነት የሚኖሩባት ገነት" ተባለችና በማርከስ ጋርቪ "Back to Africa Movement" ወደ አፍሪካ እንመለስ ተቀነቀነ። የጃማይካውያን ዐይኖች ሁሉ በስፋት ወደ ኢትዮጵያ ተመለከቱ። እነሆም በ1923 ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ብቸኛዋ የመንግሥታቱ ህብረት አባል ሆነችና ራስ ታ (ራስ ተፈሪ) በነጮቹ መሀከል ተገኙ። ('ትንቢት ቁጥር አንድ ተፈፀመ።')፤

1936 ዓ.ም ኢትዮጵያ በጣሊያን ተወረረች። በዚህ ወቅት የጃንሆይ ተአምረኛ ዲስኩር ጄኔቫ የመንግሥታቱ ህብረት (League of Nations) አዳራሽ ውስጥ ተስተጋባ። እንዲህም አሉ፦ "እናንተ ዛሬ ኢትዮጵያ ስትወረር ዝም ብትሉ ... ከመሀከላችሁ አንድ ኃያል ይነሳና ታሪክ የሚፈርደው እልቂት ይሆናል"። በሶስተኛው ዓመት 1939 ሂትለር በከፋት ተነስቶ በአስር ሚሊዮኖች የሰው ልጅ ህይወት ረገፈ። ትንቢተ ኃይለሥላሴ ዓለም ዕያየው ተፈፀመ። ('ትንቢት ቁጥር ሁለት ሆነ' ፤



t.me/OLDBOOKSPDF

የጃማይካ ሰማይ ደመና አጥቶ ዓመታት ተቆጠሩ። ረሀብ የሰውን ልጅ እንደ ቅጠል አረገፈ። 'የዳቦ ቅርጫት' ተብላ የምትጠራው ኢትዮጵያ መሪ ጃንሆይ የእርዳታ እህል አስጭነው እጃቸውን ለመዘርጋት ወደዚያች ምድር ተጓዙ። ጃንሆይ ሲጓዙ ፀሐይ ቢኖርም ባይኖርም ጥላ ይያዝላቸዋል። አውሮፕላን ጣቢያው ሲደርሱ ወትሮም በሁለቱ ትንቢቶች የተማረከው ጃማይካዊ ጥቅጥቅ ብሎ ይጠብቃቸው ነበረና የጃንሆይ ጥላ /ጃንጥላ ተዘረጋ። ጃማይካዎች ጃን-ጥላ ለምን እንደተዘረጋ ሲገረሙ የደመና ቁልል ተሰብስቦ ሰማይ ጠሉን ወደ ምድር ያለ ስስት ዘረገፈው። (ተአምር ቁጥር ሶስት ተደረገ)፤

ከዓመታት በኋላ በመጣ ዝናም ሰዉ በደስታ ጮቤ ረገጠ። አንድ ተአምር ቀረ። ሳይሞት የሚያርገውን መሲህ ፍፃሜ መጠባበቅ። መስከረም 2/ 1967 ደርግ ጃንሆይ መሞታቸውን አወጀ። በጃንሆይ ሻሸመኔ ሰፍረው የነበሩ ጃማይካውያን 'እውን ሞቱን?' በማለት ለማረጋገጥ አዲስአበባ ካሉ ሌሎች ጃማይካውያን ጋር ነገር ማነፍነፍ ጀመሩ። ደርግ ከገደላቸው በኋላ በምስጢር ስለቀበራቸው የአስከሬናቸውን ዳና ማግኘት አልተቻለም። የጃንሆይ ሙት አካላቸው ዱካ የጠፋቸው ጃማይካውያን "ራስታ አረጉ" እያሉ በደስታ ሰከሩ። ደስታውን ወደ መላው ዓለም ጃማይካ ላኩ። 'መሲህ አረጉ።' (ተአምር ቁጥር አራት የተአምራት ሁሉ ፍፃሜ።)

ከጃማይካዎች የተወሰኑት የኢትዮጵያን ምድር የሚረግጡት በባዶ እግራቸው ነው። ለምን መጫሚያቸውን እንደሚያወልቁ ሲጠየቁ 'ይህቺ ምድር የተቀደሰች ስለሆነች ነው' የሚል ምስክርነታቸውን በኢትዮጵያ በሚተላለፉ የቴሌቪዥን መርሐ ግብሮች ጭምር ቀርበው ተመሣሣይ መልስ መስጠታቸው ታይቷል። አረንጓዴ ቢጫ ቀይ የኢትዮጵያ ባንዲራ ለጃማይካዎች ቋሚ ምልክታቸው ነው። ጃማይካዎቹ የቀዳማዊ አፄ የኃይለሥላሴን ስብእና እደገትና ያከናወኗቸውን ፍፃሜዎች ከኢትዮጵያውያን በተሻለ ደረጃ ጠንቅቀው የማወቃቸው ምስጢር በዚህ እምነታቸው ውስጥ የታመቀ ነው።

4. ዐፄ ኃይለሥላሴ እና ትምህርት፡- ንጉሠ ነገሥቱ ለትምህርት ከፍተኛ ትኩረት በመሥጠት አያሌ ትምህርት ቤቶች በመላ ሀገሪቱ እንዲከፈቱ አድርገዋል። ከተለያዩ ብሔረሰቦች የተውጣጡ ተማሪዎች የትምህርትን ብርሀን እንዲያዩ አድርገዋል። ከ1974 - 1919 በፖለቲካው ቁልፍ ሚና የተጫወቱና በመጫወት ላይ ካሉ ጉምቱ ፖለቲከኞች አብዛኞቹ፣ በርካታ የምጣኔ ሀብት፣ የማህበራዊ ሳይንስ እና የተፈጥሮ



t.me/OLDBOOKSPDF

ላይገስ - በምጡቅ ልሂቃን ደረጃ ያሉ ምሁራን ንጉሡ ባመቻቹት የትምህርት እድል ተጠቃሚ የሆኑ ናቸው። የዛሬው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ) ከአባታቸው ልዑል መኮንን ቀጥሎ የኛንሆይ ቤተ መንግሥት ነበር። ቤተመንግሥቱን ለታላቁ መካነ ትምህርት አሳልፈው መስጠታቸው ለትምህርት የነበራቸውን የላቀ ግምት ማሳያ ነው።

በራንዲ ሮኒንግ ባልስሺከ፦"Haile Sellassie's Students: The Intellectual and Social Background to Revolution, 1952 - 1974" መፅሐፍ እንደተብራራው ከ1935 የኢጣሊያ ወረራ በፊት 200 ኢትዮጵያውያን ከፍተኛ ትምህርት ለመቅሰም ወደ ውጭ ሀገር ተልከው ነበር። ከነፃነት በኋላ 1941 -1959 ቀጥሩ ጨምሮ 553 ወንድና ሴት ተማሪዎች በውጭ ሀገር ትምህርታቸውን ተከታትለው ተመልሰዋል። በ1950ዎቹ ማብቂያ እና በ1960ዎቹ መጀመሪያ አካባቢ በየዓመቱ 1,000 ያህል ተማሪዎች ወደ ውጭ ለትምህርት ይላኩ ነበር።

ከአሥር ዓመታት በኋላ ይህ አኀዝ በእጥፍ ጨምሯል። የኢትዮጵያ ተማሪዎች በ40 የዓለም ሀገራት ትምህርታቸውን ይከታተሉ ነበር። ከ1960 - 1971 ስለነበረው ወቅት በ1964 እና 1971 ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ፅህፈት ቤት ያወጣቸው ማስረጃዎች እንደሚያመላክቱት 780,598 ተማሪዎች በመንግሥት፣ 95,144 ተማሪዎች በሚሲዮን፣ 123,413 ተማሪዎች በግል፣ 35,376 ተማሪዎች በቤተ ክህነት እና 11,642 ተማሪዎች በ'ኮሙኒቲ' "ትምህርት ቤቶች ትምህርታቸውን ይከታተሉ ነበር። በወቅቱ የአሜሪካ፣ ጀርመን፣ ፈረንሳይ፣ እንግሊዝኛ፣ ናዝሬት ትምህርት ቤት እና ቅዱስ ዮሴፍ ትምህርት ቤቶች ዓለማቀፍ ደረጃ ጥራቱን የጠበቀ ትምህርት ይሰጥባቸው ነበር። (ባልስሺከ *.*) ከዚህም በተጨማሪ በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት የሚታተመው "Ethiopia Today Education" በጁላይ 1973 እትሙ የሚከተለውን መልእክት አስፍሮ ነበር።

> *Already in time of Emperor Theodore (1855 -1868) there had been a demand for foreign craftsmen to teach the skills of metalwork and carpentry. In 1877 Emperor Menelik was instrumental in bringing a few Swiss artisans to Ethiopia.*



t.me/OLDBOOKSPDF

ይሆን አሰከተሉ ለሙያ ትምህርቶች የተሰጠውን ትኩረት ያትትና (ይኸው ምንጭ ገፅ 14 ላይ):- "In the academic year 1971-72 there were 716,729 students attending school in elementary schools. The cost has increased from just over 200,000 in 1941-42 to more than 71,000,000." በማለት የእድገቱን መጠን ከማሳየቱም በላይ ወደፊት ሊገነባ የታሰበውን ግዙፍ ዩኒቨርሲቲ ፕላን በገፅ 26 ላይ አስፍሯል። በዘመኑ የፈሩ ፋንዴ ምሁራን ለሰውጥ ከምንም በላቀ ሁኔታ ትጋት እንደነበራቸውና ለትምህርት ጥራት ይሰጥ የነበረው ዋጋ ከፍተኛ እንደነበረ (በዘመን መነፅር ወደኋላ ተጉዞ በመመዘን) ማስተዋል ያስችላል።

5. ሕገመንግሥት፦ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያውን የተጻፈ ሕገመንግሥት (1931) እና የተሻሻለው ሕገመንግሥት (1955) ከነውስንነታቸው ሥራ ላይ እንዲውሉ አድርገዋል። የተቋቋመው የእንደራሴዎች ምክር ቤት በሁለት የተከፈለ ሆኖ የህግ መወሰኛ ምክር ቤት (Senate) እና የህግ መምሪያ ምክር ቤት (Chamber of Deputies) ነበሩት። ለህግ መምሪያ ምክር ቤት የምርጫ ውድድር መጀመሩ እና የተወሰኑ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በ1955 ህገመንግሥት መካተታቸው ለሀገራችን አዲስ ጅምር ነበር። በተግባር ሲመዘን በዘመኑ ይርግም ሆነ በወያኔ የአገዛዝ ሥርአት የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር በወረቀት ላይ የሠፈሩ የይስሙላ እና አፈፃፀማቸው ከቀደመው ጊዜ የከፋ እንጂ የተሻሉ አልነበሩም። በመሆኑም ከዘመኑ አስተሳሰብ የመነጩት ህገ መንግሥቶች ላይተገበሩ ከተግፉት የይስሙላ የተሸምነሙኑ ቃላት የወረቀት ዋጋቸው ቢያንስም በአተገባበር የተሻሉ ነበሩ።

6. በዲፕሎማሲው መስክ የታዩ ለውጦች፦ በ1936 ጣሊያን ኢትዮጵያን በወረረችበት ወቅት በሀገሪቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ሊባል በሚችል ደረጃ በወቅቱ ልሂቃን ተመክሮበት እና ድምፅ ተሰጥቶ በተወሰነ ተቃውሞ ጃንሆይ ከሀገር ወጥተው የኢትዮጵያን ጉዳይ ለዓለማቀፉ ማህበረሰብ እንዲያቀርቡ በተወሰነው መሠረት በጄኔቫ ታሪካዊ ንግግር አድርገዋል። ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ "ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ፣ አንደኛ መፅሐፍ" ገፅ 243 እንደተመለከተው፦

ከአዲስ አበባ ወደ ውጭ አገር ለመሄድ መቆረጡና ስለመሄዳችን - ሚያዝያ 22 … ንጉሠ ነገሥቱ ወደ አውሮፓ ሄደው ኢጣልያ የሠራችብንን ግፍ ሁሉ ለዓለም



t.me/OLDBOOKSPDF

መንግሥታት ማህበር ቢያመለክቱ፣ መልካም ነው ተብሎ በምክር ከተቆረጠ በኋላ ... የሚመጣልን ወሬ ንጉሠ ነገሥቱ አዲስ አበባ ስለገቡ ከተማውን በቦምብ ሊያቃጥሉት ነው...

በዕለቱ ውስጥ ሁለት እውነታዎችን እናስተውላለን። የመጀመሪያው - መኳንንቱና መሣፍንቱ በአዲስ አበባ ተሰብስበው ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ውጭ እንዲሄዱ በምክር መወሰኑንና ሁለተኛው - አጼው ከሀገር መውጣታቸው 'ሊግ ኦቭ ኔሺን' ውስጥ አቤቱታ ማቅረብ መቻላቸው፣ ከነጀነራል ዊንጌት እና ሳንድፎርድ ጋር ባይመጡ የብሪታንያ መንግሥት ከነፃነት በኋላ ይፈጥር የነበረው ጫና መታየት ይገባዋል። ጃንሆይ እንግሊዝ ሀገር ከሄዱ በኋላ አርፈው አልተቀመጡም። የኢትዮጵያን በጣልያን መያዝ ጉዳይ. ለዓለም ማህበረሰብ በተለያዩ ደብዳቤዎች በመማፀን የሀገራቱን ሉዓላዊነት ለማስከበር ከመጣር መሣ ለመሣ ወደ ኢትዮጵያ መሪዎች ደብዳቤዎችን ያለማሰለስ ይፅፉ ነበር። ለአብነት፡- "ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ፣ አንደኛ መፅሐፍ" ገፅ 25 የሚከተለው ተመልክቷል፡-

*ይድረስ ከራስ እምሩ*

*እንግዴህ የነገሩን አኳኋን በአንደኛው ደብዳቤ እንዳስረዳንህ እግዚአብሔር ቢረዳን ገንዘብና መሣሪያ ካገኘን ጉዳዮችን ሳይቋቋም የሚቀር አይመስለኝም። ቢሆንም እንኳ በጦርም በሰላምም ጊዜ ቢሆን ሰብሳቢና ጠቅላይ ያስፈልጋልና በኢትዮጵያ ምዕራብ በኩል ላለው ኢጣልያኖች ባልገቡበት አገር ሁሉ አንተ የኛ ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴና የጦር መሪ ሆነህ እንድትሠራ...*

አፄ ኃይለሥላሴ በጻፏቸው ሁለቱ መጽሐፎች ጠበሰቅ ያለ ዝርዝር የሠፈረ ሲሆን ለተደራሲያን ፍንጭ ለመስጠትና ለሚነሱ ክርክሮች ሥዕል ለማስያዝ (ከዚሁ ምንጭ ገፅ 29) ዘለግ ያለ መልእክት በምክንያት እንደሚከተለው አቅርበናል።

*የፋሺስት ፕሮፓጋንዳ የዓለምን ጆሮ ስላደናገረው እኛም ዓለም በዚህ ፍሬ በማይገኝበት ልፈፋ እንዳይታለል እውነተኛውን የኢትዮጵያን አቋምና ፍላጎት ... ጳጉሜን 3 ቀን 1928 ዓ.ም ማክሰኞ (8-9-1936) ሎንዶን ላይ በሌጋሲዮናችን ሆነን ከዚህ የሚከተለውን ቃል ለዓለም ህዝብ አሰማን። "ፋሺስት ኢትዮጵያን በሙሉ ይዣለሁ፣ ተከታዮቼም አየበዙ በመሄድ ላይ*



t.me/OLDBOOKSPDF

ናቸው በሚለው የጉራ ወሬ የዓለም አስተያየት በከፊል መታለሉ የታወቀ ነው። ይህም የፐሮፓጋንዳ ወሬ አርግጥ አንዳልሆነ ማንም ሊረዳው ይችላል። ከኢትዮጵያ በተገኙት መረጃዎች መሠረት የኢትዮጵያ ግዛት ከሦስት አጅ ሁለቱ አጅ አንዳልተያዘ መናገር ይቻላል። የኢጣልያ የጦር ኃይል አሁን የተያዘውንና ሊይዘው ያሰበውን ግዛት የሚከታተለው በአየር ሲሆን ህዝቡን ጨቁኖ የሚይዘው በባላገሩ ላይ ኢፕሪት የሚባለውን የጋዝ ጭስ በብዛት በመርጨት ነው።

ጃንሆይ ያደረጉት ያላሰለሰ ዲፕሎማሲያዊ ጥረት ፍሬ ማፍራቱን በተመለከተ (ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ እና ሀሮልድ ማርከስ በፃፏቸው መፅሐፎች ውስጥ የሚከተሉትን ሀሳቦች እናገኛለን።)

በ1941 ዓለማዊው ሁኔታ የፈጠረውን ዳራ ተከትሎ ከጀነራል ሳንድፎርድ፣ ጀነራል ዊንጌት፣ የጊዴኦን ጦር እና የኢትዮጵያ አርበኞች ጋር በመሆን ከሱዳን በመነሣት ሜይ፣ 1936 አዲስ አበባ በመግባት የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ አውለብልበዋል። 1942 እና 1944 ከእንግሊዝ ጋር በመደራደር ከፍተኛ ጥረት ባያደርጉ ዘመኑ የቅኝ ግዛት እንደመሆኑ ብሪታንያ ኢትዮጵያን ከጠላት የተወሰደ፡- "የተያዘ የጠላት ግዛት አስተዳደር Occupied Enemy Territory Administration /O.E.T.A" ለመመሥረት ከፍተኛ ጫና አሣድራ እንደነበር አይዘነጋም።

ሁኔታውን ካረገቡ በኋላ የእንግሊዝ ፍላጎት ኤርትራ እና ኦጋዴን ላይም የበረታ ስለሆነ የወቅቱን ኃያል አሜሪካን በመቅረብ በ1945 ከፕሬዚደንት ፍራንክሊን ደ. ሩዝቬልት ጋር በግብፅ ተገናኝተው በኤርትራ፣ በኦጋዴን እና በባቡር ሀዲድ ዙሪያ ውይይት አድርገዋል። በሜይ 1952 ከአሜሪካ ጋር በተደረገው የ'ፖይንት ፎር' ስምምነት መሠረት፡- በእርሻና ህብረተሰብ ጤና ትምህርት፣ በአንበጣ መቆጣጠሪያ ተቋም፣ የህዝብ አስተዳደር ሥልጠና እና የውጭ ትምህርት እድል በመስጠት ረገድ አመርቂ ውጤት ታይቷል። በ1930 እና 1934 የዘመናዊ ጦር ትምህርት ቤቶች በቤልጂየም እና ስዊድኖች አሰልጣኝነት ተቋቁሞ የነበረ ሲሆን በጣልያን ወረራ ወቅት ተቋርጦ ነበር።

ኢትዮጵያ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአሜሪካ ተልእኮ ሥር በኮርያ ጦርነት በ"ቃኘው ሻለቃ" ተወከላለች። በዚህ ስኬታማ ጉዞ ምክንያት ከ1950 - 1953 የአሜሪካ ወታደራዊ ድጋፍና አማካሪ ቡድን (MAAG) እያንዳንዳቸው 60,000



t.me/OLDBOOKSPDF

ሠራዊት የያዙ ሦስት ክፍለ ጦሮች (180,000 ሠራዊት) በ5 ሚሊየን ዶላር ድጋፍ ለማሠልጠን የሚያስችል ስምምነት ተደርጓል። በ1970ዎቹ መጀመሪያ አሜሪካ ለአፍሪካ ከሠጠቺው ጠቅላላ ድጋፍ 60 እጁ ለኢትዮጵያ መሆኑ ሲታይ ከፍተኛ ስሌት ነበር። ከ1946 - 1972 አሜሪካ 180,000,000 ዶላር ወታደራዊ ድጋፍ ሰጥታለች። ከ1953 - 1968 ባለው ወቅት 2,500 ኢትዮጵያውያን በሀገረ አሜሪካ በተለያዩ የትምህርት መስኮች ትምህርታቸውን ተከታትለዋል።

ዘመናዊ አየር ኃይል በጠያራዎች (ጄቶች)፣ ፀረ-ታንክ እና ፀረ-አውሮፕላን መሣሪያዎች፣ በባህር ኃይል ጥበብ፣ በእግረኛ እና የነፍስ ወከፍ መሣሪያዎች ጭምር አሜሪካ ሠፊ ድጋፍ አድርጋለች። ለኢትዮጵያ ሠራዊት አሜሪካዊ ስሪት ያላቸው ወታደራዊ የደንብ ልብሶች ጭምር በማቅረብ አሜሪካ ልዩ ድጋፍ አድርጋለች።

በሲቪል ሥራዎች፦ የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን በ1945 የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በተሣተፈበት ወቅት ከአሜሪካኖች ጋር ተቀራርቦ ባደረገው ውይይት መሠረት በዚያው ዓመት ሲቪል አቪዬሺን ከአሜሪካው ታዋቂ አየር መንገድ "ትራንስኮንቲኔንታል ኤንድ ዌስተርን ኤርላይንስ" በመስማማት ተምሳሌት የሆነው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ተቋቁሟል። በዓለማቀፍ ደረጃ ዝነኛ የሆነው የኢትዮጵያ' አየር መንገድ መሠረትም የተጣለው በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት ነው። የመንገድ ሥራ በመልሶ ልማት ግንባታ ዓለማቀፍ ባንክ (IBRD) በተገኘ ብድር ሥራው ተቀላጠፈ። የስኳርና የተለያዩ ፋብሪካዎች ግንባታ፣ በኮሙኒኬሺን መስክ የቴሌፎንና የቴሌግራፍ ሥራ፣ የባንክ አገልግሎት፣ ንግድና ኢንዱስትሪ በአጠቃላይ በተለያዩ ዘርፎች ምጣኔ ሀብቱ እንዲነቃቃ የሠሩት ህያው ገቢር ለተከታታይ ትውልዶች ተሰንዶ ሊተላለፍ ይገባል። (ይሁንና ዐፄ ኃይለሥላሴ እንደ አፍሪካ፣ እስያ፣ ደቡብ አሜሪካ እና መሠል መሪዎች አርጅተውም ወንበሩን ሙጥኝ ማለታቸው ዋጋ አስከፍሏቸዋል። የንጉሡ መሠረታዊ ድክመት ከዚሁ ጋር ተያይዞ መነሳቱ ተገቢ ነው። ከአባዜው ባለመላቀቅ በየወቅቱ ወረፋ የሚጠብቁ መሪዎችን ማየት የተለመደ ነው።)



t.me/OLDBOOKSPDF

## የደርግ ወታደራዊ አገዛዝ ሥርዓት (1974 - 1991)

የቀደመውን መሪ ታሪክ ማከፋፋት ለመጀመሪያ ጊዜ ጎልቶ የወጣው በደርግ ዘመነ መንግሥት ነው። ደርግ ያለ የሌለ ውርጅብኙን ኃይለሥላሴ ላይ በማዝነብ የቀደሙ መሪዎችን ግን ጥንካሬም ሆነ ድክመት እያነሳ ተጉዟል። ደርግ የአፄ ኃይለሥላሴ ታሪክ ላይ የሚከተለው መርህ ምህረት የለሽ የማጠልሸት ዘመቻ ነበር። ከዘመነ ደርግ ተከትሎ የመጣው የወያኔ ሥርአት መሪዎችን ብቻ ሳይሆን ያለፈውን የኢትዮጵያ ታሪክ በሙሉ ለመደምሰስ የቆረጠ ሆኖ ወጣ። በዚህ ዘመቻው ከ1991 - 2018 በነበረው ጊዜ ከአፄ ምኒልክና አፄ ኃይለሥላሴ ቀጥሎ ታሪክ ለትውልድ (በጎው ከከፋው ጋር ለመማማሪያ እንዳይቀርብ መጥፎው ብቻ እንዲወሣ በመደረጉ፤ የታሪኩን ገፅታ ለማስተካከል ባለመ አግባብ የሚደረግ ጥረት ሁሉ ፈታኝ ሁኔታ ያጋጥመዋል።

ለመሆኑ ከ1974-2018 (ለ44 ዓመታት) ያለማቋረጥ ጥላቻን ብቻ ሲጋት የነበረ አእምሮ የቱንም ያህል እውነት ቢነገረው እንደምን ሊቀበል ይቻለዋል? ከምክንያት ይልቅ ስድብ እርግማን ኩነኔ ጥላቻ ከፋት ብቻ ሲሰማ የባጀ ወገን ሀቁ ሲነገረው አልቀበል ቢል ለምን ይፈረድበታል? ታሪክን በአግባቡ ማቅረብ እጅግ በጣም ፈታኝ፣ አዳጋች፣ አስፈሪና የማይሞከር መምሰሉ ብዙዎችን በዝምታ ሸብቧል። ይህ ፅልመት መገፈፍ አለበት። ታሪክ ለዓላማው እንዲውል ሁሉም ዜጋ ኃላፊነት አለበት። ከወያኔ ቀጥሎ የከፋው የደርግ ወታደራዊ አገዛዝ ጭምር በጎ ሥራዎች መወሳት ይገባቸዋል።

በታሪክ ውስጥ መጥፎው ብቻ ከተወሳ ትውልዱ ምን ይማራል? በየትኛው በጎ ላይ ተመሥርቶ ወደፊት ይራመዳል? ታሪክስ ስህተትን ለማረም፤ በዋናነት ጥንካሬን አውስቶ ለመራመድ ካልሆነ ጠቀሜታው ምንድነው? በእርግጥ የቅርብ ጊዜ የፖለቲካ ታሪክ አብዝቶ ካልተኮነነ ግርሻው አደጋ ስለሆነ መሠነድ አለበት። ጀርመኖች የሂትለርንና የናዚዎችን ታሪክ መሠነዳቸው እነርሱም ዓለምም ትምህርት እንዲቀስምበት ሆኗል። መልካሙ ነገር ትኩረታቸው በቀጥታ የናዚ አባላት ላይ እንጂ ኣጆቻቸው ላይ እንኳ ቢሆን ያነጣጠረ አይደለም። በመሆኑም በዘመነ ደርግ 'ተከናወኑ መልካም ሥራዎችን 'በደማቅ የታሪካችን ሰበዞች' አውዶች ውስጥ ማስፈር ስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። በእርግጥ አንዳንድ የአገዛዝ አይነቶች የሚተረኩላቸው አንድ ታሪክ ሰበዝ ቢኖር እንኳ ከምርቱ አረሙ ረዝሞ በበጎ ለማውሣት አስቸጋሪ ንደሚሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው።



t.me/OLDBOOKSPDF

የሥልጣን ዘመኑን በ1974 "ሀ" ብሎ የጀመረው ወታደራዊ የበታች ሹማምንቶች ቡድን "ፓ" ብሎ ከሥልጣን በመጣበት መንገድ እስከተወገደበት 1991 ድረስ የገዘፋ ድክመቶችና የበረቱ አምባገንንቶች እንደነበሩት አያከራክርም። ሆኖም በታሪካችን ውስጥ ያስተመጣቸው የደማቅ ታሪክ ሰበዞች የወያኔ ዳዋ ውጧቸው ሲሸፈኑ ማየት አዳጋች ይሆናል። በዚህም መሠረት ስሙን በመለዋወጥ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ አደራጅ ኮሚሽን (ኢሠፓአኮ) ተልዕኮውን ጨርሶ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ (ኢሠፓ)፤ ከጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ እስከ የኢትዮጵያ ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢህዲሪ) ካከናወናቸው ድርጊቶች አንኳሮቹን እንደሚከተለው ለመዳሰስ እንሞክራለን (ዓመተ ምህረቶቹ በመፅሐፉ ከፍል የተጠቀሱት በሙሉ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር የተቀመጡ ናቸው። ሆኖም በደርግ ዘመን የተፈፀሙ ክንውኖች አሁን ካለው ትውልድ ትውስታ አንፃር በኢትዮጵያ አቆጣጠር እንዲሆኑ በማሠብ በዚሁ መንገድ ቀርቧል:-

የካቲት 1966 በነገሌ ቦረና ከተማ የሚገኘው አራተኛ እግረኛ ብርጌድ የመጀመሪያውን ወታደራዊ አመፅ አካሄደ። አመፁን የጀመረው የምድር ጦር አዛዥ የነበሩትን ሌተናል ጀነራል ድረሴ ዱባለን ከነተከታዮቻቸው በማሠር ነበር። ይህ እንቅስቃሴ የለውጡ ፋና ወጊ ሆኖ የአብዮቱን ችቦ ለኮሰ። ደርግ በተለያዩ የጦር ክፍሎች ጥምረት ሰኔ 21 ቀን 1966 ተመሠረተ። የወሰዳቸው ዋና ዋና እርምጃዎች (ከተለያዩ ምንጮች በተለያየ ጊዜ ተሰብስበ ከግል ማስታወሻችን የተወሰደ):-

1. መስከረም 24 ቀን 1967 የቅንጦት የቤት አውቶሞቢሎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ታገደ። በዚሁ እለት የመንግሥት ሹማምንት የነበረባቸውን ውዝፍ የመሬት ግብር እንዲከፍሉ የሚያደርግ አስገዳጅ ህግ ወጣ።

2. ጥቅምት 8 ቀን 1967 "እድገት በህብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ" ታውጆ 60,000 ዘማቾች እና መምህራን በመላው ኢትዮጵያ ተሠማሩ። አደረጃጀቱ በ80 ሄክታር አንድ ቀበሌ ገበሬ ማህበር እንዲቋቋሙ ተደርጎ በመላው ኢትዮጵያ 7,000 ተመሣሣይ ማህበሮች ተመሠረቱ። ደርግ "ዕውቀት ይስፋፋ፤ ድንቁርና ይጥፋ" በሚል መፈክር በሀገሪቱ በሙሉ በዘረጋው የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ አማካይነት ገበሬው ሳይቀር ማንበብና መፃፍ የቻለ ሲሆን በርካታ እናቶች የእድሉ ተጠቃሚ ሆነዋል።



t.me/OLDBOOKSPDF

3. በዘመኑ ሦስት አይነት የገበሬዎች የህብረት ሥራ ማህበራት ነበሩ። እነርሱም፦ ሀ) የእምራቶች የህብረት ሥራ ማህበር (ማልባ)፤ ለ) የአምራች ገበሬዎች የህብረት ሥራ ማህበር (ወልባ) እና ሐ) በማልባ እና ወልባ ጥምረት የሚቋቋም ወላንድ ነበሩ።

እነዚህ አደረጃጀቶች እና ታላላቅ የግብርና ተቋማት ወያኔ በእቅድ እስኪያፈራርሳቸው ድረስ በገበሬው ህይወት ላይ ትርጉም ያለው ለውጥ አምጥተዋል።

4. ጥቅምት 25 ቀን 1967 ታላላቅ ህንፃዎችና ቤቶች ተወረሱ።

5. የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበር ተመሥርቶ የላብአደሩን ኑሮ በማሻሻል በኩል የራሳቸውን ሚና ተወጥተዋል።

6. ታህሳስ 14 ቀን 1967 የሀይማኖት መርሆዎች አይነኬ መሆናቸው ታወጀ። (ተግባሩ ግን አመርቂ አልነበረም።)

7. ታህሳስ 15 ቀን 1967 የኦሮምኛ ቋንቋ ፕሮግራም ሥርጭት ሥራ ጀመረ። በኦሮምኛ ቋንቋ ጋዜጠችና መፅሔቶች በሰፊው መታተም ጀምረዋል። የብሔረሰቦች የቋንቋ የባህል እና እኩልነት መብት አዋጅ ተደነገገ።

8. ታህሳስ 23 ቀን 1967 ባንኮችና የኢንሹራንስ ድርጅቶች ተወረሱ።

9. ጥር 21 ቀን 1967 60,000 ዘማቾች የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ ላይ ለመሣተፍ ዝግጅታቸውን አጠናቀቁ።

10. የካቲት 25 ቀን 1967 በተማሪዎች እንቅስቃሴ ወቅት ጎልቶ የወጣው መፈክር "መሬት ለአራሹ" በሥር ነቀል ደረጃ በመመለሥ የገበሬውን ህይወት የለወጠው የአርሻ መሬቶችን ለገበሬዎች ያደረገው አዋጅ የመሬት ሁኔታን ለም ለም ጠፍ እና ለም፤ የቤተሰብ ሁኔታን ባገናዘበ መልክ ለእያንዳንዱ ገበሬ ዝቅተኛው 2 ሄክታር እና ከፍተኛው 10 ሄክታር እንዲሆን ተወስኖ ተግባራዊ ሆኗል።

11. መጋቢት 29 ቀን 1967 የከተማ ቦታና ትርፍ ቤቶች በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ወደ ህዝብ ይዞታነት ተዘዋወረ።



t.me/OLDBOOKSPDF

12. ግንቦት 11 ቀን 1967 የሳይንስና ቴክኖሎጂ ጥናትና ምርምር ኮሚሺን በህግ እንዲቋቋም ሆነ፡፡ የኢንዱስትሪውን ዘርፍ በማነቃቃት እና በአነስተኛ የእደ ጥበብ ዘርፍ (የድንጋይ ማስዋብ ሥራዎች፣ የሽመና፣ የቆዳ፣ የብረታብረት፣ ወርቅ፣ ብር፣ ነሀስ፣ መዳብ፣ የፀጉር፣ የቃጫ፣ የጂማት፣ የጭራ፣ የአለላ፣ የግቻ፣ የዘንባባ፣ የሸክላ አፈር፣ የቀርከሀ እና ሸንበቆ ሥራዎች) እንዲቋቋሙና እንዲደገፉ በማድረግ ከፍተኛ የሥራ እድሎች መፈጠር ችለዋል፡፡

13. በተለየዩ አቅጣጫዎች ከሶማሊያ የተቃጣውን ወረራ ህዝቡን፣ መደበኛ ጦሩን፣ ከፍተኛ ሚሊሺያ፣ የኩባ ወዳጆች እና የሩሲያ ድጋፍ በማቀናጀት ወረራውን መቀልበስ ችሏል፡፡ ደርግ ወደ ሥልጣን ንጉሡን በይፋ ከሥልጣን መስከረም 2 ቀን 1967 አውርዶ ወደ ሥልጣን እንደመጣ ያጋጠሙት የውስጥ የልዩ ልዩ ፓርቲዎች ሽኩቻ፣ የሶማሊያ ወረራ፣ ያላባራ የወያኔ ሀገራዊ ጥቃትና ሌሎች ፈተናዎች ቢኖሩም ይህንን በመቋቋም ያስመዘገበው ለውጥ የሚዘነጋ አይደለም፡፡ የደርግ የመጀመሪያ ዓመታት ጭካኔ በይቅርታ ካልሆነ የማይዘነጋ ሆኖ ከስኬት አንፃር በመጀመሪያው ዓመት ለአብነት የዘረዘርናቸውን ለውጦች ማየቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በተለይም የሀገር ፍቅር ስሜትን በመፍጠርና ጠብታ የብሔረሰብ ጥላቻ ሳይኖር በመምራት በኩል ላሳየው የላቀ ለውጥ በትውልዶች ልቡና ውስጥ ጎልቶ ይታወስ ዘንድ ለጥቆ የመጣው የጨለማ ዘመን መቼም የማይናፈቀው - 'ትላንት እንዲናፈቅ' ምክንያት ሆኗል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF







t.me/OLDBOOKSPDF

## የተማሪዎች ንቅናቄ

የተማሪው ወገን ከምንም በላቀ ሁኔታ የህብረተሰቡን ሃላፊነት በመሸከም ግዴታውን ለመወጣት እንቅስቃሴ ማድረግ እንዳለበት ለጥያቄ አይቀርብም። የሠለጠነ የዴሞክራሲ ልምድ ቢዳብር የተማሪዎች ትኩረት ትምህርታቸውና በዩኒቨርሲቲው ዙሪያ ባሉ አስተዳደራዊና የግብአት ሁኔታዎች በተመረኮዘ ነበር። እንዳለመታደል ሆኖ ከ17 እስከ 21 ዓመት እድሜ ያልዘለሉ አፍላ ወጣቶችን ለፖለቲካ አጀንዳ መጠቀም የሀገራችን የፖለቲካ ልምድ ሆኗል። ከኋላ የሚደበቁ ስውር እጅ ያላቸው (Crocodiles) ፊትለፊት ከሥርአቶች ጋር በመጋፈጥ ለእልቂት የሚዳርጉትን የማንበር ስጋዎች /የዩኒቨርሲቲ ተማሪወች (Front Figures) በማሰለፍ በሸር ፖለቲካ የሚንቀሳቀሱ ቀላል አይደሉም። ወትሮም 'ስድስት ኪሎ' ዩኒቨርሲቲ እያነሳሳ 'አራት ኪሎ ዩኒቨርሲቲ' የፖሊስ ዱላና ጥይት ሲያስተናግድ መቆየቱ ሳይረሳ።

የሰለጠነው ዓለም (Civic Political Culture) የሚከተል በመሆኑና መንግሥት የዴሞክራሲ መርሆዎችን በመጠበቁ የተነሳ አብዛኛውን ጊዜ የትምህርት ተቋማት ከፖለቲካ ነፃ (Secular) ናቸው። መንግሥት ሁሉን ጠፍንገ በሚይዝበት (Subject Political Culture) እና ጎሳ ከሀገር በሚቀድምበት የተያያዝነው የዘመነ መሣፍንት አይነት (Parochial Political Culture) የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ፖለቲካ ውስጥ መዘፈቅና ማዝቀጡ የድንቁርናችን ውጤት ነው። እንዲትም እናት ብትሆን ልጇ ከዩኒቨርሲቲ ተመርቆ ቀጥሎ ወግ ማዕረጉን ልታይ እንጂ አስከሬኑን ልትቀበል አትሻም፣ አይገባምም። ሆኖም የገለፅነው የእኩያን ፍላጎት ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ገብቶ በየጊዜው 'ከድጡ ወደ ማጡ' ቢሆንም ለመጡ ለውጦች ጉልህ ድርሻ ነበራቸው።

ማን ይፈራል ሞት ማን ይፈራል?

ለእናት ሀገር ሲባል።

ፋኖ ተሰማራ ፋኖ ተሰማራ

እንደነ ሆቺሚን እንደ ቼ ጉቬራ

በዱር በገደሉ ህዝቡን እንድትመራ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ልጓዝ በድል ጎዳና በተሰዉት ጀግኖች ፋና።

ፍፁም ነው እምነቱ

የትግሉ ነው ህይወቱ።

(ዓላማ ያለው ኢርሽበርም።)

አገሌ አከሊት ... ለምን ለምን ለምን ሞተ? ሞተች?

የመሳሰሉት ልብ የሚያሞቁ አገላለፆች የወጣቱን ልብ የማሸፈት ችሎታቸው ከፍተኛ ነበር። ይበተኑ የነበሩ ፅሑፎች፡- "አብዮት"፣ "ዴሞክራሲያ"።፣ "የሰፊው ህዝብ ድምፅ"፤ መፅሔቶች "ታገል" እና "ታጠቅ"፤ ከዚህም ባለፈ በየጊዜው ፓርላማው ሲሰበሰብ ያነቧቸው የነበሩ መፈክሮች፡- መሪዎች ሲመጡ የአዲስ አበባ ለማኞች ሸላ ማገሪያ ጣቢያ ይቀመጡ ስለነበር ተማሪዎቹ፡- "ድህነት ወንጀል ነው ወይ?" የሚል መፈክር (በኢትዮጵያ አቆጣጠር 1966)፤ የቤተ ከህነት ሰዎች ከመንግሥት ጋር ተመሳጥረው በሚያደርጉት ደባ የተሰማቸውን ቅሬታ ለመግለፅ፡- "በወንጌል ስም ወንጀል" (1967 -68)፤ "እያ ጅቦ ሳታመኻኝ ብላኝ" - በሀገር ሰበብ ወገን ሲገደል፤ በ1969 (እንደራሲዎን ለመምረጥ ተመዝግበዋልን?)

ከላይ ያሉትን ስንመዝን ከኋላቸው የሚያንቀሳቅሳቸው ከውስጥ እስከ ውጭ የተዘረጋ ውስብስብ ህቡዕ አደረጃጀትና መዋቅር ቢኖርም፤ የተማሪዎች ሚና ታላቅ ነበር። ለምሳሌ፡- "ዴሞክራሲያ" በ1971 በምዕራቡ ዓለም በሚኖሩ ሰዎች ጀርመን በርሊን ውስጥ መመሥረቱን ጠቅሰናል። ይህ ቡድን የኢትዮጵያ ህዝቦች አርነታዊ ግንባር (ኢህአግ) የሚልም መሥርቶ አባሎቻቸው ፍልስጥኤም ተልከው ይሰለጥኑ ነበር። (ፍልስጥኤምና ግንባር) እስምረን እንቀጥል። የተማሪዎች እንቅስቃሴና የኢህአፓ ትግልም ቢሆን የጠብመንጃ ትግልን ማራመድና ተቃናቃኞች ትጥቅ የያዙ በመሆናቸው በራሳቸው ቋንቋ ማናገሩ እንዳለ ሆኖ፤ የራሳቸውን አባላት መግደልም ያልተለመደ አይደለም። በውስጥ ሽኩቻ ብርሀነመስቀል ረዳ ሲያመልጥ ጌታቸው ማሩ መገደሉን ጠቅሶ ማለፍ ይበቃል።

በኢህአፓ የትግል ወቅት መቼም የማንዘነጋው መቶ ሺህዎች ወጣት በደርግ የሰላ ፋስ ተጨፍጭፏል። ውስጥን የሚያደማውን እውነታ ለማሳየት የአዘጋጁን ማንነት



t.me/OLDBOOKSPDF

በተረፈው የነጌሌ ቦረና ከተማ (ከአዲስ አበባ በስተደቡብ 600 ኪሎ ሜትር ርቀት በምትገኝ ከተማ) ብቻ በርካቶች ህይወታቸውን ማጣታቸውን ዋቢ አድርጎ መጥቀስ ይቻላል። ሶማሌ ወንድማችን አብዱላሂ አብዲ፡- "ያልታደለው ትውልድ" በሚል ርዕስ ባዘጋጀው ጦማር ከገፅ 82 -88 የጠቀሳቸውን ብቻ ብንወስድ የሚከተሉት ወጣቶች ተሰውተዋል፡-

በሪሁን ገብረህይወት፣ አስረስ ካሳ፣ ዋሪዮ አዲ፣ ካሱ መኮንን፣ ተከስተ ገብረመስቀል፣ ፀጋዬ መኮንን (መምህራን)፤ (ከተማሪዎች)፡-ንጉሴ ወንድሙ፣ እሸቱ ተሰማ፣ በሀይሉ ተስፋዬ፣ ሙሉዓለም ንጋቱ፣ ዋሲሁን ኃይለሚካኤል፣ ዘሪሁን አስፋው፣ በሺር ኤደን፣ የናስ ማሞ፣ ምንዳዬ ሲሳይ፣ መለሰ ጥላሁን፣ ገነት ከፈለው፣ ሰለሞን ሀይሌ፣ ዘነበ በሁሉ፣ አንተነህ ርስቱ፣ አልማዝ አለማየሁ፣ ከንፉ እሳቱ፣ ግርምትዓለም ደገፉ፣ አለማየሁ ታደሰ፣ ዳንኤል ፈጠነ፣ ሀገሬ ከበደ፣ ምርአት አሰግድ፣ ዳንኤል ታፈሰ፣ ተካልኝ ሆቴቴ፣ አለማየሁ አጅብ፣ ኢደን አብዲ፣ ተስፋዬ ገዛኸኝ፣ እሱባለው ሳህሉ፣ ፍቃዱ መላት፣ አበበች ካሳ፣ አድማሱ አንዳርጌ፣ ኑሩ ሀሰን፣ ታምራት ከበደ፣ ተስፋዬ ካሰኝ፣ አጢዎስ ተከለማርያም፣ እስጨናቂ እሳቱ፣ መሰለ አየናቸው፣ አልማዝ ጣፋ እና አድራሻቸው ያልተገኘ (ኢብራሂም አሊ እና ሥዩም ወልደመስቀል)፤ ከወታደሮች መሀከልም የኢህአፓ አባላት በመሆናቸው ሙቶ አለቃ ጌታቸው ገብረመድኅን፣ አሥር

አለቃ ቦጋለ መኮንን፣ ተራ ወታደሮች፡- አብዲ ሰንደሎ፣ ተስፋዬ ዳመሳ፣ ተካ መኮንን፣ ገብረኢየሱስ ጎሳ፣ ደምሴ ገብረሥላሴ፣ ጎሳዬ ሽብሩ እና ምንተስኖት ዛፉ ተጠቃሽ ናቸው።


በወቅቱ የነበረውን ድባብና ከመከራው ፅዋ መጎንጨታቸውን አስመልክቶ በምስክርነት የቆሙ ሦስቱ መምህራን ወርቃለማሁ ንጋቱ፣ መሰለ ወንድሙና ወርቅአገኘሁ ኃይለጊዮርጊስ ከገፅ 29-51 በተጠቀሰው መፅሐፍ ውስጥ አካፍለዋል። በአጠቃላይ በመቶ ሺህዎች የኢትዮጵያ ተማሪዎች በታሪክ ውስጥ ለከፈሉ ተማሪዎች ምስጋና ያንሳቸዋል። (ይሁንና ተማሪዎች በፖለቲካ ውስጥ መጠቀሚያ መሆናቸው እምርረን የምንዋጋው መሆን አለበት። በተለይ አንድ ሆኖ የኖረው የኢትዮጵያ ልጆች ያለ ምክንያት በጎሳ መንጋ ተቧድኖ መገዳደል ለክብራቸው አይመጥንም።)


የሀገራችንን ደማቅ የሚሊዮኖች ዓመታት መነሻና የ6,000 ዓመታት ታሪክ በርዕስ ደረጃ ብቻ እንዘርዝር ብንል ድፍረት ይሆናል። ከትግራይ ጫፍ አከሱም እስከ ሞያሌ፤ ከጋምቤላ ጥግ እስከ ጂቡቲ መዳረሻ ያልተነካ፤ በስሱ እየተጠና የተቀመጠ እልፍ



t.me/OLDBOOKSPDF

አእላፋት የታሪክ ገፅ አለ። ጊዜ ገድቦን በጥልቀት አመሳክረን መሰነድ ባለመቻላችን ዝቅ ብለን ይቅርታ እንጠይቃለን። ቢያንስ 500 ማህበረሰብ የሚፃፍለት ታሪክ አለው። የበለጠ እንድንተዋወቅ ጠቢባን ብዕራችሁን አንሡ ጥሪያችን ነው።





t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ሦስት

## ዘመነ ፅልመት (1991 - 2018)

ይህ የታሪክ ወቅት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ "የጨለማ ዘመን" ብለን ስንሰይመው 'ለምን?' የሚል ጥያቄ ማስነሣቱ አይቀሬ ይመስለኛል። በመሆኑም የሚነሳውን ጥያቄ ለመመለስ መንደርደሪያ ማቅረብ መልካም መስሎ ታየኝ።

የመጀመሪያው ምክንያት፦ የሚመራውን ሀገርና ህዝብ ታሪክ "በመቶ ዓመት" የሚያቀነጭር ከመቶ ዓመት ወደኋላ አሻግረው እንዳያዩ ጥቁር መጋረጃ በመሆኑ፤ ወገን የሚኮራበትን የጋራ ታሪክ - "የአክሱም ሐውልት ለወላይታው ምኑ ነው?" ብሎ ሐውልት ሳይቀር በክልል የሚሸነሽን፣ በዓለም ታይቶ የማይታወቅ የታሪክ አረዳድ በመከተሉ ዘመኑ ለኢትዮጵያ ታሪክና ለኢትዮጵያውያን ፅልመት በመሆኑ ነው።

ሁለተኛው ከታሪክ ዓላማ በተቃራኒ ታሪክ 'ብሔረሰቦችን ለማገዳደል ታቅዶ' የተሠራበት ወቅት በመሆኑ ድቅድቅ ጨለማነቱ ጥያቄ አያስነሳም።

ሦስተኛውና የተጠቃለለው ምክንያታችን ታሪኩን የማያውቅ፣ በታሪኩ የማይኮራ፣ እንዲያውም ታሪኩን የሚፀየፍ ትውልድ በመፍጠሩ ነው። በውጤቱም የተፈጠረው



t.me/OLDBOOKSPDF

የታሪክ ተንኮል ሦስት ትውልድ በአንድ ዘመን አስገብቶ ስላመከነ ጨለማነቱ አጠራጣሪ ባለመሆኑ ነው።

የመፅሐፉ አዘጋጅ ህወሓት ወደ ሥልጣን ከመምጣቱ አንድ ዓመት ቀድሞ በመምህርነት አዲስ አበባ በመግባቱ በየጊዜው የሚለዋወጠውን የፖለቲካ ትኩሳት ለመከታተል እድሉ ነበረው። በተለያዩ ስልጠናዎች፦ በዩኒቨርሲቲዎች የሚመደቡ አዳዲስ መምህራንን፣ ከሃያ ያላነሱ የመንግሥትና የግል ትምህርት ቤቶች መምህራንን፣ ወጣቶችን፣ ሴቶችንና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን የማሠልጠንና የማወያየት እድል ስላገኘ፣ በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች የማስተማር እድሉን ስላገኘ፣ በታላላቅ መድረኮች ከመንግሥት አመራሮች ጋር ፊት ለፊት የመወያየትም የመጋፈጥም እድሉ ስለነበረው፣ የህዝቡን ብሶት ለመታዘብ በመቻሉና በወያኔ ህወሓት ሥርአት የግፍ ሰለባ ከሆኑ መነኮሳት፣ ኡስታዞች፣ የአየር ኃይል አባላት እና ተስፋ በመቁረጥ መሣሪያ አንስተው ከታገሉ ጋር በመገናኘቱ፣ መፅሐፉ በሚዘጋጅበት ወቅት በቀጥታ በመንግሥት መገናኛ አውታሮች ጭምር የተላለፉ የሰቆቃ ድምፆችንና አካላትን በዐይኑ ስለተመለከተ ያሠፈረው ታሪክ የአሁኑ ትውልድ ማለትም በ2019 እድሜው ቢያንስ 20 ዓመት ከሞላ ጀምሮ ላለው ትውልድ ግልፅ ስለሆነ ማስረጃ ሳያሻው መቅረብ የሚችል ነው። በጥቅሉ የወያኔ ህወሓት ሥርአት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ሀገርና ህዝብ ከምንጊዜውም በላይ የተዋረዱበት፣ ጥላቻ በአደባባይ በሁሉም አይነት ሚዲያዎች የተሰበከበት እና ከፋት ለማስተማር መዋዕለ ነዋይ የፈሰሰበት ነው።

ዘመኑን ዘርዘር አድርገን ስንቃኝ ገና ከጅምሩ አንድን ወገን በሚናገረው ቋንቋ ፈርጀ "ጠላታችን ነውና ከምድረ ገፅ መጥፋት አለበት" ብሎ በ"ማኒፌስቶ" የደነገገ፣ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን በየትመጣቸው ፈርጆ፦ "ኦሮሞ - ጠባብ"፣ "አማራ - ትምክህተኛ"፣ "ደቡብ - የስብዕና መሸርሸር አለበት"፣ ወጣቶችን - "አደገኛ ቦዘኔ" እና "የጎዳና ላይ ነውጠኞች"፣ መምህራንን - "ዋልጌዎች"፣ ኡስታዞችንና ገዳማውያንን - "አሸባሪዎች"፣ ለመብት የሚታገሉ ወገኖችን - "ፀረ ሰላም፣ ፀረ ልማት፣ ፀረ ዴሞክራሲ፣ የሻዕቢያ ተላላኪዎች፣ አነጎች፣ የአርበኞች ግንቦት ሰባት አባላት፣ የቀለም አብዮተኞች" ወዘተርፈ በማለት እና በመፈረጅ በአደባባይ የሚሳደብ፣ በጠራራ ፀሐይ ፊታችን 'ስናይፐር' (ከረጅም ርቀት አልሞ በመተኮስ ለመግደል የሚያስችል በአንድ ነው ሊያዝ የሚችል የጦር መሳሪያ) በተባለ የነፍጥ አይነት ያለ ፍርድ የሚረሽን፣ ነእስር ቤቶች አሰቃቂ ግፎችን የፈፀመ...



t.me/OLDBOOKSPDF

…ሉ ጭፍጨፋውሌ ታደሰ ብሩ በነበረው የ2001 ምርጫ የምርጫ ክርክር መድረክ፣ ታሪክን በማጣቀስ፡ እና በማጥላላት "ዘመነ ርኩሰት" ሁለንተናዊ ውድቀት የታየበት ዘመን… በታሪክ አመለካከቱ በኩል (ዘመኑ በሌሎች ሰዎች ካከበሩቸው ሰዎች እና ያለማቋረጥ ለማያውቁት ትላንት የሚጠራ ጥላቻ ከሰናት ጠብቶ ጀምሮ ዘመነ እጥረት ከተጋቱ መኳንንቶች በየቀርሩ] ያለፈውን ዘመነ ወያኔ/ ዘመነ …/ ዘመነ ደደቢት በማለት ምላሽ የሚያሠጥ መሆኑ ቅንጣት አላሉት የለበትም።

ሌሎ የሚመራው ህዝብ ያለበትን ታላቅ ሀገር -ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ ብሎ ሲሞ መጥራት ተጠየፍ፡ ይጋግም "ሀገሪቱ" የሚል፣ የኢትዮጵያን መለያዎች ያረከሰ፣ ታሪክን ያቆሸሸ፣ ታላቅ ክብሯን ያረከሰ፣ ትግሉን በጠባብነት የባንክ ዝርፊያ ቅሌት ጀምሮ በአመራር ዘመኑ በሰነድ 'መብትህን ራሱ እምጥ አስፍሮ እስከ ውድቀቱ ጉሊት ለይቶ ህዝብ ለማፍረስ የተጋ 'ሊቀ ሰይጣን' ቡድን (ህወሓት) የነበረውን የአገዛዝ ዘመን በኢትዮጵያ ታሪክ - "ዘመነ ፅልመት" የመባሉን ግልፅ እንደቅሬሽ አመክንዮ ለታሪክ የመሠነይ፡ አስፈላጊነት ሳይታለም የተፈታ ነውና በህይወት ዘመናችን ካየነው፣ በጆሯችን ከሰማነው፣ ከመዛግብት ካፈተሸነው፣ ከዐይን ምስክሮች ከተረዳነው ታዛቢን የቅርብ ጊዜያችንን ታሪክ እነሆ።

በዘመነ ወያኔ ህወሓት ውስጥ ተጠያቂ የሚሆን ህዝብ የለም። ህዝብ በየትኛውም የታሪክ ዘመን - መጠኑ ይነሰም - ይብዛ በደል አሰካለ የስቃይ ሰለባ ከመሆን አያመልጥም። ወያኔ ህወሓት መነሻው ከዩኒቨርሲቲ በሂደት ደደቢት ተራራ (ትግራይ) ይሁን እንጂ በሰነልቡናም ሆነ በየትመጣው ከትግራይ ህዝብ የመነጨ አይደለም። በዚህም ምክንያት የትግራይ ልጆች ላይ ጥምር ታሪክ ይቅር የማይለው ግፍ ፈፅሟል። ከደሆነት ሃላፊው ከጎፈ እና ከነባር ታጋዩና አመራሩ ጀነራል ሀየሎም አርአያ ሞት ጀምሮ እስከ አያሌ የትግራይ ልጆች መሰወር በቁጭት በትግራይ ልጆች የተሰነዱ በማሮችን መፃሕፍት መደርደሪያዎች ላይ ማየት ያልተለመደ አይደለም።

በመሆኑም 'ማን ይናገር የነበረ፣ ማን ያርዳ የቀበረ' እንዲባል የትግራይ ተወላጅ የሆነው አሥራት አብርሀም ሀገር ውስጥ እንዳይታተም በተከለከለውና 'እኛ እያለን አንነትህን አትደፋም' ባሉትና በምስጋና ገፁ በገለፃቸው ሦስት የትግራይ ሰዎች እርዳታ በሀገረ አሜሪካ በታተመው፡- "ከአገር በስተጀርባ - የትሮይ ፈረስና የባለፈረሱ ተልዕኮ" በተሰኘውና የ"ህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ"ን ገመና ባጋለጠው መፅሐፉ ካሳቸውን ሀሳቦች የተወሰኑትን መጥቀሱ ለአንባብያን አብርሆት ይሰጣል ብለን ቃል



t.me/OLDBOOKSPDF

ሳንለውጥ እንደሚከተለው አቅርበናል። (ማሳሰቢያ:- ገባ ብሎ የተከመከመው ፅሑፍ የትግራዮቹ፡ ፀሐፊዎች ሲሆን እየተከተለ የሚቀርበው ማብራሪያ የእኛ መሆኑን ለማሳወቅ እንወዳለን።)

በገፅ 52 ላይ:- ‹‹የህወሐት መሪዎች ገና የትጥቅ ትግል ለመጀመር ከመውሣናቸው በፊት በያኔው ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ በአሁኑ አአዩ ውስጥ ማገብት (ማሕበር ገስገስቲ ብሄረ ትግራይ) በሚል ህቡዕ ስም ተሰባስበው ...››

ገፅ 33 ላይ:-

> *የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስትራችን ከየትኛውም አቅጣጫ ይኑሩ እምነታቸውና ዓላማቸው ምንም ይሁን ምን የኤርትራውያን ኢትዮጵያዊነትና የሁለቱንም ህዝቦች አንድነት በሚደግፉ ሰዎች ላይ ያላቸው ጥላቻ ከምን የመነጨ እንደሆነ ለመገመት ያስቸግራል። አስገራሚነቱ ግን አንድም ሁለትም የለውም።*

ዘውጌዎች ተመሳሳይ ጥላቻ የሚያንፀባርቁ ከእነርሱ አመለካከት ውጭ ላሆነ የራሳቸውም ወገን ጭምር የማይመለሱ፤ አደገኛ ዐተያይ ያላቸው ናቸው። ስለየትኛውም አንድነት ፍቅር ህብረት አብሮነት መተሳሰብ ሲነገር አብዝተው ይታመማሉ።

ገፅ 71:-

> *... በሌላ በኩል ደግሞ የህወሐት መሥራቾች በወቅቱ ትግራይን በመገንጠል ራሷን የቻለች የትግራይ ሪፐብሊክ ለመመሥረት ቆርጠው የተነሱበት ስለነበረ ስለኢትዮጵያ ታሪክ፣ ማንነትና መጪው እድል የሚያሳስባቸው ጉዳይ አልሆነም። እንዲያውም አንዳንዶቹ ከዚያም አልፈው የትግራይ ጉዳይም የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው ለማሰኘት፤ 'ኢትዮጵያ የምትባል አገር አልነበረችም። ይቺ ዛሬ ኢትዮጵያ የምትባለው አገር የዛሬ መቶ ዓመት በአፄ ምኒልክ መሪነት በአማራው ገዢ መደብ ተስፋፊነት ልዩ ልዩ ብሔረሰቦችን በመጨፍለቅ፤ በኃይልና በአመፅ የተፈጠረች ነች።*

ይህንን የሚለው ቡድን (የቀድሞውን በይደር አቆይተን) ከንጉሥ ምኒልክ በፊት የነገሡት አፄ ዮሐንስ አራተኛ ለምን በካፋ፣ በጎጃም፣ ሸዋ ጉዳይ ጣልቃ እንደገቡ፣



t.me/OLDBOOKSPDF

ወሎ መሳሊያ ላይ ለምን እርምጃ እንደወሰዱ፤ ልጃቸውን አርአያሥላሴ ዮሐንስን ለምን ከምኒልክ ልጅ ዘውዲቱ ጋር እንዲጋቡ፣ ራሳቸው አፄ ዮሐንስ ቀድመዋቸው የነገሡትን የዋግና ላስታ መሪ (የአፄ ተክለጊዮርጊስን 1868 - 1871) እህት ድንቅነሽን እንዳገቡ፣ ጎንደር - መተማ ድረስ ሄደው ለምን እንደሞቱ ብንጠይቅ መልስ ይኖራቸው ይሆን?

ለመሆኑ የትርክቶቹ ፈጣሪዎች እነማን ናቸው? ይህንን ጥያቄ መመለስ በምዕራፍ አራት ለሚኖረን ውይይትም ሆነ ለዚህ ምዕራፍ ጠቀሜታው የበዛ ስለሆነ የልቦለዱ መነሻ ከድርጅቶቹ ደራሲ የሚመነጭ እንደመሆኑ በሁሉም አቅጣጫ ያሉ 'ተሠሪ ዘውጌዎች' በተመሣሣይ ድምፀት ሲያስተጋቡት ስናይ ምንጩን ለህሊና ፍርድ ትተን ከባለጉዳዮችን ጋር ለመቆየት እንገደዳለን።

ገፅ 59:-

> *በአርግጠኝነት ሻዕቢያ በሙሴ አስተባባሪነትና በጃማይካ አማካሪነት ህወሐትን አሰልጥኖና አደራጅቶ ከሌላ ሀይል ጋር በማቀናጀት በኢትዮጵያ ውስጥ ይካሄድ የነበረውን ፀረ መንግሥት የተቃውሞ ትግል ለማጠናከርና የኢትዮጵያን የኃይል ሚዛን በማዛባት በኩል የራሳቸው አስተዋጽኦ ይኖራል ብሎ በማመኑ ነው። ... ሙሴና ጃማይካ የህወሐትን ሠልጣኞች ይዘው ወደ ትግራይ ሲነሱ ለሁለቱ የተሰጣቸው ከሌሎቹ የተለየና ዘመናዊ የሆነ የትጥቅ መሣሪያ ስንመለከት ነገሩ በደንብ ግልፅ ይሆንልናል። የህወሐት መሪዎች ግን ከኤርትራ ድርጅቶች ጋር ስለነበራቸው ግንኙነትና ሙሴ ስለነበረው ሚና እውነታው እንዳይታወቅ ስለሚፈልጉ ብቻ ያልነበረና ያልሆነ ታሪክ ፈጥረው ሀቁን ለማድበስበስ እየጣሩ ነው ያሉት።*

ፀሐፊው ሁለት መሠረታዊ ቁም ነገሮች አንስቷል። 1ኛ/ "...ከሌላ ኃይል ጋር በማቀናጀት"፣ ያ ሌላ ኃይል ማነው? 2ኛ/ 'ሁለቱ የተለየ ትጥቅ የያዙት ከየት የመጡ ናቸው? መልሱን ራሱ ፀሐፊው ገፅ 60 ላይ በጥያቄ ይመልስልናል።

ገፅ 60:- "*ሙሴ ለምንድነው ከሻዕቢያ ተነስቶ ከህወሐት ጋር መታገል የፈለገው?....*'

በአንክሮ ማስተዋል ከተቻለ እነዚህ ወገኖች ከንጉሥ ምኒልክ መነሣት (1889) ጋር በተመሣሣይ ዘመን የሞቱትን የትግራዩን አፄ ዮሐንስ አራተኛ:- ትግራይን፣ ጎጃምን፣

ጎንደርን፣ ወሎንና ምኒልክን በኃይል ያስገብሩ ስለነበር በዝብዝ ካሳ (አፄ ዮሐንስ አራተኛ)፤ የሸዋ የጊቤ የሲዳ የአርሲ የአብዛኛው ምዕራብ ምሥራቅ እና ደቡብ ሰሜን ሙሉ በሙሉ ገዢ የነበሩትን የራሳቸውን ሰው እንኳ ይከዳሉ። ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም፡- "ከህደት ራሱን የቻለ በሽታ ሲሆን ማስካድ ደግሞ የባሰ ነው።" ማለታቸውን እዚህ ሥፍራ መጥቀሱ ተገቢ ይመስለናል።

ህወሓት በአልባኒያ ሶሻሊዝም ፍልስፍና ላይ ተቸከላ ቆማ የቀረች ግንባር እንደመሆኗ ስትመሠረት ከኢህአፓ ያላስማማት ሀገር እየመራች ጭምር የሚያስባንናት ቅዠት፡- "በኢትዮጵያ ውስጥ መካሄድ ያለበት የመደብ ትግል ሳይሆን የብሔር ጥያቄ ነው" የሚለው አብደት በፍትህዊ ሥልጣን የሚፈታን ችግር ብሔረሰብ ብሔረሰብን የጨቆነ ይመስል በተሰነቀረችበት እስከመጨረሻው የሙጥኝ ማለቷ የማይፈታ ቋጠሮ ቢመስልም ብሔረሰቦችን አጫርሳ ኢትዮጵያን የማፍረስ ተልዕኮዋ አካል ስለመሆኑ ፍልስፍና አይጠይቅም። "ከአገር በስተጀርባ" ገፅ 75፡-

ከጀብሀ ይልቅ የሻዕቢያ አመራሮች ለተወሰኑ የማገባበት መሥራች አባላት ከስጋ ዝምድናና ከአካባቢ ልጅነት አንፃር እጅግ ቅርብ ነበሩ።"

ሲለን "መሥራቾች" የሚለው ላይ በደማቁ አስምረን ወደ ሌላው ማስረጃ እናመራለን። ገፅ 103፡-

*"ለትግራይ ነው የምንታገለው ይበሉ እንጂ የኤርትራ ጉዳይ ዋነኛ አጀንዳቸው ሆኖ ቀጥሏል።"* ገፅ 52፡- *"ገና ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በማገባት ደረጃ እያሉ የኤርትራ ጉዳይ ከቅኝ ግዛት የመውጣት ጥያቄ ነው።"* ገፅ 53፡- *"ለዚህ አቋም ያደረሳቸው በአመራር ደረጃ ላይ የነበሩት በግልና በቡድን ከኤርትራ ኃይሎች አመራር (በዋናነት) "ሻዕቢያ ጋር በነበራቸው ማንነታዊና ስነልቡናዊ ትስስር ምክንያት ...*

ፀሐፊው አስራት አብርሃም የስምሪቱን አንድ መነሻ ዐሳይቶናል። ሠፋ አድርገን ስንመለከተው ደባው ከዚህም አልፎ በግብፅ፣ በአረብ ሊግ አልፎ እስከ ካፒታሊስቱ ሌሎች በአካባቢው ጠንካራ መንግሥት ከተፈጠረ ጥቅማቸውን ሊያሳጣቸው እስከሚችል ኃይላት ድረስ ይዘረጋል።

የህወሓት ነባር ታጋይ የነበሩት ሌላው የትግራይ ሰው፣ የህወሓትን መሠረ አካሄድ በመረዳት በሽፍትነት ትግሉ ወቅት የከዱት አቶ ገብረመድህን አርአያ፡- "የትግራይ



t.me/OLDBOOKSPDF

በጠላት እጅ መውደቅና በኢትዮጵያ ያስከተለው መዘዝ" በሚል ርዕስ በፃፉት ጠማር ክፍል ሁለት ከገፅ 2 ጀምሮ ካሠፈሩት እውነት ደግሞ እጅግ በጣም የሚያሳቅቅ፤ ምናልባትም የትግራይን ወጣት የሚያነቃ፣ ለመላው ዜጋ አስረጂ የሆነ ታሪክ እናገኛለን።

*በ1977 ድርቅ ወቅት የህወሓት መሪዎች ለትግራይ ህዝብ የመጣውን እርዳታ በሱዳን ውስጥ ከፍተኛ የድለላ ችሎታ ያላቸውን ሱዳናውያን ደላሎች በመጠቀም ለሱዳን ነጋዴዎች በመሸጠን በቢሊየን የሚቆጠር ዶላር አግኝተው ነበር። የትግራይ ህዝብ በረሀብ እንደ ቅጠል እየረገፈ እስከሬኑ ቀባሪ አጥቶ የጅብ ቀለብ በሆነበት ወቅት ለ15 ቀናት በቀጠለው የማሌሊት ምሥረታ በዓል አከባበር ከፍተኛ ወጪ ይወጣ ነበር። ለቅድመ ዝግጅቱ 300 ከብቶች ለእርድ ቀርበዋል። ... በየቀኑ ሁሉም ጉባኤተኛ ጧት አምባሻ በስጋ ጥብስ፣ ምሳና እራት በነጭ ጤፍ እንጀራ የተለያዩ የስጋ ወጥ አይነቶች፣ የታሸጉ ፍራፍሬዎችና አትክልቶች እንደልብ፣ ጉሽ ጠላና የዶሮ ዐይን የመሰለ ጠላ ... እንኳን ሽምቅ ተዋጊ የአንድ ሀገር ሀብታም መንግሥት ወጪውን አይችለውም።*

ይህንን በትግራይ ህዝብ ላይ የተፈፀመ የበደል በደል፤ ወደኋላ እንደምንመለከተው በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የተፈፀመ የግፍ ግፍ ስናስተውል ለመሆኑ የህወሓት ቁልፍ አመራሮች እነማን ናቸው? በየከልሉ የሚያስማሯቸው አመራሮች ከማህበረሰቡ ስነልቡና የራቁት የሚሆኑት ለምንድነው? 'ነጠብጣቦቹን በማገናኘት እውነታውን ፍለጋ' መልፋት ይጠይቃል።

በህወሓት ሴራ የተማረሩ የትግራይ ወገኖች ከቋጠሩት ስንኝ የሚከተሉትን እንመልከት፡-

"ለእኔ 'ብሎ' መጥቶ በእኔ እየማለ፣

ህልሜን ሳያነጋ ራዕዬን ሳይፈታ - ለምን ተሰቀለ?

ለዚህ ለዚህማ - የነበረ እንዳለ፣

ትግል ሳያስፈልግ - በዚያው በቀጠለ።"



t.me/OLDBOOKSPDF

ለመለስ ዜናዊ አስረስ ደግሞ፡-

"እንኳ ይሄ አልሰሙ እነ አሉላ እነ በዝብዝ ካሳ፤

የልጅ ልጅ ተብሎ በቤታቸው ሆኖ -

እንዳያት እንዳባት በደንቡ እያገሳ፤

ማደጎ ይመስል

ውጭ ውጭ እያለ- አልለምድ አለንሳ።"

አስራት አብርሀም ገፅ 118

የሚል በቁጭት የተቃኘ ጥልቅ መልዕክት የያዙ ስንኞችን ስናነብ ምንጊዜም ቢሆን ጭቁና የቡድን የጦር አበጋዞች እንጂ ከህዝብ ጋር ጨርሶ የማይገናኝ እንደሆን በበረዶ ያህል ንጣት ጥርት ብሎ ይታየናል።

"ከአገር በስተጀርባ" - ገፅ 85 ላይ፦ *"አንዳንድየህወሓት መሪዎቸ ለኤርትራ ነፃነት ከማንም በላይ የተዋደቅነው እኛ ነን።" ማለታቸውን 'አበይ' ስብሓት ነጋን ጭምር ጠቅሶ ይነግረናል።*

*የማለሰቦቹን ጭካኔ ገፅ 104 ላይ ሲያመላክት፦*

> *... ስለ ታጋዮቹ ያልሆነም ይሁን የሆነ ነገር ካወራህ 'ትፈሊጋለህ' ተብለህ ትወሰድና ወደ ቤት አትመለስም። በዚህ መልክ የተወሰዱ ሰዎች ዛሬም ድረስ የት እንደገቡ የሚታወቅ ነገር የለም። ምናልባት አንድ ቀን የስርአቱ ግብአተ መሬት እውን ሲሆን እያለቀስን ከተቀበሩበት ጉድጓድ አውጥተን በስርአት እንቀብራቸው ይሆናል። በዚህ ወንጀልም በተራቸው የሚጠየቁ ይኖራሉ።*

ህ ቁጭት በስተጀርባ በወያኔ ህወሓት የአገዛዝ ዘመን ጠፍተው የቀሩ በርካታ ችን፤ በሶማሌ ክልል የተገኙ የጅምላ መቃብሮችን እናስብና የትግራይ ወገኖቻችን ፈሰሶ እንደማይቀር መሻታችንን አስቀምጠን፤ ታሪክ የበቀል ሳይሆን እንዳይደገም ተማሪያ ነውና የተደበቁ እውነታዎችን እንገልጣለን። ወያኔ ህወሓት ከሸፍታነት



t.me/OLDBOOKSPDF

ዘመኗ አንስቶ ኢትዮጵያ የሚል ስያሜ የያዙ ቡድኖችን እያሳደደች በመምታት፣ በብሔረሰብ የተደራጁትን ደግሞ አቅፋና ደግፋ መያዟ የማይታበል ሀቅ ነው። ከፊትለፊቷ አፐለዋለሁ ብላ ያሰበቺው ጠንካራ ሀይል - ደርግ እያለ የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ፓርቲ (ኢህአፓ)ን አሲምባ ላይ፣ ከኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ዩኒየን (ኢ.ዲ.ዩ) ጋር በተለያዩ ሥፍራዎች መዋጋት እስከ ፍፃሜዋም በሀሳብ የተደራጁ የዜግነት ቡድኖችን (ቅንጅት፣ መኢአድ፣ ሰማያዊ ፓርቲ ወዘተርፈ) በማፍረስ በመሰንጠቅ እና የብሔረሰብ ድርጅቶችን በማጎልበት የሙጥኝ ያሉበት አሠራር እንደነበር የተሰወረ አይደለም። በስተመጨረሻ ግን እሾህን በእሾህ ሆነና ራሳቸው የሠሩት አደረጃጀት ለውድቀታቸው መነሻ ሆነ።

ህወሓት ደርግን ያሸነፈው በትጥቅ ትግል ነውን?

ህወሓትን የመሠረታትና ከአነሳሷ ጀምሮ የሚዘውራትን ኃይል ምሥጢር መሆን በፍለጋችን አካትተን ስለሁኔታው የተሻለ መረጃ ያለው የአሜሪካ የስለላ ድርጅት (ሲአይኤ) አባል እንደሆነ የሚገመተው ሀሮልድ ማርክስ:- "A History of Ethiopia" በተባለው የታሪክ መፅሐፉ ካስቃኘን ውስጥ የተወሰኑ ነጥቦችን እናንሳ ከገፅ 221 - 222:-

> *ከ1970ዎቹ መጀመሪያ አንስቶ በዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን የሚከታተሉ የትግራይ ተማሪዎች 'የአማራ ገዢዎችንና የትግራይ ተባባሪዎቻቸውን መራር የመደብ ትግል በማድረግ መገርሠሥ አለብን የሚል ድምዳሜ ላይ ደረሱ። በመጀመሪያ የትግራይ ብሔራዊ ድርጅት / Tigray National Organization, TNO መሠረቱ፣ በሂደት ከሽሬ 65 ኪሎ ሜትሮች ርቀት ላይ በምትገኘው ተራራ ሥር ስሙን ወደ ህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት) በመቀየር ፌብሩዋሪ 18, 1975 ተቋቋመ።*

እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ነገር ሥርአቱን የሚዘውሩት:- ብርጋዲየር ጀነራል ተፈሪ በንቲ (አጭር ቆይታ ቢሆንም ኦሮሞ)፤ መንግሥቱ ኃይለማርያም ወልዴ እያና (ኦሮሞ)፤ ደበላ ዲንሳ -ምክትል ፕሬዚደንት (ኦሮሞ)፤ ሥርአቱን ለመጣል በሚደረገው መራራ ትግል በወቅቱ ከዋለልኝ መኮንን ጀምሮ በሠፊ ቁጥር የተሰዉት አማራ ተማሪዎች መሆናቸውን ዕያዩ 'አማራ' የሚለው ሥር የሰደደ ጥላቻ ምንጭ

ከኋላ ኢትዮጵያን ለማፍረስ የሚተጋውን ኃይል ያሳየናል። በዚህ ዓብይ መንደርደሪያ ወደተነሳንበት ነጥብ ስንሸጋገር ወያኔ 16 ዓመታት (1975 - 1990) 'ወከሉኩህ' ያለችው ህዝብ ከሚደግፋት ከልሷ እየተንደፋደፈች ሳትወጣ ቆይታ እንደምን በአንድ ዓመት ጊዜ ገስግሳ መላውን ኢትዮጵያን ተቆጣጠረች? ለሚለው ጥያቄ አንድ መጠኛ ምላሽ ማርከስ ከገፅ 230 - 231 ይፈነጥቅልናል፡-

*መለሥ በፌብሩዋሪ እና ማርች 1990 ሎንዶንን እና ዋሺንግተንን ጎበኘ።*

*መለሥ ያሰበውን ለማሳካት የማይሆነው ነገር የለምና ለሁለቱ ካፒታሊስት መንግሥታት የሚከተሉትን ለመተግበር ቃል ገባ፡-*

*'ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን እርግፍ አድርጌ ተዋለሁ። የነፃ ገበያ ሥርአት ዘረጋለሁ።በኢትዮጵያ ዴሞክራሲ አሰፍናለሁ። የመለስ ቁርጠኛ መምሰል ለአሜሪካ "ስቴትስ ዲፓርትመንት" ከአፕጋቢ በላይ ነበር። ... ከሁሉም በላይ መለስ ዜናዊና ኢሳያስ አፈወርቂ የአሜሪካ ፖሊሲ አውጪዎችን አስደመሟቸው። አሜሪካኖችም ያለፐርፐር ሁለቱ ወጣቶች የወደፊት የአፍሪካ ዴሞክራሲ ፈር ቀዳጅ እንደሚሆኑ ተሰፋ ጣሉባቸው። በመቀጠል ወያኔም ሻዕቢያም በድል ላይ ድልን በመቀዳጀት መንገዱ ጨርቅ ሆነላቸው።*

የደርግ አደረጃጀት፣ የወሰዳቸው እርምጃዎችና የአማራና የኦሮሞ ህዝብ እንደምን መንገዱን አልጋ በአልጋ አደረገላቸው? የሚለውን አንኳር ይዘት እንደሚከተለው እንተንትን፡-

በደርግ ዘመን ቀድሞውንም እየተገነባ የመጣውና ሠፊ አደረጃጀት ያለው እጅግ በጣም ጠንካራ የኢትዮጵያ ሠራዊት በአየር ኃይል፣ በባህር ኃይልና በምድር ጦር ገንብቷል። ከዚህም በተጨማሪ ህዝባዊ ሠራዊት፣ የሚሊሺያ ሠራዊት፣ የብሔራዊ ውትድርና ዘማቾች እና የተለያዩ የፖሊስ አደረጃጀቶች ፈጥሮ ቆይቷል። ዘመናዊ ሥልጠናው ኮማንዶ፣ ስፓርታ፣ ነበልባል፣ የበሰሉና ልምድ ያላቸው አመራሮች፣ የሀገር ፍቅር ስሜት፣ የሎጂስቲክስ አቅርቦት፣ መሣሪያ፣ ወኔ፣ የቁጥር ብልጫ፣ ሠፊ ድጋፍ እና ሁሉ ምሉዕ ቁመና የነበረው ሠራዊት ነበር። በተቃራኒ የተሠለፈው የወያኔ ሠራዊት ከአንድ አይነት የውጊያ ስልት "የቀረጣ ውጊያ" በስተቀር ሌላ አይነት የመዋጊያ ብቃት የሌለው ከመሆኑም ሌላ የኢትዮጵያ ሠራዊት ለዚህ 'የላም ቀንድ የውጊያ ስልት' እንግዳ አይደለም።



t.me/OLDBOOKSPDF

የግላጣ ዕናት አላቸው' ተብሎ የተደሰኮረላቸው ተጋዳላይ ጉጅሌዎች ስብእናቸው ሲመዘን "ገንጣይ - አስገንጣይ"፣ የባንክ ዘራፊዎች፣ የሚታገሉለት ዓላማ 'ብሔረሰብን መጥላት የሆነ'፣ ከአንድ ከልል ፍላጎት ርቀው የማያስቡ፣ ዝለሉ ሲባሉ 'እስከየት' የሚሉ፣ የትምህርት ዝግጅታቸው መነሻና መድረሻቸውን ለማየት የሚጋርዳቸው፣ ሳይንሳዊ የውጊያ ስልት የማይረዳቸው ጉጅሌዎች ናቸው። በድምሩ በሁለቱ መሀከል ያለው ንፅፅር የአይጥና የዝሆን ያህል ነበር። ወያኔ የኢትዮጵያን ሠራዊት ባለው ነባራዊ ሁኔታ እንዲያሸንፍ የግድ መለኮታዊ ጣልቃ ገብነት ወይም ልዩ ተአምር ያስፈልጋል።

ማርከስ ከነገረን የረቀቀ የሲአይኤ ድጋፍ በተጨማሪ ሌሎች አስቻይ ሁኔታዎች ነበሩ። ከእነዚህም ዋነኞቹ፡- ለደርግ ድጋፍ ያደርግ የነበረው የሶቭየት ህብረት መፈራረስ፣ ከሠራዊቱ አመራሮች የተወሰኑቱ ለገንዘብ ሀገርን መሸጣቸው፣ የተራዘመው ውጊያ የፈጠረው ድባብ፣ የብሔራዊ ውትድርና ዘማቾች የግዳጅ ምልመላ ለወያኔ ጡንቻ መፈርጠም ማገዝ፣ የወያኔ መረንነት አብያተ ክርስቲያናትን ሳይቀር መዋጊያ ማድረግ፣ በጭካኔ ለፖሊቲካ ትርፍ ሲባል ለደርግ የተሳሳተ መረጃ በመስጠት የሐውዜንና መርሣን ህዝብ ማስደብደብ፣ የአማራንና የኦሮሞን ወገን ደርግ መሣሪያ በማስፈታቱ የተፈጠረ ቁጭት፣ በህዝቡ ዘንድ የተፈጠረው 'ከደርግ የባሰ አይመጣም' በሚል 'ሰዶ ማሳደድ ቢያምርህ ዶሮህን በቆቅ አትለውጥ' እንደሚሆንበት አለመገመቱ፣ የትዮጵያ ህዝቦች ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ /ኢህዲን እና የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ መኮንኖች አንድነት ንቅናቄ (ኢ.ዴመአን) ድጋፍ፣ ወያኔን ጠፍጥፎ የሠራት የሻዕቢያ ድጋፍ ይጠቀሳሉ። በቁጭታቸው የተነሳ የተደገሰላቸውን ሳያውቁ የአማራ ህዝብ ከደብረ ታቦር በስተቀር መከላከል ሳያደርግ እየመራ ወደ 'ኦሮሚያ' አደረሳቸው። በተመሣሣይ የኦሮሞ ህዝብ ከአምቦ በስተቀር በእርምጃ ወደ መዲናዋ አቃረባቸው። ወያኔ እቅም አልባ እንደነበረች በሚገባ ከሚያስረዱ ጉዳዮች የመጀመሪያ ተጠቃሾቹ ደብረ ታቦር እና አምቦ ያለ ረባ የጦር መሣሪያ እና ዝግጅት እምሽክ ያደረጓት መሆኑ ነው።

የኢህአዴግን ጭምብል ያጠለቀው ወያኔ የእህትና አጋር ድርጅቶች ውህደት፡- ሀሮልድ ማርከስ በተመሣሣይ መረጃ፡-

በ1980ዎቹ አጋማሽ በአብዛኛው በአማራ የተገነባው ኢህዲን ከህወሓት ጋር ተቀራርቦ በ1989 "የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር" /ኢህአዴግ መሠረቱ። የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር (ኦነግ) ግን 'ትግራይ እና አማራ ታሪካዊ ጠላቶቻችን ናቸው' የሚል አቋም ስለነበረው ከሁለቱ ጋር ግንባር የመፍጠር



t.me/OLDBOOKSPDF

ላሳየም። ከዚህ አኳያ የኦሮሞ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት /ኦህዴድ
፣ እንግቦት የተነሳው ዓላማ 'የብሔረሰቦች እኩልነት ከተረጋገጠ ኢኮኖሚው
፣ ቁጥር ለኦሮሞ የተሻለ እድል ይፈጠራል በሚል አቋም ተቀላቀለ/ ተፈጠረ።
እና 1989 ከደርግ የተማረኩ መኮንኖችን አደረጃጀት ኢዴመአን በመፍጠር
አሰማመረላት ይለናል።

ንደታዘብነው፡- "ዘመቻ ቴዎድሮስ"፣ "ዘመቻ ዋለልኝ"፣ "ዘመቻ ቢሊሱማ
ማ"... በሚሉ ሽፋኖች እየተረማመደች "የሽግግር መንግሥት" መሠረተች።
ሁት ሥልጣን ከያዙ በኋላም ምሁራን እንዳይቀርቡ ጥንቃቄ በማድረግ
ባለሟሎች በርካታ አሻንጉሊቶች መጨመር የጉዞዋ አካል ሆነ። ከእሀት
- ደኢህዴን፣ በአጋር ሶዴፓ፣ አብዴፓ፣ ሐብሊ፣ ጋህዴግ፣ ወዘተርፈ
እንደ ዳማ ጠጠር የሚገፉ ቡድኖች ፈጠረች። ህሲና ያላቸው አባላቷ
ሲሉ ምክንያት ፈልጋ ስታስራቸው፣ ሌሎች ሀገር ጥለው ሲሰደዱ፣ ጥቂት
፦ ድርጅቱን ለቅቀው በዐይነ ቁራኛ ከትትልና ሜና እየተደረገባቸው እስከ
ኦጠሉ።

## ህወሓት የአገዛዝ ስልቶችና አፈፃፀማቸው

ወሓት በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የፈፀመቻቸው ሁለንተናዊ የመብት ጥሰቶች
ዑሰብሰብ፣ ረቂቅና ታሪክ ይቅር የማይላቸው ናቸው። ከወንጀሎቹ ስፋትና
የተነሳ ሁሉንም መግለፅ ባይቻልም በአንጻ እየከፋፈሉ ማሣየቱ የትኛውም
፦ ከአረመኔያዊ ድርጊቶች እንዲታቀብ፣ ወንጀል የእድገትና የሀገር ፀር መሆኑን
ዘብ፣ ከፋት መጨረሻው ውርደት መሆኑን እንዲረዳ፣ በእምነትና የሞራል
ሀሮዎች ላይ ተመሥርቶ የሰው ባህርይ ያልሆኑ ሰይጣናዊ ድርጊቶችን አምርሮ
ፍ እንዲርቃቸው፣ በህይወት ዘመኑ ከኢሰብአዊ ድርጊቶች እንዲርቅ... ታስቦ
ለው የአገዛዙን ምንነት የሚገልፅ ማስረጃ ከታሪክ ጋር ተዛምዶ ተሰናድቷል።

ነወሓት ከታች የተፈፀሙ ድርጊቶችን መፈፀሙን ያመላከትንበት መሠረታዊ
ኮ ዓለም ከቅርብ ጊዜ ጥፋቷ መማሯ ጠንካራ ህጎችን እንድታወጣ ስላዣት
ነምሳሌ፡- ደጋግመን በምክንያት እንደምናነሳው አፍሪካዊቷ ሀገር ሩዋንዳ
በ1994 በመቶ ቀናት ውስጥ ብቻ 800,000 ቱትሲዎች በሁቱዎች በአሰቃቂ
ተጨፍጭፈዋል። ያ የእብደት ምዕራፍ በየዓመቱ የተለያዩ ሀገራት መሪዎች
ነት ይታወሳል። ምክንያቱ ደግሞ ያንን አሰቃቂ ምዕራፍ ሩዋንዳውያን ብቻ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሳይሆን ሌላውም ዓለም እንዲማርበት ነው። ሩዋንዳ ከአሰቃቂ ታሪኳ ትምህርት ቀሰማ የብሔረሰብን ጉዳይ ማንሳት በህግ እንደሚያስቀጣ ደንግጋለች። በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ብሔረሰብ ተኮር ጥቃት (እስከ 1019) ተግ አላለም፤ የወደፊቱን ታሪክ የሚያሳየን ይሆናል። በመገናኛ አውታሮች ከማውራት ባለፈ የተበላሸውን ለማረቅ ሠፊ ትግልና ቁርጠኝነት ያስፈልጋል። ፍቅር በሥርአተ ትምህርት ውስጥ ሳይቀር በምዕራፍ ደረጃ ተካትቶ መሠጠት አለበት።

በዓለማቀፍ ደረጃ የተነወሩ ወንጀሎች (Internationally Recognized Crimes) በወየኔ ህወሓት ስለመፈፀማቸው፡-

1. ጅምላ ጭፍጨፋ (Genocide):- 'ጄኖሳይድ' የሚለው ቃል ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በፊት አይታወቅም። የከፉ ወንጀሎች መጠሪያ ቢበዛ "የጦር ወንጀለኝነት / War Crimes" በመባል ይታወቅ ነበር። ከ1939 - 1945 በነበረው አሰቃቂ ድባብ ግን ከስድስት ሚሊየን በላይ አይሁዶች እጅግ በሚዘገንን እና ለመስማት ጆሮን ጭው በሚያደርግ፣ ተሰምቶም በማይታወቅ አኳኋን በጀርመን ውስጥ በናዚዎች ተጨፈጨፉ። ስለኦሽዊትዝ፡-

"Auschwitz" በሚል ርዕስ - "Eye - witness account of the atrocities committed inside the most terrible of Nazi death camps" በዶክተር ሚክሎስ ኒስሊዝስ የተዘጋጀውን መፅሐፍ ያነበበ ሰው ለቀናት እንቅልፍ በዐይኑ አይዞርም። በኦሽዊትዝ እና ሌሎች የማጎሪያ ካምፖች ወንጀሎቹ በሚከናወኑበት ወቅት በልምምጥ መርሆ (Appeasement Policy) ይታወቅ የነበረውን የብሪቲሹን ጠቅላይ ሚኒስትር ኒቪሌ ቻምበርሌይንን በመተካት ሥልጣን የያዘው ቆራጡ መሪ ዊንስተን ቸርቺል በቁጭት መንፈስ፡- "ያለንበት ዘመን ስም አልባ ወንጀል የሚፈፀምበት ነው።" በሚል ያደረገው ገለፃ በብሪቲሽ ሚዲያዎች በጉልህ ተስተጋባ።

ሁኔታውን በስሜት ያዳምጥ የነበረው ዶክተር ካፋኤል ሌምኪን ሁለት የግሪክና የላቲን ቃላትን፡- "ጄኖስ" - ህዝብ እና "ኦቺዲዮ" - በጅምላ ማጥፋት አቀናጅቶ "ጄኖሳይድ" / የጅምላ ጭፍጨፋ የሚለውን ቃል ፈጠረ። ቃሉ በእንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት ውስጥ ሰፍሮ ዓለም በስፋት እየተገለገለበት ይገኛል። በመፅሐፉ ገፅ 86 ናዚዎች ስለ አይሁዶች ያላቸው አመለካከት ተፅፏል። ሆድ ውስጥ ካለ ፅንስና ጨቅላ ልፃናት



t.me/OLDBOOKSPDF

› በጭካኔ ታረዱ? የሚል ጥያቄ ካነሳን ፅንፈኛ ብሔርተኝነትን ለመፋለም
ቦ የመጀመሪያም እንጨከናለን:-

*... Because in the course of its long history the Jewish race had degenerated into a people of dwarf and cripples. By mixing with other races, they had sullied, and threatened to contaminate with degeneracy, the only pure race: the Aryan.*

በረጂም ዘመን ታሪካቸው ከተለያዩ ዘሮች ጋር በመቀላቀል የተሸመደመዱ
ድ)፣ የተበላሹ፣ የቀነጨሩ በመሆናቸው ብቸኛውን ንፁህ የአርያን ዘር
።" ይህ ቆሻሻ አመለካከት ራሱን የሚገልፅባቸው የተለያዩ ምልክቶችን
ከፍል ለማየት ሞክረናል። "እኛ ወርቅ ዘር ነን" ሲሉ ተከታዮቻቸው ሌላውን
፣ አህያ፣ ሃድጊ" በማለት ሲቀጥሉ፤ ማንነቱ ሲሰደብ ሌላውም እየተፈተነ
ሌሎችን ለመከላከል ስሜታዊነት አይሎ በመጓጓን መልካም ግንኙነት
ራል። ቀና የነበረው ሰው ሳይቀር በእልህ የአዙሪቱ ሰለባና አካል ሆኖ ራሱን
። ለዚህ ነው እምርረን ከምልክቶቹ ጀምሮ ማገድ ያለብን።

ፖለቲካ እና በአጠቃላይ የማህበራዊ ሳይንስ ምሁራን ለቃሉ የሰጡት ትርጓሜ
ቅ አንድን ግለሰብ ባጠፋው ወንጀል ወይም ጥፋት ሳይሆን በሆነ ቡድን
፡ (ብሔረሰብ፣ ፆታ፣ ሀይማኖት ወይም ሌሎች መለያዎችን ታሳቢ በማድረግ)
መው ወይም ያለምንም ወንጀል መግደል በ'ጄኖሳይድ' ክልል ውስጥ
ቃል። ወንዶችን ብቻ ለይቶ ማጥፋት - 'አንድሮሳይድ'፣ ሴቶች ላይ አነጣጥሮ
ፃም ጥቃት - 'ፌሚሳይድ'፣ በህዝብ ላይ የሚፈፀም - 'ሆሚሳይድ' እና መሠል
ዮች የጄኖሳይድ አካል ሆነው ተበይነዋል።

· ቀርቶ ሰዎችን ለኑሮ አመቺ ባልሆነ ሥፍራ አስቀምጦ እንዲያልቁ ማድረግ
ላ ጭፍጨፋ አካል ነው። (የዘር ማጥፋት ወንጀል ደግሞ ከጅምላ ጭፍጨፋ
ች አንዱ እና ትልቁ መገለጫ ሆኖ ይጠቀሳል።) ከዚህ ንድፈ ሀሳባዊና ገቢራዊ
፣ ተነስተን ስንመዝን ወያኔ ህወሓት የአማራን እና የኦሮሞን ህዝብ በማንነታቸው
ማነጣጠር በማይገመት ቁጥር በማምከን እና በተለያዩ ቦታዎች ጥበቃ እንዳያገኙ
ረግ፣ በተዘዋዋሪ መንገድ በማስጠቃት እና በማፈናቀል፣ በማጎሪያ ካምፖቹ



t.me/OLDBOOKSPDF

ውስጥ መግደል፤ መሰወርና ማጥፋት፣ በሰልፎች ላይ በቀጥታ አግዚ በሚባል ልዩ ኃይል አማካይነት ፈፅማለች። ድርጊቶቹ በግልፅ በአምቦ ሻኪሶ ባህርዳር ጎንደር ለቀምት ሞያሌ ሻሸመኔ ራያ ወልቃይት (በመላው አማራና ኦሮሚያ) ከመፈፀማቸውም ሌላ በኮንሶ ማህበረሰብ ላይም ግልፅ የጅምላ ጭፍጨፋ ተፈፅሟል። ወንጀለኞቹ በህግ እየተጠየቁ ከመሆኑ ጋር ድርጊቶቹ ስለመፈፀማቸው ከመንግሥት የመገናኛ አውታሮች እስከ ዐይን እማኞች ምስክርነት ሰጥተዋልና አከራካሪ አይሆንም።

ወያኔ ህወሓት በሥልጣን ላይ በነበረቺባቸው ዓመታት ለጅምላ ጭፍጨፋ አስቻይ ደረጃዎችን ከማመቻቸቷ ሌላ ለ44 ዓመታት የአማራ ማህበረሰብ ከምድር ገፅ እንዲጠፋ በህቡዕና በገሃድ ሠርታለች። "የአማራው ገገር ሞደብ" ከሚል አገላለፅ እስከ "አማራ መጥፋት አለበት" 'ማኒፌስቶ' እና አዶልፍ ሂትለር ያደረጋቸውን ቅድመ የዘር ማፅዳት እርምጃዎች ወስዳለች። "ወርቅ ከሆነው የትግራይ ህዝብ በመፈጠሬ ኮራለሁ" የመለስ ዜናዊ ንግግር ውስጠት መቀባቢያ ሳያስፈልገው፡- "Aryans are master race" ከሚለው የሂትለር ንግግር ጋር አንድና ያው ነው። አግአዚ የተባለው ገዳይ ቡድን በናዚዎች ከተቋቋመው ከመንግሥት ውጭ ከሆነው የግል ጦር "Brown Shirts/ Storm Troopers" የአወቃቀርም ሆነ የይዘት ልዩነት የለውም። በበደኖ ማንቁፍቱ፣ አርባ ጉጉ፣ ጉራ ፈርዳ፣ ጋምቤላ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ኮንሶ እና ሶማሊ ክልል የተፈፀሙ ድርጊቶች እና የ"ጄኖሳይድ ኢሥር ደረጃዎች" (በቀደመው ክፍል ካሳየነው አኳያ) ወያኔ "ጅምላ ጭፍጨፋ" መፈፀሟ እና እንዲፈፀም ማመቻቸቷ ሥልጣኗን ለማራዘም የተጠቀመችበት አንድ ስልት ነው።

**2-መንግሥታዊ ሽብርተኝነት (State Terror)፡-** ሽብርተኝነት በግለሰብ ደረጃ በ44 ዓ.ዓ ጁሊየስ ቄሳር በአስደንጋጭ ሁኔታ ሲገደል የተጀመረ ሲሆን፣ በሀገር ደረጃ በ18ኛው ክፍለ ዘመን ሁለተኛ አጋማሽ በፈረንሳይ ውስጥ ከጃኮቢኖችና ጂሮንዲንስ መገዳደል ጋር ተያይዞ ተስፋፍቷል። በደርግ ዘመን ቀይ ሽብር ተፈፅሟል። የነጭ ሽብር ምልክቶችም ታይተዋል። በዓለማችን ውስጥ በተለያዩ ስፍራዎች ቀይ ሽብር እና ነጭ ሽብር ተካሂደዋል። በዘመናችን ሉላዊነት መተሣሠር ውስጥ ሽብርተኝነት ራሱን በተለያየ መንገድ እየገለፀ ዋነኛ ስጋት የጋረጠ አደጋ ሆኗል። ለአንዱ ሽብርተኛ የሆነው ለሌላው ነፃ አውጪ ስለመሆኑ የሚነሱ እሰጥ አገባዎች የርዕሳችን መነሻዎች አይደሉምና ብንዘላቸውም፤ ንፁሐን ዜጎችን (እናቶች ህፃናት ሰላማዊ ዜጎች) መግደል ግን በመላው ዓለማዊ ሁናቴ ሽብርተኝነት ብቻ ሳይሆን ጅምላ ጭፍጨፋ ጭምር መሆኑ አምርረን እንኮንነዋለን።



t.me/OLDBOOKSPDF

በዚህም መሠረት ወያኔ ህወሓት ከአገዛዝ ዘይቤዎቿ አንዱ መንግሥታዊ ሽብርተኝነት ነበር። መግደል፣ እስር ማሰቃየት፣ መሰወር፣ ማሸማቀቅ፣ ማስፈራራት፣ ጠመንጃ የያዘ ሠራዊት ከተማ ውስጥ እንደ ጉንዳን መሰመር እየሠራ እንዲተምም ማድረግ፣ ከጠባቦች ተላላኪዎች ፀረ-ሰላም ሀይሎች ጀምሮ የሚኙርጎደጎዱ ስድቦች፣ የመረጃ መረቦችን መስበር፣ ከሥራ በጅምላ ማፈናቀል፣ አንዱን ብሔረሰብ በሌላው በማስመታት 'ካላረፋችሁ ይቀጥላል' አይነት መልእክት፣ ከተሞችን ስትቆጣጠር ምሽት እየጠበቁ ጥይት እንደ ፈንድሻ ማንጣጣት፤ በየጊዜው የ17 ዓመታት ትግል በሚል በሚዲያዎች የሚቀርቡ ከአንድ ወገን የሚተኮሱ፣ በአንድ ቋንቋ ብቻ ተዋጊዎች እየተንጫጩ ሲተኩሱ ማሳየት ... በድምሩ የከፉ የሽብርተኝነት ማሣያዎች የሥርአቱ መገለጫዎች ነበሩ። የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አመራሩ አሰፋ ማሩ በአደባባይ በጥይት መገደል፣ ዜጎች ከፎቅ ላይ ተወርውረው ላያቸው ላይ መኪና መንዳት፣ (ለምሳሌ፡- ኤቢሳ አዱኛ የኦሮምኛ ዘፋኝ ከነህይወቱ በመኪና ኋላ ታስሮ መጎተት)፣ እናት ልጇ አስከሬን ላይ መቀመጥ፣ የኢሬቻ አምልኮ ሥፍራ ታቅዶበት የተፈፀመ እልቂት ተዘርዝረው የማያልቁ ግፎች የመንግሥታዊ ሽብርተኝነት ውጤቶች ናቸው።

**3. ህገወጥ የሰዎች እና የእፅ ዝውውሮች** (Illegal Human and Drug Trafficking):- ወያኔ ህወሓታውያን በቀጥታ የህገወጥ የሰዎች ዝውውር እና የዕፅ ዝውውር (በኮንትራባንድ መልክ በመታገዝ) በስፋት አከናውነዋል። በየድንበሩ ሳይገቱ ይጓዙ የነበሩ ዜጎች እና በየኬላው ሳይፈተሹ የሚያልፉ ሸቀጦችና ዕፆች የሥርአቱ መገለጫዎች ነበሩ። በፈላሻ ስም በከፍተኛ የገንዘብ እና ሌሎች ምሥጢራዊ ድርድሮች ወደ እስራኤል የተጓዙ ዜጎች ቁጥርም ቀላል አይደለም። የኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ሰነድ ገፅ 136 የሚከተለውን ያትታል፡-

> *ከኢትዮጵያውያን ቤተ-እስራኤሎች ወደ እስራኤል መፍለስ ጋር ተያይዞ በኢትዮጵያና በእስራኤል ግንኙነት ላይ መለስተኛ ቅራኔ ተፈጥሮ የነበረ ቢሆንም ይህ ጉዳይ የኢትዮጵያ ህገ መንግሥት መሠረት ካደረገው የእያንዳንዱ ዜጋ በተናጠል በነፃ የመንቀሳቀስ መብቱን በሚያስከብር ለጓኋን አንዲፈታ በመደረጉ ቅራኔው ተወግዷል።*

የሚል ግልፅ ፊዝ አስቀምጧል። የትኛው ኢትዮጵያዊ ዜጋ በነፃ ወደሚፈልግበት የውጭ ሀገር ተንቀሳቅሶ ያውቃል? በአሥር ሺህዎች የሚቆጠሩ እስራኤሎች በቀጥታ ካእስራኤል አውቶኖሽ አውሮፕላን ከኢትዮጵያ በቀጥታ እየተጫኑ - "የእያንዳንዱ



t.me/OLDBOOKSPDF

ዜጋ በተናጠል በነፃ የመንቀሳቀስ መብት" የሚሆነው በምን ሒሳብ ነው። ቅራኔን ለመፍታት ከ2,000 ዓመታት በላይ በኢትዮጵያ የኖሩ "ካይላዎችን" - "ፈላሻ" ወይም "ቤተ እስራኤል" ብሎ መላኩ በሀገር ላይ ቁማርና ማዳከም የተፈለገው ማህበረሰብ ላይ የተነጣጠረ ሰውር ዓላማ ነበር። እንደ ውስጥ ምንጮች ከሆነ በማይገመቱ ዶላሮች ተሸጠዋል?! በዚህም መሠረት ወያኔ ህወሓት ለሀገርና ለህዝብ ደንታ ቢስ ስብስብ ስለነበረ ራብጣ እስካስገኘለት በህዝብ ከመደራደር ወደኋላ እንደማይል እንደ ማሳያ ሊወሰድ ይችላል። ከዚሁ ጋር ሆን ተብለው የሚተላለፉ በሽታዎች (Deliberately Transmitting Diseases) መሰክ የተፈፀሙ ወንጀሎችን በምክንያት አልፈናቸዋል።

## 4. የተደራጀ ታላቅ ሌብነት (Grand Corruption)

በአፈፃፀሙ ከጅምላ ጭፍጨፋ የከፋ አሉታዊ ውጤት የሚያስከትል የህወሓት የአገዛዝ ሥርአት አይነተኛ መገለጫ ነው። ምክንያቱም በከፋ መንግሥታዊ ሌብነት የተነሣ፦ በርካታ ዜጎች በስደት ከኬንያ እስከ ደቡብ አፍሪካ በተዘረጋው የብዝበዛ ሥንሰለት ምክንያት የአውሬ ቀለብ ሆነዋል፣ ከመደፈር ጀምሮ ህሊና የማይገምተው ሰቆቃ ደርሶባቸዋል። ሜዲትራንያን ባህር ውስጥ በአዞና የባህር ፍጥረታት ሲጋቸው የተቀረጠፈውን ዜጎች ባህር ይቁጠራቸው።

እስካሁን 'ከዛሬ ነገ ይመለሱልኝ ይሆን?' በሚል በተስፋ የሚጠብቀው ወገን የትየለሌ ነውና ቤቱ አይቆጥራቸውም። (*በኤፕሪል 1915 በአይሲስ የታረዱ 27 ኢትዮጵያውያን ጉዳይ በአልጀዚራ ቢቢሲ ሲኤንኤን ፕሬስ ቲቪ እና የዓለም መገናኛ አውታሮች "ኢትዮጵያውያን በአይሲስ ታረዱ" ተብሎ ሲጠየቅ የህወሓት መንግሥት የሰጠው ምላሽ 'ዜጎቼ ከሆኑ አጣርቼ ገልፃለሁ' መሆኑ ሲታሰብ - ይህቺ እናታችን ኢትዮጵያ 'ማፍያ' እየመራትም መቆየቷ የዘመናት የህዝቡ አብሮነት ላይ ፈጣሪ ታከሎበት ነው እንጂ ሌላ ምን መገለጫ ይኖረዋል?) ወያኔ ህወሓት በቢሊዮኖች ዶላር የሀገር ሀብት በውጭ ባንኮች አከማችታለች።

ሜቴክን ጨምሮ የታላላቅ ኩባንያዎች ዝርፊያ፣ በጉምሩክ፣ አየር መንገድ፣ ቴሌ፣ የኤሌክትሪክ ኃይል እና ጨረታዎች የተፈፀሙ የቢሊየኖች ዝርፊያዎች፤ ትውልድ ሊከፍለው አይችል የነበረ የቻይና ብድሮች፣ ህገወጥ የዶላር ንግድና ተዛማጅ ወንጀሎች (Money Laundering)፣ መንግሥት በ2018 በይፋ የገለፀው የታወቀ



t.me/OLDBOOKSPDF

በአሥር ዓመታት ውስጥ ብቻ የ50 ቢሊየን ዶላር ከሀገር ማሸሽ ብቻ ሳይሆን ሥርአቱ ራሱ በተደጋጋሚ በሌብነት መብከቱን ይገልፅ ነበር። (*በከት የሚለው ቃል ወያኔ ]ወሓት ራሱን የገለፀበት ነው።)

. **የከፋፍለህ ግዛው መርሆ** ("Divide and Rule Policy"):- በቅኝ ግዛት ዘመን ]ሪታንያ ያላት የሰው ኃይል አነስተኛ በመሆኑ ሳቢያ ታራምደው የነበረው ዘዴቢ ፋፍሎ መግዛት ነበር። ወያኔ መሠረት አድርጋ የቆየቺው አንዱ ችካል አሮሞና ማራን ማለትም 2/3ኛ ገደማ የኢትዮጵያ ህዝብ በዋናነት በአንድ በኩል፣ ሔረሰብን ከብሔረሰብ እና የአንድን ቋንቋ ተናጋሪዎች እርስ በርስ ማናከስ በሌላ ኮል የታየ ነበር።

ላይ የተዛባ ታሪክን መሣሪያ በማድረግ በአማራና በኦሮሞ መሀከል ከፍተኛ ግጭት ፎጠራቸውን በቅርበት ያጤኑት ጉምቱ የፖለቲካ ሳይንስ ምሁር ፕሮፌሰር መረራ ና:- "አማራ እና ኦሮሞ ቢተባበሩ ወያኔ በተቅማጥ ታልቃለች" ማለታቸው ኔታውን አስከፊነት በመገንዘባቸው ነው። ወያኔ እንደ ዳማ ጠጠር እየገፋቻቸው ሞና አማራን በማጋጨት የወያኔን ተልዕኮ የሚያስፈፅሙትን የኦህዴድ (ኦዴፓ) ራሮች የታዘቡት እኚሁ ፕሮፌሰር:- "ማታ ማታ አማራ ሚስቶቻቸውን አቅፈው ሩ፤ ቀን ቀን ኦሮሞና አማራን ያጋጫሉ" ሲሉ ጠበቅ አድርገው ገስፀዋል።

ው በርግጥም እጅግ የሚያሳዝነው ወላጆቻችን ባቆዩን የዘመናት የማይበጠስ የኦህዴድ / ኦዴፓ አመራሮች አማራ ሚስቶችን አግብተው ልጆች አፍርተዋል። ም ከወንድም፣ እህት ከእህት ማናቆራቸው ግን ያሸማቅቃል። በሌላ ገፅ ወያኔ ወድቅ ከፍተኛውን ሚና የተጫወተው "የኦሮማራ ጥምረት" (የኦሮሞና ጥምረት) በወቅቱ የሀገሪቱ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን -2018) የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር አቶ ገዱ ቸው የተመሠረተው "ቲም ገዱ" እንዲሁም በተመሣሣይ ወቅት የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር በነበሩት አቶ ለማ መገርሣ እና የአሁኑ ማኒስትር ዶክተር ዓብይ አህመድ (2018 - ...) የተፈጠረው "ቲም ለማ" ነበር። ለወያኔዎች 'የፈሩትይደርሳል - የጠሉት ይወርሳል' ሆነባቸው።

**ሀብታዊ የበላይነትን መመሥረት**:- ወያኔ ህወሓት የበላይነቷን በሁሉም ገረጋገጥ የተለያዩ ዘዴዎችን ቀይሳ ተግባራዊ አድርጋለች። በተለይም



t.me/OLDBOOKSPDF

የምጣኔ ሀብቱን ምንጭ ጠቅልላ በእጇ ለማስገባት ረቂቅ ስልቶችን በመንደፍ ተግበራለች፡፡ በተደራጀ ሌብነት ሥር የገለፅነው እንዳለ ሆኖ አባ ዶዮ ዘጂጋማ የተባለ ፀሐፊ፡- "የዓባይ አዳ" በተሰኘ ጠማፉ ከገፅ 104-105 ያሰፈረውን አኅዛዊ መረጃ •በቋሚ ንብረት የተገለፀ እና እንዳለ የቀዳነውን እንመልከት፡-

1. *መሰቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ ቁ.1 = 3.467 ቢሊዮን

2. መሰቦ ሲሚንቶ ቁ.2 = 4.395 ቢሊዮን

3. *ሱር ኮንስትራክሺን= 4.179 ቢሊዮን

4. *ትራንስ ኢትዮጵያ 650 መኪኖች= 2.934 ቢሊዮን

5. *መሥፍን ኢንደስትሪያል ኢንጂነሪንግ መቀሌ= 2.500 ቢሊዮን

6. መስፍን ኢንጂነሪንግ ቃሊቲ እና ዱከም= 2.643 ቢሊዮን

7. ጉና ኮርፖሬሺን በመላው ኢትዮጵያ 23 ቅርንጫፎች= 5.412 ቢሊዮን

8. *ሜጋ ኮርፖሬት= 1.2 ቢሊዮን

9. *ውቅሮ ሳባ ቆዳ ፋብሪካ= 600,000,000

10. አዲግራት መድኃኒት ፋብሪካ= 700,000,000

11. ኢዛና የወርቅ ማዕድን= 910,000,000

12. ብሩክ ተስፋ ላስቲክ ፋብሪካ= 480,000,000

13. ማይጨው ቾፒድ ፋብሪካ =746,000,000

14. ሀይወት እርሻ ሜካናይዜሺን= 820,000,000

15. ተከዜ ፕልቅ ጉድጓድ ቁፋሮ= 437,000,000



t.me/OLDBOOKSPDF

16. ኢድዋ አብነ በረር ፋብሪካ = 790,000,000

17. ኢድዋ ጨርቃጨርቅ ስፌት ፋብሪካ = 315,000,000

18.ኢድዋ ጨርቃጨርቅ ቁ.1 ፋብሪካ = 1.757 ቢሊዮን

19. ኢድዋ ጨርቃጨርቅ ቁ.2 ፋብሪካ = 1.917 ቢሊዮን

20. መስፍን ኢንጂነሪንግ ትናንሽ መኪና መገጣጠሚያ = 350,000,000

21. ስታር መድሐኒት አስመጪና አከፋፋይ = 150,000,000

22. ደደቢት ብድር እና ቁጠባ = 6.25 ቢሊዮን

23. TCA. የተሸከርካሪ ጎማ አከፋፋይ = 560,000,000

24. ሁመራ ጥጥ መዳመጫ = 200,000,000"

አባ ዶዮ ዘጁጋማ ያልጠቀሳቸው ካምፓኒዎች፣ ኮርፖሬሽኖች፣ ሪል እስቴቶች፣ ግዙፍ እርሻዎች እና ታላላቅ የንግድ ተቋማት የምጣኔ ሀብትን በመያዝ ሌሎችን ተገዢ የማድረግ ታላቅ ደባ ነው። ወያኔ ህወሓት በሰነዶቿ በሙሉ "ነጭ ካፒታሊዝምን እያራመድን ነው" የሚለው ድፍረት የተሞላው አገላለፅ ብትደነግርም እርስ በርሱ በሚጣረሰው - "መንግሥት በተመረጡ መስኮች ጣልቃ ይገባል" መርሆ በመጠቀም "ነጋዴ መንግሥት" መሥርታ የኢትዮጵያን አንጡራ ሀብት መዝብራለች።

ማዕከሏ የትግራይ ህዝብ ባይሆንም በስሙ ከምትነግድበት ህዝብ አመኔታ ለማትረፍ የሚያጋጥማትን ተቃውሞም ለመቀነስ አንፃራዊ "የትግራይ የበላይነት" እንዲኖር አበክራ ሠርታለች። ከበርካታ መገለጫዎች የተወሰኑትን ለማሣየት፦ ትግራይ ለብሔራዊ ባንክ ቁጥር አንድ ወርቅ አቅራቢ እንድትሆን በማድረግ በምትኩ ሠፊ ገንዘብ ከባንኩ እንድታገኝ ተሠርቷል። ዋነኞቹ የወርቅ ምንጮች ግን ሻኪሶ እና ወለጋ መሆናቸው ይታወቃል። የአፋር ጨው፡ ከ85 እጅ በላይ በትግራይ ባለሀብቶች እጅ መሆኑን የክልሉ ተወላጅ የሰብአዊ መብቶች ሊቀ መንበር አቶ አህመድ ገአስ ከኢሳት ቴሌቪገርን ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ገልፀዋል። ወልቃይትና ራያን ከአማራ ክልል



t.me/OLDBOOKSPDF

በመንጠቅ የሁመራን ሰሊጥና የአካቢውን ሀብት መቆጣጠራቸው ሌላው የገሃድ በዝባዥነት መገለጫ ነው።

በኢንቨንትመንት ገመናው አና የጋምቤላ ሠፋፊ መሬቶች እና የሀገራችን ታላላቅ የአበባ እርሻዎች ለትግራይ ባለሀብቶች በገፍ ቀርበዋል። በደሉን የሚያጎላው ቱጃሮች ገንዘቡን ሠርተው ያገኙት ሳይሆን በስርቆትና ከባንክ ብድር እየተመቻቸላቸው በአቋራጭ ያገኙ ስለነበር ነው። ለምሳሌ:- የ"ኤድና ሞል" እና በስማቸው የተከለ በርሀን አምባዬ ኮንስትራክሺን" ባለቤት 4 ቢሊዮን ብር ብድር ከባንክ ተመቻችላቸው ስለመሆኑ ይፋ መንግሥታዊ መረጃ አረጋግጧል። በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ንብረትነታቸው በአብዛኛው የስልጤና የጉራጌ የነበሩ ሱቆች በአቅድ እሳት እየተለኮሰ እንዲቃጠሉ ተደርጎ ቤሳ ቢስቲን ያልነበራቸው ከከፍተኛ እስከ መካከለኛ ንግድ እንዲቆጣጠሩ መንገድ የተጠረገላቸው የትግራይ ተወላጆች በደሀ ሀብት ላይ ሀንፃ ሲቆልሉ ተስተውሏል። ከዚሁ ጋር ነባርና የደረጁ ሠፈሮችን ማህበራዊ መስተጋብር ለማጥፋትና የኢኮኖሚ የበላይነትን ለማጠናከር ልደታ ቂርቆስ ካዛንቺስ አራት ኪሎ እና በከተማዋ የተለያዩ ክፍሎች የሚገኙ ደሆች ቤታቸውና ኑሯቸው ፈርሶ የትም ሲበተኑ የሚጮህላቸው የብሔረሰብ ድርጅት ባለመኖሩ እንባቸው በለሆሳስ ፈስሷል።

በተመሣሣይ አዲስ አበባ ዙሪያ የነበሩ ገበሬዎች ከጀሞ፣ ሀና ማርያም፣ ቡልቡላ፣ ለሚ፣ ሲኤምሲ ከስድስት እስከ ስምንት ብር በካሬ ሜትር ተወርውሮላቸው በመፈናቀል ሜዳ ላይ ሲወድቁ በምትኩ ከ90 እጅ በላይ የትግራይ ብሔር አባላት በስፍራው መኖሪያ ቤቶችና ታላላቅ ህንፃዎችን ሠርተው እንደሚኖሩ በጉልህ መሬት ላይ የሚታይ እውነት ነው። (ይሁንና ድርጊቱ የሥርአት በደል እንጂ ከህዝብ ጋር እንዳች ግንኙነት የሌለው መሆኑ መታወቅ አለበት። ከሁሉም በላቀ ደረጃ እንደ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ወገናቸው ላባቸውን አንጠፍጥፈው ሀብት ያፈሩ የማይናቅ ቁጥር ያላቸው የትግራይ ተወላጆች መኖራቸው የማይታበል እውነት ነው።)

የምጣኔ ሀብት. የበላይነት መፈጠሩን አስመልክቶ በግልፅ የታዩ በደሎች በምሬት ከተገለፁበት አግባብ የሚጠቀሱት:- "ቶላ ቡና አብቃይ ሐጎስ ቡና ላኪ"፤ "እውላቸውና መገርሳ ሟች፣ ኪሮስ ገዳይ፣ ገብረመድህን ቀብር አስፈፃሚ" ... በሞታቸውም የማትረፍ መራራ ሀቅ። (*የዚህ መፅሐፍ አዘጋጅ ገበሬዎች ከመኖሪያ ቤታቸው በተፈናቀሉበት ወቅት ካሳ ተብሎ ዓመት የማያደርስ ገንዘብ ተሰጥቷቸው ከነቤተሰቦቻቸው ሜዳ ላይ ከሚበተኑ ለእያንዳንዱ አባ ወራ በነፍስ ወከፍ ሁለት



t.me/OLDBOOKSPDF

ቢ.ያንስ ባለ ሁለት መኝታ ከፍል ተሰጥቶ፤ አንዱን አከራይቶ በአንዱ ከቤተሰቡ ጋር መኖር ይችላል በሚል በተከታታይ መድረኮች፤ በተለይ የሰላም ልማትና ዴሞክራሲ ፎረም" አዘጋጅነት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እስከ ሸራተን አዲስ በተካሄዱ መድረኮች ምከረ ሀሳብ አቅርቧል።)

**7. ማህበራዊ ዴሞክራሲ** / Social Democracy፡- በማህበራዊ ዴሞክራሲ "ሰዎች በሙሉ በህግ ፊት እኩል ናቸው" ብሂል በወያኔ ሥርአት ፈፅሞ የሚታሰብ አልነበረም። "አኒማልስ ፋርም" በተሰኘው የጆርጅ ኦርዌል ታዋቂ መፅሐፍ ላይ፡- "እንስሳት ሁሉ እኩል ናቸው፤ አንዳንድ እንስሳት የበለጠ እኩል ናቸው" ሽሙጥ ቢወሰድ ለበሸቀጠው አገዛዝ ማሳያ መስታወት ሆኖ እውነታውን ያስረዳል። በሌላ በኩል በሥርአቱ ማብቂያ 2018 የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ባዘጋጀው ዓመታዊ መፅሔት "Bu'aa Geengoo Qulqullina Barnootaa" ገፅ 2 ላይ በታችኛው የከፍል ደረጃ የትምህርት ሽፋን የሚከተለውን ይመስል ነበር።

1. *የትግራይ ክልል 93.2 ፐርሰንት*
2. *ሐረሪ 90.2 ፐርሰንት*
3. *አማራ 45.1 ፐርሰንት*
4. *ቤኒሻንጉል ጉሙዝ 40.1 ፐርሰንት*
5. *ኦሮሚያ 31.9 ፐርሰንት*
6. *ጋምቤላ 25.9 ፐርሰንት*
7. *አፋር 11.7 ፐርሰንት*
8. *ሶማሊ 7.4 ፐርሰንት*
9. *ደቡብ ብ/ብ/ህ/ክ 72.2 ፐርሰንት*



t.me/OLDBOOKSPDF

ከላይ ከቀረበው መረጃ በግልፅ የአማራና የኦሮሚያ አቻዎቹ ደግሞ ከ45 እጅ በታች ነበር። የአማራ መገናኛ ብዙኃን ድርጅት በ2018 የክልሉን መንግሥት ጠቅሶ በቀረበው መረጃ የአማራ ክልል የጤና ሽፋን ትግራይ አቻው ላይ ለመድረስ ተጨማሪ 250 ሆስፒታሎችን መገንባት ይጠበቅበታል። የአማራ ክልል በህፃናት መቀንጨር ከዓለም የመጀመሪያውን ደረጃ መያዛቸው ከመነሻው የገለፅናቸው ደባዎች አካል መሆኑን ያስረግጥልናል። በኦሮሚያ ሻኪሶ አካባቢ የወርቅ ማዕድኑ ኬሚካል ባስከተለው መዘዝ የኦሮሞ ንፁሐን ህፃናት ቦርቀው ሳይጠግቡ የዛሬም የነገም ህይወታቸው መቀማቱን በሥፍራው ከተደረጉ ምሥጢራዊ ጥናቶች የተገኙ ምስሎችን በመመልከት ማረጋገጥ ከመቻላችን በላይ በማህበራዊ ትሥሥር ድረገፆች (2018) ይፋ አድርገናል።

በድምሩ በመሠረተ ልማት፣ በጤና ዘርፍ፣ በትምህርት ተደራሽነት እና በተለያዩ ማህበራዊ አገልግሎቶች የሠፋ ልዩነት ታይቷል። ለምሳሌ:- ከነጌሌ ቦረና ከተማ በተሰበሰበ ሀብት ትግራይ ውስጥ "ነጌሌ ቦረና ትምህርት ቤት" ሲገነባ - ነጌሌ ከተማና ዙሪያዋ ግን በቂ የትምህርት ቁሳቁስ አልነበራቸውም። ከሻኪሶ በገፍ ወርቅ እየተዛቀ በአንፃሩ የረባ የመንገድ መሠረተ ልማትና የጤና አገልግሎት ድጋፍ በቦታው አልነበረም።

8. **የፖለቲካ ዴሞክራሲ** / Political Democracy:- ፖለቲካው በሙሉ የሚዘወረው ከኢትዮጵያ ህዝብ ከስድስት እጅ ከማይበልጠው የትግራይ ህዝብ በወጡ (የትግራይን ህዝብ የማይወክሉ) ጉጅሌዎች ነበር። የጋንታዎቹ መሪዎች በሀገሪቱ እጣ ፈንታ ዙሪያ በህወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ እስኪወስኑ ድረስ አሻንጉሊቶቹ ኦህዴድ (ኦዴፓ)፣ ብአዴን (አዴፓ)፣ ደኢህዴን እና አጋር ድርጅቶች ምን እየተካሄደ እንደሆነ እንኳ በወጉ አያውቁም። ወያኔ ህወሓት ፈጭታ አቡክታ ጋግራ ያቀረበችው የትኛውም ውሳኔ 'አረረ መረረ' ጥያቄ ሳይነሳበት "ተሠሪዎቹ" በሚተላለፍላቸው ትእዛዝ መሠረት "ዝለሉ" ሲባሉ "እስከየት?" ከማለት ባለፈ የመቃወም፣ የማሻሻል፣ የመከለሥ እና መሠል ሚናዎች የላቸውም። እንደ በቀቀን የተነገራቸውን መልሰው በተገቢው መንገድ ማስተጋባት የቻሉ የሹመት እድሎች ይመቻቹላቸዋል።

የፖለቲካ ብቃት መለኪያ "በህወሓት ማመን" ነው። 'እስከደገፈን ማይምም ቢሆን መምራት ይችላል' የማደንዘዣ መርፌ ሆኖ እስከ ወያኔ ውድቀት ዋዜማ አገልግሎ ነበር። ዙሪያውን በደካሞች ተከብቦ ብርቱ የመሠለው የአድሜ ዘመን መሪያቸው



t.me/OLDBOOKSPDF

መለስ በሞት ሲለይ የሠራው የአንባይ ካብ መናዱ ከጅምሩ የሚጠበቅ ነበር። 'ዝንጀሮ ወደ ላይ ከፍ ባለን ቁጥር መቀመጫችን ታየ' እንዳለችው ሊቀ ሰይጣኑ ሲለየው የደደቢት በዓለማችን ተሞክሮ የማያውቀውና ግራ የገባው "አብዮታዊ ዴሞክራሲ" በአንድ ጭንቅላት የተደረሰ፣ የሚመራ፣ የሚወሰን፣ አቅጣጫ የለሽ የተመሰቃቀለና የጨረባ ተዝካር የሚሉት አይነት ስለነበር ባዶ ፍልሰፍና እንደመሆኑ እርቃኑ ተገለጠ። ከማገባት - ማሌሊት - ህወሓት እንደ እርጥብ ቂጣ እየተገለባበጠ ከ1970ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ የተተከለ የአልባኒያ ሶሻሊዝም እምነት ድንገት በ1990 ዋሺንግተን በተደረገ የአንድ ቀን ውይይት ይቀየራል ብሎ ማሰብ ከየዋህነት የዘለለ ሞኝነት ነው።

9. ባህላዊ ዴሞክራሲ / Cultural Democracy፡- ባህል ሠፊ እና ፈርጀ ብዙ ዘርፎችን ያካተተ ፅንሰ ሀሳብ ነው። በውስን ዕይታ በግልፅ ለማሳየት እንደሚቻለው ወያኔ ላይ ላዩን ሲመለከቱት የማይረዱት፣ ጠልቀው ሲበረብሩት የሚያሳዝን በረቀቀ ንኮሎች የሚመራ አደገኛ ባህልን የመናድ ሴራ ይፈፅም ነበር። ለምሳሌ፦ አለባበስ በኩል የትግራይ ሴቶችና ወንዶች ፀአዳ ለብሰው፣ በወርቅ ተንቆጥቁጠው፣ ኩለውና አምረው በሥልጣኔ ጎልምሰው በየመድረኩና በቴሌቪዥን መስኮት ከሰቱ፤ የኦሮሞና አማራ ዘፋኞች በካኪ፣ ሻማ፣ ሱቲ፣ 'ጎጃም አዘነ' እና መናኛ ገሀላቸው ባፈነገጠ አለባበስ ፈገዘው ይታዩ ነበር።

ጉቱ የሚፈፀመው አዘጋጅ ለሚባሉ ግለሰቦች የተዛባ አስተምህሮ በመትከል ነው። ልብ ለሚመለከት ወገን የጉዳቱ መጠን ግልፅ አይሆንም። ኢህአዴግ የተባለው ነሙላ ድርጅት በመዲናዋ በዓሉን ባከበረ ቁጥር የሌሎች ብሔረሰቦች ዘፈኖች ፈኑ በተወሰኑ ግለሰቦች ፍላጎት ብቻ በጥቂት አጃቢዎች ተቀንቅኖ የትግርኛ ዘፈን ፈት ደግሞ 'አዋራው ጨሰ' በሚያስብል ስሜት ከዳር እስከዳር ሁሉም ሊባል ችል ደረጃ ጭፈራውን ያስነካዋል። 'ምነው በባህልህ ሳትዘፍን አሁን እንደ ፈንጣ ህ?' ከተባለ 'ትግርኛ ቀላል ስለሆነ ነው' በማለት ይመልሳል። ይህንን የተዛነፈ ነት ለማስተካከል ሁሉንም ብሔረሰብ በአንድ አይነት ዐይን በመመልከት ትና በብሔረሰቦች አለባበስ ላይ በቂ ጥናት ተደርጎ መነሻውን ሳይለቅ መከወን ።

ቁሳቁሶች፣ ቅርሶች፣ "ራስ ደጀን ተራራ ጭምር ትግራይ ደርሶ መመለሱን" ት ገፆች ውስጥ በስህተት መስለው የተደነጎሩ የመዝረፍ ፍላጎት ያዘሉ ዮች፣ እስከ ደርግ ጊዜ ከሱዳን ማትዋሰነው ትግራይ "ጋምቤላና ቤኒሻንጉል



t.me/OLDBOOKSPDF

...ምንም አካትታ ድንበሯን ከሱዳን ለብቻዋ ተጋርታ"፤ ኤርምያስ ለማሪያን ከሱዳን ...እንደሚሰጡት የገደበው እና በውስጥ አዋቂዎች (በትክክል በምርጫ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን ሚኒስትር ደኤታ በነበረው) ኤርምያስ ለገሰ ጭምር የተጋለጠው የምስጢራዊ ካርታ ካነበብነው አብዛኛው የሚነገረን እውነት እለ።

10. አሸንፋሊት ተቋማት :- የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፡- የተወካዮቹ ...ምርጫ እንዳለመሆኑ በደነዘዘ ስብሰባ ንቁ ተሳትፎ ያደረጉባቸው ...አስታውቀዋል። በመስኮት ምሥል እንደታዘብነው የሚከፈላቸው ስወካዮቹ ህዝብ በመሆን ሳይሆን በማንቀላፋት፣ በማጨብጨብና እጅ በማውጣት ችሎታ ይመዘኑ ነበር። ተፅፎ የተሰጣቸውን ጥያቄ መቶ ጊዜ አጥንተው በንባብ ለማቅረብ ሲቸገሩ ...አይ ኢትዮጵያ ያልገባቸው ቀናት ጥቂት አልነበሩም። ፍርድ ቤቶች፡- ህጊና ...ማስረጃን አቀናጅተው ከመወሰን ይልቅ ሌሊት እስር ቤት ገብተው ከፖሊስ ጋር ሲገርፉ አድረው ቀን ቀን 'ማታ ያልከውን አልደገምህም' በሚል ስሜት የሚፈርዱ ሆኑ።

በህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም፡- የህዝብ ዕንባ እንዳይፈስ ቀድሞ ሲከላከል ቀርቶ ዜጎች ደም ዕንባቸው ጉንጫቸውን እየገመሠ እንዲወርድ የመንግሥት ተባባሪ ነበር። የሰብአዊ መብት ኮሚሽን፡- ለይስሙላ የተቋቋመ ሰብአዊ መብቶች ሲደፈጠጡ ሽፋን የሚሰጥ፣ የሀሰት ሪፖርቶችን በማዘጋጀት እንደ አምነስቲ ኢንተርናሽናል አይነት ድርጅቶች የሚያቀርቡትን ሪፖርቶች በማጣጣል ለመንግሥት ከንድ የሚሆን 'የሰብአዊ መብቶች አስጣሽ' ድርጅት ነበር። (*በሥርአቱ መውደቂያ አካባቢ 2017 ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተድበሰበሰ ሪፖርት አቅርቦ የነበረ ቢሆንም እንደማይተገበር እያወቁና ለ12 ሰአት ሩብ ጉዳይ ነበር። ተቆርቋሪ ነን ካሉ ለምን እነዳቸው እንኳ ከሥልጣን ለመልቀቅ ጥያቄ አላቀረቡም?) ምርጫ ቦርድ፡- ኮሮጆ የሚያስገለብጥ፣ የህዝብን ድምፅ የሚነጥቅና በደሎችን ባላየ በማለፍ ሳይወሰን በንግግሩ በዜጎች ቁስል እንጨት የሚሰድድ ነበር።

11. ደካማ ልሂቃን፡- ምሁራን፡- በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ አሉ የሚባሉ ምሁራን በደርግ ፖለቲካ የተቃውሞ ወይም የድጋፍ ጎራ፡- ኢህአፓ/ ኢህአወሊ ጠቅላዩ ማርሴዊህ መኢሶን ኢጭአት ኢላትአማ ኢሴትአማ ሰደድ ኢዲዩ እና የተለያዩ ድርጅቶች ውስጥ ተሻኩተው የከሰመው ረገፈ። ባለተራውም ወረፋው ሲደርስ መከነ። የመበላላት ፖለቲካ ያስጠላው ወገን 'ፖለቲካና ኤሌክትሪክን በሩቁ' በማለት ዳር ሆነ። ሚዛናዊው ምሁር የነገሮች አካሄድ ቆሽቱን እያሳረረው ማጉተምተም ካልሆነ



t.me/OLDBOOKSPDF

የግንባር ስጋ መሆኑ ዋጋ እንደሚያስከፍል ታዘበና አርምሞን መረጠ። የታገለው የሀሊና እስረኛ ወይም ስደተኛ ሆነ። የተረፈው የወያኔ ህወሓት ተላላኪ ሆኖ እንዳጨበጨበ ቀጠለ። 'የሀይማኖት አባቶች':- ኡስታዞችንና ገዳማውያንን እስር ቤት እየላኩ በለየለት ካድሬነት ውሎ አዳራቸውን በየስብሰባ አዳራሹና በየሆቴሉ የመንግሥት ዘቲ መከፈልትና መህራ በመከጀል ህሊናቸውን አጉድለው ሆዳቸውን የሚምሉ ሆኑ። 'የሀገር ሽማግሌዎች':- ወደ መንግሥት ሽማግሌነት ወርደው ሽመል የሚያቀብሉ፣ ሽበታቸው ሺ ውብት ከመሆን ይልቅ የእንጨት ሆነ።

**12. ግለ ስብእናን መገንባት / Personality Cult:-** የሶሻሊስት መሪዎች አይነተኛ መገለጫ ከሆኑ ማሳያዎች አንዱ የመሪዎችን ግለ ስብእና መኳል ነው። ለራሳቸው የማርክስ ኤንግልስ እና ሌኒን ደቀ መዛሙርት ቦታ የሰጡት ማኦ ሴቱንግ፣ ጆሴፍ ስታሊን እና ፊደል ካስትሮ በብዙዎች ህሊና የማይጠፉ ነበሩ። መለስ ዜናዊ እንደ አልባኒያ ሶሻሊስት አቀንቃኝነቱ ከተጠናወተው አስመሳኪነት ጋር ወደ መቃብር ወርዶም ሳለ "መለስ አልሞተም" ህዝቡን አደንቁሮት ነበር። ከነገሥታት እስከ ፓትርያርኮች በተቀበሩበት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ከሙታን ብቻውን ተለይቶ በታንክ የመጠበቁ ምስጢር ምን ይሆን? በተመሣሣይ ወቅት የሞቱት ፓትርያርክ አስከሬን ሲታይ የመለስ ፊት አለመታየቱ ሁልጊዜም ጥያቄን ያጭራል። ዞሮ ዞሮ 'መለስ የህዝብ ልጅ'፣ 'ባለራዕዩ መሪ'፣ 'የህዳሴው መሀንዲስ' ያልወጣለት የዳቦ ስም አልነበረም። 'አፍ የሌለው አፌ ጉባዔ፣ አቅም የሌለው አቅም ግንባታ'፣ ይዞ 'ደግ ታሪክ የሌለው ታሪክ አጥፊ' ሆነና አለፈ። ራዕዩን ሜቴክ በላው። በተንኮል የገነባው ዝናና ስም ብዙም አልዘለቀም። እንደተጠላ ኖሮ እንደተረገመ የሞተ መሪ መዝጊያችን ሆነ።

**13. የትምህርት ሥርአቱን መግደል:-** ወያኔ ህወሓት የትምህርት ሥርአቱን የመግደል ሥራን የጀመረቺው ሀገር አንጡራ ሀብቷን አፍስሳ ያፈራቻቸውን አንቱ የተባሉ 42 ምሁራን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በማባረር ነበር። በመቀጠል የዩኒቨርሲቲዎች ሹመት ሳይቀር በፖለቲካ ወገንተኝነት ሆነ። መምህረ ጉባዔ ለመሆን የኢህአዴግን የዘወትር ጸሎት መቀበል መለኪያ ሆነ። የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን በይፋ 'ስትመረቁ ኮብልስቶን ትፈልጣላችሁ' በማለት ማሸማቀቅ፣ መምህራን ከብር እንዲያጡ በአደባባይ "ዋልጌ" ተባሉ። ለአህዳዊ ትምህርት ምቹ ሁኔታ በሌለበት በአንድ መምህር ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍል በማስተማር ተማሪን መግደል ተጀመረ። በአሥረኛ ክፍል ፈተና ከፍተኛ ውጤት ያመጡ ወደ መሠናዶ፣ መሀከለኛ ውጤት ያስመዘገቡ ወደ ቴክኒክና ሙያ፣ ዝቅተኛ ውጤት የያዙ ወደ መምህርነት መላክ ጀመሩ። ትምህርት ጸሀፊት



t.me/OLDBOOKSPDF

ቤቶች በጀማሪ መምህር፣ ትምህርት ቤቶች በካድሬዎች መመራት እጣ ፈንታቸው ሆነ።

በየጣልቃው ስለትምህርት ጥራት ሳይሆን ምኒልክ ላይ ጀምሮ ደርግ ላይ የሚያቆም ፖለቲካ የመወያያ ርዕስ ሆነ። ማይነበብ ጋዝ ጋዝ የሚል ልሳን እየዞረ መገምገሚያው 'ልሳን ወስደሀል?'፣ 'ወርሀዊ መዋጮ ከፈልሀ?'፣ መምህሩም በፖለቲካ አቋሙ ደረጃ ይቀመጥለት ጀመር። ለአቅመ ፖለቲካ ያልደረሰው ተማሪ በወጣት ሊግ ታቅፎ ከስነ ዜጋ መምህሩ ጋር ስለ 'ሴኩላሪዝም' ትምህርት ቤት ከሀይማኖትና ከፖለቲካ ነፃ ነው ተብሎ ሠሌዳ አጠገብ እንዳልተማማሉ "10ኛ ጨ" ከፍል ተሰብስበው በ1 ለ 5 ይወያያሉ። ኩረጃ ዐይን አወጣ። መምህሩ ከ50 በታች ውጤት ከመዘገበ 'ለምን አላበቃኸውም?' ስለሚባል ለተማሪው 50 ከሙቶ ሰጥቶ (አሽሮ) ይገላገላል።

በትምህርት ቤቶች ዙሪያ ከሜት ቤት እስከ ቀን ራቁት ጭፈራ ቤት በአዋኪ ነገር ይምላል። (ነጋዴዎቹ ከህወሓት ሰዎች ጋር የተሳሰሩ ስለሆኑና ትውልድ መግደል ስለሚፈለግ መረር ያለ እርምጃ አይወሰድም።) በትምህርት ቤት ግቢ መምህሩ አጣቃሽ መፃህፍት ፈልጎ፣ አስተዋፅዖ አውጥቶ፣ ከተማሪው ተማክሮ ለለውጥ ሊታትርበት ይገባ የነበረ ሰአት - ቻይና ኮርያ ሲንጋፖር ደርሼ መጣሁ ባለ ያልገባው ባለሥልጣን፦ ውጤት ተኮር፣ ቢፒአር፣ ቢኤስሲ፣ ፖርትፎሊዮ፣ ሲፒዲ፣ ካይዘን፣ ደሊቨሮሎጂ ... እየተባለ አሣሩን ይበላል። ለምን ለውጥ አልመጣም? ለሚለው ጥያቄ መልሱ "የአፈፃፀም ችግር ነው"፤ ለዓመታት የአፈፃፀም ችግር? ካልተፈፀመ ለምን ይጀመራል?

**14. የማጎሪያው 'ካምፕ'** (Concentration camp)፦ በዓለማችን የተፈፀሙ አሰቃቂ ግፎች እና ያልተሰሙ ከስተቶችን ያስተናገዱት ልዩ ሲያሎች የወያኔ ህወሓት እስር ቤቶች ነበሩ። የእስር ቤቶቹ አደረጃጀቶች ሲታይ የየዞኑ ሃላፊዎች መቶ ፐርሰንት ሊባል በሚችል ደረጃ በትግራይ ብሔር አባላት የተያዙ ናቸው። በእስር ቤት ቆይተው የወጡት የትግራይ ተወላጅ ታዋቂ ፖለቲከኛ ዶክተር ኃይሉ አርአያ እንደተናገሩት፦ "በቆይታዬ ምርመራ ያካሄዱብኝ 27 ሰዎች በሙሉ ትግርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ናቸው። እኔ የራሴ ብሔረሰብ አባላት ሆነው እንዲህ ከጎፈነነኝ ሌሎች ብሔረሰቦች ምን እንደሚያስቡ ሳሰላስል ዘገነነኝ" በዚህ ድባብ ውስጥ የሚከተሉት ግፎች መፈፀማቸውን ከመንግሥት ሚዲያዎች፣ ከቃለ መጠይቆችና ራሳችን በአካል



t.me/OLDBOOKSPDF

ካገኘናቸው የዋልድባ ገዳም መነኮሳት፣ ጨለማ ቤት ታስረው ከነበሩ ሙስሊምና ክርስቲያን ወገኖቻችን ያገኘነውንና ይፋ መረጃዎችን መሠነድን መረጥን።

ዜጎች ከዱር አውሬዎች ጋር አብረው ታስረዋል። የወንድ አካላቸው ላይ ከባ ተንጠልጥሎ የዘር ፍሬያቸው ፈስሷል፣ መክነዋል። በግብረ ሰዶም በተመሣሣይ የታ ተደፍረዋል። ሴት ወንዶች አፍ ላይ ሸንታለች። ሴቶች እርቃናቸውን እየሄዱ መሣለቂያ ሆነዋል፣ ተደፍረዋል፣ በማህፀናቸው ብረት ገብቷል። ዜጎች ተዘቅዝቀው ተሰቅለዋል። የእግርና የእጅ ጥፍሮቻቸው በፒንሳ ተየቅለዋል።

የአማራና የኦሮሞ ልጆች በማንነታቸው ተሰድበዋል፣ ተዋርደዋል። ወፌ ላላ በሚባለው የግርፍ መንገድ 'ቶርቸር' ተፈፅሞባቸዋል። ውሀ ውስጥ መድፈቅ 'ወተር ቦርዲንግ' የመዝፈቅ ወንጀል ተፈፅሞባቸዋል። ልባቸው ላይ በጫማ ተረግጠው ደም ተፍተው ሞተዋል። ህክምና ተከልክለው እግራቸው ተቆርጧል። እሳት ተለኩሶ ከእሳት ሲሸሹ በስናይፐር ተደብድበዋል። በእሳት ተለብልበው ህይወታቸውን አጥተዋል። ማታ እንዳይተኙ እጅና እግራቸው በተቃራኒ አቅጣጫ ተወጥሮ ታስረዋል። ጨለማ ቤት ተወርውረዋል። በድብደባ ሳቢያ ዐይናቸው ፈርጧል።

የአምልኮ ሥርአታቸውን ተከልክለዋል። ከመንግሥት እስር ቤቶች ውጪ የግል ማጎሪያ ካምፖች ተዘጋጅተው ዜጎች የስቃይ ሰለባ ሆነዋል። በነዚህ ድርብርብ ሰቆቃዎች ምክንያት አዕምሯቸውን የሳቱ በርካቶች ናቸው። በማጎሪያው ካምፕ ተዘዋዋሪ ተፅዕኖ የህይወት ዋጋ ከከፈሉት ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ የእጅ አምባር ሲጠለቅላቸው ሲገባ ካቴና እጃቸው ላይ እስካጠለቁት ፕሮፌሰር መረራ ጉዲና ለነፃነት በተደረገ ትግል ዋጋ ተከፍሎበታል። ለወገናቸው ክብር ሲሉ ስቃዩን የተቋቋሙ ያልተዘመረላቸው ጀግኖች ከብራቸው ተዋርዷል። በትውልድ ልብ የከፍታ ሰገነት ውስጥ ግን ለዘላለም ደምቀው ይኖራሉ።

**15. ጥርነፋ፦** የወያኔ ህወሓት አንዱና የከፋ መገለጫ ህዝብን በሙሉ የምስለልና ለዚህም እንዲያመች ሲባል የመጠርነፍ ሂደት ነው። ከመኖሪያ መንደር ጀምሮ ማህበረሰቡን በአንድ ለአምስት፣ በየመሥሪያ ቤቱ እና ተቋማት፣ በእምነት ተቋማት ሳይቀር በመጠርነፍ በህዋስ ውይይት፣ በመሠረታዊ ድርጅት፣ በቡድን ውይይት እና በኃይል መድረክ በ"ሀሳባችሁን በነፃነት ግለፁ" ብሂል በመጠቀም የምትፈልገውን አመለካከት ለመትከል፣ የሰዎችን ጀርባ ለማጥናት፣ ለማስፈራራት እና ህዝቡን ለመከፋፈል ትጠቀምበታለች።



t.me/OLDBOOKSPDF

ማንኛውም ዜጋ ከትንሽ እስከ ትልቅ መድረክ አስተያየት ሲሰጥ ስሙን እንዲናገር ይጠየቃል። የሰብሳቢዎች ማስመሰያ 'እንድንተዋወቅ ብለን ነው' የሚል ይሁን እንጂ በተጨባጭ የተለያዩ አንድምታዎች አሉት። ይኸውም ተናጋሪው ግለሰብ ስሙን በመናገሩ ምክንያት ከሥርአቱ አስከፊነት በመነሳት ሊደርስበት የሚችለውን አደጋ በመገመት ጠንከር ያሉ ቃላትን ከመሠንዘር ይቆጠባል።

ቀጣዩ ተናጋሪ ስሙን ከመናገር ይልቅ እጅ አውጥቶ አለመናገርን ይመርጣል። ወያኔ ደግሞ የግለሰቡን አዝማሚያ በማየት በሀሰት ለመወንጀል፣ ለማፈንና ለመሰወር፣ ግርግር ከተፈጠረ 'እነሳሽ ጠንሳሽ አቀነባባሪ በማለት ለማሰር ትጠቀምበታለች። ግለሰቡ እፋሽ አጎንባሽ ከሆነም ጉያዋ ውስጥ ወሽቃ ልትሰግርበት ትመለምለዋለች። ዘልሆነ መድረከ መሪው በአንድ ነቁጥ መተዋወቁ ጓደኛው ሆኖ አይደዋወሉ ነገር ምን ይጠቅመዋል? አባል ደጋፊና ተቃዋሚ ለመበየን ጥርነፋው ይግዛል። ህዝቡን ለማፈን አብዝቶ ይጠቅማል ሀገር በጆሮ ጠቢ ታምሳ ነበር። ሲጠቃለል የወያኔ ስብሰባ ችግሮች በዚህ ውስጥ የታመቁ ናቸው - ለመናገር እንጂ ለመስማት ዝግጁ አይደለችም። ይህም በታሪክ ጭምር የማትተምነው ዋጋ እያስከፈላት ይቀጥላል።

የድባቡን አስፈሪነት ለማሳየት አንድ ቀልድ መሠል መራራ እውነት አለ። 'በአንድ ስብሰባ ላይ በጣም የሚፈራ በቅጥል ስሙ አግአዚ የሚባል ግለሰብ ነበር። ከሚወስዳቸው የጭካኔ እርምጃዎችና በቀል የተነሳ ደፍሮ አጠገቡ ጉብስ ጉብሱን ካልሆነ መረር ያሉ ቃላትን መተንፈስ አይቻልም። ከእለታት በአንዱ ቀን በፈገግታ ተጥለቅልቆ "እስካሁን ያልተገባና ጫና የበዛበት አካሄድ ስንከተል ቆይተናል። ጉዳዩ ተገቢ አለመሆኑን በማመን ከእንግዲህ ሀሳባችሁን ነፃና ግልፅ ሆናችሁ ማራመድ ትችላላችሁ።" በማለት መድረኩን ለውይይት ክፍት ያደርጋል።

ይህንን ተከትሎ ሁለት እጆች በፍጥነት ውስጣቸው ያመቁትን ሊዘረግፉ ይወጣሉ። እድሉን ያገኘው የመጀመሪያው ተናጋሪ የሥርአቱን አስከፊነት፣ ከፋፋይነት፣ ነጠኝነት፣ አፈና፣ ሌብነት እና መሠል ድርጊቶችን ዘከዝኮ ሲጨርስ አግአዚ "የእረፍት ሰአት ስለሆነ ለሃያ ደቂቃ የሻይ እረፍት አለን" አለና ውይይቱ በእረፍት ተግ አለ። ስብሰባ ባለ ቁጥር በአካባቢው የሚዘዋወሩ ተልከስካሾች አግአዚን አገኙትና አጭር ሀሳብ ተለዋወጡ። ከእፍታ በኋላ ተናጋሪውን መታወቂያ በማሳየት ከግቢ ይዘውት ተሰወሩና ከእረፍቱ በሁዋላ ውይይቱ ሊደራ ተሰብሳቢዎች ስፍራቸውን ያዙ። አግአዚ ወደ ሁለተኛው ባለ እድል ተመለከተና "ወንድሜ ቀጥል" አለ። ተናጋሪውም በእድሉ በመጠቀም "እኔ እንኳ ሌላ ጥያቄ የለኝም፤ የመጀመሪያው ተናጋሪ የት ሄደ?" በማለት



t.me/OLDBOOKSPDF

ጠየቀ። እግአዚ "ጥያቄው ከተሰበሰብንበት ዓላማ ጋር ተዛምዶ ስለሌለው ፍሬ ከርሥቲ እና ስብሰባውን ለማወክ የተደረገ ነው።" በማለት ነበር ምላሽ የሰጠው። በምላ እረፍት የሁለተኛውን ተናጋሪ መዳረሻ እንፈልጋለን።

**16. 'የአቅም ማምከኛ ሥልጠና'**:- በስመ አቅም ግንባታ የሀገር ሀብት ጊዜ አባክኖ ለፍቅር ሳይሆን ለጥላቻ፤ ለአንድነት ያይደለ ለመከፋፈል፤ ሥራን ለማሳለጥ የማያግዝ ቀርፋፋ፤ ታሪክ አበላሽተው በድን ሀሳብ ይዘው፤ መአት ሰነድ ተዘጋጅቶ የሠልጣኞች አሰልጣኝ 'ያልገባውን ላልገባቸው ሊያስረዳ' ሥራ ቆሞ ጭምር በመንግሥት አበል ከመርሀ ውጭ የድርጅት መተከል ለመትከል ይመረግዳል። መምህሩ ስለትምህርት ጥራት፤ የግብርና ባለሙያው ስለአመራረት ዘይቢዎች፤ የጤና ባለሙያው ስለመከላከል፤ ተማሪው ስለጥናትና ምርምር ውጤታማነት ሳይሆን ምኒልክ ተነስተው ያስተዳድሩት ይመስል ታሪኩ አኖሌ ላይ ተጀምሮ ጨለንቆ ላይ ያልቃል። ከሁሉም በላይ በታሪክ ምሁራን ጠንካራ መሆኑ የሚታወቀው የወላይታና የካፋ የመከላከል ሂደት አይነሳም ማለት ይቻላል። ግቡ አማራና ኦሮሞ አብረው እንዳይኖሩ ማድረግና ኢትዮጵያን መበተን ነው።

አቅም መምከኑን የምንለካበት የመጀመሪያ ምክንያት ከዘመናት ጋብቻ ፍቅር አብሮነት እና ፍፃሜ ውስጥ አንድ አኖሌ ተመዝዞ መገዳደያ መሆኑ ብቻ አይደለም። ከ1991 - 2018 ለሃያ ሰባት ዓመታት በዐይኑ ያየውን ግፍ ባላየ ባልሰማ አልፎ 132 ዓመታት ወደኋላ ሄዶ በተፈጠረለት ታሪክ መነታረኩ ነው።

**17. ግምገማ / 'ገምጋም'**:- ወያኔ 'በከተናል' ብላ የማትጠራበት፤ ከአደጋ የማትጠራበት፤ ከድጡ ወደ ማጡ ያምትዘቅጥበት አንዱ ማሳያ ግምገማ ነው። ስብሰባና ግምገማ ሀገር ቢያሳድግ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ 'ያቀን ሦስት ጊዜ ይበላ' ነበር። አንድ ዳቦ ሦስት ቦታ ቆርሶ ይሁን ሦስት ድንች የሚታወቅ ነገር የለም። ከህወሓት ትርጉም አልባ አገላለፅ እንውጣና በስብሰባ የባከነው ሀብት "ታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ" ገንብቶ ይጨርስ ነበር። እንደ ጥርነፋው ሁሉ ግምገማው የአቋም መለኪያ እና ከወያኔ ፍላጎት ውጭ የሄዱትን ወንጀል ፈጥሮ በመለጠፍ እስከ እስር ለመዳረግ የሚኬድበት የታላቁ ሴራ አካል ሆኖ አገልግሏል። ብዙዎችም ሰለባ ሆነው በእሥር ማቅቀዋል።

**18. የደህንነቱ መዋቅር**:- ከንፈን ሃየሎምንና የጠጠሩ ወገኖችን እየሰለቀጠ የተጓዘው በዋናነት 'በሬት አልባው' ጌታቸው አሰፋ የሚመራው ይህ መዋቅር ከጥላቻው በላይ



t.me/OLDBOOKSPDF

ፉትን የሚከታተል አደገኛ መሠሪ ቡድን ነበር። ጥላ ጣራ ስር ስትገባ ወይም ዐሐይ በሰላ አይከተልህም። የደህንነቱ መዋቅር ግን በሥራ ገበታህ ፊትለፊትህ ተቀምጦ ከሚማረው ተማሪ ጀምሮ 'ዛሬ ቡና አላፈላችሁም እንዴ?' በማለት ሰተት ብሎ ቤታችሁ እስከሚገባው ጎረቤት ይከተላችኋል። ከኪክ ቤቶች እስከ ታላላቅ ሆቴሎች ለብለብ ብላችሁ ስታወጉ ወይ ካሜራ አለ ካልሆነም ትከሻችሁን ከብድ የሚላችሁ መንፈስ አለ።

ጋዜጣ የሚያነብ መንፈስ፣ ባለመለዮ ባለመነፅር ባለስካርፍ መንፈስ፣ አብድ መስሎ የሚከተላችሁ መንፈስ፣ በእንቅስቃሴያችሁ ሁሉ ውልብ የሚል መንፈስ። ወያኔ አንዷን የሚቃወሙ ወገኖችን ይቅርና የሰበሰባቸውን የራሴ የሚላቸውን ባለማመን አንዱን በአንዱ የሚሰልል ርኩስ መንፈስ ነው። ወጣቱ በፎረም በሊግና በማህበር ተከትቷል። ሴቶች በተመሳሳይ አደረጃጀት ተሸንሽነዋል።

ከሥራ በኋላ ስለትዳር፣ ስለልጆች አድገት፣ ስለማህበራዊ ህይወት፣ ስነምግባር ጠብታ ሀሳብ የለም። የእናቶች ክብር ረክሶ በየቀበሌው እንዘጥ ዘጥ ሲሉ መዋል በእጅጉ ያሳዝናል። ደህንነቱ የኤሌክትሪክ ምሰሶ መገመም፣ የውሀ ማስተላለፊያ ቱቦዎች መበከል ወገን ላይ ስለሚያደርሱት አደጋ፣ ወጣቶች በየሺሻ ጫት ሀሺሽ ጭፈራ ቤቱ ህይወታቸው ስለመበላሸቱ፣ ስለህገወጥ የዶላር የሰው የመሣሪያ ዝውውር ኮንትራባንድ፣ ስለመድሀኒቶች መበላሸት፣ የሥጋቱራና የፍቅፋቂ እንጀራ ጉዳይ፣ባእድ ነገር ከምግብ ጋር መቀላቀል፣ የአይጥ የውሻ የጅብ የአህያ አርድ፣ ዝርፊያ ማጅራት መምታት ...

በአጠቃላይ ስለህዝቡ ደህንነት ጉዳዩ አይደለም። ደህንነት ማለት ዜጎችን ለማፈን የተቋቋመ ድርጅት አድርጎ ይገምታል። አገሌ ደህንነት ነው ከተባለ ወይም በደህንነት ጽህፈት ቤት አጠገብ ስናልፍ ደህንነት አይሰማንም። ደህንነትን የሚፈትን ደህንነት። 'ፊት አልባው' "ይፈሊጋል" በውስጡ ያጨቃቸው ምሥጢሮች ከተጎለጎሉ ልቃቂቱን ተከትሎ ውሉን ማግኘት ስለሚቸግር 'ተከድኖ ይብሰል' የተመረጠ ይመስላል። ህወሓት ጌታቸው አሰፋን አሳልፎ ከሚሰጥ 'ታምሞ ቢሞት' ይመርጣል። ሰውየው ቢያዝ የስንቱ ስኳር - የምን ያህሉስ ግፊት ከፍ ይላል?

19. **የፖለቲካ ፓርቲዎች፡-** የፖለቲካ ፓርቲዎች ከጅምሩ እስከ ፍፃሜው የሚደራጁት ለህወሓት አጃቢ ሚዜና አገልጋይ እንዲሆኑ ታቅዶበት ነው። በ2005 (1997) ምርጫ 'ውጉ ይድረሰኝ' ብሎ 'ይሉኝን በሰማሽ ገበያ ባልወጣሽ' የሆነው ህወሓት



t.me/OLDBOOKSPDF

"ምርጫ ላካሄድ ነው ያውም ነፃ ፍትሀዊ አንከን - የለሽ ተአማኒ የዘመኑ የተሬዱት 'ቅቡል' አለና ከአውሮፓ ጭምር ታዛቢ ካልመጣልኝ 'ያዙኝ ልቀቁኝ' በማለት ለምን ለገራኘ አስቸግር ድንኳን ጥሎ ኮሮጆ አንጠለጠለ። ዕህሬት ቢዮንን አየዘጋ፣ የፓርቲ አባላትን እያሳደደ የገሰገሰው የወያኔ መንግሥት በሦስት ወራት የተሰባሰቡ ፓርቲዎች ይጥሉኛል ብሎ አላሰበም። ይባስ ብሎ የአብዮታዊ ዴሞክራሲው ደራሲ በሲልቢት ለምርጫ መግት መናጀዎችን ይዞ ለምርጫ ክርክር ቀረበ።

በባዶ ሜዳ ድንኳን ገሸሮ፣ ፈንድሻ እንደ መትረየስ እያንጣጣ፣ ድሮ ዳቦ አሸከሞ፣ ከተማውን ዝንብ በሚመስል የንብ ምስል የሚወረው ወያኔ ህወሓት - ባላሰበው መንገድ የእሮጊቶቹ ስብስብ በወጣቶቹ ፓርቲዎች ከፉኛ ተፈትኖ በገዘረራ ተሸነፈ። የአውሮፓ ህብረት ታዛቢ ቡድን ወያኔ (ኢህአዴ ግንባር) መሸነፉን አረጋገጠ። ህወሓትና ጭፍራዎቹ በመላው ኢትዮጵያ እንደሚብረከረኩ የታወቀው እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ግንቦት 6 የወጣውን ጅረት አይተው "ይህንን ጎርፍ እያየ ምርጫው ተጭብረበረ የሚል አለ ይሆን?" ብለው ጠየቁ። በማግሥቱ ግንቦት 7 ጅረቱ መለያ ለውጦ ሁለት ጣቱን እያምጠሞጠ ያልተጠበቀ ወቅያኖስ ውስጥ ገብቶ ማዕበል ሲመጣ የወያኔ ዕጢ ዱብ አለ።

ኮሮጆ ገልብጣ ከአዲስ አበባ በስተቀር በአብላጫ ድምፅ አሸንፌያለሁ ስትል የራሷን ምርጫ ቦርድ ውጤት ለመጠበቅ ጭምር አልታገሰችም። 'የዴሞክራሲያዊ ምርጫ ሽሏ ጨነገፈ። የካድሬዎቿ ሪፖርት የህዝቡን ፍላጎት እንደማይመስል አወቀች። ከአፈጣጠሯ ጀምሮ ትምህርት የማይባት ህወሓት ብልጥ እንጂ ብልህ ስላልነበረች ከ2005 - 2018 ሳትለወጥ 'አባብ ያየ በልጥ በረየ' ሆነና ውብቷን ያጎሉላት ይመስል አስቀያሚ ሚዜና አጃቢ የፖለቲካ ፓርቲዎች አበጃጅታ ከእነርሱው ጋር ስትሟሟቅ ጀምበሯ ጠለቀ። ህወሓት ወያኔ አጠንክረው ከሚቃወሙት መሀከል ጨከኖ ማይጨከነው ቀን ቀን ተቃውመው ማታ እራት ላይ መረጃ ሚያቀብሉትን ብቻ ነበር። እንደየተፅዕኖ ፈጣሪነታቸው ከውሎ አበል እስከ ሆቴል ተበርከቶላቸዋል። በተግባር የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎቹ ጥቅም ሲመዘን የህዝቡን ብሶት በማስተንፈስ የወያኔን እድሜ ማራዘም፣ በዓለም ማህበረሰብ ዘንድ ተቃዋሚ አለ እንዲባል ማገዝ እና ማጀብ ነበር። ተቃዋሚ ተባሉ "ተፎካካሪ" የይዘት ለውጥ የለውም።

በእንግሊዝኛው "Opposition parties" ወደ አማርኛ ሲመለስ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ነው። የሀገራችን የወቅቱ ችግር አደረጃጀቱ በብሔረሰብ ስለሆነ ብትቃወም ብሔረሰብን ብትፎካከርም ብሔረሰብን ነው። እንጂማ ፓርቲዎች በአመክንዮ



t.me/OLDBOOKSPDF

በደራጅ ኖሮ ብትታጠም ሀሳብን ብትፎካከርም ሀሳብን ነው። ለመሆኑ ሀሳብን እንታመማለን ወይስ እንፎካከራለን? በርግጥ በብሔረሰብ ደረጃ ስለተደራጅን እንፎካከራለን። ዘራፍ! ማል አባ ኢሺ! ወዲ ሰበይቲ!

**20. 'ሚዲያ'ዎችን መቆጣጠር:-** የወያኔ የጀርባ አጥንት ከሆኑ ዋነኛ ማፈኛዎች አንዱ ሚዲያን መቆጣጠር ነበር። የተለያዩ የመገናኛ አውታሮች:- የብዙኃን መገናኛ፣ ማህበራዊ 'ሚዲያ'፣ የህትመት 'ሚዲያ'፣ 'የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ' በሙሉ በ'ሞኖፖሊ' የጠረነፈው ወያኔ በማያፈናፍነው የ'ሚዲያ ህግ' ማፈኑን ተያያዘው። ጋዜጠኞች 'አክቲቪስቶች' የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ሲቪል ማህበራትን በሙሉ በዛጥጥሩና በተፅዕኖው መዳፍ ሥር አዋላቸው።

ኢሳት አኤምኤን እና 'የህዝብ ድምፅ' የሆኑ የቴሌቪዥንና የድምፅ ጣቢያዎችን 'የረሀብን ጉንፋን ከሚስሉ' ዜጎች ጉሮሮ እየነጠቀ ለቻይና በሚከፈሉ ዶላሮች ከአየር ላይ እንዲወርዱ አደረገ። በአጠቃላይ በጥብቅ የ'ሴንሰርሺፕ'/ ሳንሱር ቀለበት ውስጥ አስገብቶ የህዝቡ ድምፅ እንዳይሰማ ነገር ዓለሙን ጠረቀመ። የውጭ ጋዜጠኞችን እና ዓለማቀፍ ታዋቂ ስብእናዎችን በገንዘብ በመደለል የራሱን የገፅታ ቅብ ሲከብበት ሀገር ገድሎ ራሱንም አላዳነም።

ለጊዜው ከተነሳበት የደደቢት ተራራ ግርጌ ኢትዮጵያውያንን ከማስቃየት እንደ 77ቱ ድርቅ 'ያዳቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይለቅ' ሆኖ የትግራይ ለውጥ ፈላጊ ወገኖቻችንንና ህዝቡን ከሙቹውም ጊዜ በላይ ጠርንፎ ይዟል። የኢትዮጵያ ህዝብ ነፃ ይውጣ አይውጣ ሳይለይለት በመንታ መንገድ ላይ ቆሟል። የትግራይ ወገኖችን ግን 'ከነፃ አውጪው' ነፃ ሳይወጣ ...

## የባቢሎን አወዳደቅ (የመጨረሻው መጀመሪያ)

ወያኔ ሀወሓት የመከፋፈል ስልቱን በአቅም ግንባታ ሰነዶችን በመጠቀም ብቻ ሳይሆን መፃሕፍት የሚያዘጋጁለት እኩይ ግለሰቦችን በመጠቀም በህዝብ መሀከል ያለውን ግንኙነት ለማሻከር በርካታ ሙከራዎችን አድርጓል። ከነዚህም መሀከል ሃላፊነት በጎደለው መልክ በህዝቦች መሀከል መጠራጠርን የሚፈጥሩ ፅሑፎችን የሚፅፈው የአማርኛ መምህሩ ገብረኪዳን ደስታ እና ኤርትራዊው ተስፋዬ ገብረአብ ይጠቀሳሉ።



t.me/OLDBOOKSPDF

የነርሱን እጅግ የወረዱ የጥላቻ ዕሑፎች መጥቀስ ቢቻልም በሽታቸው ለመዕሐፉ ክብር ስለማይመጥን እየመረረን ለማለፍ ተገደድናል። ወያኔ የቱንም ያህል የሰው ልጅ በታሪኩ ያለፈባቸውን አሰቃቂ ስልቶች በሙሉ አጣምሮ በመጠቀም እድሜውን ለማራዘም የመጨረሻዎቹን ካርታዎች በሙሉ መዘዘ፤ ቢጫወትም አወዳደቁን ማሳመር አልቻለም። ከየትኛውም የታሪክ ወቅት ሊላው ቀርቶ ከደርግ በብዙ እጥፎች ከፍቶ ለሦስት አሥርት ዓመታት አካባቢ ህዝብን ለማፈን ተጣጥሯል።

ሆኖም እየፋመ የሚግመውን እና ለመውደቁ ዋነኛ ምክንያት (Basic Cause) የሆነውን የዘመናት የበርካቶችን መስዋዕትነት የጠየቀ ትግል ማስቆም አልቻለም። የውድቀቱ ማገባደጃ ቅፅበታዊ ምክንያት (Immediate Cause) "የተቀናጀ የኦሮሚያና የአዲስ አበባ ማስተር ፕላን" ሆኖ የተከተለውን እቶን እሳት (የቄሮ እና የፋኖ ትግል) እንደ ቀደመው በአግአዚ ስናይፐር ማስቆም የማይችልበት ደረጃ ደረሰ።

ወያኔ በበላይነት ትቆጣጠራቸው የነበሩና በትግራይ ተወላጆች የበላይነት የሚዘወሩት የመከላከያ፣ ደህንነት፣ ፌዴራል እና አግአዚ ኃይሎች የሚተኩሱት ጥይት ሳይበግረው መንገድ የሚዘጋው፣ ገበያ ጭር ሚያደርገው፣ የነዳጅ ማመላለሻ ባለ ታላላቅ አንስራ ተሽከርካሪዎችን ያገደው፣ የፐብሊክ ሰርቪስ አገልግሎቶችን ያቆመው ሁሉአቀፍ የትግል ስልት በአንዳች መናበብ እየተመራ ወደፊት ተወነጨፈ።

1991 - 2017 የተለፋበት አማራና ኦሮሞን የማበላላት ዘዴ ላይሠራ የኦሮሞ ወጣቶች (ቄሮ) በሚል ይፋዊ ያልሆነ አደረጃጀት ወንድሞቻቸው ሲገደሉ፤ የእናት አንጀት አላስችል ያላቸው የአማራ እቻዎቻቸው ወጣቶች (ፋኖዎች) በእሥር ላይ የነበሩ የኦሮሞ መሪዎችን ምስል እና የደም ቃልኪዳን መፈክር አደባባይ አንግበው በመውጣት፦

**"የፈሰሰው የኦሮሞ ደም የኔም ደም ነው!"**

የሚለውን ድምፅ አስተጋባ። በእልህ የጦፈው ወያኔ ልክ እንደ ፋሺስት ጦር በማይራራ አንጀቱ አግአዚ በተባለው ሠራዊት በመታገዝ የባህርዳርን እና ጎንደርን ወጣቶች በሰላ ፋሱ ጨፈጨፋቸው። የአማራ ደም ስለኦሮሞ ፈሰሰ። "ጣና የመተሣሠሪያ ገመዳችን ነው" በማለት ወደ ባህርዳር በግርማ ሞገሥ የተመመው የኦሮሞ ወጣት አምቦጭ አረም ላይ ከአማራ ወጣቶች ጋር ጎን ለጎን በመሆን ክንዱን አንስቶ፤ በወል አያቶቹ



t.me/OLDBOOKSPDF

የቀለለ በተመንግሥት ከንድ ለከንድ ተሰናኝቶ ምስል አሰቀርቶ የከፋፋዩን ወያኔን ሴራ ቀበረው።

የገፋት ውሀ እስከአንገታቸው ውጧቸውም ህወሐቶች ቅጥ ያጣ ዳንኪራ ይመቱ ነበር። ደም እንደ ጎርፍ እየፈሰሰ በአሽቃባጭ አርቲስቶቻቸው ታጅበው እታጥ መደለቅና አስረሽ ምቺው የአዘቦት ተግባር ሆነ። ዶላር እንዳሻቸው እየረጩ፣ ልጆቻቸውን በምዕራቡ ዓለም እያዝናኑ፣ በብርሀን በተንቆጠቆጡ ሰገነቶቻቸው ሆነው የድመቶቻቸውን ልደት ሳይቀር እያከበሩ ዜጎችን እስር ቤት አጉረው ተቀናጡ። ለልጆቻቸው ፍራፍሬና 'አይስክሬም' ይዘው እየገቡ በዚያው እጃቸው ዜጎችን መግደል የመዝናኛ ያህል ሆነላቸው። በመኪናቸው ጎማ ርጋጭ በየአስፋልቱ ዳር ውሀ ካቆረው ጎዳና በግዴለሽነት ጭቃ እየረጩ ልቅላቂያቸውን መድፋት የትዕይንት ያህል ያስደስታቸው ነበር። አምቦ በየዓመቱ የልጆቿን ደም ገበረች። የወያኔ ጡጫ የቱንም ያህል ቢበረታ አንኳን ሀሊናን ይቅርና ግዘፈ አካልን ማንበርከከ አቃተው።

የማፋቸው ፅዋ ድርበቡን አልፎ ሞልቶ ፈሰሰ። "የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ" አውጥቶ በአንቀራሪት ቀርቁርታና የእንጭራሪት ጭርጭርታ ሰቅጣጭ ድምፅ "የማያዳግም እርምጃ እንወስዳለን!" የማስፈራሪያ ጋጋታ መግለጫ ቢያወጣም፡-

"መፍራት ራሱን ፍርሀትን ነው!" የሚል የአፀፋ ምላሽ ከህዝቡ ወገን በረታ። እምባገነኖች ከታሪክ አይማሩምና የደደቢቶች ስብስብ ለከት ያጣ አብሪት በተነሳበት ላይ ቆሞ 1975 ላይ ተቀርቅሮ ንቅንቅ አላለም። ወትሮም ለኢትዮጵያ ህዝብ ታላቅ ለነሶቡና የማይመጥነው የደደቢት ጉጅሌዎች ጥርቅም ከህዝቡ የለውጥ ፍላጎት አብሮ የሚራመድበት ዕውቀት ከህሎትና አቻቻይነት አጥቶ ነጠፈ።

## የኦሮማራ' ጥምረት የውድቀቱ ማጠቃለያ

የወያኔን አብሪትና ልክ ያለፈ በደል ሞቋቋም ያቃታቸው የአዴፓ አመራሮች፡- (ነፍሳቸውን በገነት ያሳርፍልን ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ የኢፌዴሪ ፕሬዚደንት)፣ ሁሴን አሊ የኦሮሚያ ፕሬዚደንት፣ አልማዝ መኮ አፈ ጉባኤ፣ ኤርምያስ ለገሰ ዋቅጂራ ሚኒስትር ደ ኤታ እና አያሌ አመራሮች ሹመታቸውን በፈቃዳቸው ተዉ። አንዳንዶቹም ሀገር ለቀው ተሰደዱ። የአማራ ክልል የሚመራው ከትግራይና ከክልሉ ውጭ በሆኑ ጨካኝ አመራሮች ስለነበር ተሰቅዞ ተይዞ ከፍተኛ ዋጋ ከፈለ። ለምሳሌ፡-



t.me/OLDBOOKSPDF

"የዓብይ እዳ" በተሰኘ ርዕስ አባ ዶዮ ዘጀጋማ በፃፈው መፅሐፍ ገፅ 65 ላይ የሚከተለው ተከትቧል፦

ምንም እንኳ በፖለቲካ ቁማር አምሃራ ሳይሆን አምሃሮችን እንዲመራ በመሾሙ ዘንዲ ትእዛዝ ብእዴንን የተቀላቀለው ተሯሯ ዋልዋ፦

አምሃራ አሚባ የያዘ የጎርፍ ውሀ ጸበል ነው ብሎ የሚጠጣ ሰዎችን በግዴ ወንዝ ውስጥ እየገፈተረ ጸበል አጠመቅሁ የሚል ትምክህተኛ ነው። 1997 ዓ.ም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና መንግሥት ሠራተኞች በፕላዝማ ቴሌቪዥን ፕሮግራም ላይ የተናገረው ነው።

ይህ ባህርይ ከአማራ ክልል ውጭ መሪዎቻቸውን ባይረገና ልዩ ተልዕኮ በተሰጣቸው አብዛኞቹ የክልሉ ከፍተኛ አመራሮች ይገለፅ የነበረ ባህርይ ነው። በሂደት ከክልሉ የተገኙ አመራሮች የወገናቸው በደል የእግር ውስጥ እሳት ሆኖ አንገበገባቸው። አህዴድ ውስጥ ብቅ ያሉት አቶ አለማየሁ አቶምሳ የኦሮሚያ ፕሬዚደንት በተመረጡ የኦሮሞ ወገናቸው ላይ የሚደርሰው በደል አንገሽግሿቸው የለውጥ እርምጃዎች ውስጥ ገብተው ብዙም ሳይቆዩ "ይሩ ባልሆነ ህመም" ህይወታቸውን አጡ። ጥርጣሬያችን ለታሪክ ፍርድ ትተን በተለይ ከ2016 - 2018 "ቲም ለማ" እና "ቲም ገዱ" ወያኔን የሚፈታተን ጠንካራ ጥምረት ፈጠሩ። ጅማሪው ግልፅ ባይሆንም እኩል ዋጋ የምንሰጣቸው የሚከተሉት አካላት እንደ ጥሩ 'ስኳድ' ተናበቡ።

ሀ. አቶ ደመቀ መኮንን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር (አማራ) እና ዶክተር ዓብይ አህመድ አሊ የወቅቱ የኦሮሚያ ምክትል ፕሬዚደንት / በለውጡ ጠቅላይ ሚኒስትር (ኦሮሞ)፤

ለ. አቶ ለማ መገርሳ ዋቆ የኦሮሚያ የወቅቱ ፕሬዚደንት /ከለውጡ በኋላ የመከላከያ ሚኒስትር እና አቶ ገዱ አንዳርጋቸው የአማራ የወቅቱ ፕሬዚደንት ከለውጡ በኋላ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፤

ሐ. አቶ ንጉሡ ጥላሁን የወቅቱ የአማራ ክልል መገናኛ ድርጅት ዳይሬክተር/ ከለውጡ በኋላ በጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ የፕሬስ ሴክሬታሪያት ሃላፊ እና አቶ አዲሱ አረጋ ቂጤሳ የወቅቱ የኦሮሚያ ኮሙኒኬሽን ቢሮ ሃላፊ/ ከለውጡ በኋላ የገጠርና ግብርና ልማት ቢሮ ሃላፊ ... እና ሌሎች የኦሮሞና የአማራ አመራሮች በህይወታቸው



t.me/OLDBOOKSPDF

ተመራርደው የህወሓትን የበላይነት የሚሸከም ጫንቃ ላይኖራቸው ጀገኑ። በሁለቱም ክልሎች ለሚካሄዱ ትግሎች ተዘዋዋሪ ድጋፋቸውንና ወገንተኝነታቸውን ማሣየት ቀጠሉ። ከደኢህዴን የተወሰነው ወገን ከ2018 ጀምሮ "የለውጡ ኃይል" እየተባለ ከሚጠራው ጎራ ተርታ ሲሰለፍ፤ ሌላው ከቆሞ ቀሩ ህወሓት አመራር ጋር ተለጥፎ ከፍፍሉ እየጦዘ ቀጠለ። ወያኔ መልካም ግንኙነቱን "መርህ አልባ ጉድኝት" በማለት በተለመደ ድንፋታዋ አጅባ ብትወራጭም ለለውጥ ዝግጁ የነበረው ወገን ከአቋሙ ፍንክች አላለም። ውጥረቱ ከመጠን በላይ አየለ።

በውጭ ሀገር የሚኖሩ ወያኔ ህወሓት "እሳትና ጭድ" በሚል እንዳይጣጣሙ ፈርጇ የተማመነችበት ወገን (ለጊዜውም ቢሆን) የመከፋፈል ሴራው ተባነነበትና "ጭቃና ጭድ" ሆኖ አብሮ ሊገነባ መዘጋጀቱን አወጀ። ወያኔ የመጨረሻው የምጥ ጣር ላይ መሆኑ በማያሻማ መልኩ ተስተዋለ። ከውጭም ሆነ ከውስጥ ጫናው በረታ በመጨረሻው ሰአት ለጥገናዊ ለውጥ ቢወተረተርም ቀኑ መሸቶ ነበር። የኦሮማራ ጥምረት ወደ ደቡብ ከበቡን ማስፋቱ ለወያኔ በቡሀ ላይ ቆረቆር ሆነና ጭንቀት ናረ። አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ በሼ ጠቅላይ ሚኒስትር በአንዳች አስገራሚ የመንፈስ ጥምረት ሥልጣን በአፍንጫዬ ይውጣ በማለት መልቀቂያ አስገቡ።

ሊያግባባቸው ለሚቅበዘበዘው አማላጅ ቡድን ፋታ ሳይሰጡ ፈጣን ጋዜጣዊ መግለጫ ሠጡ። ወያኔ የተለመደውን ደባ ለማውጠንጠን ከመላላጥ ውጭ ቀናነት ተፈጥሮው ስላልነበር አደገኛ ሴራ አቀደ። የኦሮሞና የአማራን ፍቅር ላሻከር የምችለው አቶ ደመቀ መኮንንን ቀጣይ ጠቅላይ ሚኒስትር ባደርግ ነው የሚል ጅል ፈሊጥ ይዞ ብቅ አለ። በስሌቱ መሠረት ህወሓት 25 እጅ፣ ብአዴን 25 እጅ፣ ከደኢህዴን የተወሰነ ድምፅ፣ የአህዴድ ታማኞችን በመያዝ ውጥኑን ዳር ማድረስ። ካልሆነ አቶ ሺፈራው ሽጉጤን ሁለተኛ አማራጭ አድርጎ መያዝ (ሰውየው በደቡብ አመራሮችም የተጠሉ ስለሆኑ ይህኛው እቅድ ብዙም እንደማያስኬድ ግልፅ ነበር።)

ህወሓቶች ዶክተር ዓብይን በግምገማ ላይ ለማጥላላት አሉኝ የሚሏቸውን የጭቃ ልቅላቂዎች ደፉ። ይሁንና የ42 ዓመቱ ጎልማሳ ዶክተር ዓበይ ያላቸው ቁጥብነት ለለደፋው ማረፊያ ጥግ አላመቻቸም። ከዚሁ ጎን ለጎን አቶ ደመቀ መኮንን ከህወሓት ሰዎች ያልተለመደ ፈገግታ በገፍ ይቀርብላቸው ጀመር። ርግቡ ደመቀ ከአንገት በላይ ለሆነው ግልፈጣ የለበጣ ምላሽ እየሰጡ ያቺ ቀን ደረሰች። "የለውጡ ኃይል" ብልህ፤ ህወሓት ደግሞ ብልጥ ሆነው ወደ አዳራሹ ገቡ። በዚህ ምርጫ የቴክኖሎጂው ሰዎች ቆቅ ስለነበሩ እንደተለመደው የቀደሙ የህዝብ ምርጫዎች ኮሮጆ መገልበጥ የሚቻል



t.me/OLDBOOKSPDF

አልሆነም። (መከላከያው ውስጥ ባለው ስብጥር በቅደም ተከተል አብላጫ ቁጥር ያላቸው አማራ እና ኦሮሞ ምርጫውን በአንክሮ ይከታተሉ እንደነበር አከራካሪ አይደለም።)

ዐራት ግለሰቦች ለእጩ ጠቅላይ ሚኒስትርነት ተጠቆሙ።

አቶ ደመቀ መኮንን ከብአዴን

አቶ ሽፈራው ሽጉጤ ከደኢህዴን

ዶክተር ደብረፅዮን ገብረሚካኤል ከህወሓት እና

ዶክተር ዓብይ አህመድ ከኦህዴድ

ቀጣዩ ሒደት የድምፅ አሰጣጥ ሥርአት ነው። ድንገት አንድ አስገምጋሚ ድምፅ ከደርባባ አካል ውስጥ፡- "ድምፅ ከመሠጠቱ በፊት" አለ። "ይቀጥሉ!" የአስመራጩ ሰላላ ድምፅ። አቶ ደመቀ ደልደል ካለ ተክለ ሰውነታቸው ጉሮሯቸውን በመሳል፡ "ከምርጫው ራሴን አግልያለሁ። ምክንያቱ ደግሞ በቦታው አዲስ ፊት ማየት ስለምፈልግ ነው" አሉ። ለምርጫው የቀረቡት ሁለት ፊቶች አሰልቺና የተለመዱ ስለሆኑ አዲሱን ፊት የመንካት ያህል ነበር። "የፈሩት ይደርሳል፤ የጠሉት ይወርሳል።" ሆነና "የኦሮማራ ጥምረት" ህወሓትን አንበረከከ። ህወሓቶች ፊታቸው እንደረዘመ ወደ ደደቢት አቅራቢያ ወደ መቀሌ ረጅሙን ጉዞ ተያያዙት። "ያዳቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይለቅም" እንዲሉ ለተንኮል እንደማያንቀላፉ ለመረዳት አስማተኝነት አይጠይቅም። የለውጥ አመራሩ "አዲስ ወይን ጠጅ በአሮጌ አቁማዳ አይቀመጥም" በሚል ብሂል ይመሥላል ታላቅ መጥረጊያውን አንስቶ የሸረሪት ድሩን መጠራረጉን ተያያዘው።



t.me/OLDBOOKSPDF

መንታ ገፅ

ጊዮርጊስና መንበሩን" የተቆናጠጠው "ዐቢይ አመራር" አጀብ በሚያሰኙ ለውጦች ታጅቦ የመጀመሪያ መንፈቅ ጉዞውን አጠናቀቀ። ወገን መፍታት፣ ወገን ደብር ማፍረስ፣ በደስታ ደረትን የሚያስቡ ንግግሮች፣ ኢትዮጵያዊነት፣ሰውና ሞሳወና ሲሉ የፍቅር ጉዞ። ከሰሜን ዋልታ በሰተቅር ኩኖር እሰሳሰር የአገርነት ስሜት የሚያስቱ በደስታ ረገዱ። የደስታ ዘለላ ዕንባዎች፣ "ከአንተ ያስቀድሙኝ" ምኞቶች በደስታ መጣበር በረታ። ዋል አደር ሲል ጠብመንጃ ያነገቡና ከኢትዮጵያ ከስልቡና ርቀው የቆዩ ሰብሳናዎች በተፈጠረው ገዳ በመጠቀም ከየጎሬያቸው ጠብመንጃ ጭምር እያነገቡ እንደ ገመሬ ዝንጀሮ በየአውራ ጎዳናው መንጎማለል ጀመሩ።

"ዝንጀሮ ጎፈሩ ሲረዝም አንገቱ የሆነ ይመስለዋል።" እንዲሉ መርጋት የጀመረውን ጥሩ መንፈስ ሊያውደው የጀመረውን ሀገር በጠበጡና ራሳቸው በተው ይለብስ አቀረኑት። ጀግጂጋ፣ አሶሳ፣ ቡሌ ሆራ፣ ለቀምት፣ ባህርዳር፣ ጎንደር፣ ቡራዩ፣ ጣና በለስ፣ ደሴ፣ አዳማ፣ ኢሳ፣ ሻሸመኔ፣ ሐዋሳ፣ ቀቤና፣ ጉጂ፣ ሞያሌ፣ ራያ፣ ከሚሴ፣ አጣዬ፣ አርጎባ፣ ኮሬ ... ላይ ጦራቸውን የሰበቁ ኃይሎች ለሦስት አሥርት ዓመታት ያህል የተጋቱትን መርዝ አቀረሹ። *ጠቅላይ ሚኒስትሩን የመግደል ሙከራ በኢትዮጵያ አቆጣጠር ሰኔ 16 ቀን 2010 ተሞከረ። 'የመፈንቅለ መንግሥት አይነት ያልተለመደ ወታደራዊ ትርኢት' ያሰበውን ሳያሳካ ከሸፈ።

አዲሱ አመራር ደህንነቱን የሚያጠናክሩ እርምጃዎች ወሰደ። በዋናነት የሪፐብሊካን ጋርድ እና የአየር ኃይሉ ትርኢት ቢጠቀሱ ገላጭ ይሆናል። በሂደቱ አስገራሚው ድራማ "ለኦሮሞ ህዝብ እታገላለሁ" የሚለውና በየዘመኑ እምነት ይግባ እስከምን የማይታወቀው እንግ 27 ዓመታት (1991 - 2018) በኦሮሞ ህዝብ ላይ የዘረዘርናቸውን ግፎች ከፈፀመው ወያኔ ህወሓት ጋር የተረገመ ጋብቻ ፈፅሞ፣ ትጋባዥ፣ ቡራኬ ተቀብሎ፣ በኦሮሞ ደም ላይ ተምነሸነሸ መግባቱ ነው። ይባስ ብሎ "ONN" ቴሌቪዥንን ጣቢያ ትግራይ ውስጥ ሊመሠርት መርጡ እና ይቅርታ የሌላቸው ጥፋቶች መፈፀሙ ነው። ... ይህ መራራ ሀቅ የሚያማቸው ቢኖሩም ከእውነታው ሸሽቶ የትም አይደረስም። የአማራ ነፃነት ታጋይ ነን ባሉ ቡድኖች እርበኛ መጥፎነት፡- "ትግራይን አንጨብጭባታለን"

በማለታቸው ተደመምን። በፍቅር መጨባበጥ ሲገባ 'እንጨቢበጣታለን' ለማንም አይበጅም። በ"የዓባይ አዳ" ገፅ 64 እንደተጠቀሰው፡- "አምሓራን እንዲያንሰራራ ሊያርገን ቀብረነዋል!››ጀነራል ሳሞራ የኑስ የአምሓራን ህዝብ አስመልክቶ የተናገሩት።

የአርበኛው ንግግር ለጡረተኛው ጀነራል ሳሞራ የተሰጠ የአፀፋ ምላሽ ነው የሚሉ የፖለቲካ ተንታኞች አሉ።

ወያኔን እንዳይተካ ያጠራጠረው የቀድሞው አህዴድ የወቅቱ፣ የኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኦዴፓ) አቋም ግራ ይሁን ቀኝ ለጊዜው አልለየለትም። ተስፋ የሰነቀውና ስጋት የሰቀዘው ወገን እነዘ ተመጣጥኗል። ታሪክ ሁልጊዜም ለሀገር በጎው ይሆን ዘንድ ይመኛል። ቀጣዩ ጉዞ መልካሙ ይገጥመው ዘንድ ሀሊናችን የአህጉራችን ደቡብ ጫፍ ድረስ ተጓዘ። ለጥቁሮች ነፃነት መራራ መስዋዕትነት የከፈሉት እና 27 ዓመታት በነጮች ሮቢን ደሴት ታስረው የነበሩት የደቡብ አፍሪካ የመጀመሪያው የነፃነት ፕሬዚደንት ኔልሰን ማንዴላ፡- *"የጥቂት ነጮችን የበላይነት አገዛዝ (1948-1990)አገዛዝ የተጠየፍኩትን ያህል፣ የጥቁሮች የብዙኃን አገዛዝ ያቅለሸልሸኛል።"* ማለታቸውን ያለማሰላሰል በቀጥታ አፅድቀነዋል።



t.me/OLDBOOKSPDF

"ከዘረኛ ጋር ተነጋግሮ መግባባት ይቻላል ...

ከብሔረሰብ መወያየት እንዴምን ይቻላል?"

ዶክተር ዳኛቸው አሰፋ

"ማታ ማታ በማራ ሚስቶቻቸውን አቅፈው ለየተኙ ቀን ቀን በማራን እና አሮሞን ያጋጫሉ፡፡

... አሮምና አማራ ቢተባበሩ ወያኔ በተቅማጥ ታልቃለች፡፡"

ፕሮፌሰር መረራ ጉዲና

"ከሀደት ራሱን የቻለ በሽታ ሲሆን

ማስኪድ ደግሞ እጅግ ይብሳል፡፡"

ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም

"የአከሱም ሐውልት ለወላይታው ምኑ ነው?"

አቶ መለስ ዜናዊ

"ያልተማሩ ምሁራን ያቆይዋትን ሀገር

የተማሩ ማይማን ሊያፈርሷት አየታገሉ ነው"

የመፅሐፉ አዘጋጅ፡- ታየ ቦጋለ አረጋ አ.ሌመ ደሱ አዳ



t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ዐሬት

## መራራ እውነትን ፍለጋ

የኢትዮጵያ ታሪክ በዓለምም ሆነ በአፍሪካ ጉልህ ስፍራ ይዞ ይወጣ ዘንድ የገዳ ዴሞክራሲያዊ ሥርአት፣ ቅድመ አክሱም ሥልጣኔዎች፣ ዳማት አክሱም ላሊበላ ፋሲለደስ ጀጎል ጢያ አባጂፋር ኮንሶ የእደ ጥበብ ውጤቶች፣ ቁሳዊና መንፈሳዊ ሀብቶች፣ ድንቅ መስተጋብር፣ ፅሑፍ፣ ኢሬቻ መስቀል ጨምበለላ፣ የአፋር ዳጉ፣ የሐረሪ፣ የቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ የሶማሊ የጋምቤላ ...ከ80 በላይ ማህበረሰቦች ሀብር፣ የአበው ወእመው የዘመናት መስተጋብር ... ደምቆ እንዳይታይ የፖለቲካ ልሂቃን ከፋ መሻት ታሪካችን ላይ ርጉም ጥላ አጥልቶ ግርዶሹ በረታና እነሆ የወል ታሪካችንን መሠነድ ተቸግረን ስንውተፈተፍ ዓመታት ጣጥለውን ነጎዱ። ዓለም ታሪክን ዓላማውና ለባለሙያው ትቶ በየሠለጠነበት መስክ ለሳይንስ ለጥበብ ለፈጣን ለውጥ ታትር እኛ ከኢትዮጵያ ውጪ ዓለም የሌለ ይመስል ከራሳችን ጋር - 'በስሚ ስሚ-ሽ አሉሽ' ... ነገርን ከሥሩ ሳንመዝን፤ የሌለ የጦስ ዶሮ ፈልገን ለማረድ እና ታረድ ስንንደፋደፍ ማየት 'የሀገር ያለህ' አስባለንና ለመሆኑ ታሪካችን ለአተካራ ?በቃ ነውን? ምላሹ አገብሮን ፈጣሪ በፈቀደልን መጠን እውነትን ልንገልጥ ሰው አወዛጋቢ ገፆችን እንደሚከተለው ገለጥን። "የዓባይ እዳ" (ከላይ የጠቀስነው ፍ ገፅ 45)፡-



t.me/OLDBOOKSPDF

በቅርብ ጊዜ ከ27 ዓመት ወዲህ ህወሓት / ኢ.ህአዴግ ተጥሮ ባስገፋቸው የእነ ተስፋዬ ገብረአብ እና መምህር ገብረኪዳን እና ተከታዮቻቸው የተሃፉ መፃሕፍት ራሱን ያነበጠው ትውልድ ነው። በዚህም ምክንያት አንድ ኦሮሞን እንኳን ለፖለቲካዊ ድል ለማዋል ተቸግረናል።

ደራሲው አባ ዱዮ ዘጃጋማ ይህንን ያለው ወዶ አይደለም። በኢትዮጵያ ታሪክ ዙሪያ ከ1970ዎቹ ጀምሮ ሆነ ተብሎ የተሰበከ የተዛባ የታሪክ ትርክትና ከ1990ዎቹ መጀመሪያ ጀምሮ በመንግሥት እየተደገፈ የተነዛ የታሪክ አሉባልታ በቀላሉ እመክንዮን ለመቀበል ዝግጁ ይሆናል ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው። በተለይ ተስፋዬ ገብረአብ (ኤርትራዊ)፣ ገብረኪዳን ደስታ (ትግራዋይ) ሆነው 'ከጳጳሱ በላይ ካቶሊክ' ሆነው 'አዛኝ ቅቤ አንጓች' ተልዕኮ ታጥቀው የኦሮሞ ወጣት ስነልቡና ላይ መዝመታቸው የታሪኩን እውነት የማብራቱ ሂደት ፈተና ይገጥመዋል። ለመጥፎ ዓላማ ያሰፈሰፉ የኦሮሞ ልሂቃን ሽፍጥ ሲጨመርበት ደግሞ የታሪክ ውይይቱን ወደ ጭቅጭቅ ደረጃ ያወርደዋል።

በኦሮሞ የሞራል ደረጃ ልክ ያሉትና አብሮ መኖር ያከበራቸው በሽበት እና በሞራል ደረጃ (ሰቃ) አንቱ የተባሉት የቀድሞ የፓርላማ አባል ከቡር አቶ ቡልቻ ደመቅሳ:- "በኦሮሞም ሆነ በኦሮሞነት አፍረን አናውቅም። ኦሮሞን እንወከላለን በሚሉና ኢትዮጵያን በሚጠሉ ጠባብ ፖለቲከኞች እናፍራለን።" ያሉበት ምክንያት የሁኔታዎች አካሄድ ስላሳሰባቸው መሆኑ አነጋጋሪ አይሆንም።

በዚህም መሠረት ዘውጌዎች "የብሔረሰብ ታሪክ ፀሐፊዎች" ኢትዮጵያ በአንድነት እንዳትቀጥል የተቀበሉትን ተልዕኮ ለማሳካት የተጠቀሙበት የመጀመሪያው ዘዴ የፈጠራ ልቦለድ ድርሰቶችን መከተብ፤ የፈበረኩን ታሪክ ስሜት ኮርኳሪ በሆኑ ትርክቶች ማጀብ፣ ጥላቻውን 'ውሸት ተደጋግሞ ሲነገር እውነት ይሆናል' በሚል ስልት በሰነድ እና በሥልጠና ጭምር ማራገብ፤ ፍቅርን ገፍቶ ለበቀል እንዲውል ታቅዶና በጥልቀት ታስቦበት ሐውልት ማቆም፤ በትላንት ታሪክ ጠያቂም ተጠያቂም እንደሌለ እየታወቀ ሆነ ተብሎ የማይመለከተውን - ሌላውን ጠልቶ ያልተፈጠረውን - ስለትላንት የማያውቀውን ወገን ማስጠላት - የኢትዮጵያዊነት ጠላትነት መሆኑን ከግምት ሳያስገቡ ታሪኩን ለመረዳት መታገል ያስቸግራል።

ሰግግሽ ከፍለ ዘመን የተደረተና ለሩብ ከፍለ ዘመን የደደረ የውሸት ፣ ከፋትን በእውነት ሸብልቅ ለመፈረካከስ መነሣት ቀላል እንዳልሆነ ጠንቅቀን ተገንዝበን፤ ሀቅ



t.me/OLDBOOKSPDF

ማሸነፏን መዝነን ሌላ እንዳይቀበል ተደርጎ የተዘጋጀን 'ሶፍትዌር' የመቀየር ያህል አስቸጋሪ ሁናቴን በማስረጃ ተመርኩዘን የተተረተረውን ልንሰፋ እነሆ መርፌና ክር። ወደ አመክንዮ ለመሻገር የአርቲስት የጌትነት እንየውንና የገጣሚ ለታ ቀነዒ አጋ የስንኝ ቋጠሮዎች ለታሪክ እንዲመዘገቡ ወድደን መሸጋገሪያ አደረግናቸው።

## "እኛው ነን!"

"እኛ ነን፣ እኛው ነን፣ እኛ የዘሬዎች

በእጥር የተቀጨ፣ የሩቅ መንገደኞች

ሰላሳ ህልመኞች፣ ሰላሳ ተስፈኞች፣ ሰላሳ ወጣቶች

ሀገር እንደሌለው በሰው ሀገር ምድር ሲቀላ አንገታቸው

ወገን እንደ ሌለው ከሰው ሀገር ባህር ሲቀየጥ ደማቸው

በአገር ቁጭ ብለን ከዓለም ጋራ እያየን

ከሬት የመረረ ከቋጥኝ የሚከብድ

ከቶን የሚያቃጥል ከብራቅ የሚያርድ

ሀገር ያህል መርዶ በሰንበት አመሻሽ በአገር የተሸከምን

በገዛ ሞታችን እዝን የተቀመጥን፡፡

ካሳለፍነው ህይወት ካለፈው መከራ

መማር የተሳነን ደመና ወራሾች፣

የሞትነውም እኛ ያለነውም እኛ

ከፋይም ተቀባይ እኛው ነን ባለእዳች፡፡

እኛው ነን....



t.me/OLDBOOKSPDF

ከቅጣትም ቅጣት ከመርገምትም መርገት፣

የገዛ አንገታችን በስለት ሲቀላ

የገዛ ደማችን ባህሩን ሲያቀላ

የራሳችንን ሞት ቆሞ መመልከቱ፣

ምን ያህል ነው ፍሙ ምን ያህል ይከብዳል

ሰቆቃው እሳቱ?

ምን ያህል ነው ሸከሙ? ምን ያህል ይዘፍቃል?

መከራው ከብደቱ

ምን ያህል ይጠልቃል? ምን ያህል ይሰማል?

መጠቃት ስለቱ

ኃዘን ነው? ቁጣ ነው? ጸጸት ነው? ምንድነው

መጠሪያው? ምንድነው ስሜቱ?

እውን ይህን መአት ይኼን የእኛን መቅሰፍት

ቋንቋዎች በቃላት ችለው ይገልጹታል?

እውን ይህን ስቃይ፣ ይህንን ሰቆቃ፣ እናትና ሀገር

ሸከሙን ይችሉታል?

እኛው ነን እኛው ነን...

ለዚህ ከፉ እጣችን ለዚህ መርገምታችን

ለዓለም ለፈጣሪ አልፈታ ላለው እንቆቅልሻችን



t.me/OLDBOOKSPDF

መነሻም መድረሻም ጥያቄዎች እና መልሶችም

እኛው ነን፡፡

እኛው ነን የገፋን፣ እኛው ነን የከፋን

እኛው ነን ያጠፋን ፣እኛው ነን የጠፋን፡፡

ከዘመን ጋር አብሮ መዘመን ተስኖን

ሰፊ አገር ይዘን በሀሳብ እየጠበበን

በፍቅር ተሳስቦ አብሮ መራመዱ አቀበት የሆነን

ቂም እየቆነጠርን፣ ቂም እየመነዘርን

በዛሬ መንጋጋ የትናንቱን ድርቆሽ የምናመነዥክ

በዛሬ ምድጃ የትናንቱን አመድ ታቅፈን የምንሞቅ

ባንድ ላይ ከመጓዝ በየፊና ሩጫ አረሩ ምንደፍቅ

እኛው ነን እኛው ነን....

ከእምነት የተፋታን ከፈጣሪ የራቅን፡፡

እኛው ተጋፊዎች፣ እኛው ተገፊዎች

እኛው አሳዳጆች፣ እኛው ተሳዳጆች

ካሳለፍነው ህይወት ካለፍነው መከራ

መማር የተሳነን ደመና ወራሾች

እኛው ነን እኛው ነን እኛ የዛሬዎች

የነገ፣ የታሪክ ያገር ባለእዳዎች፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

እኛው ነን...

በንፍገት በስስት በስግብግብ መዳፍ

ከድሆች ጉሮሮ ካፋቸው መንጭቀን

ሌሎችን ረግጠን ሌሎችን ጨፍልቀን

በሌሎች ጀርባ በሌሎች ጫንቃ ላይ ወደ ላይ መሳቡ

ቅንጣት የማይጨንቀን

በማስመሰል ጥበብ በአድርባይ አንደበት በሸፍጥ የሰለጠን

ከብዙዎች ድርሻ ተሻምተን ተናጥቀን

ላንድ ሰራሳችን በወርቅ ላይ አልማዝ በህንጻ ላይ ህንጻ

ስንቆልል ስንከምር የማይሰቀጥጠን፣

የመንፈስ ድውዮች የንዋይ ምርኮኞች

የወንበር ሱሰኞች የሆድ አምላኪዎች

ከሰውነት ወርደን በነፍስ የኮሰመን የስጋ ብኩኖች

የራሳችን ሀጢያት የራሳችን ሲኦል እኛው ነን መርገምቶች

እኛው ነን!

በዚህ ሁሉ ግና .....

መቼም ቢሆን መቼ ሰው ይሞታል እንጂ ተስፋ አይሞትምና

በመንገድ የቀሩት ወጣቶቻችን

በአጭር የተቀጨው ሀሳብ ምኞታቸው



t.me/OLDBOOKSPDF

ተስፋ አለን ተስፋቸው::

በአገራቸው አፈር በታናሾቻቸው

ነገ ውብ ይሆናል ለምልሞ ይጸድቃል በዛሬው ደማቸው

ዛሬ የመከነው ውጥን ርዕያቸው

በጊዜና በአገር ነገ እውን ይሆናል ይፈታል ህልማቸው

ይህ ነው መፅናኛችን ይህ ነው መፅናኛቸው::"

አርቲስት ጌትነት እንየው

---

**የአንድ እናት ልጆች ነን፣ ደምህ ከደሜ የተቀዳ፤**

**ጠላቶች እኮ አይደለንም፣ ሟች እንጂ ለወል ዕዳ።**

ታየ ቦጋለ አረጋ፣ ኢልሞ ደሱ ኦዳ

---

"Fakkaattii koo dhiiga koo

Kutattuu ilma firaa

Inni si keessa jiru

Ana, haadhoo kee keessas jira!

Maqaa tokkoon waamamne

Maqaa tokkoon dhaanamne

Maqaa tokkoon saamamne....



t.me/OLDBOOKSPDF

Dhibee kee na dhukkuba

Quuqama kees nan haada

Aariin kee aarii kooti

Na waxala na waada...

Ati boonyaan boo'eera

Ati cabnaan cabeera

Anis (*Itiiyoopiiyaa'f) jedhee

Jireenya koo dhabeera...

Mee as natti maxxanii

Harka narra keewwadhu

Dhahannaa laphee koorraa

Dhugaa koo dhaggeeffadhu!

Inni kaleessaa darbeera

Tokko taana qaxalee

Nu waliif diina miti

Nu waliif dhiiga malee!"

Leta Kenei Aga

(አንድ *ቃል ብቻ በማሻሻል የተወሰደ)



t.me/OLDBOOKSPDF

ከመጽሐፉ መቅድም እና መግቢያ ጀምሮ እስከ ምዕራፍ ሦስት ባደረግነው የታሪክ ጉዞ፣ በየጊዜው ለሚነሱ የታሪክ ሙግቶች መልስ ለመስጠት ሞክረናል። ይሁንና ራሳቸውን አስችለን ብንወያይባቸው ጠቃሚ የሆኑ ነጥቦችን ሠፋ አድርገን በዚህ ክፍል መቃኘቱ ተገቢ ምስል ለመፍጠር ይረዳል ብለን በማሰብ እንደሚከተለው አቅርበናል። በውይይቶቹ ውስጥ አወዛጋቢ ጉዳዮችን በአመክንዮ መቋጨት ሲሳነን የዓለም አብዛኛው ልምድ ዳኛ ይሆነናል። ሁለት ፅንፎች ይዘን ዳር እና ዳር ገመድ መጓተቱ ውጤቱ በአንድ አሸናፊ የሚቋጭ አይደለም፤ ይልቁኑ የበለጠ ወደ ማያቋርጥ የግጭት ሽከርከሪት ውስጥ ይዘፍቀናል።

የትኛውም የታሪክም ሆነ የፖለቲካ እሰጥ አገባ ከ100 ሚሊየን በላይ የሚሆነውንና በየጊዜው እያደገ የሚሄደውን ህዝባችንን (ከመሀከል እስከ አራቱ ማዕዘናት በጉስቁልና የሚኖረውን መብራት፣ ውሀ፣ መሠረተ ልማት ብቻ ሳይሆን ልጆቹን ወደ ትምህርት ቤት መላክ ዳገት የሆነበትን ምስኪን አርሶአደር፤ ጎዳና ጠርዝ ላይ ሆነው የቀኑ ዋዕይና የሌሊቱ ቁር ከረሀብ ጋር የሚጠብሳቸውንና ህይወት የፈተነቻቸውን ወገኖች፣ በስደት፣ በአስቀያሚ የሴተኛ አዳሪነት ህይወት፣ በስራ አጥነትና ተጓዳኝ ችግሮች ተስፋ ቢስ የሆኑ ወገኖችን እያሰብን መሆን ይገባዋል።) እንዳችን "ሌላኛችን ክልል" ውስጥ (በአንድ ሀገር ውስጥ ሆነን የኛ ያልሆነ ክልል ይኖር ይሆን?)፤ ከፋ ዘመን የተከለብንን አጥር አልፈን የወገናችንን መንሳቆል ብንመለከት ለፀብ የሚሆን ሥፍራ ባላገኘን ነበር። ለዚህ እስተውሎ አልታደልንምና በታሪክ ክርክር መያዛችን ማይገታ ሆኖ ስለተገኘ መስታወቱን እነሆ፡-

## ታሪካችን የተናጠል የየአንዳንዱ ጎሳ፣ የየብሔረሰቡ ወይስ የጋራ?

*"የእከሌስም ሐውልት ለወላይታው ምኑ ነው?"*

አቶ መለስ ዜናዊ አስረስ

የጫካውን በከፋት የተሞላ የሽፍትነት ዘመኑን ትተን ከ1991 ጀምሮ ግብአተ መሬቱ እስከተፈፀመበት ድረስ ኢትዮጵያን የርስት ያህል በጠቅላይ ሚኒስትር ይዞ ያመሰቃቀላት 'ሊቀ ሰይጣን' መለስ በተንኮል የተካነና ማበላሸት የሚፈልገውን



t.me/OLDBOOKSPDF

ማንነታቸውንም ጉዳይ ቃላት ሳይመርጥ በመወርወር ሁሌጊዜም ከፊት ተሰላፊ ነበር። የሚሰነዝራቸው ቃላት በሚገባ ታስበባቸው ዲላማውን ለመምታት በመርገ የተለወሱ ሆነው የሚቀሰቀሱ ናቸው። ኢትዮጵያንና ታሪኳን ለማፍረስም የመለስ ዜናዊን ያህል የተጋ ሰው ይኖራል ብሎ ማሰብ ይከብዳል።

መቶ ሚሊዮን ሕዝብ የሚመራ ግለሰብ በአደባባይ አንድ ዜጋ በሀገሩ ታሪክ እንዳይኮራ ሲናገር ከመስማት በላይ ምን ሚያሳቅቅ ነገር አለ? ሲዳማው በጢያ ችክል ድንጋይ፣ ቦረናው በኮንሶ የአስተራረስ ዘዴ፣ ጂማው በጅጎል ግንብ፣ ሶማሊው በከፋው ከልደመቀ በአንድ ሀገር የመኖር ትርጉሙ ምንድነው? ለተሸከርካሪ 'አማ አሮ ትግ ሐረ...' ብሎ ብሔረሰብ የመደበው ሥርአት ብርቅዬ የዱር እንስሳትን በክልል ጠርንፎ 'ቀይ ቀበሮ ለጋምቤላ ምኑ ነው?'፣ 'ሉሲ ለጉሙዙ ምኑ ናት?' በማለት ኢትዮጵያን በተፈጥሮ ሀብት፣ በቅርስ፣ በአሴት ሸንሽኖ ለማፍረስ የተጋ የታሪክ አራጅ ስለመሆኑ በድፍረት እንናገራለን።

በሌሎቹ ከፍሎች ለማየት እንደሞከርነው አቴንስ ዴሞክራሲዋን በጀመረችበት ወቅት (ከሌሎቹ የዛሬዋ ግሪክ ግዛቶች ጋር ፈፅሞ አንድነት አልነበራትም። ሁሉም ግዛት የተለያየ መንግሥትና ህልውና ነበረው።) የክብር ዶክተር የነበሩት ከበደ ሚካኤል፦ "የዓለም ታሪክ" በሚል ርዕስ ከ60 ዓመታት በፊት ባሳተሙት መፅሐፍ ገፅ 160፦ "ግሪኮች በብዙ ከተሞች ተለያይተው ለየብቻቸው መንግሥት ስላቆሙ የፖለቲካ አንድነት አልነበራቸውም ነበር..."በማለት መረጃ ጠቅሰው ታሪክ አኑረውልናል።

ከውህደታቸው በኋላ ግን ሁሉም የግሪክ ከተሞች ያለልዩነት የአቴንስ ዴሞክራሲ የጋራችን ነው ብለው ይኮሩበታል። (የአቴንስ ሰዎች ብቻቸውን ይህ ታሪክ የኔ ነው ብለው አይመፃደቁበትም። ሁሉም ግሪካዊ በመላው ዓለም ሲጓዝ ታሪኩ የእኔ ነው በማለት ይደምቅበታል።)

ኢራቅ እንደ ሌላ ምሳሌ ብትወሰድ በቅኝ ገዢዎች ከመጋጠሟ በፊት የነበራት የባቢሎን የሜሶፖታሚያና መላው ታሪኳ የጋራ እንጂ የተበጣጠሰ የቀበሌ ታሪክ አይደለም። እንኳን እንደ ኢትዮጵያ ህዝብ የተገመደ የዘመናት ህልውና ያለው ህዝብ ቀርቶ በቅርቡ የተዋሀዱት የቅኝ ግዛት ስሪቶች (ከ1960 በኋላ የአፍሪካ ሀገሮች ጭምር) ታሪካቸውን ከቅርብ ጊዜ አይጀምሩም።



t.me/OLDBOOKSPDF

ሁኖን በ1776 ከብሪታኒያ ቅኝ አገዛዝ ነፃ የወጡበት አዋጅ "American ation of Independence አውጀው (ጦርነቱ ከ1775 እስከ 1783 በሂደቱ 13 መንግሥታት ይዘው ሀገር መሠረቱ። በ1860ዎቹ 33 ሆነው 50 ያህል ግዛት ማለትም:- አላባማ አላስካ አሪዞና አርካንሳስ ካሊፎርኒያ ኮኔክቲኩት ዴለዋሬ ፍሎሪዳ ጆርጂያ ሀዋይ ኢዳሆ ኢሊኖስ ኢንዲያና ሎዋ ,ንተኪ ሉሲያና ሜይን ሜሪላንድ ማሳቹሴትስ ሚቺጋን ሚኔሶታ ሚሲሲፒ ንታና ኔብራስካ ኔቫዳ፣ ኒው ሃምፕሻየር፣ ኒው ጀርሲ፣ ኒው ሜክሲኮ፣ ኒው ኖርዝ ካሎሪና፣ *ኖርዝ ዳኮታ፣ ኦሀዮ ኦክላሆማ ኦሪጎን ፔንሲልቫኒያ፣ ሮዲ ድ፣ *ሳውዝ ካሮሊና፣ *ሳውዝ ዳኮታ፣ ቴኔሲ ቴክሳስ ኡታህ ቬርሞንት ዋሺንግተን፣ *ዌስት ቨርጂኒያ፣ ዊስኮንሲን የሚገኙ እና ዲስትሪክት ኦፍ የ ናቸው። (*የአቅጣጫ መገለጫዎች ከስያሜ ጋር ስለተያያዙ ወደ አማርኛ ብዙም አስፈላጊ መስሎ አልታየኝም። ሆኖም በሊሎቹ ርዕሶች አብዝተው . ስሞችን ሰሜን ደቡብ ምዕራብ እና ምስራቅ ተጠቅመናል።)

ተለያዩ ጊዜያት በጉልበት በግገር በድርድር እና በተለያዩ ሁኔቴዎች የተዋሀዱ የአንዱ ግዛት ታሪክ የኔ አይደለም' አይሉም። በየትኛውም ግዛት ያለው ኔ ነው በማለት ይኮሩበታል እንጂ። ሌላ ምሳሌ ለማከል:- ቅኝ በመግዛት ከፍለ ዘመን ማብቂያ ሩብ ያህሉን የመሬት ከፍል የተቆጣጠረቻው ቀድሞ የቼልቲኮች ሀገር ሆና ቆየች። ከ5ኛው ከፍለ ዘመን ጀምሮ አንግሎች ጁቶች እና ቱሪንጂያውያን ወደ ግዛቲቱ መግባት ጀመሩ። በ829 ችና ሳከሶኖች አንድ የአንግሎ ሳከሶኖች መንግሥት ተመሠረተ። በ18ኛው ን መጀመሪያ ከሌሎች ግዛቶች ጋር ተዋሀደች። (Act of Union)፤ የታሪኳ ሆኖ ሳለ ከጥንት ቼልቲኮች ጊዜ ጀምሮ ያለው ታሪኳ የሁሉም ዜጎቿ የጋራ ርጋ ትቀበላለች።

ላይታ ሰው አሜሪካ ሀገር ስለኢትዮጵያ ታሪክ እንዲገልፅ ሲጠየቅ ደረቱን መ ታሪክ ከሉሲ ቀድሞ በመነሣት እስከ ቅርብ ጊዜያትን ታሪክ ይተነትናል ነገራችን የሆኑ አከሱሞች፣ ዛግዌዎች፣ ስሎሞናውያን፣ የገዳ ሥርአት ዱ ማህበረሰቦች በተለያዩ ጥጎች ነበሩ ታሪኩ ለእኔ ምንም አይደለም' ብሎ ዓለም እንደሚሳለቅበት ለውይይት አይቀርብም። ወደ ኢትዮጵያ ታሪክም በቀደመው ከፍል እንደተመለከትነው የአንድ ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ



t.me/OLDBOOKSPDF

አባላት ጭምር የየግላቸው የታሪክ ፍሰት ቢኖራቸውም፤ ታሪኩ የወል የሀገሪቱ እንጂ የተናጠል ወከፍ አይደለም። ለምሳሌ:- የቦረና ኦሮሞ ከ1467 ጀምሮ የራሱን አባ ገዳዎች በመምረጥ፤ በራሱ ምክር ቤት "ጉሚ ጋዮ" እና አስተዳደራዊ ሥርአት የሚመራ ነበር።

አዋሳኝ ከሆኑት የጉጂ ኦሮሞዎች፣ የሶማሊ ጎሳዎች፣ ኬንያ ውስጥ ካሉ ሌሎች ጎሳዎች ጋ ጭምር እየተዋጋ እስከ 1991 ይኖር ነበር። (ግጭቱ የግጦሽም አልነው የሌላ መነካካቱ አሁንም ቀጥሏል። *አሁን ሰንል 2019 መሆኑ ታሳቢ ይደረግ።) ቦረና ምንም እንኳ ከጉጂ ኦሮሞዎች ለዘመናት በግጦሽ እና አንዱ የሌላውን ወገን በማጥቃት የበቀላ እርምጃዎች በሁለቱም ወገን ቢካሄዱም፤ በሌላ በኩል አጠገቡ ካለው የኮንሶ ማህበረሰብ ጋር ግን አንድም ግጭት ሳያደርግ አብሮ ኗሯል። ለተመሣሣይ ያህል ዘመን የጉጂ ኦሮሞ ከቦረናው ያልተናነሠ ዴሞክራሲያዊ የአስተዳደር ሥርአት መሥርቶ እስከዛሬ (2019) ዘልቋል። የኦሮሞ ጊቤ ነገሥታት ጂማ ጉማ ጎማ ጌራ እና ሊሙ ኢናርያ እንዲሁም ሌቃ ቄለም እና ሌቃ ለቀምት ከቦረና እና ከጉጂ ከተለያዩ ቢያንስ ከ1460 ዎቹ ጀምሮ የየራሳቸው አስተዳደር መሥርተው በኋላም በንጉሥ (ሞቲ) መመራት ጀምረዋል።

ይህም ዐፄ ምኒልክ ወደ ሥፍራው ከመንቀሳቀሳቸው በፊት ለመሆኑ የሚከተለውን ማሳያ ዋቢ እናድርግ:- ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ በእንግሊዝኛ ቋንቋ "A Modern History ..." በተሰኘው መፅሐፋቸው ገፅ 62:- "ከ1882 - 1886 የኦሮሞ ግዛቶች በሰላም ለራስ ጎበና ዳጬ እጅ መስጠታቸውን፤ ከእነዚህም ደጃዝማች ኩምሳ ሞሮዳ (ገብረእግዚአብሔር) የሌቃ ለቀምት ገገር፤ ደጃዝማች ጆቴ ቱሉ የሊቃ ቄለም መሪ፣ ዳግማዊ ጂማ አባ ጂፋር የጂማ ንጉሥ..." ተጠቅሰዋል።

በተመሣሣይ በአርሲ እና በሸዋው ንጉሥ ምኒልክ በሚመራው የሸዋ የምዕራብና የደቡብ ጦር መሀከል ግጭት ሲደረግ "የአርሲ መሪዎች ሱፋ ኩሶ እና ደሙ ኡሱ እጅ እንስጥ ሲሉ ሌሎቹ ገገርዎች እምቢ አሉ። የአርሲዎችን የውስጥ ክፍፍል በመጠቀም ራስ ዳርጌ አሸነፉ።" በኩረ ፅሑፉ ከአርሲዎች የተወሰኑ ክፍሎች እንደ ጊቤ እና ሌቃ አቻዎቻቸው በሰላም እጅ ለመስጠት የወሰኑ መሆኑን እና ግጭቱ ከተወሰኑ ክፍሎች ጋር መሆኑን እንመለከታለን።

አይኬ ሀበርላንድ:- "አርሲዎች ከያዙት የቦታ ስፋት የተነሳ በአንድ ገዳ የማይተዳደሩ፤ የተለያዩ ሃላፊዎችና የየራሳቸው መተዳደሪያ መመሪያዎች ነበራቸው" ሲል ገልጿል።



t.me/OLDBOOKSPDF

የእኛ ሀገር ታሪክ ሲወሳ ከሌሎቹ (በቅርብ ተዋህደው ታሪካቸውን የጋራ ካደረጉት ይልቅ) የበለጠ ተሳስረን በመኖራችን የአንዱን ብሔረሰብ ታሪክ አንፃፍ ስንል የበርካቶችን መንካት ግድ ይሆናል። የመገፋፋቶች የአብሮነት የፍቅር ታሪክ ጭምር አለንና፡ በርካታ ጥናታዊ ፅሑፎች "Inter Ethnic Relations" (የማህበረሰቦች ግንኙነት ታሪክ ሲፅፉ፣ በተለያዩ ርዕሶች ስር ቀድመንም ወደፊትም እንደምናየው ታሪኩ የጋራችን ነው።)

በአጭሩ በመላው ዓለም በየትኛውም ሀገር የፖለቲካ ካርታ ውስጥ የተቀመጠ የህዝብ ታሪክ የጋራ እንጂ የተናጠል አይደለም። ትግራዩ አከሱምን የብቻዬ፣ አገው ላሊበላን የኔ ብቻ፣ ጎንደር በፋሲለደስ አትምጡብኝ፣ ኦሮሞ በገዳ ሥርአት ምን ኮነሰራችሁ? ካለ ... አብረን በወል ታሪካችን ካልተዋብን የታሪክ ትርጉሙ ምንድነው? በሀገርስ አብሮ መኖር ምን ፋይዳ አለው? በዩኔስኮ ያስመዘገብናቸው ቅርሶች በክልል ወይስ በሀገር? የማነስ የትንሽነት የተበጣጠሰ ታሪክ የመያዝ አናሳ መንፈስ ሊመታ ሊወገዝ ሊነወር ሊደፈቅ የተገባ ነው።

## ኃይል ሲጠቀም የኖረው ማነው?

መላው ዓለም የተመሠረተው በኃይል አንዱ ሌላውን አሸንፎ፣ እያስገበረ፣ ባርያ አድርጎ እየሸጠ፣ በቅኝ ግዛት እየያዘ፣ በይገባኛል ጥያቄ እየተፋለመ ነው። በቅርቡ (2016-2019) በኢትዮጵያ ውስጥ የተከሰተውን ብቻ ብንመለከት ሁለት ሚሊየን ኦሮሞ ከሶማሊ፣ ከግማሽ ሚሊየን በላይ ሶማሊ ከኦሮሚያ፣ ከግማሽ ሚሊየን በላይ ጌዴኦ በጉጂ፣ በመቶ ሺህዎች አማራዎች ከተለያዩ ስፍራዎች ተፈናቅለዋል። (በየስፍራው ከደረሰው መሠናዘር የተወሰነው በዚህ መፅሐፍ ውስጥ ተወስቷል።) በየትኛውም የታሪክ ወቅት ህዝቡ ሌላውን ወገኑን ጠልቶ 'ይውጣልኝ' ብሎ ሰላማዊ ሰልፍ አድርጎ አያውቅም። የመንጋው መሪ በግል ፍላጎቱ ወይም ከኋላ ባሉ ገፊ ኃይሎች ተነሳስቶ "በሰው" ሲል፣ ሊበው፣ ጦረኛው፣ ስራ አጡ፣ የስነልቡና ቀውስ ያለበት ግሪሳ "ግር" ብሎ ይነሳል።



t.me/OLDBOOKSPDF

ዝብ እንጂ፥ ኢያረረ ባለመደራጀቱና ባለመታጠቁ ወሮበሎችን ማስቆም አይችልም። ርአት አልበኝነት እንዳይነግሥ መሥራት መንግሥት ከህዝብ ጋር የሚገባው መጀመሪያው ውል (Contract) ነው። በተለያዩ የኢትዮጵያ ታሪክ ዳራዎች አከሱም ፍን ተሻግራ ሜሮዌን ደምስሳለች። ሀሮልድ ማርከስ ገፅ 10 ላይ እንዳሰፈረው፡- ጀግራል አብርሀ መዳከሟን ዐይቶ አሻፈረኝ እስከ.ል ደቡብ አረቢያን ገዝታለች።' ዲት በ10ኛው ክፍለ ዘመን በርካታ ሥፍራዎች ላይ ጉዳት አድርሳለች። ዛግዌዎች አክሱማውያን በጉልበት ሥልጣን ነጥቀው የተለያዩ አስተዳደሮችን መሥርተው ሰፊ ኢትዮጵያን ክፍል መርተዋል።

'ሰሎሞናውያኑም' በተመሣሣይ ከዛግዌዎች ሥልጣን ነጥቀው ያንንው መንገድ ተከትለዋል። አፋር አርጎባ ሐረሪና ሶማሊ አማራና ትግራይ ላይ ጉዳት አድርሰዋል። የኦሮሞ የተለያዩ ጎሳዎች ጦረኞች በሌሎች ማህበረሰቦች ላይ ዘምተው ተፋጥረዋቸዋል። ካፋ በጎረቤት ማህበረሰቦች ላይ ኃይል በመጠቀም አዋህዷል። አንዱ በሌላው ላይ መዝመቱ የሰው ልጅ የማያቋርጥ የሀብት፣ የቦታ፣ የዝና፣ ስግብግብነት ወይም አንድም የዘመን ኋላ ቀርነት - ሁለትም ከዘመን ቀድሞ አደጋን በማየት አንድ የመሆን ፍላጎት ነው። የግጭቱ መነሻ ቀና የመሆን ያለመሆኑ ጉዳይ ሌላ ነገር ሆኖ የትኛውም ያልተገባ የኃይል አጠቃቀም ትላንትም ዛሬም ነገም ሊወገዝ ይገባዋል። የውግዘቱ ዓላማ ተመሣሣይ ድርጊቶች እንዳይፈፀሙ ለማስቀረት (Preventive approach) ለመከተል ነው።

ወንጀሎች ከተፈፀሙ እርምጃው (Curative Approach) የመንግሥት ድርሻ ነው። ህዝበኝነትን (ለመጥፎ ዓላማ በጋራ መነሳት) አስወግደን ህዝባዊነት (ለመልካም ፍፃሜ በጋራ መነሳትን) እንላበስ። የአኖሌን ሐውልት በተመለከተ አንድ ቀን የእናቱን ጡት እየጠባ ያደገው የኦሮሞ ልጅ አፍርሶ በምትኩ በስፍራው ላይ "የኦሮሞና አማራ አንድነት ሐውልት" ይገነባበታል። ዛሬ ዓለማችንን የሚያስጠሩት ብርቅዬ የአርሲ አትሌቶቻችን ያዩቶቻቸው ከየት እንደሄዱ ስናስስ ሸዋ ላይ መጥተን እናርፋለን። (አንዱ 'ጥንት ጡት ተቆረጠ፤ ሌላው እስከ ቅርብ ጊዜ የወንድ አካል ሲቆርጥ ነበር') በማለት የትውልዱን ወርቃማ አብሮነት ማበላሸት ተገቢ አይደለም። ዛሬ ከሳሽም ሆነ ተከሳሽ የለም። የታሪክ ማወራረጃ የሚሆን ተጠያቂም የለም።

አንኳን የጥንቱን ቀርቶ የቅርብ ጊዜያት በደሎችን በይቅርታ እየሸፈንን ድርጊቱን በጋራ እያወገዝን ካልተጓዝን ትርፍ ስናሰላ ውጤቱ ኪሳራ ነው። ታሪክን ለዓላማው ብቻ



t.me/OLDBOOKSPDF

እንጠቀምበት። 'የቦረና ታሪክ ለጂማው ምኑ ነው?' ኢይባልም። ለመሆኑ 'አማራው ኦሮሞ ወንድሙ ላይ ዘምቷልን?' ቀደም ብለን እንዳየነው ታሪክ የመገፋፋቶች ድምር ውጤት ጥምር ነው። ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አንድ ብቻ የነበረ ሲሆን፤ ንጉሦች በተለያዩ አካባቢዎች በርካታ ሊሆኑ ይችላሉ። የጂማ ንጉሥ (ሞቲ)፣ የጎጃም ንጉሥ፣ የሸዋ ንጉሥ፣ የጉራጌ ንጉሥ አዝማች አበጋዝ፣ የካፋ ንጉሥ (ታቶ)፣ የወላይታ ንጉሥ (ካዎ)፣ የየም (አኖ)፣ የሸካ (ታቶ) የሀዲያ (ገራድ)፣ የቦረና መሪ (አባ ገዳ)፣ የጉጂ መሪ (አባ ገዳ) ... አንዱ በሌላኛው ጉዳይ ጣልቃ ሳይገባ በተመሳሳይ የታሪክ ወቅቶች ጎን ለጎን እየተገፋፉ፤ አቅም ሲደረጅላቸው ሌላውን እየገፉ በአንድ ሀገር (ኢትዮጵያ ውስጥ) ኖረዋል።

በቅርብ ዘመን ታሪክ አፄ ምኒልክ ሀገርን መልሶ በማዋሀድ ሂደት (Reunification) ከላይ ከጠቀስናቸው የኦሮሞ አስተዳደሮች ጋር ከ1882 - 1886 ያለምንም ደም መፋሰስ ሰላማዊ ግንኙነት ፈጥረው መጓዝ ችለዋል። ግጭት በነበረባቸው በአርሲ አኖሌ (1886) እና ከሐረሪዎች በኢሚር አብዱላሂ የሚመራ ጦር ጋር (1887) በተደረገው ጦርነት የደቡቡም፣ የምዕራቡም፣ የመሀከሉም ጦር ዋና ተዋናዮች ሆነዋል። በእነዚህ ጦርነቶች ውስጥ የጎጃም አማራ፣ የጎንደር አማራ እንዲሁም የወሎ አማራና የወሎ ኦሮሞዎች (በአፄ ዮሐንስ አስተዳደር ስር ስለነበሩ) በአኖሌም ሆነ በጨለንቆ ጦርነት ላይ አልተሳተፉም። የሸዋ አማራ፣ የሸዋ ኦሮሞ፣ የሌቃዎች ኦሮሞ፣ የጊቢዎች ኦሮሞ እና ሌሎች የደቡብ አካባቢ የጦር አበጋዞች ከሸዋው "ንጉሥ" ምኒልክ ጦር ጋር በማበርና በመተባበር በራስ ዳርጌ አማካይነት አኖሌ ላይ ዘምተዋል።

ከዚህ ቀደም ብሎ በጎጃሙ ንጉሥ ተክለሀይማኖት የጦር አበጋዝ ደጃዝማች ደረሶ የሚመራውን ጦር - በራስ ጎበና ዳጬ የሚመራው የሸዋ (ኦሮሞ/አማራ) ጣምራ ኃይል ሊሙ ላይ ወግተው አሸንፈዋል። ሁለቱ ንጉሦች (ተክለሀይማኖት እና ምኒልክ) ደግሞ እምባቦ ላይ (1882) ተዋግተው የጎጃም አማራ ተሸንፏል። ይህ መራራ እውነት የሚያሳየን የሸዋ አማራ እና የሸዋ ኦሮሞ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች በመሆን በአንድ በኩል የጎጃም አማራን በሌላ በኩል የአርሲ ኦሮሞን፤ ከደቡብ የተለያዩ ማህበረሰቦች ጋር በመተባበር በጦርነት መውጋታቸውን ነው።

ይህ ሀቅ እነማ ወለጋ አካባቢ ከተመሠረተበት 1870ዎቹ ጀምሮ በአጠቃላይና ወያኔ ኢትዮጵያን በተቆጣጠረበት ጊዜ (1991) እስከ የኦሮሚያ አመፅ (2016) ድረስ የሸዋ ኦሮሞን "የጎበና ዘር"፣ "የምኒልክ ተባባሪ"፣ "ሸዋ እኮ አማራ ነው" የሚል ተቀጥላ



t.me/OLDBOOKSPDF

እየተነጠለው (በቋንቋው ከአማርኛ ጋር ጉራማይሌ መሆን ጋር ተያይዞ ጭምር) መገፋት እንደደረሰበት መካድ፤ የምንኖርበት እውነት ላይ ዐይን ማጉረጥረጥ ከመሆን የዘለለ አይደለም። ዘውጌዎች በብሔረሰብ ቋንቋ ላይ ተመሥርተው የጀመሩት ከፍፍል በአካባቢያዊነት ትርምስ (The tribal politics of Somalia) አይነት እንደሚቋጭ ጥርጥር የለውም።

የታሪኩን ቅጥፈት በምን መልኩ እንደሚቀነባበር አንድ ማሳያ እንመልከት። የኢትዮጵያ ፀር የሆነው መለስ ዜናዊ አስረስ፦ "ዴሞክራሲና ዴሞክራሲያዊ አንድነት በኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ ብሔረሰቦችን ለማናከስ ባዘጋጀውና ለህትመት በበቃው ሰነድ ገፅ 4 ላይ የሚከተለው ይነበባል።

> *የአፄ ምኒልክ ወታደሮችና የጦር አበጋዞች በአብዛኛው ከተነሱበት ከሰሜን ሸዋ አካባቢ የመነጩ ስለነበሩ ነፍጠኛው በመሠረቱ የአማራ ብሔር ተወላጅ ነው ማለት ይቻላል። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የአፄ ምኒልክን ሠራዊት የተቀላቀሉ የተለያዩ የደቡብ ምዕራብና ምሥራቅ አገራችን አካባቢ ገዢዎችም በጥቅም በከፊል እንዲጋሩ ተደርጓል። ለዚሁ በምሳሌነት የሚጠቀሱት እንደ ራስ ጎበናና አባ ጂፋር ያሉት ናቸው። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ነፍጠኛ ማለት በመሠረቱ አፄ ምኒልክን ተከትለው የዘመቱ የጦር አበጋዝና ወታደር ስለሆነም የአማራ ብሔር ተወላጅ ነው ማለት ይቻላል።*

ሲል ይደመድማል። ይህንን የመለስ ዜናዊን ፅሑፍ ስንመለከት በውስጡ ሊተከላቸው የፈለጉ መርዞች እንዴት እርቃኑን እንደሚያስቀሩት እንመለከታለን። ጥቂት ነጥቦችን እናንሳ፦

1. "ጦረኞቹ ከሰሜን ሸዋ አካባቢ የዘመቱ ናቸው" በሚለው ውስጥ መለስ የአማራ ህዝብ ሳይሆን ጦረኞች ያውም ከሰሜን ሸዋ አካባቢ የተነሡ መሆኑን አልደበቀም።

2. "የተለያዩ የደቡብ ምዕራብና ምስራቅ አካባቢ ገዢዎች ... እንደ ራስ ጎበና ጂማ አባ ጂፋር ያሉቱ..." መለስ እንደገለፀው ከሆነ ገዢዎቹ ብቻቸውን አልዘመቱም። ለምሳሌ ጎበና እና አባ ጂፋርን ሲገልፅ ብቻቸውን መጥተው የሰሜን ሸዋውን ጦረኛ እንዳልመሩ ይታወቃል። ለምሳሌ ሲጠቅስልን እነ ጆቴ ቱሉ እና ኩምሳ ሞሮዳን እንድንጨምር እየፈቀደልን ነው። እነዚህም ብቻቸውን የሰሜን ሸዋን ጦረኛ አልመሩም።



t.me/OLDBOOKSPDF

3."የደቡብ ምዕራብና ምስራቅ አካባቢ ገገሮችም..." በብዙ አገላለፅ ተጠቅሞ ሳለ መለስ ዜናዊ ለአኩይ ዓላማው አንድ ሰሜን ሸዋ ላይ ይንጠለጠልና

4. በአሳፋሪ ሁኔታ መደምደሚያው ላይ "ነፍጠኛ ማለት በመሰረቱ አፄ ምኒልክን ተከትሎ የዘመተ የጦር አበጋዝና ወታደር ስለሆነም የአማራ ብሄር ተወላጅ ነበር ማለት ይቻላል።" ይላል። ለቃሉ አገላለፅ ይቅርታ ይደረግልንና ለመለስ ዜናዊ 'መሠሪነት' ከዚህ በላይ ምን ማሳያ ሊቀርብ ይችላል?

አፄ ምኒልክን ተከትለው የዘመቱ የጦር አበጋዞች ከሰሜን ሸዋ፣ ከደቡብ ምዕራብና ምስራቅ የጠቀሳቸውና ያልጠቀሳቸው ሆነው እያለ (አማራ:- ወሎ ጎጃም ጎንደር እንደሌሉበት ራሱ እየመሰከረ)፤ ነፍጠኛ ነፍጥ (ጠብመንጃ) ያነገበ መሆኑ ነፍጠኛም ነፍጥ የያዘ መሆኑ የማያሻማ ሆኖ ሳለ "ነፍጠኛ ... የአማራ ብሄር ተወላጅ ነበር ማለት ይቻላል።" ሲለን በደሙ ውስጥ የሠረፀውን አማራን የመጥላትና የማጥፋት "የህወሓት ማኒፌስቶ" እምነቱ እስከ እለተ ሞቱ አብሮት እንደቆየ በሚገባ ያሳየናል።

ነፍጠኛ በመሠረቱ ነፍጥ ይዞ የተከተለ ማለትም:- የሸዋው ጎበና ዳጬ፣ የጂማው አባ ጂፋር፣ የሸዋው ምኒልክ፣ የወሊጋው ጆቴ ቱሉ እና ኩምሳ ሞሮዳ ሠራዊት፤ ስለሆነም ነፍጥ የያዘ በሙሉ ነው። አስተማሪ፣ ሀኪም፣ ገበሬ፣ በሊመና የሚተዳደር፣ ሲተኛ አዳሪ፣ ጎዳና ተዳዳሪ፣ የግብርና ባለሙያ፣ ሥራ አጥ ተንከራታች ... ከኦሮሚያም ይነሳ ከትግራይ ከጉራጌም ይነሳ ከአማራ "ነፍጠኛ" አይደለም።

እያንዳንዱ ሙያ ወይም አስገዳጅ የህይወት ፍርቱና አለው። የሀገር ዳር ድንበር ለመጠበቅ የተዋደቀ ሠራዊትና ዛሬም መሣሪያ ይዞ ሀገር ያቆመ ሠራዊት ነፍጠኛ አይደለም። ይልቁኑ ዛሬም ነፍጥ ነከሰው ሰላማዊውን ነዋሪ አላላውስ፤ ከስፍራ ስፍራ አላንቀሳቅስ ያሉ 'የ21ኛው ክፍለ ዘመን ነፍጠኞች' በተባበረ የህዝብ የአእምሮ ክንድ እና ሰላም በሚያስከብረው ወገን መደፈቅ አለባቸው። ከላይ በጠቀስነው ሰነድ ገፅ 3 መለስ ዜናዊ የከተበው እንዲህ ይነበባል:- "አፄ ምኒልክ ... በሰሜን የነበሩ የአማራና የትግራይ ተቀናቃኞቻቸውን ለማስገበር ... የአፄ ምኒልክን የበላይነት ላለመቀበል ቢፋለሙም የማታ የማታ የበላይነታቸውን አሜን ብለው ተቀበሉ።"

መለስ አፄ ምኒልክ አማራና ትግራይን በተመሳሳይ እንደተፋለሙ ገልፆ ማጠቃለያው ላይ "አማራ ነፍጠኛ ነው" ሲል የከበበው ግሪሳ መንጋ እንደ ገደል ማሚቱ ይሆንንው



t.me/OLDBOOKSPDF

ደግሞ ያስተጋባል። (እዚህ ቦታ ላይ ደግሞ ፍላጎቱ አማራውን እርስ በርሱ ከፋፍሎ ማዳከም ነው።) ለበቀቀኖቹ መለስ ከተናገረ የቅዱሳት መፃህፍት ቃል ያህል ነው። በተቀን ያለህ!!!

(የዓለማቀፍ ጋዜጠኛ አበበ ገላው በአንድ ዓለማቀፍ ጉባዔ ላይ አዳራሽ ውስጥ ገብቶ በዓለም መሪዎች ፊት፦ "Meles zenawi is a dictator!" - በማለት ድምፅ ላልነበራቸው ኢትዮጵያውያን ድምፅ ሆኖ የህዝብን ብሶት ማስተጋባቱ ተገቢ መሆኑን ጠቅሰን መለስን በአጭሩ ስንገልፀው፦ ውርደት ልብሱ፤ ቅሌት ምግሡ፤ ርኩሰት ትሩፉ፤ ቅጥፈት ማንነቱ ነውና (ሐረጎቹን መጠቀሙ ከባድ ቢሆንም "መራራ እውነት" በጠጣር ቃላት ሀቅን ከመጋፈጥ አትቦዝንምና ተገቢ አድርጋ ትወስዳለች። በህይወት ቢኖር የሚገባው የህዝብ ፍርድ ሌላ ነበር።)

መለስ፦ በተለያየ ጊዜ በአካታችነቱ ወደር የማይገኝለትን የኦሮሞን ማህበረሰብ "ጠባቦች" ማለቱም ከቶውኑ አይዘነጋም። የኢትዮጵያ ታሪክ መጋኛ መለስ ዜናዊ እንደመሆኑ መቶ መፃሕፍት ከመጥቀስ "አውራዋን እናት ንብ" ብናጠቃ መንጋው ይበተናል። መለስ በዚሁ ድርሳኑ ገፅ 18 ደግሞ የሚከተለውን ይላል፦

> *...በአሁኑ ጊዜ ኢብሳ ጉተማ በጠባብ ብሔርተኝነት የሚታወቀው የኦሮሞ ነፃነት ግንባር ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ቢሆንም በተማሪነቱ ወቅት ብሄራዊ ማንነቱን አሳልፎ ለመስጠት የነበረውን ዝግጁነት በግጥሙ አመላክቷል። ... ከነፍጠኛው ገዢ ጋር ተሰልፈው የጥቅም ተጋሪ መሆን ይፈልጉ በነበሩ አንዳንድ የጭቁን ብሄር ምሁራን ዘንድ ምን ያህል ወጤት እንደነበረውም ያሳያል።*

መለስ ዜናዊ በዩኒቨርሲቲ ተማሪው ኢብሳ ጉተማ ላይ የዘመተበት ኢብሳ "ኢትዮጵያዊ ማነው?" በሚለው ግጥሙ 'ብሔረሰብ ለእኔ ትርፍ ነው እልፉ ያሚጋዬ ኢትዮጵያ ናት።' አይነት ይዘት ያለው መልዕክት ስላስተላለፈ፤ ሌሎች የኦሮሞና የኢትዮጵያ ልጆች ኢትዮጵያን እንዳያስቀድሙ ለመመረዝ አልሞ ነው። መለስ ከአፋ የማይነጥለው ዋለልኝ መኮንን "ታገል" መፅሔት ቅፅ 5 ቁጥር 2 ላይ የከተበው የሚከተለው መልእክት ነው፦ *"ይህ የተወገረገረ ብሄርተኝነት ምንድን ነው? በቀላሉ*



t.me/OLDBOOKSPDF

ሲታይ... የአማራ ትግሬ የበላይነት አይደለምን? ማንኛውንም ሰው የኢትዮጵያ ቋንቋ ምን እንደሆነ ጠይቆ... ምላሹ ወይ የአማራ ነው አሊያም የአማራ ትግሬ ነው።"

መለስ ይህንን በመኪድ ቢፅፍም መጨረሻ ላይ "አማራ ነፍጠኛ ነው።" በማለት ያጠቃልላል። ዋለልኝ መኮንን ምንድነው? ከመለስ ጋር ተሰልፈው የተዋጉና የተሰዉ (በሬ ከአራጁ) የአማራ ኢህዴን ብአዴን አባላት ምንድናቸው? በዚህ መልክ ስለ ትግሬ ትንፍሽ ሳይሉ አማራን በአንድ የሰሜን ሸዋ ቀበሌ ጦረኞች (9/10ኛው የሸዋው ምኒልክ ጦረኛ ከአማራ ውጭ መሆኑ እየታወቀ) ህዝብን መፈረጅን ምን ይሉታል?

ከዚህ አኳያ እውነታው አርሲ አኖሌም ሆነ ጨለንቆ ላይ የተፈፀመው የትኛውም ጥቃት ተዋናዮች ህዝቡ ሳይሆን ከሸዋ አማራ፣ ከሸዋ አሮሞ፣ ከሌቃ አሮሞ፣ ከጊቤ አሮሞ፣ ከጉራጌ እና ሌሎች በምዕራብና ደቡብ የተውጣጡ የጦር አበጋዞች በሸዋው ንጉሥ (የወቅቱ የሸዋ አሮሞና የሸዋ አማራ በዋናነት "የሸዋው ንጉሥ" ምኒልክ) የጦር አበጋዝ ራስ ዳርጌ መሪነት የተፈፀሙ ጥቃቶች ሲሆኑ፤ ሌሎቹ ጦርነቶች ደግሞ በራስ ጎበና ዳጬ የተፈፀሙ ናቸው። ልብ ሊባል የሚገባውና በጣም ሊሰመርበት የሚገባው ጉዳይ በአኖሌም ሆነ በጨለንቆ ጦርነት ጊዜ (1872 - 1889) የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የትግራዩ አፄ ዮሐንስ አራተኛ ነበሩ።

ከሸዋው ንጉሥ ምኒልክ ጋር ባደረጉት ስምምነት ምኒልክ ላይ ከፍተኛ ግብር በየዓመቱ እንዲከፍሉ ጭነውባቸው ግብሩን ለመክፈል ወደሁሉም አቅጣጫ እንዲንቀሳቀሱ ፈቅደው ለጦርነቱ ይሁንታ እንደሰጡ መደበቅ አይቻልም። በተመሣሣይ የአማራው ህዝብ በአንድ አስተዳደር ሥር አልነበረም። በዘመነ መሣፍንት (1769 - 1855) የተከፋፈለ እርስ በርስ የሚዋጋ ከመሆኑም ሌላ ሸዋ በንጋሢ ክርስቶስ አማካይነት ከ1696 ጀምሮ የራሱ መሪ ያለው፣ በዘመነ መሣፍንት 1813 - 1847 በራሱ ንጉሥ (ሳህለሥላሴ) የሚመራ እና ከሌላው አማራ'የተገነጠለ' ነበር።

ከላይ ቀደም ብሎ የተጠቀውን መራራ ሀቅ ለአሮሞ ፅንፈኞች፣ ከታች የተጠቀሰው መራራ እውነት ለአማራ ፅንፈኞች፣ ድምሩ ደግሞ ለትግራይ ፅንፈኞች እንደሚጎመዝዛቸው የታወቀ ነው። ምክንያቱም ሁሉም መንጋዎች እንደ ሀገር ሳይሆን እንደ ጎጥ በማሰባቸው የተጣባቸው በሽታ በቀላሉ ስለማይተዋቸው ነው። በመለስ ዜናዊ ስሌት ከሄድን 'የቦረና አሮሞ ታሪክ ለወለጋው ምኑ ነው?'፤ 'የጉጂ አሮሞ ታሪክ



t.me/OLDBOOKSPDF

ለአሁኑ ምን ነበር? ፣ "የግንቦር ሌሊቶች ታሪክ የሚያው ምን ነው? እያሉን የዛሬን ታሪክ ሸንግነን ማጣሪያችን አይፈልጉም። ለመማር በመሥማሪያችን ታሪክ የጋራችን አሻ የተናዘለ አይደለም። የሕብረተሰብ የሆነ ትንሽ የሚያ ስዶች ዜማዎች መፃፊት አንዱን የዛሬን ታሪክ መማሪያችን አይፈልጉምን? ዓላም ምር አንድነት ታሪክን በጥንቱ አይፈልጉም።

ከዚህም ጋር አያይዘን በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ እጅግ በጣም ብዙ የፍቅር ዘመን ያለፈ የሆነ መጨረሻውን አለመስራም ድርስ የተጠሉ እየሰራው ዜማችን ነው። የተወለዱ ምሁራችን ለማግኘት እጅ ቴዎድሮስ የሸዋን ሰው እጅን ቆርጠው ንጉሥ ምኒልክን ማርከው በወሰዱበት የበረከት ጦርነት (1856) የተገጠመው የዘመናት መዝሙር ሰንኝ፡

"ወይ ቴዎድሮስ እጅግ ተጫረዱ፣

የሸዋን ሰው ሁሉ እጅ ነሰተውት ሄዱ።"

ንጅ ነሰተውት" እጅን ቆርጠው ማለት ነው። ድርጊቱ የተፈፀመው በቀጥታ ከአኖሌ ጦርነት ሠላሳ ዓመት በፊት ነበር (1856 እና 1886)፤ ሆኖም ድርጊቱ 'አማራው - አማራው ላይ የፈፀመው ነው' በማለ አንድም ጊዜ አይጠቀስም። ""አኖሌ ላይ ጡት ተቆርጧል።" የሚለው ተረክ ሆን ተብሎ የተፈጠረ እንጂ በኢትዮጵያ ታሪክ "ሴቶችን የሚገድል፣ የሚጎዳ ድርጊት "ከግርዛት፣ ጠለፋ፣ ማህፀን መስፋት፣ ያለእድሜ ጋብቻ፣ ማገለል ውጪ ተሰምቶም ታይቶም አይታወቅም።

ከወሬ ያለፈ አንድም በፅሑፍ የተቀመጠ ታሪካዊ ማስረጃ የለም። የሚያሳዝነው አሣና ወያኔ (በተለይም ወያኔ አብዝተው ለጥላቻ ስለተጠቀሙበት) በወያኔ ሥርአት ጊዜ ውስጥ (በ1990ዎቹ) አርባ ጉጉ፣ አርሲ ውስጥ የሴቶች ጡት በሌለ ብቀላ ተቆርጧል። ማንቁርት ገደል ውስጥ አማራዎች በቋንቋቸው ምክንያት ብቻ ከህይወታቸው ተወርውረዋል። ጡት አልተቆረጠም እንጂ ቢቆረጥ ኖሮ ዛሬ ታሪኩ የሚጎዳው ማን ማንን እንዲጎዳ ነው? የወጠኑት ማጨራረስ አርባ ጉጉ ላይ ተፈፅሞ ዛሬ አፍርቶላቸዋል። ዛሬ ዘመኑ የሚጠይቀው በየእምነታችን ሰውነታችን የሞራል ልዕልናችን ይቅርታ ፍቅር አንድነት ተሰናስለን መራመድ ነው።



t.me/OLDBOOKSPDF

የከሀደት እና የጥላቻ አዙሪት የያዘን እኛ፤ 'ሁሉን ቢናገሩት ሆድ ባዶ ይቀራል' ሆኖ እንጂ የወንድ አካል መቁረጥ (መሰለብ) በእኛው ትውልድ አካባቢ፣ በመዕሐሩ አዘጋጅ እድሜ አልነበረምን? የደማቅ ታሪካችን ሰበዞች ቢወሱ ትውልድ ስለሚያንፁ እንጂ እልፎ አልፎ የምንፈፅመው የከረፋ ተግባር ይወሳ ከተባለ የአርባ ምንጭ የገሊ ቦረና የጌዴኦ የአደላ ሰዎች ቢጠየቁ አይመሰክሩምን? ራያ አካባቢስ የተሰለቡ አሁን በህይወት ያሉ ብዙዎች አይደሉምን?

በታሪክ ባልቻ ሳፎን በ1870ዎቹ እና 80ዎቹ ነገሌ ቦረና የነበሩት ካህን አባ ወልደመስቀል፣ በተመሣሣይ ጊዜ የአዶላው ካህን አባ ፈለገብርሀን የራያ ሰለባዎች መሆናቸውን የማያወቁ የየከተማዎቹ ነዋሪ የለም። ደግሞስ ጣና በለስ ሰው በብሔሥሰቡ ምክንያት በድንጋይ ወግረን የገደልን፣ በራዩ ላይ የጨፈጨፍን፣ ጂግጂጋ እና ለቀምት ከነህይወቱ ያቃጠልን፣ ሻሸመኔ ዘቅዝቀን የሰቀልን፣ ወንድማችን የሆነን የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ቀጥቅጠን የገደልን (2018 - 2019) በምን የሞራል ልዕልና 132 ዓመታት ወደኋላ ሄደን በዚያን ዘመን በነበሩ ጦረኞች ምክንያት ዛሬ ላይ ዘመን ተበድረን ጣት እንቀሳሰራለን? ወንጀለኞችን ዛሬ (2019) በጉያህ ሸጉጠህ ስለምን ድሮ ታወራልኛለህ? ብለን ብንጠይቅ መልስ የለም። ሲጠቃለል ታሪካችን የሁሉም ኢትዮጵያዊ መስተጋብር የጋራ ድምር ታሪክ ውጤት ነው።

## የስንት ዘመን ታሪክ?

በቀዳሚው የጋራ ታሪካችን ብያኔ ላይ ተመሥርተን የኢትዮጵያ ታሪክ የ3ሺህ ዘመን ወይንስ የ100 ዓመት? የሚሉ ሙግቶችን ለመመልከት የሚረዱንን መንደርደሪያዎች እናገኛለን። በአንድ ሀገር ውስጥ የሚገኝ ህዝብ ታሪኩ የቁጥቁጥ በጥብቆ ውስጥ የሚሸጎጥ ትንሽ ሳይሆን በወል የካበተ ትልቅ ነው። ኢትዮጵያ ሀገራችን ቅድመ ታሪክ የሰው ልጅ መነሻ ስለመሆኗ በማውሳት ቡትዘር ካርል፡- "The Rise and Fall of Axum, Ethiopia. A Geo - archaeological Interpretation" ገፅ 46 ላይ በዝርዝር ስለ ሉሲ "በአንፃሩ ወጣቷ አፅም" በማለት በሚገባ አስረግጧል።



t.me/OLDBOOKSPDF

በተመሳሳይ ድህረ ታሪክ (በታሪክ ዘመን) የሰው ልጅ ስሉፍ ሲጀምር የዛሬ 6ሺህ ዓመት ጤፍ ዳጉሳ እና እንሰት ኢትዮጵያ ውስጥ ስለመተከላቸው የታሪክ ድርሳናት ያሳያሉ። ለአብነት ሀሮልድ ማርከስ፡- "A History of Ethiopia" በተሰኘው ጥልቅ ጥናቱ ገፅ 3 "ከክርስቶስ ልደት በፊት ሶስት ሺህ ዓመት የነበሩ 36 አይነት አዕዋትና አዝርዕት በተለይ ጤፍ እና እንሰት ቀዳሚ ወይም ሁለተኛ ትሆናለች።" ይለናል። ኢትዮጵያ ቅድመ ታሪክ ከዓለም የመጀመሪያ፤ በታሪክ ዘመን ደግሞ እንደ መሪው ጥንካሬ ወይም ድክመት እስከ አረቢያ እና ሶማሊያ በተለያዩ አቅጣጫዎች ስትሰፋ እና ስትጠብ ኖራለች።

በዘፈቀደ የኢትዮጵያ ታሪክ ተንታኝ የሆነው መለስ ዜናዊ በሰከነና ከሸፍጥ በፀዳ ህሊና፣ የማይፅፍ እንደመሆኑ፤ እርስ በርሱ በሚላተመው ዕሳቤ፡- "ዴሞክራሲ እና ዴሞክራሲያዊ አንድነት በኢትዮጵያ" ሰነድ ገፅ 2 ላይ ሳያገናዝብ ሀቁን እንደሚከተለው አፍረጥርጦታል፡- " ... *የማዕከላዊ መንግሥት ግዛት በየወቅቱ ሲሰፋና ሲጠብ የነበረ መሆኑን የታሪክ ምሁራን ያወሳሉ።"*

አሜሪካዊው ማርከስ "የኢትዮጵያ ታሪክ" በተሰኘው ጠማሩ ካስቀመጣቸው ነጥቦች የተወሰኑት መስተጋብሩን እንዲያመላክቱ በማሰብ በጥልቀት ጥናት ማድረግ ለሚፈልጉ ገፆቹንና ይዘቶቹን በአማርኛ ተርጉመን እንደነገሩ ሁኔታ አስፈላጊ መስሎ ሲታየን እንግሊዝኛውን እንዳለ በማስፈር ለአንባቢዎች ግልፅነት ለመፍጠር ጥረት አድርገናል። ይህ ጥረት የኢትዮጵያውያንን የዘመናት ትስስር የመግለፅ አቅም አለው ብለን እናምናለን።

ገፅ 24፡-

> *አቡነ ያዕቆብ በአፄ አምደፅዮን (1314 - 1344) ባለው ጊዜ ከግብፅ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት እንደመሠከሩት 'አፄ አምደፅዮን የአዋሽ ሸለቆን ተሻግሮ ወደ ደቡብ ገስግሷል። ዋናው ፍላጎት ማዕከላዊና ደቡባዊ ሸዋ ውስጥ ዳሞትን ጨምሮ አዳዲስ ለተቋቋሙ አብያተ ክርስቲያናት ካህናትን ማሟላት ነበር።'*

ገፅ 32 ላይ፡-



t.me/OLDBOOKSPDF

> 'በኢማም አህመድ ኢብራሂም (ግራኝ አህመድ) አብዮ፣ ክርስቲያናዊ ንጥየ ቅድሳት ሲቃጠሉ ለማዳን አልተቻለም። ባሌ፣ ሲዳሞ እና ሀድያ በፍጥነት ተያዙ። አፄ ልብነድንግል ከትግራይ አማራ አገው፣ ቤገምድር ጎጃም እና ሸዋ ጦር አውጣጥቶ ከአዲስ አበባ 50 ኪ.ሎ ሜትር ርቀት ላይ ስለመሸነፉ ያወጋል። ፀሐፊው የጠቀሰው የሽምብራ ኩሬ ጦርነት መሆኑ አያከራክርም። እዚህ ላይ አዲስ አበባን ጨምሮ ጥንታዊ የተደበቁ ፅላቶች የመገኘታቸውን ምሥጢር ማጤን መልካም ነው። አፄ ዘርዓያዕቆብ 1445 ላይ የምሥራቁን የአዳል መሪ ሱልጣን አህመድ ባድላይ መርታታቸውን ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ፦ "A Modern ..."

ላይ ገልፀዋል።

ማርከስ ገፅ 25 ላይ ስለ ዘርዓያዕቆብ ያኖረው ሐተታ በጣም ቁልፍ በመሆኑ እንደወረደ እነሆ፦

> *"Zara Yakob ... Together clergy and king created an ideology for a united state ... In the most remote areas, the emperor liberally endowed monasteries and churches, making land grants with property confiscated from defeated rulers ... Zara Yakob was a great leader of Ethiopia. He was remarkably consistent in working for Ethiopia's unity from Eritrea south through Shewa into Sidama country.*

ሲዳማ የሚለው በስፋት ለደቡቡ ክፍል የሚያገለግል ሆኖ ቦረናች እና ጉጂዎች አማርኛንም ሆነ ሌሎች ከኦሮምኛ ውጪ የሆኑ ቋንቋዎችን ዛሬም "አፋን ሲዳማ" በማለት የሚጠሩ ስለሆነ የትሥሥሩን ጥልቀት ለማሳየት ይረዳል። አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ለኢትዮጵያ አንድነት ከኤርትራ እስከ ሲዳማ በርትተው ይሰሩ እንደነበር እንመለከታለን።

ገፅ 29 ሲነበብ፦ 'የሀዲያው መሪ ልጅ ንግሥት እሌኒ የተለየ ብቃት ያላት ትንታግ ነንስት መሆኗን! ከባለቤቷ ከአፄ ዘርዓያዕቆብ ሞት በኋላ በአፄ በዕደማርያም ጊዜ



t.me/OLDBOOKSPDF

(1468 - 1478) ቀጥላ እስከ አፄ ልብነድንግል (1508-40) ወሳኝ መሆኗን ስንገዘብ የመስናኝታችን ቅኔ እስከየት እንደሚዘልቅ እናስተውላለን። ማቴዎስ በተባለ አርመናዊ ነጋዴ አማካይነት ለፖርቱጋል መንግሥት የመጀመሪያውን ደብዳቤ የፈቸውም የሀዲያው መሪ ማሂቀ ልጅ ንግሥት (Queen Mother) እሌኒ ነች። ዘርዓያዕቆብ ይፋት ፈተጋር ባሌ ሀዲያ ወላይታእንጦጦ መናገሻ የረር ጅባት እና ዝዋይ ደሴትን ጭምር ተቆጣጥሮ ነበር።

የኢትዮጵያ ግዛት ወሰን የመስፋትና የመጥበብ ባህርይ በሀገራችን ብቻ የተፈጠረ የተለየ የታሪክ ፍሰት ሂደት ሳይሆን፤ በመላው ዓለም የተለመደ የሰው ልጆች ግንኙነት አካል ነው። የኛን ለየት የሚያደርገው በዘመናት መስተጋብር ውስጥ በተፈጠረው ድንበራችን ሊነገር በማይችል ፍቅር ስንዋህድ እንደቆየን የታሪክ ማስረጃዎችና የወላጆቻችን ትውፊቶች ይነግሩናል። እኛም በመፅሐፉ ካካፈልናቸው ማስረጃዎች በተጨማሪ ከጳውሎስ ኞኞ "አጤ ምኒልክ" ገፅ 445-447 ላይ የቀዳነውን ማስረጃ እነሆ፦

አልፎንሶ አልበከርክ (1503 ዓ.ም) ባስቀመጠው ማስታወሻ፦

> *የሀበሾች ግዛት ዳርቻ ከምፅዋ ሱዋኪን አርኪኮ ጀምሮ እስከ ሞቅዲሾና ሶፋላ በመዘርጋት ከኑብያውያን ጋር ይዋሰናል" ይለናል። ይህም ከሰሜን ጫፍ እስከ ምስራቅ ጫፍ አሁን ከያዝነው ወሰን እልፎ ወደ አጎራባች ሀገራት ይዘልቃል።*

የሊበላን አብያተክርስቲያናት ዐይቶ ነፍስ ያልቀረለት ፖርቱጋላዊው ፍራንሲስኮ አልቫሬዝ 1520፦

> *የሐበሾች ግዛት ከትልቁ ወደባቸው ከቢሊ በመጀመር በአዳል ምድር አልፎ ሀዲያ፤ በህንድ ውቅያኖስ እስከ ሞቅዲሾ የተንጣለለ ነው። ሀበሾች ወደ ድንበራቸው ሲጓዙ መንገድ እያበጁ ነው*

ሲል ያወጋናል። አምደፅዮን በ1316 ዳሞት፣ 1317 ሀዲያ እና ጎጃምን ከመያዙ በተጨማሪ ሰፊ ግዛት ለማስገበሩ በርካታ የተሰነዱ ድርሳናት ይነግሩናል። የሚከተለውን ማስረጃ እንመልከት።

ካርት ደስ ኖቫስ 1521፦



t.me/OLDBOOKSPDF

*ህበሾች ተዋጊና ጠላት በተነሱባቸው ጊዜ ሀገራቸውን እንደተርብ አየተናደፉ የሚከላከሉ፤ ግዛታቸው ቀይ ባህርን ተሻግሮ አረቢያ ድረስ የተዘረጋ ነው፤*

በማለት ካርታውን በዐይነ ህሊናችን ስሎ ዛሬም ያሳየናል።

ከዚህ አኳያ የኢትዮጵያ ዳር ድንበር ከምፅዋ እስከ ሶማሊያ፣ ከምዕራብ እስከ ደቡብ (አሁን ካለን ግዛት የሰፋ ቢሆንም)፤ የውስጥ ፍቅራችን ከጎለበተ ጅቡቲ፤ ኤርትራ እና 'ላንዶች' በፈቃዳቸው ወደ ሆታችን መቀላቀላቸው አይቀርም። ባይሆንም እንኳ ድንበር የማያግደው የአውሮፓውያን አይነት ነፃ ዝውውር ልንፈጥር እንችላለን። ከሁሉም የሚቀድመው መላ ኢትዮጵያውያን አፍ ከልብ ሆነን እና ያለ ጎጥ ልዩነት በምክንያት በማመን ሀገራችንን ለመለወጥ ስንተጋ ነው።

ከ1862 ጀምሮ በፈረንሳይ ተይዛ የነበረችውን አቦክ (ጅቡቲን) ከ27 ዓመታት በኋላ በ1889 ወደ ሥልጣን የመጡት ምኒልክ በተለመደው ብልህት ፈረንሳይን አግባብተው የሊዝ ኮንትራት አስፈረሟት። እንዳለመታደል ሆኖ (ጥናት የሚጠይቅ ሆኖ) በመመለሻዋ ጊዜ ሀገራችን ውስጥ ስምምነት በመታጣቱ፣ ኮሎኔል መንግሥቱ አሳልፈው ሊሰጧት እንደተገደዱ በገደምዳሜ "ትግላችን" - በተባለው የራስ ግለ ታሪክ መፅሐፋቸው ሊደብቁን አልቻሉም።

## የኦሮሞ መነሻ (ምንጭ) ከየት ነበር?

ስለኦሮሞ መነሻ በኢትዮጵያ ስነፅሑፍ እና ታሪክ ውስጥ የተለያዩ መረጃዎች አሉ። አንዳንዶቹ፡- "ከማዳጋስካር"፣ ሌሎቹ "ከደቡብ ምስራቅ እስያ"፣ የተወሰኑት ደግሞ "ከሶማሊያ" የሚሉ ጠማሮች ለንባብ አብቅተዋል። ለምሳሌ፡-

ቻርለስ ቤከ፡- 'ኦሮሞ ከባሮ ወንዝ በደቡብ ምሥራቅ በኩል በመነሳት ወደ ወለጋ ገባ' ሲለን፤ የስኮቲሽ ተወላጅ የሆነው ጀምስ ብሩስ ደግሞ፡- 'ኦሮሞ ሲናር ከተባለ ሥፍራ ከሱዳን ተነሳ' በሚል የጀምስ ብሩስን የጉዞ አቅጣጫ ይከተላል።



t.me/OLDBOOKSPDF

ክሪስቶፈር እህረት፡- "Cushitic Prehistory. In : Non Semitic Languages of Ethiopia" ገፅ 88፡- የኦሮሞን መነሻ ሰሜን ሶማሊያ አካባቢ ያደርገዋል። ይህ ሀሳብ ስፔንሰር ትሪሚንግሀም፣ ሃንትግሮፎርድ፣ አንቶኒዮ ዲ. አባዲ 'የኦሮሞ መነሻ ከውጭ ሀገር ነው' በማለት ከጠቀሱት ጋር ተመሳሳይ ነው። ኢንሪኮ ቼሩሊ እና ኢዮ ኤም ሌዊስ በተመሣሣይ የኦሮሞን መነሻ ከኢትዮጵያ ያርቁታል። እነዚህ ወገኖች የሚያቀርቡት ማስረጃ መሠረተ ቢስ መሆኑን በኦሮሞ ታሪክ ዙሪያ ሰፊ ጥናትና ምርምር ያደረጉ ምሁራን ይስማሙበታል። የእኛም ምልከታ ከታሪክ ምሁራኑ ጋር ለምና ወርቅ ነው።

ከቶሊ ካዊው መነኩሴ አለቃ አፅመጊዮርጊስ ገብረክርስቶስ በሌላ በኩል ኦሮሞዎች ከገላና ወንዝ አካባቢ የተነሱ ሲሆን፡-

'ኤርጋን ዱ'ፍተን ዱ'ፍቲ አማን ወላቡ ባ፡፤

ዱቢ አከና ኤገሬ ሂምቢከኑ'

ከይዘት አኳያ ሲተረጎም 'የፍጥረት ዘመን ከተቆጠረ ጊዜ አንስቶ እንደዚህ ያለ ክስተት ለምተን አናውቅም' እንደሚሉ አስረድተዋል። አከለውም የተለያዩ አዳዲስ ጉዳዮች ሲፈጠሩ፡- 'ከወላቡ ከተንቀሳቀስን ወቅት ጀምሮ እንዲህ አይነት ነገር አጋጥሞን አያውቅም።' ማለታቸውን ጠቅሰዋል። በርግጥም ኦሮሞ በአናት ምድሩ ኢትዮጵያ ውስጥ በነበረ ታሪካዊ መገፋፋት ዘመናት የተሻገረ እንቅስቃሴ ማድረጉን በማስረጃ አስደግፈን ማረጋገጥ እንችላለን። እንደ "The World Almanac (2010)" ማስረጃ ገፅ 778፡- ‹‹ የኢትዮጵያ ህዝብ ስብጥር ኦሮሞ 32%፣ አማራ 30%፡ ትግራዋይ 6%፡ ሶማሊ 6% ..." ያህል እንደሆነ ይገመታል።

በዚህም መሠረት ከእያንዳንዱ ሦስት ኢትዮጵያዊ አንዱ ኦሮሞ ነው። ይህ ከኢትዮጵያ ህዝብ ሲሶ የሚሆነው የኦሮሞ ማህበረሰብ በጋራ እና በጎሳ ወይም አካባቢ ደረጃ የተናጠል ኑባሬ ቢኖረውም በኢትዮጵያ ታሪክ አካልነቱ እንጂ በተናጠል ሊጠና አይችልም። የወሎ ኦሮሞ ከቋንቋው በስተቀር ከሌላው ኦሮሞ በላቀ ሁኔታ በአቅራቢያው ካለው ህዝብ ጋር በበርካታ ሁነቶች ይመሳሰላል። ሶዶ ኦሮሞና ሶዶ ጉራጌ አንድና ያው ናቸው። ቦሬ ያለው ጉጂ ሀገረ ሰላም ካለው ሲዳማ ጋር ከቶውኑ አይለይም።



t.me/OLDBOOKSPDF

የሸዋ አማራና የሸዋ ኦሮሞ ያለው ስነልቡናዊ ጥምረት ጎጃም እና ሸዋ አማራ መሀከል ካለው በብዙ እጥፍ ይበልጣል። ግብፅ መጠሪያ ስሟ "United Arab Republic" ነው። ሞሮኮ ሊቢያ አልጄሪያ ኢራቅ ... አረቦች ናቸው። አንድ ቋንቋ መጠቀማቸው እና ሀይማኖታቸው አንድ አላደረጋቸውም። ሶማሊ አንድ ቋንቋ እና ሀይማኖት መጋራት በአንድ ጥላ ስር አላሰባሰበውም። የቦረና ኦሮሞ 1/3ኛው ኬንያ ውስጥ ነው። ሶማሊያ እና ኬንያ ጦርነት ቢገጥሙ ኬንያ ውስጥ ያሉ ሶማሊያዎች ሶማሊያ ውስጥ ካሉ ሶማሊዎች ጋር፤ ኢትዮጵያ ከኬንያ ብትጋጭ የቦረና ኦሮሞ በሁለት በኩል፤ አፋር በሶስት ሀገር... መጋጨቱ አይቀርም። በጣም ግልፅ ለማድረግ ኢትዮጵያና ኤርትራ ጦርነት ሲገጥሙ፦ ትግርኛ ተናጋሪው በሁለቱ ተቃራኒ ጎራ፤ አፋርኛ ተናጋሪው፤ ኩናማው በሁለቱ ተፃራሪ አቅጣጫ ሆነው ሲፋለሙ ዐይተናል። የሀገር ትርጉሙ በጣም ሰፊ ነው።

የኦሮሞን የትመጣ በተመለከተ የታሪክ ምሁራንን በመጠቀምና መረጃና ማስረጃዎችን በማጣቀስ የተለያዩ ፀሐፍት የበኩላቸውን አበርክተዋል። ከእነዚህም መሀከል ከ1974 - 1991የኢትዮጵያ ፕሬዚደንት የነበሩት፣ የሸዋ ኦሮሞው ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ወልዴ እያና፦"ትግላችን - የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ" በተሰኘው መፅሐፋቸው ገፅ 26፦ ከፃፉት በቀጥታ የተወሰደ፦

> *የኦሮሞ ብሔረሰብ በኢትዮጵያ ደቡብ ክልል ዛሬ ቦረና ብለን በምንጠራው አካባቢ ለብዙ ጊዜ ሠፍሮ ኖረ። በ16ኛው ምዕተ ዓመት አንዷሁ ከቦረና በመንቀሳቀስ በጋሞ ጎፋና በሲዳሞ ክፍለ ሀገሮች መሀከል በሚገኙት በጫሞ በአብያታ በአዋሳና ዝዋይ ሀይቆች አካባቢ ....ታችን በባሌ ክፍለ ሀገር ውስጥ በተለይ በገናሌ ወይብና በዋቢ ወንዞች ሸለቆዎችና አካባቢዎች ተንሰቶ ሰላማዊ እንቅስቃሴ አደረገ።... በ16ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ የአገሩን ደጋማ ክፍሎች መቆጣጠር ጀመረ። በመንገዱ የሚያገኛቸውን በአገሪቱ ደቡብ፣ ምዕራብ፣ ምስራቅ እና እንዲሁም መሀል ሀገር ነዋሪ የሆኑትን የተለያዩ ነገር ማህበረሰቦችና የህብረተሰብ ክፍሎች እየተቆጣጠረ ... የጎሳ ማህበር አባልና የኦሮሞ ቋንቋ ተናጋሪ አደረጋቸው።*

ይህንን መረጃ በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት የፋይናንስ ሚኒስትር የነበሩት አቶ ይልማ ዴሬሳ፦ "የኢትዮጵያ ታሪክ በአስራ ስድስተኛው ክፍለዘመን"በተባለ ርዕስ በፃፉት መፅሐፍ የኦሮሞን እንቅስቃሴን (የኦሮሞን ማህበረሰብ መነሻ) አስመልክቶ



t.me/OLDBOOKSPDF

ከሰነዶሉን አጅግ የሠፋ ይዘት ውስጥ ሁለት አጫጭር መረጃዎችን እንጥቀስ። ገፅ 12፡ "መጀመሪያ የኦሮሞ ነገድ ከደቡብ ኢትዮጵያ ወደ ሰሜንና ወደ ምሥራቅ ጎርፎ የሚበዛውን ይጋ አገር ይዞ ስለሰፈረበት፤ በዘመኑ ታሪክ ውስጥ የኦሮሞን ነገድ ፈንታ ብናነሳው ያለፍን እንደሆነ የ16ኛው መቶ የኢትዮጵያ ታሪክ ሙሉ ሆኖ አይገኝም።"

ይልማ ዴሬሳ 'ኦሮሞ ከውጪ ፈልሶ የመጣ ነው' ከሚሉ ወገኖች በተለየ አኳኋን የኢትዮጵያ ታሪክ ተሟልቶ ይፃፍ ዘንድ፤ ከኢትዮጵያ ልጆች አንዱ የሆነው የኦሮሞ ከገዋ መከተት እንዳለበት ትኩረት ሰጥተው ገልፀዋል። "ሠፈረ" የሚለው ቃል - ሠፈር መሠረተ ከሚለው አገላለፅ ጋር አንድና ያው ነው።

ይልማ ገፅ 227 ላይ ያኖሩት ደግሞ እንደሚከተለው ነው:-

> *"እስከ አስራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ድምፁን ሳያሰማ የቆየው የኦሮሞ ነገድ በ1524 ዓ.ም ከደቡባዊ መኖሪያው መንቀሳቀስ ጀመረ።... ስለዚህ 'ታላቁ ወረራ' ግንባር ቀደም ለመሆን ዕድል የመረጣቸው ጃዊ የተባሉት የባርቱማ ክፍል ጎሳዎች ናቸው።"*

ከላይ ያለውን የይልማ ዴሬሳን አገላለፅ ስንቃኝ፤ ግለሰቡ የዘመናቸው አስተሳሰብ ውጤት እንደመሆናቸው በወቅቱ የተለመዱ አገላለፆችን አስቀምጠዋል። ይሁንና በፅሑፋቸው ውስጥ ልክ እንደ ትግራይና ኦሮሞ ፅንፈኛ ዘውጌዎች ሁሉ ተመሳሳይ ጎልህ ግድፈቶችን በይዘቶቹ ውስጥ እንታዘባለን። የመጀመሪያው ስህተት በሀገሩ ክልል ውስጥ በመገፋፋት ሂደት ማህበረሰብ በአንፃራዊ መልኩ ጉልበቱ ደከም ወዳለው ይንቀሳቀሳል እንጂ 'ወረራ አደረገ' የሚለው አገላለፅ ተገቢ አይመስለንም። የ16ኛው ክፍለ ዘመን የኦሮሞ ጦረኞች እንቅስቃሴ እና የ19ኛው ክፍለ ዘመን የምኒልክ ጦረኞች እንቅስቃሴ ዓላማቸው ይለያይ እንጂ የሂደት ልዩነት የለባቸውም።

የአንዱ እንቅስቃሴ "ወረራ" ከተባለ፤ የሁሉም ያለልዩነት "ወረራ" ነው። የአንዱ ንቅናቄ ከሆነ የሌላውም ንቅናቄ ይሆናል። የአማፂው አህመድ (ግራኝ)፣ የኦሮሞ ጦረኞች፣ የቴዎድሮስ ሠራዊት፣ የዮሐንስ ሠራዊት፣ የምኒልክ ሠራዊት... በታሪክ የተመለከትናቸው ዘመቻዎች በሙሉ፤ የምጣኔ ሀብትና የፖለቲካ የበላይነት ፍላጎት ያገፋቸው የነበሩ ተመሳሳይ ጠባይ የነበራቸው እንቅስቃሴዎች ነበሩ።



t.me/OLDBOOKSPDF

የኢትዮጵያ ታሪክ ችግር ጎጠኞች ሁልጊዜም "የእኔ" የሚሉት ወገን ቅቢ እየቀባ የሚዋብ፤ ሌላው ጦረኛ ሆኖ እንዲሳል መፈለጋቸው ነው። ይህ አይነቱ ታሪክ አንዱ ወገን ደራርቦ ቢለብሰው፤ ለሌላው ወገን ስለሚበርደው፤ ፍፃሜው ስምምነት ማጣት ነው። መልካሙን እየተውን ከፋውን እናንሳ ካልን - 'አዘያም ቤት እሳት አለና' 'የቆከከር ቤት ሳይዘጋ ያድራል።' ላለውም ለመጪውም ትውልድ ሚያስፈልገው ከዘመን ጋር መራመድ እንጂ ከትላንት ጋር በመንታረክ ህይወት የሆነውን ጊዜውን መብላት አይደለም። የትላንት የየአካባቢው መሪዎች ዛሬ የሉምና መፈራረድ አንችልም። በቅገርት ዓለም በድንግዝግዝ ከመደናበር ወጥተን፤ በግላጭ የዛሬዋን ጀንበር ዕንይ። መፅሐፈ ጥበብ 'የሚያስተራርቁ ብፁዓን ናቸው' ይላል።)

Edward Ullendorf:- "The Ethiopians. An Introduction to Country and People" በተሰኘው ጦማሩ ገፅ 76 ኦሮሞዎች በሌሎች ነባር ህዝቦች መሀከል መስፈራቸውን በስፋት አትቷል። አባ ባህሬ የተባሉ በትውልድ ትግሬዋይ የሆኑ የጋሞ መነኩሴ በ16ኛው ክፍለ ዘመን የፃፉት የዐይን ምስክርነት:- ኦሮሞዎች በአፄ ወናግሰገድ ዘመነ መንግሥት ከባሌ አካባቢ ገላና የሚባለውን ወንዝ አቋርጠው መጡ ይላሉ። (*በወላይታ ዙሪያ በተፃፉ በርካታ የታሪክ ምንጮች እንደተገለፀው በ14ኛው ክፍለ ዘመን ክርስትናን በተቀበሉት ሞቶሎሚ አማካይነት "ወላይታ ማላ" የሚባል ሥርወ መንግሥት መሠረቱ።

በ15ኛው ክፍለ ዘመን ምንጩ ከትግራይ የሆነ ሥርወ መንግሥት የመንግሥት ግልበጣ በማድረግ "ትግሬ ሥርወ ማንግሥት" መሠረተ። ወላይታ ጋሞ ጎፋ እና ዳውሮ አካባቢ ከትግራይ በርካታ ካህናት ለቤተ ክህነት አገልግሎት ያተጓዙ ሲሆን የጋሞው መነኩሴ አባ ባህርይ ከነዚህ መሀከል አንዱ ናቸው። አባ ባህሬ (ባህረ):- 'በእንቅስቃሴው ወደ ኋላ ቀርተው የነበሩ ቦረናዎች አፄ ፋሲል ሊወጋቸው በመጣ ጊዜ በኩየራ በኩል መጡ።' ሲሉን ቦረና? የሚለው ስም መጠቀሱ አስደናቂ ይሆናል። በዚህ ዙሪያ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ:- "የአባ ባህርይ ድርሰቶች ኦሮሞዎችን ከሚመለከቱ ሌሎች ሰነዶች ጋር" በሚለው ስራቸው ሙሉውን ይዘት አቅርበውታል።

በታሪኩ ዙሪያ የሚፈጠረው ችግር አባ ባህሬ የዛሬ 600 ዓመታት አካባቢ የነበሩና የዘመናቸው ውጤት መሆናቸውን አለመገንዘብ ነው። አሮጌ አዲስ ስፍራ ሲይዝ ወይም ማህበረሰብን የራሱ አካል ሲያደርግ በዋናነት የሚያደርጋቸው ነገሮች



t.me/OLDBOOKSPDF

የቀደመውን ስም በመተው አዲስ ስያሜ መስጠት ነው። በመሆኑም የቀድሞና አዲስ ይዞታዎችን ለመለየት ያስቸግራል።

ትግራይ አማራና ሌሎች አካባቢዎች የቦታ ስም የመቀየር ልምድ ስለሌለ አሮሞ ደርሰባቸው የነበሩ ሥፍራዎችን ለማወቅ ብዙም አንቸገርም። የአሮሞ የዘውግ ታሪክ ፀሐፊዎች መሠረታዊ ችግር የሌላውን ማስረጃ አፈታሪክ በማለት ሲያጣጥሉ፤ የእነርሱን መረጃ (የፈጠራ ድርሰት) ሌላው እንዲቀበል ከውይይት ያፈነገጠ አካሄድ መከተላቸው ነው። ተመሳሳይ ዝንባሌ በአማራና ትግራይ ዘውግ ልሂቃን ይንፀባረቃል።

የታሪክ መምህሩ የካፋ ተወላጅ በቀለ ወልደማርያም አደሎ፡- "የካፋ ሕዝቦችና መንግሥታት አጭር ታሪክ" በተሰኘው በ2004 በአማርኛ ቋንቋ ለህትመት በበቃው የምርምር ሥራው ያነሳቸውን አንኳር ሀሳቦች ማስፈሩ ለውይይቱ ያለውን ጠቀሜታ ከግምት አስገብተን እንደሚከተለው አቅርበነዋል።

ገፅ 91፡-

> *በ17ኛው ክፍለ ዘመን መግቢያና አጋማሽ ላይ የሸካና የሂናርዮ መንግሥታት በአሮሞ ተስፋፊዎች መሸነፍ ለካፋ መንግሥታት ምቹ ሁኔታዎች መፍጠሩን ላንጌ ይገልፃል። እነዚህን መንግሥታት በየተራ ያሸነፈው የአሮሞ ተስፋፊ ኃይል በ17ኛው ክፍለ ዘመን ማብቂያ ላይ በካፋ ጦር ዲንቻ (ጊቻ) ሸለቆ አካባቢ ድል ሆኖ መመለሱን ከላይ ለመግለፅ ተሞክሯል።*

ገፅ 88፡-

> *በኋላም በዚሁ በ17ኛው ክፍለ ዘመን ማብቂያ ላይ የአሮሞ ወራሪዎች ባደረጉት የመስፋፋት ጦርነት በዲንቻ ሸለቆ አካባቢ ከፍተኛ እና ወሳኝ ሽንፈት ደርሶባቸው አብዛኛው ጦር ሲደመሰስ ቀሪውም ምርኮኛ ሆኗል። ከዚህ ወሣኝ ድል በኋላም ካፋ ለሁለት መቶ ተከታታይ ዓመታት ፖለቲካዊ ነፃነቷን ጠብቃና ሉዓላዊ መንግሥት ሆና መቆየቷን አረጋግጣለች። (ላንጌ 1982፣ ቢበር 1923)*

t.me/OLDBOOKSPDF

{በቃላ ወ. አዩሎ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ለረጅም ዓመታት በታሪክ መምህርነት የቆየ ቢሆንም ለቃላት አጠቃቀሙ ጥንቃቄ እንዳላደረገ ሰናያለን። ግለሰብን ወይም ቡድንን በጠንካራ ቃላት መግለፅ የተለመደ ነው። ሆኖም "የአርሞ ወራሪዎች" አይነት አገላለፅ ተገቢ አለመሆኑን ልናሰምርበት ይገባል።

በሀገሪቱ ሁሉ ክፍል አሮሞ እንቅስቃሴ ማድረጉ እርግጥ ሆኖ ከውጭ እንደመጣ የሚቀርቡ የታሪክ ትርክቶች ውሀ ማይቋጥሩ መሆናቸውን ማስገንዘቡ የታሪክ ክርክራችንን ሙሉ ያደርገዋል።) በተለያዩ ጊዜያት በኦሮሞ ዙሪያ የፃፉ የታሪክ ተመራማሪዎች፡- አይኬ. ሐበርላንድ፣ ሔርበርት ሌዊስ፡ መሀመድ ሀሰን እና ኡልሪሽ ቤሬውስካምፐር እንዲሁም የኦሮሞ ታሪክ ምሁር የሆነው *መሀመድ ሀሰን፡- 'የኦሮሞ መነሻ ደቡብ ኢትዮጵያ በተለይም በቀድሞዎቹ የባሌ እና የሲዳሞ ጠቅላይ ግዛቶች (ክፍለ ሀገሮች) እንደሆነ ይስማማሉ። (*መሀመድ ሀሰን ዘግየት ብሎ የአቋም ለውጥ በማድረግ ኦሮሞ በሰፊው የኢትዮጵያ ክፍል እንደነበር ለማሳየት ሞክሯል።)

ለታሪክ ሙግት ይጠቅም እንደሆነ እንጂ ኦሮሞ አሁን ከያዘው ስፍራ ሚያነቃንቀውም ሆነ፣ ተጨማሪ አንድ ስንዝር መሬት የሚያስጠይቀው ዳራ የለም። ባንታደል ነው እንጂ፣ ሁሉም የኦሮሞ ነው - ኦሮሞም የሁሉም ነው። በአንድ ምድር እየኖሩ አንዱ ለሌላው ባይተዋር የመሆን ስሜት ሀሊናን ደም በደም ያደርጋል፡፡በኦሮሞ ዙሪያ የሚነሳው የታሪክ እሰጥ አገባ በሁሉም መስክ የአንበሳውን ድርሻ ይይዛል። በመሆኑም የበለጠ ግልፅ ለማድረግ አሜሪካዊው ሀሮልድ ማርከስ በኦሮሞ ዙሪያ ከሌሎች ፀሐፍት በተሻለ ሚዛናዊ ዕይታ ያሰፈረ ይመስለናል።

የኦሮሞን መነሻ፡- 'ከኢትዮጵያ ውጭ አርቀው' የሚያመላክቱንም ሆኑ፣ 'መላውን ኢትዮጵያ ጠቅልለው ለኦሮሞ የሚያጎናፅፉ' "ጠቅላይ አግላዮች" የሆኑ የኦሮሞ ልሂቃን፣ ሁለቱም ጎራ ከእውነታው አብዝተው አፈንግጠው ስሜታቸውን ሲያንፀባርቁ የሚገርመው ጉዳይ መነሻቸው የሚያሳፍር መሆኑ እንጂ ወርቃማው መንገድማ የአፍሪካ ሀገሮች ጭምር በመሀከላቸው የሚነሳውን የድንበር ውዝግብ በአንፃሩ የፈታው፡- "ያለውን ነገር ዛሬ ባለበት ሁኔታ ማስቀጠል" /Status quo ነው። ለታሪክ ፍጆታ ማርከስ ያነሳቸውን ነጥቦች በመጠኑ ሰፋ አድርገን እንቃኝ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ገፅ 34፡-

*Muslims, especially in the border provinces of Yifat, Dawaro and Bale, remained disaffected, and in the extreme south the Oromo awaited their chance to occupy large areas of the fertile highlands. The original homeland of the Oromo, a Cushitic speaking pastoralist people, has been located in northwest Borena.*

የኦሮሞን መነሻ ሰሜን ምዕራብ ቦረና እንደሆነ ይገልፅልንና ገፅ 35 ላይ፡-

*Some Oromos may have attained the high plateaus as early as the late thirteenth century, only to be contained by the garrisons that the Solomonic state established along the empire's periphery. When the defenses were destroyed during the Muslim war, the Oromo resumed infiltrating, even as Lebna Dengel restored a semblance of Solomonic government in the empire's territory.*

ከ13ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የተወሰኑ ኦሮሞዎች አምባዎችን የመቆጣጠር ሁኔታ እንደነበራቸው፤ ወደፊት እንዳይገፉ የሰሎሞናውያኑ በየዳርቻው መከተም እስቸጋሪ እንደሆነባቸው፤ ኢማም አህመድ መከለያዎቹን ሲደረምስ ኦሮሞዎች ልብነድንግል አንፃራዊ አቅም እያለው ጭምር አልፈው መግባት መቻላቸውን ያስረዳል።

ገፅ 36 ፡-

*ኦዲሱ ጦረኛ ቡድን (ሉባ) ሥልጣን ከመረከቡ በፊት ኦዲስ ስፍራ መያዝ ይጠበቅበታል። ... ኦሮሞ በሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ ወደ አርሲ ሸዋ ወለጋ ጎጃም እና በሰሜን ምሥራቅ ወደ ሐረርጌ እና ወሎ (traditional Amhara) በመንቀሳቀስ ሠፈ ቦታ መያዙን ይገልፃል። በርካቶች*



t.me/OLDBOOKSPDF

እንደሚሰማሙበት የኦሮሞ እንቅስቃሴ በጣም ኢሲሎ የሆነው ከ1522 - 1618 ነው።

ገፅ 38፡-

"Shewa, where the indigenous Amhara had been driven from the middle highlands into the highest and coldest parts of Menz and Merhabete or into the relatively unhealthy adjacent lowlands.

በመረጃው ውስጥ የምናየው ዋና ጉዳይ በሸዋ የቀደሙ ነዋሪዎች የነበሩ አማራዎች ከመሀከለኛ ከፍተኛ ቦታዎች ተገፍተው እጅግ በጣም ተራራማ እና ቀዝቃዛ ወደሆኑት መንዝና መራቤቴ ወይም በአንፃራዊ መልኩ ለኑሮ አመቺ ወዳልሆኑ (ለጤና ተስማሚ ያልሆኑ) ተጎራባች ዝቅተኛ ሥፍራዎች (ቆላ) ወርደዋል። በዚህ ገፅ ክርስቲያኖች ከሀናቱን ንብረታቸውን ለኦሮሞ በመተው ስፍራውን እርግፍ አድርገው እንደተዉ ያስረዳል።

(*የመማሪያ መፃሕፍትን እንደ ዋቢ መጥቀሱ የተለመደ ባይሆንም - ከፈጠራ ድርሰ ተነስተው ሳይሆን ከታሪክ ምንጭ ቀድተው - ቢያንስ ከ2006-2019 በአገልግሎ ላይ ያለውን የ11ኛ ክፍል ታሪክ የታሪክ መፅሐፍ፡ ከገፅ 92-97 ስንመለከ ያዘጋጁት የታሪክ ምሁራን፡- አልጄሪራ ቴጁባ እና ወንዱ ተከለመድህን፣ አርቃ ብርሀኑ ላሚሶ እና የመጨረሻ አርትዖት - ተመስገን ጉዲና ካነሷቸው ነጥቦች ው የሚከተሉት ይገኛሉ፡-

1. የኦሮሞ መነሻዎች - መዳ ወላቡ፣ ሆሮ ወላቡ፣ ቱሉ ወለል፡ ቱሉ ቱርቁር፣ ሆሮ ... የባሌ ከፍተኛ ቦታዎች ናቸው።

2. የኦሮሞ እንቅስቃሴ ከ1522 - 1618 የተካሄደ ሲሆን በተለይ በ155( በ1580ዎቹ በጣም የተጠናከረ ነበር።

3. አፄ ገላውዴዎስ የኦሮሞን እንቅስቃሴ ማስቆም አልቻለም። ኦሮሞዎች ሀዲያ ሻርካ፣ ደዋሮ እና ፈጠጋርን አጥቅተዋል። መጀመሪያ ኡዱ ዝቢ ላይ አዲስ



t.me/OLDBOOKSPDF

ከመሠረቱ በኋላ ጥቃታቸውን ወደ ቢዛሞ ዳሞትና ጋፋት ላይ ከፈቱ። ቢዛሞና ዳሞት ወደ ጎጃም አቅጣጫ ሲሸሹ የተቀሩት ተዋሀዱ። የኦሮሞን እንቅስቃሴ ካፋ በሚገባ መከላከል ሲችል ኢናርያ ግን አልቻለም።

5. የገዳ ሥርአት ከ16ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የከሰመባቸው ምክንያቶች፦

5.1 በረጅም ርቀት ንግድ እና በተከታታይጦርነት አባ ዱላው ተፈላጊነቱ እየጨመረ ስለመጣ አባ ገዳውን ችላ በማለት ራሱ ሞቲ (ንጉሥ) መሆኑ

5.2 ገዳ በሥራ ቦታ ላይ ውጤታማ ሊሆን ስለማይችል

5.3 ከአምቲከ ዘውዳዊ የአገዛዝ ሥርአት የአስተዳደር ዘይቤውን በመውሰድ እና

5.4 የእስልምናን አስተዳደራዊ መዋቅር በመላመዳቸው ነው።

6. ቀደም ብለው ቢያንስ ከ13ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ተመሥርተው የነበሩ የሙስሊም ሡልጣናዊ አስተዳደሮች ሸዋ ዳህላክ ኢፋት ሃዲያ ባሊ ሻርካ ደዋሮ ደራ ፈጠጋር አርባባኒ እና አዳል ነበሩ።)

*ምሁራኑ ያቀረቧቸው መረጃዎች በዝርዝር ካኖርናቸው እውነታዎች ጋር የተዛመዱ ከመሆናቸውም ሌላ በጥንቃቄ የተዘጋጁ ናቸው። በእርግጥ እንቅስቃሴ ወቅት በርካታ ማህበረሰቦች ቋንቋቸው ወደ ኦሮምኛ፣ ባህላቸው የመወራረስ ሁኔታ ለማሣየቱ ከቦታ ወደ ቦታ ላለው ልዩነት ምክንያት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ከሁሉም በላቀ ደረጃ ግን ለኢትዮጵያውያን ውህደት አይነተኛ አስተዋፆ አበርክቷል። የኢትዮጵያውያንን መልክ ለመለየት አዳጋች የሆነበት አንዱ ምስጢርም ይኸው ነው።

የኦሮሞ የትመጣ ኢትዮጵያ ውስጥ ከደቡባዊው ክፍል ሆኖ ከኢትዮጵያ ህዝብ በአጠቃላይና ከአማራ ህዝብ በተለይ፤ ሁለቱም ከሰሜን ወደ ደቡብ እና ከደቡብ ወደ ሰሜን ባደረጓቸው እንቅስቃሴዎች ተገምደዋል። የኦሮሞና የአማራን የዘር ግንድ "አንድነት" ፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሣ ሲተነትኑ ምሣር የበዛባቸው ከሁሉም በላይ "አንድነቱን በማይፈልጉ ሀይሎች" ነው። እውነታው ምርምርም ጥናትም የሚጠይቅ ጉዳይ አይደለም።



t.me/OLDBOOKSPDF

"የኦሮሞና የአማራ የህዝብ ለህዝብ ትሥሥር ጉባኤዎች ሲካሄዱ መድረክ ላይ አዳዲስ ሆነ (2019) የአማራ እና የኦሮሞ 'ፕሬዚደንቶች' አቶ ሽመልስ አብዲሳ እና ዶክተር አምባቸው መኮንን የተመለከተ በምን ይለያቸዋል? አዳራሹ ውስጥ የታደሙ ተሰብሳቢዎችን በባህል ልብስ ካልተገኙ በምን ሊታወቁ ይችላሉ? ልብሱንም በፍላጎት የአንዱን መለያ ሌላው ሊለብስ ይችላልና እንቆቅልሹን ለመፍታት የሀሮልድ ማርከስን፦ "A History of Ethiopia" ከገፅ 39 - 80 ማንበብ ወደ እውነታው ይወስደናል።የተወሰኑ ነጥቦችን ሆነ ብለው ትርጉም ለማያዛቡ በር ላለመክፈት ቀጥታ ከበኩረ ፅሑፉ ብንቀዳ ፍንትው አድርጎ ያበራልናል።

ገፅ 39፦

> *"Susenyos (r. 1607 - 1632) ... had an interesting and creativemind, and his policy of integrating Oromo into the Solomonic state's political life was a daring gambit. His previous experience with the Oromo - he had lived among them and had married a daughter of a ranking gada official - convinced him that the new comers might have a role to play in Ethiopia's politics.*

ሱሰንዮስ በኦሮሞ ውስጥ ማደጉ እና "አዲሶቹ ነዋሪዎች" (ኦሮሞዎችን ማለቱ ነው) በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ሊጫወቱት የሚችሉትና ሚና ተገንዝቦ የወሰደው ጥበብ የተሞላበት እርምጃ ግልፅ ብሎ ታይቷል። ሱስንዮስ በገዳ ስርአቱ ትልቅ ደረጃ ላይ የሚገኙ ግለሰብን ልጅ ማግባቱ እና የሱስንዮስ ልጅ ፋሲለደስ በካቶሊክ ሀይማኖት ምክንያት የተነሳውን ግጭት ወደ ቀደመ እምነቱ ተመልሶ እንዲያረጋጋ የኦሮሞ አማካሪዎቹ ድርሻ የላቀ ነበር። (ገፅ 40)፤ ገፅ 43፦ ከሁሉም በላይ የጎንደር ዘመን መንግሥት መገለጫ የሰሎሞናውያን ከኦሮሞ ጋር መዋሀድ (Assimilation) ነው። ከገፅ 45 - 46 የአፄ ባካፋ (1721 - 1730) የመጫ ኦሮሞዎችን በመመልመል እስከ ትግራይ ድረስ ማጥቃት (*ባካፋ ኦሮምኛ ሲሆን ትርጉሙ ሲራመድ ወልከፍ ወልከፍ የሚል ማለት ነው።)



t.me/OLDBOOKSPDF

አፄ ኢያሱ ዳግማዊ ከወሎ ኦሮሞዋ ዋቢ ተጋብተው አፄ ኢዮአስን (1755 - 1769) መውለዱ (እና ከ3,000 ያላነሰ የኦሮሞ አባ ወራ ጎንደር በተለምንግሥት መግቢ ከማስታወሻ የተወሰደ)፤ "A River of Blessings, Essays in Honor of Paul Baxter" በመሀመድ ሀሰን ገፅ 29 እንደተጠቀሰው፡- "የአፄ ሱስንዮስ ሰራዊት ትልቁ አካል ጢና ኦሮሞ ነበር።"

ፋዘር ማርሻል ደ ሳልቫይክ፡- "An Ancient..." ገፅ 41፡-

> *"... Meanwhile, the territory of Harer had not suffered from the first invasion of Oromo. under the domination of the Emir Nour, the tribe of Barentu Oromo began to move in this direction. The Emir after gaining some success against them, had to retreat and enclose himself in his capital.*

የሐረሩ ኢምር በሐረር አቅጣጫ ይንቀሳቀስ በነበረው የባሬንቱ ኦሮሞ ላይ በመጀመሪያ ድል ቢቀዳጅም የኋላ ኋላ አፈግፍጎ ወደ ዋና ከተማው ማምራቱን እንገነዘባለን።

ገፅ 41 (የተጠቀሰው ምንጭ)፡-

> *The Oromo occupied all the high and fertile plains around Harer, about 1700. The old population disappeared or was absorbed.*

በግልፅ ኦሮሞዎች ለምና ከፍተኛ ቦታዎችን በ1700 መያዛቸውና ነባሩ ማህበረሰብ መጥፋቱን ወይም መዋጡን ፀሳይተነዋል። ይህ የበርካታ ኢትዮጵያውያን ማህበረሰቦች እጣ ፈንታ ነበር። ይህንን በመካድ ወደ አንድ አቅጣጫ የታሪክ በደልን ለመግፋት መሞከር አይጠቅምም፤ አያስተምርም። እውነትን ለመናገር ጎበና ካሰኘ፤ የወለጋው ኦሮሞ ፕሮፌሰር ጳውሎስ ሚልኪያስ በ21ኛው ክፍለ ዘመን የፖለቲካ ትኩሳት በማዘን የተናገሩትን እንመልከት፡-



t.me/OLDBOOKSPDF

*በአባቴም በእናቴም ኦሮሞ ነኝ። በዚህ ጉዳይ ከአንግ መሪዎች ጋር ብዙ ጊዜ ተከራክሬያለሁ። እኔ በኢትዮጵያዊነቴ የማምን ነኝ። እስከመጨረሻው ይህን እምነቴን ማንም አይነቀንቀውም። የኢትዮጵያ ህዝብ አንድ ህዝብ ነው። የተለያየ ቋንቋ ይናገራል እንጂ የሚለየው የለም።*

ይህ አይነቱ አገላለፅ አብዝተው ሀሊናችንን ያቆስለናል። ይህንን የመሰለ እውነት ለመግለፅ ፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ (የጂማሳ የልጅ ልጅ)፣ ኢርጋምያስ ሰገሎ (የዋቅዮ የልጅ ልጅ)፣ አበበ ቶላ (የፊይሳ የልጅ ልጅ) ... "የገመቹ የልጅ ልጅ ነኝ" እስከማለት ለመሄድ የኦሮሞ ኢትዮጵያዊነት፤ የኢትዮጵያ ህዝብ በቋንቋ ካልሆነ አለመለያየት አንድና ሁለት አለው እንዴ? (ለገንጣይ አስገንጣዮችና ከሃዲዎች የኢትዮጵያ ህዝብ በአንድ ሀገር የሚኖሩ የተለያዩ "ህዝቦች" ናቸው። እንደግመዋለን፡- አንድ አዳራሽ ውስጥ አስገብተህ በዐይንህ በማየት በየትኛ ከረጢት ለያቸው? ካልቻልክ አንድ ነን።) ኢዮአስ በትግራዩ ራስ ሚካኤል ስሑል መገደሉ ይታወቃል።

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከሚነሱ እሰጥ አገባዎች ትልቁና ዘውጊዎች አብዝተው የሚረባረቡበት ነጥብ 'አፄ ምኒልከን የኦሮሞ ጠላት አድርጎ መሳል ነው። በቀደሙት ከፍሎች ለጅማ አባ ጂፋር የዓፋትን ደብዳቤ፣ ከሸዋ እና ወለጋ ጋር የነበራቸውን ፅኑ ወዳጅነት፤ ከአርሲም ቢሆን ከተወሰኑ መሪዎች ካልሆነ ከሰፊው ክፍል ጋር የነበራቸውን ወዳጅነት በማስረጃ አስደግፈን ለማሳየት ሞክረናል። ቀጣዩን የውይይት ክፍል እንደሚከተለው አቀረብን። ዳግማዊ አፄ ምኒልክና ኦሮሞ መሀከል የነበረውን ጥብቅ ወዳጅነት አስመልክቶ በኦሮሞ ታሪክ ዙሪያ ከ1970ዎቹ በፊት የተፃፉ እና ለፖለቲካ ዓላማ ተፈጥረው ያልተፃፉ ሰነዶች ያረጋግጡልናል።

የገዳ ሥርአት ከዳግማዊ ምኒልክ በፊት ስለመክሰሙና ምኒልክ እንዳፈረሱት ተደርጎ የሚወራው ባዶ ቅጥፈት በተለያዩ ማስረጃዎች የተደገፈ. ስለሆነ ብዙም አንሄድበትም። የቦረና እና የጉጂ የገዳ ሥርአት ከቶ ማን ነካው? ማርከስ ገፅ 48፡- የጊቤ ኦሮሞ አስተዳደሮች ጎናቸው ካሉ ውጤታማ ዘውዳዊ አመራሮች አሞቲክ (ጎንጋ) በተለይም ሰቃ እና ከፋ ልምድ ቀስመው መዳዛቸውን ያወጋል። ፕሮፌሰር ባሀሩ ዘውዴ ይህንንው እውነት "በዘመናዊ የኢትዮጵያ ታሪክ" ጥናታቸው አረጋግጠዋል። ማርከስ ገፅ 56 ላይ፡- በ1855 የቀዳማዊ አባ ጂፋር ሥርወ መንግሥት በጣም የተማከለ እንደነበረ እና ከሰምንት የተለያዩ አባ ዱላዎች ጋር ደም አፋሳሽ ጦርነት አድርገው ንግሥናቸውን እንዳስጠበቁ አስምሮበታል።



t.me/OLDBOOKSPDF

ገፅ 76፡- ምኒልክ በ1876 ጎጃምን ለመምታት ሲዘምቱ፡ ሸዋ ውስጥ ብጥብጥ በመነሳቱ ተመለሱ። ገፅ 79፡- የምኒልክ ቀኝ እጅ ጎበና (መጀመሪያ ደጃዝማች በኋላ ራስ የሚሉ ማዕረጎች በቅደም ተከተል የተሾሙ) የኦሮሞ ጊቤ ግዛቶችን ያዙ። ገፅ 76፡- አፄ ዮሐንስ አራተኛ እና ንጉሥ ምኒልክ ባደረጉት ድርድር አፄ ዮሐንስ በዘውዳቸው ሥር የምኒልክ ግዛት አድርገው የተቀበሉት፡- በስተሰሜን እስከ በሺሎ ወንዝ፣ በምዕራብ እስከ ዓባይ ወንዝ እና በምስራቅና ደቡብ እስከ አዋሽ ሆኖ ምኒልክ ለአፄ ዮሐንስ አራተኛ እንዲያቀርቡ የታዘዙት ግብር እጅግ የተጋነነ ነበር።

ይኸውም በዓመት ሁለት ጊዜ የሚከፈል ነው። ለምሳሌ፡- በዲሴምበር ወር 1880 ላይ 600 በቅሎና ፈረስ፣ 80ሺህ ዶላር የሚያወጣ የጥጥ ምርት፣ 50ሺህ ዶላር በጥሬ ገንዘብ የከፈሉ ሲሆን፤ በሜይ ወር 1881 ውስጥ 50ሺህ ብር የሚያወጣ ጥራጥሬ፣ ዱቄት፣ ቅቤ እና ከብቶች፣ በጥሬ ገንዘብ 10ሺህ ዶላር እንደከፈሉ መወሳቱ እና ምኒልክ ባዶ እጃቸውን የሚመለሱበት ጊዜ እንደነበር ተወስቷል። (*ከግል ማስታወሻ የወሰድነው ደግሞ፡- በጎብሩ መብዛት የተናደዱ ሸዌዎች አፄ ምኒልክ የምጣድ ማሰሻ ሳይቀር ለመገበር ተስማሙ ያሉ ሲሆን፤ በግጥም ደግሞ፡-

'ሲሆን አገልድመው ሳይሆን አጣፋው፣

ማደግደግ አይሆንም እንዳንት ላለ ሰው።'

እንደተባለም ይነገራል።)

ውሸት ተደጋግሞ ሲነገር እውነት እንዳይሆን እውነትን እንግለጥ። ለመሆኑ "የጨለንቆ ጦርነት" (1887) እንደተወራለት ነበር ወይ? ማርከስ ገፅ 84፡-

ምኒልክ አዘውትረው አዲስ ቦታ ሲይዙ እንደሚያደርጉት ሁሉ ለሐረሩ ኢ.ምር አብዱላሂ እንደ ጂማ አባ ጂፋር በሰላም እጅን ሰጥቶ ግዛቱን እንዲያስተዳድር መልእክት ሰደዱለት። መልስ እየጠበቁ ሳሉ ኢሚሩ መላ ይፈልግ ጀመር።

ድንገት "በክርስቲያኖች ገና በዓል" ጥቃት ፈፀመ። ኢምር አብዱላሂ ያሰበው በበዓል ምግብ እና መጠጥ ወስደው በጥጋብ እና በስካር ስለሚዝሉ በቀላሉ አሸንፋለሁ ብሎ ነበር። ሸዋዎች ወዲያውኑ ራሳቸውን በማደራጀት እና መልሰው በማጥቃት በትንሽ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሰብአዊ ኪሳራ ድል አደረጉ። አብዱላሂ ወደ ሶማሊ ሸሽቶ አጎቱ የነበረው 'ቃዲ' ለምኒልክ እጅ እንዲሰጥ አደረገ።

ሐረርን የባሬንቱ የኦሮሞ ክንፍ መውጋቱን፤ ጨለንቆ ላይ የተደረገው ጦርነት አጭርና ከሐረሩ ኢምር አብዱላሂ ጋር መሆኑ እየታወቀ፤ ድል በተደረገበት ግጭት የታሪክ ሽሚያው የሚያስገኘው ፋይዳ ምን ይሆን? (አፄ ምኒልክ ሐረር ከመድረሳቸው ሁለት ዓመት በፊት ከ1875 - 1885 ሐረር በግብፆች ቁጥጥር ስር ውላ ነበር።)

አዲስ ቦታ ላይ ሲዘመት ግጭት የሌለ ይመስል አንድ ወገን የተጠቂነት ስሜት እንዲያዳብር ማድረግ አይጠቅምም። ከዚሁ ጎን ለጎን የደቡብ መንግሥት ሆኖ ሳለ በሊሙ ኦሮሞ ተመትቶ ማንነቱን ጭምር ያጣውን ኢናርያ ሂናርዮ ማህበረሰብ፤ በኦሮሞ ከተያዘ በኋላ በትግል መልሶ ራሱን ነፃ ያወጣውን ሸካን፣ የካፋ እና ወላይታን የኦሮሞን እንቅስቃሴ በጦርነት መከላከል፤ በኦሮሞ እንቅስቃሴ ማንነታቸውን ያጡ በርካታ ህዝቦችን ማሰቡ ይጠቅማል።

ፕሮፌሰር ባህሩ፡- "A History of Modern ..." ገፅ 19 ጆቴ ቱሉ በጭካኔ የተሞላ ወታደራዊ ኃይል በመጠቀም ከንግድ ከፍተኛ ገቢ ይሰበስብ ነበር። ከአሶሳ (አቆልዲ) በሼክ የሚመሩ ግዛቶች አብዝቶ ይዋጋ ነበር። ሲጠቃለል እንኳን በዚያ የሩቅ ዘመን ቀርቶ በዘመናችን ሠለጠነ በሚባለው ዓለም እየኖርን መቼ ከጭካኔ ታቀብን?

## የሸዋ ፖለቲካ፤ ዐዲስ አበባ እና የታሪክ ውዝግብ

ሸዋ በጂኦግራፊያዊ አቀማመጧም ሆነ በፖለቲካዊ ማዕከልነቷ ከጥንት ጀምሮ ከሰሜን ወደ ደቡብ እና ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ በተደረገው መስተጋብር ውስጥ ቁልፍ ሥፍራ ይዛ ቆይታለች። የኢትዮጵያ ታላላቅ የንግድ መስመሮች ከቦንጋ ተነስተው ጂረን ከደረሱ በኋላ ሰቃ ደርሰው በሁለት ይከፈላሉ።

አንደኛው በአሰንዳቦ በኩል ወደ ባሶ ዳሬታ ጎንደር ደርሶ ጎንደር ላይ ባላ ሰርቶ አንዱ ተዘንቶፎ ወደ መተማ ሲዘልቅ፤ ቀጣዩ ከጎንደር በአድዋ በኩል አልፎ ወደ ምፅዋ ተዘርግቶ ሁለቱም ከውጪው ዓለም ኢትዮጵያን ያገናኟታል። ሁለተኛው መስመር ከወንድሙ ከተለየበት ሰቃ ተነስቶ በሶዶ በኩል ሮጌ፣ አሊዩ አምባ፣ (የጁቢ እና



t.me/OLDBOOKSPDF

አብዱል ራሱል የታወቁ ገበያዎች ነበሩ።) በባቲ አቅጣጫ ድጋሚ ወደ ምስራቅ ታጥፎ ይጓዛል።

ከአሊዩ አምባ በቀጥታ ወደ ሐረር ተጉዞ ሶማልያ ውስጥ ዘይላ እና በርበራ ድረስ ይዘረጋል። ይህ ጥንት በአክሱማውያን ዘመን በተለያየ አቅጣጫ ያለ ድምፅ በምልክት (Silent Trade) እና እቃን በእቃ መለወጥ (Barter trade)፣ በአሞሌ፣ ማርዳ፣ ጨሌ፣ ዶቃ፣ አቡጀዲ ጭምር እየተገበያየ፣ እየተዋሀደ እየተሰናኘና እየተገመደ አንድ መልክ የያዘ፣ በማየት የማይለይ አንድ ህዝብ እየሆነ መጥቷል። በዚህ የረጂም ዘመናት መስተጋብር በርካታ ሁነቶች ነበሩ። በቦሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት 2010 (2002) የተዘጋጀ መፅሔት ገፅ 9:-

> *የዐርሐ አርያም ቅድስት ሥላሴ ገዳም ... በቦሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ቀበሌ 14/15 ልዩ ስሙ የረር ጎሮ አካባቢ የሚገኝ ሲሆን የገዳሙ ታሪክ እጅግ አስደናቂና ጥንታዊ ነው። የገዳሙ አድማ ከአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ይጀምራል። በአብርሀ ወአፅብሀ ንግሥና ዘመን በንጉሥ አብርሀ እንደተሠራ ይነገራል። ... በዮዲት ጉዲ የጦር ዘመቻ ምክንያት በመሬት ውስጥ ተቀብሮ ለዓመታት ቆይቷል። በ1997 (2005) ቤተ ክርስቲያኗ ከ700 ዓመታት በኋላ በድጋሚ ተገኘች።*

ይህ ምንጭ በኢዛና ዘመነ መንግሥት ከ330 -360 በአክሱምና በአዲስ አበባ መሀከል የነበረውን ትሥሥር ቁልጭ አድርጎ አመላክቷል። በመቀጠል:-

በቁፋሮው ወቅት የተገኙ እድሜ ጠገብ ቅርሶች መረመሚያ ድንጋይ፣ *የብራና ማስተካከያ፣ የብራና መፅሐፍ፣ 'ኩስኩስት' - የቅዳሴ ፀበል ማቅረቢያ፣ 'ባዞላ' - የቅዱሳን አፅም ታሽጎ የቆየበት፣ ወፍጮ - ምግብ መፍጫ፣ ከባልጩት ድንጋይ የተሠራ የቤተ ክርስቲያን ጉልላት፣ ገበጣ ናቸው።

ምንጮችን ከአስተማማኝነት ባለፈ ቅርሶቹ አሁንም የሚገኙና በዐይን ሊታዩና ሊረጋገጡ የሚችሉ ናቸው።

ጄ. ስፔንሰር ትሪሚንግሀም "Islam in Ethiopia" በሚል ርዕስ ለኅትመት ባበቃው መፅሐፍ ገፅ 58:-



t.me/OLDBOOKSPDF

*የሸዋ ሡልጣን 896/7 ተመሠረተ። 1214-87 ኢ.ብን ሰዒድ (1285) ኢ.ብን መላዝማ፣ ኢ.ፋት (ዋፋት) የጠንካራው ንጉሥ ከተማ ስትሆን ህዝቡ ለጅግ በጣም የተቀየጠ (Mixed) ነበር። በተ መንግሥቱ ተራራ ላይ የተመሠረተ ሆኖ ዝናብ በየቀኑ ይዘንባል። መግና ሸንኮራ አገዳም ይመረት ነበር። የከተማዋ 'አስትሮኖሚያዊ' አቀማመጧ በግምት 8 ዲግሪ 'ላቲቲዩድ' እና 57 ዲግሪ 'ሎንጊቲዩድ' እንደ አረቦች ቀመር ከሆነ የሸዋ ምስራቃዊ ጫፍ ነው።*

ይህ እውነት የኢትዮጵያ ሕዝብ መስተጋብር ምን ያህል ጥልቅ፣ የሸዋ የጋራ መሆን እንዴት ጥልቅ እንደሆን ይረዳል። ሀሩን ያህያ "The Evolution Deceit" በሚለው መፅሐፉ የፃፈው ለእምነት ቢሆንም ተምረውም፡ እውነቱን እያወቁም መረዳት ለማይፈልጉ በሚቀጥለው መልክ የጠቀሰው በትክክል ይገልፃቸዋል። ከቅዱስ ቁርዓን ሱረቱ አል - አረፍ፣ 179:- "የማያምኑ ልብ አላቸው አያገናዝቡም። ዐይን አላቸው ዐያዩም። ጆሮ አላቸው አይሰሙም። ትእዛዙን ስላላከበሩ እንደ እንስሳት ደመ ነፍሳዊ (አቀጣጫቸውን የማያውቁ ይሆናሉ።

"Ethiopia, The Red sea and The Horn" ኢንሪኮ ቹሩሊ በ1941 የአረብኛ ፀሐፊ ትእዛዝ ኢ.ብን ሃውቃል (977) ላይ የፃፈውን ተርጉሞ:- *"የሸዋ ሡልጣን በ9ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ተመሠረተ። ግዛቱ ከምስራቃዊ የሸዋ ከፍተኛ ቦታዎች ስከ ጨርጨር የተዘረጋ ነው። ... የሸዋ ሡልጣን ንግሥት ባዲን የማያ ልጅ 1063 ሞተች።"*

ምንጩን ተከትለን የሡልጣኑን ሚስት ንግሥት ማለቱን ይዘን። የሸዋ ሡልጣን 896/97 መመሥረቱን፣ በ1285 በወላዝማ ሥርወ መንግሥት በኡመር ወላዝማ መያዙን፣ በአምደፅዮን በ1332 ሲመታ ወደ ምስራቅ አፈግፍጎ አዳል ላይ መከተሙን፣ በ16ኛው ክፍለ ዘመን በኦሮሞ እንቅስቃሴ ሰለሞናዊው ሥርወ መንግሥት በሚናስ ዘመን ወደ ሰሜን ማፈግፈጉን፣ የሸዋ አማራ ኦሮሞና ሌሎች ማህበረሰቦች በፍቅር መሰናሰላቸውን "በሸዋ ፖለቲካ" ውስጥ እናያለን። በ13ኛው ክፍለ ዘመን አቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ ዝቋላ መምጣታቸውን ,በተመለከተ፡- "Ethiopia, The Red Sea and The Horn" ገፅ 117 ላይ በተመሳሳይ ምንጭ እናያለን።



t.me/OLDBOOKSPDF

ዶክተር ኃይለገብርኤል ዳኜ የአዲስ አበባን መቶኛ ዓመት ምሥረታ አስመልክቶ በአዘጋጀው መፅሔት ገፅ 29 ላይ:- "ቀራንዮ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን በ1816 በንጉሥ ሣህለሥላሴ ዘመነ መንግሥት ተሠራ" ሲሉ ይጠቅሳሉ። ፋዘር ማርሻል ደ ሳልቫይክ "An Ancient People..." በሚለው መፅሐፋቸው ገፅ 31 የፃፉትን እንመልከት:-

> *Abyssinians ... Their African empire extended from the south of Egypt to 6 degree latitude north; the present desert of the Adal, ... similarly half of the vast region occupied today by the Oromo and the Somali, Harer and Gurage, whose two twin languages, although they are separated by distance, are of the same Amharic origin were Ethiopian provinces.*

የፀሐፊው መሠረታዊ ስህተት ሶማሊና ኦሮሞን ውጫዊ አድርጎ ማሰቡና ህዝቡ በዘመናት መስተጋብር አብሮ መኖሩን፤ ሁለቱ ማህበረሰቦች ድራቸውም ማጋቸውም ኢትዮጵያ መሆኗን ነው። ለዚህም ሆነ ለሌሎች ከሞሉ በርካታ መረጃዎችና ማስረጃዎች ጥቂቶችን ጠቅሰናል።

**ከፋው ገፃችን**

**(ለሙግት መቅረብ የሌለበት እውነት):-**

ዶክተር አሉላ ፓንክረስት ለዘመናት በኢትዮጵያ ውስጥ የተገለሉ ማህበረሰቦች ("Marginalized communities") እንደነበሩና እንዳሉ ይገልፃሉ። ዶናልድ ሌቪን (1974 ገፅ 56)ን ጠቅሰውና የራሳቸውን ሠፊ የምርምር ሥራ አካትተው:-

በመላው ኢትዮጵያ በቁጥር አነስተኛ የሆኑና ከዋናው ማህበረሰብ የተገለሉ የእደ ጥበብ ባለሙያዎችና አዳኞች አሉ። ከስተቱ በሰሜንና በደቡብ፤ በከተማና በገጠር አለ። (pan - Ethiopian cultural trait)፤ የመገለሉ ሁኔታ በዕቃ ልውውጥ፣



t.me/OLDBOOKSPDF

በገበያና ማህበራዊ መስተጋብር፣ በአመጋገብ ሥርአት / የምግብ እና የመጠጥ ሥርአት፣ በሰላምታ አሰጣጥ ይንፀባረቃል።

የእደ ጥበብ ባለሙያዎችን በተመለከተ በአንዳች ሰማያዊ ርግማን እንደተፈጠሩ (ከውሻ የተወለዱ፤ ከአስከሬን የተወለዱ) እንደሆነ አድርገው የመሳል ሁኔታ እንደሚንፀባረቅ ጥናቶች ይገልፃሉ። እንደ ዶክተር አሉላ ፓንከረስት ደግሞ መገለሉ በአምስት ተያያዥነት ባላቸው መስኮች ይንፀባረቃል። እነዚህም፡-

1) በቦታ አቀማመጥ - በከተማ ዳርቻ ይገለላሉ፤

2) በምጣኔ ሀብት - የደቀቁ፤

3) በፖለቲካ ተሳትፎ የሌላቸው፤

4) በማህበራዊ ህይወት - ከጋብቻ ጀምሮ የማይቀየጡ እና

5) በባህል ተፅዕኖ የሚደርስባቸው ነበሩ" ይሉና

ለምሳሌ፡- ምጣኔ ሀብታዊ ገፅታውን ለማሳየት፡- "ሸክላ ሠሪ ለሌሎች እንስራ ሠርቶ ለራሱ በቀዳዳ ውሀ ይቀዳል።" - የከምባታ አባባል እና ባህላዊ ገፅታው ላይ የአይዳዎች አባባል፡- 'የማናና የአህያ ጩኸት ማብቂያ የለውም፡፡ማለቱን ይጠቅሳሉ። ገፅ 37 ላይ፡- "ወይጦ- በጣና ሀይቅ አካባቢ፣ ማንጆ - በካፋ አካባቢ (ሙሉ ሰው ያልሆነ 'ፓሪያህ) ከማለታቸው ሌላ ዶክተር ዳግማዊ ተሰፋዬ በሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ፅሑፉ፡- 'asho ne manjo ne? - (ሰው ነው ወይስ ማንጆ ይሉ እንደነበር፣ ዋታ - በኦሮሞ..."

በዚህ መሠረት እያሌ የተገለሉ ማህበረሰቦች ነበሩ። ይህ አይነት አመለካከት በመላው ዓለም የታየ ክስተት እንጂ የሀገራችን የተለየ ገፅታ አልነበረም። ዛሬ ሰዉ የአመለካከት ለውጥ ሲያመጣ እነዚህ ጥበበኞች የኢንዱስትሪ አብዮት አብቃይ እንደነበሩና ማግለላችን ዋጋ እንዳስከፈለን ተገንዝበን፤ ዛሬ ራሳችን እደ ጥበብን ፍለጋ በመንከራተት እያሳለፍን እንገኛለን። ዛሬ በየቦታው ባለሙያዎቹ የክብር መገለጫ ሆነዋል። የአስተሳሰብ አድማስ ሲሠፋ ትላንትን በጋራ ረግመን፤ ዛሬን በፍቅር



t.me/OLDBOOKSPDF

እንናገራለን። ዛሬ ይህንን አንስቶ 'በድለኸኝ ነበር' የሚል ካለ ስህተት ነው። የሙግት ርዕስ መሆንም የለበትም።

## የአዲስ አበባ ጉዳይ እንዴት ይታያል?

በዝርዝር ለማሳየት እንደተሞከረው ሸዋ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ናት። ሸዋ፦ የሸዋ፣ የኢፋት፣ የዋፋት፣ የሀዲያ፣ የወላዝማ፣ የአዳል፣ የአርጎባ፣ የአማራ፣ የጉራጌ... የሁሉም ናት፤ ዝዋይ (ዛይ)፣ ጉራጌ፣ ስልጢ፣ በዛግዌ ዘመን የተሰራችው አዳዲ ማርያም፣ የነገሥታት የዘመናት ጋብቻ፣ የአምደፅዮን፣ የዘርዓያዕቆብ፣ የዳዊት ከተማ፣ የበረራ ከተማ፣ ፍንፍን የሚለው የፊንፊኔ ምድር፣ ሸገር (እንደ ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ / አፈሩን ገለባ ያድርግላቸውና - 'ሸጋ ሀገር') - የመላው ኢትዮጵያውያን ናት። በታሪክ አጋጣሚ በዓለም ከአራቱ ዲፕሎማቲክ መናኸሪያዎች አንዷ፣ የአፍሪካ መዲና፣ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ናት።

ከ2005 ወዲህ የኦሮሚያም የፖለቲካ ማዕከል ሆናለች። ሁሉንም አቅፋ መኖር ያልከበዳት እና ህብረት ልምዷ የሆነው አዲስ አበባ ለሁላችንም ዋና ከተማችን የሆነቸው በጣይቱ መሻት እና በምኒልክ ውሳኔ ነው። ባይሆንማ ኖሮ ዛሬ የተለያዩ ማህበረሰቦች የሚኖሩባት ቢሾፍቱ አካባቢ እንዳለ አንድ የገጠር ቀበሌ በሆነች ነበር። የአሰራሏን ህዝብ የሚያህል ወገን የያዘቺው አዲስ አበባ የማደግ እድል ብታገኝ እንደ ጃፓኗ ዋና ከተማ ቶኪዮ 33ሚሊየን ህዝብ (የአዲስ አበባን ህዝብ አምስት እጥፍ) ለማቀፍ የሚያስችል ብርቱ አቅም አላት።

ይህቺ አዲስ አበባ የሸዋ አማራንና የሸዋ ኦሮሞ ብብቷ ውስጥ ከትታ አቅፋ በርካቶችን በንግድና በ'ፐብሊክ ሰርቪስ'፣ በውትድርና እየያዘች ደረጀች። ያኔ ጣልያን በሦስት ቀን ሠላሳ ሺህ ነዋሪ ሲጨፈጭፍ አብራ ደም እንባ አልቅሳለች። በሐደት "የክልል 14 መስተዳድር የአምስት ዓመት መርሐ ግብር ረቂቅ፣ 1990-1994" ታትሞ በወጣው ጥቅምት 1990 - ለካ በዚህ ዘመንም ክልል ነበረች? ገፅ 2 ላይ የሕዝብ ስብጥሩን ሲገልፅ፦ *አማራ 48.3%, ኦሮሞ 19.2%, ጉራጌ 17.5%, ትግራይ 7.6%*



t.me/OLDBOOKSPDF

የሰላም /ዕብዩ 'ዲሞክራሲው' ለሰጣ እንዲሳተፉ እናምናለን።) ከየትኛውም ዘመን በላይ ኢትዮጵያ የተቀናጀችና መረብሯን ለንብረት ማወቅ የቻለ ሕዝብ የተፈጠረበት ነው። ያን ለዩን ግላቻው ለማማ ከፍለዘመን ከመቼውም ጊዜ በላይ ግንዉ ተቋማቱና ድርጅቶችም እንደ አሸን እየፈሉ ነው።

ፕሮፌሰር መሀሪ ታዳና "Ethlopia: From Autocracy to Revolutionary Democracy" በሚለውና ለህትመት በበቃው የምርምር ሥራቸው፡- "በ1990ዎቹ በኢትዮጵያ የተደራጁ ሥራዎች ምናልባት በዘመናት ውስጥ ስለማህበረሰቡ ከተገኙት ምርጥ ዶክመንቶች" ገለፃቸው ሲታይ የዕሁፍ የማሳወቅ፤ ለበጎም ይሁን ለጥፋት የመመዝገብ፣ ተግባር የኑን ያህል እንዳደገ መገንዘብ ያስችለናል። የመንግሥት ሥራ ህግ ማውጣት፤ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶቹ አማካይነት ህግ መፈፀምና ማስፈፀም እንዲሁም ህግ መተርጎም ነው። የምሁራን ሚና በተግባር መሣተፍና በትችት አቅጣጫ ማሳየት ነው። ከ.ንያ 2,000 'ቲንክ ታንክ' (Think Tank) ቡድኖች፤ የኢንግሊዝ ዴሲ ተመሣሣይ 300 ቡድኖች አሉ። የውይይት ባህልን በማሳደግ እና መንግሥትን በማረቅ ወደ ተገቢ አቅጣጫ በመውሰድ ድርሻቸው ታላቅ ነው።

የአዲስ አበባን ጉዳይ ከዓለማችን ሀገሮች ተሞክሮና ከራሷ የግል ባህርይ አያይዘን በአጭሩ ለመዳሰስ የሚከተለው ቅኝት ቀርቧል። በዓለማችን 28 ሀገሮች ብቻ ፌደራሊዝምን ይከተላሉ። ለሎቹ ሀገሮች በሙሉ የአሀዳዊ መንግሥት አወቃቀር የሚከተሉ ናቸው። አሀዳዊ መንግሥታት ውስጥ የጎጥ ድንበር እምብዛም ቦታ ስለሌለው "የእኛ"፣ "ኬኛ" በጠባብ መንገድ አይንፀባረቅም። የእኛም ሆነ ኬኛ ሁፍተው በሀገር ደረጃ ስለሚወሰዱ በሽታዎችና የግጭት ምንጮች አይደሉም። ፌደራላዊ መንግሥት ከሚከተሉት 28 ሀገሮችም ቢሆን ከአፍሪካ እንኳ ደቡብ አፍሪካና ናይጄሪያን እንደ ማሳያ ብንጠቅስ የመከፋፈል ምንጭ ሊሆኑ አይችሉም። ምክንያቱም መነሻቸው የአንዱን ፍላጎት በሌላው ላይ መጫን አይደለም።

አሜሪካ እና ሌሎችም ቢሆኑ የፌደራል አወቃቀራቸው በጂኦግራፊ (አቅጣጫ) በመሆኑ እንደ ስዊዘርላንድ አይነቶቹ ደግሞ የቋንቋ ችግር ስለሌለባቸው፤ የተግባቦት እንቅፋት ሲሆኑ ዐይታይም። ስዊዘርላንድ ውስጥ ተማሪዎች ከ1ኛ እስከ 6ኛ ክፍል በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው፣ ከ7ኛ ክፍል ጀምሮ በሀገሪቱ ብዙዎችን የሚያግባባውን ቋንቋ፣ ከ9ኛ ክፍል ጀምሮ ሦስተኛ ሌላ ቋንቋ የሚማሩበት ሁኔታ ስለሚከተሉና አብዛኛው ወገን እንግሊዝኛን ጨምሮ ስለሚማሩ ቋንቋ አይገታቸውም።



t.me/OLDBOOKSPDF

አዲስ አበባ በባህርይዋ 99 እጅ ነዋሪዋ በአማርኛ ቋንቋ በሚገባ ይግባባል። 20 እጅ የሚሆነው የኦሮሞ የአዲስ አበባ ተወላጅ ውስጥ ኦሮምኛ መናገርና መፃፍ የሚችለው ከሦስት እጅ አይበልጥም። ችግሩ የትኛውንም ውሳኔ ለመወሰን የሚቀድመን ጥበብ ሳይሆን የግል ፍላጎት፣ በጥናት ላይ ሳይሆን በስሜት፣ ከራስ አንፃር በሌላው ጫማ ውስጥ ራስን አስገብቶ ማየት አለመቻሉ። የከፋው ደግሞ በብሔረሰብ የመንጋ ፍላጎት መመራቱ ነው።

አዲስ አበባ ላይ የሚወሰን ውሳኔ ሁሉ ቀጥተኛ ተፅዕኖ የሚያሳርፈው የጎጃም የወሎጋ የጎንደር የቦረና የመቀሌ የጉጂ ማህበረሰብ ላይ አይደለም።አዲስ አበባ የተገነባችውም በሁሉም ኢትዮጵያዊ መስተጋብርና ላብ ነው። የተገፋው የሸዋ ገበሬ ጉዳይ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ህመም እንጂ የተወሰኑ ቡድኖች አይደለም። ችግሩን አቻችሎ መፍታት የግድ ያስፈልጋል። አዲስ አበባ ከዙሪያዋ የኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ አሰፋፈር አንፃር የኦሮምኛ ትምህርት ቤቶችና ፍርድ ቤቶች ሊኖሯት ይገባል።

በየመሥሪያ ቤቱ አልፎ አልፎ በአማርኛ መግባባት የማይችሉ ግለሰቦች ሊኖሩ ስለሚችሉ አስተርጓሚዎች ቢኖሩና በደብዳቤ ልውውጥ ወቅት እንዳስፈላጊነቱ ኦሮምኛና አማርኛ ጎንለጎን ቢፃፉ ተደራሽነቱ የበለጠ ያድጋል እንጂ ማንንም አይጎዳም። በጥናት ላይ ተመሥርቶ ኦሮምኛ ከአራተኛ ክፍል ጀምሮ እንደ አንድ የትምህርት አይነት ቢሰጥ ጠቀሜታው ብዙ፣ ጉዳቱ ምንም ነው።

በቋንቋውዝግብም መታየት ያለበት ከዚህ አንጻር ነው። የምንከተለው ፌደራላዊ ሥርአት እንደመሆኑ የ80ውም ብሔረሰብ ተወካዮች በአዲስ አበባ ጉዳይ ገዘፍ አይውጣ እንጂ የራሳቸው ፍላጎት አላቸው። በተለይ የደቡብ ኢ/ብ/ብ/ህ ክልል፣ የአማራ ክልል፣ የትግራይ ክልልና የኦሮሚያ ክልል ፍላጎት ከፍተኛ መሆኑ ለጥያቄ አይቀርብም። የአፋርና የሶማሊን በአዲስ አበባ ዙሪያ ያለ ፍላጎት ጠልቆ ማየት ይቻላል።

ዋና ከተማ ሆኖ ማደግ ያለበት በእኔ ክልል ውስጥ ያለ ከተማ ነው የሚል ጥያቄ እድገቱ ለኦሮሚያ ካለው ልዩ ጥቅም አንጻር ከሌሎች ክልሎች የተበደልን ጥያቄ ሊመጣ እንደሚችል ራቅ አድርጎ ማሰብ ይጠቅማል። በሌላው ተፅዕኖ ስር "በአፓርታይድ ሥርአት" እየተረገጥሁ መቀጠል አልፈልግም የሚል የውስጥ እና ሌሎች ከልሎችም 'በአንድ ቡድን ተፅዕኖ የምትሽከረከር ከተማ አትወክለኝም' ስሜት ሊያንፀባርቅ ይችላል።

የውስጥ ግጭት፣ የሚፈጥረው ልዩነት ሰፍቶ የከተማዋ ሰላም መደፍረስ ከጀመረ ደግሞ የአፍሪካ ህብረት ከተማ መቀመጫነቷ ሊያከትም። የቆንሱላ አባላትም ይህን ተከትለው ጓዛቸውን ሸክፈው መሥሥ ማለታቸው አይቀሬ ነው። ለዚህም ነው ደጋግመን አሥር ጊዜ ለከቶ አንዴ ስለመቁረጥና ወርቃማ የግጭት አወጋገድ መንገድ የምናወሳው። እርቃ ልርቃ ስሜት ይበርታ። አዲስ አበባ የሚመጥናት ታላቅ ለውጥ አድገት ዘመናዊነት እንጂ የበረራ ፊንፊኔ እና የእኛ ትርከት አይደለም።

በዓለማችን ካሉ 200 ያህል ሀገሮች ለራስ ፍላጎት በሚያመች መልኩ የአራት ሀገሮችን ብቻ ልምድ ወስዶ (ያውም ከሌላ ስፍራ መጥተው በቅኝ ግዛት አይነት፡- ምክር ቤቱን፣ አስፈፃሚውን እና ህግ ተርጓሚውን እኛ እናስተዳድር፤ እናንተ አዲስ አበቤዎች በእኛ ስር ኑሩ የሚል ፓርቲ መቼም ቢሆን አዲስ አበባ ላይ አሸናፊ መሆን እንደማይችል ያውቃል።) አዲስ አበባን ዕውቀቱና ብቃቱ ያለው ከንቲባ፣ ምክትል ከንቲባ እና ስራ አስኪያጅ ቢመራት ተገቢና የሚደገፍ ነው። ከወረዳ (ቀበሌ) ጀምሮ እስከ ላይ ያለውን አመራር ከህዝቡ ውጭ ማድረግ ግን ይቅርታ የሌለው በደል ነው።

የናይጄሪያ ፌዴራላዊ መርሆ ዋና ከተማዋ ተጠሪነቷ ለፌዴራል መንግሥት ሆኖ አቡጃ በፌደራል መንግሥት ላይ ጫና ሳትፈጥር ሃላፊነቷን በተገቢው መንገድ እየተወጣች ከ250 ያላነሰ ቋንቋ ተናጋሪ በከተማዋ ላይ እምነት አሳድሮ እንዲጓዝ አመቺ መደላድል ፈጥሮላታል። ከ"World Almanac, 2010" ባቀረብነው መረጃ መሠረት ዋሺንግተን አንድ ራሷን የቻለች ክልል (State) ናት። የቤልጂየም ዋና ከተማ ብራሰልስ ልምድ ቢወሰድ ደግሞ "አዲስ አበባ የነዋሪዎቿ ብቻ" የሚል ሆኖ ሌሎችን "የሁላችንም ናት እንዳይሉ" ስለሚገፋና አዲስ አበባ የሁሉም ኢትዮጵያውያን በመሆኗ "ጠቅላይ ገፊ" ስሜት ስለሚፈጥር የምንደግፈው አይሆንም።

የካናዳ ህግ ደግሞ ከተማዋ በምትገኝበት ክልል ማለትም "አዲስ አበባ በኦሮሚያ አጠቃላይ የአሠራር መዋቅር ሥር እንድትወድቅ" ይገፋታል። ጥቂት 'ፍሬንች ካናዲያንስ' ኪውቤክ አካባቢ ሁለት ጊዜ የ'ሪፈረንደም ጥያቄ' ከመጠየቃቸው ውጪ አብዛኛው ህዝብ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪ ስለሆነ ከአዲስ አበባ አጠቃላይ ሁኔታ ጋር በአራምባም ሆነ በቆቦ ተዛምዶ የለውም። አዲስ አበባ በዋና ከተማነት ከ100 ዓመታት በላይ አድማ ያስቆጠረች ሲሆን የዘረሬው አማራ ክልል (ወሎ፣ ጎጃም፣ ጎንደር እና ሸዋ)፤ የዘሠሬው ኦሮሚያ ክልል (ሸዋ፣ አርሲ፣ ሐረርጌ፣ ሲዳሞ፣ ወለጋ፣ ባሌ፣ ኢሊባቡር)፤ በደርግ ጊዜ አምስት ራስ ገዝና 25 አስተዳደር አካባቢ ሆኖ



t.me/OLDBOOKSPDF

ተበታትኖ (በኢትዮጵያ ጥላ ሥር ብቻ አንድነቱ ተረጋግጦ) የኖረ፤ የ1991 ሥሪት መሆኑን መገንዘብ ይገባል።

ደግሞ አንድ ቢያደርግ ኖሮ አረቦች አንድ ሀገር፤ ሶማሊዎች አንድ ሀገር፤ እንግሊዝኛ ደግሞ ተናጋሪዎች ደግሞ አንድ ሀገር በሆኑ ነበር። ለዚህ ነው ጎንደር ከጋምቤላው የተለየ፤ ወለጋ ከሶማሊው የተለየ መብት በአዲስ አበባ ላይ የለውም የምንለው። የምንከተለው ፌደራሊዝም ከኮንፌዴሬሺን ወይም በሀገሮች ፍላጎት የተገነባ ሳይሆን በነበረ የሀገር አወቃቀር ውስጥ ያለ ፍላጎት የተጫነ ነው። ያም ሆኖ የተመሠረተው የፌደራሊዝም አይነት (Holding Together Federal system)

ስለሆነ የትኛውም ክልል የባለቤትነት ጥያቄ ሊያነሳበት አይችልም። "የኦሮሚያ ልዩ ጥቅም" ከብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቱ ፅህፈት ቤት እና ሌሎች መሥሪያ ቤቶች፣ የባህል ማዕከል፣ የሰርቪስ አገልግሎት፣ ገበሬዎች በቅርበት ሰፊ ገበያ ከማግኘታቸው፣ የቤት አገልግሎትን በተሻለ ዋጋ መሸጥ፣ የታክሲ አገልግሎቶች (ኦሮ) በተደራቢነት አዲስ አበባ ውስጥ መሥራት እና መሠል ዳራዎች አንፃር በከፊል አሸየተመለሰ ሲሆን ሌሎችን በዘርፉ ጠለቅ ያለ እውቀት ላላቸው ትተነዋል። ለማንኛውም የበሰለ የተተነተነና የጠለቀ ሥልጡን ውይይት ችግሮቻችንን ለመፍታት ከጡንቻችን ይልቅ ዘላቂ የአሸናፊነት ጥቅም አለው።

## የዐማራው ገገር መደብ ትርክት

የአነግም ሆነ የወያኔ ዘውጌዎች የሰደሯቸው ሰነዶች ከሚያመሳስላቸው ጉዳዮች አንዱ ከየትኛውም ዓለም ተዛምዶ የሌለው ብቻ ሳይሆን ፍፁም ተአማኒነት የሌለው መነሻና መድረሻው ከጥላቻ የሚቀዳ የፈጠራ ድርሰቶች ባለቤትነታቸው ነው። ባዶነታቸው ከሚገለፅበት አንዱ "የአማራው ገገር መደብ" የሚለው ልቦለድ ነው። ለመሆኑ የኢትዮጵያ መሪዎች እነማን ነበሩ? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ በሀገራችን የነበሩትን ሁለት የአስተዳደር አይነቶች እንመልከት፦



t.me/OLDBOOKSPDF

1) ኢትዮጵያ ውስጥ ከመንግሥት ምሥረታ ጋር ተያይዞ፣ የመሪዎች አቅም ሲያይል የሚሰፋውና ጥንካሬያቸው ሲዳከም የሚጠበው ማዕከል (Center) በአንድ በኩል፤
2) በሌላ በኩል የየአካባቢው ገገርዎች በሌላ ገፅ ተከፍለው ሲመዘኑ:-

2.1 የየአካባቢው ማህበረሰብ እስከ አፄ ዮሐንስ ዘመን (1872 - 1889) ከራሳቸው የየአካባቢ መሪዎች ውጭ ሌላ ኃይል ለጥቂት ጊዜ በጊዜያዊነት ከሚጫንባቸው (ወይም አጠገባቸው ባለ ወይም በህዝቦች ንቅናቄ ከሚዋሀዱበት ሂደት) ሌላ ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳድሩበት ሁኔታ ሰፍኖ ቆይቷል።

ለመጀመሪያ ጊዜ አፄ ዮሐንስ አራተኛ ካሩ ላይ የነኛሙን አዳል ተሰማን (ንጉሥ ተከለሀይማኖት በመሾም ስም እና ሥልጣን አስፍተው) በጣም ከንጉሥ ምኒልክ ጋር ለማጋጨት በማሰብ ኗኛምና ካፋን አዳብለው እንዲያስተዳድሩ ከመሾማቸው እና ከእምባቦ ጦርነት በኋላ ካፋን (ከንጉሥ ተከለሀይማኖት ቀምተው፤ ወሎን ከንጉሥ ምኒልክ ቀምተው ለራሳቸው ልጅ አርዓያሥላሴ ዮሐንስ በመስጠት (ምኒልክ አሸናፊ ስለነበሩ፤ በፖለቲካ ጋብቻ ለማሰር አርአያሥላሴን ከ'ዘውዲቱ፡ ምኒልክ ጋር አጋቡ)። ከዚህ ሌላ የማስገበር ሂደት ካልሆነ የየአካባቢውን ማህበረሰብ ማንም ከሌላው ማህበረሰብ በመሄድ በውስጥ ጉዳዩ ጣልቃ ገብቶ አስተዳድሮት አያውቅም።

2.2 በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት:- በሰላም እጅ የሰጡ (Peaceful Submission) አብዛኞቹ የኢትዮጵያ ግዛቶች ራሳቸውን የማስተዳደር ሙሉ መብት ሲሰጣቸው፤ አሻፈረኝ ብለው የተዋጉ (Forceful Subjugation) ስለማይታመኑና በቀጥታ ከማዕከል ሰው ይመደብባቸው ነበር። (ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ፣ ሀሮልድ ማርከስና ጳውሎስ ኞኞ ሰፋፊ ማስረጃ አያይዘዋል።) የሚመደቡት መሪዎች በአመዛኙ ከሸዋ ነበሩ። ለምሳሌ:- ባልቻ ሳፎ 'የሲዳሞ' ጠቅላይ ግዛት ገዢ ሆነው መሾማቸውን ማየት ይቻላል። የኢትዮጵያ የዘመናት ታሪክ ሲፃፍ የዘመናት ማዕከሉ ከመንግሥት ምስረታ ጋርና እንደ ሌሎቹ ሀገሮች ሁሉ በማሰባሰብ ሂደት መነሻ ሆኖ ወደ ቆየው ማዘንበሉ አይቀርም።

በታሪኩ አጻጻፍ ሂደት ምን አይነት የአጻጻፍ ስልት እንከተል? ለሚለው ጥያቄ ከቅድመ ታሪክ ተነስተን በየደረጃው ከመንግሥት አመሠራረት ሂደት ጋር ተያይዞ ወካይ ታሪክ ማዘጋጀት ይቻላል። የኢትዮጵያን ታሪክ በሌሎቹ ሀገሮች ተማስሎ (Model) ከወሰድነው ማዕከሉን እንደ ታላቅ ወንዝ፤ ሌሎቹን እንደ ንፁህ ምንጮች ከወንዙ



t.me/OLDBOOKSPDF

የሚለናኝ አድርገን መውሰድ ተመራጩ መንገድ ይመስለናል። ይህም አንድ የሆነውና በተለያዩ መስተጋብሮች ከልዩነቱ ይልቅ የሚያመሳስለው የሚበዛውን፤ በጣት ዘሚቆጠሩ ግጭቶች በስተቀር ፍቅሩ ጎልቶ የሚታየውን ህዝብ ታሪክ መግፍ ይቻላል። "የኔ ታሪክ" የሚል ጠቅላይ አግላይ ስሜት ጠፍቶ "የእኛ ታሪክ" በማለት የሚነሳው ገድል ሁሉ "የኢትዮጵያ ነው" የሚል የምጥቀት ደረጃ ላይ ስንደርስ፤ ከአገሉ ልከፍት ተላቅቀን በወል ታሪካችን መኩራት እንጀምራለን።

ቅድመ ታሪክ ከአፋር ተነስተን በመራመድ "ሉሲ" ዓለምን ስትዞር ጠብታ አስተዋፅዖ ላይኖረን እንኳ - "ኢትዮጵያ ምድረ ቀደምት" ስትባል የማንኮራው ለምን ይሆን? ፕሮፌሰር አየለ በከሬ "Ethiopia: An African Writing System, Its History and Principles" በተሰኘው የምርምር ሥራቸው ገፅ 53 ስለ ፑንት ምድርና ግብፅ ግንኙነት ሲያወሱ፡- "ከክርስቶስ ልደት በፊት (2743 - 2731) ሳሁሬ በተባለው ፈርዖን ዘመን ከርቤ (Myrrh)፣ ዞጲ (Ebony) እና (Electrum) ከፑንት ምድር መገብየቱን፤ ዘመን ሳይጠቅሱ በአሶሲ ጊዜ ድንኮች (አጫጭር ሰዎች) መወሰዳቸውን (*የግል ማስታወሻ ለቤተ መቅደስ አገልግሎት እንደሆነ ይጠቅሳል)

በፔፒ ጊዜ (2625 - 2475) ካፒቴን ሰብኒ በተባለ ሰው መጫ፣ የዝሆን ጥርስ፣ ወርቅ እና የእንስሳት ቆዳዎች፤ በኋላም ማዕድናት፣ እንስሳት እና የተለያዩ የእንጨት አይነቶች ቀረፋ ነጭ ዕጣን መጓጓዛቸው፤

ገፅ 46 ላይ ደግሞ፡-

"ኢትዮጵያ የእፅዋትና እንስሳት መብቀያ ከሆኑ የዓለም ሀገራት ተጠቃሽ ናት። እንደ ጤፍ (Eragrostis teff)፣ ኑግ (Guizotia abyssinica)፣ False Banana (Musa enesetta)" ይጠቅሱና የጤፍን ሀገር በቀልነት ያስረግጣሉ። በማጠናከርም፡- "ቡና (Coffee arabica) ኮፊ ካፋ ከሚለው ቃል የመነጨ እንደሆነ Kobischanov, Axum (1979) ከገፅ 126 - 132 ዋቢ ጠቅሰው ያሳዩናል። በተጨማሪም ፕሮፌሰሩ 'ጎበዳራ - አከሱም እና በሰቃ ሀይቅ አካባቢ ቢያንስ 2,000 ዓመት እድሜ ያስቆጠሩ የአዝርዕት አይነቶች ስለመገኘታቸው' ፊሊፕሶን "African Archaeology" (1985) እማኝ አድርገው ያወሳሉ።



t.me/OLDBOOKSPDF

'ኢትዮጵያ የጥንት ምድር አካል መሆኗ' በታሪክ ምሁራን መረጋገጡን ስናስብ የውጭ ግንኙነት ረጅም እድሜ ያለን መሆኑ በእጅጉ ያስደስታል።

በሀገራችን የመጀመሪያዋን መንግሥት ዳማትን ጠቅሰን፣ ወደ አክሱም አልፈን፣ ዛግዌ 1150 - 1270 ብንመጣ ከአማራ የዘር ሐረጉን የሚመዝ ስልጣን ላይ የተቀመጠ ግለሰብ አናገኝም። ከ1270 - 1974 ባለው 700 ዓመታት ጊዜ ሥልጣን አሸንፎ መምራት እንደመሆኑ :- ለ15 ዓመታት ኢማም አህመድ መሪ ለመሆን ያደረገውን ሰፊ ትግል እናስተውላለን። "ጥንታዊ የኢትዮጵያ የሰላም ጥበቃ ታሪክ (ከቅራት እስከ ዘመናዊ ፖሊስ) ገፅ 88:-

ግራኝ ልብነ ድንግል ካልተያዘ ወይም ካልሞተ የኢትዮጵያ ገገር እንደማይሆን በማመኑ ባገኘው ድል አልተደሰተም። ይህንን ከፍፃሜ ለማድረስ 'ገራድ' አህማኙ የተባለው የጦር አዛዥ ልብነድንግልን ተከታትሎ እንዲይዝ ታዘዘ። ብዙ ቀን ተከታትሎት ሳያገኘው ተመለሠ።

በማለት ኢማም አህመድ ኢብራሂም መሪ ለመሆን የነበረውን የጋለ ፍላጎት ያሳየናል። የመሪነት ወይም የበላይ ሆኖ የመያዝ ፍላጎት ብሔረሰብ የማይለይ፣ በመላው ዓለም ያለ የነበረና የሚኖር የሰው ልጆች መሻት ነው። የቅዱሳት መፃሕፍትን ታሪክ ስናነብ በየዘመኑ ጎልተው የሚወጡ ስብዕናዎችን እናገኛለን። ለ80 ዓመታት ደግሞ የየጁ ኦሮሞ በምን አይነት ጥበብ ነገሥታትን አሻንጉሊት አድርጎ በወራትና በቀናት ጭምር እየለዋወጠ እንደመራ ማየት ይቻላል። ለ20 ዓመታት አካባቢ አፄ ዮሐንስ አራተኛ ከትግራይ መርተዋል። በታሪክ ከቅርብ ወደ ሩቅ ማሳየት ባይደገፍም ዓላማችን ሙግቱን ለመግለጥ ስለሆነ:-

ከ2018 - 2019 ዶክተር ዓብይ አህመድ አሊ (ኦሮሞ)

ከ2012 - 2018 አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ቦሼ (ወላይታ)

ከ1991 - 2012 መለስ ዜናዊ አስረስ (ትግሬ)

ከ1974 - 1991 መንግሥቱ ኃይለማርያም ወልዴ አያና (አሮሞ)

ከ1930 - 1974 አፄ ኃይለሥላሴ መኮንን ወ.ሚ. ጉዲሳ (አሮሞ)



t.me/OLDBOOKSPDF

'ኢትዮጵያ የጉንት ምድር አካል መሆኗ' በታሪክ ምሁራን መረጋገጡን ስናስብ የውጭ ግንኙነት ረጅም እድሜ ያለን መሆኑ በእጅጉ ያስደስታል።

በሀገራችን የመጀመሪያዋን መንግሥት ዳግማትን ጠቅሰን፣ ወደ አክሱም አልፈን፣ ዛግዌ 1150 - 1270 ብንመጣ ከአማራ የዘር ሐረጉን የሚመዝ ስልጣን ላይ የተቀመጠ ግለሰብ አናገኝም። ከ1270 - 1974 ባለው 700 ዓመታት ጊዜ ሥልጣን አሸንፎ መምራት እንደመሆኑ :- ለ15 ዓመታት ኢማም አህመድ መሪ ለመሆን ያደረገውን ሰፊ ትግል እናስተውላለን። "ጥንታዊ የኢትዮጵያ የሰላም ጥበቃ ታሪክ (ከቅራት እስከ ዘመናዊ ፖሊስ) ገፅ 88፡-

ግራኝ ልብነ ድንግል ካልተያዘ ወይም ካልሞተ የኢትዮጵያ ገገር እንደማይሆን በማመኑ ባገኘው ድል አልተደሰተም። ይህንን ከፍፃሜ ለማድረስ 'ገራድ' አህማዱ የተባለው የጦር አዛዥ ልብነድንግልን ተከታትሎ እንዲይዝ ታዘዘ። ብዙ ቀን ተከታትሎት ሳያገኘው ተመለሠ።

በማለት ኢማም አህመድ ኢብራሂም መሪ ለመሆን የነበረውን የጋለ ፍላጎት ያሳየናል። የመሪነት ወይም የበላይ ሆኖ የመያዝ ፍላጎት ብሔረሰብ የማይለይ፣ በመላው ዓለም ያለ የነበረና የሚኖር የሰው ልጆች መሻት ነው። የቅዱሳት መፃሕፍትን ታሪክ ስናነብ በየዘመኑ ጎልተው የሚወጡ ስብዕናዎችን እናገኛለን። ለ80 ዓመታት ደግሞ የየጁ ኦሮሞ በምን አይነት ጥበብ ነገሥታትን አሻንጉሊት አድርጎ በወራትና በቀናት ጭምር እየለዋወጠ እንደመራ ማየት ይቻላል። ለ20 ዓመታት አካባቢ አፄ ዮሐንስ አራተኛ ከትግራይ መርተዋል። በታሪክ ከቅርብ ወደ ሩቅ ማሳየት ባይደገፍም ዓላማችን ሙግቱን ለመግለጥ ስለሆነ፡-

ከ2018 - 2019 ዶክተር ዓብይ አህመድ አሊ (ኦሮሞ)

ከ2012 - 2018 አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ቦሼ (ወላይታ)

ከ1991 - 2012 መለስ ዜናዊ አስረስ (ትግሬ)

ከ1974 - 1991 መንግሥቱ ኃይለማርያም ወልዴ አያና (ኦሮሞ)

ከ1930 - 1974 አፄ ኃይለሥላሴ መኮንን ወ.ሚ ጉዲሳ (ኦሮሞ)



t.me/OLDBOOKSPDF

ከ1916 - 1930 ዘውዲቱ ምኒልክ (3/4ኛ ኦሮሞ + 1/4ኛ አማራ)

ከ1913 - 1916 ልጅ ኢያሱ መሀመድ አሊ (ኦሮሞ እና 1/8ኛ አማራ)

ከ1889 - 1913 አፄ ምኒልክ ኃይለመለኮት ሣህለሥላሴ (ኦሮሞ እና አማራ)

ከ1872 - 1889 አፄ ዮሐንስ ምርጫ (ትግራይ)

ከ1868 - 1871 አፄ ተክለጊዮርጊስ ገብረመድህን (ዋግና ላስታ)... በዚህ መሠረት በዘመናት ውስጥ ዘርዝረን የማንዘልቀው ውህደት እና አብሮነት ያለ መሆኑ ጥያቄ ስለማያስነሳ ወደ 'ሰሎሞናውያኑ' እንለፍ።

አፄዎቹ ራሳቸው አንድም ቀን አማራ ነን ብለው አያውቁም። የራሳቸውን ማስረጃ እንጥቀስ፡-"ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ"፤ "ሥዩመ እግዚአብሔር"፤ "ንጉሠ ነገሥት (ቀዳማዊ ዳግማዊ ሣልሳዊ ራብዓዊ ...) ዘኢትዮጵያ" - ይህንን በመተንተን ብንሄድ "አንበሳው" ከይሁዳ ነገድ መነሻውን ያደርጋል። ይሁዳ (እስራኤልን) እንጂ አማራውን አይወክልም። የመሪዎቹ መነሻ በአባታቸው በኩል የእስራኤሉ ንጉሥ ሰሎሞን ከአብራኩ የተከፈለው 'ቀዳማዊ ምኒልክ' ነው ይላሉ። (ዘር ሚጠራው በአባት ነው የሚሉ የመሪዎቹ መነሻ አባት እስራኤል በመሆኑ ምን ይውጣቸው ይሆን?) ለመሆኑ የአማራ መገኛ እሥራኤል ነውን? በመሆኑም ነገሥታቱ ተመቹንም ኀረበጡን ካባቸው በአንድ በኩል የእስራኤል ነበር።

"በእግዚአብሔር የተሾመ" ከሚለው አገላለፅ በአብዛኞቹ ሥርወ መንግሥቶች ሁሉ ሌላው ሥልጣናቸውን እንዳይደፍር የሚጠቀሙበት ሥልት ነው። የግብፅ ፈርዖኖች (Incarnate god / demi god) እንደሆኑ ተቆጥሮ ማንም ሰው ወደ መንበራቸው የሚጠጋው ፊታቸው ላይ ሰግዶ ነበር። የዛግዌ አገው መሪዎች ከፊትለፊት "ቅዱስ" - የመጠሪያ ቅፅል ሆኖ አገልግሏል። በቀለ ወልደማርያም አዴሎ፡- "የካፋ ሕዝቦች እና መንግሥታት አጭር ታሪክ" በሚል ርዕስ ባሳተመው መፅሐፉ የካፋ ነገሥታት "መንፈሳዊ መሪዎች" እንደነበሩ ያወሳል። በመፅሐፉ ከገፅ 114 ጀምሮ የሥርአቱን አወቃቀር በዝርዝር ሲገልፅ፡- ጉጀራሾ (ጉቻራሾ)፡- "የጠቅላይ ሚኒስትርነት እና የምክር ቤት ሰብሳቢነት ሚና" እንዳለው ያትትና "የንጉሡን ባሮች ይቆጣጠራል።" በማለት ያስቀምጣል። (ሰሎሞናውያኑ በርካታ አካባቢዎችን ከባርነት ቀንበር ነፃ



t.me/OLDBOOKSPDF

ማጠቃለያቸውንም ቃኝተን አንዘልፍ።) - ለማንኛውም "በእግዚአብሔር የተሾመ" የሚለው ከአማራ ጋር ግንኙነት የለውም። የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት 'ቀዳማዊ' የሚል ቅጽል ቅጥያ ካስገባ በዚያ ስም ቀድሞ የነገሠ የለም ማለት ነው። ዳግማዊ :- ከንጉሡ ቀድሞ በተመሣሣይ ስም የተሾመ ካለ ለምሳሌ:- ቀዳማዊ ቴዎድሮስ (1412 - 1413) ነግሦ ስለነበር፤ ሁለተኛው ዳግማዊ (1855-68) ተባለ።

ከአፄ ዮሐንስ አራተኛ በፊትም ቀዳማዊ ዳግማዊ እና ሣልሳዊ በዮሐንስ ስም የነገሡ ነበሩ፡ በዚህም መሠረት ከአንድ ቤተሰብ የዘር ሐረግ ውጪ አማራው በምንም ተአምር እንደማይነግሥ እየታወቀና አጠገቡ ያሉ መረጃዎች ግፍ ከፈፀሙም የዘመናት የመከራ ፅዋው ቀማሽ አማራ ሆኖ እያለ - "የአማራ ገዢ መደብ" የሚለው ሸፍጥ ዓላማው አማራውን የለለ የጦስ ዶሮ ማድረግ ነው። ከዚህ በተጓዳኝ የቀዳማዊ ምኒልክ እናት "ንግሥተ ሳባ" የአክሱም ንግሥት መሆኗ ይታወቃል። መቼም እንደ መለስ 'አክሱም ለአማራው ምኑ ነው?' እንልም፤ አብርሆት ከመስጠት ግን አንቦዝንም። በሌላ አመክንዮ የጀርመን ነገሥታት የሚጠሩት "ሆሄንዞለርን ሥርወ መንግሥት"፤ የሩሲያ "ሮማኖቭ"፤ የኦስትሪያ - ሀንጋሪ "ሀፕስበርግ"፤ ኢትዮጵያ ውስጥ:- የየም - ሞቄ፤ የሸዋ - ማከዙማይት፤ የኢፋት - ወላዝማ ... ይህንን መረዳት ለሚያዳግተው ከዘፍጥረት ወይም ሱረቱ አልፋቲሀህ መጀመር ሊያስፈልገን ነው። በመሆኑም 'የአማራው ገዢ መደብ የሚባል ነገር የለም።'

አማራው ራሱ ገዢዎቹ እንደማንኛውም የኢትዮጵያ ማህበረሰብ (እንደውም በበለጠ ደረጃ የሚበድሉት)፤ ከልሉም ኋላ ቀርነት የሚያጠቃው፤ በየትኛውም ሥፍራ ተጋብቶ ተዋልዶ በአብዛኛው በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው። በዚህ ደረጃ ወርዶ መተንተን የሚያስፈልግበት ምክንያት በዐይናችን የምናየውን እውነት 'የአቅም ማምከኛው ሰነድ' በፈጠረው የለለ ብኽርታ እና የጥላቻ የተጠናከረ ዘመቻው ተዳልቦ በደመ ነፍስ የሚነዳው ወገን ቁጥሩ የማይናቅ በመሆኑ ነው።

ለዚህም ነው በተማሪዎች እንቅስቃሴ እና በኢህአፓ በግንባር ቀደምትነት፤ ሌላው ቀርቶ መጀመሪያ በኢህዲን፤ ኋላ በረከሰው የወያኔ ትግል ውስጥ በኢህአዴግ አማራው ሁለተኛውን መስዋዕትነት የከፈለው። በመሆኑም በአማራው ላይ የተከፈተው ዘመቻ አማራው ላይ ያነጣጠረ ቢመስልም የመጨረሻ ግቡ ኢትዮጵያን መበተን ነውና አመለካከቱን ሁላችንም ያለልዩነት አምርረን ልንዋጋው ይገባል፤ የሰለጠነ ሰው የሚታገለው ለእያንዳንዱ ዜጋ መብት ነው። በቀጥታ ሲሆን፤ በጋብቻ



t.me/OLDBOOKSPDF

ተደምሮ 2/3ኛውን የኢትዮጵያን ህዝብ የማጥቃት እና የማስጠቃት ፍላጎት መነሻው መድረሻው ተልእኮው ግቡ ምንድነው? ሙሉ ሥዕል በያዘንበት ተጨማሪ ማስረጃ ፍለጋ እንዳክርም። ከዚሁ ጋር "በኢትዮጵያ የረጂም ዘመናት ታሪክ ውስጥ ማነው ተጠያቂው?" የሚል አንኳር ጥያቄ ብናነሳና በማስረጃ ብናስደግፍ በርካታ ጥራዞች ብንፅፍ እንኳ ሊገልፁት አቅም የላቸውም። በአባት ወንጀል ልጅ አይጠየቅም። በጦረኞች ወንጀል ህዝብ አይወቀስም።

በትላንት ታሪክ ዛሬ ላይ ማንም ተከሳሽ አይኖርም። የአክሱም ስልጣኔ ለምን ወደቀ? በዋናነት በ702 አረቦች የአዱሊስን ወደብ ስለደመሰሱ። የቢጃ ወልቃይትና አገው ህዞቦች ስለተነሱባቸው። ጀነራል አብርሀ ደቡብ አረቢያ ውስጥ ስላመፀ። እንደከዚህ ቀደሙ ማስተዳደር ስላልቻሉ የሚሉት ምላሾች ናቸው። ሥልጣኑን ማን ነጠቀ? ስንል አገዎች የሚል ሌላ መልስ ጋ ያደርሰናል። ሥልጣን የሚነጠቀው ደግሞ ጉልበትን ተገን አድርጎ ነው። ከአክሱም ምን ወሰዱ ስንል፤ ምላሻችን እጅን በአፍ የሚያስጭኑ የቤተ ክርስቲያን አሠራር ጥበቦችን አሻሽለው መውሰዳቸውን እናስተውላለን። ይሁንና ከዚህ የሠፉ ስልጣኔዎች በዛግዌ ዘመን አናይም። ዛግዌ በይፋ የሚታወቁ አራት ክፍለ ሀገራት ነበሩት። እነርሱም የሚተዳደሩት በንቡረ እድ፣ ርእሰ ርእሳን፣ ሊቀ ካህናት እና ፓትርያርክ መንፈሳዊ ስያሜ ባላቸው ባለሥልጣኖች ነበር ።

ቀጥሎ እነማን ሥልጣን ተረከቡ? ሰሎሞናውያን የሚል ምላሽ ላይ እንደርሳለን። ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ እንደሚነግሩን ወላይታ ማላ ሥርወ መንግሥትን ከሰሜን የመጣው የትግራይ ሥርወ መንግሥት በ15ኛው ክፍለ ዘመን በመፈንቅለ መንግሥት ስልጣን ያስለቀቀው ሲሆን፤ የየም አስተዳደርም በተመሳሳይ ሞዋ የተባለ ከሰሜን የመነጨ ሥርወ መንግሥት ተቆጣጥሮታል። ከይኩኖ አምላክ እስከ ኃይለሥላሴ ታሪኩ ተቀንጭቦ በዚህ ሰነድ (ምዕራፍ ሦስት ውስጥ አለ።)*በተመሣሣይ:- ዮዲት 'ጉዲት' እንዴት ተጓዘች? ግራኝ አህመድ እንዴት ተንቀሳቀሰ? የኦሮሞ ጦረኞችስ? ካፋ ማንጃ ላይ ምን ፈፀመ? የቦረና ጉጂ ገሪ እና ወዩ ግንኙነት ምን መልክ ነበረው? ከምባታና ሀዲያ ጉርብትናቸው ምን መልክ ይዞ ቆይቷል? ጎጃምና ጎንደር፣ ሸዋና ወሎ፣ ኦሮሞና ጉራጌ፣ አፋርና ኢሳ፣ ጌዴኦና ጉጂ፣ ጎጃምና ጎንደር፣ ጉሙዝ እና ወለጋ... ግንኙነታቸው የፍቅር ብቻ ነበር ወይ?

ሌላው በጣም የሚያሳቅቀው ጉዳይ በአንድ በኩል የተገናኘነው በቅርቡ ነው ይሉና መልሰው "ለዘመናት ወደ ኋላ አስቀርተውን" ሲሉ ይደመጣሉ። እየተስተዋለ እንዷ



t.me/OLDBOOKSPDF

ጎበዝ! አፍሪካ ውስጥ እኮ ነን። ጎረቤት ሶማሊያን እንመልከት፡- ከቅኝ ግዛት በፊት መቼም ኢትዮጵያውያን አላስተዳደሯት። ምነው ኋላ ቀረች ነው ወይስ የኢንዱስትሪ አብዮት አካሂዳ ነበር? የአርብቶ አደር ኑሮ አይደለምን?*ኬንያስ? አርብቶ አደርና ከፊል አርሶ አደር ደረጃ ላይ መሆኗ አያከራክርም።

ነመሆኑ የትኛውን የሥልጣኔ ምጥቀት አስመዝግበን ቆይተን ነው ወደ ኋላ ያስቀሩን? ሬም የትላንት መልኮቻችን ማሳያዎች እነርሱን በረገሙት ደርጎችና ወያኔዎች ለፈው አጠገባችን አሉ። ሙርሲ ኛንጋቶም አሪ ባስኬቶ (ያውም በዱንጋ ባህላዊ ዋታ በዱላ እስከሞት እየተፈላለጡ...) ማስተዋል በገንዘብ የማይገዛ ሀብት ነው። ደመው ከፍል ያኖርነውን የቋንቋዎችን ዝርዝር ዐይተን ማህበረሰቦቹን ማን ወደፊት ጉበት ወደ ኋላ አስቀራቸው? ብለን ጠይቀን እናልፋለን። ለምሳሌ፡- ትግራይን ሱም የባሪያ አሳዳሪ ሥርአተ ማህበር ጀምሮ በዘመናት ውስጥ ከራሷ ሌላ ማንም ዓድጅት አያውቅም።

ገደ ኋላ አስቀረኝ ልትል ነው? አማራውንስ ማን ወደ ኋላ አስቀረው? አፍሪካን ት እነማን ወደኋላ ጎተቷት? ምክንያት አጥጦ ስሜት ሲገነግን የታሪክ አፃፃፍ ። (በዚህ ርዕስ ዙሪያ ዘርዘር ያለ ሐተታ ማቅረብ ያልወደድነው ከጥቅሙ ግዝናል በሚል አሳቤ በምክንያት ነው።) ይሁንና ሁሉም ራሱን ወደ ውስጥ ብለን ብቻ በይደር እናልፈዋለን። አንድ ጠንካራ መራራ ትዝብት ግን ትላንትን ለመውቀስ በደረስንበት ሠለጠነ በሚባልበትና ምርጥ ተሞክሮ ም የሚሰቀጥጥ ወንጀል አየፈፀምን ዕየታየን፤ ለመሆኑ ምን የ'ሞራል' ? ስናጠቃልለው 'የአማራው ገገር መደብ' አልነበረም። ሁላችንም ወደ ነዳንዳችን ውስጥ እናስተውል።

፣ የውስጥ ውበት የማጉላታችንን ያህል ሌሎቹን በተመለከተ ሥልጣን ምር አዲስ ቦታ በጉልበት መያዝ ቅድመ ሁኔታ የነበረበትንና ቢነሱ ዎዶችም እንደነበሩት መገንዘብ ይበጃል። ዛሬ አዲስ ዘመን ላይ ነን። ሞከሮዎችን አቀብላናለች። ከገዳ ሥርአት ጀምሮ ድንቅ ልምዶችም ነ፣የስወገድን በጎዎችን ይዘንና አምጥቀን ወደፊት። 'የኋላው ከሊለ ር ይዘን፣ አርፍ ጨብጠን ወደፊት የሚለማው እርሻው እያለልን የምናብ ማሳ በመፈለግ ጊዜያችንን በከንቱ እናሳልፍ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# የኤርትራ እና የአሰብ ወደብ ጉዳይ

## የኤርትራ ጥያቄ

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አወዛጋቢ ከሆኑ አጀንዳዎች መሀከል የኤርትራ ጉዳይ ጎልቶ ይጠቀሳል። የኤርትራ ጉዳይ ያበቃለት እና የተደመደመ (Foregone Conclusion) ቢመስልም በየጊዜው እየተነሳ የመከራከሪያ አጀንዳ ከመሆን አልዘለለም። በመሆኑም ግልፅና አሻሚ ያልሆኑ የታሪክ መረጃዎችን ሳይሆን ተጨባጭ ማስረጃዎችን በመጥቀስ እነሆ የሚከተለውን አጭር የታሪክ ምልከታ አሠፈርን። ኤርትራ እንደየትኛውም የሀገራችን ክፍል ከኢትዮጵያ ጋር የኖረችበት ታሪካዊ ዳራ በመረዎች ጥንካሬ ላይ የተመሠረተ ሆኖ ቆይቷል። ለባህር በር ቅርብ መሆኗ የደቀነባት አደጋ ቀላል ግምት የሚሰጠው አይሆንም። በተለያዩ ወቅቶች በኦቶማን ቱርክ፣ ግብፅ እና ጣልያን ተፈትናለች።

የመጨረሻው መጀመሪያ፡- በ1869 ንብረትነቱ የጁሴፔ ሳፔቶ የሆነው ሩባቲኖ የመርከብ ሥራ ድርጅት የአሰብን ወደብ ከአፋሩ ሡልጣን ሳላህ ሳቢህ ገዛ። ወቅቱ ቅኝ ገዢዎች አፍሪካን መቀራመት የጀመሩበት ነበር። ፖርቱጋል ስፔይን ቤልጂየም ብሪታኒያ ፈረንሳይ ጀርመንና ጣሊያን የኢንዱስትሪ አብዮት የፈጠረውን ከፍተኛ ፍላጎት ተከትሎ ዐይናቸውን ወደ አፍሪካ ጣሉ።

አፍሪካ ከዓለም በሥልጣኔ እጅግ ወደ ኋላ የቀረችና አውሮፓውያንም በቀላሉ ወደ ውስጥ ዘልቀው መግባት እንዳይችሉ ገዳይ የሆኑት ሁለት የአፍሪካ ወታደሮች (ወባ እና ፀ-ፀ ዝንብ) ከለከሏቸው። ከ1500 - 1800 ባለው ጊዜ ከአፍሪካ የሚዲትራንያን እና ምዕራባዊ ድንበር አካባቢዎች ጋር የንግድ ልውውጥ ጀመሩ። ለአፍሪካ ምዕራባዊ ጠረፎች ከሚያገኙት ሸቀጥ በመነሳት፡- የዝሆን ጥርስ ዳርቻ (Ivory Coast)፣ የወርቅ ዳርቻ (Gold Coast)፣ የባሪያ ዳርቻ (Slave Coast)፣ የቅመም ዳርቻ እና ሌሎች ስያሜዎችን መስጠት ቀጠሉ።

ከዛሬ 200 ዓመታት አካባቢ በፊት አውሮፓውያን የአፍሪካን ውስጥ ግፋ ቢ አሳሾችና ተጓዦች ወይም ሚሲዮናውያን ካልሆኑ አያውቁትም ነበር ብንል ትክክ



t.me/OLDBOOKSPDF

ነን። አንዳንድ ጨዋዎች 'ለአፍሪካ ኋላ መቅረት ተጠያቂዎቹ አውሮፓውያን ናቸው' ሲሉ ይደመጣሉ። እውነታው ግን አፍሪካ በጣት ከሚቆጠሩ ጥቂት ቦታዎች በስተቀር የሰብአ ትካት አኗኗር፣ የአርብቶ አደር ዘይቤና ጥቂት ገና በአርሻ ሥራ ዳዴ እያለ ነበር። አፍሪካ ችግሮቿን እንጥራ ለይታ መፍትሔ ከማስቀመጥ ይልቅ 'ወደ ሌሎች ሊባ ጣቷን ስትቀስር የተቀሩት ጣቶች ባከሽ ውስጥሺን ተመልከቺ' እንዲሏት ዘመናት ነጉደዋል። አውሮፓውያን በመጀመሪያው የንግድ ግንኙነት መስመር የአፍሪካን ጉልበት ወስደው በአሜሪካ እና አውሮፓ ተጠቀሙበት።

ይህንን የ10 ሚሊዮኖች የባሪያ ጉልበት የተዘረፈበት የ300 ዓመታት ዘመን ህገወጥ ንግድ (Illegitimate Trade) ይሉታል። ጉልበቱ አውሮፓ ባይሄድ አፍሪካ ውስጥ በአደንና ፍራፍሬ ለቀማ፣ እንስሳት ማርባት እና እርሻ ሥራ ላይ ይውል ስለነበር በርግጥ ያስቆጫል። የኢንዱስትሪ አብዮት በብሪታኒያ በ1750 ተጀምሮ ወደ ሁለተኛው ምዕራፍ 1850 ከመሸጋገሩ በፊት አዳዲስ ፍላጎቶች ጎልተው ወጡ።

በቅኝ ግዛት አፍሪካን በመያዝ፡- ርካሽ ጉልበት አፍሪካ ውስጥ መጠቀም፣ ጥሬ ዕቃ መዝረፍ፣ ሠፈራ ማካሄድ፣ የኢንቨስትመንት አማራጭ ማየት እና ሠፊ ገበያ መፍጠር ዋነኛ መሻታቸው ሆነ። የወባ መከላከያ መድሀኒት "ኩዊኒን" መፈልሰፉ የሰጣቸውን 'የይለፍ ፈቃድ' በመያዝ አፍሪካን በመጠኑ እያዘመኑ ሥፍር ቁጥር የሌለው ግፍ 'ፈፀሙበትን እና በዘረፉ የሚገለፀውን ይህንን ዘመን "ህጋዊ ንግድ (Legitimate Trade)" የሚል የለበጣ ስያሜ አለበሱት።

ሰው መነገድ (የባሪያ ንግድ) በጣም አረመኔያዊ ድርጊት ቢሆንም ቅኝ ግዛት መላ የንነትንና ምንነትን መጨፍለቅ እንደመሆኑ ከባርነት ያልተናነሰ፤ ከዚያም አልፎ ጅግ በጣም የከፋ የጭካኔ ጥግ ነበር። በዚህም መሠረት ብሪታንያ ከ1839 ጀምሮ ደን ባህረ ሠላጤን በመያዝ ለአካባቢው ሥጋት ሆነች። በ1862 ፈረንሳይ አቦክ ቡቲ) ላይ እግሯን ተከለች። ከላይ እንደተመለከትነው 1869 ጣሊያናዊ የሚስዮ ነንያ የገዛውን የአሰብን ወደብ ለጣሊያን መንግሥት አስረከበች።

ው በጣም ግልፅ ነበር። አውሮፓውያን አሳሾችን ለጥናት አስቀድመው በመላክ ነትለው ሚሲዮናውያንን ለተጨማሪ ስለላ እና መረጃ ያስማራሉ፤ በመሠለ ንያ ልከው፣ ለጥቀው የማጭበርበር ስምምነት (Fake Treaty) 'ሌላ አውሮፓዊ በጉልበት እንዳይይዛችሁ እንጠብቃችሁ (Protectorate) - /የቅኝ ግዛት የበ



t.me/OLDBOOKSPDF

ስም ነው' ይሉና በመጨረሻ በጉልበት ይጠቀልላሉ። (Outright Conquest) ለቅድመ ሁኔታው 1882 ሩባቲኖ ኩባንያ አሰብን ለጣልያን መንግሥት አሳልፎ ሰጠ። የአሰብ ወደብና አካባቢው በጣልያን ሥር ወደቀ። የወቅቱ የኢትዮጵያ መሪ አፄ ዮሐንስ አራተኛ ነበሩ (1872 - 1889)፤ በዚህ በኩል አፄ ዮሐንስ ከ1872 - 1889 (ለ17 ዓመታት) አንዳችም ተቃውሞ አላቀረቡም።

በምስዋ በኩል የግብፅ ፍላጎት ከኦቶማኖች በሊዝ ኮንትራት በወሰደቺው ዳርቻ ሳይገታ ወደ ውስጥ በመዝለቅ የኤርትራን አካባቢዎች ለመቆጣጠር በመፈለግ ከአፄ ዮሐንስ አራተኛ ጋር የጉንዲት በአጭር ሰአት የተጠናቀቀ ውጊያ (1875) እና ደም አፋሳሽ የሆነ የሦስት ቀናት የጉራ ጦርነት (ማርች 7 - 9፣ 1876) ተደርጓ በሁለቱም ጦርነት አፄ ዮሐንስ ወደ 4,000 ገደማ ወገን ተሰውቶ በህያው ተጋድሎ በጦርነት አንፀባራቂ ድል አገኙ። (በታሪኩ ዙሪያ ያለው ጎዶሎ ድሉ የተጠናቀቀ አለመሆኑ ነው። ምክንያቱም አፄ ዮሐንስ ግብፆች ምፅዋን ጨምሮ የያዟቸውን የኢትዮጵያ ግዛቶች ለማስለቀቅ አንዳችም ሙከራ አለማድረጋቸው በፕሮፌሰር ባህሩ፣ ሀሮልድ ማርከስና በጉዳዩ ዙሪያ ጥልቅ ጥናት ያደረጉ የሚስማሙበት እውነት ነው።)

በመሆኑም በዘመናዊ የኢትዮጵያ ታሪክ ዙሪያ ወደር የማይገኝለት ሥራ ያበረከቱት ኢሜሪተስ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ እንደገለፁት ከ1876 - 1884 የግብፅና የኢትዮጵያ ግንኙነት "ጦርነትም ሰላምም የለም" (No War - No Peace) ሆኖ አለፈ። በ1881 በሱዳን ውስጥ መሀዲ (የእስልምና እምነት ትክክለኛ የአምልኮ ሥርአት አመላካች) ተብሎ በተሰየመው ሙሀመድ ኢብን አል ሰይድ አብደላ አማካይነት የመሀዲስቶች እንቅስቃሴ በሱዳን ውስጥ ተጀመረ።

የመሀዲስቶች ንቅናቄ ሁለት መልክ ነበረው። የመጀመሪያው ከ1821 - 1861 ለስድሳ ዓመታት ግብፅ የዓባይን ተፋሰስ መነሻ ለመያዝ ባላት ፍላጎት ሱዳንን በጉልበት ይዛ ስለቆየች ከግብፅ አገዛዝ ቀንበር የመላቀቅ ፍትሀዊ የነፃነት ትግል እና በግብፅ የአምልኮ ሁኔታ ውስጥ የታየውን ዝንፈት የማረቅ ትግል (Religious nationalist and revivalist movement) አጣምሮ የተካሄደ ትግል ነው።

በአጭር ጊዜ 100ሺህ ሱዳናውያንን ያስተባበረው ትግል የግብፅን ጦር አጣብቂኝ ውስጥ ከተተው። ከወዲህ ኢትዮጵያ ከወዲያ መሀዲስቶች በሁለት አለቶች መሀከል ተፈጥርቆ ተያዘ። ታሪካዊ ግጥምጥሞሽ ሆነና በ1882 ብሪታንያ ግብፅን ተቆጣጠረች።



t.me/OLDBOOKSPDF

በመሆኑም እንደ 'በላይ ጠባቂነቷ' በሱዳን ውስጥ ያሉት የግብፅ ወታደሮች በመሀዲስቶች ተሰቅዞ መያዝ ቀላል ብልሀት ያስፈለገው ነበር። ያለ ዝግጅት ጦርነት ውስጥ መግባት መጠኑ ይነስም ይብዛ ዋጋ ያስከፍላል። በመሆኑም ድንገት ቢሳካልን በሚል አሳቢ አጋር ፍለጋ ሲያማትሩ በቅርቡ ለካ አፄ ዮሐንስ አራተኛ አሉ።

## የፀፄ ዮሐንስ ታሪካዊ ስህተት

የብሪታንያ መንግሥት ልዑክ በከቡር ሪር አድሚራል ዊሊያም ሂወት እየተመራ ወደ ፀፄ ዮሐንስ ቤተ መንግሥት በመምጣት ከፀፄው ጋር "የሂወት ስምምነት ወይም የአድዋ ውል" እየተሰኘ የሚታወቀውን ሰነድ ተፈራረመ (Hewett Treaty or Adwa Treaty) ጁን 3 ቀን 1884። ስምምነቱ ሰባት ነጥቦችን ያዘለ ሲሆን የተፈረመው በብሪታንያ ግብፅ እና አፄ ዮሐንስ ስምምነት ነበር። በዋነኛነት ከኤርትራ ጋር የሚያያዘው - ፀፄ ዮሐንስ መሀዲስቶችን ወግተው የግብፅን ጦር በማስለቀቅ ምፅዋ በኩል እንዲያልፉ መርዳት እና ለዚህ ውለታቸው በግብፅ የተያዙትን ምፅዋንና ሌሎች የኢትዮጵያ ግዛቶች በችሮታ መልክ ከብሪታንያ መንግሥት መቀበል ነር።

ግብፅ ጋር ከጉራ ጦርነት (1876) በኋላ ለዘጠኝ ዓመታት መዋጋትና ግዛታቸውን ያስመለስ ያልደፈሩት ዮሐንስ ጅል ውሳኔ ወስነው፤ በሚያሳፍር መልኩ በሱዳን ስጥ ጉዳይ ጣልቃ ገብተው እና አሉላን በመላክ መሀዲስቶችን ወግተው የግብፅን አስለቀቁና በምፅዋ በኩል እንዲሻገር ረዱት። በአፀፋው የተገባላቸውን ቃል ባበቁ እንግሊዝ በ1885 ግብፅን አስወጥታ ጣሊያን ምፅዋንና የተያዙ የኢትዮጵያ ችን ከፌብሩዋሪ 5 ቀን 1885 ጀምሮ እንድትቆጣጠር አደረገች።

ግሊዝ ጣሊያንን የጋበዘቺው ከአፍሪካ ከሰሜን ካይሮ ወደ ደቡብ ኬፕታውን ዝ በምታደርገው ሩጫ፤ በሌላ ዛቢያ ከዳካር እስከ ጂቡቲ የምትገሰግሰውን ይን ጉዞ ለመግታት ነበር።) አፄ ዮሐንስ የጣሊያኖች ስፍራውን መያዝ ቸው ወደ ብሪታንያዋ ንግሥት ቪክቶሪያ፦ 'ምነው ስምምነታችን ፈርሶ ቦታውን ያዘችን?'የሚል ደብዳቤ ሲፅፉ የተሰጣቸው ምላሽ የሚገርም ነበር። የ ምላሿ፦ "አርፈህ ኃያል ከሆኑ ጎረቤቶችህ ጣሊያኖች ጋር በሰላም ኑር" ምጨጭ ያለ ሆነ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ዉ ዮሐንስ በሱዳኖች የነፃነት ጉዳይ ጣልቃ ገብተው የከፈሉት አላስፈላጊ መስዋዕትነት - 'ግብፅ መቼም ወዳጅ ላትሆን' ሁለት ጠላት ገዙበት። በሰሜን ጣልያን በምዕራብ መሀዲስት ሱዳን። 'እስሬ ሳይለኩ እንዴ የቆረጡት' አፄ ዮሐንስ በፈፀሙት ታሪክ የማይታገሰው ስህተት፤ ጣሊያኖች ምሽግ እየቆፈሩ ኤርትራ ውስጥ እንዲናኙ በር ከፈተላቸው። 'ለእጅ የተጠየፉት ለመቀመጫ ይተርፋል' ሆነና ከግብፅ የሸሹት ውጊያ ከጣሊያንና ከመሀዲስቶች ጋር ሲጋፈጡት ከፊት ለፊታቸው ተጋረጠ። ወደ ጣሊያን የከተት ዘመቻ አደረጉና በቀደመው ክፍል ያየነው ከዶጋሊ ግጭት (1887) በስተቀር ከጣሊያን ጋር ለወር ተፋጥጠው እያለ መሀዲስቶች ለብቀላ መተማን ወረሩ።

ከጣሊያን ጋር 'ካብ ለካብ' ሲተያዩ የመሀዲስቶች ዜና ሲመጣ ሊዋጉ ወደ መተማ እየተመሙ የወሬ ጭምጭምታ ሰሙ "ጎጃምና ሸዋ አድመው ብሀል" የሚል። በዚህ ጊዜ ጣሊያንን የሚያህል ኃይል የሚያስተዳድሩትን ግዛት ይዞ፤ መሀዲስትን የሚያህል ጦር ዋጋ ሊያስከፍላቸው ከፊትለፊታቸው ተደቅኖ እያለ ጎጃምን በሺህዎች ጨፈጨፉት። 'በእኔ ይሁን በገበሬው ጥፋት አላውቅም፤ እጇ በደም ጎርፍ ታጠበ' በማለት ሳይገቱ - ሸዋን ለመምታት ገሰገሱ። ምኒልክ ሽማግሌ ልከው እርቅ ፈፀሙና 'እከተልሀለሁ' አሏቸው።

አፄ ቴዎድሮስን መርተው አስገድለው ማርከስ "በኢትዮጵያ ታሪክ" ጦማሩ ገፅ 50 እንዳስቀመጠው፡- "የትግራዩ ካሳ ምርጫ (ከ1872 -1889 አፄ ዮሐንስ አራተኛ) የእንግሊዝን ጦር አጅበው መንገድ መርተው፣ አቅጣጫ ዐሳይተው፣ ስንቅ አቀብለው በመርዳታቸው እና አፄ ቴዎድሮስን በማስገደላቸው የረካው የጦሩ መሪ ናፒየር፣ ከድሉ በኋላ በመርከብ 500,000 'ስተርሊንግ ፓውንድ' (የእንግሊዝ ውድ ገንዘብ)፣ ከባድ መሣሪያዎች፣ የጠብመንጃ አይነቶች (Muskets and rifles) እና በርካታ ጥይቶች በስጦታ አበርክቶላቸዋል።" ታዲያ ቴዎድሮስን ያስገደሉትን ዮሐንስን፣ ጎጃምን የጨፈጨፉትን ዮሐንስን፣ አፄ ምኒልክን በግብር ጫንቃቸውን ያጎበጡትን ዮሐንስን፣ ወሎን ከምኒልክ ነጥቀው ለልጃቸው አርአያሥላሴ የሰጡትን ዮሐንስን፣ የቅባት መነኮሳትን በሩ ሜዳ ጉባዔን ተከትሎ ምላስ ቆርጠው፣ የወሎ ሙስሊሞችን የጨፈጨፉትን ዮሐንስን ... ምኒልክ ቂም ሳይይዙ ታላቋን ሀገር ኢትዮጵያን ተመልከተው በፍጥነት መንቀሳቀስና መደገፍ ሲገባቸው 'የቀንድ አውጣ ጉዞ'



t.me/OLDBOOKSPDF

ማድረጋቸው ቢያስወቅሳቸውም - 'የቁርጠኝነታቸውን ልክ' ገመትነው እንጂ ማረጋገጫ የለንም።

ዐፄ ዮሐንስ ጣሊያንን ኤርትራ ውስጥ ትተው፣ ወደ ቀዳሚው መነሻቸው ትግራይ እየገሠገሠ እያለ ወደ ጎንደር ምን አስገሰገሳቸው? ሲባል - የሚነሱ ተረት ተረቶች አሉ። እውነታው ምን እንደሚመስል ከአሜሪካዊው ሀሮልድ ማርከስ ገፅ 85 እናንብብ፡-

> *In November 1887 General Alessandro Asinari di San Marzano, commander of the special corps, began to fortify the small Italian colony: he built roads and bridges to ensure mobility and communication and constructed a railway from Mitswa to Sahati... San Marzano fortified Sahati, Mitswa, Hargigo, and Hitmulo, hoping that the emperor would attack and destroy his army against the colony's new defenses.*

ከላይ እንደምንመለከተው ጣሊያኖች ከ1887 ጀምሮ በኤርትራ ውስጥ መንገድ ምሽግ የመገናኛ መንገዶችን ዘርግተዋል። ሰሀቲ ምፅዋ ሀርጊጎ እና ሂትሙሎ ላይ ከአፄው የሚደርስባቸውን ጥቃት ለመከላከል ምሽግ ሲሰሩ የተወሰደ እርምጃ አልነበረም። ዋናው ጉዳያችን ገፅ 86 ላይ የተገለፀው ሀቅ ነው። በምክንያት ረዘም ያሉ መልእክቶቹን በቀጥታ ወስደናል። ይኸውም፡-

> *Whatever the emperor hoped to accomplish, his army was too big for a siege. His supplies quickly ran out, and he was forced to order retreat in early April, by which time his hungry men were ill with dysentery and his draft animals were dying from rinderpest.. He had weakened his army and lost considerable face apparently for nothing, and while he was preoccupied at Sahati, the Mahadists had invaded Gojam and Begemdir.*



t.me/OLDBOOKSPDF

በአፄ ዮሐንስ ጦር ከበባ ሊያደርግ በሚችልበት አቋም ላይ አልነበረም። በኤፕሪል መጀመሪያ ለማፈግፈግ ተገደዱ። በምግብ እጦት የተጎሳቆለው ሠራዊታቸው በተቅማጥ ተሰቃዩ። እንስሳቱን የከብት ህመም አጠቃቸው፣ ሰዎቻቸውንም አጡ።

እዚያው ገፅ 86 ላይ ሆን ተብሎ የተደበቀውን ታሪክ ሀሮልድ ማርከስ በሚከተለው መልክ አትርቷል:- *"After Menelik's army had secured Gojam and Begemdir, the emperor ordered the Shewan to return home via Welo, where the two men would meet"* ምኒልክ ጎጃምና ቤጌምድርን ከመሀዲስቶች ካዳኑ በኋላ፣ አፄ ዮሐንስ ሸዋዎች እንዲመለሱ እና በወሎ በኩል አግኝተዋቸው እንዲያልፉ አደረጉ።" (አፄ ዮሐንስ ይህንን ያደረጉት ለሥልጣናቸው በመሥጋትና በቀላሉ መሀዲስቶችን እንደሚያሸንፉ ገምተው ሊሆን ይችላል።

ሀሮልድ ማርከስ በመቀጠል:- "ወዲያውኑ የአፄ ዮሐንስ ልጅ አርአያሥላሴ በመሞቱና የእንስሳት ህመም በመጠናከሩ ሹመታቸውን የመተው ፍላጎት አሳደሩ። ወዲያው መሀዲስቶች ጎጃምን መውረራቸውን ሲሰሙ በቀላሉ አሸንፌ ክብርና ዝናዬን አስጠብቃለሁ የሚል እምነት አሳደሩ።" ገፅ 87 ቀኝ "እጃቸውንና ደረታቸውን ተመቱ።

መሀዲስቶች መተማ ላይ ዮሐንስን ገድለው፣ አንገታቸውን በመሰየፍ፣ የተቆረጠ ጭንቅላታቸውን በግመል ጀርባ ላይ በሳንጃ ሰክተው አዞሩት። እዚህ ሥፍራ የሚነሱ መጣቶች እርባና የላቸውም። አንድ ሀገር የተያዘባትን ቦታ የምታስመልሰው የሌላ የማይመለከተውን ጎረቤት ሀገር ወግታ ሳይሆን ቢቻል በሰላማዊ መንገድ አማራጭ ከጠፋ ደግሞ በኃይል ነው። ምፅዋንና ግዛቶችን በድርድር ለማስመለስ ሱዳንን መውጋት ምንም አመክንዮ የማይረታው ቂልነት ነው። ከዚሁ ጋር 'አፄ ዮሐንስ መተማ ባይሰዉ ኖሮ ነፃነትህን ታጣ ነበር' የሚል የተላሎች መከራከሪያ አለ።

በመጀመሪያ ደረጃ:- አፄ ዮሐንስ መሀዲስቶችን ለጠብ ባይጋብዙ ኖሮ ወደ መተማ ባልመጡ ነበር። ሲቀጥል:- አፄ ዮሐንስ መቼ አሸነፉና ነው መተማን የታደጉት፣ መሀዲስቶች ለብቀላ መጡ፣ ዮሐንስን ገድለው የበቀል ጥማታቸውን አረኩ፣ በድሪ ግዳያቸውን ጭንቅላት ይዘው 'ሆ' እያሉ በጭፈራ ተመለሱ። የመጡት ለብቀ ባይሆን ኖሮ አሸንፈው መተማን ተቆጣጥረው የአፄ ዮሐንስ ጦር ሸሽቶና ተበትኖ እያ ምን የሚያስወጣ ጉዳይ አጋጠማቸው?



t.me/OLDBOOKSPDF

-ቶች፥ ጣሊያን ከፊል የኤርትራን ከፍል ይዟል። በምኒልክ ታሪካዊ ስህተት 20 ችን የያዘ የውጫሌ ውል (1889) ግሚሱን የኤርትራን ከፍል ብቻ ይዞ ዛል ምኒልክ የተፈራረሙትና በራስ መኮንን ወልደሚካኤል ሮም ውስጥ ነት ማጣት ለጣሊያን የተመረቀላትን "ተጨማሪ ስምምነት" / Additional ention በመጠቀም ጣሊያን መረብ ድረስ ገሰገሰች። አፄ ምኒልክ አመፂ ችን አስተካክለው ለማይቀረው ጦርነት መላ እያበጁ መላውን ኢትዮጵያዊ ሰብ፥ የሀይማኖት፥ የፆታ እና ሌሎች አጥሮች ሳይገድቡት አስተባብረው ወደ ው የአድዋ ድል በግርማ ሞገሥ ተንቀሳቀሱ።

ው ጣሊያኖች እና የትግራዩ መንገሻ ዮሐንስ ከራስ አሉላ እንግዳ (አባ ነጋ) ጋር ልክን ለመውጋት በ1890ዎቹ መጀመሪያ "የመረብ ስምምነት" / Mereb ntion ፈርመዋል። አብረውኝ ይሰለፉ ይሆን ወይ? የምኒልክ ጥያቄ ነበር። ፡ ገገርዎች በክህደት የጀመሩትን ጉዞ በመቃመን ሲያካከሱ - ወደ ሸዋ መጡ። ማርክስ ገፅ 95፡-

> *መንገሻ ከምኒልክ ጋር ሰላም ለመፍጠር ወሰኑ። ጁን 2 ቀን 1894 ምኒልክ በቤተ መንግሥታቸው በተሠራው አዲስ የእንግዳ መቀበያ አዳራሻቸው ትልቅ ዘውድ ደፍተው ጠበቋቸው። መንገሻና ሶስት የጦር አዛገች ራስ አሉላን ጨምሮ ከመንገሻ ጋር ነበሩ። ሁሉም ለምኒልክ ማደራቸውን ለማሳየት በትከሻቸው ድንጋይ ተሸክመው ይቅርታ እንዲደረግላቸው ጠየቁ። enelik simply declared them pardoned, this bringing back Tigray into the empire.*

ለመንገሻ፥ ለአሉላና ለሌሎቹ አዛገች ምንም ደጅ ሳያስጡ ይቅርታ ው ይህም ትግራይን መልሶ የኢትዮጵያ አካል አደረጋት። (ኢትዮጵያዊነት ጥንካሬ ሲሆን እንዲህ ያምራል።) ትንሽ ቆይቶ መንገሻና አሉላ የጣሊያንን ርትራ ወንድሞቻቸው ተረድተው መረብን በመሻገር ሰንዓፌ እና ከዓቲት 5) ተዋግተው ቃላቸውን አደሱ። ጣሊያኖች የሰንዓፌ እና ከአቲትን ግጭት አዲግራትን አልፈው፣ መቀሌን ተሻግረው፣ ወዲህ ትግራይ ደቡባዊ ጫፍ ድረስ የጦሩን መዳከም ተመልከተው ያዙ። (መላውን ትግራይ ሲባል ረጃ ተቆጣጥረው) ጫፍ ድረስ መጡ።



t.me/OLDBOOKSPDF

በመሟሊያን ውል ለማፍረስ ጣሊያኖች በቂ ምክንያት አገኙ። ልብ ሊባል የሚገባው ጣሊያን ከያዘቻቸው የኤርትራና የትግራይ አካባቢዎች 10,000 ትግርኛ ተናጋሪ 'አስከሪስ' በጦሯ ውስጥ አካትታ ነው ወደ ጠቅላላ ጦርነቱ የገባችው። ሳውራሪ ገበየሁ አምባላጌ ላይ ጣሊያኖችን ደመሰሱ። እቴጌ ጣይቱ መቀሌ ላይ ጣሊያንን ጦር ከብበው በብልሀት ወደ አድዋ ተከተሉት። አድዋ ላይ 1896 ታሪክ ሠራ። 20,000 ወገን ተሰውቶ፤ በሺህዎች ቆስሎ ስንት የጨረሰው የኢትዮጵያ ሰራዊት - አፄ ዮሐንስ ጣሊያን ገና ሳይደረጅ 80,000 ዘመናዊ አደረጃጀት ይዞ ጦር ያህል ያልተከሩት ጦር ምሽግ ቆፍሮና የሰው ኃይል አደራጅቶ መግጠም ከፍተኛ ጋ ያስከፍል ነበር።

አፄ ምኒልክ በተዳከመ የሰው ኃይል ጦርነቱን ቢቀጥሉ ከኬንያ ተነስታ ቦረናን ከፊል የተቆጣጠረቺው ብሪታንያ መዳረሻዋ የት ድረስ ይዘልቅ ነበር? ሱዳንና ትዮጵያ ድንበር ላይ ያሉ ወገኖቻችን በተመሣሣይ የብሪታንያ እንቅስቃሴ ለሁለት ከፈላቸው ስለሚታይ ብሪታንያ የት ድረስ ትገሰግስ ነበር? ጂቡቲን ይዛ የነበረቺው ረንሳይስ? አፄ ምኒልክ ከፊት ያሉቸውን የኤርትራን ግዛትና የመላውን ኢትዮጵያን ር ከጣሊያን ጋር ተባብሮ ይወጋ የነበረው "ትግርኛ ተናጋሪ ጦር አስካሪስ" - ከኋላ ያጡት ይችሉ የነበረው ሀገር ራሮት - (በበቂ ስጋት ላይ በተመሠረተ ትንተና ማዘን) የምኒልክ እርምጃ ተገቢ ነበር ብለን እንወስዳለን።

ተጨማሪ ምኒልክ የወሰዱትን እርምጃ ትክክለኝነት በ1906 ብሪታንያ ፈረንሳይ እና ሊያን ኢትዮጵያን ለመቀራመት ሎንዶን ውስጥ የተፈራረሙት "የሦስትዮሽ ነምነት" / Tripartite Treaty ዛሬ ህዝባችን በተለያዩ ሀገሮች ከመኪተት ታደጉ ማረጋገጥ እንችላለን። በተጨማሪ የአፄ ምኒልክን ሚና በአድዋ ድል ዙሪ ; ለመዘንጋት የመሞከር ጉንጭ አልፋ ሙግት በማብራሪያ ለማሳየት ከመሞከ ቅ በአጭር አገላለፅ:- አፄ ምኒልክ ባከተት ጥሪ መላውን ኢትዮጵያዊ ባያስተባ በምንም ተአምር ድሉ አይታሰብም ነበር። ማን ነበር መላውን የኢትዮጵያ ህ ቅቱ ሊያሰባስብ የሚችለው? ስንል ምላሹ - ምኒልክ ብቻ ይሆናል።

ቃለል የአድዋ ድል የመላው የኢትዮጵያውያን ነው፤ የድሉ መሪ ደግሞ ኒልክ ነበሩ። ከህደት ሀገር ይበድል እንደሁ እንጂ አያሳድግም።



t.me/OLDBOOKSPDF

በኋላ አፄ ምኒልክ ወደፊት መግፋት የሚያስከትለውን ዞሪያ መለስ አደጋ
• ጣሊያንን ኤርትራ ውስጥ እንዳለች ተዋት። ከድባቡ በተጨማሪ የአድዋ ድል
ተመገገበ፡- በዚያው ዓመት የአዲስ አበባን ስምምነት፣ የኢ.ምባሲ መከፈት እና
ዐስጥ ቀውስ መፈጠር በሁለቱም በኩል ታሳቢ ሊደረግ ይችላሉ። ድሉን
• ኤርትራ የጣሊያን ቅኝ ግዛት ሆና ከ1890 - 1941 ቆየች። ይሁኝ
ኛው የዓለም ጦርነት ጣሊያን - ጀርመን ከምትመራው የ'አክሲስ ኃይሎች'
ጣቀሏ ምክንያት በቃልኪዳኑ ሀገሮች ምድብ መሪ የነበረችው ብሪታንያ
፣ አቅድ አካል በነበረው - 'የጠላትን ጦር በያዘው ቅኝ ግዛት የመፋለም አቅድ
፡- ጀነራል ፐላት ኤርትራ ውስጥ የሚገኘውን የጣልያን ጦር ደመሰሰ።

ተከትሎ ብሪታንያ ኤርትራን በመያዝ እና ዘግይቶ ከተመድ ምሥረታ በኋላ
ላት የሞግዚት አስተዳደር (Mandate Rule) አማካይነት በድምሩ ለአሥር
ተቆጣጠረች። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማብቂያ በኋላ የተሸናፊ
ሀገሮች እጣ ፈንታ ሲወሰን የጣሊያን ቅኝ ግዛቶች የነበሩት ሊቢያ እና
የአሰራር ሂደቱን ተከትሎ ነፃ እንዲወጡ ሲወሰን፤ በኤርትራ ጉዳይ ላይ ግን
ች ኃያላን መንግሥታት" የጋራ ስምምነት ላይ መድረስ አልቻሉም።
ቸው ደግሞ የየሀገራቱ የግል ጥቅም ነበር።

ከአፄ ኃይለሥላሴ ጋር የተጀመረውን መልካም ግንኙነት ተንተርሳ
ከኢትዮጵያ ጋር እንድትቀላቀል ትፈልጋለች። ይህ ከተሳካ በወቅቱ
• ቴክኖሎጂ' ስላልዳበረ ጣሊያን ኤርትራ ውስጥ የተከለቺውን የመገናኛ
ጣቢያ "ሬዲዮ ማሪና" በኋላ "ቃኘው ጣቢያ" ጨምሮ የኤርትራን
ባዊ 'አቅጣጫ በመጠቀም መሀከለኛው ምስራቅ እና የሜዲትራንያን
ቅይ ባህር አካባቢዎች መቆጣጠር ዋነኛ አቅዷ ነው።

ነሬት (ሩሲያ) ደግሞ፡- ኤርትራ እንድትገነጠልና የራሷን ተፅዕኖ በማሣደር
ር ተመሣሣይ የሆነ ፍላጎቷን በቀጣናው ላይ የመጫን ፍላጎት አላት።

ሩናዋ፡- ኤርትራ ለሁለት እንድትከፈል (Dismemberment) - በዚህም
ሬብኛ ተናጋሪ የኤርትራ ህዝብ በመስተጋብር እና ስነልቡና ለሱዳን
በሱዳን ውስጥ እንዲካተት፤ ከፍተኛው የ'ደጋው' ክፍል በስነልቦና
በቋንቋ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር አንድ ስለሆነ ወደ ኢትዮጵያ እንዲቀላቀል



t.me/OLDBOOKSPDF

ሀሳብ አቀረበች። ምክንያቷ ደግሞ በግርግር ከፊል ሱዳንን ወደ ራሷ ግዛት ለማጠቃለል ነበር።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በነዚህ የማይቀራረቡ ፍላጎቶች ዙሪያ ውሳኔ ለመሥጠት ስለተቸገረ የኤርትራን ጉዳይ አጥንቶ መፍትሔ የሚያስቀምጥ አንድ የልዑካን ቡድን አቋቋመ። የልዑካን ቡድኑ በቦሊቪያው ተወላጅ ኤድዋርዶ ሄንዞ ማቲየንዘ የሚመራና አምስት ሀገራትን ያቀፈ ሆኖ ተቋቋመ። ሀገሮቹ፡- ኖርዌይ ጓቲማላ ፓኪስታን በርማ እና ደቡብ አፍሪካ ነበሩ። የጥናቱ ውጤት ሲጠቃለል የባለዳዛው ዓለም ጦርነት እየጦዘ በ1945 ተጀምሮ ሩሲያ ከአራት ዓመት በኋላ (1949) የአሜሪካ አይነት 'አቶሚክ ቦምብ' ማምረቷ እና የነበረው ድባብ በአጥኚ ቡድኑ ሪፖርት ውስጥም ተፃራሪ ፍላጎት ማንፀባረቁ አልቀረም።

ኖርዌይ፡- የአሜሪካ ፍላጎትና የዘውዳዊ ሥርአት ተከታይነቷ ተጨምሮ - 'የኤርትራ ህዝብ ፍላጎት ከኢትዮጵያ መቀላቀል ስለሆነ - የኢትዮጵያና ኤርትራ ውህደት መካሄድ አለበት' የሚል የውሳኔ ሀሳብ አቀረበች። (የአሜሪካ ፍላጎት ነበር።)

ፓኪስታንና ጓቲማላ፡- ከተለያዩ መነሻዎች ኤርትራ ነፃ ሀገር ሆና መመሥረት ይኖርባታል' የሚል ምክረ ሀሳብ ሰነዘሩ። (የሩሲያ መሻት፣ የሀገሮቹ ርዕዮተ ዓለም የወለደው ሀሳብ)

በርማና ደቡብ አፍሪካ፡- የኤርትራን ነባራዊ ሁኔታ በማገናዘብ ገለልተኛ በሆነ አቋም 'ኢትዮጵያና ኤርትራ በፌዴሬሺን ቢተሳሰሩ ይሻላል' የሚል አቋማቸውን አንፀባረቁ። በወቅቱ የኤርትራ ህዝቡ ፍላጎት ከግማሽ በላይ ወደ ኢትዮጵያ መቀላቀል ሆኖ አቋሙን የሚያራምደው - "የአንድነት ፓርቲ"፣ "ሊበራል ፕሮግረሲቭ ፓርቲ" - የብሪታንያ ሞግዚት አስተዳደር እንዲመሰስ፤ "ፕሮ ኢጣልያ" - ስሙ እንደሚያመለክተው ዳግም ጣሊያን እንድትተከል እና "ራቢጣ አል ኢስላሚያ" - ኤርትራ ተገንጥላ ራሷን የቻለች ሙስሊም ሀገር እንድትሆን የሚታገሉ ነበሩ። (አብዛኞቹ ከሀገር ይልቅ የግል ጥቅማቸውን ያስቀደሙ ነበሩ።)

ሁኔታውን ያጠናው የተመድ የፀጥታው ምክር ቤት በውሳኔ ቁጥር 390 ንዑስ አንቀፅ 5 መሠረት በ1952፡- ኢትዮጵያና ኤርትራ በፌዴሬሺን እንዲተሳሰሩ ወሰነ። (አንዳንድ ወገኖች ውሳኔው "ኮንፌዴሬሺን" እንደሆነ አድርገው ይቆጥራሉ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ኮንፌዴሬሺን ከሀገራት አወቃቀር አንፃር - ራሳቸውን የቻሉ ነፃ መንግሥታት የሚመሠርቱት ጥምረት ሆኖ በቅርብጊዜያችን ታሪክ በዋናነት ለወታደራዊ እና ምጣኔ ሀብታዊ ትብብር የሚመሠረት ነው። ለምሳሌ፡- አፍሪካ ህብረት፣ ተመድ፣ ኢጋድ፣ የሰሜን አትላንቲክ የቃልኪዳን ድርጅት (NATO) እና የመሣሠሉትን መጥቀስ ይቻላል።

ከዚህ አኳያ ጥምረቱ 'ፌዴሬሺን' መሆኑን መረዳት ይቻላል። በአጭር አገላለፅ ኤርትራ ውስጣዊ ነፃነት ያላት የኢትዮጵያ አካል ሆና የራሷ ሀገመንግሥት፣ ባንዲራ እና ፕሬዚደንት እንዲኖራት ሆኖ ትምህርት በአረብኛ እና ትግርኛ እንዲሰጥ ተወሰነ። የውሳኔው ሌላ ገፅታ ሲታይ የሚከተሉትን መሠረታዊ ዘርፎች በኢትዮጵያ መንግሥት ሥር ብቻ የሚተዳደሩ (Exclusive Rights of the Ethiopian State) እንዲሆኑ ወሳኝ ድንጋጌዎች አቅፏል፡-

1. ወደቦችን (Ports) ሙሉ በሙሉ 2. የውጭ ጉዳዮች 3. የመከላከያ ሠራዊት 4. የወረቀት ገንዘብም ሆነ ሳንቲም ማተም እና 5. የውጪ ንግድ እና መሠል ነለማቀፋዊ ጉዳዮች ኤርትራ የማይመለከታት ሆኖ በኢትዮጵያ ሥር ብቻ እንዲውሉ ተወሰነ። ውሳኔው ኤርትራን የኢትዮጵያ አካል እንጂ ሉዓላዊ ሀገር አያደርጋትም። ሉዓላዊነት፡- ዋነኛ መገለጫዎቹ የዓለማቀፍ ስምምነትን መፈራረም፣ በሌሎች ሀገሮች ንደ ሀገር እውቅና ማግኘት፣ ከውጪ ቀጥተኛ ተፅዕኖ ነፃ መሆን፣ በዓለማቀፍ ርጅቶች መሣተፍ እና የመሣሠሉትን የሚያካትት ሲሆን ለኤርትራ ሙብቶቹ ሙሉ ሙሉ በተመድ ያልተሰጡ በመሆኑ ደረጃዋን ማወቅ ያስችላል።) ቀጥሎ እንደምን ሀ ውሳኔ ተሽሮ የኢትዮጵያና ኤርትራና ውህደት (በምን አኳኋን እንደተፈፀመ) ያፀባራ ሙግት አለ። በእኛ እምነት አፄ ኃይለሥላሴ እና አሜሪካ ባደረጉት ሥጢራዊ ስምምነት ይመስለናል። (ተጨማሪ ጥናት ይጠይቃል።)

952 - 1991 ፌዴሬሺኑን ተከትሎ ከኢትዮጵያ ጋር በውህደት የቆየቺው ኤርትራ ሳያዩ አስገንጣዮች እና በተገንጣዮች" ከእናት ሀገሯ ተለየች። ከረጅም በመንጃ ፍልሚያና አሻጥር በኋላ ወያኔ ህወሓት ኢትዮጵያን ስትቆጣጠር ሣሣይ ጊዜ ሻዕቢያ ኤርትራን ተቆጣጥሯል። ይሁንና ኤርትራ በዓለም ታሪክ ት በማይታወቅ መልኩ - ቢያንስ ቢያንስ፡- 'መገንጠል ወይስ አንድነት?' የሚል ጭ ሊቀርብላት ሲገባ፡- "ነፃነት ወይስ ባርነት?" የሚል ምርጫ ለህዝቧ ቀርቦ ጵያ ውስጥ ጭምር ለኤርትራውያን ድምፅ እንዲሰጡ ሲደረግ ...



t.me/OLDBOOKSPDF

ኢትዮጵያ ኤርትራ እንድም ወደነበረው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ውሳኔ እንድትመለስ መጠየቅ፤ ሁለትም ወደብ ላይ መደራደር ሲገባ - በተቃራኒው መርቃ መራርቃ ሰጥታ፤ ከዓለም ሀገራት ወፍ ሳይቀድማት ዕውቅና ሰጠች። "የአብዮታዊ ዴሞክራሲ. የሰላም መስመር" በመለስ ዜናዊ የተገፈ. ገፅ 14:-አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚከተለው መንገድ በኤርትራ ሪፈረንደም እንዲካሄድና የኤርትራ ህዝብ ነፃነት ተቀብሎ የመልካም ጉርብትና ግንኙነት መፍጠር ነበር። "ከአገር በስተጀርባ" ገፅ 79 የሚከተለውን አስፍሯል። ከመጀመሪያው ጀምሮ ወያኔ ህወሓት ዋነኛ ፍላጎቷ የትግራይ ሪፐብሊክን መገንባት ሲሆን፤ አቋሟን ሳትወድ ያስቀየራት ሻዕቢያ ነው።"

በዚህም ሳትወሰን ቡና ማታበቅለው ኤርትራ በዓለም ታዋቂ ቡና ላኪ፤ የቀንድ ከብት ላኪ መሆኗ ያስቆጫቸው የትግራይ ልጆች - "እምቢኝ" ማለታቸውን ተከትሎ በመለስና ደደቢቶች ሴራ 80,000 ወጣት ኢትዮጵያዊ ለባድመ ዋጋ ከፈለ። መለስ ባድመ ያ ሁሉ መስዋዕትነት ተከፍሎባት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አስወስኖ በፊርማው አፅድቆ 'ለኤርትራውያን እንካችሁ' ማለቱን ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዓብይ አህመድ (2018) ፓርላማ ላይ ሲያረዱን - ያ ሁሉ የፈሰሰ የወገን ደም ለምን ይሆን? ብለን መጠየቃችን ከተገቢ በላይ ነው።

ታሪካዊ ሂደቱ ምንም ይሁን ምን፤ ኤርትራ ዛሬ ሉዓላዊ ሀገር ትሁን አትሁን ... ሌላ ነገር ሆኖ፤ 100ሚሊየን የሚሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ ዓለም ያስቀመጠለት የወደብ መብት አለው። አጠቃቀሙን ፍትሀዊ በማድረግም 'ሁለቱን ሀገሮች' በሚጠቅም አግባብ ሊፈፀም ይገባል። አንድ ቀን ብልህ የኤርትራና የኢትዮጵያ መሪዎችና ልጆች በሚፈጥሩት መቀራረብ - በእርታ ልርቃ ስሜት - ያ እሳት እውን ይሆናል። ጥርኘ ብርኘ እያለ በ2018 የተጀመረው መልካም ግንኙነት ተጠናክሮ ይቀጥል ይሆን? ጊዜና ሁኔታ መልስ የሚሰጡን ይሆናል።



t.me/OLDBOOKSPDF

## ሕገ መንግሥት/ 'ሕገ አራዊት':-

በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት ተገቢነት ዙሪያ

በፖለቲካ ታሪካችን ዙሪያ የሚነሣው ውዝግብ እጅግ ዘርፈ ብዙ መልኮች ያሉት ሲሆን ከወቅታዊ ሁኔታዎች አንፃር በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ዙሪያ የሚነሡ ነጥቦች ሰፊውን ቁጥር ይይዛሉ። ሕገ መንግሥት በአጭር አገላለፅ:- የአንድ ሀገር የመንግሥት ስያሜ፣ አወቃቀር፣መርሆዎች፣ የዜጎች መብቶች፣ ግዴታዎች፣ የሥልጣን ገደቦች እና መሠረታዊ የህግ አቅጣጫዎች የሚቀመጡበት (Power Map) በዚህም መሠረት ሀገር የምትመራበት ሰነድ ነው። እንደ አዘጋጁ እምነት ሲያሜው "ህገ ሀገር" ቢባል ይመረጣል። በሀገራችን የታዩ የ1931፣ 1935፣ 1987 እና 1995 ህገ መንግሥቶች የህዝብ ይሁንታ ያልነበራቸው ስለነበሩ ግን ህገ መንግሥት መባላቸው ላይ ተቃውሞ የለንም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በቀመናው ልክ የሚመጥነው መንግሥት ሲያገኝ ሰነዱ "ሕገ ሀገር" ይሆናል። ሀገር በውስጡ:- 1) ህዝብ፣ 2) የየብስ የአየርና ከታደለ የባህር ክልል፣ 3) መንግሥት፣ 4) ሉዓላዊነት እና 5) ሰፋ ባለ ዕንስ ሀሳብ - ከሌሎች ሀገሮች የምጣኔ ሀብትና መሠል ጥገኝነት መላቀቅ መቻልንም ያካትታል። በህዝብ ስምምነት የሚፀድቅ ህገ መንግሥት የሁሉም የወል ይሆንና የፀብ ሳይሆን የተሻለ የፍቅር ምንጭ ሲሆን በርግጥም "ህገ ሀገር" ይሆናል።

ህገ መንግሥት ከባህርዩ አንፃር በተለያዩ አመዳደቦች ይከፈላል። ከእነዚህም መሀከል:-

1. የተፃፈ ሕገ መንግሥት እና ያልተጻፈ ሕገ መንግሥት

ሀ) የተፃፈ ህገ መንግሥት:- ከመግቢያ ጀምሮ እስከ የትርጉም ህጋዊነት በአግባቡ የተሰደሩ ህጎችና መርሆዎችን አካትቶ በአንድ ሰነድ የተካተተ (Structured and Codified) ነው። ዘመናዊ ህገ መንግሥት ለመጀመሪያ ጊዜ በሀገረ አሜሪካ በ1781 ነፋ ሆኗል። በዘመናዊ ልምዱ ላይ በመመሥረት ዛሬ አብዛኞቹ የዓለም ሀገሮች ተፃፈ ህገ መንግሥት አላቸው።



t.me/OLDBOOKSPDF

ለ) ያልተፃፈ ህገ መንግሥት:- ይህ አይነት ህገ መንግሥት በተለያዩ ጊዜያት የወጡ ህጎች፣ አሠራሮች፣ ልማዶች፣ ስምምነት ላይ የተደረሰባቸውን ሰነዶች የሚይዝ በአንድ ጥራዝ ያልተካተተ (Unstructured and Uncodified) ነው። ያልተፃፈ ህገ መንግሥት ያላቸው ሀገሮች ብሪታንያ እስራኤል ኒውዚላንድ ኦማን ቡታን እና ሳዑዲ አረቢያ ናቸው።

2. ተግባራዊ ህገ መንግሥት እና የይስሙላ ህገ መንግሥት

ህገ መንግሥት ሥራ ላይ ሲውል ከሚኖረው ፋይዳ አንፃር በሁለት ተከፍሎ ይመደባል።

ሀ) ተግባራዊ ህገ መንግሥት:- ሰነድ ላይ የሰፈረው የዜጎች መብት ሳይሸራረፍ የሚከበር፣ የመንግሥት ሥልጣን አካላትና መዋቅሩ በዜጎች ላይ እንዳሻው ሳይፈነጩ የህግ ገደብ ሲጣልበት፣ የመንግሥት አሠራር መርህን ተከትሎ የሚፈፀም ከሆነ አውናዊ (Effective) ነው።

ለ) የይስሙላ ህገ መንግሥት:- ህገ መንግሥቱ ከወረቀት ያልዘለለ እና መንግሥት በዘፈቀደ እንዳሻው ፈላጭ ቆራጭ ከሆነ ህገ መንግሥቱ ለላንቲካ የቆመ (Nominal) ይሆናል።

3. የሚላመድ ህገ መንግሥት እና ግትር ህገ መንግሥት

ሀ) የሚላመድ (ተለማጭ) ህገ መንግሥት:- በየጊዜው ከሚያጋጥሙ ሁኔታዎች ጋር ተያይዞ በርካታ ውጣ ውረዶች ሳያስፈልጉ በቀላሉ በአንድ ሸንጎ አነስተኛ አብላጫ ድምፅ (Simple Majority) 50% + 1 ወይም በተሻለ አብላጫ ድምፅ (Plural Majority) 2/3ኛ ወይም ከዚያ በላይ የህገ መንግሥቱ ክፍሎች የሚሻሻሉበት ነው።

ለ) ግትር ህገ መንግሥት:- ከህገ መንግሥቱ አንዱን ንዑስ አንቀፅ ጭምር ለማሻሻል (ለምሳሌ የኢፌዴሪ ህገ መንግሥት:- ከልሎች፣ የፌዴሬሽን ምክር ቤት፣ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና ሌሎች አካላት ተሳትፈውበት...) በርካታ ውጣ ውረዶችን የሚጠይቅ ነው። በዚህም መሠረት የኢፌዴሪ ህገ መንግሥት ከ1995 - 2019 አንድ አንቀፅ ይቅርና ንዑስ አንቀፅ አልተሻሻለበትም። ይሁንና የህጉ መሻሻል ወይም አለመሻሻል የዴሞክራሲያዊነት አሊያም ኢዴሞክራሲያዊነት መገለጫ ሆኖ



t.me/OLDBOOKSPDF

አይወሰድም። አሜሪካ በዚ.ሀ ረጅም ዘመን ጉዞዋ ያደረገቻው 27 ማሻሻያዎችን ብቻ ነው።

4. ሕገ መንግሥት አሀዳዊ እና ፌደራል ተብሎም ሊከፈል ይችላል።

የወያኔ ህወሓት ህገ መንግሥት ያለ ህዝብ ውክልና በህዝብ ላይ የተጫነ በበርካታ አሜከላዎች የተሞላ በመሆኑ የፕሮፌሰር መሥፍን ወልደማርያም ስያሜ "ህገ አራዊት" በሚገባ ይመጥነዋል። ለምሳሌ:- ህወሓት በአማራ ላይ ከነበራት የገነነ ጥላቻ የተነሳ አንድም የከለሉ ተወላጅ ወይም አማራ የሆነ ሰው እንዳይሳተፍ አድርጋለች። ከእነዚህም መሀከል በጣም ታዋቂዎቹን ለማሳያ ብንዘረዝር:- ታምራት ላይኔ፣ አዲሱ ለገሰ፣ በረከት ስምዖን፣ ሀላዌ ዮሴፍ፣ ተፈራ ዋልዋ፣ ዳዊት ዮሐንስ እና ከለሉን ወያኔ እስከትወገድ በከፍተኛ አመራርነት ረግጠው የያዙ ሊጠቀሱ ይችላሉ። (በብሔረሰብና በዘር ጥላቻ በተደራጀ መዋቅር ባይሆን የማለሰቦቹ የትመጣ ጉዳዮችን ባልሆነ ነበር።)

በደሉ ውስጥ ድረስ ዘልቆ የተሰማቸው ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት (መአሕድ) መሥርተው የህይወት መስዋዕትነት ከፍለዋል። የወያኔ ህገ መንግሥት (1995) ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ኢትዮጵያ ውስጥ የተለያዩ የህግ መርሆዎችን ያዘሉ ሰነዶችና ማስተዳደሪያ ዘይቤዎች ነበሩ። ከእነዚህም የገዳ ሥርአት ህግ፣ ከብረ ነገሥት፣ ፍትሀ ነገሥት፣ ሥርአተ መንግሥት፣ የተፃፉት የ1931፣ 1955፣ 1987 ህገ መንግሥቶች እና የወያኔ የሽግግር መንግሥት ቻርተር ሊጠቀሱ ይችላሉ። '1995 ህገ መንግሥት ዋነኛ ተዋናዮች ወያኔ እና አነግ እንደመሆናቸው የሚወክለው ሁለት ድርጅቶችን ፍላጎት እንጂ የኢትዮጵያን ህዝብ እውነት አይደለም። በመሆኑም ውዝግብ ዋነኛ ምንጭና ኢትዮጵያ እንዳትረጋጋ እንዱ መንስዔ ሆኗል።



t.me/OLDBOOKSPDF

## የፌደራሉ ሕገ መንግሥት (1995) መሠረታዊ ችግሮች

1. መግቢያው - የሕገ መንግሥቱ መግቢያ፡- "እኛ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች".

በማለት ይጀምራል። አገላለፁ በበርካታ ህፀፆች የታጨቀ ነው። ከትርጓሜው ስንነሳ ብሔሮች (Nation/s)፡- ይህ አገላለፅ በሀገር ደረጃ ላለ አሐድ የሚሰጥ ነው። ከአመዳደብ አንፃር በወያኔ ትርጉም፡- ብሔር እና ብሔረሰብ አንድ የሚያደርጋቸው የጋራ ባህርይ ሁለቱም በተወሰነ ቦታ የሚኖሩ፣ ተመሳሳይ ቋንቋ፣ ባህል፣ ማንነት እና መሠል ሁኔቶችን የሚጋሩ ሆኖ፤ ብሔር ከብሔረሰብ የሚለየው በአንፃራዊ መልክ በሚገለፅ የምጣኔ ሀብት ከፍተኛ ደረጃ ላይ መገኘቱ ነው። ለምሳሌ፡- በትግራይ ክልል ውስጥ ትግርኛ ተናጋሪው (ትግራዋይ) ብሔር ይሆንና ኩናማ ብሔረሰብ፣ ኢሮብ ብሔረሰብ ተብለው ይጠራሉ።

ኦሮሞ፣ በአማራ ክልል ውስጥ ብሔረሰብ ይሆንና ኦሮሚያ ውስጥ ብሔር ይሆናል። በዚህም መሠረት ገመቹ፣ አማራ ክልል ውስጥ የኦሮሞ ብሔረሰብ አባል ነው። ያው ገመቹ፣ ኦሮሚያ ውስጥ የኦሮሞ ብሔር አባል ነው። ተጨማሪ ማሳያ ለማሳየት "በደቡብ ኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል" ብሔሮች፡- ወላይታ ሲዳማ፣ ብሔረሰቦች፡- ኛንጋቶም አሪ ... መሆናቸው ነው። (ትክክለኛው አገላለፅ በነጠላ ብሔረሰብ እና በብዙ ቁጥር ሲገለፅ ብሔረሰቦች ቢሆን የተሻለ ይመስላል።) "እኛ የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች" - ሕዝብን በመከፋፈል፣ አንድነትን በማላላት እና በመነጣጠል ይጀምራል።እስቲ የዘመናዊ ህገ መንግሥት መነሻ የሆነውን የአሜሪካ በ1781 ፀድቆ እስከ ዛሬ ሥራ ላይ የዋለ ህገ መንግሥት መግቢያ ከ "The World Almanac (2010)"ገፅ 502 እንመልከት፡-

> *We the People of the United States, in order to form a more perfect Union, establish Justice, insure domestic Tranquility, provide for the common defence, promote the general welfare, and secure the Blessings of Liberty to ourselves and our Posterity, do ordain and establish this Constitution for the United States of America.*



t.me/OLDBOOKSPDF

ስጥ በገሏህ እንደተመለከተው "People" ህዝብ እንጂ አላለም። ይህ አንድነትን የሚያሳይ እንጂ አንዳንዶች ነትነትን አያመለክትም። የሰዎችን የት መጣ መጨፍለቅን ማንነት በሌላው ላይ መጫንን አይደግፍም። በአንድነት፣ ዓላማ መሥራትን ግን ያበረታታል። ለጥላቻ አይጠቀሙበት ሮቀስ አሜሪካ ውስጥ ነውር ካለመሆኑ ሌላ የተለመደ ነው። ነሳ ብሔረሰብ ሀይማኖት የቆዳ ቀለም የቁመት መጠን የተለያዩ ችግር የሚሆነው ልዩነቶቹ ፀጋ ሆነው ሳለ ለከፍፍል ዘሁ ምንጭ ገፅ 605 የዋሺንግተን ህዝብ ብዛት ሲቀመጥ:-

ስብጥሩ:- ነጭ 84.3%፣ ጥቁር 3.7%፣ እስያዊ 6.7%፣ ዊ (Native American) 1.7%፣ ሀዋያዊያን፣ የፓስፊክ ወይም ሦስት ዝርያዎች የተገኙ 0.5%፣ የሂስፓኒክ ህዝብ ርያ (any race) .8% በማለት ይከፍላቸዋል።

ን፣ ከተከፋፈልን እንወድቃለን" ለሚለው መተከል የተገዛው ሳይሆን የአሜሪካ ትልቅነት ይታየዋል።

ወረድ ብሎ:- " ... የራሳችን መልከዓ ምድር አስፋፈር አንዱ በሌላው ውስጥ ያለውን ህልውና ሽምጥጥ አድርጎ ቅስቃሴና መስተጋብር እንዳልነበረ ይደፈጥጣል። ሌላው ል ውስጥና አማራ ክልል ውስጥ አለ። ኦሮሞ አማራ እና ነ። (አይጋጭምን?) ቋጠሮውን ሊያላላ የሚሞክረው ህገ 40, እና20 የብሔረሰቦችን የውክልና ቀመር) "ኢፍትሀዊ" ሳዎች አንዳች ቦታ ያለመስጠት የሁለተኛ ዜግነት ደረጃ ን የቦረና እና ሶማሊ አብሮ መኖር ይገፋል... መላዋን መግቢያው ሲያጠቃልል:- "... እንዲወከሉን መርጠን ማካይነት..."

ደመድማል።



t.me/OLDBOOKSPDF

አንቀፅ 1፡- የመንግሥት አወቃቀር፡- "የኢትዮጵያ ፌደራላዊ? ዴሞክራሲያዊ? ሪፐብሊክ?" ጥያቄ ምልክቶቹን በምክንያት አስቀምጠናል። "ዴሞክራሲያዊ" ማብራሪያ አያስፈልገውም። 56 ብሔረሰቦችን በአንድ "ደቡብ" አቅጣጫ ቅርጫት ውስጥ የከተተ ፌዴራላዊ፤ በ"ትግራይ ክልል" ውስጥ ኩናማ ራያ ወልቃይትና ኢሮብን በትግራይ ማንነት ሥር የጨፈለቀ ፌዴራላዊ፤ በ"አፋር ክልል" የአርጎባን ማንነት፤ በ"አማራ ክልል" የኦሮሞ፣ ቅማንት፣ አገውን ማንነት፤ በ"ኦሮሚያ ክልል" 15 ሚሊዮን የሌላ ብሔር ተወላጆችን ማንነት ... "ማንነት" - የወያኔ አገላለፅ ስለሆነ ነው ገደል ከትቶ የብዙኃን አመራር የጥቂቶች መብትን - "Majority Rule/ Minority Rights" - "የጥቂቶች መብት" የማይጠበቅበት፣ "ህፃናት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ይማሩ" የሚለውን ዓለማቀፍ ህግ የጣሰ፣ ተወካይ የሌላቸው በርካታ ዜጎችን የፈጠረ ነው። በመሆኑም የይስሙላ ፌደራሊዝም የተሸከመ የከንቱ ከንቱ ህገ መንግሥት ነው።

አንቀፅ 2፡- ከዐማራ ራያና ወልቃይትን፣ ከአፋር ሰፊ ቦታ ነጥቆ፣ ስውር ካርታ አዘጋጅቶ ስምምነት ያልተደረሰበት "የደም ወሰን" ትርጉሙ ለኢትዮጵያ ህዝብ ግጭት እንዲ መንስዔ ሆኖ ታይቷል።

አንቀፅ 3፡- "የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ"

የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማን በተመለከተ የመቀየሩ ሂደት ታሪክን የመናድ አንዱ መገለጫ ነው። ቀደም ብለን ለማሳየት እንደሞከርነው መላው ዓለም ባሪያ ይፈነግል ነበር። መላው ዓለም ፊውዳላዊ ጭቆና ነበረው። ዛሬም በመላው ዓለም ካፒታሊስታዊ የረቀቀ ብዝበዛ ይካሄዳል። 100 ቢሊዮን ዶላር ሀብት ያለው አንድ ግለሰብ ባለበት ሀገር ከጎዳና ላይ የሚመገቡ ዜጎች አሉ። የዓለም 2/3ኛው ስጋ ደዌ ተጠቂዎች (Leprosy cases) ባሉባትና ቆሻሻ ላይ ከትመው የሚኖሩ ዜጎች ባሉባት ሀንድ ውስጥ መኖሪያ ቤቱ ብቻ በአንድ ቢሊዮን ዶላር የተገነባ ግለሰብ ይኖራል።

ግፎች በደሎች ግጭቶች እና የተፈፀሙ ታሪካዊ ስህተቶች በምንም መልኩ ከበደል ጋር አይያያዙም። ግፍና ባንዲራ የሚያያዙ ቢሆንማ ኖሮ (ምዕራፍ ሦስት ላይ ያየነው በደል በተፈፀመባት ሀገር) የወያኔ ህወሓት ባንዲራ ህወሓት ሲከስም ለአንድም ቀን ባልተውለበለበ ነበር። ለማንኛውም በበርካቶች ስምምነት የሚውለበለበው ባንዲራ (ሰንደቅ ዓላማ) ላይ ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች አሉ። መደቡና መደቡ ላይ የሚያርፈው



t.me/OLDBOOKSPDF

'ሀገርንና ህዝብን የሚወክል) ይሆንና አርማው ከመንግሥት
ጭ ሁኔታ ጋር ይያያዛል። ለምሳሌ፦ የአሜሪካ ሰንደቅ ዓላማ
ደቡ አስራ ሦስት ቀይና ነጭ መስመር (13 መጀመሪያ
፤) ያለው ሆኖ እነዚህንው የሚያመለክት አርማ 13 ኮከቦች
፡ህም ሲንከን ዘመን ግዛቶቹ 33 ሲሆኑ መደቡ እንዳለ ሆኖ
ኮከቦቹ ወደ 33 አደጉ። በሂደት 50 የሚሆኑ ኮከቦች
· አልተቀየረም።

ቢጫ ቀዩ ሰንደቅ ዓላማ በኢትዮጵያ ውስጥ ዘመናት
ላይ የሚያርፈው መደብ በየጊዜው ሲለዋወጥ ቆይቷል።
እንኳ፦ የአፄ ቴዎድሮስ የተለየ አርማ፣ የአፄ ዮሐንስ
ያም ሙዚየም ቀለሙ ደብዝዞ አለ) ሞዓ አንበሳ እያለ
ኒ ቀጥሎ፣ ደርግ አርማውን የሶሻሊዝም ርዕዮት ዓለም

ነባቢ ይውለበለቡ እንጂ የሀገሪቱ ባንዲራ አረንጓዴ
አኖሌ ስልጢም ሆነ ጨለንቆ (ገና የሸዋ ንጉሥ ሳሉ
፤ዩ ሆነው) ሲዘምቱ ባንዲራ ያላውለበለቡ ከመሆኑም
ገደል አካል አይደሉቼም። የባንዲራው ቀለማት
ረቡና ግልፅነት መጥፋቱ አንዱ ሌላው ችግር ነው።
ህርት መፃሕፍት ላይ የሚከተለው ሰፍሮ ይገኛል፦

የህተብ፣ የኅብረት በጥብቅ ማሰሪያ ሐረግ ነው።
ቃህን፣ ነጋሪት እየተጎሰመ፣ ሠራዊት እየተመመ
ጌል፤ ትዕምርተ መዊዕ ነው። ሰንደቅ ዓላማችን
ቸው። ምሳሊያቸውም፦

ፍሬ



t.me/OLDBOOKSPDF

*ቀዩ - መስዋዕትነት ደም እና ጀግንነት የተፈፀመበት የአባቶቻችንን የአርበኝነት ዋጋ ማዘከሪያ ነው።*

በዚህ ነጥብ ዙሪያ *ሀይማኖት አርማውን የሚያመለክት በመሆኑ ከማስወጣት በስተቀር አንዳች እንከን የለበትም። ለትውልዱ በዚህ መልክ ተብራርቶ ተገልፆለት ባንዲራውን እንዲወድ ወይም እንዲወስን እድል ነበረውን? (1991-2018) አይታሰብም። ይህ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ቀለም የሁሉም ብሔረሰቦች ሀይማኖቶች የታዎች ኢትዮጵያውያን በዓለም መድረክ ቁጥር አንድ የደመቁበትን የአድዋ ድል የሚዘክር ሰንደቅ ነው። ኢትዮጵያውያን በዚህ ሰንደቅ ጎን ለጎን ወድቀዋል። በአንድነት ተሳስረውበታል።

ይህ ሰንደቅ አርበኞች ለአምስት ዓመታት ተሰውተውለታል። ይህ ባንዲራ ኢትዮጵያ የመንግሥታቱ ህብረት (1923)፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (1945)፣ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት / የአፍሪካ ህብረት (1963- 1995)፤ የገለልተኛ ሀገሮች እንቅስቃሴ (1955)፣ ውጭ ሀገር ኮሪያ እና ኮንጎ፣ ከሶማሊያ ወራሪዎች ጋር ተዋድቀውበታል። የዓለም ዋና ፍፃሜዎችን፦ ኦሎምፒክ እና ዓለማቀፍ ውድድሮች ተሳትፈንበታል። ባንዲራውን በተመለከተ የአፋሩ ሡልጣን እንፍሬ፦ "እንኳን እኛ ግመሎቻችን የኢትዮጵያን ባንዲራ ያውቁታል" ብለው ተመከተውበታል። በደቡብ የተለያዩ ማህበረሰቦች መገለጫ ነው።

12 የአፍሪካ ሀገሮች (ማሊ፣ ሳኦቶሜ፣ ሴኔጋል፣ቡርኪናፋሶ፣ ቤኒን፣ ቶጎ፣ ካሜሩን፣ ኮንጎ ብራዛቪል፣ጊኒ፣ ጊኒ ቢሳዎ፣ ጋና እና ፕሪንሲፔ) መድመቂያ አድርገውታል። የፓን አፍሪካኒዝም፣ ኢትዮጵያኒዝም ኔግሪቲዩድ የካሪቢያን ስሜት ነው። አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ቀለማት ፓን አፍሪካን (የመላው አፍሪካ) ቀለማት በመባል ይታወቃሉ። በአንፃሩ የህወሓት ባንዲራ ከኤርትራ ወንድሞቻችን ጋር ተገዳድለንበታል። በከፍተኛ ደረጃ ተለያይተን ተላልቀንበታል የመጥፎ ግርሻ ማስታወሻችን ነው። ኮከብ በየትኛውም መለኪያና ልምድ መተሣሠሪያ አይሆንም። የአልባኒያ ሶሻሊዝም እና (የመጥፎ ምልኪ መነሻ) የሆነውን እንደ ህገ መንግሥቱ በግድ የተጫነብንን አርማ በሰንደቃችን ላይ ማየት ዘግናኝ ስሜት ይፈጥራል።

አንቀፅ 4፣ አንቀፅ 8 ... "በየሥፍራው የኢትዮጵያ ህዝቦች" የሚሉ አገላለፆች ሆነ ብለው ተደንጉረዋል። ትክክለኛው አገላለፅ አንድ ሕዝብ በርካታ ብሔረሰቦች ነው።



t.me/OLDBOOKSPDF

በተያያዘ ከአንቀፅ 8-12 የተጠቀሱት መሠረታዊ ዴሞክራሲያዊ መብቶች፣ ከአንቀፅ 14 እስከ አንቀፅ 28 ሰብአዊ መብቶች፣ ከአንቀፅ 29 - አንቀፅ 44 ዴሞክራሲያዊ መብቶች፤ በድምሩ 1/3ኛው የህገ መንግሥት ክፍል ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች (1/4ኛው የህገ መንግሥት ክፍል ስለ ሰብአዊ መብቶች ያወሳል) - ሙሉ በሙሉ መደፍጠጣቸውን በምዕራፍ 3 ተመልከተናል። በውስጡ የተቀመጠው አንቀፅ 39:- "የብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች መብት እስከመገንጠል" ሌሎች ሀገሮች ያላስቀመጡበት መሠረታዊ ምክንያት ፈፅሞ አስፈላጊ ስላልሆነ ነው። ከኢትዮጵያ ህዝብ የዘመናት ትሥሥር አንፃርም የማይመጥን ነው።

ሶቭየት ኅብረት አቻ አንቀፅ በህገ መንግሥቷ ማስቀመጧን ተከትሎ የባልቲክ ሪፐብሊክ የሆኑት ላቲቪያ፣ ሊቱኤንያ እና ኢስቶንያ በብርሀን ፍጥነት መገንጠላቸውን ሲያውጁ፤ እነ አዘርበጃን፣ ኡዝቤኪስታን፣ ካዛኪስታን ... እያሉት ወደ አሥራ አምስት "ትንንሽ" ተቀየረች። መሬት "የህዝብና የመንግሥት" ስለተደረገበት ምክንያት የወያኔ ሕገ መንግሥት ሲያብራራ ትኩረቱን ያስመሰለው "ገበሬው ተቸግሮ መሬት እንዳይሸጥ እንዳይለውጥ" ማታለያ ነው። 'የሀገራችን ገበሬ እንኳን መሬቱን ጠቦቱን ሲሸጥ ተመካክሮ ነው። በተግባር እንደ ህወሓት ገበሬና ነዋሪ እያፈናቀለ መሬቱን ያለ ተመጣጣኝ ካሳ የነጠቀ የለም።

ገበሬውም ያለማቋረጥ ካልፈለገ መሬቱን ሲሸጥ ሲለውጥ ከርሟል። ዛሬ ህገ ወጥ ተብለው ከየቦታው የሚፈናቀሉት ከገበሬው መሬት የገዙ ዜጎች ናቸው። አመራሩ ደላላ ሆኖ ያሻሻጣቸው። በውጤቱ ጥቂቶች ከበሩ፣ ብዙኃን ደም እንባ አለቀሱ። ዓላማው መሬትን መቀራመት ነበር። ህገ መንግሥቱ በስመ የቡድን መብት ዋነኛውንና ዓለም ያከበረውን የግለሰብ መብት የደፈጠጠ 'ህገ አራዊት' ነው። በሌሎች ክፍሎች እንዳየነው 56 ብሔረሰቦች በአንድ ቅርጫት የከተተ ፌደራሊዝም፣ ኩናማና ኢሮብን በትግራይ የቋጠረ፣ አርጎባና ኦሮሞን ሁለት ክልል ውስጥ የቆራረጠ ፌደራሊዝም፣ የማህበረሰቦችን መብት በክልል ከረጢት አስገብቶ (ታሪክን ከግምት ሳያስገባ) ሁለተኛ ዜጋ አድርጎ የሚረግጥ ፌደራሊዝም፤ ከፍቅር ይልቅ የፀብ ምንጭ የሆነ ህገ መንግሥት ለዘመኑ የኢትዮጵያ ህዝብ አይመጥነውም።

በነዚህና በየጊዜው በሚነሱ አከራካሪ ጉዳዮች ምክንያት ህገ መንግሥቱ ምሁራን መክረውና ዘክረው ሊያስተካክሉት የተገባ ነው። የፖለቲካ ታሪካችን በደሎች ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ የተፈፀሙ አስመስሎ ለጥላቻ ከማራገብ ይልቅ መፍትሔ



t.me/OLDBOOKSPDF

አየሰጠ ቢሄድ አብሮነትን ባጎለበተ ነበር። ለምሳሌ:- የሴቶች ተሳትፎ በፓርላማ የአሜሪካ 12.71%፣ አረቦች 4.3%፣ እስያ 13.2%፣ አውሮፓ 13.2%፣ ፓስፊክ 3.6% እና ከሰሀራ በታች የአፍሪካ ሀገሮች 9.8% ነው።

በቀጥታ ይህንን ገሌፆ (2018 -2019) እንደተተገበረው ፕሬዚደንት፣ የፍርድ ቤት ፕሬዚደንት፣ የምርጫ ቦርድ ሰብሳቢና ግማሽ ያህል ሚኒስትሮች ሴት ሾሞ ሀገርንም ዓለምንም በማስደመም ለተሻለ ለውጥ መስፈንጠር ከጥላቻ ይልቅ ትውልድ እንደ አቦ ሾማኔ ለለውጥ እንዲተጋ ያደርገዋል። ህንድና ቻይና ውስጥ ሴቶች መምረጥ የጀመሩት በ1949 መሆኑን ጠቅሶ ማለፉ ተመራጭ ይሆናል። በኢትዮጵያ ውስጥ በ1955 ፓርላማ ውስጥ የተመረጡ ሴቶች 2፣ በደርግ ጊዜ 14 እንደነበሩ (የኢትዮጵያ ፓርላማ ታሪክ ገፅ 12) ያሳያል። ቻይናና ህንድ ገና መምረጥ ሲጀምሩ ኢትዮጵያ ሴት የፓርላማ አባላት ነበሯት፣ ድንቅ ነው።

የስነምግባርና የስነዜጋ ትምህርት ይዘት ከመጀመሪያ ደረጃ እስከ ዩኒቨርሲቲ ድረስ አሰልቺ በሆኑ ድግግሞሽ ከሚሞላና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች የመምህራን 'ዓብይ ትምህርት (Area of specialization) ዕውቀት መለማመጃ' ከመሆን ወጥተው 70 እጅ ስነምግባርና የዓለምና የሀገራቸውን ታሪክ ዋና ዋና አውዶች ቢገነዘቡበት ለሀገር ሰላም፣ ለህዝብ ፍቅርና አንድነት ታላቅ እርምጃ ወደፊት ነው።

ዓለም ዴሞክራሲን በአንድ ጀምበር አልገነባችም። የተሻለ ልምድ ያላት ብሪታንያ በ1215 "ማግና ካርታ" ስምምነት:- የህዝብን መብትና ነፃነት ማክበር፣ በወገን ፊት መዳኘት እና ዜጎች ያላግባብ እንዳይታሰሩ ደነገገ። የነገሥታቱንም ሥልጣን በንጉሥ ጆን ዘመነ መንግሥት (1199-1216) ገደበ። 1628 "ፒቲሺን ኦቭ ራይትስ" - ግብር በንጉሡ ፈቃድ እንዳይሰበሰብ ከለከለ። ነፃ ምርጫና ዜጎች ሀሳባቸውንና አቤቱታቸውን በነፃነት እንዲያቀርቡ ሆነ። በ1776 የአሜሪካ "ቨርጂኒያ ቢል ኦቭ ራይትስ":- በህይወት የመኖር፣ የማይጣስና የማይገሰስ ሰብአዊ መብት፤ 'የነጭ ወንዶች እኩልነት'፣ ነፃነትና ደስታን ማጣጣም፣ የመረጃ የስብሰባ፣ መንግሥት ጭካኔ የተሞላበት ቅጣት እንዳይጥልና ዜጎች መንግሥትን መከሰስ እንዲችሉ ደነገገ።

በ1789 "ፍሬንች ዲክላሬሺን ኦቭ ዘ ራይትስ ኦቭ ሜን ኤንድ ሲቲዝን":- ነፃነት እኩልነት ወንድማማችነትን በማወጅ ለዜጎች ያልተገደበ የእኩልነት መብትን



t.me/OLDBOOKSPDF

አጎናፀፈ። 1917 የሩሲያ አብዮት የዴሞክራሲያዊና ማህበራዊ መብቶችን ይፋ አደረገ። 1945 የተመድ ድንጋጌዎች፣ 1948 የተመድ ሁሉአቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች (UN/ UDHR)፣ ዓለማቀፍ የፖለቲካና የሲቪል መብቶች ስምምነት 1964፣ ዓለማቀፍ የባህል፣ ምጣኔ ሀብታዊና ባህላዊ መብቶች ... እንዲ ከሌላኛው ነየወሰደ እያሻሻለ፣ ከራሱ ሁኔታ እያዛመደ፣ አዳዲስ ድንጋጌዎችን እየጨመረ ወደፊት ፡ራመዳል። የራስን ግለ ስብእና ለመትከል ከመሯሯጥ ይልቅ ለአንዳች ተጨባጭ ውጥ ጥረት ቢደረግ፤ ህዝብ ከምግባር ተነስቶ ክብርን እንደሚለግስ የታወቀ ነው።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ማጠቃለያ

ኢትዮጵያ ሀገራችን የእያሌ ዘመናት ድንቅ ታሪክ ማህደር ናት። ቅድመ ታሪክ አቻ የማይገኝለት ቅድምና አላት። በታሪክ ዘመንም ከዓለም ቁንጮዎች መደዳ ተሰልፋለች። ይሁንና የታሪክ ሽሚያና የፖለቲካ አውድ አኩሪ የገዘፈ ታሪኳ ተመዝግቦ እንዳይያዝ እንቅፋት ሆኗል። ታሪኳ በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ሰሜኑ የሀገራችን ክፍል እና ከሌሎች አንጓዎች ይልቅ በፖለቲካ ታሪክ ላይ ተንጠልጥሎ ቆይቷል።

ከ1970ዎቹ ጀምሮ የተፃፉ ታሪኮች ያለፈውን በጎ ጎን ሸፍነው ድክመቶችን አጉልተው በመፃፍ ተጠምደዋል። በማይጠበቅ መልኩ ከታሪክ ዓላማ አፈንግጠው ወገንን ከወገን ለማለያየት እና ለጥፋት መነሻ መሆናቸው በተጨባጭ ታይቷል። ስውር ግዙፍ እጅ ኢትዮጵያን ለማፍረስ ተግቶ እንደሚሠራ አለመጠርጠር አይቻልም። በሚያሳዝን ሁኔታ ውስብስብ ችግሮቹን መዝኖ ከታሪክና ከትውልድ እንዲሁም ከሀሊና ተወቃሽነት ለመተገን በመልካምነት ተነሳስቶ የተዛባውን ታሪክ ለማረቅ የሚደረግ ጥረት የለም ማለት ይቻላል።

ኢትዮጵያ ዕንቁ ታሪክ እያላት ተሸፍኖ ሲቀር የማይቆጭ ምሁር ሊኖር አይገባም። አንባቢ ምሁራን (Functional Illiterate) በመሆን ከሸበበን የዳተኝነት ድባብ ጠርምሰን በመውጣት ታሪካችን መፃፍ አለበት የሚል ቁርጠኝነት ከምሁራን እስከ መምህራን ያስፈልጋል። የምሁርነት ብያኔ እንደ ሮበርትስ እና ጆይ ውድ "Intellectual Virtues" እምነት ቢያንስ የሚከተሉትን ላሟሉ ትንታጎች የሚሠራ ነው። ዕውቀትን ማፍቀር፣ ፅኑ አቋም፣ ልበ ሙሉነት፣ አካዳሚያዊ ነፃነቱን የሚያስጠብቅ፣ ቀናነት፣ ለሰው ልጅ በሙሉ ቀናዒ አመለካከት የተላበሰ፣ ደግነትና በእሳት ተፈትኖ የሚያልፍ... ብያኔያቸው ቢያንስ እንጂ የበዛ አይደለም። ዕውቀት፣ ከሀሎትና ለበጎ መትጋት ያልታከሉበት ጥበብ የመከነ ነው፡፡ ለከፋት የዋለ ዕውቀት ምሁር ካሰባለ በዘመናችን ካሉ ቁንጮ አራጆች አንዱ የአይሲስ (ISIS) መሥራች አቡበከር አልባግዳዲ ሊያውም በስነመለኮት ትምህርት የሦስተኛ ዲግሪ (PhD) ባለቤት ከምሁራን ተርታ ይመደብ ነበር።



t.me/OLDBOOKSPDF

ወደ ሀገራችን ታሪክ አዘጋጅነት ስንመለስ ታሪክ በዘፈቀደ የሚፃፍ ባለመሆኑና ቀይደው የያዙት ችግሮች እንደፃዛ የሚፈቱ ባለመሆናቸው መንግሥት ልዩ ትኩረት ሰጥቶት ራሱን የቻለ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ትምህርት ክፍል የሚመራ 'የታሪክ ዝግጅት ኤጀንሲ' ሊያቋቁምለት፤ በአሠራር ሂደቱም ጣልቃ ሳይገባ ቢቻል አቅጣጫ ብቻ በመስጠት ሊያግዝ ያስፈልጋል። ይሁንና 'ኤጀንሲው' የኢትዮጵያን ታሪክ በመፃፍ ሂደት የሚያጋጥሙትን መሰናክሎች ባገናዘበ አኳኋን የስነልቡና የህግ እና ተዛማጅ የማህበራዊ ሳይንስ ምሁራን በተለያዩ ማዕዘኖች የምንጠቀምባቸው አገላለፆች ሊያሳድሩ የሚችሉትን አሉታዊ ተፅዕኖ መዝነው አዎንታዊ ፋይዳው ጎልቶ እንዲወጣ የመሠረት ድንጋይ ሊጣል ይገባል።

የታሪክ ሽሚያው ማንንም ለይቶ ጎዶሎውን እንደማይሞላላት ተገንዝበ ዓላማው ላይ አፅንዖት ቢሰጥ፤ የተለፋበት ሰነድ በአግባቡ ተቀንብቦ ከትውልድ ወደ ትውልድ ተሸጋጋሪ ይሆናል። አለበለዚያ በአንድ ወገን ፍላጎት ከተጫነ ሻጩ መልሶ ይገዛው ካልሆነ በስተቀር በሌላው ወገን ተቀባይ አያገኝም። ዓለም በጥቡብ እየናኘች በየቅፅበቱ አጀብ የሚያሰኙ ለውጦች ስታስመዘግብ እኛ በትላንት እየተናቆርን የትውልዱን ዛሬና ነገ ማጨለም አይገባንም። የተበተበን አርጌ አመለካከት፤ በትላንት ላይ የቸነከረን ጎታች ዝንባሌ እና ቢያንስ ዛሬ ላይ ከሁሉም ሙያተኞች አንዳች ተጨባጭ ፍሬ ለማየት በጉጉት የሚጠብቀውን 100ሚሊየን ህዝብ እያሰቡ ዘመኑን በዋጀ አእምሮ ልክ መለወጥ ያስፈልጋል።

በሩቅም ሆነ በቅርብ ጊዜያችን ታሪክ በተፈፀሙ ጥፋቶች ሁሉ የድርጊቱ ፈፃሚዎች ተለይተው ከመጠየቃቸው ውጪ ህዝብ አይከሰስም፤ አይወቀስም፤ በድርጊቶቹም ተዋናይ አይደለም። ለተበረከቱ በጎ አስተዋጽዖዎች ለይተን ያወደስነው ወገን እንደሌለ ሁሉ፤ ለመጥፎዎቹ ጣታችንን የምንቀስርበት ጠብታ አመክንዮ የለም። ዛሬ ላይ ቆመን ገለኛ አድሚ ብንመዝን በአፄ ኃይለሥላሴ ጊዜ በደል ፈፀሙ ያላቸውን ንጉሠ ነገሥቱን ጨምሮ 60 ሚኒስትሮችን ደርግ (1974 - 1975) ረሸናቸው። ከደርግ ውድቀት ኋላ ወያኔ ህወሓት በደርግ ዘመን ጥፋት ሠርተዋል ያላቸውን ከማሠር አልፎ ማይመለከተው ላይ ጭምር እርምጃ ወሰደ። ከፉው አለመለጠም፡ ደጉም አብሮ ወቅጧል።

2018 ጀምሮ እየተወሰዱ ባሉ እርምጃዎች ግፍ የፈፀሙ እየተጠየቁ ናቸው። ዘሁ መጠየቅ ያልቻሉትንም ህሊናቸው እያሳደዳቸው ባለመኖር መኖር የቀም ኑንነት ድንዛዜ አውድ ውስጥ ይቀጥላሉ። በ1974 ለአቅመ ፖለቲካ የደረሰ የ22



t.me/OLDBOOKSPDF

ዓመት አድሜ ግለሰብ ቢኖር ዛሬ (2019) ቢያንስ የ67 ዓመት እድሜ ባለፀጋ ነው። የጠፋ ቢኖር በድርጊቱ ይጠየቅ። ይህ ትውልድ ግን 'ላለፈው ከረምትም ሆነ በጋ' መደሉም የጥንካሬውም አካል አይደለምና - ባለበት የዕውቀት ተአምራዊ ተደማሪ የሉላዊነት ለውጥ ዘመን ውስጥ ዕውቀቱን ሰብስቦ በጥበብ ይኖርበት። እጃችሁን ከላዩ ላይ አንሡ! በሰላም ይኑር፣ ተዉት፣ ለቀቅ አድርጉት!

ከ1991 - 2018 በነበሩት ዓመታት ውስጥ፦ 'ስንኖር ብሔረሰብ፤ ስንሞትም ብሔረሰብ' ሆነን፤ ኢትዮጵያዊ ነን ማለት አሳፍሮን ባጀን። የስራ እድል ለማግኘት በእውቀት ሳይሆን በብሔረሰብ ኮታ ተሰፈርን። (ሊያውም በፌዴራል ደረጃ እና በአዲስ አበባ 35ሚሊዮን የማህበረሰብ አባላት ያቀፈውም፤ 6ሚሊዮን የማህበረሰብ አባል ያለውም እኩል እድል ተሰጥቶን/ተነፍገን። 40 የቤተሰብ አባላት ላሉት አባ ወራ እና 6 የቤተሰብ ብዛት ላሉት ሌላ አባ ወራ በነፍስ ወከፍ 1 ኪሎ ስኳር ቢሰጣቸው፤ ለባለ 40ው 1 ማንኪያ እንኳ አይደርሰውም። ባለ ስድስቱ ግን ቢያንስ ዱቄት ጨምሮ ኬክ ጋግሮ ይከፋፈልበታል። ሰርክ እንጀራው በአንድ በኩል እየወፈረ 2018 ደረስን።)

መታወቂያችን ሰው ከመሆናችን በላይ ብሔረሰብ መሆናችን ያገብረዋል። እርስበርስ ስንተዋወቅም ሆነ ንግግር ስናደርግ ኦሮሞ አማራ ትግሬ ወላይታ ነኝ በየመሀከሉ ጣል ማድረግ የየእለት ከስተት ነበር። ሀሳባችን የሚመዘነው በውስጣዊ ይዘቱና በአመክንዮ ጥልቀቱ ሳይሆን በብሔረሰብ ሆነ። ምን ቁም ነገር አስተላለፈ?' የሚል ጥያቄ ቀረና 'ቆይ የምን ብሔረሰብ አባል ነው?' ዋነኛው መመዘኛ ሆነ። የሰውነት ሚዛን ቀለለ። የሀሳብ ትልቅነት ቀነጨረ። የአመክንዮ ጉልበት ዛለ።

የምናያቸው ግዑዛን ነገሮች ሳይቀር ከሀገር ዜግነት ሰውነት ይልቅ ብሔረሰብን ያገዝፋሉ። የመኪና ሠሌዳዎች አሮ አማ ትግ ሐረ ሶማ ቤጉ ... ያስቀድማሉ። የምንገረፈው የምንታሰረው የምንሠፈረው በብሔረሰባችን ሆነ። ስብሰባ ስንሰበሰብ፦ 'አማራ እዚህ አዳራሽ፣ ኦሮሞ ወዲያኛው ክፍል፣ ደቡቦች እዚያኛው አልፍኝ ግቡ' እየተባለ ዜጎች በአቅጣጫ መጠራት ጀመሩ። መቼም 56ቱ ተራ በተራ አይጠራ ነገር! መስተጋብራችን ሁሉ በብሔረሰብ ሆነ።

በመካነ ትምህርቶች፣ በመሥሪያ ቤቶች፣ በየእንቅስቃሴዎችን ሁሉ ብሔረሰብ ገዘፈ። ድሮ ከነበደሉ ሁሉም ሥፍራ ሀገርህ ነበር። ከ1991 ወዲህ ግን በኃሳህ ምክንያት



t.me/OLDBOOKSPDF

ከተሸከርካሪ ተለይተህ ወርደህ ትደበደባለህ። ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ዐብ ከተኛ ድንገት 'ይሄም የዚያ ጎሳ አባል ነው' ተብለህ የመከራ ዶፍ ይወርድብሀል። ከተሰመረልህ ክልል ውጪ ስትኖርም ሆነ ስትጓዝ ደህንነት አይሰማህም። በመሆኑም ስንኖር እንደ ብሔረሰብ፤ ስንሞትም እንደ ብሔረሰብ እንሞታለን። ግብአተ መሬታችንም ሲፈፀም 'የት ክልል ተቀበረ?' ተብሎ ይጠየቃል። የሟች ወገኑን በቀል ሸሽተን - "በሌላው ክልል ከሆነ" ቀብርም ላይ ላንገኝ እንችላለን። ስለሆነም በብሔረሰብ ተከበበን እንቀበራለን።

'ትውልደ አማራ' ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ውስጥ ቢገደል የቁጣ ሰልፍ የሚካሄደው ጎንደር ወይም ጎጃም እንጂ አሶሳ ውስጥ አይደለም። የወላይታ ልጅ ሐዋሳ ውስጥ ቢገደል፤ ሰልፉ ወላይታ ሶዶ ይሆናል። 'ረከስን፤ ከብራችን ተነካ፤ አዋረዱን፤ ስማችን ጠፋ' ብለው መነሳት ያለባቸው አሶሳና ሐዋሳ ሊሆኑ በተገባ ነበር። የ27 ዓመቱን ዘር አሁን በየወረፋችን እያጨድን ነው። የዘራነው በቅሎ እያመከነን ቀጥሏል። ያም ሆኖ - እንደ ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር ተስፋ አለን - አንድ ቀን ልጆቻችን በቋንቋቸው ሳይሆን በህክምና ጠቢብነት፤ ዘር በመዝራት እውቀት፤ በማስተማር ብቃት፤ በንግድ ማሣለጥ፤ በገቢ አሰባሰብ ስሌት፤ በማሽከርከር ክህሎት እንደሚመዘኑ... አንድ ቀን 'መሪዎች ምን የከፋ ቢሆኑ'፤ እነርሱን ሳናይ እኛ የነበረንና ለሦስት አሥርት ዓመታት የተነጠቅነው የወላጆቻችን ፍቅር እንደሚመለስ እናምናለን። የዚያች ኢትዮጵያ ትንሣኤ አይርቅም። ግማሽ ልባችን የፍቅር ጉዞው ተጀምሮስ ቢሆን? ሲል ከፊል ናችንን ስጋት ቀስፎ ይይዘዋል። ምንም ይሁን ምን - ኢትዮጵያ የወላድ መካን ይደለቺምና - ቶሎ ተስፋ አንቆርጥም።

**ንግሥት በብሔረሰቦች መሀከል ላቻን ለመዝራት የሀገርን አንጡራ ሀብት ዘርፎ እና ፋት መርሐ ግብር ዘርግቶ ሀገራዊ ቀውስ እንደፈጠረ ሁሉ፤ የተከለውን የከፋት ገዝ ከነሰንኮፉ ለመንቀል የላቀ ሀብት መድቦ ፍቅርን ወደ ነበረበት የመመለስ ታ አለበት።**

ጨረሻም በመግቢያው ላይ እንደጠቀስነው መፅሐፉ ለመጀመሪያ ጊዜ ሊባል ችል ደረጃ በኢትዮጵያ የታሪክ አፃፃፍ ሂደት ያልተደፈሩ የታሪክ እውነታዎችን ዝር አፍረጥርጦ በማሳየት እና ለግማሽ ክፍለ ዘመን የተፈጠረውን የሀሰት ታሪክ ሳጥ ብዙ ርቀት ተጉዟል። ታሪክን እንደወረደ በማስቀመጥ ደረቅ የትምህርት



t.me/OLDBOOKSPDF

መፅሐፍ ዝግጅት አይነት አስልቺ አካሄድ ከመከተል ይልቅ የአንባቢውን ቀልብ ይዞ ለመዝለቅ የሚያስችል ያልተለመደ የአፃፃፍ ስልት ተከትሏል።

ቃቢ. መፃሕፍትን በቁጥር ለያይቶ (Notes) ወይም የግርጌ ማስታወሻዎች እያስቀመጡ ለተደራሲያን ግልፅ ያልሆኑ፤ በአመዛኙ ለታሪክ ሰዎች እና መሠል ምሁራን ብቻ ተደራሽ ከሆኑ አቀራረቦች ይልቅ ምንጮቹን በቀላሉ ፈልጎ ለማግኘት በሚያስችል አግባብ ተሰድሯል። ምንም የማያሻሙ እና ማንኛውም ሰው በቀላሉ ሊያገኛቸው ከሚችልና ተቀባይነት ባላቸው በይነመረቦች ሞልተው የፈሰሱ ምንጮች ያላቸውን ከመጥቀስ ይልቅ - በስፋት መረዳት የሚፈልግ ወገን ሁሉ እንዲያገኛቸው - አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ጭምር ተቀምጠዋል። በዋቢ መፃሕፍት ዝርዝር ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የጠቀሙንን እና የተጠቀምንባቸውን አውቅና እንሰጥ ዘንድ አካትተናል።

ወያኔም ሆነ ኦነግ ተጠቃሁ የሚል ስሜት እንዲፈጠርበት የሠሩት ከኢትዮጵያ ህዝብ ሲሶ የሆነው የኦሮሞ ማህበረሰብና - ሆን ተብሎ እንደ ጦስ ዶሮ እንዲሆን የተጫለበት የአማራ ማህበረሰብ በመሆኑ - የታሪኩን እብደት ለመፈወስ የመፅሐፉ ዝግጅት የሁለቱን ማህበረሰቦች ዳራ በጥልቀት ለመፈተሽ ሞክሯል።

ያልተለመዱ አይነት መፅሐፉ ውስጥ ያሉ ባህርያት በሙሉ በምክንያት የሆኑ ናቸው። የበርካታ የኢትዮጵያ ማህበረሰቦች ታሪክ በስፋት መካተት ሲገባው ባለመካተቱ አዘጋጁ ይቅርታ እየጠየቀ፤ በቀጣይ 'የቦረና እና የጉጂን ማህበረሰብ አስደናቂ መስተጋብር'፣ 'መፅሐፈ ነገሥት' እና 'የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ' ፈጣሪ ቢፈቅድና ብንኖር የሚያቀርብ መሆኑን በላቀ አክብሮቱና ትህትና እንገልፃለን። በፅሑፉ ውስጥ ስሜታችሁን የሚነካ አገላለፅ ቢኖር ማንንም ለመጉዳት ሆን ብሎ ታቅዶበት የተፈፀመ አይደለምና መነሻችንን መዝናችሁ ይቅርታ ታደርጉልን ዘንድ እንማፀናለን።



t.me/OLDBOOKSPDF

## መውጫ

ኢትዮጵያ በአንድ ጀንበር ያልተገነባች፤ ሕዝቧ በኢትዮጵያዊነት መንፈስ እርስ በርሱ የተሳሰረ፤ አንዱ ማኅበረሰብ ራሱን ሌላ ውስጥ የሚያገኘው፣ በማይበጠስ ረቂቅ ነፍስ እና ሥጋው የተሳሰረ ነውና ሊያፈርሱት (እናት ሀገሩን ሊያፈርሷት) የሞከሩ ሁሉ ከውርደት ጋር ፈርሰው - ኢትዮጵያ ያከበሯትን እያከበረች ቀጥላለች። ኢትዮጵያ አንድ ናት። "የእናንተ" እና "የእኛ ኢትዮጵያ" የሚል ስንኩል አመለካከት ሁለት አያደርጋትም። በአንዲት ኢትዮጵያ ውስጥ ቡራቡሬ አመለካከት መያዛችን የመረጥነውን እንድንመገብ የቀረበ ብፌ አድርገን ልንወስደው እንችላለን። አመለካከቱ ሚያገዳድል ሚያናቁር ሚከፋፍል ከሆነ ግን መርዝ ነው። ለህዝባችን መርዝ አንሁን። በፍቅር ከተጓዝን ሁሉም የእኛ ነውና የተለየ "የእኛ" - "የእኔ" ስሚት ካልገደለን በስተቀር የኢትዮጵያ ትንሣኤ ሩቅ አይሆንም። ይህ መፅሐፍ የጎጠኞችን ዛር ቀስቅሶ የሚያንዘፈዝፋቸው የቡዳ መድሀኒት - "ቆርቻ ቡዳ" ስለሆነ የዘውግ አጋንንት የሠፈረባቸው ሁሉ እንደሚረባረቡበት ሳይታለም የተፈታ ነው። በመሆኑም አበክሬ ማሳወቅ የምወደው የሁሉም ኢትዮጵያውያን ውሰታ የገነባውን የዘመናት የአባት እናቶቼን ጀግንነት፡-

የሀሳብ ቀንጨራዎች፤

የአስተሳሰብ ድዉዮች፤

የአመክንዮ ኩርማኖች፣

የውይይት ስንዝሮዎች፣

የዜግነት ጳጉሚዎች፣

የሰውነት ጎዶሎዎች፣

የእምነት ወናዎች፣



t.me/OLDBOOKSPDF

የምራል ግልቦች፣

ነባብ አርሚዎች፣

የጥላቻ አጋፋሪዎች፣

የመለያየት አስተናባሪዎች፣

የአብሮነት ፀሮች፣

የኢትዮጵያዊነት ጠላቶች

በድምሩ ጥቂት ኮልኮሌዎች...

በአንቁራሪት ቁርቁርታና በእንጭራሪት ጭርጭርታ በቀቀናዊ ማንነት እንዳይደርሱበት - እጅግ በጣም ወደ ህዋ በማራቅ ከፍ አድርጌ ሰቅዬዋለሁ። ታሪክ ደጋግሞ እንዳሳየን በስተመጨረሻ 'ፍቅር ያሸንፋል።'

መጽሐፉ መልእክቱን በጥልቀት ቃኝተውና በብሩህ አዕምሮ ተረድተው ሊማሩበት ለሚሹ ሁሉ ለታሪክ አረዳዳቸው አብርሆት ፍቱን መድህኒት እንደሚሆን ሳይታለም የተፈታ ነው። ( 'ከታሪክ የማይማሩ እንዲደግሙት ይፈረድባቸዋል') ወዳጆቼ፡- በህይወት ዘመናችን ደጋግመን 'እንቅፋት መታኝ' በማለት ስንሳሳት አድገናል። አባባሉ ከማህበረሰባችን የወረስነው ጠብደል ስህተት ነው። ለአእምሯችን መላልሰን ይህንን ውሸት ስለነገርነው ልክ እንደ ጠጣር እውነት አምነን ተቀብለነዋል። ሀቁ ግን እንቅፋቱን የመታነው እኛ ራሳችን ነንና ማለት የሚገባን፡- 'እንቅፋት መታሁ' ነበር። ልብ አድርጉ ጋሬጣው ወይም ድንጋዩ ስለማይናገር 'መታኝ' ብለን የራሳችንን ስህተት በሌላው አላከክን። ይህ ልምድ ሁልጊዜም ችግሮቻችንን ወደ ውስጥ ዐይተን ራሳችንን እንዳናርም ያደርገናል። ይልቁኑ ለጥፋታችን አብዝተን ሌላ ውጫዊ ኃይልን ተጠያቂ እናደርጋለን። (Externalizing the problem or blame shifting) ይሉታል ባሪቶኖች። ያለመለወጣችን አንዱ እንቅፋት እኛው ራሳችን የተከልነው የአስተዳደግ ሥርአት ነው።

ታሪካችንም ሲፈተሽ ለግማሽ ከፍለ ዘመን ባጠቃላይ እና ላለፈው ሩብ ክፍለ ዘመን በተለይ ለፖለቲካ ትርፍ አለቅጥ ተጣምሞ እየተነገረን ስላደግን፤ ዛሬ ዳራው ፈቅዶ እውነታው ሲነገረን ላለመቀበል ብዙ እናንገራግራለን። ከዚሁ ጋር ተያይዞ 'እንቅፋቱን



t.me/OLDBOOKSPDF

የመታቺውን ወይም የመታውን ህፃን' ማልቀስ ተከትለን ጊዜያዊ ዕንባቸውን ለማድረቅ ሲባል የተገጨውን ጋሬጣ ወይም በአቅራቢያው የተገኘውን በሙሉ የማይመለከተውን ሰውን ጨምሮ 'ቱፍ በይ፤ ምራቅህን ቱፍ በል' እያልን እንመታለን። ተቀበልነውም አልተቀበልነው ይህን በማድረጋችን በህፃናቱ ጨቅላ አእምሮ የብቀላ ስነልቡናን እናዳብራለን። ጊዜያዊ መውጫ ፍለጋ ረጂም ዘመንን ማበላሸት እንመርጣለን። መሆን የሚገባው ህፃናቱ አልቅሰው ይውጣላቸው።። ልቅሶ በአስፈላጊ ጊዜ የህሊና እረፍት ይሰጣል። የስነልቡና ምሁራን እንደነገሩን ተገቢ ልቅሶ የዕንባ 'ቴራፒ' ፈውስ ነው። በዚሁ ተንደርድረን በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ለተፈጠረው የጥላቻ ህፀፅና የፖለቲካ አብሾ የፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያምን አባባል መዋስ ገላጭ ይመስለናል፦

"ከህደት ራሱን የቻለ በሽታ ሲሆን፤

ማስካድ ደግሞ እጅግ የባሰ ነው"

እንበባችሁ ስትጨርሱ በቅጥፈት ማስካድ ቀርቶ

በእውነት እምናችሁ ለፍቅር በአንድነት እንድትቆሙ ተመኘሁ።አንድ ቀን በቀናት ግጭት ላይ ተመስርተን የገተርናቸው የጥላቻ ሐውልቶች ፈርሰው ትውልዱ በአንድነት ስራቸው ቁጭ ብሎ ታሪኩን ሻይ ቡና እያለ በክብር የሚዘከራቸው 'የፍቅር ሐውልቶች' እንደሚያቆም እምናለሁ።

በፈታኝ ሁኔታ ውስጥ ሆኜ ሳልሰስት ያበረከትሁትን ይህንን የበኩር ሥራዬን ሳትሰለ ላነበባችሁን ሁሉ ፈጣሪ ያከብርልኝ።

አነሳስቶ አስጀምሮ፤ አበርትቶና አፅንቶ "መራራ እውነት"ን ያስጨረሰኝ ፈጣ ይመስገን። እግዚአብሔር ቢፈቅድና ብንኖር በፍቅር እንቀጥላለን።

አዘጋጁ፦ ታየ ቦጋለ አረጋ (ኢልመ ደሱ አዱ)

ነጌሌ ቦረና - ነጌሌ ቦረና ወ ጉጂ

Horaa Bulaa – Deebanaa



t.me/OLDBOOKSPDF

# ዋቢ መጻሕፍት (References)

መጽሐፍ ቅዱስ

ቅዱስ ቁርዓን

ሐዲስ ዓለማየሁ፣ 2002. "ፍቅር እስከ መቃብር"፣ ሜጋ አሳታሚና ማከፋፈያ ኃላ.የተ.የግ. ማህበር።

ኅሩይ ወልደሥላሴ፣ 1936፣ "የኢትዮጵያ ታሪክ" (ግለ ታሪክ) የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

ሀይላይ ሀድጉ፣ 2001፣ "ፅንዓት"፣ Dubai: Alghurair Printing Press.

መርስዔኃዘን ወልደቂርቆስ፣ "በዳግማዊ ምኒልክ ዘመን ካየሁትና ከሰማሁት"

------------- "የዘመን ታሪክ ትዝታዬ በአቤቶ ኢያሱ ዘመነ መንግሥት"

------------- "የዘመን ታሪክ ትዝታዬ በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት"

መንግሥቱ ኃይለማርያም (ኮሎኔል)፣ 2004. "ትግላችን - የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ"፣ ፀሐይ አሳታሚ ድርጅት።

ማኅተመሥላሴ ወልደመስቀል፣ 1962 ዓ.ም፣ "ዝክረ ነገር"፣ አዲስ አበባ።

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ .1965. "ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ" ቅጽ 1፣ 1972/73። ኢንግላንድ - ባዝ።

------------------------- "ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ" ቅፅ 2፣ 1973/74.

በቀለ ወልደማርያም አዴሎ፣ 2004፣ "የካፋ ሕዝቦችና መንግሥታት አጭር ታሪክ"፣ ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ብርሀኑ ዘሪሁን፣ የቴዎድሮስ ዕንባ

ቦሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር፣ ባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት፣ መፅሔት፣ 2002

ተከለፃድቅ መኩሪያ፣ 1956፣ "ከይኩኖአምላክ እስከ ዐፄ ልብነድንግል"፣ አዲስ አበባ።

________________1965፣ "ከአፄ ልብነድንግል እስከ አፄ ቴዎድሮስ"፣ አዲስ አበባ።

________________ 1966፣ "የግራኝ አህመድ ወረራ

________________ 1983፣ "አፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት"፣ አዲስ አበባ።

ታየ (አለቃ)፣ 1955፣ "የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ"፣ አዲስ አበባ።

ታደሰ ዘወልዴ፣ 1960 ዓ.ም፣ "ቀሪን ገረመው - የአርበኞች ታሪክ"፣ አዲስ አበባ።

ንጉሤ አየለ፣ 2010፣ "ታላቁ ጥቁር - ኢትዮ አሜሪካ - ዘዳግማዊ ምኒልክ፣ ማንኩሳ ማተሚያ ቤት።

አለባቸው ረታ (አፈ መምህር)፣ 2009. "ቅዱስ ላሊበላና አብያተ መቅደሱ"።

አስራት አብርሀም፣ 2010፣ ከአገር በስተጀርባ - የትሮይ ፈረስና የባለፈረሱ ተልዕኮ። USA.

አእምሮ ንጉሤ፣ 2000፣ "ጥንታዊ የኢትዮጵያ የሰላም ጥበቃ ታሪክ (ከቅሪት እስከ ዘመናዊ ታሪክ)፣ ት.መ.ማ.ማ.ድ

አቤ ጉበኛ፣ 1983. አንድ ለእናቱ።

አብዲ አብዱላሂ፣ "ያልታደለው ትውልድ"

አፈወርቅ ገብረኢየሱስ፣ ጦቢያ። (ዓ.ም እና አሳታሚ አልተገለፀም።) አከፋፋይ፦ ወንዱ የመፃሕፍት መደብር።



t.me/OLDBOOKSPDF

---------------------- 1901፣ ዳግማዊ ምኒልክ፣ ሮም።

"አባ ኮስትር በላይ"

አባ ዶዮ ዘጃጋማ፣ 2010፣ "የዓብይ እዳ"

አታኽልቲ ሓጎስ፣ 1998፣ "ሓቅ ሓቁን ለህፃናት"

ከበደ ሚካኤል፣ 1948 "የዓለም ታሪክ"፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

------------------------- "ጃፓን እንደምን ሰለጠነች?"

"የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት"፣ 1995.

የኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይና አገራዊ ደህንነት ፖሊሲ ስትራቴጂ፣ ሁለተኛ እትም፣ 1996 (2004)፣ በማስታወቂያ ሚኒስቴር ፕሬስና ኦዶቪዥዋል መምሪያ።

"የኢትዮጵያ ፓርላማ ታሪክ"

"የአብዮታዊ ዴሞክራሲ የሰላም መስመር" 1997 ዓ.ም።

የክልል 14 መስተዳድር የአምስት ዓመታት መርሐ ግብር ረቂቅ (1990-1994)፣ ጥቅምት 1990

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር 100ኛ ዓመት የአከባበር በዓል ምስረታ መፅሔት

ይልማ ዴሬሳ፣ 1959 ዓ.ም፣ "የኢትዮጵያ ታሪክ በአስራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን። አሳታሚ፡- ወይዘሮ ሶፊያ ይልማ ዴሬሳ።

ከበደ ተሰማ፣ 1912 ዓ.ም፣ "የታሪክ ማስታወሻ"፣ አዲስ አበባ።

ገብረሕይወት ባይከዳኝ፣ 1912፣ "አፄ ምኒልክና ኢትዮጵያ - ብርሀን ይሁን"፣ አስመራ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ገብረመድህን አርአያ "የትግራይ በጠላት እጅ መውደቅና በኢትዮጵያ ያስከተለው መዘዝ" (ክፍል ሁለት)

ገብረሥላሴ ወልደአረጋይ፤1959 ዓ.ም.፤ "ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ"፤ አዲስ አበባ።

ጌታቸው ኃይሌ፤ 1997 ዓ.ም፤ "የአባ ባህርይ ድርሰቶች ኦሮሞዎችን ከሚመለከቱ ሌሎች ሰነዶች ጋር"፤ አዲስ አበባ።

ጳውሎስ ኞኞ፤ 1985፤ አጼ ቴዎድሮስ፤ አዲስ አበባ።

ቡጋዬ ገብረመድኅን፤ "እሳት ወይ አበባ"።

"ዕናት" ቅፅ 1 እና ቅፅ 2 .1998 ዓ.ም.

"Bu'aa Geengoo Qulqullina Barnootaa. 2010 EC.

Abebaw Bogale. 1886. 'The Culture of Pastoralist Guji of Borena Province.' BA thesis (Addis Ababa University Sociology).

Addis Hiwet.1975. Ethiopia: From Autocracy to Revolution. London.

Andargacgew Tiruneh. 1993. A Transformation from an Aristocratic to a Totalitarian Autocracy. Cambridge: Cambridge University Press.

Annu Waqoo. 2001-2003. Baruulee Waaqefannan.

Asmarom Legesse. 1973. Gada: Three Approaches to the Sudy of African Society. New York: The Free Press.

----------------------------- .2000.Oromo Democracy.

uschwitz. 1962. "Dr. Miklos Nyiszli's Eye-witness account of the atrocities committed inside the most terrible death camps. Granadan Publishing Limited in 1973.



t.me/OLDBOOKSPDF

Ayele Bekere. Ethiopic: An African Writing System, Its History and Principles. The Red Sea Press, Inc.

Bahru Zewde. 2001. A History of Modern Ethiopia 1855-1991. 2nd edn. London, Addis Ababa, Athens: James Currey, Addis Ababa University Press, Ohio University Press.

-----------------. 2002. Pioneers of Change in Ethiopia. The Reformist Intellectuals of the Early Twentieth Century. Oxford, Athens (Ohio) and Addis Ababa: James Currey, Ohio University Press and Addis Ababa University Press.

-----------------. 2008 SOCIETY, STATE AND HISTORY Selected Essays. Addis Ababa: Addis Ababa University Press.

-----------------. 'Economic Origins of the Absolutist State in Ethiopia (1916-1935)', Journal of Ethiopian Studies XVII (1984).

Bates, Darrell. 1979. The Abyssinian Difficulty. The Emperor Thedorus and the Maqdala Campaign 1867-68.

Baye Felleke. (DNS) "Questions About Kibre Negest.

Belay Gidey "Axumite Civilization".

Bender, M.L, Bowen, J.D., Cooper R.L., and Ferguson, C.A., eds. 1976. Languages in Ethiopia. London.

Bonnie K. Holocomb and Sisay Ibsa. 1990. The Invention of Ethiopia. The Red Sea Press.

Butzer Karl. 1981. The rise and Fall of Aksum, Ethiopia. A Geo-archaeological Interpretation. American Antiquity.

Cerulli, Ernesta. 1956. Peoples of Southwest Ethiopia and its Borderland. London: International African Institute.

Chalaby, Abbas. 1989. Egypt. E.E.C: Centro Stampa Editoriale.

Christopher Ehret. 1976. Cushitic Prehistory. In: Non-Semitic Languages of Ethiopia. Michigan University Press, USA.



t.me/OLDBOOKSPDF

Clapham, Christopher. 1988. Transformation and Continuity in Revolutionary Ethiopia. Cambridge: Cambridge University Press.

------------------------------ "Ethnicity and the National Question in Ethiopia", in Woodward, P. and M. Forysth (eds.) Conflict and Peace in the Horn of Africa: Federalism and its alternatives, Aldershot... Sydney, 1994a.

Dursila Dunjee Houston. 1926. Wonderful Ethiopians of the Ancient Cushite Empire.

Donald Crummy. 2000. Ethiopian Historiography in the Latter Half of the Twentieth century. + Johansen, Donald C., and Edey, Maitland. 1981. A. Lucy: The Beginnings of Mankind. New York.

Donham, D. 1999. Marxist Modern: An Ethnographic History to the Ethiopian Revolution. Berkeley, Los Angeles: University of California Press. Oxford.

-------------------.1986. "Old Abyssinia and the New Ethiopian Empire: Themes and Social History" In D. Donham and W. James (eds.). The Southern Marches of Imperial Ethiopia: Essays in History and Social Anthropology. Cambridge: Cambridge University Press.

Clapham, Christoper. 1988. Transformation and Continuity in Revolutionary Ethiopia. Cambridge: Cambridge University Press.

David Henige. 1982. Oral Historiography. Longman Group Limited.

Dena Freeman and Alula pankhurst. 2001. Living the Edge Marginalized Communities of Craft workers and Hunters in Southern Ethiopia. Dept. of SOSA AAU.



t.me/OLDBOOKSPDF

Edward Ullendorf. 1965. The Ethiopians: An Introduction to Country and People.

"Ethiopia Today Education" 1973. Berhanena Selam HSI Printing Press.

Fage J. D (ed.) 1970. Africans Discovers Her Past. London: Oxford University Press.

Forest Colbert. "The Tragedy of Ethiopia's Intellectuals"

Gadaa Melbaa. 1988. Oromia: An Introduction. Khartoum, Sudan.

Gilkes, Patrick. 1975. The Dying Lion: Feudalism and Marginalization in Ethiopia. New York: St. Martin's Press.

George G., M. James. 1988. Stolen Legacy. San Fransisco: California.

Graham Hancock. 1997. The Sign and The Seal. Berlin.

Gregory. 2012. "Ten Stages of Genocide".

Greenfield, R.. 1965. Ethiopia. A New Political History. London and New York: Praeger.

HaileGabriel Dagne. 1971. "Quran School System in Ethiopia." A paper presented for the interdisciplinary seminar of the facúlties of Arts and Education, HSIU- Mimeo.

Harun Yahya. 2001. The Evolution Deceit: The Scientific Collapse of Darwinism and Its Ideological Background. Ta-Ha Publishers.

Heather Lehr Wagner. 2002. People at Odds Israel and The Arab world. Chelsea House Publishers.

Ibrahim Amae Elemo. 2005. The Roles of Traditional Institutions Among the Borana Oromo Southern Ethiopia. Contemporary Issues in Borana and the 28th Gumii Gaayoo Assembly. Finfinne.



t.me/OLDBOOKSPDF

Spencer Trimingham. 1952. Islam in Ethiopia. Oxford University Press. London New York Toronto.

hn Hammer. 1987. Human Development Participation and Change Among the Sidama of Ethiopia. University of Alabama Press.

dson L. James. 1969. American Political parties. Western Publishing Company. Inc.

ASA AND KASA". 1990. The Book Center. AAU.

mbert Bartels. 1983 Oromo Religion Myths and Rites of the Western Oromo of Ethiopia: An Attempt to Understand, Berlin.

ıge, Werner J. 1982. History of the Southern Gonga (Southwestern Ethiopia). Wiesbaden.

ort, Rene. 1983. Ethiopia: An Heretical Revolution. London.

ine, Donald. 1974. Greater Ethiopia: The Evolution of a Multiethnic Society. Chicago: University of Chicago press.

ıis, Joan. 1955. Peoples of the Horn of Africa: Somali, Afar and Saho. London: International African Institute.

ıtel Niecko, Joanna. 1980. The Role of Land Tenure in the System of Ethiopian Imperial Government in Modern Times, Warsaw.

cus Harold. 2002. A History of Ethiopia. University of California Press.

------------------ 1975. The Life and Times of Menelik II. Ethiopia 1844-1913. Oxford, 1975.

akis John. 1986. Anatomy of Traditional Polity: Addis Ababa, Nairobi and New York: Oxford University Press.

al De Salvaic ('Father") .1901. An Ancient People in the State of Menelik. The Oromo.



t.me/OLDBOOKSPDF

Marwick, Arthur. 1989. The Nature of History. London: Macmillan Education ltd.

Merera Gudina . 2003. Ethiopia: Competing Ethnic Nationalisms and the Quest for Democracy, 1960-2000. Chamber Printing House.

---------------------- .2011. Ethiopia: From Autocracy to Revolutionary Democracy, 1960s-2011. Addis Ababa University.

Mesfin WeldeMariam. 1972. An Introductory Geography of Ethiopia. Addis Ababa.

M. Bernal ... Blach Atena

Mohammed Hassen. 1990. The Oromo of Ethiopia: A History 1570-1869. Cambridge and New York: Cambridge University Press.

----------------------------- .1994. In "A River of Blessings, Essays in Honor of Paul Baxter.

Nega Ayele. 1970. 'Centralization versus Regionalism in Ethiopia: The case of Gojjam. BA thesis (HSIU Political Science).

Oljira Tujuba. 1993. A History of the Oromo Liberation Front to Early 1991.

Pankhurst, Richard. 1987. "Development in Addis Ababa during the Italian Fascist Occupation 1936-1941) in Ahmed Zekaria et al.

---------------------- .1968. Economic History of Ethiopia 1800-1935, Addis Ababa.

Pankhurst, Sylvia. 1955. Ethiopia: A Cultural History. London: Lalibela House.

Plowden, Walter. 1868. Travels in Abyssinia and the 'Oromo' Country. London.



t.me/OLDBOOKSPDF

Randi Ronning Balsvik. Haileselassie's Students: The Intellectual and Social Background to Revolution, 1952-1974.

Robert Roberts and Joy Wood: "Intellectuals Virtues"

Rubenson, Sven. 1966. King of Kings Tewodros of Ethiopia. Addis Ababa.

-----------------------. 1976. The Survival of Ethiopian Independence. London.

S. Pierre Petrides. 1983. The Boundary Question Between Ethiopia and Somalia. People's Publishing House, New Delhi, India.

Sergew Hablesellassie. Ancient and Medieval History of Ethiopia to 1270 A.D.

Tadesse Tamirat. 1972. Church and State in Ethiopia 1270-1527. Oxford: Clarendon.

Tessema Ta'a. 2010. Issues in the Historiography of Africa. Office of the DRPO.

------------------------------, 'Journal of The Social Sciences and Humanities Vol. VIII, No.1, June 2012.'

Vansina, Jan. 1985. Oral Tradition as History. London.

Wallelign Makonnen. 1969. "On the Question of Nationalities in Ethiopia." Struggle 17.1.1969.

The World Almanac, 2010.

Wudu Tafete. 1994. 'Meison: From Opposition to Critical Support, 1974-77.

Zanab 'aleqa'. The Chronicle of King Theodore, ed. Enno Littmann. Princeton, 1902.

Zewde Gebresellassie. Yohannes of Ethiopia: A Political Biography. Oxford, 1975.

Grade 11 History Text Book. 2006. Berhanena Selam Printing Press.




t.me/OLDBOOKSPDF

## ተዛማጅ የአብርሆት ዕይታዎች (Related 'Enlightened' Readings)

በጽሑፉ ውስጥ በቀረቡ ሐሳቦች ላይ የበለጠ ጥልቅ ምልከታ ለማድረግ ለሚሹ የሚከተሉትን ርዕሶች እንጋብዛለን፦

የሉዋ ሥርአት፣ ሎኮ፣ ሙዳ፣ ምክሬኞ፣ ሞገሳ፣ ጉዲፈቻ፣ ሲቄ፣ ጉሚ ጋዮ፣ ጨፌ፣ ሰፉ፣ አዳ፣ ስነምግባር፣ ግብረ ገብነት፣ ደቦ፣ ጅጊ፣ ወንፈል፣ አቆልቋይ፣ የጡት ልጅ፣ አበ ልጅ፣ ዕቁብ፣ ዕድር፣ የከብር ዘብ፣ ቅራት፣ ሳባ፣ ሥርአተ መንግሥት፣ ርስት፣ ርስተ ጉልት፣ ጉልት፣ የቃቄ ወርድዎት፣ ባህር መዝገብ፣ አሴኒ፣ ከብረ ነገሥት፣ ወንጌል ዘወርቅ፣ የጁ ሥርወ መንግሥት፣ ዳጉ፣ የገዳ ሥርአት፣ ጣይቱ፣ ፍትሐ ነገሥት፣ ኪነ ጥበብ፣ ጥበብ፣ ስነፅሑፍ፣ ኪነህንፃ፣ የኢትዮጵያ የግብር ስሞች፣

Aksum, Arab - Israeli Wars, Balfour Declaration, Bob Gildolf, Boru Meda Council, Camp David Agreement, Conflict Management, Damat, Christian Topography, Der Sultan Monastery, Dynasties: (Adal, Ifat, Wolayota Malla, Tigre, Solomonic, Mowa,...), Democratic Rights. Emancipation Proclamation (America), Ethio-Eritrean Federation and Union, Ethiopianism, Hewett (Adwa) Treaty, Historia Ecclesias, Homestead Law (America), Human Rights, Internationally Registered Crimes, Lalibela, Liche Treaty, Land Tenure, Magna Carta (Britain), Makhzumite Dynasty (Shewa), Mein Kampf, Muslim Sultanates in Ethiopia, Nationalism, Nine Saints (Ethiopia), Pan Africanism, Patriotic Resistance Movement (1936-41), Patriotism, The Periplus of the Erytrean Sea, Prester John of Indies, Punt, Tripartite Treaty (Britain, France and Italy) Shimbra Kure, UN/UDHR, Virginia Bill of Rights (America) Wuchale Treaty, Zionist Movement



t.me/OLDBOOKSPDF

(*በመፅሐፉ ውስጥ እንደገለፅነው አብዛኞቹ ምንጮች በቀጥታ የተጠቀምንባቸው ሲሆን፤ ውስን የሆኑት ከዘመናት ማስታወሻችን የቀዳናቸውና በተዘዋዋሪ የተጠቀምንባቸው ናቸው። ለሁሉም ምስጋና መስጠት ቢቻል ግሩም ነበር። ሥራቸውን በአንድ መስመር ማስቀመጥ ሲያንሳቸው ነው። I am the synergistic product of many minds. Please visit my personal Facebook account for further clarity. It reads: Taye Bogale Arega)

========= ===== ተፈፀመ ============



t.me/OLDBOOKSPDF

[illegible]
በማፈላለግ ፈንታ - እኩይ የታሪክና የፖለቲካ ልሂቃን 'በቡሀ ላይ ቆረቆር'
እንዲሉ በብሔረሰብ የተናጠል ልቦለድ ትርክት ሊከትፏት መሆኑ ሲመዘን
ያሸማቅቃል። በመርገምት ሴራቸው ምክንያት ታሪክና ፖለቲካ በረከሠ ጋብቻ
ተዛንቀዋል። ታላቁ የደባ ፖለቲካ ምሱን ፍለጋ የሌለ የጦስ ዶሮ ለእርድ
አቅርቧል። በዘውጌዎች የታሪክ ልቦለድ ውስጥ አስቸጋሪው ነገር መሸቱ
በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ዐይን የሌለው ጥቁር ድመት መፈለግ ላይ ማተኮሩ
ነው። አሰሳው የበለጠ አስቸጋሪ የሆነው ደግሞ ድመቱ ባለመኖሩ ነው። በዚህ
ስቢያ የሀሰት ትርክቱ ሦስት ትውልዶችን በደምሳሳው አምክኗል።

የታሪክ ምሁራንም በአመዛኙ በአንድ ወይም በሌላ መልክ በየየት መጣቻው
የጎጥ ከረጢት ጠበው አድሏዊነት ጠፍንጎ አሥሯቸዋል። በሌላ በኩል
ጨለምተኝነት እና ስብእናዎችን በአካባቢ መመዘን በነገሠበት ዳራ (ሚዛናዊ
የሆኑት እንኳ) በመገኛቸው ምክንያት በአንዱ ጎራ ተፈርጀዋል። ከዚህ አኳያ
የመፅሐፉ አዘጋጅ (ታዬ ቦጋለ) በሽፋን ገፁ ላይ ውብ ቃላት የሚያኖሩለት
የታሪክ ምሁራን አሊያም ጉምቱ ፖለቲከኞች ያሞካሹት ዘንድ አላሻውም።
ጠማሩ ራሱ በማያወላዳ ሁናቴ በአይነቱ በተለየ አኳኋን ባለ ሁለት ስይፍ ሆና
ስለተሣለ ሙግቱ ባመቃቸው የበሰሉ ጭብጦችና በአንባቢው ህሊና መሀከል
በቻ እንዲካሄዱ ተወጥኖ ተደጉሷል። የአገላለፁ ውበትና የድርጊቶቹ ፍሰት
ተደምረው አንዴ ማንበብ ከጀመሩ ሳይዘልቁት ተግ እንዳይሉ ራሱ በፍቅር
ያስገድዳል።

ለሁሉም 'ፈረሱም ሜዳውም ይኸው'

ዋጋ 200
$ 25